

# አጤ ቴዎድሮስ

በ

ጳውሎስ ኞኞ

04-182-0001.0600 9 —

# አጤ ቴዎድሮስ

በ

ጳውሎስ ኞኞ

የመጀመሪያው እትም
በግንቦት ወር 1985 ዓ. ም. ታተመ
አዲስ አበባ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

የሽፋን ሥዕል — ሥዩም ታደሰ

ቦሌ ማተሚያ ድርጅት

# ማ ው ጫ


| | | | ገጽ |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ | 1. | ትውልድና አነሳስ | 7 |
| ምዕራፍ | 2. | ራስ አሊ አሉላ፣ እቴጌ መነን፣ ደጃች ጐሹ ዘውዴ | 34 |
| ምዕራፍ | 3. | የጐጃምና የሰሜን ጦርነት | 49 |
| ምዕራፍ | 4. | ደጃች ብሩ ጐሹ፣ ደጃዝማች ውቤ | 55 |
| ምዕራፍ | 5. | ንግስ | 78 |
| ምዕራፍ | 6. | —ደጃች ተድላ ጓሉ፣ —አቡነ ሰላማ፣ —ወይዘሮ ተዋበች አሊ፣ —ፕላውዴን፣ —ዮሐንስ ቤል እና ደጃዝማች ንጉሤ | 97 |
| ምዕራፍ | 7. | —የቴዎድሮስ ሰውነት፣ — ጠባይ፣ — ርሀ ራሄ፣ — ጭካኔ እና ፍርድ | 125 |
| ምዕራፍ | 8. | የአረቦች ጥንሰስ | 150 |
| ምዕራፍ | 9. | ልማት | 155 |
| ምዕራፍ | 10. | ፈረንጆቹ ለምን ታሠሩ? | 173 |
| ምዕራፍ | 11. | የራሳም መልዕክተኛነት | 194 |
| ምዕራፍ | 12. | እስረኞቹ ተፈትተው ታሠሩ | 214 |
| ምዕራፍ | 13. | የእስረኞቹ የመቅደላ ኑሮ | 243 |
| ምዕራፍ | 14. | ጦር መጣ | 262 |
| ምዕራፍ | 15. | ጦርነቱ ተጀመረ | 287 |
| ምዕራፍ | 16. | እቴጌ ጥሩወርቅ፣— ልጅ ዓለማየሁ ቴዎድሮስ | 316 |
| ዋቢ መጻሕፍት | | | 336 |

ይድረስ ከመጽሐፉ አንባቢዎች
የተላከ ከጳውሎስ ኞኞ
2ኛ ተሰሎንቄ 3፡17

የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ በብዙ ሰዎች ተጽፍዋል ። ቴዎድሮስ በመሳፍንት ተከፋፍላ የወደቀች አገራቸውን ለማንሳት የተነሱ ታላቅ አገር ወዳድ ነበሩ ። ቴዎድሮስ በብዙ ገዢዎች ተቆራርጣ የነበረችውን ኢትዮጵያ እንደነበረችበት አንድ ለማድረግ ከፍተኛ ድካም ደክመዋል ። ያለ እረፍት ሠርተዋል ። የግል ዝና እንጂ የአገር ጉዳይ የማይሰማው የዘመናቸው መኳንንት ቢሸሙት እየሸፈተ ፡ ቢሽልሙትና ቢያምኑት እየከዳ ስላስቸገራቸው በተፈጥሮአቸው ቁጡ የሆኑት ቴዎድሮስ አይቀጡ ቅጣት እየቀጡ ተቃዋሚዎቻቸውን ለማጥፋት ሞከሩ ። ግን አልሆነላቸውም ።

ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ከተለያዩ መኳንንት አገዛዝ አውጥተው ባንድ መንግሥት ሥር እንድትተዳደር ለማድረግ የጥርጊያውን መንገድ የከፈቱ ዋናው መሐንዲስ ናቸው ። ለአጤ ዮሐንስና ለአጤ ምኒልክ መንገዱን መንገድ በሕይወታቸው የከፈቱ ቴዎድሮስ ናቸው ።

የአጤ ቴዎድሮስ ድካም እምብዛም ተዘርዝሮ ባንድነት አልተጻፈ ስለነበረ ከየመጽሐፍቱ ሲቃቅሜ ዘርዘር ለማድረግ ሞክሬአለሁ ። የየተቃዋሚዎቻቸውንም ታሪክና የአገዛዝ ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ለመግለጥ ሞካክሬአለሁ ። ምኞትና ሐሳቤ አገሩን ወዳድ የሆነው ኢትዮጵያዊ ትውልድ በመጠኑም ቢሆን ታሪኩን እንዲያውቅ ለማድረግ ነው ።

ቴዎድሮስ ብዙ ጊዜ የቀረቡልን ጨካኝና ክፉ ሰው ሆነው ነው ። ይህ ባህርያቸው ቢኖርም ቴዎድሮስ ጨካኝ ብቻ ሳይሆኑ ደግና ሩህሩህም ነበሩ ። አጋጣሚ ክፉ ያደርጋቸዋል ። አጋጣሚም ደግ ያደርጋቸዋል ። እነኚህንም ተለዋዋጭ ባህሬአቸውን ለመግለጥ ሞክሬአለሁ ።

ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ታሪኩን ሳጠራቅም አራት ዓመት ያህል ፈጅቶብኛል ። ከሚስቴ ከወይዘሮ አዳነች በስተቀር ማንም የረዳኝ ስለሌለ በዚች ቦታ ላይ የማመሰግነው ሰው የለኝም ።

ደህና እንሁን ብቻ

ሟቹ ባለቤቴ አቶ ጳውሎስ ኞኞ በሕይወት ሳለ ፥ “ጀርመን አገር ለሕክምና ሄጄ በነበረበት ጊዜ መታመሜን ሰምተው ዕርዳታ ላደረጉልኝና በራሳቸው ወጭ አሜሪካን አገር ድረስ ወስደው ላሳከሙኝ ለአቶ መሐመድ አላሙዲ

“ አጤ ቴዎድሮስ ”

የተባለው መጽሐፌ ሲታተም መታሰቢያቸው እንዲሆን ብሎ በነገረኝ መሠረት ይህ መጽሐፍ የአቶ መሐመድ አላሙዲ መታሰቢያ እንዲሆን አድርጌአለሁ ።

ወ/ሮ አዳነች ታደሰ

ምዕራፍ 1

# ትውልድና አነሳስ

ካሣ በ1811 ዓ.ም. ጥር 6 ቀን ተወለዱ ። የተወለዱትም ከጐንደር ከተማ 12 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ከምትገኝ ዳዋ ከተባለች መንደር ነው ። የካቲት 16 ቀንም ጐንደር ከተማ በሚገኘው በአባ አቢየ እግዚእ ቤተ ክርስቲያን ክርስትና ተነስተው የክርስትና ስማቸው ገብረኪዳን ተባለ ።

በኋለኛው ዘመን አጤ ቴዎድሮስ የተባሉት ካሣ አባታቸው አቶ ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ ይባላሉ ። አቶ ኃይሉ በ1810 ዓ.ም በመስከረም ወር የእንፍራንዝዋን ተወላጅ ወይዘሮ አትጠገብ ወንድ በወሰንን አገቡ ። በተጋቡ በዓመቱም አትጠገብ ለአቶ ኃይሉ ወንድ ልጅ ወለዱላቸው ። ልጁም ካሣ ተባለ ።

አቶ ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ የመጨረሻ ልጃቸውን እድገት ሳያዩና ናፍቆቱም ሳይወጣላቸው ካሣ በተወለዱ ባመቱ ማለት በ1812 ዓ.ም. ሞተው ሰቀልት ወረዳ ባለው ጋጋና ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ። ካሣም በእርግብ በር እምባ አደጉ ።


ካሣ ወይም በኋለኛው ዘመን ቴዎድሮስ የተባሉት የኮሶ ሻጭ ልጅ መሆናቸውን አንዳንድ የውጭ አገር ፀሐፊዎች ጽፈዋል ። ያገራችንም ታሪክ ፀሐፊዎች ይህንኑ እምነውበት ቴዎድሮስ የኮሶ ሻጭ ልጅ ናቸው እያሉ ተርከዋል ። እናቲቱ ኮሶ ለመሸጣቸውንን የሚያቀርቡት ማስረጃ የለም ። እኔም አላገኘሁም ። ወይዘሮ አትጠገብ በምን ምክንያት ኮሶ ይሸጡ እንደነበር በዚያ ዘመን ኮሶ ከየዱሩ በሚሸመጠጥበት ጊዜ የኮሶው ገቢያ ምን ያህል የኑሮ መግፊያ ጥቅም ይሰጣቸው እንደነበረም የሚተርክ የለም ። የወይዘሮ አትጠገብን የኮሶ ሻጭነት ወሬ ያባዛውና በመጽሐፉ ለዓለም ያዳረሰው ሚስዮናዊው ሄነሪ እስተርን ነው ። እሱም የጻፈው ከሰዎች የሰማውን የሐሜታ ወሬ ይዞ ነው ።

ካሣን ከደሃ ቤተሰብ ልጅነት አውጥቶ ከሀብታሞች ጉያ ለመጨመር መከራከሬ ሳይሆን እውነተኛውን ወይም እውነት የሚመስለውን ታሪክ ለመከተል ብዬ ነው ። የካሣ ወይም የአጤ ቴዎድሮስ አያት ማለት የአቶ ኃይሉ አባት ወልደ ጊዮርጊስ ደጃዝማች ናቸው ፤ ይህንንም አቶ ገሪማ ታፈረ በመጽሐፋቸው ውስጥ በስፊው ባሳዩት ዘር ቆጠራ አስፍረውታል ። በሴት በኩል ደግሞ የካሣ አያት ወዳጆ የራስነት ማዕረግ ያላቸው ናቸው ። ራስ ወዳጆ ፥ ወንድ በወሰንን ይወልዳሉ ። ወንድ በወሰን ደግሞ የእንፍራንዝ ባላባት ልጅ የሆኑትን ወይዘሮ ትሻልን አግብተው ወይዘሮ አትጠገብን ወለዱ ። ወይዘሮ አትጠገብ ካሣን ወለዱ ። ይህ ከሆነ የካሣ እናት ወይዘሮ አትጠገብ እንዴት ባንድ ጊዜ ደህይተው ኮሶ ከመሸጥ ደረጃ ደረሱ ?

እንደኛው ወገን በመንግሥት ተወርሶ ደኸየ ቢባልም በአባትም ሆነ በእናት በኩል የራስና የደጃዝማች የልጅ ልጅ የሆኑት ኪሣ በድህነት አደጉ ለማለት አያስደፍርም ። በሌላው በኩል ደግሞ አቶ ገሪማ ታፈረ ካገር ሽማግሌዎችና ከቆዩ የግዕዝ መጻሕፍት ባገኙት መረጃ እንደጻፉት የካሣ አባት አቶ ኃይሉ ከወይዘሮ ተክሌ ደጃች ክንፉን መውለዳቸውን ይገልፃሉ ። በዚህ ገለፃ መሠረት ደጃዝማች ክንፉ ታላቅ ወንድም ፤ ደጃዝማች ማሩ አጐታቸው ሆነው እነኚህና ሌሎችም ዘመዶች በሕይወት እያሉዋቸው የካሣ እናት ወይዘሮ አትጠገብ ልጃቸውን ኮሶ እየሸጡ አሳደጉ ማለት የማይመስል ትረካ ነው ። እነኚህ ዘመዶች ቢኖሩም የካሣን ከኃይሉ መወለድ አልተቀበሉም ነበር እንዳይባል ካሣን በሕፃንነታቸው ወስደው እያስተማሩ ያሳደጉ አጐታቸው ደጃች ማሩና ደጃች ክንፉ ናቸው ። ይህንንም ታሪክ ፀሐፍት ሁሉ ተስማምተውበታል ።

ለኔ እውነተኛ ትረካ መስሎ የታየኝና የተቀበልኩትም አቶ ገሪማ ታፈረ የጻፉት አተራረክ ነው ። የአቶ ገሪማ ታፈረ መጽሐፍ ትረካው እንዲህ የሚል ነው ። ወይዘሮ አትጠገብ በወይና ደጋው ክፍል አውሊድ ማርያም በተባለው ሠፈር ካሉት ዘመዶቻቸው ጋር በመሬት ውርስ ምክንያት ተጣልተው ይከራከሩ ነበር ። በኋላም በሽማግሌ እርቅ ተደርጐ ሽማግሌዎች የተጣሉትን ዘመዶች አስታርቀው መሬት ሲያካፍሉ ኮሶ አላየ በሚባለው ቦታ ያለ መሬት ለወይዘሮ አትጠገብ ደረሳቸው ። ወይዘሮ አትጠገብም ይህንኑ በዕጣ የደረሳቸውን መሬት ለማሳረስ ደኑን ሲያስመነጥሩ




አጤ ቴዎድሮስ

በደኑ መሀል አንድ ያፈራ ትልቅ የኮሶ ዛፍ ስለነበር ይህ ዛፍ እንዳይቆረጥ ለደን መንጣሪዎቹ ነግረው ወደ ጐንደር ተመለሱ ። በሌላ ጊዜ የዚያ የተመነጠረ የእርሻ ቦታ ሥራ ከምን እንደደረሰ ለመመልከት ከጐንደር ተነስተው ወደ ኮሶ አላየ ሔዱ ። ሥራውን ተመልክተው ወደ ጐንደር ቤታቸው ሊመለሱ ሲሉ ያ የኮሶ ዛፍ በብዛት ማፍራቱን ያየች ገረዳቸው ኮሶውን ስትሸመጥጥ አይተው ወይዘሮ አትጠገብ ተይ ምን ያደርግልሻል ብለው ተቆጧት ። ገረዲቱም ለቤት የሚሆን ለመያዝ ብዬ ነው ብላ የሸመጠጠችውን ኮሶ ይዛ ጐንደር ገባች ።

ይህን ከተመለከቱት የመሬት ባላንጣዎቻቸው መሀል አንደኛው በሰንበቴ ማህበር ላይ እየተበላና እየተጠጣ ሲጫወቱ “ አትጠገብ በአለባበሰዋና በሁኔታዋ ሴት ወይዘሮ ትመስላለች ። ግን ከዚህ ኮሶ እያስለቀመች ጐንደር ወስዳ ትሸጣለች ” ብሎ አወራ ። በዚያም የሰንበቴ ማህበር ከጐንደርና ከገጠር የሚመጡ ማህበረተኞች ስለነበሩበት ወሬውን ወይም ሐሚታውን በየቦታው አዳረሱት ። እንደ ገሪማ ታፈረ አፃፃፍ ወይዘሮ አትጠገብ ኮሶ ሻጭ አልነበሩም ። የኮሶ ሽያጭም ለንግድ ትርፍ ሥራ ምንም የማይጠቅም ነበር ። እንኳን በዚያን ዘመንና እኔ በደረስኩበት በኔ ዘመን

እንኳ በእፍኝ እህል የሚለወጠው ኮሶ ለአንድ ቤተሰብ መድኃኒትነት
በቂ ነበር ። ታዲያ አትጠገብ ምን ትርፍ ያስገኝልኛል ብለው ነው
የኮሶ ነጋዴ የሆኑት ? በዚያን ዘመን ላልነበርነው ሰዎች ነገሩ እንቆቅ
ልሽ ቢሆንብንም ለማመንም አስቸጋሪ ነው።አንዳንዶች የውጭ አገር
ታሪክ ፀሐፊዎች ማንኛውንም ሐሜታና የእረኛ ወሬ እያጋበሱ ስለ
ሚሶፋም እያጣሩ ማመኑ የኛ ድርሻ ይመስለኛል ። ወደፊት እንደም
ናነበው ቴዎድሮስ " ከትቢያ ላይ የተነሳሁ ነኝ " እያሉ የሚናገሩት
አንደኛ ለትህትና ብለው ነው ። ሁለተኛ ዳዊት ደጋሚ ስለነበሩ
በዳዊት መዝሙር ውስጥ የእሥራኤሉ ንጉሥ ዳዊት ስለራሱ ሲናገር
ከትቢያና ከአመድ ላይ የተነሳሁ ነኝ እያለ ስለጻፈ በአገራችን እምነት
መሠረት ለትህትና በዚያ መመራታቸው ነው ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ባልታተመው ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ
ነገሥት ዘኢትዮጵያ በሚለው መጽሐፋቸው " . . . .ልጅ ካሣ ባላባ
ትነት ካላቸው ውስጥ መወለዳቸው እርግጥ ሆኖ እናትዬዋም በድ
ህነት ምክንያት ኮሶ እየሸጡ ልጅ ካሣን ማሳደጋቸው የታመነ ነው ።
. . . ." ብለዋል ። አትጠገብ በእናት በአባታቸው ከባላባቶች
ከተወለዱ ውርስ አላቸው ። የባላባትነቱ ውርስ ቢቀር ርገራኘ
ኩርማንም ብትሆን የመሬት ውርስ አላቸው ። ብዙዎቻችን እንደ
ምናውቀው እንኳን በዚያ ዘመን በቅርቡም ቢሆን ባላባት ብዙ
መሬት ያለው ሰው ነው ። ይህ ከሆነ ቅድም እንዳልኩት በእናታ
ቸውም በአባታቸውም በኩል በሙሉ ካልተወረሰ እንዴት ሙልጭ
ያሉ ደሃ ሊሆኑ ይችላሉ ? በባላባት ልጅነታቸው ከተማመንን በዘ
መኑ እንደነበረው አባባል ዘር ማሰደቢያ የሆነ ንግድ እንዴት
ሊጀምሩ ይችላሉ ? ይህ ጥያቄ በዘመኑ በቴዎድሮስ ዘመን ጐንደር
ለነበረው ለእንግሊዛዊው መልዕክተኛ ለሚስተር ራሰምም አልተመ
ለሰም ።

ራሳም በ1ኛው ቮልዩሙ መጽሐፉ ላይ ስለዚሁ ሲፅፍ " . . . .
እስተርን እንደፃፈው እናትዬዋ ኮሶ ሻጭ መሆናቸውን ለማጣራት
ሞክሬ ነበር ። አንድም ሰው ኮሶ ሲሸጡ አይቻለሁ የሚል የዓይን
ምስክር አላገኘሁም ። ያነጋገርኳቸው ሁሉ የሚነግሩኝ የባለባት
ዘር መሆናቸውን ፤ አባታቸውም የአማራ ሳይንት ራስ መሆናቸውን
ነው ። . . . . በአበሻ ውስጥ ታላላቅ ከሚባሉት ሰዎች ዘር መወለ
ዳቸውን ነው ያጣራሁት ።

" . . . .እስተርን በንጉሡ ችሎት ቁሞ ቴዎድሮስ ሲያነጋግ
ሩት የድፍረት ቃል እየመለሰ ጣቱን በማስጮሁ በለው ብለው በሸ





እጤ ቴዎድሮስ ከእናታቸው ጋር

ሙል ሲመታ ከኪሱ የማስታወሻ ደብተሩ ወደቀች ። በዚያችም
ደብተር ላይ " ንጉሱ ገዳይ ናቸው " የሚል ቃል በመገኘቱ
ፅቃው ሁሉ ተፈትሾ ታሠረ ። ከዚህ በኋላ ሲለቀቅ ያን ቂሙን
ለመወጣት ያዋረደ መስሎት የኮሶ ሻጭ ልጅ ብሎ ጻፈ ። . . . "
ብሏል ። ይህ በቂሁ ይብቃን ።

ካሣ በደጃች ክንፉ ቤት በነበሩበት ጊዜ አንድ ቀን ደጃች
ክንፉ ለማህበረ ሥላሴ መነኮሳት " አልጋዬ ከልጆቼ እንዳይወጣ
እዘኑልኝ ። እትርሱኝ " ብለው በዘመኑ በነበረው ልማድ መሠረት
ሥጦታ አስይዘው ሁለት የሚስጥር አሽከሮቻቸውን ወደ መነኩ
ሳቱ ላኩ ። መነኮሳቱም " ከልጆችህ አልጋህን የሚወርስ ሰው

የሰም ። ገዢው ካሣ ነውና አደራ ብለህ ንገረው ” ብለው መልስ ላኩባቸው ። በዚህ ነገር ደጃች ክንፉ ካሣን ጠሉዋቸው ። ቂምም ያዙባቸው ። ይህን የደጃች ክንፉን ቂም መያዝ የሰሙት ወይዘሮ አትጠገብም ልጃቸውን ወስደው ደንቢያ ውስጥ ካለው ቸንክር ተክለሃይማኖት ደብር ተደብቀው እንዲማሩ አደረጉ ።

ይህ በሆነበት ጊዜ ጠቅላላው የቤጌምድር ገዢ ራስ ይማም ነበሩ ። በደንቢያ ደጃች ማሩ በራስ ይማም ላይ ሸፈቱ ። ራስ ይማምም ደጃች ማሩን ለመያዝ ወደ ደንቢያ በዘመቱ ጊዜ ካሣ ይማሩበት የነበረውን ቸንክር ገዳምን በጦር ወረው በዚያ ያሉትን ብዙ ሰዎች ገደሉ ። ከተማሪዎችም መሐል 48 ልጆችን ሰልበው ጥለዋቸው ሔዱ ። ካሣ ግን ተሸሽገው ያለምንም ጉዳት አመለጡ ።

ምንም ያህል ሳይቆዩ ደጃች ክንፉ ሞቱ ። ደጃች ክንፉ እንደ ሞቱ ልጆቻቸው ልጅ ጋረድ ፣ ልጅ መኰንንና ልጅ ይልማ በሥልጣን ውርስ ተጣሉ ። ልጅ ካሣ ኃይሉ ለልጅ መኰንን ለመርዳት መጥተው ከልጅ መኰንን ጋር ሆኑ ። መኰንንና ይልማ ሁለቱ ወንድማማቾች ዘንጊ በሚባል አገር ላይ ተዋግተው ልጅ መኰንን ክንፉ በወንድማቸው በይልማ ክንፉ ድል ሆኑ ። ልጅ ካሣም ተማረኩ ። ነገር ግን ከይልማ ክንፉ ጋር የቅርብ ወንድማማቾች ከመሆናቸውም ሌላ አብሮ አደጎች ነበሩና ምርኮኛውን ካሣን ከነፈረሳቸው ነፃ ለቀቋቸው ።

ካሣ አቶ ቢተዋ ከሚባሉ መኳንንት ቤት እንደ ዘመኑ ልማድ ወታደር ለመሆን አሽከርነት አደሩ ። ካሣ ጋማው እጅግ የረዘመ ድንቅ ፈረስ ነበራቸው ። አቶ ቢተዋ ዝሆን አደን ሲሔዱ ካሣም ጌታቸውን አቶ ቢተዋን ተከትለው ከዝሆን አደኑ ሔዱ ። አቶ ቢተዋ አንድም ዝሆን ሳይገድሉ ካሣ በዚያ ፈረሳቸው ሆነው ሁለት ዝሆኖች ገደሉ ። በዚህ ግዳይ አቶ ቢተዋ እንደተቀጡዋቸውና እንዳኰረፉዋቸው ባወቁ ጊዜ የገዳይነት ምልክት የሆነውን ሰበባ አውልቀው ጥለውላቸው ከእሉሃ ገስግሰው ወፍታ ከሚባለው ሠፈር ገቡ ። ከእሉሃ እስከ ወፍታ ድረስ ሁለት ቀን ያስኬዳል ። ካሣ ግን እንደ ተናደዱ በዚያ ፈረሳቸው ባንድ ቀን ገቡ ።

የደጃች ክንፉ ልጆች ተስማምተው ከታረቁ በኋላ ጥንድነት ሆነው የጐጃሙን ገዥ ብሩ ጐሹን ሊወጉ ወደጐጃም ዘመቱ ። ይህን የሰሙት ካሣም አብረው ዘመቱ ። የሁለቱ ወገኖች ወታደርም ቸንጢ በር በተባለው ሥፍራ ተጋጥሞ ሲዋጋ የደጃች ክንፉ



ልጆች ድል ሆኑ ። ካሣም ከጦርነቱ ቦታ ሸሽተው ዘርጊ ከሚባለው አገር ገብተው ካንድ ባላገር ሰው ቤት ተደበቁ ። ቀን ቀን ከሜካ እየዋሉ ለሊት ለአዳራቸው ከዚያ ሰው ቤት እየገቡ እያደሩ ወር ሙሉ ተሸሸጉ ። አገር ደህና ሲሆንም ከዚያ ወጥተው ወደ ዳሞት ሔዱ ።

ካሣ ዳሞት ሔደው ለደጃች ጐሹ ሎሌነት አደሩ ። ደጃች ጐሹ ከልጃቸው ከብሩ ጋር አንጋጣ ላይ በተዋጉ ጊዜ ካሣ ከደጃች ጐሹ ጐን ነበሩ ። በጦርነቱም አንድ ሰው ማርከው ሁለት የጠላት ጦር ይዘው ፣ ፈረሳቸው ቆስሎ ተመለሱ ። ከጌታቸው ከደጃች ጐሹም ዘንድ ተርበው በፎከሩ ጊዜ ደጃች ጐሹ ተደስተው አንድ ፈረስ ሸልመው ቀይ ለምድ አለበሷቸው ። እየቆዩ ግን ደጃች ጐሹ ስለ ጠረጠሩዋቸው ወይም ሥልጣን ይቀማሉ ብለው በለፈሩዋቸው ለማሰር ሲያስቡ ይህን የሰሙት ካሣ አምልጠው ወጡ ።

ካሣ በጀግንነታቸው ምክንያት ሁሉም ይፈሯቸዋል ፣ ይጠሏቸዋልም ። ካሣ መሔጃ አጡ ። በኋላም አስበው ድሮ ከነበሩበት ቤት ከአቶ ቢተዋ ጋር ይሄን ያህልም ጠብ ስለሌላቸው ተመልሰው ካቶ ቢተዋ ዘንድ ሔዱ ። አቶ ቢተዋ በቋራ ላይ የራስ አሊ እናት የእቴጌ መነን ምስለኔ ነበሩ ። ካሣ አቶ ቢተዋ ዘንድ የሔዱት አቶ ቢተዋን ለመጠጋት ብቻ ሳይሆን ከተወለዱበት አገር ከቋራ ለመግባት ብለውም ነበር ። አቶ ቢተዋ የማይወዷቸውን ካሣን እንደገና በማግኘታቸው ተቆጥተው አሠሩዋቸው ። ካሣም ከአቶ ቢተዋ እስረኛነት አምልጠው ቋራ ወደተወለዱበት ሠፈር ሔዱ ።

ካሣ ወደቋራ አምልጠው በወረዱበት ጊዜ 12 ሰዎች ተከትለዋቸው ወረዱ ። ይልማ ወሰን የሚባል ከእቴጌ መነን ተጣልቶ ሸፍቶ ቋራ ነበርና ካሣ ወደሱ ዘንድ ሔደው ተደባለቁ ። መጠጊያ ቦታ አሳዳሪ ጌታ ያጡት ካሣ አሁን ሽፍትነት ጀመሩ ።

ካሣ ከይልማ ወሰን ዘንድ በሔዱ ጊዜ በደስታ ተቀብሏቸው “አይዞህ የአውራዬ ልጅ ። የእንጨት ፍሬ በልተን እንኖራለን ” ብሎ አበረታታቸው ። ጫቆ በሚባለው ቦታ ላይ ሰባ የሚሆኑ ሽፍቶች ነበሩ ። ካሣ ከእነኚህ ሽፍቶች ጋር አንድ ውል ተዋዋሉ ። ውሉም አንደኛው ወገን ያገኘውን ከሌላው ቡድን ጋር እንዲካፈል የሚል ነበር ። በዚህ ተስማምተው ከተለያዩ በኋላ ካሣ ከክራሆ ገበያ የሚመለሰውን ነጋዴ ዘርፈው በውላቸው መሠረት ለዚያኛው የሽፍታ ቡድን “ ኑና ያገኘሁትን እንካፈል ” ብለው ላኩባቸው ። እነኚያም

የሰረቁትን ሠንጋ አርደው ብቻቸውን ይበሉ ነበርና የካሣ መልዕከ ተኛ መልዕክቱን በነገራቸው ጊዜ "ወንድሞቹ በግዛት ሲያስጨን ቁን ኖሩ ። ደግሞ እሱ አሁን የሌባ አለቃ ሊሆን ነው ?" ብለው "አንተም ለራስህ ቀማ ፣ እኛም ለራሳችን እንቀማለን ብለህ ንገር" ብለው መልዕክተኛውን መለሱት ።

ልጅ ካሣም እነኛ ጓዶች ብቻቸውን መብላታቸውንና የላኩት ንም መልዕክት ከመልዕከተኛው እንደሰሙ ወዲያውኑ ተነስተው ያሏቸውን 12 አሽከሮች አስከትለው ሔዱ ። እነኛም ዘንድ ሲደ ርሱ "የተማማልነውን መሐላ የከዳችሁት ለምንድነው ?" ብለው ጠየቋቸው ። እነኛም "ለየራሳችን እንሥራ ብለን ነው" አሏቸው ። ልጅ ካሣም ተናደው እናንት ሐሰተኞች ብለው ጐራዴያቸውን መዝዘው ያዘው አሉ ። እነኚያም ሰባ ሰዎች ሲሸሹ ከመሀላቸው ሰባቱ ብቻ ተያዙ ። ልጅ ካሣም በል ቁረጥልኝ ብለው ሰባቱንም ሰዎች እግራቸውን ከጉልበታቸው ላይ እያስቆረጡ ጣሉዋቸው ። የመጀመሪያ የቆረጣ ተግባራቸው ይህ ነው ።

ከዚህ በኋላ ቱምሐ ወደሚባል ሥፍራ ሔዱ ። በዚያም ካለው የጐበዝ አለቃ ከሆነው ከአቶ ደረሰ አቡ ጋር በሕብረት ለመሥራ ትና ወዳጅ ለመሆን ተማማሉ ። ይህን ካደረጉ በኋላ መቀመጫ ቸውን ፈሮሄ ላይ አደረጉ ። በዚያም ሆነው ጐረምሳውን በማባ በል ተጨማሪ 30 ሰዎች ተከታይ አገኙ ። ይህን ካገኙና ድርጅታ ቸውን ካጠናከሩ በኋላ 45 የሚሆኑትን ተከታዮቻቸውን ይዘው ገንዳዋ ቆላ ወረዱ ። ልጅ ካሣ ወደ ገንዳዋ ቆላ የወረዱት በጣም ብዙ የሆኑ የሩቅ አገር ነጋዴ በዚያ በኩል እንዲሚያልፍ አስልለው ስላወቁ ለመዝረፍ ብለው ነው ። ያሰቡትም አልቀረ ከቆላው እንደወረዱ ነጋዴዎቹን በጦር ኃይል መትተው ብዙ ሀብት ዘረፉ ። ብዙ ፈረስና በቅሎ ፣ ገንዘብም በብዛት አገኙ ። ተከታ ዮቻቸውም በዚህ ድልና ዘረፋ በጣም ደስ አላቸው ።

ይህን ድልና ሀብት የቀመሱት ካሣ በነገሩ ለመግፋት ሠራዊ ታቸውን ያጠነከሩና ያበዙ ጀመር ። እያደርም ሠርቶ ከማግኘት ይልቅ የሌላውን ሀብት መዝረፍ ያማረው ሁሉ ይገባላቸው ጀመር ። ተከታዮቻቸው 300 ያህል በደረሱበት ጊዜ ወደወሰን ሔደው በሱ ዳን ግዛት ውስጥ ከሚኖረው እንድሪስ ከሚባለው ሻንቅላ (ግንጃር) ጋር ወዳጅነት መሠረቱ ። አብረው እየተዟዟሩ ለመዝረፍም ተስ ማሙ ።



ከእንድሪስ ጋር ባደረጉት ስምምነት መሠረት አምባ አምበ ላይ ከሚባለው ሠፈር ገብተው ለመዝረፍ ወሰኑ ። ዘጠኝ ቀናት ያህል ተጉዘው ከሥፍራው ሲደርሱ ካሣ የራሳቸውንና የእንድሪስን ጦር ባንድነት አሰለፉ ። ዘራፊው ሠራዊት ወደ ሚዘርፈው መን ጀር ከመሔዱ በፊት የመንደሩ ነዋሪዎች ኃይለኛ ጦረኞች ስለነ በሩ ካሣ ብልሃት ፈለጉ ። ያሰለፉትን ሠራዊት መንደሩ አጠገብ ደርሰው ሁሉም ባንድነት ቆሞ እንዲጮህና ወደመሀል በሚገባበ ትም ጊዜ እየጮኸ እንዲገባ አዘዙ ። ወታደሩ በታዘዘው መሠረት እየጮኸ ወደ መንደሩ ሲገባ የመንደሩ ሰው ድንገተኛ ነገር ስለሆ ነበት ሠፈሩን እየለቀቀ ሸሸ ።

ካሣ ከእንድሪስ ጋር ባደረጉት ወረራ ብዙ ዘረፋ ተገኘ ። ፍየ ልና በግ ፣ ላምና በሬ በብዛት ተዘረፈ ። ከመንደሩ ነዋሪዎችም 600 የሚሆን ሰው ተያዘ ። በነካሣ ሠራዊት ላይ ግን ከሁለት ሰዎች መቁሰል በስተቀር የደረሰ አደጋ አልነበረም ። ከዚያ ተመልሰው ሠፈራቸውን አይማ ወንዝ ላይ አደረጉ ። ሠራዊታቸውን በአይማ ወንዝ ጥቂት ቀናት እንዲቆይና ከድካሙ እንዲያገግም ካደረጉ በኋላ ደለጉ ወደሚባል ሥፍራ ተዛወሩ ።

ደለጉ ላይ ሠፍረው ሳሉ የአገው ሰዎች መክረውና አድብተው ለሊት መጥተው አደጋ ጣሉባቸው ። የካሳም ሰዎች ይህ የለሊት አደጋ ድንገተኛ ነገር ስለሆነባቸው አብዛኛዎቹ ሸሹ ። ካሣም ቀን ቀን ከሥርዋ የሚቀመጡባት ዛፍ ነበረችና ከዚያች ሥር ሔደው ቆመው አሽከራቸውን እያሸለሉ ፣ እሳቸው እየፎከሩ የሚሸሸውን ወታደራቸውን "ምን ተባብለን ነበር?ጀግና"እያሉ አበረታተው ጐራዴያቸውን መዝዘው ከመጣባቸው ጦር መሀል ገቡ ። ወዲያውኑም ከፊታቸው ያገኙዋቸውን ሦስቱን ሰዎች ሲገድሉ ያየው ወታደራ ቸው ልበ ሙሉ ሆኖ እየተመለሰ ከውጊያው ገባ ። ከዚህ በኋላ የካሣ ወታደር ማባረር ፣ የአገው ሰው መሸሸ ጀመረ ። ካሣም በፈረሳ ቸው ላይ ሆነው እያባረሩ አራት ሰዎች ገደሉ ። 360 የሚሆኑ አገዎችም ተማረኩ ።

በማግስቱ ካሣ የተማረኩትን ሰዎች አስቀርበው "ምን [illegible] ድላችሁ ነው የወጋችሁኝ?" ብለው ጠየቁ ። ምርኮኞቹም "[illegible] መኖርዎን አላወቅንም ። የመጣነው እንድሪስ መስሎን [illegible] ወጋ ነበር" ብለው መለሱላቸው ። ካሣም "እንድ[illegible] ሊሆን [illegible] ሰው አይደለምን" ካሉዋቸው በኋላ እንዲጠበቁ አዘዙ ። ለእንድሪስም

"ቀንቶ ኛልና የምሥራች ። አንተም መጥተህ እንገናኝ" ብለው ላኩ በት ።

እንድሪስ በዚያን ጊዜ የሠፈረው ከካሣ ሠፈር የአንድ ሰዓት መንገድ ያህል ከሚርቅ ሥፍራ ነበር ። እንድሪስ እንደመጣም መጀመሪያ በአረብኛ አናግረውት ቀጥለው በአማርኛ "ወንድሜ እንድሪስ ካንተ ጠላት እኔ ምርቱን እፈልሁ" ብለው ከምርኮኞቹ መቶ ሰዎች መርጠው "ያውልህ ግዛቸው" ብለው ሰጡት ። 210 ሰዎችን ደግሞ አስቀርበው "እኔ ምርቱን እንዳፈስሁ አንተ ግርዱን አፈስ" ብለው ሰጡት ። እንድሪስም እነኚያን 210 ሰዎች በሙሉ በሰይፍ እያሰመታ ፈጃቸው ። የቀሩትን አምሳ ምርኮኞች ደግሞ ካሣ አስቀርበው "እናንተስ ብትሆኑ ከኔ ደጅ ደርሳችሁ እንደዬት እንዲሁ ትሔዳላችሁ ። ንሣ አንዳንድ ጆሮአቸውን እየቆረጥህ ስደዳቸው" ብለው አዘዙ ። ጆሮአቸው እንዲቆረጥ ከተፈረደባቸው ሰዎች መሀል አንዱ ከመሞት በመዳኑ ተደስቶ "ከሞት እንዳን እንጂ እንኳንስ አንዱ ሁለቱም ጆሮ ይቆረጥ" አለ ። ካሣም ይህን ሲሰሙ "እንግዲያው እንደ ተናገረው ሁለት ሁለት ጆሮአቸውን እየቆረጥህ ስደዳቸው" አሉ ። ሁሉም ሁለት ሁለት ጆሮውን እየተቆረጠ ተለቀቀ ።

በዚህ ጊዜ ካሣ የሚበላ እህል በማጣት ከፍተኛ ችግር ላይ ነበሩ ። ወታደሮቻቸውም የሚበሉት የእንጨት ፍሬና የዱር ማር እየፈለጉ ነበር ። ይህን የተመለከተው ወዳጃቸው እንድሪስ 200 ያህል ግመል እህል አስጭኖ አመጣላቸው ። ደለጉ ላይ ከአገዎች ጋር ባደረጉት ውጊያ ያለቀው ሠራዊት ሬሳ እያደር እየገማ አላስቀምጥ ስላለ ደለጉን ለቀው ሻሆ ሔደው ተቀመጡ ።

አቶ እንግዳ ወርቅ የሚባሉ የታወቁ ታላቅ ሽፍታ ነበሩ ። ካሣ ከእሳቸው ተወዳጅተው ልጃቸውን አገቡ ። የአቶ እንግዳ ወርቅን ልጅ እንዳገቡም ወህኒ ወደሚባለው አምባ ሔደው አምባውን በጦር ወግተው ዘረፉት ። የወህኒን መወጋትና መዘረፍ የገገርው የራስ አሊ እናት እቴጌ መነን ሲሰሙ ተናደዱ ። ካሣን ከገባበት ገብቶ የሚይዝ ጦር ላኩ ። ከእቴጌ መነን የተላከው ጦርም ካሣ ካሉበት ሲደርስ ካሣ ወታደራቸውን አሰልፈው ጠበቁት ። ከእቴጌይቱ የተላከው ጦር የካሣን ሠራዊት ተሠልፎ ባየ ጊዜ ሁኔታውን አመዛዝኖ ሳይዋጋ ተመለሰ ። እቴጌ መነን የካሣን መበርታት የሕዝቡን ማበር በሰሙ ጊዜ ከጦርነት ይልቅ በወዳጅነት መያዙ የሚጠቅም መሆኑን መዝነው ታረቋቸው ። ቋራንም በምስለኔነት እንዲያስተዳድሩ ተሾሙ ።



ካሣ በራስ አሊ ቤት ጥቂት ጊዜ እየታዩ ከቆዩ በኋላ እቴጌ መነን ዘንድ ሔደው ወደ ግዛቴ እንድሔድ ያሰናብቱኝ ብለው ጠየቁ ። እቴጌ መነንም እሺ ቆይ አሰናብትሃለሁ ብለው በሌላ ቀን "ቋራ የደጃዝማች አገር ነው ። የበላይ ሆኖ የሚያስተዳድር አንድ ባለነጋሪት ደጃዝማች ይዞ መሔድ አለበትና ንገሩት "ብለው ሰው ላኩባቸው። ካሣም እምቢ ቢሉ ወዲያው ተይዘው እንደሚታሠሩ ስለሚያውቁ መልዕክተኛው መልዕክቱን ሲነግራቸው "እሺ መልካም ነው" ብለው እጅ ነሱ ። ወዲያውም ወደ ቤተ መንግሥት ሔደው ከእቴጌ መነን ዘንድ ቀርበው "የበላይ ሆኖ የሚመለከት ሹም ስላደረጉልኝ አመሰግናለሁ ። በዚህም ተደስቻለሁ ። ምክንያቱም አገሩ ክፉ ስለሆነ በጅ ብሎ አይገዛም ። ለእኔም ቢሆን ታዛቢ ሆኖ የሚያይልኝ በማግኘቴ እቴጌን ከልብ አመሰግናለሁ ብለው እጅ ነሱ ። በማግስቱም ቀርበው "አዲስ ሹም ይገኛ ስሔድ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገው እንዲቆዩኝ ለሕዝቡ ሰው መላክ ይገባልና እንድልክ ይፈቀድልኝ" ብለው አመለከቱ ። እቴጌም ፈቀዱላቸው ።

ካሣ ፈቃዱን ካገኙ በኋላ ፈጣን አሽከር መርጠው ለቋራ ሕዝብ ሁለት ዓይነት መልዕክት ላኩ ። አንደኛው ለሚያምኑዋቸው ሰዎች በሚስጥር የሚነገር ሆኖ ሕዝቡ ከብትና ፍየሉን ወደማይገኝበት ቦታ እንዲያሸሹ ። እህሉንም ከጉድጓድ እየከተተ ሰውም እንዲሸሽ እንዲያደርጉና ". . . .እኔ የወሎን ሕዝብ ይዤ መምጣቴ ነውና የአሞራ ክቢን ተራራ ስንዘልቅ ተመልክታችሁ ቤታችሁን እሳት ልቀቁበትና በየቦታው ቃጠሎው እንዲታይ ይሁን ። ከቃጠሎውም ጋር እ.እ.ታ እንዲሰማ አድርጉ ብለህ ንገር" አሉት ።

ሁለተኛው መልዕክት ደግሞ ሚስጥር ሳይሆን ሕዝብ በተሰበሰበበት የሚነገር ነው ብለው "የእቴጌን ደጃዝማች ከብዙ ሠራዊት ጋር ይዤ ልመጣ ነኝና እንጀራው እንደቅጠል ፣ ጠጁ እንደውሃ ሆኖ ይቆየኝ ። ብዙ ፍሪዳም እንዲቀርብ ፣ ሰፈ ዳስም እንዲሠራ ይሁን ። ይህ ሳይሆን ቢቀር በምን ጠፋን እንዳትሉኝ ብለህ ንገር" ብለው ላኩት ።

ይህን መልዕክት ከላኩ በኋላ እቴጌ መነን ዘንድ ሔደው ከኔ ጋር የሚሔደው ለቋራ የተሾመው ሰው ማነው ብለው ጠየቁ ። እቴጌም ደጃዝማች በለው ነው አሏቸው ። ካሣም እጅ ነስተው ወጡ ። እቴጌ መነንም ለደጃዝማች በለው ብዙ ጥሙንጃ ሰጥተው እንዲሔዱ አደረጉዋቸው ። ካሣም ሁሉን ነገር በሆዳቸው ይዘው


ለደጃዝማች በለው መንገድ መሪ ሆነው ይጓዙ ጀመር ። ካሣ የደጃች በለውን ሠራዊት ለማድከም ቅርቡን መንገድ እየተው በሩቅ መንገድ እየመሩ ያጉዟቸው ጀመር ። ከመንገዱ ርቀትም ሌላ አድካሚና ገደላ ገደል በሆነው መንገድ እየመሩ ወሰዷቸው ። የደጃች በለው ሠራዊትም ጉዞው ስለደከመው በጉዞው ምክንያት እየተመረረ እየተበታተነ የትም ቀረ ። ፈረስና በቅሎውም ገደል እየገባ አለቀ ።

ደጃች በለው በመንገዱ መጥፎነትና ርቀት እየተመረሩ "ደህና የተሻለ መንገድ የለም ወይ?" እያሉ ሲጠይቁ ካሣ "ደርሰናል" እያሉ ያጉዙዋቸው ጀመር ። በብዙ ድካምና ችግር ተጉዘው ቋራ ደረሱ ። በቋራም ወታደሩ በያለበት እንዲሠፍር ታዘዘ ። ወታደሩ መሰፈር እንደጀመረ ሕዝቡ ቤቱን እያቃጠለ እሪ እያለ ይጮህ ጀመር። ይህን የሰሙት ካሣም ከደጃዝማች በለው ሠራዊት ጋር ሆነው እየተታኮሱ ከአገሬው መሐል ገብተው ሕዝቡ ወደ ቆላ ወደ አብተጋሆ እንዲሔድ ነግረው ተመለሱ ። ደጃዝማች በለው ዘንድም ቀርበው "እዩልኝ ይሄን እርጉም አገር ? ዘላለም እንዲሁ በጦርነት ነው የምንኖረው ። አመለኛ ስለሆነ ምንም ቢደረግለት እሺ ብሎ አይገዛም " አሏቸው ። ሰላማዊ ለመምሰልም የእራሳቸውን የእህል ጉድጓድ ከፍተው ለደጃች በለው ሠራዊት አደሉ ።

የደጃች በለው ሹማምንትና መኳንንትም ካሣን "እቢህ የከፋ አገር እንዳመጡን ወደ ደህናው አገራችን ይመልሱን " አሏቸው ። ካሣም " ግድ የለም አሁን የተበታተነውን አገር በግድ እየያዝሁ አመጣዋለሁ ። አገሩም ደህና ይሆናል ። አንድ ሳምንት ያህል ተቀምጣችሁ ተመልከቱ " አሏቸው ። የደጃች በለው የወሎ ሠራዊትም ፈፅመን አንከርምም ብለው እምቢ ስላሉ የጐንደር መመለስ ጉዞ ተጀመረ ። የመልሱም ጉዞ ቢሆን ሰላማዊና ምቾት ያለው አልነበረም ። ካሣ ግማሽ ወታደራቸውን ከፍለው የአመፀ ሕዝብ በማስመሰል በየዱር እያደፈጠ የደጃች በለውን የወሎ ሠራዊት በብዛት ፈጀው ። ፈረስና በቅሎም እየማረከ ወሰደ ። በእንዲህ ዓይነት የመከራ ጉዞ የቋራን ግዛት አልፈው ደንቢያ ሲደርሱ ካሣ ደጃች በለው ዘንድ ቀርበው " እንዳዩት አገሩ የዱር አውሬ ነው ። ዘላለም ለምንንና አቆላምጠን ነው የምንኖረው ። አሁንም ባላገሩ እሺ ቢለኝ በእርቅ እንዲገባ ለማድረግ ወደ ቋራ እመለሳለሁ ። ከእርስዎ ጋርም ሆኜ የደረሰብኝን መከራ ሁሉ ለእቴጌ መነን ይንገሩልኝ " ብለው ተሰናብተው ተመለሱ ።



ደጃች በለውም ጐንደር ገብተው የደረሰባቸውን መከራና ስቃይ ሁሉ ለእቴጌ መነን ነገሩ ። እቴጌም " ካሣ የት ቀረ ? " ቢሉ " ደንቢያ ድረስ ሸኝቶኝ ወደ ቋራ ተመለሰ " ብለው ነገሩዋቸው ። እቴጌም በካሣ ወደ ቋራ መመለስ ተናደው ተቆጡ ። ወዲያውኑም የካሣ እንደገና መሸፈት ተሰማ ። ይህ ሲሆን ራስ አሊ ደብረ ታቦር ነበሩና የካሣን መሸፈት እንደሰሙ " እቴጌ በድለውሃል ። እኔ እክስሃለሁና ግባ " ብለው የታወቁ ታላላቅ ሽማግሌዎችንና ቀሳውስትን ላኩባቸው ። ሽማግሌዎቹ ሁለቱንም ወገኖች በመሀላ አስታረቋቸው ። ራስ አሊም ለደጃች ካሣ ግዛታቸውን ቋራን መርቀው ሰጡዋቸው ።



የንጉስ ፋሲለደስ ቤተመንግሥት (ጐንደር)

ካሣ የቋራ ግዛታቸውን ሰላማዊ ለማድረግ ሲያስቡ በወሰን ያለው ግንጃር (ሻንቅላ) በመተማ በኩል ወሰን እያሰፋ አገር ውስጥ እየገባ በመዝረፍ አስቸገረ ። ካሣ ይህን ግንጃር ለመምታት ዘጠና የሚሆኑ ምርጥ አሽከሮቻቸውን ይዘው ወደ መተማ ዘመቱ ። አገሩ በአንድ በኩል የወዳጃቸው የእንድሪስ ዘመዶች ያሉበት በመሆኑ ነገሩን በጦር ሳይሆን በሰላም ለመጨረስ አሰቡ ። መተማ እንደደረሱም ወታደሮቻቸውን ሲመከሩ " ግንጃር ብዙ ሆኖ ተሰልፎ ለማስፈራራት ይመጣባችኋል ። አትፍሩ ። አትንቀጥቀጡም ። ዝም በሉት" አሉ ። ካሣ እንዳሉት ሁሉ ግንጃሩ በፈረስ እየሆነ ተሰልፎ መጣ ። የካሣ ሠራዊትም እንደታዘዘው አጠገቡ እስቲደርስ ድረስ ዝም ብሎ ቆሞ ጠበቀው ። ግራ የገባው የግንጃር ሠራዊትም ከፈረሱ እየወረደ በእግሩ ወደ ካሣ ሠራዊት ተጠጋ ። ካሣም ከሠራዊታ

ቸው መሀል ወጥተው በሰላም ከግንጃርቹ ጋር ተገናኙ ። ወደ መተማ ከተማም አብረው በሰላም ገቡ ። ጥቂት ቀናት አብረው በመቆየት ጉዳያቸውን በሰላም ጨርሰው ሊመለሱ ሲሉ 12 የዝሆን ጥርስ ፣ 200 ብር ፣ 8 ባርያ ፣ ሁለት ስንና ብርት (የጅ ማስታጠቢያ) አሊጋ ፣ ምንጣፍና ሌላም ዕቃ ግንጃርቹ ለካሣ ሰጥተው በሰላም ተለያዩ ። ካሣም በደስታ ተመልሰው ይህን ያገኙትን ዕቃ ለእቴጌ መነን በስጦታ ላኩላቸው ። እቴጌ መነንም በሥጦታው ደስ አላቸው ።

ካሣ በሽፍትነታቸው ዘመን በሱዳን ወሰን በኩል የሚያስቸግረውን በአረቦች የሚታዘዘውን ሠራዊት እየደጋገሙ በመምታት የተደጋገመ ድል አገኙበት ። የካሣን ዝና በኢትዮጵያም ሆነ በሱዳን በኩል በጣም ከፍ ያደረገው ይኸው የተደጋገመው በሱዳን ወሰን በኩል ያስገኙት ድል ነው ። እንዲህ አይነቱንም ጀግና በጠርነት ሳይሆን በወዳጅነት ለመያዝ አስበው እቴጌ መነን የልጃቸውን የራስ አሊን ልጅ ሊድሩላቸው ፈለጉ ። "የአቶ እንግዳ ወርቅን ልጅ ትተህ የኔን ልጅ አግባ" ብለው ላኩባቸው ። ካሣም በነገሩ ተደስተው በ1840 ዓ.ም. የራስ አሊን ልጅ ፣ የእቴጌ መነንን የልጅ ልጅ ወይዘሮ ተዋበችን በሕግ አገቡ ።



የአጼ ዮሐንስ 4ኛ ቤተመንግሥት (ትግራይ)



ካሣም ምንም እንኳን የመስፍኑ የራስ አሊና የአጼ ዮሐንስ ባለቤት የእቴጌ መነን አማች ቢሆኑም ሶስቱም ታላላቅ መሪዎች የካሣ ጋብቻ የእኩያ ጋብቻ ስላልነበረ ካሣን ይንቋቸው ነበር ። ካሣ ወይዘሮ ተዋበችን ካገቡና ለመሪዎቹ ቤተኛ ከሆኑ በኋላ ብዙ ችግር ደረሰባቸው ። ግዛታቸው እየተቀነሰ ፣ ፍርዳቸው እየተገለበጠ በሕዝብ ዘንድ ንቀት እመጣባቸው ። በግዛታቸው ማነስ ምክንያት ገባረውም እያነሰ በመሔዱ ካሣ ለአሽከሮቻቸው እንኳ የሚያበሉት በማጣት እጅግ ተቸገሩ ። ሰዎቻቸውም ተራበ ። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ የካሣን መሻከምና የሠራዊታቸውን መላላት ያወቁት ገዢዎቻቸው ካሣን እስከ ጭራሹ ለማስገደል ስለሚፈልጉ ተዋበችን ባገቡ በሁለተኛው ዓመት ካሣ ወደወሰን ሔደው እንዲዋጉ አዘዟቸው ።

ካሣ ወደወሰን ሔደው እንዲዋጉ የታዘዙት ያለ ምክንያት አልነበረም ። አረቦች በሱዳን በኩል እያለፉ በመደጋገም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እየገቡ ቤት በማቃጠል ፣ በመዝረፍና በመግደል አስቸግረው ስለነበረ ነው ። ይህንንም ኃይለኛ ጦር የካሣ ሠራዊት ያስረዳት ብቻውን ሔዶ እንዲጋጠም ታዘዘ ። ካሣ አላንገራገሩም ። ዘመቱ ።

በዘመኑ ዘመናዊ መሣሪያ ከታጠቀው የግብፅ ጦር ጋር የካሣ ሠራዊት ወሰን ላይ ተጋጠመው ። በጦር አወጋገና በጉራዴ አመታት ከፍተኛ ወጊያ ከተካሔደ በኋላ ካሣ ድል አድርገው የግብጾችን ምሽግ አፈራርሰው በርከት ያለ የጦር መሣሪያ ማረኩ ። ወሰን አልፈው ገብተውም የሸሸውን የግብፅ ጦር ራግድ ከተባለ ወንዝ ላይ ደርሰውበት ያመለጠው ሲያመልጥ የተገኘውን ፈጁት ።

በዚህ ጦርነት ላይ ካሣ ቆስለው ነበር ። ድሉን እንዳገኙ ወዲያውኑ ገስግሰው መጥተው ለበላይ ገዢዎቻቸው እንደ ዕቃ በተቀመጡት ለአጼ ዮሐንስም ሆነ ወይም ለመስፍኑ ለራስ አሊ ፣ ዝቅም ቢል ለእቴጌ መነን ግዳይ ጥለው አልፎከሩም ። ምክንያቱም ቁስላቸው የበረታ ስለነበረ ጨንገር ከተባለው መንደር ካንድ የባህል መድሃኒት አዋቂ ቤት ተኝተው ይታከሙ ነበር ። መድኃኒተኛውም ካሣን በሚገባ ሲያክም ከቆየ በኋላ "ቁስሉ በቶሎ እንዲድን በሚገባ መቀለብ አለብዎ" ስላላቸው ድህነት ያጠቃቸው ካሣ ለንጉሡ ለአጼ ዮሐንስ ፣ ለመስፍኑ ለራስ አሊ ፣ ለእቴጌይቱ እቴጌ መነን ማገገሚያ ስንቅ እንዲልኩላቸው መልዕክተኛ ላኩ ።

ንጉሱ አጤ ዮሐንስ ይህን መልዕክት እንደሰሙ አንድ ሰንጋ
ብዙ እንጀራና ጠጅ ላኩ ። እቴጌ መነን ግን አንድ ብልት ሥጋ ፤
30 እንጀራና አንድ ገንቦ ጠጅ ይላከለት ብለው አዘዙ ። ይህን
ትእዛዝ የሰሙት ሰዎችም “ ምነው እሜቴ ። የካሣን ጠባይ ሁላች
ንም እናውቀዋለን ። ኩሩ ነው ። ፍሪዳ አላጣን ፣ ምናለ ሲሆን አንድ
ፍሪዳ ያለዚያ አንድ የበግ ሙክት ቢላክላቸው አይሻልምን ”
ብለው አማከሩዋቸው ። እቴጌይቱም “ ለፍየል ጠባቂ ቆለኛ አንድ
ብልት ሥጋ አንሶት ነወይ ” አሉ ።



አጤ ዮሐንስ 4ኛ በዙፋን ላይ

ይህን የእቴጌይቱን አነጋገር አንድ ወዳጃቸው ለካሣ ነገራቸው
ካሣ ግን ያልሰሙ መስለው ከሁለቱም የተላከውን ሥጦታ አመስ
ግነው ተቀበሉ ። ከንጉሱ ከአጤ ዮሐንስ የተላከው ሰንጋ ታርዶ
እንዲበላ ሲያዙ እቴጌይቱ የላኩት አንድ ብልት ሥጋ ግን በአገል
ግል እንዲቀመጥ አደረጉ ። ወይዘሮ ተዋበችም ካሣ ከተኙበት ገብ
ተው “ሲሆን በቤተ መንግሥቱ አዳራሽ ፍሪዳው ታርዶ ፣ ማቶቱ
በጠጅ ርሶ ፣ መጥኑ ተግበሰብሶ በተቀበሉን ነበር ። በቀረሰ ድልቡ
ፍሪዳ ቀሚስ ለብሶ ፣ ሥጋው በመልከኛ ፣ ጠጁ በገንቦኛ በተላከልን
ነበር ። እንዴት እንደምን ብንናቅ ነው አንድ ብልት ሥጋ የተላከ
ልን ? ጀግና ሰው እወዳለሁ ። ፈሪ ወንድን ግን እንቃለሁ ። ከፈሪ
ሰው ጋርም አብሬ መኖር አልፈቅድም ” አሏቸው ፣ ይህን የሚስ



ታቸውን ንግግር የሰሙት ካሣም ጥቅምት 5 ቀን 1842 ዓ. ም.
ሸፈቱ ።

የካሣ መሸፈት እንደተሰማ በቤተ መንግሥቱ ታላቅ ድን
ጋጤ ፈጠረ ። ወዲያውኑም እቴጌ መነን ካሣ በሽፍትነት ሳይደራ
ጁና ኃይል ሳያበጁ ቀድመው ለማስመታት አሰቡ ። የተደራጀ
ጦራቸውን አዘው ካሣ በሸፈቱ በሳምንቱ ማለት ጥቅምት 12 ቀን
ካሣን የሚወጋ ጦር ተላከ ። የተላከውን ጦር እንደ አመጣጡ ለመ
ቀበል የካሣ ሠራዊት ጫቆ በተባለ ሥፍራ መሽጐ ቆየ ። የዚያን
ጊዜ ካሣ የነበራቸው ሠራዊት 22 ጠመንጃ ያዥና 400 ጦርና
ጋሻ የያዙ ሰዎች ብቻ ነበሩ ። ጦሩ እንደመጣባቸው ያወቁት ካሣ፤
ሠራዊታቸውን ሰብሰበው “ . . . . ጦርነት የምገጥምበት ጊዜው
ተቃርቧል ። ቢሆንም እኔ የመለከትና የእምቢልታ ድምጥ
ባላሰማህ እንዳትንቀሳቀስ ። የመለከት ድምጥ በሰማህ ጊዜ ግን ወደ
ኋላ ብትል ለራስህ እወቅ ብለው በእዋጅ ካስለፈፉ በኋላ ከድ
ንኳናቸው ገብተው ተኙ ። ካሣ ጥቂት እንዳሸለባቸው የጠላት ጦር
ፊታውራሪው (ቀዳሚው) ሲመጣ ባለቤታቸው ወይዘሮ ተዋበች አይ
ተው ካሣ ዘንድ ገብተው ቀሰቀሱዋቸውና “ ጦሩ መጥቶልሃል ።
ቶንስ ታጠቅ ” አሏቸው ። ከዚህም በኋላ የካሣ የፈረስ ስም ታጠቅ
ተባለ ።

ካሣም ታጥቀው ወጡና የጠላት ሠራዊት ከእሳቸው ሠራ
ዊት አቅራቢያ እስቲጠጋ ድረስ በፀጥታ ቆመው ቆዩ ። ከተጠጋጉ
በኋላ መለከት ንፋ ብለው አዘዙና መለከቱ መነፋት ሲጀምር
“ በለው እንግዲህ ” ብለው አዘዙ ። ከዚህ በኋላ የሁለቱም ሠራ
ዊት ተደበላልቆ ጦርነቱ በጨበጣ ውጊያ ተጀመረ ። የካሣ ሠራዊ
ትም በርትቶ በመዋጋቱና የእቴጌንም ሠራዊት ጥይት አላስተኩስ
በማለቱ ያልጠበቀው የጦር መላ ስላጋጠመው የእቴጌ ሠራዊት
ድል ሆነ ። ድሉ ያለማወላወል የካሣ ቢሆንም ከሁለቱም ወገን
ብዙ ሰው ሞተ ። ብዙ መኳንንትና ተራ ሰዎችም በካሣ እጅ ተማ
ረኩ ። አንድ መቶ ያህል ጠመንጃም በመማረኩ ደከሞና ወድቆ
የነበረው የካሣ ሠራዊት እንደገና ተደራጀ ።

ጫቆ ላይ የተዋጋው የመነን ሠራዊት ወደ ካሣ ከመዝመቱ
በፊት ከእቴጌ መኳንንቶች አንዱ ቀኛዝማች ወንድይራድ የሚባ
ለው ጀግና ለእቴጌ ሲፎክር “ ይህን የኮሶ ሻጭ ልጅ አሁን እንደ
ሙጭልጭላ አንገቱን እንቄ አመጣልሻለሁ ። አይዞሽ ” ብሎ ፎክሮ
ነበር ። ይህን ፉከራውን ካሣ ሰምተዋል ። ጫቆ ላይ በተደረገው

ውጊያ ድል ካገኙ በኋላ ወንድይራድ ተማርኮ በመያዙ ካሣ ደስ አላቸው ። ሠራዊታቸውን ሰብስበውም “ ኮሶ የሚመገብ እንግዳ መጥቶብኛልና ኮሶ ሰብስበህ አምጣልኝ ” ብለው አዘዙ ። ኮሶው መጥቶ ተደቁሶ ከተዘጋጀ በኋላ ካሣ የተበጠበጠውን ኮሶ አስቀርበው ፣ ጦራቸውን ከጭናቸው ላይ አድርገው ፡ ሕዝቡን ሰብስበው ቀኛዝማች ወንድይራድን አስጠሩ ። ወንድይራድ እንደቀረቡም “እናቴ ከገበያ ሳይሸጥላት የቀረ ኮሶ አለ ። አሁን እህል ታጥቷልና ይሄን ኮሶ ተመገብ” ብለው በትልቅ ጥዋ ሙሉ አስጠጡዋቸው ። ቀኛዝማች ወንድይራድም ግማሹን ያህል እንደጠጡ አስታወካቸው ። ከዚህ በኋላ ኮሶ እያጠጣሁ አሠርልኝ ብለው ሶስት መኳንንት ካሳሰሩ በኋላ ሌላውን ምርኮኛ በምሕረት ለቀቁት ።

የተላከው ጦራቸው ድል ሆኖ መበታተኑን እቴጌ መነን እንደሰሙ እንደገና ሕዳር 12 ቀን ከፍተኛ ጦር ሰደዱ ። በአሁኑ ጊዜ የካሣ ጦር ቀደም ብሎ ባገኘው ምርኮ ተጠናክሮ ነበርና ከእቴጌ መነን የተላከውን ጦር ሰቀላ ወርኳ ከተባለ ቦታ ገጥሞ በቀላሉ ድል አድርጐ ብትንትኑን አወጣው ።

ይህን የካሣን ሠራዊት መጠንከር ያወቁት እቴጌ መነን ልጃቸውን እራስ አሊን ወገራ ላይ ትተው እሳቸው ራሳቸው የጦር መሪ ሆነው ወደካሣ ዘመቱ ። እቴጌይቱ ልጃቸውን ራስ አሊን ወገራ ላይ የተውበት ምክንያት የሰሜኑ ገዥ ደጃች ውቤ ጐንደርን ይዘው ሊነግሱ ነው እየተባለ ይወራ ነበርና ሁለቱም ከወጡ ውቤ ጐንደር ይገባሉ በማለት ራስ አሊ ጐንደርን ለመጠበቅ ወገራ ላይ ቀሩ ። እቴጌ መነንም 20 ሺ የሚሆነውን ሠራዊታቸውን እየመሩ በሰኔ ወር ጉዞ ጀመሩ ።

በጉዞም ላይ እንዳሉ እቴጌይቱ “ ይህ ቆለኛ ወዴት አባቱ ይገባ ይሆን ” ብለው ተናገሩ ። የካሣ ጦር ካለበት ሶማ ከተባለው ቦታ ሲደርሱም የካሣ ሠራዊት ለጦርነት ተሰልፎ ቆያቸው ። እቴጌይቱም የካሣን ሠራዊት ተሰልፎ ሲያዩ “ አያፍርም እኮ ይሄ ቆለኛ ፣ ከኔ ጋር ሊዋጋ ተሰልፏል ” አሉ ። ይህን ሁሉ ካሣ ሰምተዋል ። ወዲያውም ጦርነቱ ተጀመረ ። የእቴጌ መነን ሠራዊትም የካሣን ሠራዊት ምስቅልቅሉን አውጥቶ በጦር ገረፈው ። በካሣ አበረታችነት ሠራዊታቸው እንደገና በርትቶ በሚዋጋበት ጊዜ ከጦሩ ጋር ሆነው ያዋጉ የነበሩት እቴጌ መነን በጦር ጭናቸውን ተወግተው ወደቁ ። በዚህ ጊዜ የካሣ ሠራዊት የቆሰሉትን እቴጌን አን



ስቶ ወደ ካሣ ሲወስድ ሌላው የካሣ ሠራዊት ደግሞ በጦሩ መሀል እየዞሩ የእቴጌይቱን መማረክ እየለፈፈ ይነግር ጀመር ። የእቴጌ ሠራዊት ድል ሆኖ ካሣ ድል አደረጉ ። ካሣ ቁስለኛዋንና ምርኮኛይቱን እቴጌን በእስረኛነት ወደ ቋራ ሰደዱዋቸው ። በዚያም የተሰደቡትን ብድር ለመመለስ ባቄላ ያስፈጩዋቸው ነበር ይባላል ።

የእናታቸውን መማረክ ራስ አሊ እንደሰሙ ደነገጡ ። ያላቸውን ሠራዊት ይዘው ካሣን ወግተው እናታቸውን ለማስለቀቅ ተዘጋጁ ። በመሀሉ ግን ጦሩ ከመዝመቱ በፊት ይጠየቅ ስለተባለ ራስ አሊ “ እናቴን ፈትተህ ቶሎ ላክልኝ ” ብለው ላኩባቸው ። ካሣም ከጐጃም አድባራት ተውጣጥተው የተላኩትን 30 ቀሳውስት በሚገባ ተቀብለው መልዕክቱን ከሰሙ በኋላ “የደጃች ከንፉ ግዛት የነበረውን ሁሉ ይልቀቁልኝና እኔም እናትዎን እለቃለሁ ” ብለው መልስ ላኩ ።

ራስ አሊ ይህን ቀሳውስቱ ያመጡላቸውን መልስ እንደሰሙ ካሣ በጠየቁት እርቅ አልስማማም ብለው እምቢ አሉ ። ከካሣ ጋር ከመታረቅ ይልቅ ከሌላው ጠላታቸው ከደጃች ውቤ ጋር መታረቅና ጦርን ባንድ አቅጣጫ መምራት የተሻለ መሆኑን ያወቁት ራስ አሊ ከደጃች ውቤ ጋር ታረቁ ። ለደጃች ውቤ ተሰልፎ የነበረውን ጦርም አቅጣጫውን አስለውጠው ወደ ካሣ አዞሩት ። ይህን የአሊን ጦር ማስከተት የሰሙት እስረኛይቱ እቴጌ መነን “ ከዚህ መዋፎ ቦታ በሰላም ካላወጣኸኝ በጦርነት ልታገኘኝ አትችልም ” ብለው ለልጃቸው ላኩባቸው ።

ራስ አሊም በእናታቸው ምክር ተስማምተው ካሣ በጠየቁት የእርቅ ድርድር መሠረት ፈፀሙ ፡ ካሣም ደጃዝማች ተብለው የሙሉ ደምቢያና ቋራ ፤ ከፍርቃ በር እስከ ዳሞት ፣ በሰሜንም እስከ እርማጨሆ ድረስ ገዢ ሆኑ ። የራስ አሊንም እናት እቴጌ መነንንም ከእሥራት ፈትተው ላኩዋቸው ።

ካሣ ይህን ጦርነት ከመጀመራቸው በፊት ራሳቸውን ለጦርነት በሚያዘጋጁበት ጊዜ ሴትና ንዝ ለእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ እስጠቂ መሆኑን ስለወቁ ሚስታቸውን ወይዘሮ ተዋበችን ከወላጅ ዘመድ ቤት ለማስቀመጥ አሰቡ ። ለዚህ አደራ ማስቀመጥ ጉዳይ ከሁሉም የተሻለ ሆኖ ያገኙት ታማኝ ወዳጃቸውን አይከል ኮልባን ነው። አይከል ኮልባን አስጠርተው “ ወዳጅ ሆይ ፣ ወደፊት ኃይለኛ ነገር እንደሚገጥመን አውቃለሁ ። የጀመርኩትንም ከመጨረሻው ለማ

ድረስ በርትቼ መዋጋት አለብኝ ። አሁን የአደራ ዕቃ እንድታስቀም
ጥልኝ አሰጥሃለሁ ። ይህንንም በምድር የሰጠሁህን በሰማይ ትሰጠ
ኛለህና ከዛሬ ጀምሮ ይሄው ልጅህ ናት ” ብለው እጅ ለጅ አጨ
ባብጠው ተዋበችን በአደራነት ሰጧቸው ።

አይከል ኮልባ ሰው የማያውቃቸው ሁለት ዋሻዎች መቀነት
ግርያም ከተባለው ሥፍራ መኖራቸውን ያውቃሉ ። በነዚያም ዋሻ
ዎች በአንደኛው ተዋበችን አስቀምጠው በሁለተኛው እሳቸው
ለመቀመጥ ወሰኑ ። ይህን ከማድረጋቸው በፊት ልጃቸውን ዘውዱ
የሚባለውን ጠርተው ጉዳዩን ሳይገልጡ ምግባቸውን በየቀኑ በገ
መድ እንዲያቀብላቸው አዘው ተዋበችን ይዘው ከዋሻዎቹ ገቡ ።
ልጃቸው ዘውዴ ምንም የሚያውቀው ነገር ሳይኖር በታዘዘው
መሠረት ብቻ በገመድ በየቀኑ ምግብ ሲያቀብል ኖረ ።

ካሣ በጦርነት እቴጌ መነን ድል አድርገው ለሚቀጥለው በሚ
ዘጋጁበት ጊዜ ሚስጥር የሚያውቅ ወታደራቸውን ጠርተው የተዋ
በች ጤንነት እንዴት እንደሆነ ጠየቁት ። ወታደሩም ‘‘እሳቸውማ
ምን አለባቸው ። የአይከል ኮልባን ልጅ ዘውዴ አይከልን ወዳጅ
ነት ይዘው ይሽሞነሞናሉ ብሎ ነገራቸው ። ካሣ እንኳን ለራሳቸው
ለሌላውም የሚቀኑ ሰው ነበሩና ተናደው አይከል ኮልባን የሰጠሁ
ህን ዕቃ ይዘህ አለሁበት ቦታ ድረስ እንድትመጣ ብለው ላኩባ
ቸው ።

አይከል ኮልባ ወይዘሮ ተዋበችን ይዘው ወደ ካሣ ለመሔድ
ጉዞ ጀመሩ ። በዚህን ጊዜ ዘውዴ ከሠፈር አልነበረምና ከሔደበት
ሲመለስ “ አባትህ ወደ ካሣ ተጠርተው ሔዱ ” ብለው ሰዎቹ ነገ
ሩት ። ዘውዴም አባቱን ተከትሎ ለመሔድ ወዲያውኑ በማስጋቤ
ጉዞ ጀምሮ ከመንገድ ደረሰባቸውና አብረው ወደ ካሣ ሔዱ ።
ከካሣ ዘንድ ሲደርሱም ካሣ ግብር አገቡላቸው ።

ግብር የተዘጋጀው ለሰላምና ለፍቅር አልነበረም ። ካሣ በግ
ብሩ ጊዜ ጣምራ (ሁለት) ጦር በጭናቸው ላይ አድርገው ተቀምጠ
ዋል ። አስተያየታቸውና አነጋገራቸው ሁሉ የቁጣ ነው ። ሁሉም
በፍርሃት ተመስጦ በሚመገቡበት ጊዜ ካሣ በድንገት ወደ
ወይዘሮ ተዋበች ዞር ብለው “ ተነሺና አንድ ዋንጫ ጠጅ ለዘ
ውዴ አይከል ስጪው ” ብለው አዘዙ ። ወይዘሮ ተዋበች ከቴዎድ
ሮስ ቁጣ ለመዳን ለዘውዴ የሚሰጡትን አንድ ዋንጫ ጠጅ አስቀ
ድተው ይዘው ከመቀመጫቸው ተነሱ ። ተዋበች ፈርተው ይነሱ



እንጂ ዘውዴ የቱ እንደሆነና የትስ እንደተቀመጠ አያውቁም ነበ
ርና ከመሀል ቆመው ዓይናቸው ይንከራተት ጀመር ። ካሣ ግን ጦራ
ቸውን እየነቀነቁ የተዋበችን እርምጃ ይከታተላሉ ።

ግብር የገባው ሰው ሁሉ ፈርቶና ደንግጦ እርጭ ብሎ ሲያ
ይና ሲያዳምጥ ተዋበች የባሰ ተደናግጠው ዙሪያውን እየዞሩ
ዘውዴ የተባለው የቱ እንደሆነ ይፈልጉ ጀመር ። ዘውዴ አይከል
ግን የተቀመጠው ከዚያው ከአጠገባቸው ነበር ። በሁኔታው ግራ
የገባቸው ካሣም የተዋበችን ሁኔታ አይተው “ ዘውዴ አይከልን
አታውቂውም እንዴ ? ” ብለው ጠየቋቸው ። ተዋበችም “ እኔ
አላውቀውም ” ብለው መለሱ ። ካሣም “ ዘውዴ አይከል ማለት
እሱ አጠገብሽ ያለው ነው ” ብለው አሳዩዋቸውና የተነገራቸው
ውሸት መሆኑን አውቁ ። ወዲያውም ያን የነገራቸውን ወታደር
በዓይናቸው ከግብሩ መሀል ቢፈልጉ አጡት ። ወታደሩ ቀደም
ብሎ ተሾልኮ ጠፍቶ ነበር ። ካሣ ጠቅላላ ታሪኩን ከሰሙ በኋላ
ለዘውዴ አይከል የአዛዥነት ማዕረግ በጥተው ከርብ በላይ ያለው
የበጌምድር ገዢ አደረጉት ። በሕመም በሞተ ጊዜም ለተዝካሩ
ማውጫ ብለው በግዛታቸው ውስጥ ካሉ ገበያዎች ሁሉ ያንድ
ቀን ቀረጥ እንዲሰጥ አዘዙ ።

እዚህ ላይ የቴዎድሮስ የምርመራ ዘዴ የሚደነቅ ወይም የሚ
መሰገን አይደለም ። ሚስታቸውን ወይዘሮ ተዋበችን አደራ የሰ
ጡት ለአይከል ኮልባ ነው ። ዘውዴ ደግሞ አባቱ ቤት የሚኖር
የአይከል ኮልባ ልጅ ነው ። ዘውዴ በአባቱ ዘንድ ታማኝ ሆኖ
አባቱ ሚስጥሩን ሊነግሩት ይችላሉ ። በታማኝነቱም ወይዘሮ ተዋበ
ችን ሊያስጠብቁት ይችላሉ ። አልተደረገም እንጂ አይከል ኮልባ
ለልጃቸው ሚስጥሩን ገልጠው ቢሆን ኖሮ የንፁሆቹ የወይዘሮ
ተዋበችና የዘውዴ አይከል ደም በከንቱ ሊፈስ ነበር ። ቴዎድሮስ
ሁለት ጦር ይዘው የተቀመጡትም አንዱ ለተዋበች ሌላው ደግሞ
ለዘውዴ አይከል መሆኑ ነው ። ተዋበች በመንገድ ላይ እንኳን
ዘውዴ አይከልን ተዋውቀውት ቢሆንና ያን ዋንጫ ጠጅ ለዘውዴ
ቢሰጡ ኖሮ የንፁሃኖቹ ሕይወት በከንቱ ሊያልፍ ነበር ።

ካሣ ከራስ አሊ ጋር ተራርቀው ደጃዝማች ከተባሉ በኋላ አዲ
ሱን ግዛታቸውን ማስተዳደር ጀመሩ ። ከግዛታቸውም ሌባና ሽፍ
ታን አጥፍተው ፍፁም ሰላማዊ ግዛት ለማድረግ ተነሱ ። በደም
ቢያ ሽፍታውባቸው የነበሩትን ተቀዋሚዎቻቸውን ሁሉ እያስያዙ

እጅና እግራቸውን አስቆረጠ። በግዛታቸው ላይ የበላይ ሳይናርባቸው ፈላጭና ቆራጭ ሆኑ። ይህን አድራጎታቸውን የሰሙት ራስ አሊ እንድትመጣ ብለው ላኩባቸው። ደጃች ካሣም "አሁን ጊዜው ከረምት ስለሆነ ለመምጣት አያመቸኝም" የሚል መልስ ላኩ። ክረምቱ እንደወጣም ራስ እንደ ገና እንድትመጣ ብለው ላኩባቸው። ደጃች ካሣ ከራስ አሊ ጋር የነበረው እርቅ በሁለቱም በኩል ካንገት በላይ ለጊዜው የተደረገ መሆኑን ያውቃሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን እቴጌ መነንን ማርከው በነበረ ጊዜ በእቴጌይቱ ላይ የሠሩትን በደል ያውቃሉና ለራስ አሊ "አልመጣም" ብለው ላኩባቸው።

ከዚህ በኋላ ራስ አሊ ደጃች ካሣን ከሹመታቸው ሽረው ግዛታቸውን ለጐጃሙ ገዥ ለደጃች ጐሹ መስጠታቸውን በሕዳር ወር 1845 ዓ.ም. በአዋጅ አናገሩ። ወዲያውም ራስ አሊና ደጃዝማች ጐሹ በአንድነት ሆነው ደጃች ካሣን ሊወጉ ዘመቱ። ካሣም እነዚህን ሁለቱን ታላላቅ መኳንንት በአንድነት ለመውጋት እንደማይችሉ ራሳቸውን ገምተው ደንቢያን ለቀው ወደ ትውልድ ቦታቸው ወደ ቋራ ሔዱ። ራስ አሊም የደጃች ካሣን መሸሽ እንዳዩ ደንቢያ ላይ የደጃች ጐሹን ገዢነት አውጀውና አደላድለው ተመለሱ።

ደጃዝማች ጐሹም በነበራቸው የጐጃም ግዛት ላይ ደንቢያ ስለመጨመሩ በጣም ተደሰቱ። ከደንቢያም ሆነው ጦራቸውን በየግዛቱ ያደላድሉ ጀመር። ራስ አሊ ርቀው ሲሔዱላቸው ደጃች ካሣ ከተደበቁበት ወጥተው ወደ ጉርአምባ መጡ። ይህን የካሣን መነሳት የሰሙት ደጃች ጐሹም ጦራቸውን ሰበሰቡ። ጣፋጭ የሚባል የደጃዝማች ጐሹ አዝማሪም ከተሰበሰበው ሠራዊት መሐል ገብቶ

> እያቸሁትን የኛን እብድ፣
> እምስት ጋሞች ሆኖ ጉር አምባ ሲወርድ።
> ያንጓበባል እንጂ ሙች ይዋጋል ካሣ፣
> ወርደህ ጥመድበት በሸንበራው ማሳ።
> ወዶ ወዶ
> በሴቶቹ በነጉንጭት ለምዶ እያለ ተሳደበ።

የደጃች ካሣና የደጃች ጐሹ ጦር ሕዳር 19 ቀን ጉርአምባ ላይ በጦርነት ተጋጠመ። ሠራዊቱ እንደተጋጠመ የደጃዝማች ጐሹ ሠራዊት አጠቃ። የደጃዝማች ካሣ ሠራዊትም መሸሽ ሲጀምር ካሣ ከጥቂት ወታደሮች ጋር ሆነው ከጦሩ መሀል ገብተው ይዋጉ



ጀመር። ደጃዝማች ጐሹም በፈረስ ሆነው ከሠራዊታቸው ፊት ቀድመው ሲያዋጉ በድንገት በጥይት ተመትተው ወደቁ። ድሉም ባለማወላወል የደጃዝማች ካሣ ሆነ። ደጃዝማች ካሣም የደጃች ጐሹን ሬሳ አስነስተው በአሽከርነት አድረውላቸው የነበረ ጊዜ የሠሩላቸውን ውለታ በማሰብ በክብር አስቀበሩዋቸው።

በዚህ ጦርነት ካሣ ብዙ ሀብትና ምርኮ አገኙ። ከተማረኩትም ሰዎች መሀል ጣፋጭ የሚባለው አዝማሪ ተፈልጎ እንዲመጣላቸው አድርገው "እንዴት ብለህ ነው የሰደብከኝ!" ብለው ጠየቁት። እሱም ቢጨንቀው በቀልድ እንዲምሩት ፈልጎ

> "እወይ የእግዜር ቅጣ፣ እወይ ያምላክ ቅጣ፣
> እፍ ወዳጄን ያግል ሥራ ሲያጣ፣
> ብትር ይገባዋል የአዝማሪ ቀልባጣ!" ብሎ ገጠመ።

ካሣም በፈረደው ፍርድ በሽመል አስደብድበው አስገደሉት።

ደጃች ካሣ ተቀምጠው ግዳይ እየጣሉ የሚፎክሩላቸውን ሲሰሙና ምርኮ ሲቀበሉ ባላምባራስ ገልዋ የሚባሉት ጀግና አሽከራቸው ቆስለው መጡ። ባላምባራስ ገልዋ በጦር የተወጉት ከጉንጫቸው ላይ ነበር። ጦሩም በአንደኛው ጉንጫቸው በኩል ገብቶ በሌላው ጉንጫቸው የወጣ ስለነበረ ባላምባራስ ገልዋ የጦሩን ዘንግ በጥርሳቸው ነክሰው በፈረስ እየጋለቡ መጡ። ደጃች ካሣም ይህን ሲያዩ ከመቀመጫቸው ተነስተው ባለህበት ቆም ብለው ወደ ገልዋ ሔዱ። ከዚያም ከፈረስ አውርደው ደግፈውን ጦር ነው ጦሩ ተሰብሮ ጉንጫቸው እየተቀደደ ጅንፎው ወጣላቸው። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት ምን ዓይነት ጀግኖች እንደነበሩን ያሳያል።

ባላምባራስ ገልዋ ከደጃች ጐሹ ጋር የሚደረገው ጦርነት ተጧጡፎ የጐሹ ሠራዊት እያጠቃ ለድል በተቃረበበት ጊዜ ሸሽተዋል ተብሎ ተወርቶባቸው ነበርና አንዲት ዘፋኝ ከደጃች ካሣ ፊት ቀርባ ስታሜውት "አይሸሽም ያልከው ገልዋ እንኳን ሸሸ
የደንቢያን ግራር እያበላሸ"
ብላ ገጠመች። ደጃች ካሣም ይህን ገልዋን የሚያሰድበውንና ፈሪ የሚያደርገውን ግጥም እንደሰሙ "አብለሻል እንጂ እውነቱን አላልሽም፣
በዙበት እንጂ ገልዋስ አይሸሽም"
ብለው መለሱ።

ይህ ጦርነት በተደረገ ጊዜ ራስ አሊ ጐጃም ነበሩ ። የጐሹ ሠራዊት ድል በመሆኑና ጐሹም በመሞታቸው አዘኑ ። ደጃች ካሣም ይህን ድል በማግኘታቸው ቢደሰቱም በድሉ ሳይኩራሩና አሊንም ሳይንቁ ካህናትን ሰብስበው ከራስ አሊ አስታርቁኝ ብለው ወደ ራስ አሊ ላኩ ። ቀሳውስቱም እንደተላኩት ሔደው ራስ አሊን “ ይታረቁልን ” ብለው ቢጠይቁ እምቢ አሉ ። የአሊን አንቢታ የሰሙት ካሣ የራስ አሊን ሰዎች እየሻሩ በነሱ ቦታ የራሳቸውን ሰዎች ይሾሙ ጀመር ።

ራስ አሊ የእርቁን ጉዳይ እምቢ ብለው ካህናቶቹን ከመለሱ በኋላ አዲስና ያልተነካ ጦር ያደራጁ ጀመር ። ለዚህም ለሚቀጥለው ውጊያ የላስታው ደጃዝማች ብሩ አሊጋዝ ፣ ደጃዝማች በለው ደጃዝማች አቤ ፣ ደጃዝማች ያዘው እነኚህ አራት ደጃዝማቾች ተመረጡ ። እነዚህም ጦራቸውን አሰልፈው በሁዳዴ ጦም የካቲት 8 ቀን ደጃዝማች ካሣን ለመውጋት ሔዱ ። ለዚህ ጦርም ከሰሜን ከደጃዝማች ውቤ ጦር በሶስት እምበል የሚመራ ሠራዊት እንዲጨመርላቸው ተደርጐ ሁሉም ጉዞውን ወደ ደንቢያ አመራ ።

ለዚህ ለሚዘምተው ጦር የካሣ ሠራዊት ተወዳዳሪ እንደማይሆን የታወቀ ነው ። ሆኖም ካሣ ከ800 እስከ አንድ ሺ የሚገመት ጠመንጃ የያዘ ጦር ነበራቸው ። ካሣ ያላቸውን ጦር አዘጋጅተው ብቸኝ ከተባለው ሥፍራ ሲጠባበቁ ሚያዝያ 5 ቀን ገጣሚያቸው ጦር ደረሰና ብርቱ ጦርነት ተደረገ ። በሁለቱም ወገን ብዙ ሰው ካለቀ በኋላ ደጃዝማች ካሣ ድል አደረጉ ። የተላኩት መኳንንትም በሙሉ አልቀው ካሣ ብዙ ምርኮ አገኙ ።

ለዚህም ውጊያ ከትግራይ የመጣው የደጃች ውቤ ወታደር ድል ሆኖ አገሩ ሲገባ “ራስ አሊ ለቑቑ በለሳ

ፍሩይ ሰብእይ እንከብ ተወልደ ካሣ ።
ደጅያት ውበውን ልቀቁ የፀገደ
ፍሩይ ሰብእይ ካሣ እንካብ ተወልደ”
እያለ ዘፈነ ።

ደጃዝማች ካሣ ይህን ድል ካገኙ በኋላ ገሰግሰው ሔደው የራስ አሊን ከተማ ደብረታቦርን አቃጠሉት ። የሠራዊታቸውን ድል መሆንና የከተማቸውን መቃጠል ተደራርቦ የሰሙት ራስ አሊ አሁን ፍርሃት አደረባቸው ። ከእንግዲህ ወዲያም ካሣ በጦር ኃይል አንደማይቻሉ ተገነዘቡ ። ስለዚህ የሚሻለው መንገድ እርቅ በመሆኑ



ከጐጃም አድባራት 30 ካህናትን አውጣጥተው “ አንታረቅ ። ከአባይ ወዲያ ላንተ ይሁን ። ከአባይ ወዲህ ለኔ ይሁንና እንታረቅ ። አባትና ልጅ እንሁን” ብለው ላኩባቸው ።

እነኚህ አስታራቂ ካህናት ደብረ ታቦር በደረሱ ጊዜ ደጃዝማች ካሣ ሥራ ላይ ነበሩ ። በበጌምድር ያሉትን ብረት ሠራተኞች ሰብስበው አንድ ሺ ማረሻ አስቀርበው አረር ያስቆርጡ ነበር ። የድሮው ጠመንጃ ባሩድና ብረት ባንድነት በጨርቅ እየተጠቀለለ ይጐርስና በሚተኰስበት ጊዜ የባሩዱ የማስፈንጠር ኃይል አረር የተባለችው ብረት አስፈንጥሮ ስለሚወረውራት ለታለመበት ግብ አደጋ ታደርሳለች ። ይህንንም አተኳኮስ አንዴት እንደሚሠራና እንደሚተኮስ የጥንቱን ጠመንጃ በውርስ ያገኙ ባላገሮች አሳይተውኛል ። ይቺን ተስፈንጣሪቷን አረር ነው ካሣ ከማረሻ በየትንንሹ እያስቆረጡ ያሠሩ የነበረው ።

እማላጅነት የተላኩትን ቀሳውስት ካሣ የተቀበሉዋቸው ከዚያው አረር ከሚያሰሩበት ቦታ ሆነው ነው ። አማላጆቹም ከራስ አሊ የተላኩትን መልዕክት ነገሩዋቸው ። ካሣም መልዕክቱን በሙሉ ካዳመጡ በኋላ “ ከእስላም ጋር እገር አልከዳም (አልካፈልም) ። እችላለሁ ስትል የአይሻልን ሜዳ የቀበሮውን ጉድጓድ ደልድለህ አሳምረህ ቆየኝ ። አልችልም ስትል ቅዱስ ጊዮርጊስን መስጊድ አታድርገው ። ጀበናህንና ብረት ምጣድህን ፣ እርኮትህን ይዘህ ሰማይ ግንባርህን እስቲመታህ ሽሽ ። አትቆየኝ በሉት ” አሏቸው ። ወዲያውንም ከተናገሩት ቃል መንገር ፈርተው እንዳይቀንሱ ቄስ አስመጥተው አስገዘቷቸው ።

ቀሳውስቱም ከራስ አሊ ዘንድ ተመልሰው በቆይታ (በሚስጥር) ያመጡትን መልስ ነገሩዋቸው ። ራስ አሊም በመልሱ ደነገጡ ። ዘመዶቻቸውን ወረሂመኖችን ሰብስበው “ እንሽሽ ወይስ እንዋጋ” ብለው ምክር ጠየቁ ። ወረሂመኖችም በሰው አገር ከምንሞት በአገራችን ብንሞት ይሻላል ። አሁንም በረንታን ተሻግረን አገራችን እንግባ ። ከዚያ ቢመጡ ብዙ ረዳት አለን ብለው አማከሩዋቸው ። ራስ አሊ የጐጃምን መኳንንት ደግሞ ሰብስበው እንዲያማክሩዋቸውና የወረሂመኖችንም ሐሳብ ነገሩዋቸው ። ጐጃሞችም “ሲገዛ የኖረ ባለአልጋ ጥቂት እንኳ ሳይዋጋ አይሸሽም ። ለስጠው ይስጠው ። እንዋጋ” አሏቸው ። ራስ አሊም በጐጃሞች ምክር ተስማሙ ። ከዚያም ጦራቸውን አስከትተው ወደ አይሻል ሜዳ ሔዱ ።

ደጃዝማች ካሣም በዳሞት አድርገው በናዝሬት ወረዱና አይሻል አካባቢ ሲደርሱ የራስ አሊ ጦር ተሰልፎ አዩት ። ሠራዊታቸውንም ዙሪያውን እንዲከብ አዘው የራስ አሊን ጦር ዳር ዳሩን አስከበቡ ። የራስ አሊም ጦር የካሣን ሠራዊት አይቶ በማነሱ አዘነ ። ያዘነበትም ምክንያት በብዛት ለተሰለፈው ለራስ አሊ ሠራዊት ምርኮው እንደማያዳርስ ገምቶ ነው ። ለአስር ሰው አንድ ሰው ምርኮኛ አይደርሰንም እያለ ይጫወት ጀመር ። የደጃዝማች ካሣም ሠራዊት ዳርዳሩን ጊዮ፡ረ ሳይጋጠም በመቆየቱ ፈርቶ ሊመለስ ነው እየተባለም ተወራ ። ለምርኮ የተቻኮለው የራስ አሊ በው "እግዚአብሔር ይፍታህ" የሚለውን የጦርነት መጋጠሚያውን ትእዛዝ ተቻኩሎ ይጠብቅ ጀመር ።

ሰኔ 23 ቀን 1845 ዓ.ም. ጧት ጦርነቱ ተጀመረ ። ወዲያውኑ ለምርኮ ያሰፈሰፈው የራስ አሊ ሰው እየተቻኮለ ገብቶ የካሣን ሠራዊት ይጠርገው ጀመር ። እንደተመኘው ምርኮም እየማረከ መያዝ ሲጀምር የራስ አሊ ጀግና ግራኝ ወልደ ኪዳን ተመትቶ ወደቀ ። ግራኝ ወልደ ኪዳን የአሊን ሠራዊት እያበረታታ ቀድሞ የሚዋጋ ታላቅ ጀግና ሰው ነበር ። ግራኝ ወልደ ኪዳን ተመትቶ እንደወደቀ ወዲያው ሞተ ። በዚህ ጊዜ የራስ አሊ ሠራዊት ተደናገጠ ። የሠራዊቱን መደናገጥ ያዩት ደጃዝማች ካሣ ሠራዊታቸውን እያደፋፈሩ ከጦሩ መሃል ሲገቡ የድሉ አዝማሚያ እየተለወጠ ይሔድ ጀመር ። የተገላቢጦሽ ሆነና የራስ አሊ ሠራዊት በተራው እንደ ቅጠል ይረግፍ ጀመር ። የሰውም ሬሳ እየተነባበረ ወደቀ ። ደም እንደ ጐርፍ ፈስሶ መሬቱን አጨቀየው ። ደጃዝማች ካሣ ድል አደረጉ ። ወዲያው ከፍተኛ ዝናብ በመዝነቡ ከጦር የተረፈውን ቁስለኛ ሁሉ ብርድና ቆፈን ጨረሰው ።

ራስ አሊም መውጫ ቀዳዳ አጥተው በሚጨነቁበት ጊዜ ደጃዝማች ተሰማ ጐሹ ደርሰው የከበባቸውን የካሣን ሠራዊት እንደ በር አስከፍተው ይዘዋቸው አመለጡ ። የራስ አሊን ማምለጥ ያየው የካሣ ሠራዊት ለመያዝ ያባርር ጀመር ። ጀግናው ደጃዝማች ተሰማ ግን አሊን አስቀድመው እሳቸው ከኋላ በመከተልና እየዞሩ አባራሪውን እየወጉ ይዘዋቸው የጁ ለመድረስ አበቁዋቸው ።

ደጃዝማች ካሣም እያከታተሉ ራስ አሊን የሚይዝ አባራሪ ቢልኩም የራስ አሊ አድራሻ ስለጠፋ መከታተሉን ተዉት ። የአይሻል ላይ ጦርነትም የመሳፍንት አገዛዝ የመጨረሻው ሆነ ።



በታላቁ አሊ የተጀመረው የምሥፍንና ዘመን በትንሹ አሊ ዘመን ተፈጸመ ።

ደጃዝማች ካሣ ከአይሻል ድል በኋላ በደጋ ዳሞት አድርገው ሲመለሱ የደጋ ዳሞት ሕዝብ ወጥቶ ከደከመው የካሣ ሠራዊት ፤ ፈረስና በቅሎ ይማርክ ጀመር ። በየጥሻው እየተደበቀና አፋፍ ላይ እየሆነ "የጐሹን ደመኛ ፤ የአሊን ወደረኛ ትሰቀዋለህን" እያለ ብዙ አስቸገረ ። ብዙ ሰውም ገደለባቸው ። የባላገሩን መበርታትና መዝረፍ ያየው ተራው ባላገር ሁሉ ፈረስና በቅሎ ለመማረክ በብዛት ይወጣ ጀመር ። ያሳበቡት ችግር ያጋጠማቸው ደጃች ካሣ ሁሉን ነገር ችለው በሰላም አልፋለሁ ሲሉ የዳሞት ባላገር አላሳልፍ ስላላቸው ዕገድ ከሚባለው ቦታ ሲደርሱ ሠራዊታቸውን በለው ብለው አዘዙ ። የደጃች ካሣም ሠራዊት ትእዛዝ በማግኘቱ ብዙውን ባላገር ፈጀው ። ከዚህ በኋላም ሰላም አግኝተው ጉዞአቸውን ጀመሩ ። አንዲት የደጋ ዳሞት ሴት ባልዋ ለዘረፋ ወጥቶ በመገደሉ ስታለቅስ ፣

"አመጣለሁ ብሎ የካሣን ፈረስ
ሳያርመው ሞተ የዘራውን ገብስ" ብላ አንጐራጐረች ።

## ምዕራፍ 2

# ራስ አሊ - እቴጌ መነን - ደጃች ጉሹ ዘውዱ

## ራስ አሊ አሉላ

ኢትዮጵያ በመሳፍንት አገዛዝ ሥር በነበረችበት ጊዜ ራስ አሊ አንደኛው መስፍን ነበሩ ። የራስ አሊ ምስፍንና ከአያት ቅድመ አያቶቻው ጀምሮ የመጣ እንጂ እንደ አንዳንዶቹ አምባ ገነኖች ምስፍናውን ከራሳቸው የጀመሩ አይደሉም ። የጐንደርን የመሳፍንት አገዛዝ የጀመሩት ትልቁ ራስ አሊ ልጃቸው ወይዘሮ ከፈይ ፣ መርሳ በሬንቱን አግብተው ጉግሣን ይወልዳሉ ። ጉግሣ በአባታቸው የምሥፍንና አልጋ ተቀምጠው ራስ ተብለው 28 ዓመት ገዙ ። በዚህ 28 ዓመት የምስፍንና የግዛት ዘመናቸውም ሶስት ንጉሦችን አስዋውጠዋል ። ያስዋወጡዋቸውም አጤ ጊጋር ፣ አጤ ኢዮአስ እና አጤ ጓሉ ናቸው ። ራስ ጉግሳ አራት ልጆች ነበሩዋቸው ። እነሱም ይማም ፣ ማርዬ ፣ ዶሪ ፣ አሉላ ይባላሉ ። ራስ ጉግሳ ሲሞቱ በአልጋቸው ልጃቸው ይማም ተተክተው የአባታቸውን አጤ መልሰው በአጤ ጊጋር ተቀማጭነት ሶስት ዓመት ገዙ ። ራስ ይማም ሲሞቱ ወንድምየው ማርዬ ራስ ተብለው የወንድማቸውን አልጋ ወረሱ ። ራስ ማርዬ ሶስት ዓመት ገዝተው ሲሞቱ ወንድማቸው ዶሪ ራስ ተብለው የምስፍንናውን አልጋ ያዙ ። ራስ ዶሪ ለስም መጠሪያ ያህል የሚቀመጡትን አጤ ሰለሞንን በግንብ አስቀምጠው ሶስት ወር ከገዙ በኋላ የራስ ጉግሳ የልጅ ልጅ የሆኑት የአሉላ ልጅ አሊ ራስ ተብለው የምስፍንናውን ቦታ ያዙ ።

ራስ አሊ በ1822 ዓ.ም. የምስፍንናውን ቦታ ሲይዙ ምዕርሐ አምባ በእሥር ከተቀመጡት የነገሥታት ልጆች መሀል ገብረ ክርስቶስን አስመጥተው አጤ ገብረ ክርስቶስ አሰኝተው አንግሰው እሳቸው ሥልጣኑን ያዙ ። ራስ አሊ ምንም እንኳን ንጉሡን ለስም አስቀምጠው እሳቸው ሥልጣን ቢይዙም እናታቸው ወይዘሮ መነን ደግሞ ራሳቸውን እቴጌ አሰኝተው የሥልጣን ተካፋይ ነበሩ።





ራስ አሊ አሉላ

በራስ አሊ የምስፍንና ዘመን የእንግሊዝ መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት የፈጠሩበት ዘመን ነበር ። በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ስሙ የገነነው ፕላውዲን በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ሆኖ የተሾመው በራስ አሊ የምስፍንና ዘመን ነው ። በፕላውዲን ትረካ ውስጥ ወደፊት እንደምናገኘው ፕላውዲን ከኢትዮጵያ ወደ አገሩ ሄዶ የእንግሊዝ መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር በወዳጅነት እንዲተሳሰር ባመለከተው መሠረት የእንግሊዝ መንግሥት የጉዳዩን አሳሳቢ ፕላውዲንን በኢትዮጵያ መንግሥት ዘንድ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ብሎ ሾመው ።

ፕላውዲን ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስ በኋላ የሹመቱን ደብዳቤ ለማቅረብ ሔዶ በራስ አሊ ቤት ስላየውና ስለራስ አሊም ሰውነትና ጠባይ ሰፋ ያለ ታሪክ ጽፏል ። ፕላውዲን ከፃፈው ትረካ በመጠኑ እናንብ ። “.... ከራስ ቤት ውጪ የተለያየ ማዕረግ ያላቸው ሰዎች ይቀመጣሉ ። አንዳንዶቹም በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ናቸው ። በድንጋይ ወይም ከመሬት ላይ ከጠሀይ መከለያ ጥላ በሌለበት ቦታ ይቀመጣሉ ። ጉዳያቸው እስኪፈፀምላቸው ድረስም ለብዙ ሳምንታት ይቆያሉ ። ... በዚያ ላይ አጋፋሪዎች ማንንም ሳይመርጡ በዘንግ እየመቱ ያባርሩዋቸዋል ።....ከሰዎቹም አንዳንዶቹን ስለማውቅ ጉንጭ ለጉንጭ

እየተሳሳምን በሩን አልፌ ከውስጠኛው የችሎት ቦታ ገባሁ ፡፡ በዚያም ቦታ የማውቃቸውን ታላላቅ ሰዎችን ፣ መልዕክት ተላላኪዎችንና ሥራ ቤቶችን ሁሉ አገኘሁ ፡፡ ከከፍታ ሰገነት ላይ አፈ ንጉሡ ከሁለት ይሁን ከሶስት ሽማግሌዎች ጋር ሆነው ከበታቻቸው የሚንጫጫውን የሕዝቡን አቤቱታ ይሰማሉ ፡፡ አልፎ አልፎም አንዳንድ ሁኔታዎችን ለራስ ይነግራሉ ፡፡ ከሁለት ይሁን ከሶስት ደቂቃ በኋላ እኔና ቤል ገብተን እጅ ነሳን ፡፡ ከመሬት በተነጠፈ ቆዳ ላይ አንድ ትልቅ አለቃ ተቀምጠው አየሁ ፡፡. . . .ጥቂት የጋላ ልጆች ይጫወታሉ ፡፡ አንድ አሽከር ቆሞ ትእዛዝ ይጠባበቃል ፡፡ ራስ እኔን በማየታቸው መደሰታቸውን ገለጡልኝና ወዲያውኑ ምን እንዳመጣሁላቸው ጠየቁኝ ፡፡ ይህም የተለመደ ጥያቄ ነው ፡፡ እኔም በጊዜው እንደሚያዩት ነገርኳቸውና ማረፊያ ቤት እንዲሰጡኝ ጠየቅኋቸው ፡፡ እሳቸውም ወደ እሳቸው ቤት እንድመጣ ነገሩኝ ፡፡ እኔ ግን አልፈልግም አልኳቸው ፡፡ እብረን ቁርስ ከበላን በኋላ 200 ያርድ ያህል ከሚርቀው ከአንድ እስላም ባለሥልጣን ቤት እንድገባ ታዘዘልኝ ፡፡ ይህም ቤት ኮረብታ ላይ ሆኖ ደስ የሚልና ዙሪያውን በደህና አጥር የታጠረ ነው ፡፡ በጣም ደስ አለኝ ፡፡

“ራስ ቀኑን ሙሉ መልዕክተኛ እየላኩ ያመጣሁላቸውን ጠመንጃ ወይም ሌላ ነገር እንዳሳያቸው ይጠይቁኛል ፡፡ በማግስቱ ዕቃዬን ተሸክመው የመጡትን ሰዎች ሂሳባቸውን ከፍዬ አሰናበትሁና ከሰዓት በኋላ ለራስ ያመጣሁትን ስጦታና ለንጉሡ የተፃፈውን ደብዳቤ ይዤ ሔድሁ ፡፡. . . . ቆሜ ከንግሥታችን የተላከውን ደብዳቤ አነበብኩላቸው ፡፡ ነገሩ ምን እንደሆነ አልገባቸውም ፡፡ ከዚህ በኋላ የተላኩላቸውን ስጦታ አቀረብሁ ፡፡ ተመሰጡ ፡፡ . . . . ከዚያም ወጥቼ ሔድሁ ፡፡. . . .

“ በሌላ ቀን እነኚህን ስጦታዎች ለመቀበል ያሳፍረኛል ፡፡ ምክንያቱም የዚህን ስጦታ መልስ ለንግሥታችሁ የምሰጠው የለኝም ፡፡ ድሃ ነኝ አሉኝና ሁለት መንደሮችን ሰጡኝ ፡፡ ሲሰጡኝም ፈረስና በቅሎህን የት ታስቀምጣለህ ፡፡ እነዚህ ከሌሉህስ ማርና ቤት የት ታገኛለህ አሉኝ ፡፡. . . .እውነታቸውን ስለሆነ. . . .እሺ ብዬ ተቀበልኩ ፡፡. . . .መሰንበቻቸውን ራስ በቀን ሶስቴና አራቴ መልክተኛ እየላኩ ያለኝ እየመሰላቸው ተጨማሪ ጠመንጃና ሽጉጥ እንድሰጣቸው ይልኩብኛል ፡፡. . . . በመጨረሻም ያለኝን ጠመንጃና ሽጉጥ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎቻችንና ድንኳኔን ጭምር እንድሰጣቸው ጠየቁኝ ፡፡



“ በ1848 ዓ.ም. ታላቁ የአበሻ ገዢና በኛ መንግሥት የታወቁትን ራስ አሊን ሁለት ፊውዳል መኳንንት አስቸግሩዋቸው ፡፡ የትግሬው መስፍን ውቤ በስሜን አመፁባቸው ፡፡ የጐጃሙ መስፍን ብሩ ደግሞ በደቡብ በኩል ሸፈቱባቸው ፡፡ ይህም አዲሱ ተዋናይ (አክተር) በሰገነቱ ላይ እስቲታይ እስከ 1853 ዓ.ም. ድረስ ቆየ ፡፡ በ1853 ዓ.ም. የቋራው ደጃች ካሣ ተነሳ ፡፡. . . .

“ ራስ አሊ ልዩ የሆነ ጠባይ አላቸው ፡፡ ከእሳቸው ጋር ተነጋግሮ አንድ ነገር ለመወሰንም በጣም አስቸጋሪ ናቸው ፡፡ ሥልጣን የያዙት በ12 ዓመት ዕድሜያቸው ገና ልጅ ሆነው ነው ፡፡. . . . ሰውን ሁሉ የሚንቁና ራሳቸውን የሚወዱ ሰው ናቸው ፡፡. . . . በራሳቸው ላይ በሚደርስ መጥፎ አጋጣሚ እንኳ የሚስቁ ፣ ከግዛታቸው ተቀንሶ አገር ቢወሰድ ፣ በጦርነት ድል ቢኮን ፣ የጦር አዛዦቻቸው ቢሞቱ እንኳ ጥቂትም የማይቆጫቸውና የማያናድዳቸው ናቸው ፡፡. . . . በተንኮልና በሰላይ መጠቀምን የሚወዱ ናቸው ፡፡ ጨካኝ ባለመሆናቸው መቅጣት ስለማይወዱ በግዛታቸው ውስጥ ብዙ ከሰነ ሥርዓት ውጪ የሆኑ ሰዎች አሉ ፡፡ መበቀልን አይወዱም ፡፡ ጠላቶቻቸውን እንኳ እየናቁ የሚተዉ ሰው ናቸው ፡፡. . . . በቅርብ ከሚያውቋቸው ይልቅ በሩቅ ሆነው በጥቂቱ የሚያውቁዋቸው ይወዱዋቸዋል ፡፡. . . . በአካል መካከለኛ ቁመት ያላቸው ፣ ኃይለኛና ፈጣን ናቸው ፡፡ . . . .ጥሩ ተኳሽ ፣ ጥሩ ፈረስ ጋላቢ ፣ የታወቁ ጦር ወርዋሪና ሯጭ ናቸው ፡፡ በአበሻ ውስጥ አሉ ከሚባሉት ጥሩ ፈረስ ጋላቢዎች አንዱ እሳቸው ናቸው ፡፡ ስአለባበስ ወይም ለማንኛውም ጌጣጌጥ ማድረግ ግድ የለሽ ናቸው ፡፡ ንፅሕናን ግን ይወዳሉ ፡፡ ከጥሩ ጠባዮቻቸው አንዱ ፣ አንዴ ሰውን ከወደዱ ፈጥነው የሚለወጡ (የሚጠሉ) አይደሉም ፡፡ ለጠላቶቻቸው እንኳ ቢሆን ቸርና ደግ ሰው ናቸው ፡፡ . . . .” በማለት ፅፎላቸዋል ፡፡

ራስ አሊ ቀደም ብለን እንዳነበብነው አይሻል ላይ ከደጃች ካሣ ጋር ተዋግተው ድል ከሆኑ በኋላ መውጫ አጥተው ሲጨነቁ የደጃች ጐሹ ልጅ ደጃች ተሰማ ደርሰው ከዚያ ቁማታና ሽብር አውጥተው ከሚያባርራቸው ጋር እየተታኮሱና እየተከላከሉ ደንበጫ አደረሱዋቸው ፡፡ በደምበጫም እረፍት አድርገው ከአደሩ በኋላ በማግስቱ አመዳሚት ከሚባል ቦታ አደረሱዋቸው ፡፡ ደጃች ተሰማ እስከ አመዳሚት ድረስ አድርሰው ሊመለሱ ሲሉ ራስ አሊ “. . . አልጋህን ለባዕድ አይበለው ፡፡ ከከፉ እሚታደግ ከጭንቅ የሚያወጣ የተባረከ ዘር ይስጥህ ፡፡ እኔ የመረቅሁህ ዛሬ ብቻ አይደለም ፡፡

ሬትም በአባትህ ለንስለት ተለውጠህ የታሠርከ ዕለትም ነው. . .” ብለው ደጃች ተሰማን መርቀዋቸው ተሳስመው ተለያዩ ።

ከአመዳሚት ደግሞ ይመር ጣሹ የሚባል ሰው እስከ አባይ ወንዝ ድረስ ሸኝቷቸው ማህደረ ማርያም አደሩ ። ከማህደረ ማርያም ተነስተው ዋድላ ገቡ ። ከዋድላም ደራ ገብተው ከደራው ገዥ ከዋቆ ዲቦ ዘንድ ተደብቀው መኖር ጀመሩ ። ደጃች ካሣ አገር እያሳመኑ አመዳሚት ሲደርሱ ዋቆ ዲቦ ፈርቶ “ራስ አሊ ከኔ ዘንድ ናቸው” ብሎ ለካሣ ላከ ። ራስ አሊም ይህን ሲሰሙ አዝነው ለሸዋው ንጉስ ለኃይለ መለኮት “አምኜው ብመጣና ከእሱ ዘንድ ብጠጋ ዋቆ ዲቦ አሳልፎ ለጠላቴ ሊሰጠኝ ነውና ታደገኝ” ብለው ፈጣን መልዕክተኛ ላኩባቸው ። ንጉሥ ኃይለ መለኮትም ጦራቸውን ይዘው ወደ ደራ ሔደው ዋቆ ዲቦን ወግተው ራስ አሊን አውጥተው ወደ የጁ ሰደዱዋቸው ።

ራስ አሊ ከትውልድ አገራቸው የጁ ይግቡ እንጂ ካሣን በመፍራት ተዝናንተው አልተቀመጡም ። ራያ በረሃ ወርደው በዋሻ ውስጥ ተደብቀው የመከራ ኑሮ መኖር ጀመሩ ። 48 ነጋሪት በአደባባያቸው አብጂር ሲል ይውልበት የነበሩት ታላቅ ጌታ ፣ የአውሬ ድምፅ ከሚሰሙበት ዋሻ ገቡ ። ባንድ ጉዞ 55 ሺ ወታደር አጅቧቸው ይጓዙ የነበሩት ራስ አሊ በአሁኑ ጊዜ አንድ ታማኝ አሽከር ብቻ ቀራቸው ።

ራስ አሊ ጥንቱንም ቢሆን በገና መደርደር (መምታት) ይችሉ ነበርና በዚያ በመከራ ዘመን በዚያ ጭር ባለ ቦታ በዋሻቸው ውስጥ በገና እየመቱ ራሳቸውን ያጽናኑ ጀመር ። አንድ ቀን

“የጣቴን ቀለበት አንተ አድርገው ካሣ
“በኔማ ጣት ገብቶ አስጨነቀኝሳ” ብለው አንጐራጐሩ ። ቅኔው ሲፈታም “በኔ ማጣት ችግር ገብቶብኛል” ማለታቸው ነው ። በሌላ ቀን ደግሞ በገና እየደረደሩ ሲያዝኑ

“የውቤን ደመኛ የጐሹን ጓዳይ ፣
ያሊን መንግሥት አፍራሽ ያን ዘበናይ ።
አደባባይ ቆሞ አበጀሁ ቢላችሁ
ይህን ባለ ጊዜ ምን ትሉታላችሁ” አሉ ። በኋላ ታሪኩን የምናመጣው ካሣ የደጃች ጐሹን ልጅ ደጃች ብሩንና የሰሜኑን ገዥ ደጃች ውቤን ድል አድርገው ማሰራቸውንና መንገሣቸውን



ከሰሙ በኋላ ተሰፋ ቆርጠው የበፊት የበገና ግጥማቸውን በማሻሻል “የብሩን አሳሪ ፡ የጐሹን ገዳይ ፡
የኔን መንግሥት አፍራሽ ፡ የውቤን አባታይ ።
አደባባይ ቆሞ አበጀሁ ቢላችሁ
ይህን ባለ ጊዜ ምን ትሉታላችሁ” ብለው አለቀሱ ። ከግጥሙ መዝጊያ ላይ “ይህን ቢላችሁ ምን ትሉታላችሁ” ያሉ መስለው ምስጢሩ ግን “ይህን ጊዜ የሰጠውን ሰው ጊዜ ያነሳውን ሰው” ማለታቸው ነው ።

በበረሃው ዋሻ ሆነው ከፍተኛ ረሃብና ችግር ደረሰባቸው ። አንድ ቀን ራስ አሊ ከተደበቁበት ዋሻ ብቅ ሲሉ በዋሻው አጠገብ ያለውን የማሽላ ዘር ከወፎች ይጠብቅ የነበረ አንድ ገበሬ ዝንጀሮ መስለውት ድንጋይ በወንጭፍ እያወነጨፈ ይወረውርባቸው ጀመር ። ራስ አሊም ያን አሽከራቸውን ልከው “እኔ አሊ ነኝና ተወኝ ። ይልቅስ እባክህ የማሽላ እሸት ስደድልኝ” ብለው ላኩበት ። ይህን የአባታቸውን መቸገር የሰሙት ልጃቸው የካሣ ሚስት ወይዘሮ ተዋበች ከባላቸው እየደበቁ ምግብም ልብስም ይልኩላቸው ጀመር ። በዚህን ጊዜ ኑሮአቸው በመጠኑ የተሻለ ቢሆንም እኙሁ የሚረዷቸው ልጃቸው ሞቱ ። አሊም የልጃቸውን መሞት ሲሰሙ በድንጋጤ ታመሙ ። ስለልጃቸው ሞትም በገናቸውን እየደረደሩ

“ጠጅ አማረኝ ስላት ማሩን ታስጭናለች ።
ራበኝም ስላት እህሉን ትልካለች ፡
በረደኝም ስላት ሸማ ትሰዳለች
ሌባዬ ተይዛ ባልጋ ትሔዳለች ።” በማለት አለቀሱላቸው ።

ራስ አሊም ሕመማቸው እየጠና ሔደ ። ይህን ያየው ያገለግላቸው የነበረው አሽከራቸው ድሮም በገና ደርዳሪ ነበርና በገናውን እየደረደረ
“አንተንም አፈር ይበላሃላ ፡
እኔንም ጐንደር ይሸጡኛላ ።
ከአሊ በፊት
እኔ ልሙት ።
አሊ ሲሞት ያለብኝ እሣር
የግማሽ ማጭድ የአዋሴ ምሳር ።
አሊ ሲሞት
መጠጤ አተላ መብሌ ጉበት ።
ከአሊ በፊት እኔ ልሙት” እያለ አንጐራጐረ ። ራስ አሊም

ከልጃቸው ሞት በኋላ ምንም ያህል ሳይቆዩ ሞተው ወሎ ውስጥ ሐይቅ ደሴት ተቀበሩ ። በሥልጣን ላይ የቆዩት 22 ዓመት ነበር ።

## እቴጌ መነን

መነን የራስ አሊ እናት መሆናቸውንም በጦርነትም ምን ያህል ተዋጊ ሴት እንደነበሩ እንብበናል ። ማርክሃምም "....ዝነኛ የሴት ጦረኛ ነች ። አሻንጉሊቱን ንጉስ ሽማግሌውን አጤ ዮሐንስን አግብታ በልጅዋ ስም ደንቢያን ትገዛ ነበር ...." ይላል ። እቴጌ መነን የበፊት ስማቸው ሐሊማ ነበር ይባላል ። ራስ አሊ ሥልጣን ከያዙ በኋላ የእናታቸው ስም ሐሊማ መባሉ ቀርቶ መነን እንዲባሉ በአዋጅ አስነገሩ ። ሐሊማ የሚል ሰው ቢገኝም እይቀጡ ቅጣት እንደሚቀጣ አስነገሩ ። ጐንደሮች በግጥም እመሲጋኝ መስለው መሳደብን ፣ የሰደቡ መስለው ማመስገንን ወይም ደግሞ ግልፅ ባልሆነ መንገድ ሚስጥር ማውጣትን ይችላሉ ። በዚህም ቅኔያቸው ጐንደሮችንና ጐጃሞችን የሚስተካከል የለም ። ራስ አሊ የእናታቸው ስም መነን እንጂ ሐሊማ እንዳይባል ባወጁበት ጊዜ በራስ አሊ አዳራሽ ሕዝቡ ግብር ገብቶ ሲበላና ሲጠጣ በመሀል ሆኖ ያጫውት የነበረው አዝማሪ

"አሊ ማን ይላታል እናቱን
እኛስ የምንላት እቴጌ መነን" ብሎ እንጐራጐረ ይባላል ። የቅኔው ትርጉም ያልገባቸው ራስ አሊም ተደስተው ሸለሙት ይባላል ። አዝማሪው ግን " ሐሊማ ይላታል እናቱን " ማለቱ ነው ።

ሲቨን ሮቢንሰን እንደጻፉት እቴጌ መነን ኢትዮጵያን እየከፋፈሉ ሊሸጡ ካሰማሙ ባላባቶች እንደኛይቱ ናቸው ። በእሌክሳን ድርያ የቤልጅግ መንግሥት ቆንስል የነበረው ኤድዋርድ ብሎን ዲል ከእቴጌ መነን ጋር በመነጋገር አጋሜንና እንጣሎን በ15.000 ማርትሬዚያ ብርና በሶስት ሺ ጠመንጃ ለመግዛት ተስማምተው ነበረ ። ለዚህም ጉዳይ ኢትዮጵያዊው አባ ገብረ ማርያም ለኢትዮጵያ መንግሥት ኃላፊ ሆነው ለሽያጩ ተግባር ዋና ደላላና ተዋዋይ ነበሩ ።

አባ ገብረ ማርያም ካይሮ ውስጥ ከቤልጅጉ ቆንሲል ከብሎን ዲል ጋር የተዋዋሉት ውል እንዲህ የሚል ነበር ። " በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ። እኔ ገብረ ማርያም የኢትዮጵያ እጨጌ ፣ በኢትዮጵያ ገዥ በራስ አሊ ስም የሚከተለውን ተስማምቻለሁ ። ለቤልጅግ ንጉሥ ግርማዊ ቀዳማዊ ሊዎፖልድና ለእሳቸውም ወራሾች ሁሉ እንዲሆን የአጋሜን አውራጃ በሙሉ ከአዲግራት እስከ ባህሩ ድረስ ሰጥተናል " የሚል ነበር ። አባ ገብረ ማርያም በመስፍኑ በራስ አሊ ስም ውሉን ይጻፉ እንጂ ጉዳዩን የፈፀሙት እቴጌ መነን ናቸው ይባላል ።

ነገሩን ከሥሩ ለማምጣት ያህል በግብፅ የቤልጅግ ቆንሲል የነበረው ኤድዋርድ ብሎን ዴል እ. ኤ. አ. በ1837 ዓ.ም. ለቤልጅግ መንግሥት አንድ ሪፖርት ልኮ ነበር ። ሪፖርቱም ብዙ መንግሥታት የቀይ ባህርን አካባቢ ሲሻሙበት የቤልጅግ መንግሥት ለምን ዝም እንዳለ የሚገልፅ ነበር ። በኋላም የእንግሊዙ ብሪትሽ ኢስት እንዲያ ካምፓኒ ዘይላን ይዞ ፊቱን ወደ እርጊጐ ባዞረበት ጊዜ ብሎንዴል ደግሞ የአገሩ የቤልጅግ መንግሥት ከዙላ ምሥራቅ ያለውን እንፊላን እንዲይዝ መከረ ። እ.ኤ.አ. በ1842 ዓ.ም ወደ ቤልጅግ መንግሥት ባስተላለፈው ሪፖርትም የፈረንሳይ መንግሥት ኢድ የተባለውን ቦታ ከገዛበት ዋጋ ትንሽ ጨመር አድርጐ በሁለት ሺህ ብር ከኢትዮጵያ መሬት ቦታ ለመግዛት እንዲችል ከ25.000 እስከ 30.000 ድረስ የቤልጅግ ፍራንክ ግብፅ ድረስ ቢላክለት ለቤልጅግ የመጀመሪያውን የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት ለማስገኘት እንደሚችል አስታወቀ ። ኢድ በዛሬው ጂቡቲ ውስጥ ያለች ሥፍራ ስትሆን በዚያን ጊዜ ለፈረንሳይ የተሸጠችው በ1800 ማርትሬዚያ ብር ነበር ።

የቤልጅግ መንግሥትም እንፊላን ቢገዛ ምን ጥቅም እንደሚያገኝ እንዲገልፅለት ቆንሲሉን ብሎንዴልን ጠየቀ ። ብሎንዴልም በሰጠው መልስ "....ዛሬ ከምፅዋ ወደብ በያመቱ ሁለት መቶ ሺ ፍራንክ ያህል ገቢ ይገኛል ። የእንፊላን የባህር ዳርቻ ገዝተን ወደቡን ብናስፋፋው በምፅዋ የሚገኘውን ገቢ ወደ እንፊላ ማዞር ይቻላል ። ...." ብሎ አሳወቀ ። ቀጥሎ ባስተላለፈው ሪፖርትም ኢትዮጵያ በምሥራቅ በኩል ጤናማ አገር መሆኑዋን ፣ ሀብታምና ሀብቷም ያልተነካ ሕዝቡም ዘመናዊ መሣሪያ ስለሌለው አገሪቱ በቀላሉ የምትያዝ መሆንዋን ገልጾ "...አንድ አጥኚ ወኪል ወደ ቀይ ባህር ቢላክ የእንፊላን ሁኔታና ጠቅላላውን ኢትዮጵያን ሊያጠና ይችላል። የእንፊላ ገዢዎችም በቀላሉ በጥቃቅን ድለላ የሚዋዋሉን ናቸው ። በዳርቻው ላይ ተቆናጠን መብታችን የሆነ

መሬት ከያዙን በኋላ የሚያስፈልገው ነገር 500 የታጠቁ ሰዎች ወደ ሥፍራው ብንልክ በቂ ይሆናል ። እነኚህም የሚላኩት የታጠቁ ሰዎች ይህታችንን ለማጠናከርና ጠረፉን ለመጠበቅ በቂ ናቸው ። . . . . እንፊላ ደግሞ የኢትዮጵያን ደጋ ቦታዎች ለመያዝ አመቺ ሥፍራ ነው ። . . . . እንፊላን የምጠቁመው በኔ አስተያየት ለመጀመሪያ ጊዜ ለመቆናጠጫ ጠቃሚ መሆኑን በማወቄ ነው ። እሱ ከተያዘ መላውን አገር በቅኝ ግዛት ለመያዝ መንገዱ ቀላልና ክፍት ነው የሚሆነው . . . . ” ብሎ ምኞትና ዓላማውን ገለፀ ።በዚያው ላይ ደግሞ ሪፖርቱ በሚስጥር እንዲያዝ ይጠይቃል ።

የቤልጅግ መንግሥት ጉዳዩ እንዲጠና አደረገ ። በጥናቱ መሠረት የቤልጅግ ቅኝ ገዢነት የቀይ ባህርን አካባቢ መያዝ እንደማይጠቅም ታወቀ ። የማይጠቅምበትም ምክንያት ያኔ የስዊዝ ቦይ አልተቆፈረ ስለነበረ በመርከብ ወደ ቀይ ባህር ለመምጣት በደቡብ አፍሪካ ዞሮ በመሆኑ ብዙ ወጪ እንደሚያስወጣና ጉዞውም ረጅም በመሆኑ አያስፈልግም ተብሎ ተወሰነ ። ክውጭ በእንዲህ ያለሁኔታ እንዲቀር ሲደረግ በአገር ውስጥ ደግሞ የቴዎድሮስ መነሳት የእቴጌ መነንንም ሆነ የአባ ገብረ ማርያምን ምኞት አጨናገፈው ።

# ጎሹ ዘውዴ

ቀደም ብለን እንዳነበብነው ከካሣ ጋር ሲዋጉ የሞቱት ደጃች ጉሹ የጎጃሙ የደጃች ዘውዴ ሥልን ልጅ ናቸው ። አለቃ ተክለ ኢየሱስ ስለ ደጃች ጉሹ አወላለድ ሲተርኩ ፡ የሮማርድ “. . . .የእህቱ የድንቅነሽ ባል የዳሞቱ ደጃች ዘውዴ ጉልበት ተሰምቶት በዳሞት ላይ ጎጃምን ደርቦ ሊገዛ ከጅሎ ነበረ ። ግን ራስ መርድ ቶሎ ነቃበትና በምክንያት ይዞ ሊያስር እቴን ድንቅነሽን ልያት ይዘሃት ና ብሎ ምላሽ ጠራው ። ደጃዝማች ዘውዴም የተንኮል መሆኑን ሳያውቅ ወይዘሮ ድንቅነሽን ይዞ ገባ ። ራስ መርድም ደጃች ዘውዴን ይዞ በቀራንዮ ዋሻ አስሮ እቴን ድንቅነሽን እጅ አደረገ ። ከብዙ ቀን በኋላ ምሽቱ ስትናፍቀው ጊዜ ደጃች ዘውዴ መድኃኒት ታጠጣኝ ብሎ ወደ ራስ መርድ ላከ ። ራስ መርድም ታማኝ ገረድ ስደጅለት ብሎ አዘዘ ። ደጃች ዘውዴም በሌላ እጅ አልጠጣም ብሎ እምቢ አለ ። ራስ መርድም ዘበኛ ጨምሮ ምሽቱን ሰደደለት ። ደጃች ዘውዴም መድኃኒት ይጠጣ መስሎ እንደታበረ ተገናኙ ። ያን ቀን ደጃች ጉሹ ተፀንሶ አደረ . . . .” ይላሉ



ደጃች ዘውዴ ከደጃች መርድ ጋር ታርቀው በሥልጣናቸው ተመልሰው ነበርና ደጃች ዘውዴ ሲሞቱ ጉሹ በአባታቸው ሥልጣን ተተኩ ። ራስ ጉግሳም ጉሹን ገብር ቢሏቸው ደጃች ጉሹ አልገብርም ብለው እምቢ አሉ ። ራስ ጉግሳ ሊወጓቸው ወደ ጎጃም መጡ ። ጉሹ ሸሽተው ንብረታቸውን ከጅብላ ዋሻ ከትተው እሳቸው ወደ አሞሮ ሔደው ተደበቁ ። ራስ ጉግሳም በጎጃም ላይ ደጃች ጉበናን ሾመው ወደ በጌምድር ተመለሱ ። የራስ ጉግሳን መመለስ ጉሹ እንደሰሙ ከአሞሮ ጦር ይዘው መጥተው የደጋ ዳሞትን ጦር ጨምረው ደብረዘይት ውስጥ አምስትያ ከሚባል ቦታ ከደጃች ጉበና ጋር ጦርነት ገጥመው ጉሹ ድል አደረጉ ። ለራስ ጉግሳ አልገብርም እንዳሉ ሳይገብሩ በጎጃም ግዛታቸው ላይ ተቀመጡ ።

ከራስ ጉግሳ በኋላ የምስፍንናውን ቦታ ራስ ማርዬ ሲይዙም ጉሹ አልገብርም ብለው እምቢ አሉ ። ራስ ማርየም ሊወጓቸው ወደ ጎጃም ሲመጡ ጉሹ እንደተለመደው ከጅብላ ገቡ ። ራስ ማርዬም የጅብላ ምሽግ ጠንካራ መሆኑን አይተው በአገሩ ላይ ደጃች ማጠንቱን ሾመው ተመለሱ ።ራስ ማርዬ ወደ ጎንደር እንደተመለሱ ጉሹ ከምሽጋቸው ወጥተው ማጠንቱን ሊወጉ ወደ ቢቡኝ ሔዱ ። በዚያም ሆነው

“ ተጠናከር ጎጃም ተጠናከር ዳሞት ፡
አይተንም አናውቅ በአረፋ ነጋሪት”

ብለው ለአዝማሪ ግጥም ነገሩ ። ይህን ለአዝማሪ የተነገረውን ግጥም ደጃች ማጠንቱ እንደ ሰሙ እሳቸውም አዝማሪ አቁመው

“ በል አንዳችም እስቲ በል አይጎዳም ፡
እግዚአብሔር ከሰጠ የሰው ልጅ አይነሳም ።” ብለው ነገሩ ።

ሁለቱም ደጃዝማቾች በግጥም ከተመላሰሱ በኋላ በቢቡኝ ቀበሌ ሰበዝ ሜዳ ከሚባለው ቦታ ጦርነት ተጋጥመው ጉሹ ድል ሆነው ተያዙና ቋሚ ጨርቅ ከሚባለው ቦታ ታሠሩ ። ከደጃች ጉሹም ጋር የታወቁት ጀግኖቻቸው ፊታውራሪ ገለታ እና ፊታውራሪ ባርያው አብረው ተይዘው ታሰሩ ። ከዚህ ድል በኋላ የደጃች ማጠንቱ ገረድ ስትዘፍን ፡

“ከተያዘ ገለታ ፡
ደሞዜን የኔታ ።
ከተያዘ ባርያው ፡
አገሬን ልየው ” አለች ።

የደጃች ጐሹ ልጅ ደጃች ብሩ የአባታቸውን የደጃች ጐሹን መታሰር እንደሰሙ ሠራዊታቸውን አስከትተው መጥተው ሰጉዲት ከሚባል ቦታ ከደጃዝማች ማጠንቱ ጋር ጦርነት ገጠሙ ። በዚህም ጦርነት ደጃች ማጠንቱ ድል ሆነው ሸሽተው ከደጃች ውቤ ዘንድ ገቡ ። ደጃች ብሩም አባታቸውን ደጃች ጐሹን በሥልጣናቸው መለሱ ። ደጃች ጐሹ ለጐንደር የመሳፍንት መንግሥት አልገብርም ብለው ራሳቸውን ችለው ሲኖሩ ራስ ማርዬ ሞቱ ። ከራስ ማርዬ በኋላ ራስ ዶሪ በምስፍንናው ቦታ ተተክተው አጤ ሰለሞንን በግምብ አኑረው በሚያስተዳድሩበትም ዘመን ደጃች ጐሹ አልገብርም አሉ ። ራብ ዶሪም ሠራዊታቸውን አስከትተው ጐጃምን ለመውረርና ደጃች ጐሹን ለማስገበር ዘመቱ ። ደጃች ጐሹ ከልጃቸው ከደጃች ብሩ ጋር ሆነው አመዳሚት በተባለ ቦታ ላይ ጦርነት ገጠሙዋቸውና ራስ ዶሪን ድል አድርገው መለሱዋቸው ።

ራስ ዶሪ ሞተው ሥልጣኑን ራስ አሊ ሲይዙ ጐሹን ገብር ብለው ላኩባቸው ። ጐሹም እንደተለመደው እምቢ አሉ ። ራስ አሊ በጐጃም ላይ ማለት በደጃች ጐሹና በደጃች ብሩ ግዛት ላይ ሌሎችን ሾሙባቸው ። የየጁውን አዶዮ ባቡን በአገው ፣ መሸሻ ባቡን በዳሞት ፣ ሥዩም በቃኸኝን በጐጃም ሾመው ግዛታቸውን እንዲይዙ ሰደዱዋቸው ። ይህን ሲሰሙ ጐሹ የዳሞትን ጦር ፣ ደጃች ብሩ ደግሞ የጐጃምን ጦር አስከትተው ደረቤ ሜዳ ሰኩት ከሚባል ሥፍራ ጠበቋቸው ። አዲስ ተሿሚዎቹም የበጌምድርንና የየጁን ጦር ይዘው ደጋ ዳሞትን እየዘረፉ መጡ ። ሰኩት ሲደርሱም የሁለቱ ወገን ጦርነት ተጋጠመ ። ጦርነቱ ተፋፍሞ ብዙ ሰው ከአለቀ በኋላ የደጃች ጐሹ ጦር ድል አደረገ ። ሥዩም በቃኸኝ በጀግንነት ተዋግተው ፊቴን አዙሬ አልሸሽም ብለው በዚያው በጦሩ ሜዳ ላይ ሞቱ ። መሸሻ ባቡና አዶዮ ባቡ ግን ሸሽተው ኢጋምና ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ገብተው ምህረት እንዲደረግላቸው ተማፀኑ ። ደጃች ብሩ ግን ተከትለው ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ገብተው ሁሉንም እያረዱ ፈጁዋቸው ። አልቃሽም

"መሸሻ ባቡ ፣ አዶዮ ባቡ ያስነሱበቱ ፣
ሥዩም በቃኸኝ የሞቀበቱ ፣
ሣር አላበቀለም ሰኩት መሬቱ ።
የውሃም አይደል የሥዩም ደም ነው ፣
የሰኩት መሬቱ ሳሩ ለምለም ነው ።
ሥዩም በቃኸኝ የወረደበት ፣



እምስት መቶ ላም የተነዳበት ።
ሥዩም በቃኸኝ የሞተው ዝሆን ፣
ጦር መጣ ባሉት ይነሳ እንደሆን " ብላ ገጠመችላቸው ።

ለደጃች ጐሹም " ጐሹ የኢያሱ ልጅ ዓለም የሚያውቀው ፣
ዘውዱ አባቱ ነው ቢነግስስ ምነው "
እየተባለ ተዘፈነላቸው ።

ይህን የሹማምንቶቻቸውን ማለቅ ራስ አሊ ሲሰሙ ደነገጡ ። የጐሹንም የኋላ ታሪክ አጥንተው በወዳጅነት መያዙ እንደሚሻል አውቀው በመሐላ ተራርቀው ወዳጅ ሆኑ ። ወዳጅነታቸውን ለማጠናከርም ራስ አሊ ልጃቸውን ወይዘሮ የውብዳርን ለደጃች ጐሹ ልጅ ለብሩ በሚስትነት ዳሩላቸው ።

ደጃች ጐሹ ከጐንደር መሳፍንት ጋር በጀግንነት እየተዋጉ ኖረው በራስ አሊ ዘመን ወዳጅ ሆነው እፎይ ብለው ለመኖር ለላማዊ ኑሮ ሲጀምሩ ልጃቸው ደጃች ብሩ ተነሱባቸው ። ደጃች ብሩ ሠራዊታቸው እየበዛና እየደረጀ በመሔዱ ኩራትና ጉልበት ተሰማቸው ። የአባታቸውን ግዛት ዳሞትን በጐጃም ላይ ደርበው ለመያዝ ስለፈለጉ " ግዛቱን ለኔ ልቀቅልኝና ዝም ብለህ ተቀምጠህ ቀጠባ (ተጦር) " ብለው ላኩባቸው ። ወደ ደጃች ጐሹ የተላኩት መልክተኞች መልሱን ይዘው ሳይመለሱና እሺም እምቢም ማለታቸው ሳይታወቅ ደጃች ብሩ በአባታቸው ግዛት በደገሞና በመቻከል ፣ በፈጠበዶች የራሳቸውን ሰዎች እየሾሙ የጐሹን ሹሞች አባረሩ ።

ይህን ጥንስስ የፈሩ ያገር ሽማግሌዎች በነገሩ መሀል ገብተው አባትና ልጁን ለማስታረቅ ጥረት አደረጉ ። ደጃች ብሩ " እስታሁን የገዛው ይበቃዋል ። አገሩን ለኔ ለቆልኝ እኔ እየገዛሁ እሱን እጦረዋለሁ ። በዚህ እምቢ ካለ ተዋግቼ በጉልበቴ ግዛቱን እወስዳለሁ እንጂ ምንም ቢሆን እንደ ጥንቱ ይሁን ብዬ አልታረቅም " አሉ ። ሽማግሌዎቹም ወደ ደጃች ጐሹ ሔደው " እርስዎ ይሸነፉ (እሺ ይበሉን ) እሱ ጉልበቱ እንደመራው ይያዝ " ቢሏቸው ጐሹ " ወልጄው እርስዎ እልል ። ጋሻ አንግቤ አንተ እልል ። ሰው ካል ሳቀበት ያሰበውን ያድርግ " ብለው እርቁን እምቢ አሉ ። ከዚህ በኋላ ሁለቱም አባትና ልጅ ሊዋጉ ለጦርነት ተሰላለፉ ። ደጃች ብሩ ለጦርነት ከተሰለፈው ሠራዊታቸው መሀል ተገኝተው " አባቴን ማርኩ እንጂ እንዳትገድሉ ? " ብለው በአዋጅ አስ

ነገሩ ። የሁለቱም ወገን አንጋጣ በሚባል ሜዳ ላይ ተጋጥሞ የደጃች ብሩ ሠራዊት ድል አድርጐ አባትየው ደጃች ጐሹ ድል ሆነው ሸሹና አጋምና ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ገብተው ምሕረት ጠየቁ ። ከዚህ በኋላ እንደገና የሁለቱም ወገን መኳንንቶች አባትና ልጁን አስታርቀው በሰላም መኖር ጀመሩ ።

ይህን የአባትና ልጁን መዋጋት ራስ አሊ እንደሰሙ ከደብረ ታቦር ወደ ጐጃም መጡ ። አዴት ከሚባል ቦታ ሠፈር አድርገ ውም ደጃች ጐሹንና ደጃች ብሩን እንዲመጡ ላኩባቸው ።ደጃች ብሩ አልመጣም ብለው ሶማ አምባ (ምሽግ) ገቡ ። ደጃች ጐሹ ግን " በፊት የማልኩትን መሀላዬን አላፈርስም " ብለው ወደ ራስ አሊ ሔደው ተገናኙ ። ራስ አሊም የበፊቱንና ያሁኑን ጦርነት ተር ከው ተቆጡና ጐሹን አሠሩዋቸው ። የደጃች ጐሹ ሌላው ልጃቸው ተሰማ ጐሹ የሚባሉት የአባታቸውን መታሰር ሲሰሙ ራስ አሊ ዘንድ ቀርበው " በአባቴ ሰንሰለት እኔ ተለውጬ ልታሠርና እሳቸው ይፈቱ" ብለው ለመኑ ። ራስ አሊም ተሰማ ጐሹን አመስግነው በአባታቸው ምትክ አሰሩዋቸውና አባታቸውን ደጃች ጐሹን ፈተው ለቀቁላቸው ።

አዝማሪም " እኛ የተማርነው ሊቃውንቱ ሳናውቅ
ተሰማ ለአባቱ ተሰዋ እንደ ይስሐቅ ።" ብሎ

ገጠመላቸው ። ራስ አሊም ጥቂት ቆይተው ተሰማ ጐሹን ፈትተው ለቀቁዋቸው ። ደጃዝማች ብለውም በቡሬና በአገው ላይ ሾሙዋ ቸው ። በኋላም ራስ አሊ ከደጃች ካሣ ጋር ተዋግተው ድል ሆነው ማምለጫ ቀዳዳ አጥተው በተጨነቁበት ጊዜ ከዚያ ጭንቅ አውጥ ተው የጁ ድረስ ሸኙዋቸው ።

ጐጃሞች በአስማት ተግባር እውቅ ነበሩ ይባላል ።አለቃ ተክለ ኢየሱስ እንደጻፉት በጐሹ ዘመን የተፈፀመ ለማመን የሚያስቸ ግር አንድ አስደናቂ ታሪክ አለ ። አለቃ አርእያ የሚባል አስማ ተኛ ይልማ አማኑኤል ከሚባል አገር ጐጃም ውስጥ ይኖር ነበር ። የውላ ከሚባል አገር የአንድ ሰው ሚስት በውሽምነት ይዞ አስ ማት እየደገመ ማታ ማታ ወደ ቤቱ ያመጣት ነበር ። አንድ ቀን አውሬ እንዳይበላት የሚከላከለውን ድግምት ሳይደግምባት ቀርቶ በጭለማ ወደ አለቃ አርእያ ዘንድ ስትመጣ ሳሴ ከሚባል መን ደር ስትደርስ ጅብ በላት ። አባትና እናትዋ ፤ ባልዋም ሆነው ደን በጫ ሔደው ለደጃዝማች ጐሹ አቤት አሉ ። ደጃች ጐሹም "ተጨ



ሆብሃልና መጥተህ መልስ ስጥ " ብለው ወደ አለቃ አርእያ መል ዕክተኛ ላኩ ። አለቃ አርእያም በአስማታቸው ኮርተው "አልመ ጣም" ብለው መልስ ሰጡ ።

ደጃች ጐሹም " አስማቱ ሲያድነው አያለሁ " ብለው እጃቸ ውን ይዞ የሚያመጣ ጭፍራ ላኩባቸው ። ይህን ነገር አለቃ አር እያ በሰሙ ጊዜ በቤታቸው አጥር ዙሪያውን እፀመሰውር መድ ፍኑ ዓይን ደገሙና ረጩ ። ከደጃች ጐሹ የተላኩት ወታደሮችም የአለቃ አርእያን ቤት ማየት አቅቷቸው ባላገሩን ሁሉ አሳዩን እያሉ ሲገርፉና ሲያምታቱ ቆይተው ቀኑ ሲመሽ ወደ ደጃች ጐሹ ተመለሱ ። " ከነቤቱ ተሰውሮ ጠፋብን " ብለውም ነገሩ ። ደጃች ጐሹም" እርስ በእርሳችሁ እየተስማማችሁ ነው እንጂ ቤቱ ተሰ ውሮ አይደለም " ብለው ራሳቸው ለመሔድ ተነሱ ።

"የደጃች ጐሹ መኳንንትም " ያዋርደናልና አንሒድ ። ባይሆን ባይሆን ታማኝ ሰው ሔዶ ይያዘው " ብለው ቢያማክሩዋቸው "አይሆንም ። ሰውም አላምንም " ብለው ጉዞ ጀመሩ ። አማሬ ኢየ ሱስ ከሚባል ቦታ ሲደርሱ አለቃ አርእያ እንደመጡባቸው ሰም ተው የደጃች ጐሹ ነጋሪት እንዳይጮህ ድምጥ የሚዘጋ አስማት ደገሙ ። ነጋሪት እያስመቱ መለከት እያስነፉ የሚጓዙት ደጃች ጐሹ ድንገት ነጋሪቱም የመለከቱም ድምጥ ዝም አለ ። ሠራዊ ታቸውም ደነገጠ ። መኳንንቱም ደጃች ጐሹ ዘንድ ቀርበ " ይሄን ጉድ እየን ። ሌላ ሳይመጣ ይህን ጊዜ እንመለስ ። በሌላ ቀን በድን ገት አዘንግተን ለሊት እንይዘዋለን " ብለው መከረው ተቆጡና ደጃች ጐሹ ተመለሱ ። እንደተመከረውም በሌላ ቀን ድንገት ሌሊት አስይዘው ገርፈው ዋሚት ዋሻ ከሚባለው ቦታ አሰሩዋቸው ። አለቃ እርእያም በዚያ በታሰሩበት ቦታ ሆነው የሰው ሚስት ቀም ተው አውሬ ባስበሉበት ተፀፀቱ ። የአስማታቸውንም መዝገብ በእ ሳት አቃጥለውት ሞቱ ። " . . . .የአለቃ አርእያ ደቀ መዛሙርት አለቃ አስረስ ፣ ደብተራ ሕፃን ማርያም የሚባሉ ብዙ አስማተኞች ተተክተው ይልማ አማኑኤል ነበሩ . . ." በማለት አለቃ ተክለ ኢየሱስ ይተርካሉ ።

በዚሁ በደጃዝማች ጐሹ ጊዜ ብላታ አይከል ዲዱ የሚባሉ ሀብታም ሰው ነበሩ ። እኚህ ሰው ሞገስ የሚባል ሥልጡን አሽከር ነበራቸው ። አንድ ቀን ሞገስ ከውጭ መጥቶ ምሳውን ሊበላ ሲል ጌታው ብላታ አይከል ጠሩትና ምሳውን ሳይበላ አፍጥነው ወደ

ደጃች ጐሹ ወደቡሬ ላኩት ። ሞገስም ምሳውን ባይበላ በመላኩ ተናዶ ጌታውን ሊጐዳ ፈለገ ። ደጃች ጐሹ ዘንድ ሲደርስ ያልተላከውን " መጥተው ድግሴን ይብሉልኝ ብለዋል " ብሎ ነገረ ። ደጃች ጐሹም እውነት መስሏቸው " ምን አሳሰበው ። እሺ እመጣለሁ " ብለው መሰቡሰት ። ሞገስም ወደ ጌታው ተመልሶ " ደጃች ጐሹ ሊመጡ ነውና ተሰናዱ " ብሎ ነገረ ። ብላታ አይከል ያላሰቡትን ነገር ሲሰሙ ደነገጡ ። የሞገስንም ተንኮል አውቀው " ሞገስ ? አንድ እንጀራ ብነፍግህ ሺ እንጀራ ልታስከፍለኝ ነው ? " ቢሉት ሞገስ ተንኮለኛ ነበርና " የላኩኝን ነው የተናገርሁት እንጂ ሌላ አልተናገርኩም " አለ ። ብላታ አይከልም ቢቆጡትም ሆነ ቢገርፉት ደጃች ጐሹ የሰሙ እንደሆነ እንደሚጣሉዋቸው አውቀው " ሲበሉ የላኩት ማለት አንተ ነህ ። ፍርድ የለብህም ። በደለኛው እኔ ነኝ ። ምሳህን ሳላበላህ መላኬ ጥፋቱ የኔ ነው " ብለው ለደጃች ጐሹ ግብዣ ድግሳቸውን መደገስ ጀመሩ ።

ደጃች ጐሹ እመጣለሁ ያሉት በቅርብ ቀን ስለሆነ ብላታ አይከል ጠላም ሆነ ጠጅ ለማስጠመቅ ጊዜው አጭር ሆነባቸው ። ከዘመድ ከወዳጅ መላከተኛ እየላኩ ጠላና ጠጅ አሰባሰቡ ። በቤታቸውም እምሳ ምጣድ አስጥደው ቶሎ ቶሎ እየተባለ አንድ ሺ እንጀራ ተጋገረ ። የተሰበሰበውም ጠጅ ሶስት ጋን ሞላ ። አምስት ሰንጋ አሳርደው ደጃች ጐሹ ሲመጡ ታላቅ ግብር አበሉ ። ደጃች ጐሹም ከዚያው ከብላታ አይከል ቤት አድረው በማግስቱ ሊሔዱ ሲነቡ " ምን ፈልገህ ነው እንዲህ አሰበህ የጠራኸኝ ?" ብለው ብላታ አይከልን ጠየቁ ብላታ አይከልም የሞገስን ተንኮል አጫወቷቸው ። ደጃች ጐሹም ሰቀው በድንገት ይሄን ያህል ድግስ በመገኘቱ ተደንቀው ብላታ አይከልን ሸልመው ሔዱ ።

ደጃች ጐሹ ደግ ሰው ስለነበሩ አዝማሪ

" የደጃች ጐሹ ሞግዚት ፣
እህል አታቀምስ በጊዜያት ።
ይተዋት ትቅርብዎ ፣
እናትም አትሆንዎ ። " ይላቸው ነበር ።



# ምዕራፍ 3

## የጐጃምና የሰሜን ጦርነት

ወደ አባማችን ወደ ደጃች ካሣ ትረካ እንመለስና ካሣ አሁን የቀሩዋቸው ጠላቶች የስሜኑ ደጃች ውቤ ፣ የጐጃሙ ብሩ ጐሹ ፣ የሸዋው ኃይለ መለኮት ናቸው ። እነኚህም ታላላቆቹ ጠላቶቻቸው እንጂ ሌላው ትናንሹ ሽፍታ በብዛት ነበር ። ካሣ አይሻል ላይ ራስ አሊን ድል ካደረጉ በኋላ ብሩ ጐሹን ግባ ብለው ላኩባቸው ። ደጃች ብሩም ስቀው ከዚያ በፊት በደጃች ካሣ ላይ የደረሰውን መጉላላት ያውቃሉና " ስካስ ተዘንብሏል ይሄ ሁሉ ጠጅ " የሚል አንድ መስመር የግጥም ስንኝ ወደ ደጃች ካሣ ላኩ ።

ደጃዝማች ካሣም የግጥሙን አንድ መስመር እንደሰሙ "እኔ ተጠጥቷል መስሎኝ ነበር እንጂ" ። ማለቱ ነውኮ ብለው ባለፈው ተግባር ያለመፀፀታቸውን ለማስጽ ጭምር ፣

"አይዋጋም እንጂ ጠመንጃ ተኩሶ
አይዋጋም እንጂ ዘብ ይዞ ገስግሶ
ወትሮም ልማዱ ነው ጐጃሚ ለስቅሶ" ብለው ወደ ደጃች ብሩ ላኩ ።

ከዚህ በኋላ ብሩ ጐሹን ለመፈለግ ወደ እነብሴ ሔዱ ። ቋሚ ጩርቅ ከተባለ ቦታ ሠፍረው ሳለ አንድ ቀን ግብር ላይ ደስታ የሚባል አሽከራቸው ተነስቶ ፎከረ ደስታ በብዙ የጦር ሜዳዎች ብዙ የጀግንነት ተግባር የሠራ ነው ። ቢፎክርም "እንኳን ያንተን ፊት የኛን የአሽከሮችህን ፊት የሚያይ አለን ? "ባለ ጊዜ ደጃች ካሣ በአነጋገሩ ልባቸው ተነክቶ ጠጅ ይጠጡበት የነበረውን ብርሌ ወረወሩት ብርሌዋም ከፊታቸው ካለ የአንጨት ገበታ ጋር ተጋጭታ ሳትሰበር ዳነች ገበታው ግን ተሰበረ ። ወዲያውኑ ተነስተው "እኔ የክርስቶስ ባርያ ። ክርስቶስን ከያዝሁ ማን ከፊቴ ይቆማል" ብለው ፎከሩ ። ፉከራቸውን ጨርሰው ሲቀመጡም አሽከር ብርሌ አንስቶ ጠጅ ሞልቶ ሰጣቸው ።

ደጃች ካሣ የብርሌይቱን ያለመሰበር አይተው ከተቀመጡበት ተነስተው “ማዳን ይቻልሃል ፡ ጌታዬ ሆይ ቸሩ እግዚአብሔር የሚሰበረውን አድነህ የማይሰበረውን ሰበርከ ኃያል አንተ ነህ” ብለው ሰግደው ተቀመጡ ። በብርሌዋም የተቀዳላቸውን ጠጅ ጠጡ ። ይህን የብርሌዋን ያለመሰበር ያዩት ካሣ የኃይል ብዛት ዋጋ እንደሌለው አሰበው ሠራዊታቸውን እየመሩ ወደ ደብረ ፋራን ተሻገሩ ። ደብረ ፋራን ሲደርሱ ደጃች ብሩ ጎሹ ሸሽተው ሔዱ ፡ ደጃች ካሣም ጎጃም ገብተው ሁለት ወር ያህል ተቀምጠው የብሩን ሁኔታ ይከታተሉ ጀመር ። ደጃዝማች ብሩ ጎሹም ስንቃቸውን አዘጋጅተውና ይዘው ሶማ ገቡ ።

ደጃዝማች ካሣ ቦማን ከበው ተቀመጡ ። አንድ ቀንም አሽከራቸውን ወደ ደጃች ብሩ ልከው “የፈረስዎን ስም አባ ዳምጠውን ለኔ ይተውልኝ ። ይህ ባይሆን ደግሞ ሌላ መልካም ስም ለፈረሴም ያውጡልኝ” ብለው በአክብሮት ላኩባቸው ። ደጃዝማች ብሩም ትዕቢተኛ ነበሩና “ተንጓለል በለው” ብለው መልሱን ላኩ ። ካሣ ይህን ሲሰሙ ተናደዱ ። ጠጉራቸውንም ነጩ ሶማ የገቡትን ደጃች ብሩን ለመያዝም ሆነ ጦርነት ለመግጠም ሥፍራው ፈጽሞ የማያመች ስለነበር ካሣ ሶማን ትተው ወደ ሜጫ ሔደው ይጠባበቁ ጀመር ። ብሩ ጎሹም የካሳን መራቅ እንደሰሙ ከሶማ ወጡ ። የብሩ ጎሹን ከሶማ መውጣት የሰሙት ካሣ ሌሊት በጨረቃ እየገሰገሱ ሲደርሱባቸው ደጃች ብሩ አምልጠው በሜቃታ ተሻግረው በደራና በጃርሶ አድርገው ኩታይ ገቡ ። ደጃች ካሣም ተከታትለው በድብቅ አልባሶ ደረሱ ።

ደጃች ብሩ በኩታይ ወዳጃቸው የሆነ አንድ ኦሮሞ ነበርና “ደጃዝማች ካሣ የት እንደደረሱ ሰልለህ ንገረኝ” ብለው ላኩበት ። በዚያ ያለው የኦሮሞ ብሔረሰብ በሙሉ በካሣ መወረሩን ፈርቶ ነበርና የደጃች ብሩ ወዳጅ የነበረው ኦሮሞ ከደጃዝማች ካሣ ጋር ተባብሮ ለተላከበት መልዕክተኛ “ጦርም የለ ። ደጃች ካሣም አልመጣም” ብሎ መልስ ላከላቸው ። ደጃች ብሩ ይህን ሲሰሙ አገር ሰላም ነው ብለው ሲዝናኑ ደጃች ካሣ ድንገት ደረሱባቸው ። ደጃች ብሩ የሠፈሩት ጀንዳና ጨንገር መሀል ነበር ። ካሣ ምርጥ የሆኑ ጥቂት ወታደሮች ይዘው ባካባቢው ካለው የበቆሎና የማሽላ ሰብል ውስጥ ገብተው ተደበቁ ። በዚያም አድፍጠው ሲጠባበቁ የደጃች ብሩ የጦር መኮንን (አዛዥ) አምባው ሰላም ነው ብሎ



የማዕረግ ልብሱን ለብሶ በፈረስ ሆኖ ታጅቦ ካሣ በተደበቁበት ሰብል አጠገብ ሲያልፍ ካሣ በድንገት ከተደበቁበት ወጥተው በሾጉጣቸው ጥይት ራሱን መትተው ጣሉት ። የጦሩ አዛዥ እንደወደቁ ካሣ ቶሎ ብለው የአዛዡን በደም የተነከረ ልብስ ገፍፈው በጦራቸው ላይ ሰክተው ይዘው በደጃች ብሩ ሠራዊት መሀል ገብተው “አዛዥህ ሞቷልና ተማረክ” እያሉ አሸበሩት ። ሠራዊቱም የአዛዡን በደም የተነከረ ልብስ በማየቱና አዝማቹ መሞቱን ባወቀ ጊዜ አብዛኛው ሳይዋጋ ሲሸሽ የተቀረውም ተማረከ ። በተለይም የደጃች ብሩ ድል መሆን ዋና ምክንያት የሆነው የደጃች ብሩ ሠራዊት ከደጃች ካሣ በሙሸሽ ጌታውን እየተከተለ አገር ለአገር መዞሩ ሰልችቶት ነበርና ከካሣ ጦር ጋር ምንም ሳይዋጋ ግንቦት 19 ቀን ጌታውን አስያዘ ።

ደጃች ብሩ እንደተያዙ ካሣ ወደ ጎጃም ተጓዙ ። የብሩ ጎሹ ሚስት ወይዘሮ የውብዳር ጅብላ ከሚባለው አምባ መሽገው ነበርና ካሣ የየውብዳርን ወንድሞች ደጃች ሀይሉን ደጃች ይማምን ባላቸውን ደጃች ብሩ ጎሹን ከፊት አስቀድመው “ አምባውን ልቀቂ አለቅም ካልሽ ያው ከፊት ናቸውና ወንድሞችሽን ግደያቸው” ብለው ላኩባቸው ። ወይዘሮ የውብዳርም “ ለባሌ ለብሩ አይሰጡኝ እንደሆነ አምባውን ይቀበሉኝ” የሚል መልስ መለሱ ። ካሣም በየውብዳር ጥያቄ ተስማምተው አምባውን ተረከቡ ። ከአምባው ም ብዙ ጠመንጃና ምንጣፍ ብርሌና ሌላም ዕቃ ሁሉ ተገኝቶ ተማረከ ። ደጃች ካሣም በአምባው ብላታ ደሲታን ሾመው ደጃች ብሩን ይዘው ጉዞ ጀመሩ ። አምባ ጫራ ሲደርሱም ደጃች ብሩን ሣር አምባ እንዲታሰሩ አደረጉ ። በጎጃምም ተድላ ጓሉን የጦር አዛዥ ባላምባራስ ወልታን ምስለኔ አድርገው ሾሙ ። ይህን ካደረጉ በኋላ ካሣ ወደ ደብረ ታቦር ጉዞ ጀመሩ ። በጉዞውም ጊዜ የጎጃም ባላባት ልጆች የሆኑትን የደጃማቾ ጎሹን ልጆች የሌምቱ ጎሹን ይልማ ጎሹን ንጉሤ ጎሹንና ተሰማ ጎሹን በዘበኛ እያስጠበቁ ፊት ፊት አስቀድመው ይጓዙ ጀመር ። ይህን ጉዞ የተመለከተው ሸናሻ አብጠው የተባለ አቅራሪ

“አምባ ቢጠበው ሰንሰለት ቢያንሰው
አንድ አርጎ አጓዘው የጎጃምን በው ።
ብሩን ጨው አድርገህ ከመነዘርከው ፡
ውቤን ጫማ አድርገህ ሸዋን ከፈተው” ብሎ አቅራራ

ይህ ግጥም ውቤን ረግጠህ ጣልና ወደ ሸዋ ዝመት ለማለት ነው ።

ምክንያቱም በእሁኑ ጊዜ የቀሩት ታላላቅ ጠላቶች የስሜኑ ወይም የትግሬዩ ገዢ ደጃች ውቤና የሸዋው ኃይለ መለኮት ብቻ በመሆናቸው ነው ።

ደጃዝማች ካሣ ወደ ደጃች ውቤ ለመዝመት በሐሳብ ላይ ሳሉ በጐጃም የሾሙዋቸው ደጃዝማች ተድላ ጓሉ የካሣን መራቅ አይተው ሸፈቱባቸው ተድላ ጓሉ የሸፈቱበት ምክንያት ካሣ የጐጃምን የባላባት ዘሮች ሁሉ ሊያስሩ ነው የሚባል ወሬ ስለ ተሰማ ነው ። በዚህ ባልተረጋገጠ ወሬም ተድላ ጓሉ ሊሸፍቱ አላሰቡም ነበር ። አንድ ቀን ግን በመኳንንቶች ዘንድ ሁሉ በአዝማሪቱ ታዋቂ የሆነው ጐጃሜው ሊቀ መኳስ መርሻ ከደጃዝማች ተድላ ጓሉ ሠፈር ሌሊት ገብቶ


“እናንተ የጐጃም መኳንንት ፣
ጭቃ አይነካችሁ በክረምት ።
በአገራችሁ በወንዛችሁ
ወየው ወየው በራችሁ ።
አልተከልኩ እንኳ ተገርዬ
ዱብ አለ መከራዬ ” እያለ በማሲንቆ በማዝመሩ ተድላ

ጓሉ ጉዳዩ ገብቷቸው ከዱ ። “ ወየው በራችሁ ” ማለቱ እንደ ጤፍ ልትነዱ ነው ማለቱ ነው ። ተድላ ጓሉም ዛሬ ደብረ ማርቆስ ከተባለው ከተማ መንቆረር ገብተው ሠፈሩ ። ዕድሌን ልሞክር ብለውም ራሳቸውን ደጃዝማች ብለው በጐጃም የበላይ የሌለባቸው መሆኑን አሳወቁ ። ደጃች ካሣ የሾሙዋቸውንም ሹሞች እየሻሩ የራሳቸውን ሰዎች ሾሙ ።

ደጃች ተድላ ሸፍተው በጐጃም ሹም ሽር ቢያደርጉም የደጃዝማች ካሣ ድንገተኛ አመጣጥ የማይታወቅና አደገኛም ስለሆነ በግዛታቸው ዙርያ በየበሩ ጠባቂ አስቀምጠው ነበር ። እነኚህም ጠባቂዎች ከካሣ ጋር እንዲዋጉ ሳይሆን የካሣን መምጣት ጠብቀው እንዲነግሩ የተዘጋጁ ነበሩ ።

ካሣ ግን የተድላ ጓሉን መሸፈትና የጐጃምን መያዝ ቢያውቁም ተድላን አቆይተው ትልቁን ተቀናቃኛቸውን ደጃች ውቤን ለመምታት አሰቡ ። ደጃች ውቤን መጀመሪያ በሰላም መንገድ ለመጠየቅ ብለው ጐንደር ላይ እንደሆኑ እንዲገብሩላቸው አስጠየቋቸው። ደጃች ውቤም “ እረ አንተ ማነህና ነው እኔ የምገብርልህ?” ብለው መልስ ላኩባቸው ። ደጃዝማች ካሣም ለተላከባቸው





የአጤ ቴዎድሮስ ምሽግ (መቅደላ)

መልዕክት ሲመልሱ “ የጐልያድንና የዳዊትን ታሪክ ይመልከቱ ። ጥጋብዎንም ለማብረድ በቅርብ ቀን እመጣለሁ ” ብለው ላኩ ።

ደጃዝማች ካሣ ሠራዊታቸውን በሚገባ ካደራጁ በኋላ የግዛት ወሰናቸው ወደሆነው ወደስሜን ተራራ ተጓዙ ። ደጃች ውቤም ጀግና የሆነ ሠራዊታቸውን አስከትለው ስሜን ተራራን ወጥተው ኃይለኛ ብርድ ካለበት ቧሒት ተራራ ላይ ሠፈሩ ። ደጃዝማች ካሣ የካቲት 3 ቀን 1845 ዓ.ም. ስሜን ተራራ ደርሰው ሠፈር እንደተደረገ ባጠገባቸው ያለውን ጆን ቤል የተባለውን እንግሊዛዊ “እስቲ በመነጥር አይተህ የሚታይህን ንገረኝ ” አሉት ። ቤልም “ የሸማ ድንኳን ተተክሎ ይታየኛል ” አላቸው ። ደጃዝማች ካሣም “ እያሳድረኝ ባላድረው ” ብለው ፎክረው ተነስተው ሠራዊታቸውን ተነስ አሉ ። ሠራዊቱም ተነስቶ ሲሰበሰብ ካሣ ከፍ ካለ ሥፍራ ቆመው “ እንኳን ይህን ቁርጥማታም ፣ ወሎን መትቼ ተሻግሬ የሸዋውን ንጉሥ እይዘዋለሁ ። ስሜን ስሜን እንግርሃለሁ ያልሁህ ስሚ ቴዎድሮስ ነው አይዞህ ፣ የውቤ ነፍጥ ፣ የውቤ ነፍጥ ቢሉህ አትፍራ ። የተለጐመው ጨርቅና ባሩድ ነው ። እይነካህም ። እኔ የክርስቶስ ባርያ ሁሉንም አሳይሃለሁ ። ” ብለው ሠራዊታቸውን

ሸኙት ። ሠራዊቱም ከደጃች ውቤ ሠራዊት ጋር ገጥሞ ከፍተኛ ውጊያ ተደረገ ። በመጨረሻም ድሉ የቴዎድሮስ ሆኖ ደጃች ውቤ ተያዙ ። የተረፈው የደጃች ውቤ መኳንንትም ደረስጌ ማርያም ገብቶ ተማጠነ ። ቴዎድሮስም "ደረስጌ ማርያም የገባውን የደጃች ውቤን ሰው ምሬዋለሁ" ብለው አዋጅ ነገሩ ።

ይህ ጦርነት ከተካሔደ በኋላ የደጃች ውቤ ልጅ ደጃዝማች ጓንጉል ሠራዊቱን አሰልፎ ነጋሪቱን እያስመታ አባቱን ለመርዳት ደረሰ ። መኳንንቶቹ ቀርበው "አሁን ሁሉም ነገር አልቋልና እንመለስ" ቢሉት "የሟንኩትን አረር እንደበረዶ ሳላራግፍበት ፈርቼ አልመለስም" ብሎ ጦርነት ገጠመ ። ግን ውጊያው ብዙም ሳይቆይ ጓንጉል ድል ሆኖ ሸሸ ።

ቴዎድሮስ ደጃች ውቤን አስረው "ገንዘብዎን ያምጡ" ቢሏቸው "ገንዘቤን ሁሉ የደረስጌ ማርያምን በመሥራት ጨርሻለሁ ከየት አመጣለሁ ፦" አሏቸው ። ቴዎድሮስም የደጃች ውቤ ዕቃ ወዳለበት ሀይ ወደተባለው አምባ ሔዱ ። የደጃች ውቤ ዕቃ የተቀመጠው ቤቴል ከሚባለው ሥፍራ ነበር ። ከዚያ ሲደርሱ የውቤ ልጅ ደጃዝማች ጓንጉል በአባታቸው መታሰር ምክንያት አዝነው ስለነበር ቴዎድሮስ መምጣታቸውን ባወቁ ጊዜ "አባቴን ከእስራት ይፍቱልኝ እንጂ ገንዘባቸውን አስረክባለሁ" ብለው ቀርበው አመለከቱ ። ወዲያው ዕቃውም የተቀመጠበትን አምባ አስረከቡ ። በዚያም "እጅግ በጣም የበዛ ወርቅና ብር ፣ ብርጭቆ ፣ ብርሌ ፣ ሁለት መድፍ ከነጥይቱ ፣ 500 ጠመንጃ ፣ ሁለት ጋን ሙሉ የልብስ መስፊያ መርፌ ተገኘ" ብለው አለቃ ወልደ ማርያም ሲጽፉ ዱፍተን ግን 40.000 ጥሬ ብርና 7.000 ጠመንጃ መማረኩን ጽፏል ። ከዚህ ከተገኘው ገንዘብ ለመኳንንቱና ለወታደሩ እንደየማዕረጉ ከአሥር ብር እስከ ሽህ ብር እያንዳንዱ ተሰጠው ። ደጃች ውቤ "ገንዘቤን ሁሉ የደረስጌ ማርያምን በመሥራት ጨርሼዋለሁ" ያሉት እውነታቸውን ነው ። ቤተ ክርስቲያኒቷን ያሠሩዋት ሹምጥር በሚባል ጀርመናዊ ነው ። የውስጡን ስዕሎች የሳለው ዛንደር የሚባል ጀርመናዊ ሰዓሊ ነው ።



# ም ዕ ራ ፍ 4

## ደጃዝማች ብሩ ጐሹ — ደጃዝማች ውቤ

### ብሩ ጐሹ

ስለ ደጃዝማች ብሩ ጐሹ ፕላውዴን ሲጽፍ "...እፍንጫው እንደ ሮማውያን ቀጥ ያለ ሲሆን ጠጉሩ ከግንባሩ ገለጥ ብሎ መሀል ራሱ ድረስ በራ ነው ። እንደሚሉትም እንዲህ ያደረገው ሽቶ ነው ። ሌላው ጠጉሩ ግን ጥቁር ሆኖ ያጐፈረና ውበት የሚሰጥ ነው ።.. አመለካከቱ ኃይለኛ ነው ....ሲናገርም ረጋ ብሎ ነው ። ፊቱ ጥቁር ሆኖ ጨፍጋጋ ነው ።...." ይላቸዋል ።

ፕላውዴን ከአገሩ እንደመጣ ከብሩ ዘንድ ደርሶ በዚያ ከርሞ ነበር ። ከእሳቸው ዘንድ በነበረበት ጊዜ ያየውን ሲጽፍ "....ከድንኳኑ ውስጥ ስገባ ብሩ ከመሬት ቁጭ ብሎ አየሁት ። ከእርሱ ጋር አንድ ጠጉራቸው ነጭ የሆነ ሽማግሌ ሰው አሉ ። አጠገቡ ለመድረስ አምስት ያርድ ያሀል ሲቀረኝ አጋፋሪው በያዙት አጭር በትር እንድቆም አመለከቱኝ ። ብሩም እንደተቀመጠ በፀጥታ ይመለከተኝ ጀመር ።

"....ስለንግሥታችን አንዳንድ ነገር ጠይቆኝ ስመልስለት በጣም ሳቀ ። የሳቀውም በተሰባበረው በአማርኛ አነጋገሬ ነው ። እንድቀመጥም ጋበዘኝ ።....ለሱ ያመጣሁለትን እሮጌ የፈረስኛ ሰይፍ ፣ ያስያዝኩት አሽከሬ እንዲያመጣ አዘዝሁት ። ብረቱ ግን በጣም ጥሩ ብረትና የተወለወለ ነበር ።.... ሲያየው ተደሰተ ። በእጁ ግን አልነካውም ። ....ምግብ ቀርቦልኝ ስበላም ብሩ አበላሌ ደካማ መሆኑ ገባው ። ጠጅ መጥቶልኝ በጠጣ አይቶ እንደ ሰው ትጠጣለህ አለኝ ።...ለሌሊት የሚሆነኝም አንድ ገንቦ ጠጅ አዘዘልኝ ። ....ሁለት ባልደረቦችም ሰጠኝ ። አንደኛው ባልደረባዬ አዛዡ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አጋፋሪው ነው ። አዛዡ ለምግብና ለአስፈላጊዬ ነገር ሁሉ እንዲሆን የተሰጠኝ ሲሆን አጋፋሪው ደግሞ ወደሱ ዘንድ ስሔድ ለማስገባትና መልዕክት ስልከውም እንዲነግርልኝ ነው ።

“....በማግስቱ ተጠርቼ ወደ ድንኳኑ ሔድሁ ። ድንኳኑ 70
ሜግ ያህል ርዝማኔ አለው ። ያ የሰጠሁት ሰይፍ ተመዝዞ ተቀ
ምጦ አየሁ ። ....እንደተቀመጥሁ አንድ ብርሌ ጠጅ ተሰጥቶኝ ፣
ስመለከት ጥበበኛው ሠራተኛ እሳት እያይዞ የሰይፋን እጀታ አወለ
ቀው ። የተሻለ ከአውራሪስ ቀንድ የተሠራ እጀታም አገባለት ።
ይህ ሁሉ ተግባር የተከናወነው በአምስት ደቂቃ ውስጥ ነው ።
....በሳምንቱም በፈረስ ጉግስ ጨዋታ ላይ ያን ሰይፍ ይዞ ለሕ
ዝብ ሁሉ አሳየ ።

“ አረብ ወይም ቱርክ አለመሆኔንና እንግሊዛዊ መሆኔን ነገር
ኩት ። እሱም ይህን ባለማወቁ ይቅርታ ጠየቀኝና ‘ ታዲያ ስምህን
ማን ብዬ ልጥራህ ’ አለኝ ። እኔም ስሜን ነገርኩ ። በትክክል ለመጥ
ራት ስሜ አስቸጋሪ መሆኑን ነገረኝና እንዲያው “እንግሊዝ ” እን
ዲለኝ ተስማማን ።

“ ...አንድ ቀን ማታ በጭለማ ተጠራሁ ። ደርዘን ከሚሆኑ
ሹማምንቶች ጋር ተቀምጦ መጠጥ ሲጠጣ ደረስሁ ። ተራራ ላይ
አስሮት የነበረው ደጃች መርሶ (የአሊ ሹም) ከታሰረበት ከተራራው
መጥቶዋል ። ...መርሶ ወጣትና ቆንጆ መልክ ያለው ነው ።
ቁመናውም ደስ የሚል ነው ። ቀኝ እጁን በሰንሰለት ታስሮ ግራ
እጁን ከታሠረ ከአንድ ታማኝ አሽከር ጋር አንድ ያርድ ያህል ርዝ
መት ባለው ሰንሰለት ተቆራኝተዋል ። ይመር ሣህሉንም ከዚያው
አገኘሁት ። ሆዳምና በአገሪቱ ያለ መልከ ጥፉ ክፉ ሰው እሱ ብቻ
ነው ። የድንኳኑ ውስጥ መብራት ደብዛዛ በመሆኑ ብዙም አይታ
የኝም ። የሚበራው ሁለት ጧፍ ነው ። እያንዳንዱም ባንዳንድ ሰው
ተይዞአል ። ...ጥቂት ቆይቼ ቀስ ብዬ ሹልክ ብዬ ወጣሁ ።

“በማግስቱ ብሩ በደህና መንፈስ ነበር ። በዕለቱ የጉግስ
ጨዋታ ነበርና በዚያ ቦታ ሁላችንም ተገኝተን ነበር ። ብሩ በፈ
ረስ እንደመጣ የጉግሥ ጨዋታው ተጀመረ ። ጨዋታው አልቆ በፈ
ረሱ እንደሆነ ወደ ድንኳኑ ሲሄድ ሌሎችም ተከትለውት ሔዱ ።
በአዳራሽ ግብር ተዘጋጅቷል ። በብሩ ድንኳን ውስጥም ገበታ ተዘ
ርግቷል ። በገበታዎቹ ላይ በሺ የሚቆጠር የጤፍና የሌላም እህል
እንጀራ ተደርጓል ። እኔ ስገባ ታላላቅ መኳንንቶች ከመስፍኑ
አጠገብ ከመሬት ተቀምጠዋል ። እሱ ግን የተቀመጠው ድንክ
አልጋ ላይ ነው ። ጐራዴውን የያዘው አሽከር ከኋላው ቆሟል ።
ሌላው አሽከር ደግሞ ጋሻውን ከጣምራ ጦሮች ጋር ይዞ እሱም
ከብሩ ኋላ ነው ።



“አምስት ይሁን ስድስት የሚያማምሩ የመኳንንት ልጆች
በአንገታቸው ዙሪያ የብር አሸን ከታብ ያደረጉ ዙሪያውን ቆመዋል።
አንድ ትልቅ ሰው’ ብሩ ከተቀመጠበት አልጋ አጠገብ ሆኖ
ዝንቦች እንዳያርፉበት ጭራ ይዞ ይከላከላል ። ብርሌውን የሚቀ
በልና ትእዛዙን የሚነግር አንድ አሽከር ደግሞ ከአጠገቡ አሉ ።
ሁለት ይሁን ሶስት አለቆች ዘንጋቸውን ይዘው ግብር በይውን ያኋ
ፍራሉ ። በትልልቅ ጋን የተቀመጠውን ጠጅ ሴቶች እየቀዱ ይሰ
ጣሉ ። አሳላፊዎች በብዙ መቶ የሚቆጠሩ መጠጫ ዕቃዎች ያድ
ላሉ ። ከጉሽና ከሌላ ቀንድ የሚሠራው ዋንጫ ለወታደሮች ይሰ
ጣል ። ለታላላቅ ሰዎች የሚሰጠው ግን ብርሌ ነው ። የወጥቤት
ሴቶች እያንዳንዳቸው ድስት እየያዙ ገብተው ለማቅረብ ተዘጋጁ ።
ሥጋ ቤቶችም 30 ይሁን 40 ከብት አርደዋል ።

“ በግብሩ ላይ መጀመሪያ የደረሰው ሥጋ ለመኳንንቶች
ቀረበ ። ቢለዋም ሁሉ ተሰጠ ። እያንዳንዱ ሰውም ሥጋውን ይዘው
ከቆሙት አሽከሮች ላይ የቻለውን ወይም የሚያስፈልገውን ያህል
ይቆርጣል ። እንጀራውና ጥሬ ሥጋው ተበልቶ እንዳበቃ ጥብስ
ሥጋ ቀረበ ። ተበልቶ ሲጠገብ ወይም ሊጠገብ ሲል ጠጅ ታደለ ።
....ይህም የወታደሩ የመግቢያ ጊዜ መድረሱን ማሳወቂያ ነው ።
...ወታደሩ በተራው ገባ ። ለወታደሩ ሥጋ መብሊያ ቢለዋ አይሰ
ጥም ። ጥሬ ሥጋ የሚበሉት ወታደሮች በያዙት ሾተል ወይም
ጐራዴ ነው ። ሥጋ የሚቆርጡት የሚያስገርመው ነገር ሥጋውን
በአፋቸው ይዘው ሲቆርጡ አፍንጫቸውን ያለ መቁረጣቸው ነው ።

“ በዚህ ጊዜ ሁሉ ቂላቂል የሆኑ አጫዋች ሰዎች እየገቡ
ታላላቆቹን ያስቁ ነበር ። አዝማሪዎችም ራቅ ብለው ከዳር ሆነው
ያጫውታሉ ። ከውጭ ነጋሪት ይጐሸማል ። የእምቢልታና መለከት
ድምፅም ይሰማል። ፈረሰኞች ጦራቸውን ይዘው የጦር ልብሳቸ
ውን ለብሰው በፈረስ ላይ እንደሆኑ እየሸለሉና እየፎከሩ ድንኳኑ
በር ድረስ እየጋለቡ ደርሰው ይመለሳሉ ።

“ ፈረሰኞች ድንኳኑ ድረስ እየጋለቡ መመለስ ሲጀምሩ የድን
ኳኑ በር በሰፊው ተገለጠ ። ፈረሰኞቹም እየጋለቡ ድንኳኑ ውስጥ
ይገቡና ጦራቸውን ወርውረው አለቃቸው ፊት ከመሬት ይተክሉ
ታል ። ከዚያም ፈረሳቸው ላይ እንደሆኑ ጐራዴያቸውን መዝዘው
ፈረሳቸውን እያንጐራደዱ ወይም ከውጭ ወደ ውስጥ ፣ ከውስጥ
ወደ ውጭ እየጋለቡ ድንፋታ (ቀከራ) ይጀምራሉ ። ፎካሪው ፎከሮ

ሲያበቃም እጅ ነስቶ ይመለሳል ። እንዲህ እያለም ተራ በተራ ይካሔዳል ። በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ የጦር አለቆች የሚቀመጡት ከውጭ ነው ። . . . .

" አንድ ቀን ጧት ማለድ ብዬ ወደ ብሩ ዘንድ ሔድሁ ። ቀኑ የጦም ቀን ነበር ። ብሩ ፊቱን አኮሳትሮ አየሁት ። አልተደሰተም ። የጅራፍ ድምፅ እሰማለሁ ። ጅራፉ ባንድ ጥፋተኛ ጀርባ ላይ እንደ ሽጉጥ ይጮሃል ። ጥፋተኛውም የቤት ውስጥ ሠራተኛ ወጣት (ባርያ) ሲያመልጥ ሲል ተይዞ ብሩ ዘንድ ቀርቦ 40 ጅራፍ እንዲገረፍ ተፈርዶበት ነው ። . . .ግርፋቱን የሚቆጥረው ራሱ ብሩ እያየ ነው ። . . .የተፈረደው ግርፍ እንዳለቀም ወጣቱን ከብሩ ፊት አቀረቡት ። ብሩ ከወጣቱ ጀርባ ላይ ያለው ስንጥቅጥቅ በቂ ስላልመሰለው እንደገና አስር ጅራፍ በተጨማሪ እንዲገረፍ አዘዘ ።. . . ይህም ሲያልቅ በኩርኩምና በጡጫ እየተደበደበ ከድንኳኑ ውስጥ ተባረረ ።. . .ብዙ ብዙ የጭካኔ ሥራዎችን ይሠራል ።. . .

" ነገ ጉዞ እንደሚጀመር ተነገረን ። ወዴት እንደምንሔድ ግን አልተነገረንም ። እኩለ ሌሊት ሲሆን የብሩ ሚስት በብዙ እጀብ ታጅባ ዓይነ ወጐችን ለመከላከል ፊቷን በልብስ ተሸፍና ጉዞ ጀመረች ። የእሷም ድንኳን መነቀል ለሌላው ሁሉ የጉዞውን መጀመር የሚያበስር ነበር ። ከመንጋቱ በፊት ፈታውራሪዎች ነጋሪት እያስጐሸሙ ጉዞ ጀመሩ ። ከእነሱ በኋላ ብሩ ቀጠለ ። ጓዙ በሙሉ ከተነሳ በኋላ ደጀን የሚሆነው ሠራዊት ተነሳ ። ወታደር ፣ ሴቶች ልጆች ፣ ሽማግሌዎችና በጣም ብዙ የሆኑ ከብቶች ሁሉ በአንድነት መንገዱን ይዘው ይጓዛሉ ።

"ማረፊያችን ቦታ ስንደርስ ትተነው ከመጣነው መንደር ጀምሮ እስከ አዲሱ መንደራችን ድረስ ተጓዡ የተቀጣጠለ ነበር ። እኔም ከቀዳሚው ተጓዥ ጋር ነበርኩ ። ከመንገዱ ዳር አንዲት ጥሩ ምንጭ አየሁና ለጥቂት ደቂቃዎች ቆም አልኩ ። ዓይኔን አሻግሬ ሳይ አምስት ወይም 600 የሚሆን ከጧቱ ፀሐይ ጋር እያብለጨለጨ አየሁት ።

"የብዙ በቅሎዎች ኮቴ ይሰማ ጀመር ። የነጋሪቱም ድምፅ እየቀረበኝ ሲሔድ በልዑሉ ዙሪያ የሚመታ መሆኑን አወቅሁ ። ወዲያውም ልዑሉ መጣ ። ግሩም የሆነ ሐር ቀሚስ ለብሷል ። በራሱም ላይ ሻሽ አስሯል ። ጉዞው ረጋ ያለ ነው ። ሌሎች በቅሎዎች ከፊት ይሄዳሉ ። አራቱ ተወዳጅ ፈረሶች ከኋላው ይከት



ላሉ ። ... ዙሪያውን መኳንንቶች ጀግኖችና የሚያቀርባቸው ወዳጆቹ አሉ ። አንዳንዶቹ ፈረሶቻቸውን ከራሱ እያሳቡ እነሱ በሚያማምሩ በቅሎዎች ተቀምጠዋል ። አንዳንዶቹ ደግሞ በፈረስ ሆነው ጋሻ የያዙ አሽከሮቻቸው በየበቅሎአቸው እየሆኑ ይከተሏቸዋል ። አብዛኛው ጋሻ ከብር ቡተሠራ ጌጥ ያጌጠ ነው ። ጊዜው የዓመቱ ጥሩ ወራት በመሆኑ አየሩ ግሩም ነው ። ቀኑ እጅግ በጣም ጥሩ ቀን ነበር ። ጧት ስለሆነ አልፎ አልፎ ከሳሩ ላይ ጤዛ ይታያል ። ...

"ከሠፈራችን ደረስን ። ከኛ ቀደም ብለው የደረሱት በሥራ ላይ ናቸው ። ሁሉም የጌቶቻቸውን ድንኳን ይተክላሉ ። አንዳንዶቹ ጐጆ መሥሪያ የሚሆን ሣርና እንጨት ያግዛሉ ። የእያንዳንዱ ሹም ድንኳን የብሩን ድንኳን ከብቦ ከተተከለ በኋላ እያንዳንዱ ጭፍራ ሠፈሩ የት እንደሆነ ያውቃል ። ሁሉም የየጌታውን ድንኳን የእከበበ ጐጆውን ይሠራል ። በአካባቢው ያለው እርያና አውሬ ሁሉ ይባረራል ። ለእሳት ማንደጃ የሚሆን እንጨት ይመጣል ። ከጥቂት ሰዓታት በኋላ አዲሱ ሠፈራችን ልክ እንደ አሮጌው ሠፈራችን ሆነ ።

"ሴቶችና ልጆች የያዙዋቸውን ድስቶች ምጣዶች የውሃ መቅጃ እንስራዎች ወፍጮዎችን እየያዙ ደረሱ ። ወታደሮችም እንደ ታላላቅ አዳራሽ የሚያስቡዋቸውን ጐጆአቸውን ቁርበት በማልበስ ሠሩ ። እንደ ደረስን ከልዑሉ ጋር ቁርስ በላሁ ። እንደ ተለመደው ቁርሱ ጠጅና ጥሬ ሥጋ ያለበት ነበር ። ከዚያ በኋላ የኔ ሠፈርም ሶስት ጐጆዎች ተሠርተውባት አገኘኋት ። ትልቁን ጐጆ መርጬ ያዝኩ ። አተኛና እግሬን ስዘረጋው ግን እግሬ በበሩ ከውጭ ይወጣ ነበር ። ... ማታ በየትናንሿ ሠፈራችን እሳት እያነደድን አደርን ። በነጋታው በዚያው ሁኔታ ጉዞው ተጀመረ ። ጉዞአችንም ወደ ደቡብ አቅጣጫ ነበር ። ስንጓዝ ቆይተን አባይ ወንዝ አጠገብ ካለ መንደር ሠፈር አደረግን ። ብሩ በአካባቢው ላለ የጋላ አሊቃ መልዕክተኛ ላከ ። በሳምንቱም በላሳ ፈረሰኛ አምጥተው ገበሩለት ። ... በጉዞ ላይ ትልቁ ድንኳን ከተተከለ በዚያ ቦታ ጥቂት ቀናት እንደሚቆይ ምልክት ነው ። ..."

ብሏል ።

ደጃች ብሩ ያደጉት ራስ አሊ ቤት ነው ። አባታቸው ደጃች ጐሹ ከራስ አሊ ጋር ወዳጅ ነበሩና ብሩን በልጅነታቸው ለራስ

አሊ ሰጡ ። በዚያም በጥሩ ይዞታ ተይዘው ሳለ ጉርምስና ሲሰማቸው ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት ይመኙ ጀመር ። ፕላውዲን እንደ ፃፈው በዚህ አሳባቸው "...ጓደኞቻቸው ሁሉ ይሰቁባቸው ነበር ። ..." ብሩን የራስ አሊ እናት እቴጌ መነን ይወዱዋቸው ስለነበር ወይዘሮ የውዳርን ዳሩላቸው ። የባለነጋሪቱንም አገር ነፍሴን በግዛትነት ሰጡዋቸው ።

አንድ ቀን በራስ አሊ ሠፈር ከራስ አሊ ጋር ጉግስ ሲጫወቱ ዘንግ ወርውረው ራስ አሊን በዘንጉ ወጉዋቸው ። በጉግስ ጨዋታ ደንብ በዘንግ መወጋት የሚችለው አኩያ ወይም የበታች ሲሆን እንጂ በማዕረግ የበላይ ከሆነ ወጋሁ ለማለት ዘንግን ዝቅ አድርጎ ማሳየት ነበር ። ደጃች ብሩ ግን ዘንግ ወርውረው መስፍኑን ራስ አሊን ስለወጉ ራስ አሊ ተቆጡ ። ብሩም ከቤታቸው ሔደው ታምሜአለሁ ብለው ተኙ ።

ብሩ ታምሜአለሁ ብለው የተኙት ለምክንያት ያህል ስለነበር ማታ የሚያምኑዋቸውን ጓደኞቻቸውን አሰጠርተው ሁሉም ባንድነት ለመጥፋት ተስማሙ ። 21 ዓመት ዕድሜ የነበራቸው ብሩ ሌሊቱን ከጓደኞቻቸው ጥቂቶቹ የብሩን ሚስት ይዘው በሌላ መንገድ ሲሔዱ ብሩ ደግሞ በሌላ መንገድ ወጥተው አመለጡ ። በጨረቃ እየገሰገሱ ሔደው ከግዛታቸው ነፍሴ ገቡ ። የብሩ መጥፋትና መሸፈት እንደታወቀ ራስ አሊ ሠራዊታቸውን አስከትለው ተከተሉዋቸው ። ብሩ ግን ወደ አርሞ አገር ገብተው ተደበቁ ። ራስ አሊ ሲመለሱም ብሩ ጉጃም ገብተው ለማንም የማይገብሩ የጉጃም ገገር መሆናቸውን አወጁ ።

ራስ አሊም ጉጃም ድረስ ተከትለው ሔዱ ። የራስ አሊን መምጣት ብሩ እንደሰሙ ከአባታቸው ምሽግ ሶማ እምባ ገቡ ። የራስ አሊ ሠራዊትም ሶማ እምባን ከብቦ የብሩን ሠራዊት መውጫና መግቢያ አሳጣው ። በዚህ መሀል የደጃች ብሩ አሽከር የነበሩት ጀግናው ረምሐ ከንፉ ከሶማ እምባ ወርደው ከራስ አሊ ሠራዊት ጋር ገጠሙ ። በጦርነቱም ከራስ አሊ ሠራዊት ብዙ ሰው አለቀ ። ጀግናው ረምኃ ከንፉም በዚያው በጦርነቱ ሜዳ ላይ ሞቱ ። ሬሳቸውንም የሚያነሳው ጠፍቶ በዚያው በጦርነቱ ሜዳ ላይ ስላደረ ሌሊት ሬሳቸውን ብዙ ጅብ ተሰብስቦ ሲበላው አደረ ።

ይህን የጀግናውን የረምኃ ከንፉን መሞትና በጅቦች መበላት ደጃች ብሩ ሲሰሙ አዘኑ ። እምርረውም አለቀሱ ። በገናቸውን አንስተውም እየደረደሩ (እየመቱ) በለቅሶ ዜማ ቅኔ ተቀኙላቸው ።



" ትናንት በገናው እየደረደረ
ረምኃ ከንፉ በጅማት አደረ " ብለው አንጐራጐሩ ። ቅኔው በጅብ መዓት ተበላ ለማለት ነው ። ሶማ እምባ ምሽግ ጠንክሮ የተሠራ ስለነበረ የራስ አሊ ሠራዊት አንድ ዓመት ያህል በከበባ ቆይቶ ያለምንም ውጤት ወደመጣበት ተመለሰ ። የራስ አሊ ሠራዊት እንደተመለሰ ደጃች ብሩ ከምሽጋቸው ወጥተው ሕዝቡን ግብር በማብላት ሠራዊት እየሰበሰቡ ማደራጀት ጀመሩ ። ጉልበታቸው የበለጠ እየተጠናከረም ዝናቸው ገነነ ።

ራስ አሊ ይህን የብሩ ጉሹን መጠናከርና ጉልበት ማበጀት እንደሰሙ የምርጥ መኳንንቶቻቸውን ጦር አዘው እንዲወጉዋቸው ላኩ ። በውጊያው ደጃች ብሩ አሸንፈው የራስ አሊን ሰባት መኳንንት ማረኩ ። ከእነዚህ ተማራኪዎች ውስጥ አንዱ የራስ አሊ ወንድም ነበሩ ። በዚህም በተደረገው ውጊያ ደጃች ብሩ 2000 ጠመንጃ በምርኮ ስላገኙ ጉልበታቸው የበለጠ በረታ ። የግዛት ወሰናቸውንም አባይ በመለስ አደረጉ ። ከዚህ በኋላ ካሣ ተነሱ ።

ደጃች ካሣ አልበገር ብለው ያስቸገሩዋቸውን የጉጃሙን ደጃች ብሩን ከያዙ በኋላ ጭልጋ ውስጥ ካለው አርባ ከሚባለው ቦታ በእስር አስቀመጡዋቸው ። ደጃች ብሩ አርባ እምባ ታስረው ከቆዩ በኋላ ሚስታቸው ወይዘሮ የውብዳር ከእልፍኝ አሽከሮች አንዱን መርጠው ውሽምነት ያዙ ። ይህን የእልፍኝ አሽከራቸውን ውሽምነት መያዝ ደጃች ብሩ በእስር ላይ እንዳሉ በሰሙ ጊዜ አዘኑ ፤ በገና እየመቱም አንጐራጐሩ ።

" መከራን በሰው ላይ እንዲያ ሳቀለው ፤
ምንኛ ከበደኝ እኔ ብይዘው ።
መከራ ሲመጣ አይነግርም አዋጅ ፤
ሲገሰግስ አድሮ ቀን ይጥላል እንጂ ።
ዘሃው ለበለበ ሸማኔው ተቆጣ ፤
እስተወዲያው ድረስ መጠቅለያው ታጣ ።
የኔታም አይምጡ እኔም አልመለስ ፤
ዋ ቢቾና ቀረ እስተወዲያው ድረስ ።
ከእልፍኝ ሰው አይግባ ሚስቴን ሰው አይያት አይሉም አይሉም
ፈረሴን ሰው አይጫነው ፤ በቅሎዬን ሰው አይጫነው አይሉም ፤
አይሉም ፤
ጠጁ ቀጠነብኝ ፤ ሥጋው ጐፈየብኝ አይሉም አይሉም ፤
ቀን የጣለ ለታ ፤ የጨነቀ ለታ ይደረጋል ሁሉም ።" አሉ ።

ይህን የደጃች ብሩን ኀዘንና እንጉርጉሮ አጤ ቴዎድሮስ በሰሙ ጊዜ "ሎሌዎ በድሎታል ብለዋልና ልቅጣልዎ" ብለው ለደጃች ብሩ ላኩባቸው ። ደጃች ብሩም "መንግሥትዎን ያበርክትልኝ ። ቃልዎ ደረሰኝ ። ግን የሙኩለት ሰው አለና የዚያን ቁርጥ ሳውቅ ይሁን" ብለው መለሱላቸው ። ይህን መልዕክት የያዘው አሽከር መልዕክቱን ይዞ ቴዎድሮስ ዘንድ ሳይደርስ ያን የወይዘሮ የውብዳርን ውሽማ መብረቅ ገደለው ። ደጃች ብሩም ይህን ሰምተው ተደሰቱ ። ለአጤ ቴዎድሮስም "ክርስቶስ ሰማኝ ። ፍርዱን ፈረደ ። ባላጋራዬ ሞተ" ብለው ላኩ ። ቴዎድሮስም በነገሩ ተደነቁ ።

አጤ ቴዎድሮስ የደጃች ብሩን ማዘንና በወይዘሮ የውብዳር ውሽማ ላይ የደረሰውን ተአምር አመዛዝነው ፈታችሁ አምጡልኝ ብለው አዘዙ ። ደጃች ብሩም ከታሠሩበት ተፈትተው መጥተው ከቴዎድሮስ ፊት ቀረቡ ። ከቴዎድሮስ ፊት በሚቀርቡበት ጊዜ ራሳቸውን ተከናንበው ነበር ። በዘመኑ ይደረግ እንደነበረው ይማሩኝ ለማለትም ሎሚ የምታህል ድንጋይ በትከሻቸው ላይ ይዘው ቀረቡ ። አጤ ቴዎድሮስ ይህን ሲያዩ ተቆጥተው "አሁንም ትዕቢትዎ አለቀቅዎትምሳ" አሏቸው ። ደጃች ብሩም "ክንንቡ እንደሆነ የጭልጋ በረሃ ጠጉሬን ጨርሶት ባፍር ነው" ብለው መለሱላቸው ። ቴዎድሮስም "ከበራዳው ሥፍራ ከመቅደላ ይቆዩ ። እኔ ልፈታዎ ነበር ። ነገር ግን ክርስቶስ ማቆያ የትዕቢት ምክንያት አመጣብዎ ። ፈቃዱ ሲሆን ይፈታሉ" ብለው በ1846 ዓ.ም ወደ መቅደላ ሰደዱዋቸው ።

አንድ ጊዜ እንግሊዞች ለአጤ ቴዎድሮስ ሱላድ የሚባል ጠመንጃ በስጦታ ላኩላቸው ። ቴዎድሮስ ጠመንጃውን ተቀብለው ተኩሰው ለመሞከር ሲሉ ጠመንጃው ባሩዱ በዝቶበት መጉረሱን የተመለከቱት ጳጳሱ አቡነ ሰላማ "አይሆንም ። አንተ መጀመሪያ አትተኩሰው ። በፊት በሌላ ሰው እጅ ይፈተን" አሏቸው ። አጤ ቴዎድሮስም እተኩሳለሁ ብለው ሲነሱ ጳጳሱ አትተኩስ ብለው ገዘቱዋቸው ። አጤ ቴዎድሮስም ጠመንጃውን ለጋሻ ጃግሬአቸው ሰጥተው ተኩስ አሉት ። ሲተኮስም ከባሩዱ ብዛት የተነሳ ጠመንጃው የኋልዮሽ ተራግጦ ጋሻ ጃግሬአቸውን ገደለው ። አጤ ቴዎድሮስም በጋሻ ጃግሬአቸው መሞት በጣም አዘኑ ። ለደጃች ብሩም "የምወደው አሽከሬ ሞቶብኛልና የለቅሶ ግጥም ያበርክቱልኝ" ብለው ላኩባቸው ። ደጃች ብሩም ቅን የማይናገሩ ትእቢተኛ ነበሩና ለተላከባቸው መልዕክት ሲመልሱ ፣



"አቡን ባይገዝቱ ያ ባርያ ባይኖር ፣
ያበሻ መከራ ያልቅለት ነበር ። ብለዋል ብለህ ንገርልኝ"

ብለው መለሱ ። አጤ ቴዎድሮስም "ዕድሜዬ ይፍታዎ ። ራስዎ ጐዱት እንጂ እኔን አልጐዱኝም" ብለው ላኩባቸው ።

ደጃች ብሩ በመቅደላ እንደታሠሩ እስከ ቴዎድሮስ ዕድሜ ማለቅ ድረስ 14 ዓመት ቆይተው የእንግሊዝ ጦር የመቅደላን እስረኞች በፈታበት ጊዜ ተለቀቁ ። ማርከሃም ስለ መለቀቃቸው ሲጽፍ "... ከታሠረበት ሲፈታ አጐንብሶ እጅ ነሳ ። ... ወዲያውንም ፈጥኖ ወደ አገሩ ሔደ ። ..." ይላል ። ለቴዎድሮስ አጐንብሰው እጅ ነስተው ቢሆን ኖሮ 14 ዓመት የእስራት ምርቃት (ተጨማሪ) አያገኙም ነበር ።

ደጃች ብሩ በሥልጣን ላይ በነበሩ ጊዜ ሚስታቸው ወይዘሮ የውብዳር ቤተ ክርስቲያን በሚሰሙበት ቀን ከቤተ ክርስቲያን ቀድሞ ሰው የገባ እንደሆነ ያ ሰው ተደብድቦ ይወጣ ነበር ። ለዚህም ነው በበገና ያንጐራጐሩ ጊዜ "ከእልፍኝ ሰው አይግባ ፣ ሚስቴንም ሰው አይያት አይሉም አይሉም" ያሉት ።

ደጃች ብሩ በሥልጣናቸው ዘመን ሕዝብ አይወዳቸውም ነበር ። በሚሠሩት ግፍ ምክንያት የጐጃም ሕዝብ እንዳለቀሰ ነበር የሚኖረው ። አለቃ ተክለ ኢየሱስ እንደጻፉት ብዙ ግፍ የሠሩ ሰው ናቸው ። አንድ ጊዜ በምሽጋቸው በሶማ አምባ ምስጥ አስቸገረ ። "ጉንዳን ቢኖር ኖሮ ምስጥ አይኖርም ነበር" የሚል ወሬ ደጃች ብሩ ሲሰሙ በደረቤ ሕዝብ ላይ የጉንዳን ግብር ጣሉበት ። በየወረዳው ያለው የደረቤ ሕዝብ አስር እንስራ ጉንዳን እንዲያመጣ ብለው አዋጅ አስነገሩ ። ይህ አዋጅ የተነገረበት የደረቤ ሕዝብም በሥጋ ላይ ጉንዳን እየሰበሰበ በእንስራ ሲከት ከረመ ። እንስራው ሲሞላም በቅጠል እየወተፈ በትከሻው እየተሸከመ ባላገሩ ወደ ሶማ ይጓዝ ጀመር ። ጉንዳንም ከእንስራው ውስጥ እያፈተለከ እየወጣ ተሸካሚውን እየነከሰ ቢያስቸግርም የባሰ ቅጣት የሚመጣበት ባላገር እንደምንም እያለ ሶማ አደረሰ ።

ባለገሩም "ከመከራው ሁሉ የጉንዳኑ ባሰ ፣
የተሸካሚውን ጀሮ ፣ እየተናከሰ" አለ ።

አንድ ጊዜ ደግሞ የደጃች ብሩ በቅሎዎች በሆድ ቁርጠት በሽታ እየታመሙ በሠፈር የበቅሎ በሽታ ገባ ። "ለዚህ ለበቅሎ የሆድ ቁርጠት መድኃኒት የሴት ብልት ጠጉር ነው" ብለው ለደ

ጃች ብሩ ነገሩዋቸው ። ደጃች ብሩም “ እምቢቶ ሙቶ ጉንዲ የቤት ብልት ጠጉር እግባ ” ብለው በግዛታቸው ሁሉ አዋጅ አስነገሩ ። ባላገር የቤት ብልት ጠጉር ከቤቱ እያሰባሰበ ከርሞ ሚዛን አልሞላ ቢለው የራሱን ጠጉር እየላጨ ሚዛን እየሞላ ይወስድ ጀመር ። የቤት ብልት ጠጉር ግብር ተቀባዮችም “ ይሄ የራስ ጠጉር ነው አንቀበልም ። የቤት ብልት ጠጉር አምጣና ሙላ ” እያሉ ድሃውን አስለቀሱት ። ድሃውም ጠጉር ስለማይገኝለት ገንዘብ እየሰጠ ያመልጥ ጀመር ። በዚያን ዘመን ቤት ዘመድ የሌለው ተቸግሮ እንደነበረ አለቃ ተክለ ኢየሱስ ጽፈዋል ።

አንድ ጊዜ ደግሞ ደጃች ካሣ ወደ ጐጃም ለመዝመት ማበባቸው እንደተሰማ ደጃች ብሩ የቦማን ምሽግ እያጠናከሩ ያሠሩ ጀመር ። ለምሽጉ መሥሪያ የሚሆን ግንድ ሕዝቡ ወደተራራው ሲያግዝ አንዱን ትልቅ ግንድ ስለላ ሰዎች ሆነው በሕብረት ተሸክመው ወደተራራው ሲወጡ ከጠባብና ከዘወርዋራ ቦታ ደረሱ ። ያቺንም ቦታ ለማለፍ ሲሞክሩ ግንዱ ወደ አንድ በኩል አዘንብሎ ስለላውን ተሸካሚ ይዞ ገደል ገባ ። ተሸካሚዎቹም በሙሉ ሞቱ ። ይህን ነገር ቆመው ይመለከቱ የነበሩት ደጃች ብሩ የሰዎቹን በሙሉ መሞት ሲሰሙ “ ገበሬ ምንኛ የሚዋደድ ነው ፤ በአንድነት ወርዶ አለቀ ወይ ” ብለው ቀለዱባቸው ።


## ውቤ

ደጃች ውቤ የበሜኑ የራስ ገብርዬ የልጅ ልጅ ናቸው ። አባታቸው ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ይባላሉ ። ደጃች ውቤ በካሣ ሠራዊት ድል ሆነው እስከ ተያዙበት ድረስ ለ24 ዓመት ያህል ትግራይን በመልካም ሁኔታ አስተዳድረዋል ። ደጃች ውቤ በቴዎድሮስ እጅ ለብዙ ዘመናት ከታሠሩ በኋላ በ1859 ዓ.ም ሞቱ ። የደጃች ውቤ ሁለት ልጆችም መቅደላ ላይ በቴዎድሮስ ታስረው ስለነበረ እንግሊዞች ድል አድርገው በገቡ ጊዜ ፈትተው በነፃ ለቀቁዋቸው ። ውቤ ለብዙ ዘመን በቴዎድሮስ ታስረው የቆዩት ፣ ልጃቸው እቴጌ ጥሩነሽ የአጤ ቴዎድሮስ ሚስት ሆነው ነው ።

ደጃች ውቤ በዘመናቸው ሰፊ ግዛት የነበራቸው ታላቅ ሰው ነበሩ ። ግዛታቸውም ከጐንደር አካባቢ ከወልቃይት ጀምሮ ቀይ ባህር ድረስ ነበር ። በኋላ በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል የሆነው ፕላውዴን ስለደጃች ውቤ በጻፈው ታሪክ ስለግዛታቸው ሰፊነት ሲገልጽ “. . . ከላስታ እስከ ሸንቅላ ወደ ግብጽ ግዛትም እስከ ሲናር ይደርሳል. . .” ይልና “ . . . የውቤ ጦር አዛዥ በአካለ ጉዛይና በሀማሴን ተራራዎች ላይ ሲጓዙ የሠራዊቱ ብዛት ጥቁር ደመና ያለበት ይመስላል ። . . .እኝህ ታላቅ ሰው ደጃች ውቤ 40.000 የጦር ወታደር አላቸው ። ከእነዚህም 8.000 ባለጠመንጃና 4.000 ፈረሰኞች ናቸው ። ውቤ ለራስ አሊ በያመቱ 8.000 ብር ይገብራሉ. . . ” ብሏል ።

ስለ ደጃች ውቤ ደግነት ሲጽፍም “ . . የውቤ እጅ ቸር ስለሆነ በባልደረባ እማካይነት ለማንኛውም እንግዳ ብዙ ነገር ይደረግለታል ።. . በቀን ሙቶ እንግዳ ቢመጣም ለሁሉም ባልደረባ ተበጥጦ ድርጐ ይታዘዝለታል ። . . . ለኔም አንድ ሠንጋ ፣ እንጀራ ፣ ጠጅ ፣ ጠላ ፣ የሚነድ እንጨት ፣ ለበቅሎ ሣርና ምግብ ታዞልኝ ይህንንም የሚያዘጋጁ ሠራተኞች ጭምር ወዲያው ተሰጡኝ ። . . . እኔም እምነ ነፀርፕ እንደኛይቱ ወጥ ሠሪ መታመሜን ለጌታዋ ነገረች በአበሾች ባሕል አንድ የማይበላና የማይጠጣ ሰው ሊሞት የተቃረበ በሽተኛ ነው ብለው ያምናሉ ። በነጋታው በማለዳ ጌትዮው ብዙ ነገሮችንና ለእራሳቸው የተዘጋጀላቸውን ብርዝ ላኩልኝና “በሞቴ ፣ ይህቺን ጠጣልኝ ብለውሃል” አለኝ ። እኔም በመከበሬ ደስ ብሎኝ ጠጣሁ ወዲያውኑም ሻል አለኝ ። በሶስተኛው ቀን ውቤ ሊያዩኝ እንደሚፈልጉ ተነገረኝ ። አልጠናሁም ። ተቅማጡም ቢሆን አልቆመልኝም ። ለባብሼ ወደ ግቢ ሔድሁ ። ግቢው ትልቅ ነው ። እሥር ሜማ ያህል ከፍታ ባለው ግንብ ተከቧል ። አንዳንድ ክፍል ብቻ ብዙ የሆኑ ቤቶች አሉ ። ግማሹ በግንብ የተሠራ ሲሆን ግማሹ ደግሞ በእንጨት የተሠራ ነው ። ቤቶቹ ሁሉ ክዳናቸው ሣር ነው ። . . . . ይህን ሁሉ አልፌ ውቤ ካሉበት ክፍል ገባሁ ። ጭር ብሏል ። . . . . ጥቂት ሰዎች ቆመዋል ። ሁለት ሽማግሌዎች ተቀምጠዋል ። አማካሪዎች ናቸው ። እንደገባሁ ከውቤ አልጋ አጠገብ ካለ ምንጣፍ ላይ ተቀመጥሁ ። እሳቸውም ሐር ጨርቅ የተሸፈኑ ሁለት መከዳዎች መሀል ተቀምጠዋል ። ሁለት አለቆች ከአልጋው ራስጌና ግርጌ ቆመው በጭራ ዝንቦች እንዳይጠጉዋቸው ይከላከላሉ ። በከፍሉ መሀል ባለው ትልቅ ምድጃ እሳት ይነዳል ። ክፍሉም በለምለም ሣር ጉዝጓዝ ተጐዝጉዟል ።

“ . . . . ደጃዝማች ውቤ የተከበሩት ጦረኛ የኃይለማርያም ልጅ ናቸው ። . . . . አባታቸው የሞቱ ጊዜ ሕፃን ነበሩ ። በዚያን ጊዜም አባታቸው ከትግራይ ገዦዎች ያስለቀቁትን ወልቃይትን ይገዙ



ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ (በግራ) ደጃች ውቤ (በቀኝ)

ነበር ። አባትየው ሲሞቱ ወንበራቸውን (ሥልጣናቸውን) ለትልቁ ልጃቸው ተናዘው ነበር ።

"ውቤ ወደ ጉርምስናው ሲደርሱ ሞግዚታቸው ማጂ ወልደ ኪዳን በወንድማቸው ላይ እንዲያምፁ ገፋፋዋቸው ። ከዚያም ውቤ ያሏቸውን አሽከሮች አስከትለው ሌትና ቀን እየገሰገሱ ሔደው ከእኙሁ ከአሳዳጊያቸውና ረዳሃለሁ ካሏቸው ከማጂ ወልደ ኪዳን ጋር ተደባለቁ ። በማግስቱም ወደ ወንድማቸው ሠፈር ሔደው በጥቂት ተከታዮች ያለምንም ተከላካይ ወንድማቸውን ይዘው የአባታቸው ወራሽ መሆናቸውን በአዋጅ አሳወቁ ። ታላቅ ወንድምየው ደካማና የዋህ ቢጤ ስለነበሩ ሥልጣናቸውን በሰላም ለቀቁላቸው ። ውቤም ታላቅ ወንድማቸውን ሳያስሩ በሰላም አብሮ ለመኖር በነፃ ለቀቁዋቸው ።

"ውቤ ሥልጣን እንደያዙ የጠለምቱ ባላባት ሸፈተ ባቸው ። ይህም ሰው ጥሩ ወታደሮችና አንድ ሺ ያህል ጠመንጃ ያለው ነበር ። ጥቂት ፈረሰኞችም አሉት ። ሰባት ነጋሪት እያ ስጐሸመ ታላቅ መሪ መሆኑን አሳወቀ ። ውቤ ያላቸው ኃይል 16 ጠመንጃ ዎችና ሶስት ፈረሰኞች ብቻ ነበሩ ። በዚያችው ኃይላቸው የተነሳባ




ቸውን ሽፍታ ለመግጠም ሲሉ ማጂ ወልደ ኪዳን በቅድሚያ ሰዎችን መሰብሰብና ጥሩ ወታደሮችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል ብለው መከሩ ። ውቤም የአባቴን አገር ከመልቀቅ መሞት ይሻለኛል ብለው ጥቂት ሠራዊት ይዘው ዘመቱ ። በጦርነቱም ድል አድርገው ብዙ ወታደሮች ገድለው ነጋሪቶቹንና ብዙ ጠመንጃ ማረኩ ። የሸፈቱባቸውንም ማርከው በሰንሰለት አሰረው የአባታቸው ታማኝ አሽከሮች ወዳሉበት ተራራ እንዲጠበቅ ላኩት ።

" . . . በወጣትነት ዘመናቸው ሀብትና የጦር መሣሪያ በዛላቸው ። የወታደሮቻቸውን ጥራትና ጉልበት ካረጋገጡ በኋላ ሌላ ዘዴ ይወጥኑ ጀመር ። ራስ ይማምን ወግተው ጋላን አስገበሩ ። ከዚያ ተመልሰው የንጉሱን መሞት እንደሰሙ ራሳቸውን ነፃ አድርገው አወጁ ። ከራስ ማርዬ ጋር ሾዳ ላይ ጦርነት ገጥመው ድል ሆነው ወደ ሰሜን ሸሹ ። ታላቁና ጀግናው የጋላ ተወላጅ ራስ ማርዬም ከውቤ ጋር በጦር ሳይሆን በሰላም አብረው ለመኖር አስበው ከታረቁ በኋላ አማች አደረጉዋቸው ።

" . . . ውቤ ከቋራው ገዥ ከደጃች ከንፉ ጋር ቁርቋሶ ጀመሩ ። ከንፉ አበሻን ሊወር የመጣውን ቱርክ አሸንፈው በመመለሳቸው በግብጽ ውስጥ ታላቅ ዝና ያላቸው ሰው ናቸው ። በዚያም ጦርነት የሚረኩት ብዙ ጠመንጃ ስላላቸው ጦራቸው የጠነከረ ነው ። ውቤ ከከንፉ ጋር ለመግጠም በሚያስቡበት ጊዜ ደጃች (ራስ) ማርዬ የሰሜንን አውራጃ በመዝረፍና በማቃጠል ያስቸገሩትን ገዥ ደጃዝማች ሰባጋዲስን ሊወጉ ተነሱ ። እሳቸውም ከሸዋ ወሰን በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የጋላ ፈረሰኛ ሰብስበው በውቤ መሪነት ዝነኛውን አስቸጋሪ መንገድ የሊማሊሞን ተራራ አልፈው በትግራይ ውስጥ መዝረፍና ቤት ማቃጠል ጀመሩ ።. . .በመንገዳቸው ላይ አንድም የሚያቆማቸው ሳያጋጥማቸው ተከዜን አቋርጠው ተሻገሩ ። ማይ ስላን ሲደርሱ የካቲት 7 ቀን 1823 ዓ.ም. በአበሻ ምድር የተደነቀ ታላቅ ጦርነት ተደርጐ ራስ ማርዬ ሞቱ ። ራስ ማርዬ የተገደሉት በሰባጋዲስ ልጅ በደጃች ሐጐስ ነው ። ደጃች ሐጐስም ተማረኩ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ተገደሉ ። ጌታው የተገደሉበት የጋላ ጦርም ተበረታትቶ በመዋጋቱ ድል አግኝቶ ሰባጋዲስን ማረከ ። በማግስቱ በደጃች ውቤ ትእዛዝ የራስ ማርዬን ደም ለመበቀል ተብሎ ተገደሉ ። ውቤም በትግራይ ላይ ራስ ዶሪን ሾሙ ።

". . . . .ደጃች ውቤ የትግራይን ግዛት ለማደላደል አስበው ደፊት ቢገፉም የሸፈቱት የሰባጋዲስ ልጆች ኃይላቸውን አጠናክ

ረው መስሉዋቸው ። ውቤም ወደ ሰሜን ተመልሰው ኃይላቸውን በደንብ ካደራጁ በኋላ እንደገና ወደ ትግራይ ዘመቱ ። በዚያም በእገዛ ሽማግሌዎች ከሰባጋዲስ ልጆች ጋር ታርቀው ሰላም ከወረደ በኋላ ውቤ የሰባጋዲስን ልጅ ካሣይን በትግራይ ላይ ሾሙ ።ካሣይ ግን ከዳቸው ። ውቤም ጦራቸውን ሰብስበው ፈረስ ማይ ከተባለ ቦታ ከካሣይ ሠራዊት ጋር ተዋግተው ድል አደረጉ ። ካሣይ ግን አምልጠው ከተራራ ወጥተው መሸጉ ። ውቤም የተራራውን ዙሪያ አስከብበው ውጊያ ገጠሙና ድል አድርገው ካሣይን ማረኩ ። ከዚህ በኋላም የትግራይ ባላባቶች በጠቅላላው ገበሩላቸው ።. . .



የላስታ መንደር

“ ውቤ ትግራይን በንቡረ ዕድ ወልዱ ሥላሴ እንዲተዳደር አድርገው አዲስ ያስመጡዋቸውን ጳጳስ አቡነ ሰላማን ይዘው ወደ በጌምድር ተመለሱ ። በጌምድርም እንደገቡ በራስ አሊ ላይ መሸፈታቸውን በአዋጅ አሳወቁ ። በአዋጃቸውም “ . . . የጐንደርን ነገሥታት ማዕረግ ሳላፋልስ እገዛለሁ ።. . . .ራስ አሊ በልባቸው የእስልምናን እምነት ያልተው በመሆናቸው ሃይማኖታችንን እያበጣበጡና ኢያበላሹ ናቸው ።. . . ” ብለው አሳወጁ ። ይህም የደጃች ውቤ አዋጅ በሕዝብ ዘንድ የታወቀ ትክክለኛ ነገር በመሆኑ ብዙ



ደጋፊ አገኙ ። አቡነ ሰላማም ይህንኑ አዋጅ አጠናከረው ገዘቱ ። . . . .” በማለት ጽፈዋል ።

ደጃች ውቤ የራስ አሊን ከተማ ደብረ ታቦርን ለመውረር ተጓዙ ። ራስ አሊ ጐጃም ውስጥ ነበሩና የውቤን መዝመት እንደ ሰሙ ሠራዊታቸውን አሰባስበው በግስጋሴ ደብረ ታቦር ደረሱ ። እንደ ደረሱም በጢት ጦርነት ተጋጥመው ሲዋጉ የውቤ ሠራዊት ብዙ ነበርና ጦርነቱ ብዙም ሳይቆይ ወደ ረፋዱ ገደማ አለቀ ። በጦርነቱ ድል የሆኑት ራስ አሊም ሸሽተው ወሎ ውስጥ ወረሂመኑ ገቡ ።

በጦርነቱ ድል ያገኙት ደጃች ውቤም ድል በማድረጋቸው ተደስተው ከድንኳናቸው ገብተው መዝናናት ሲጀምሩ ብሩ አሊጋዝ የተባለ የራስ አሊ ሰው በግርግሩ መሀል ባይታወቅ ከጥቂት ወታደሮች ጋር ከደጃች ውቤ ድንኳን ገባ ። በድንኳኑም ውስጥ ጳጳሱና መኳንንቶቹ ከደጃች ውቤ ጋር ሲጫዋወቱ ብሩ አሊጋዝ በድንገት ደርሶ ሁሉንም ማረካቸው ። በጦርነቱ የተማረኩትን የራስ አሊን ሠራዊትም አስለቀቀ ። ዙሪያውንም ላስደፈጣቸው አሽከሮቹ ድሉ የራስ አሊ መሆኑን አስለፈፈ ።

ብሩ አሊጋዝ የማረካቸውን ደጃች ውቤን ጳጳሱንና መኳንንቱን ይዞ ለራስ አሊ ለማቅረብ ራስ አሊን ቢፈልግ አጣቸው ። ወረሂመኑ መግባታቸውንም ሰማ ። መልክተኛም ልኮ ከወረሂመኑ ራስ አሊን አስመጥቶ በሸሹ በሰባተኛው ቀን እንደገና ለዙፋናቸው አበቃቸው ። ውቤና አሊም በእርቅ ተለያዩ ። ይህ ጦርነት በተደረገ ጊዜ አንድ ባላገር በጦር ሜዳ የዋለ ወታደር አግኝቶ “ ጦርነቱ እንዴት ሆነ ” ብሎ ጠየቀው ። ወታደሩም “ ራስ አሊ ድል ሆነው ሸሹ ። ደጃች ውቤም ተማረኩ ” አለው ። ባላገሩም ግራ ገብቶት “ እረ ተው በወግ በወግ አርገህ አውጋኝ” ቢለው “እነሱ በወግ ያላደረጉትን እኔ እንዴት ላድርገው ” አለው ።


ጥላውዲን ስለደጃዝማች ውቤ ጠባይና ሁኔታ ሲገልጽ “. . . ዝምተኛና ጨዋ ሰው ናቸው ። ተፈሪነትም አላቸው ።. . . .በሥራቸው ፈጣን ናቸው ። ወሳኝና ቆራጥ ናቸው ። አጭር መልስ የሚወዱ ረጅም ደብዳቤ የማይወዱ. . . ናቸው ። ለጠላቶቻቸው የማይተኙ ወዳጆቻቸውን የሚያጠቁ ናቸው ።. . . እንዴ የሚናገሩት እንዲጸና ይፈልጋሉ ። ትንሽም ጥፋት ብትሆን ይቅርታ የማያደርጉ ናቸው ።. . .በጦር ሜዳ ጥሩ የጦር መሪ እንጂ ጥሩ ተዋጊ አይደ

ሎም ። ፈጣንና ሳይታሰብ አዋቂ ናቸው ።. . . ቁመናቸው አጭር ፣ ከንፈራቸው ስስ ሲሆን ድምፃቸው አስፈሪ ነው ። ፈጣንና የንግግር ተሰጥኦ ያላቸው ናቸው ።. . .አፍንጫቸው ቀጥ ያለ ነው ።. . . .” ብሏል ።

ፖርኪንስ ደግሞ “. . . ወደ ታላቁ አስደናቂው የውቤ አዳራሽ ገባን ። ቤቱ ዙርያ ክብ ነው ። መሀል ለመሀል ሲለካም 30 ጫማ ያሀል ይሆናል ። በመሀል በትልቅ ምድጃ እሳት ይነዳል ። የመሬቱን መጥፎነት ለመሸፈን ከዳር እስከዳር ሣር ተጐዝጉዟል ። . . . . ወደ ቤቱ ውስጥ ብርሃን የሚገባው በበርዋ ብቻ ነው ።. . ውቤ እንዴት ናችሁ ብለው ጠየቁን ። መልሱም እጅ መንሳት ነበር ። እንድንቀመጥ ስለነገሩን ሁላችንም መሬት ላይ ተቀመጥን ። በቤቱ ውስጥ እሳቸው ከተቀመጡበት መቀመጫ በስተቀር ሌላ የለም ።. . . የተቀመጥኩበት ቦታ እንጨት ከሚነድበት ከእሳቸው ምድጃ አጠገብ ነው ። ከምድጃው አንድ ያርድ ያህል ብንርቅ ነው ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በጭሱ ምክንያት ዓይኔ ውሃ ያመነጭ ጀመር ሊያሳውረኝም ደረሰ ።. . . ዓይኔ ቀልቶ እምባዬ ሲፈስ ውቤ አይተው ይስቁብኝ ጀመር ።. . .ውቤ የተቀመጠበት የሲምርና (ቱርክ ውስጥ) ምንጣፍ በተነጠፈበት አልጋ ላይ ነው ። በተኾረጐረጐ ጨርቅ የተሸፈኑ ሁለት መከዳዎች በመቀመጫቸው ላይ አሉ ።

“. . .ውቤ ቀጭንና መልከ መልካም ናቸው ። ዕድሜአቸውም 45 ዓመት ያህል ነው ። ጠጉራቸው ጥቅጥቅ ያለ ነው ። አልፎ አልፎ ነጫጭ ጠጉር ጣል ጣል አድርጐበታል ።. . . ” ይልና አንድ ጊዜ ደጃች ውቤ ሞቱ ተብሎ ስለተነገረው ሁኔታ ሲገልጽ “. . . ውቤ ሞቱ የተባለ ጊዜ በቦታቸው ሰው እስኪ መረጥ ድረስ መሞታቸው ምስጢር ነው ተባለ ። በኋላ ግን ነገሩ ከወታደሮቻቸው ዘንዶ በመድረሱ ውቤ ጨዳኝ ገኸ ነበሩና ወታደሩ ሁሉ በመሞታቸው ተደስቶ ይሳሳም ጀመር ። ግማሹም ወታደር የውቤን ወራሽ እንቀበልም እያለ በሐውዜን ምድር ክርክሩ ተሟሟቀ ። . . .ወታደሩ ሌላ ለመሾም በሚዘጋጅበት ጊዜ ለካስ ውቤ ሞቻለሁ ያሉት ሕዝቡን ለመሰለል ኖሮ ሳይታሰብ በድንገት ከድንኳናቸው ውስጥ ተቀምጠው ታዩ ። እንዲያውም ከተለመደው የተሻለ ጤናማ ሆነው ተገኙ ። ወዲያውም በየገበያው አዋጅ እንዲነገር አዘዙ ።. . . . ” በማለት ጽፈዋል ።





የእንጣሎ ገበያ

ደጃች ውቤ አስደናቂም አስቂኝም ታሪክ ያላቸው ሰው ናቸ ፖርኪንስ ስለደጃች ውቤ የሰማውንና ያየውን አንዳንድ ታሪ ጽፏል ። እነኛንም ታሪኮች በቀጥታ ትርጉም ሳይሆን ባጫጭ ለአንባቢያን ለማቅረብ ፈለግሁ ።

ሁለት ልጆች የሾላ ፍሬ ለመብላት መንደራቸው ውስጥ ካ የሾላ ዛፍ ዘንድ ሔዱ ። አንዱ ዕድሜው አምስት ዓመት ሲሀ ትልቅዬው ደግሞ ስምንት ዓመቱ ነው ። ከሾላው ዛፍ ዘንድ እን ደረሱ ትልቅዬው ልጅ ከዛፉ ላይ ወጥቶ ለራሱም የሾላውን ፍ እየበላ ከታች ለሚጠብቀው ጓደኛውም ፍሬ ይጥልለታል ። የበሳሰ ፍሬዎችን እያየ እነኚያን ለመልቀም ትልቅየው ልጅ በዛፉ ላ ከፍ እያለ ወጣ ። ከአንድ ቦታ ሲደርስ አዳልጦት ከዛፉ ላይ አሽ ልቁሎ ወርዶ ከሥሩ ካለው ልጅ እናት ላይ ወደቀበት ። ያም ከሥ የነበረ የአምስት ዓመት ልጅ ወዲያው ሞተ ። ከዛፉ ላይ የወደቀ ግን ደህና ነበርና ጓደኛውን ቢያጋላብጠውም ቢያናግረው መልስ የማይሰጠው ሆነ ይህም የተረፈ ልጅ ደንግጦ ወደቤቱ እ ሮጠ ሔደና ሁታውን ለእናቱ ተናገረ ።

የሁለቱ ልጆች ወላጆች ተካሰው ውቤ ዘንድ ቀረቡ ። በመጨረሻው ልጁ ልጇን የገደለው አውቆ ሳይሆን በአጋጣሚ ሲጫወቱ ነውና የሟች ወገኖች የደም ዋጋ (ወጆ) ተቀብሉና ተለያዩ ቢባሉ የሟች እናት ልጇን እንደገደለ ይህም ልጅ ይገደልልኝ እንጅ የደም ዋጋ አልቀበልም ብለው እምቢ አሉ ። በዚያን ጊዜ የነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ፍርድ "ገዳይ በገደለበት ሁኔታ ይገደል" የሚል ስለነበር ደጃች ውቤ ሲፈርዱ "....እንግዲያውስ የሟች ወንድም ሰባለ ገዳዩ ከዛፉ ሥር ይቁምለትና ወንድምየው ከዛፉ ላይ ወጥቶ ተወርውሮ ከገዳዩ ላይ ይውደቅበትና ይግደለው" ብለው ፈረዱ ። በዚህ ጊዜ የሟች እናት "የቀረኝ አንድ ልጅ ነው ። ይህ ይገደል የተባለው ልጅ ከዛፉ ላይ ተወርውሮ በሚወርድበት ጊዜ ከመሬት ያረፈ እንደሆነ ይሞትብኛል ። ወይም ይሰባበርብኛልና ይቅርብኝ" ብለው ያለምንም ግድያ በሰላም ተለያዩ ።

አንድ ቀን ደግሞ አንዲት አሮጊት ከዳጃች ውቤ ድንኳን ፊት ለፊት ሆነው ጮሁ ። ደጃች ውቤም አቅርቧት ብለው አዘዙ ። እሮጊቷ ከደጃች ውቤ ዘንድ እንደቀረቡ "ልጄ ሻንቅላ አገር ዘምቶ በነበረ ጊዜ አንድ የእርስዎ ወታደር የገዛ ጓደኛው የሆነ ገደለው ። ይህም የልጄ ገዳይ የእርስዎ ወታደር ሻንቅላ የገደለ አስመስሎ ግዳይ ጥሎ ስለፎከረ ተሸለመ ። አሁን የልጄን ደም ይመጡልኝ ።" ብለው አመለከቱ ። ውቤም ያስመስክሩ አሉዋቸው ። አሮጊቷም ወሬውን የነገሩዋቸውን ከልጃቸው ጋር አብረው የዘመቱትን ወታደሮች አቅርበው ተመሰከረላቸው ።

ደጃች ውቤ የምስክሮቹን ቃል አዳምጠው ከጨረሱ በኋላ "ነገርዎ ያሳዝናል ። የልጅዎን ደም ለመበቀል እርስዎ አርጅተዋል ። ፍርዱ ደግሞ ገዳይ እንደገደለበት ይገደል ነው የሚለው ። እርስዎ ሌላ ልጅ ወይም ዘመድ የለዎትም ። እንደሰማሁትም ልጅዎ ከሞተ ወዲህ የሚረዳዎ ሰው እንኳን አላገኙም ። የልጅዎን የደም ዋጋ (ወጆ) ይቀበሉ ። 150 ብር አስከፍልዎታለሁና ይጠቅምዎታል ። ይህም ገንዘብ እስከ ዕድሜ ልክዎ መጦርያ ይሆንዎታል ።" አሏቸው ። ሴትዮዋም "መጥቀምስ ይጠቅመኛል ። ልጄ ከመሞቱ በፊት በሕይወት እያለ ሲያበላኝ ኖረ ። ከሞተ በኋላ ደግሞ ደሙን አልበላምና የልጄ ገዳይ ይገደልልኝ" ብለው አመለከቱ ። ደጃች ውቤም "ነገርዎ ትክክል ነው ። እርስዎ በዚህ አገር ዘመድ የለዎትም ። ማን ይገድልልዎታል ? እርስዎ መግደል ይች



ላሉ ?" ብለው ጠየቋቸው ። ሴትዮዋም "እኔ መግደል ባልችል እግዚአብሔር የልጄን ደም የሚበቀልልኝ ይሰጠኛልና ይፈረድልኝ" አሉ ። ይሙት በቃ ተፈረደላቸው ። ሴትዮዋም ከሠፈራቸው የሁለት ቀን መንገድ ተጉዘው የተቋጥር ዘመድ አምጥተው የልጃቸውን ገዳይ በባት ቦታ በጦር እያስወጉ አስቆስለው በመጨረሻ በጥይት አስገደሉት ።

አንድ ሰው 19 ዓመት ዕድሜ ያለውን አሽከሩን ጋሻውን አስይዞና አስከትሎት ወደ ሜካ ሔዱ ። ሰውዬው ጦር ሜዳ ውሎ እያውቅም ። በጦር ሜዳ ባለመግደሉም ገዳይ ከሆኑት ጓደኞቹ ሁሉ ክብሩ ያነስ ነው ። ከአሽከሩ ጋር በሜካው ውስጥ ሲሔዱ ድንገት ዞር ብሎ በያዘው ጦር አሽከሩን ወጋው ። አሽከሩም ቆስሎ እንደ ወደቀ "ጌታዬ ከልጅነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በታማኝነት አገልግያለሁ ። ሰባት ዓመት ሙሉ ሳገለግልዎትም አንድም ደሞዝ ተከፍሎኝ እያውቅም ። እኔም አልጠየቅዎትም ። ይሄን ያህል ዓመት በታማኝነት አገልግዬ አሁን ምን ባጠፋሁ ይገድሉኛል ?" አለ ። ጌትዬውም "ያልከው ሁሉ እውነት ነው ። እንዳልከውም በታማኝነት አገልግለሽኛል ። ሰባት ዓመት ማገልገልህንም ምን ጊዜም አልረሳውም ። አሁን ደግሞ በሞትህም ምናልባት ደግሞ ሰባት ሹመት አሾምብህ ይሆናል ።" ብሎ አሽከሩን በጦር ደጋግሞ ወግቶት ጥሎት ሔደ ።

ከሠፈር ገብቶም በሜካ ውስጥ ሽፍቶች እንዳጋጠሙት ፣ከእነኛ ሽፍቶች ጋርም ሲከላከል አሽከሩን እንደገደሉበት ፣ እሱም ከሽፍቶቹ አንዱን እንደገደለና ሌሎች ግን ሸሽተው እንዳመለጡት አድርጐ ለጓደኞቹ አወራ ። ጓደኞቹም ፈሪ መሆኑን ያውቃሉና የነገራቸውን እናምንም ብለው "ይህን ያደረግህበትን ቦታ ውሰድና አሳየን" አሉት ። እሱም "ቦታው ሩቅ ነው ። ምናልባትም ደግሞ እንኝያ ሸሽተው የሔዱት ሽፍቶች የጓደኛቸውን ሬሳ ለማንሳት ሲመጡ ድንገት የተገናኘን እንደሆነ ጦርነት ይነሳል" ብሎ አልሔድም አለ ። ሌሎቹ ሲቀሩ የሟች አሽከር ጓደኞች የሆኑ ጥቂት ሰዎች የእግር ፈለግ እየተከተሉ ከሜካው ውስጥ ገብተው የሟቹን ጓደኛቸውን ሬሳ ይፈልጉ ጀመር ። ተለያይተው በሜካው ውስጥ ሲፈልጉ አንደኛው የሚያቃስት ድምጽ ሰማ ። ቢሔድ ጓደኛቸው አልሞተ ኖሮ ሲያቃስት አገኘው ። ሌሎች ፈላጊ ጓደኞቹን ጠርቶ ያን የቆሰለ ጓደኛቸውን ተሸክመው ከደጃች ውቤ ዘንድ ሔዱ ። ደጃች ውቤም ጉዳዩ ፈጽሞ እንዳይወራና ማንም እንዳይ

ሰማ አስጠንቅቀው ቁስለኛው በሚገባ ታክሞና ተመግቦ እንዲድን
አዘዙ ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ልጁ ቁስሎቹን ዳነ ፡፡

ደጃች ውቤ ታላቅ ግብር አስደግሰው ለጀግኖች የሚሰጡ
ሽልማቶች አዘጋጅተው ወታደር ሁሉ ለግብር ተጠራ ፡፡ ጀብዱ
የሠራ ወታደር ሁሉ ከውቤ ፊት እየቀረበ እየፎከረና ግዳዩን እያስ
መሰከረ ይሸለም ጀመር ፡፡ ያም አሽከሩን ያቆሰለ ሰው ከደጃች
ውቤ ፊት ቀርቦ ታሪኩን እየዘረዘረ እንዴት እንደገደለና እነሱም
አሽከሩን እንደገደሉበት ዘርዝሮ ተናግሮ ፎከረና ሲያበቃ እጅ
ነሳ ፡፡ ደጃች ውቤ ያንን ከቁስሉ የዳነ ልጅ አጠገባቸው ካለ መጋ
ረጃ ኋላ ደብቀው ከመጋረጃው ውጭ ሽልማቶችን አስቀምጠው
ከዚያ እያነሱ ነበር የሚሸልሙት ፡፡ ሽልማቱም ከእነስተኛ ጩቤ
እስከ ጐራዴ ድረስ ነበር ፡፡ ያ ሰው ፎክሮ እንዳበቃ ውቤ ለስጦታ
የተቀመጠ ዕቃ የሚያነሱ መስለው እጃቸውን ዘረጉ ፡፡ ሰውዬውም
ደስ ብሎት ጓደኞቹን ሁሉ እየተዟዟረ በኩራት ተመለከተ ፡፡ የሰው
የውን መገለማመጥ ያዩት ውቤም " ወዳጄ ሆይ ጠጋ በል አት
ፍራ ፡፡ እንዳንተ ያለ ጀግና እወዳለሁ ፡፡ መሸለም የምወደውም ለጀ
ግና አሽከር ነው ፡፡ አይዞህ ጠጋ በል " ሲሉት በውዬው ተጠጋቸ
ውና ቆመ ፡፡

ሰውየው ተጠግቶ እንደቆመ ደጃዝማች ውቤ አጠገባቸው
ያለውን መጋረጃ ድንገት ገለጡት ፡፡ ሰውየው ገድየዋለሁ ያለውን
ልጅ ከዚያ ቆሞ ሲያየው ደነገጠ ፡፡ ለመሸሽም ሞከረ ፡፡ ግን ብርክ
ይዞት ወደኋላው በጀርባው ተንጋሎ ወደቀ ፡፡ የውቤም አሽከሮች
ፈጥነው እዚያው እወደቀበት እጅና እግሩን አሰሩት ፡፡ ውቤ ግን
ምንም ፈገግታ ሳያሳዩ ኮስተር ብለው ይመለከቱታል ፡፡ ከጥቂት ጊዜ
በኋላ " ወዳጄ አንተን ለመሰለ ጀግና የምሸልመው በቂ ሽልማት
የለኝም ፡፡ ያ ገድየዋለሁ ብለህ የጣልከው ሟች ልጅ እሱ የሚሰጥ
ህን ተቀበል " ብለው ወደ ልጁ ዞር አሉና " አንተ ደሃ ለደጉ
ጌታህ የምትሰጠውን ሽልማት ስጠው " አሉት ፡፡ ልጁም እጅ ነስቶ
አጠገቡ የተቀመጠለትን ጦር አነሳ ፡፡ በጀርባው ወደተኛው
ጌታው ሔዶ ጦሩን በሁለት እጁ ይዞ ከጌታው ሆድ ላይ
ሰካው ፡፡ ከዚያም ባለው ኃይል ሁሉ ጦሩን ቁልቁል ይገፋው ጀመር፡፡
እንደገና እየነቀለም ከሌላ ቦታ እየተከለ ሲያቆስለው ሳለ ልጁ አዞ
ረውና ወደቀ ፡፡ በደጃች ውቤ ትእዛዝ አሽከሮች ያን ሰው እንገቱን
በሰይፍ ብለው ገደሉት ፡፡



• አንድ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ነጋዴ አንዲት የደስ
ደስ ያላትን የአሥራ ስድስት ዓመት ልጅ በግርድና ቀጠራት ፡፡
በግርድና ሲቀጥራት እሱ በሚሔድበት ሁሉ አብራው እንድት
ሔድ ነው ፡፡ በተለይ ለንግድ ሥራ ብዙ ጊዜ ወደ ጠረፍ ወደ ምፅዋ
ስለሚሔድ ልጅቱ እንድትከተለው አስቦ ነው ፡፡ በዚህ ምክንያት
ደሞዝዋም በአገር ደንብ ሳይሆን ከፍ ያለ ነበር ፡፡ በዚህ ሁኔታ ከተ
ቀጠረች በኋላ አንድ ሁለት ጊዜ ከየቅርቡ ቦታ እየሔዱ ተመ
ለሱ ፡፡ ልጅቷ ውብ በመሆንዋ ብትሸጥ ደህና ዋጋ እንደምታወጣ
ለት ስላወቀ በመጨረሻው ወደ ምፅዋ አብረው ተጓዙ ፡፡ ከጠረፍ
እንደ ደረሱም ነጋዴው ልጅቷን በደህና ዋጋ ሸጦ እሱ ወደ ሌላ
የኢትዮጵያ ክፍል ተሰወሮ ገባ ፡፡

የልጅቷ ዘመዶች ነጋዴው መመለሱንና ልጅቷ ግን አብራው
እንደሌለች ጭምጭምታ ወሬ ሰሙ ፡፡ ቢጠብቁም ልጅቷ ልትመጣ
ስላልቻለች ወደ ደጃች ውቤ ዘንድ ሔደው አመለከቱ ፡፡ ደጃች
ውቤም የነጋዴውን የቅርብ ጓደኞችና የእስልምና ሃይማኖት መሪ
የሆኑትን ሰዎች አስጠርተው ልጅቷን ካለችበት አምጥተው ለዘመ
ዶችዋ እንዲሰጡ አዘዙዋቸው ፡፡ እነሱም " ልጅቷ የተሸጠችው
ከጠረፍ ስለሆነ እንዴት ማግኘት ይቻላል ! ጊዜውም ስለቆየ ባሁኑ
ጊዜ ካንዱ ወደ አንዱ እየተሸጠች ምናልባትም አረብ አገር ወይም
ግብፅ ገብታ ሊሆን ይችላል ፡፡ እንዴት እናገኛታለን ? " ብለው አመ
ለከቱ ፡፡ ደጃች ውቤም " ይቻላል አይቻልም የሚለው አነጋገር ለኔ
ምኔም አይደለም ፡፡ ልጅቷን ግን ማምጣት አለባችሁ " ብለው
ቁርጥ ቃል ተናገሩ ፡፡ ቀኑንም ቆርጠው ባንድ ወር ጊዜ ውስጥ
እንዲያመጡዋት ወሰኑላቸው ፡፡ ለመያዣም " ልጅቷ ባትመጣ ግን
ከሃይማኖት መሪዎቻችሁ ሁለት ይገደላሉ " ብለው አስጠንቅቀው
ሰዎቹን ያዙ ፡፡ የውቤ ቃል እንደማይታጠፍ ያውቃሉና እነኛ
ሰዎች ቶሎ ብለው የገንዘብ መዋጮ አሰባስበው በየአቅጣጫው
ልጅቷን ለመፈለግ ተሰማሩ ፡፡ ላውዲ አረቢያ ውስጥ ጅዳ መድረ
ስዋ ተሰማ ፡፡ ከዚያም የሚከፈለውን ከፍለውና ከስረው ልጅቷን
በማምጣት የሃይማኖት መሪዎቻቸውን ከመገደል አዳኑ ፡፡

ደጃች ውቤን የጐን ውጋት ሆኖ ቀስፎ ይዟቸው የነበረ የዲ—
የሚባል ሰው ነበር ፡፡ የዲ በደጃች ውቤ ላይ አምፀው የነበሩት
የደጃች ካህሣይ አሽከር ነው ፡፡ ደጃች ውቤ ጠላታቸውን ደጃች
ካሣይን ይዘው አሠሩዋቸው ፡፡ የጌታውን መታሰር ያየው የዲ ከፍ
ቶት ሸፈተ ፡፡ የዲ ከድሮውም ቢሆን ጋሻው በብርና በወርቅ ያጌጠ

ቢተዋው (ጨቤው) ከብር የተሠራ ፣ በራሱ ላይ የሚያደርገው፣ የአንበሳ ጐፈርም እንደዚሁ ያጌጠ ነበር ። የፈረሱ ዕቃ ውበት እንኳ ከጌታው የሚወዳደር ነበር ። ስለየዲ የዘመኑ የትግራይ ሰዎች ሲያወሩ "ጠላቱን በሚያጠቃበት ጊዜ ሰው መሆኑ ቀርቶ እንደ ፀሐይ በጠላቶቹ ሁሉ ላይ ይወድቃል" ይሉታል ።

የዲ— በጌታው መታሰር ምክንያት በውቤ ሠፈር አደጋ እየ ፈጠረ አስቸገረ ። የደጃች ውቤ ሰዎችም በየዲ ምክንያት የከብት መኖ ሣር ለማጨድም ሆነ ውሃ ለመቅዳት ተቸገረ ። ሲመሽ በሠ ፈር አጠገብ አድፍጦ ይተኛል ። ከሠፈር አንድ ሰው ብቅ ሲል ይይዝና ያለ ምሕረት አርዶ ይጥለዋል። ልጅ ፣ ሴት ፣ ሽማግሌ፣ አርጊት ማንንም አይመርጥም ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መኳንንቱ ጉግስ እስ ቲጫወቱ ይጠብቅና የጉግስ ጨዋታ በሚጀመርበት ጊዜ እየጋለበ ከመሀከላቸው ገብቶ ሁለት ሦስት ሰዎች ይገድልና ወደ ተራራው ወጥቶ ከምሽጉ ይገባል ። አንዳንዴም ደግሞ መነኩሴ መስሎ ወደ ሠፈር ይመጣል ። ከመኳንንቱ ደጅ ይቆምና እራቱን እንዲያበሉት ከለመነ በኋላ ከውጭው በር ስብስብ ብሎ ይተኛል ። እኩለ ለሊት ላይ ይነሳና የተኙትን ወታደሮችና ባለቤቱን ገድሎ በፈረስ ሆኖ እሽ ባሪ ጨኸት እየጮኸ ያመልጣል ።

እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ለጥቂት ዓመታት ሲያከናውን ቆይቶ ተያዘ ። ወዳጅ ዘመዱን ፣ እናት አባቱ የተገደለበት ሁሉ ተሰ ብስቦ እንዲገደልላቸው ከደጃች ውቤ ዘንድ እየቀረቡ ይጮሁ ጀመር ። ውቤ ግን ጀግና ሰው ይወዱ ነበርና "እንዲህ ዓይነቱ ጀግና አይገደልም" ብለው በነፃ ለቀቁት ። የሚገዛውም አገር ሰጥ ተው ሾሙት ። የዲ አንድ ቀን ከሰዎች ጋር ቆሞ ሲያወራ አንድ አባቱን የገደለበት ልጅ ካንድ ወታደር የጐረሰ ጠመንጃ ተቀብሎ ተኩሶ ገደለው ። የደፋሩ ጀግና መጨረሻው ሆነ ። የትግራይ ሰዎ ችም ለጀግኖች አቀባበር በሚደረግ የክብር ሥርዓት እያለቀሱ ቀበሩት ። ይህን የየዲን ታሪክ የጻፈው ፐላውዴን ነው ።

ከፐላውዴን መጽሐፍ ሌላም ነገር እለ ። አቶ ውርካ የሚባል አርመናዊ አድዋ ከተማ ይኖር ነበር ። የአድዋ ጅብ ብዙ ስለሆነ ውርካ ጅብ መግደል ይወዳል ። አንድ ቀን አንድ አህያ ሞቶ ከገበ ያው ላይ ወደቀ ። ማታም ያን አህያ ለመብላት የሚመጣ ጅብ ለመግደል አቶ ውርካ ሲጠባበቅ ነገር አየና ጥይት ተኩሶ ።ጅብ መስሎት የተኮሰው ጥይትም ያ ነገር ለው ኖሮ ገደለው ። አቶ



ውርካ ሰው መግደሉን ሲያውቅ ከቤተ ክርስቲያን ገብቶ ተደበቀ ። ሕዝቡም አቶ ውርካን በማጣቱ ትልቁን ልጁን ይዞ በሰንሰለት አሠረው ። የልጁን መታሰር የሰማው አቶ ውርካ ከተደበቀበት ወጥቶ ክርክር ቀጠሉ ።

በደጃች ውቤ ችሎት ላይ ውርካ "... ሳላውቅ በስህተት ጅብ መስሎኝ በተኮስኩት ጥይት ነውና የገደልኩት ምህረት ይደ ረግልኝ...." አለ ። ፈራጅ ሁሉ ሰው ከገደለ ይገደላል እያለ ፈረደ ። ደጃች ውቤ ፍርዱን እንዲያፀድቁ የመጨረሻው ተራ ሲደር ሳቸው "....ሰውና የሞተ አህያ በሌሊት ምንም ግንኙነት የለ ውም ። ቡዳ ከሆነ ግን ያን ጥንብ አህያ ለመብላት ስለሚሔድ ግንኙነት አላቸው ። ስለዚህ እሱ ተኩሶ መግደሉ ጥሩ አድርጓል" ብለው ፈረዱ ። የሟች ዘመዶች ይህን ሲሰሙ ደንግጠው ከውርካ ጋር ታርቀው 40 ብር ብቻ የደም ዋጋ ተቀበሉ ። የደም ዋጋ ደንቡ እስከ 250 ብር ነበር ።

ደጃች ውቤ ጥሩ ጥሩ ጦር ወርዋሪ አሽከሮች ነበሩዋቸው ። ከአምሳ ሜትር ርቀት በጦር ኢላማ የሚወጉ ነበሩ ። ጦራቸውንም በረጃጅም ዛፍ እናት ላይ ወርውረው ማሳለፍ ይችሉ ነበር ። በቦ ለይ ንቡረዕድ ወልደ ሥላሴና ሊቀመኳስ ደስታ በአክሱም ረጅሙ ሐውልት አናት ላይ ጦር ወርውረው ማሳለፍ የሚችሉ ሰዎች ነበሩ ።

ደጃች ውቤ የአጤ ቴዎድሮስ እግች ቢሆኑም መቅደላ ላይ ታስረው ቆይተው ሞቱ ። ከዚያን አስቀድሞ ማንም ዘመድ የሞተ በት ሰው እንዳያለቅስ በአዋጅ ተከልክሎ ስለነበር ደጃች ውቤ ሞተው ልጃቸው የቴዎድሮስ ሚስት እቴጌ ጥሩወርቅ ከተረዱ በኋላ ለቅሶ በአዋጅ ተፈቀደ ። ሕዝቡም ለደጃች ውቤ በማስመሰል አስቀድሞ ለሞቱበት ለየዘመዱ አለቀሰ ። አንዲት አልቃሽም ፣

"የኔታ ደጃዝማች ሁልጊዜ ደግነት

ዛሬ እንኳ ለድሃው እንባ አተረፉለት" ብላ አንጐራጐረች ።

ደጃች ውቤ አገራቸውን ኢትዮጵያን የሚወዱ ታላቅ ሰው ነበሩ ። አንድ ጊዜ ለዲ—አባዲ ሲያጫውቱት "....እናንት ፈረን ጆች የአገሬን አፈር እንዳትነግዱበት ትጠንቀቁ ። እንግሊዞችና እናንተ(ፈረንሳዮች) የመሬታችንን አፈር ትቆፍራላችሁ ። ጤናማ አየራችንን ያለፈቃዳችን ትጠቀሙበታላችሁ ። እንዱ እፀዋታችንን ሲቀነጣጥብ ሌላው ድንጋያችንን ይለበስባል ። ምን እንደ ምትፈ ልጉ አላውቅም ። ያን የምትፈልጉትም ነገር ከአገሬ ውስጥ እንድ ታገኙ አልፈቅድም ።...." ብለውታል ።

## ምዕራፍ 5


# ን ግ ሥ

ደጃዝማች ካሣ ደጃች ውቤን ድል ካደረጉ በኋላ በዚያው በየካቲት ወር 1845 ዓ.ም. አጤ ቴዎድሮስ ተብለው በደረስጌ ማር ያም ቤተክርስቲያን በጳጳሱ በአቡነ ሰላማ እጅ ነገሡ ። ቴዎድሮስ የነገሡበትን ዘመን ደብተራ ዘነበና አለቃ ወልደ ማርያም በጻፉት ታሪክ በ1847 ዓ.ም. ነው ይላሉ ። አለቃ ተክለ ኢየሱስ ግን በ1845 ነው ብለው ዕፈዋል ። በእነዚህ መፃሕፍት የሁለት ዓመት ልዩነት አለ ። እንደነደብተራ ዘነበና አለቃ ወልደማርያም ዘመን አገላለፅ ከሆነ ቴዎድሮስ የነገሡት 13 ዓመት መሆኑ ነው ። አለቃ ታዬ አጤ ቴዎድሮስ 15 ዓመት ነገሡ ስለሚሉ የነገሡበት ዘመን ከአለቃ ተክለ ኢየሱስ ትረካ ጋር ይጋጠማል ። አቶ መንግሥቱ ለማ የአባታቸውን የአለቃ ለማን ትረካ በፃፉበት መፅሐፈ ትዝታ ውስጥ ቴዎድሮስ በ1845 ዓ.ም. ነግሠው በ1860 ዓ.ም. ሞቱ ይላሉ ። ባላንባራስ ማህተመ ሥላሴም በዝክረ ነገር መፅሀፋቸው በ1845 ዓ.ም. ነገሡ ይላሉ ። ስለዚህ እኔም አብዛኛዎቹ በተናገሩት በ1845 ዓ.ም. ነገሡ ብያለሁ ።

ደጃዝማች ካሣ ስማቸውን ለውጠው አጤ ቴዎድሮስ ተብ ለው ከነገሡ በኋላ የዘመን መሣፍንት ፍጻሜ ሆነ ። ስማቸውን ቴዎ ድሮስ ተብለው የነገሡበትም ምክንያት "ቴዎድሮስ የሚባል ንጉስ ሲነግስ ኢትዮጵያን እስከ ባሕር ያሰፋታል ፣ ፍርድና አስተዳደርንም ያስተካክላል" የሚባል ትንቢት ስለነበረ ሕዝቡ "ይህ ትንቢት የርስዎ ነው" እያሉ ስላሞካሿቸው ስሜን ቴዎድሮስ በሉ ብለው አወጁ ።

አጤ ቴዎድሮስ እንደነገሡ ደጃች አርአያን ለትግሬ ሾመው ወደ አምባ ጫራ ተመለሱ ። ከዚህ በኋላ ደግሞ ሸዋን ለማስገበር ይዘጋጁ ጀመር ። ዝግጅታቸውን አጠናቀው ወደሸዋ ጉዞ ጀመሩ ። ገራገራ ከተባለ ቦታ ሠፈር አድርገው ሳለ ትግሬዎች የዓመት ግብ ራቸውን ለመገበር መጡ ። እንደመጡም በትግራዩ ገዥ በደጃች





የደቡብ ትግሬ ዕይታ

አርአያ ላይ ከሳሽ ተነስቶ ወነጀላቸው ። አጤ ቴዎድሮስም ደጃች አርአያን ሽረው በምትካቸው ደጃች ካሣን ሾሙ ።

ቴዎድሮስ ወደሸዋ ለመዝመት በተነሱ ጊዜ የሸዋው ንጉስ ኃይለመለኮትና የወሎዋ ባላባት ወይዘሮ ወርቂት የጦርነት ውል ተዋዋሉ ። ውሉም ቴዎድሮስ በጐጃም በኩል አቋርጠው ወደ ሸዋ ሲመጡ ኃይለ መለኮት ፊት ለፊት ሲገጥሙ ወርቂት ደግሞ ሠራዊቷን ይዛ በጐን በኩል ልትወጋቸው ነበር ። ወርቂት ከጨጨሆ እስከ ሸዋ ድንበር ትገዛ ነበር ። ይህን ምክር ቴዎድሮስ ሲሰሙ ነገሩ እንደማያዋጣቸው አውቀው የጦር መላቸውን ለወጡ ። ሁለ ቱን ባንድ ጊዜ ከመግጠም ተራ በተራ መግጠሙ እንደሚሻል አውቀው የሸዋ ዘመቻውን ትተው ወደ ወሎ ለመዝመት ይገሰግሱ ጀመር ።

ደላንታ ሲደርሱ ሠራዊታቸው ተርቦ ነበርና "እህል ዘርፈህ ብላ ። ልብስና ከብት አትንካ" ብለው አወጁ ። ቴዎድሮስ ይህን አዋጅ ቢያውጁም ሠራዊታቸው ግን አዋጃቸውን ጥሶ ከብት እየዘ ረፈ እያረደ ይበላ ጀመር ። ቴዎድሮስም በወታደሩ ተግባር በጣም ተቆጥተው "የድሃውን ገንዘብ እንዳረድኸው ባንተም እግዚአብ

ሐር አለብህ ” ብለው ደላንታን ለቀው ወደ በሸሎ ተጓዙ ። ከበ
ሸሎ ወንዝ ሲደርሱ ወታደር ሳይታዘዝ ተከፍሎ ወደዘረፋ ሔደ ።
በዚያም ያሉ ኦሮሞዎች በርትተው በመዋጋት ብዙ ወታደር ገደሉ ።
ብዙ ጠመንጃም ማረኩ ። ለምርኮ ሔዶ ከነበረው የተረፈው ወታ
ደራቸው እየሸሸ ሲመጣ ቴዎድሮስ ሁሉንም አስይዘው አንዳንድ
እጁንና አንዳንድ እግሩን እያስቆረጡ ጣሉት ። ከዚህ በኋላ በወታ
ደሮቻቸው መሀል ስነ ሥርዓት ሰፈነ ።

በሐምሌ ወር ቴዎድሮስ ቆቃ ከተባለ ቦታ ሠፍረው ሳለ የሸ
ዋው ንጉሥ ኃይለመለኮት በውላቸው መሠረት ወይዘሮ ወርቂት
ንና አሊ አደራን ለመርዳት መምጣታቸውን ሰሙ ። በዚህ ጊዜ
ከቆቃ ተነስተው ወደ አያታ መጥተው አዋ ሜዳ ከተባለው ሥፍራ
ሠፈሩ ። የቴዎድሮስን መጠጋት የሰሙት ኃይለመለኮትና የኦሮሞቹ
ባላባቶች ባንድነት ተሰብስበው “ ይህን ሰው አንችለውምና እንበታ
ተን ብለው መክሩ ። በዚህ ምክር ተስማምተው ኃይለመለኮት ወደ
ሸዋ ተመለሱ ። ሲመለሱም በክረምቱ ምክንያት ብዙ ከብትና ሰው
አለቀባቸው ። አሊ አደራም ለጋጉራ ገቡ ። ቴዎድሮስ የአሊ አደራን
ወደ ለጋጉራ መሔድ እንደሰሙ እጁን ለመያዝ ገሰገሱ ። እንደደረ
ሱም ነሐሴ 5 ቀን ውጊያ ገጥመው አሊ አደራ በጀግንነት በመዋ
ጋቱ ከቴዎድሮስ ሠራዊት ብዙ ሰዎች አለቁ ። ቴዎድሮስም ፈረሳ
ቸው ላይ ሆነው ከጦሩ መሀል ገብተው ሲያዋጉ ውጊያው ጠንቶ
ባቸው ከሰልፉ መሀል በከፍተኛ ችግር ሊወጡ ቻሉ ። ከብዙ እል
ቂት በኋላ ቴዎድሮስ ድል አድርገው አሊ አደራ በእርቅና በሰላም
ገባላቸው ። ቴዎድሮስም አሊ አደራን በአባቱ አገር ላይ ሾሙት ።

የአሊ አደራን ጉዳይ ካጠናቀቁ በኋላ እንደ አሊ አደራ ጉል
በት የሚሰማውንና የሚያስቸግረውን ሰዲቅ ዳንታ የሚባለውን
ለማስገበር ቆርቆራ ወደ ተባለ አገር ሔዱ ። ሰዲቅ ደንታም ጦር
ነት ገጥሞ አሰቃቂ የሆነ ውጊያ ተዋጋቸው ። ከቴዎድሮስ ሠራዊ
ትም ብዙ ሰው አልቆ ብዙ መማሪያም ተማረከ ። ነገሩ እንደጠና
አይተው የተረፈ ሠራዊታቸውን ይዘው ቴዎድሮስ ተመለሱ ። ከሁ
ለት ዓመት በኋላ ግን አሊ አደራ አዘንግቶ ሰዲቅ ደንታን ይዞ ለቴ
ዎድሮስ ሰጣቸው ። እሳቸውም ግሼን ላይ አስረውት ሳለ ታሞ ሞተ ።

ከሰዲቅ ደንታ ውጊያ በኋላ ቴዎድሮስ ወደ ጊምባ ዘመቱ ። ጊምባ
ሲደርሱም የሰባት ቤት ኦሮሞዎች ዙርያቸውን ከበው መሐጃም ሆነ
መመለሻ በማሳጣት አወኳቸው ። ጳጉሜ እንደገባም ጥኑ ውጊያ



ገጠሙቸው ። ሠራዊታቸውም በርትቶ እየተዋጋ ምርኮ ማምጣት
ጀመረ ። ቴዎድሮስም ከመጀመሪያው የመጡትን 47 የጊምባ ምርኮ
ኞችን አስቀርበው ሁለት ሁለት እጆቻቸውን እያስቆረጡ በገመድ
ከንገታቸው ላይ እያሰሩ ወደዘመዶቻቸው ሒዱ ብለው ለቀቁዋ
ቸው ። ከዚህ በኋላ ይህን ያዩ ወሎዬ በሙሉ ሸሽቶ መንገዱን ከፈተ
ላቸው ። የወሎዎችን እጅ መቆረጥ ያዩ ቀልደኛም “እራቱንስ ሚስቱ
ታጉርሰው ፣ እረ ቂጡን በምን ያብሰው (ይጥረገው) ” ብሎ ተናገረ ።

በሰላምም ሆነ በቅጣት ወሎ ከገበረ በኋላ ወደ ሸዋ ተጓዙ
የቴዎድሮስን ወደ ሸዋ መምጣት ንጉሥ ኃይለመለኮት እንደሰሙ
እሳቸውም ለጦርነት ተዘጋጁ ። ቴዎድሮስ ከሸዋ ድንበር ግሼ ሲገቡ
የመንዝ ገዥ አቶ ሀብተ ማርያም ጥር 7 ቀን 1847 ዓ.ም. ከግ
ድሙ ገዥ ከአቶ ሰሙ ንጉሥ ጋር ሆነው ውጊያ ገጠሙቸው ።
በጦርነቱም ሙሉ ቀን ሲዋጉ ውለው በሁለቱም በኩል መሸናነፍ
ሳይኖር ውጊያውን ምሽት ገላገለው ። በማግስቱ ውጊያው ቀጥሎ
የቴዎድሮስ ኃይል በመበርታቱ አቶ ሀብተማርያም ተማርከው ሲያዙ
አቶ ሰሙ ንጉሥ ግን አመለጡ ። በዚያ ታላቅ ውጊያ የአቶ ሀብተማር
ያም ድል መሆን በሸዋ ድንጋጤን ፈጠረ ።

ንጉሥ ኃይለ መለኮት ከወሎ ሲመለሱ ሕመም አድሮባቸው
ነበርና በሕመም ላይ እንዳሉ መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው ምክር
ጀመሩ ። በዚህም ምክር ላይ የይፍራታው ገዥ አቶ ቢድሉ ከመዋ
ጋት ይልቅ እጃችንን ብንሰጥ ይሻላል የሚል ሐሳብ አቀረቡ ።
በመረሐቤቴው ገዥ በአቶ ሰይፉ ሣህለ ሥላሴ የ ጊመሩት መኳን
ንት ግን ሳንዋጋ እጃችንን መስጠት የለብንምና መዋጋት አለብን
እንዋጋ አሉ ።

እስተርን እንደጻፈው በዚህ ጊዜ ሸዋ የነበረው የተዘጋጀ ጦር
50.000 ወታደር ይሆን ነበር ። ፕላውዲን ደግሞ የአጼ ቴዎድሮስን
ሁኔታ በመግለፅ ለአርል ክላሬንደን በፃፈው ደብዳቤ የቴዎድሮስ ጦር
50 እስከ 60 ሺ ወታደር እንደነበርና ከጐንደር ጀምሮ በየመንገዱ
ያለተው ወታደራቸው ሲቀነስ አሁን ሸዋ የገባው 40000 ወታደር
ቢሆን ነው ይልና ወታደራቸው ግን የተሻለ መሣሪያ ያለውና ስነ
ሥርዓት አክባሪ መሆኑን ይገልፃል ። በተለይም ከሽፍትነታቸው
ጊዜ ጀምሮ ቴዎድሮስን ያገለግሉ የነበሩት አንድ ሺህ ያህል ወታ
ደሮቻቸው ጥሩ ተዋጊዎች እንደነበሩም ይናገራል ።

እንደተባለው ሁሉ በመጋርያ በኩል የቴዎድሮስ ኃይል ተወ

ዳዳሪ የሌለው ነው ። ጥንት ራሳቸው በነበራቸው ላይ ከደጃች ውቤ የማረኩት ሰባት ሺ ጠመንጃና ሁለት መድፎች ተጨምረው ላቸዋል። በዚህም ባላቸው ኃይል ቴዎድሮስ መንዝን ፡ ግድምንና ይፍራታን አስገብረው ጉዞአቸውን ወደፊት ቀጠሉ ። የይፍራታው ገዥ አቶ በድሉም ከኃይለመለኮት ከድተው ለቴዎድሮስ ገቡ ። አሳቸውም ቴዎድሮስን መንገድ በመምራት ጌታቸውን ኃይለመለኮትን ለመውጋት መጡ ።

ቴዎድሮስ ጅብ ዋሻ ከተባለ ቦታ ሲደርሱ አንኮበር ያለውን የኃይለመለኮትን ቤተ መንግሥት የሚጠብቁ ሰዎች " በጌታችን ቦታ ጠላት አይገባበትም ። ጠጃንም ጠላት አይጠጣውም " ብለው ጥቅምት 16 ቀን እርብ ዕለት የአንኮባርን ቤተ መንግሥት አቃጠሉት ። ንጉሥኃይለ መለኮትም ሕመማቸው እየጠናባቸው ስለሔደ ለጦርነት ከተሰለፉበት ቦታ ጥቅምት 30 ቀን 1848 ዓ.ም. ሞተው በማግስቱ ሕዳር 1 ቀን ደብረ በግዕ ተቀበሩ ። ንጉሥ ኃይለ መለኮት እንደሞቱም የሸዋውን ጦር የኃይለ መለኮት ወንድሞች አቶ ዳርጌና አቶ አንዳርጋቸው(በኋላ ሁለቱም ራስ የተባሉት)ይመሩ ጀመር ። እነኝህም የጦር መሪዎች የኃይለ መለከትን ልጅ ሕፃኑን የአስራ አንድ ዓመቱን ምኒልክን ቡልጋ ውስጥ ደብቀው ለመዋጋት ሲያስቡ የቴዎድሮስ ጦር ደረሰባቸው ። ከዚያም ምኒልክን ይዘው ወደምንጃር ሸ ሹ ።

አጤ ቴዎድሮስ ጓዛቸውን ቁንዲ ላይ ትተው አሳቸው ጦራቸውን ይዘው ወደ ጠምቂ መጡ ። በዚያም በሰፈሩ ጊዜ የአገሬው ብዙ ነፍጠኛ ገባላቸው ። ከዚያን ተጉዘው መገዘዝ ሲደርሱ ራስ አንግዳን ፥ ቢትወደድ ብሩንና ቢተወደድ ውቤን ባንድነት አድርገው ምኒልክን እንዲይዙ ላኩዋቸው ። እነኝህም የተላኩት መኳንንት በረከት ከሚባለው ሥፍራ ምኒልክን ከሚያሸሸው ሠራዊት ጋር ተገናኝተው ውጊያ ገጠሙ ። ከሁለቱም ወገን ጥቂት ሰው ካለቀ በኋላ አቶ ናደው (በኋላ ራስ)አቶ ዳርጌ እና አቶ ሀብቴ ልጅ ምኒልክን ይዘው በፈረስ አመለጡ ። በኋላ ግን ከሚያባርራቸው ከቴዎድሮስ ኃይል ለማምለጥ ያለመቻላቸውን ባወቁ ጊዜ " እንግባ በከንቱ አንከራተት " ብለው መከሩና ምኒልክን ይዘው ከአጤ ቴዎድሮስ ታርቀው ገቡ ። ቴዎድሮስ የሸዋን አስተዳደር አደላድለው ከሾሙት በኋላ ተድላ ጓሉን ለመያዝ ወደ ጐጃም ዘመቱ ።



ቴዎድሮስ አባይን መሻገራቸውን ተድላ ጓሉ እንደሰሙ ጅብላ ገብተው መሸጉ። አጤ ቴዎድሮስም መንቆረር ላይ ሠፍረው ጅብላ የሚሰበርበትን ብልሃት ይፈልጉ ጀመር ። የጅብላ ምሽግ ጠንካራ በመሆኑ ለቴዎድሮስ ጦር አስቸገረ ።ይህን ችግር የተመለከቱት ቴዎድሮስ ጅብላን ትተው አራት መንኮራኩር ላይ ሔደው ሠፈሩ ። በዚህ ጊዜ የተድላ ጓሉ ምርጥ የጦር አገሩንም እንዲዘረፍ አዘዙ ። በዚህ ጊዜ የተድላ ጓሉ ምርጥ የጦር መሪ የነበሩት ፊታውራሪ ቸኮል በዱር ነበሩና የቴዎድሮስ ወታደር ላጋበዲስ ከተባለ ቦታ ይዞአቸው ለቴዎድሮስ አቀረባቸው ። ቴዎድሮስም ፊታውራሪ ቸኮልን ከወንድ ልጃቸው ጋር ባሶ ገበያ ላይ ሰቀሉዋቸው ።ያንጊዜም አልቃሽ ብልታቸውን ያየች አስመስላ

"ፊታውራሪ ቸኮል ሸማው አልቆበት ፥
እንደተንጠለጠለ ግንዱን አየሁት ።

አለች ። የፊታውራሪ ቸኮል ሚስትም ባላቸውና ልጃቸው ባንድነት ስለተሰቀሉባቸው

አባትና ልጁ ተጣልተው በገመድ ፡
እኔ ልቅደም አለ ወይ እንዳሻ መልመድ ።
ምን ብትደነግጥ ግንዱ ሲበጃጅ ፥
ምን ብትደነግጥ ቀንበሩ ሲበጅ
እናቴ ሔድሁልሽ አይልምወይ ልጅ " ብለው አለቀሱ ።

አጤ ቴዎድሮስ በዱር የሸፈተውን ሁሉ እያስያዙ ብዙ ሰዎችን ሰቀሉ ። ከነዚህም መሀል የታወቁት መሪዎች ወንዴ ገብረ ወልድና ካሣ ቢሰወር የተባሉት ነበሩ ። ብዙ ሰው መሰቀሉን ያየች የጐጃም አልቃሽም የመሳለሚያ መስቀል አስመስላ

" ወይ አልተባረከ ይሄ ሁሉ ሰው
ንጉሥ መስቀልዎን ቢተውት ምነው ። " አለች ። ከነዚህ

ከተሰቀሉት ሰዎች ሌላ የደጃዝማች ተድላ ጓሉ ቁባት የነበሩት ወይዘሮ ጣይቱ ኤልያስ ተይዘው በእሳት አቃጥለው ገደሉዋቸው ። የጣይቱ ኤልያስ መቃጠል ያየች አልቃሽም

"እንኳን የሰገራ የሰንበት ልትደርስ ፥
ነዳጥራ ቀረች ጣይቱ ኤልያስ " ብላ ገጠመች ። የሰገራ ፥ የሰንበት እና ነዳጥራ የአገር ስም ነው ። በአገር ስሙ አስመስላ ነደደች ለማለት ነው ።

አጤ ቴዎድሮስ በጐጃም ላይ ይህን የመሰለ ጥፋት ቢያደርሱም ሙሉ በሙሉ በጭካኔ ተግባሩ ብቻ ያተኮሩ አልነበሩም ። አንድ መነኩሴ ከሽፍቶች ጋር ተባብሮ ነበር ተብሎ ተማርኮ ከቴ

ዎድሮስ ፊት ቀረበ ። ቴዎድሮስም የተናደዱበት ጊዜ ነበርና ያን መነኩሴ እንዳዩ “ በል በልልኝ ” ብለው አዘዙ ። መነኩሴው የታዘዘበትን ትእዛዝ ሲሰማ “ ጃንሆይ እግዚር ያሳይዎ ፤ ቄስ ነኝ ቄስ ነኝ ” እያለ ጮኸ ። ቴዎድሮስም “ ቄስ ከሆንክ እስቲ ዳዊትን ቁጠር ። ስንት ነው ? ” አሉት ። መነኩሴውም በዳዊት ውስጥ ስንት መዝሙሮች እንዳሉ አያውቁም ነበርና “ ጃንሆይ እንዲያው ይማሩኝ እንጂ የሚዳ ቄስ ነኝ ” አላቸው ። በንዴት ላይ የነበሩት ቴዎድሮስ በመነኩሴው አመላለስ ስቀው መማራቸውን ሩቢላ ያሳተሙት ደራሲው ያልታወቀው ታሪክ ፀሀፊ ገልጸታል ።

በዚሁ ጊዜ ደግሞ አጤ ቴዎድሮስ ደጃዝማች ተድላ ጓሉን አድፍጠው አረላስተው ለመያዝ አስበው ወደ ሸዋ የሔዱ መስለው ሠራዊታቸውን ሁሉ ዱር ውስጥ ደበቁት ። የተድላ ጓሉን ሁኔታ እያሰለሉ ሲጠብቁ አንድ ቀን ማታ ራሳቸው ቴዎድሮስ ተራ ልብስ ለብሰውና ተራ ሰው መስለው አንድ አሽከር አስከትለው መንቆረር ከተማ ገቡ ። ከያኔው መንቆረር ከዛሬው ደብረ ማርቆስ ከተማ እንደገቡ በየመንደሩ ሲዘዋወሩ ቆዩና በመጨረሻው ገደማ ከንዲት ባልቴት ቤት ገቡ ። እንደገቡም ሴትዮዋን “ እንዴት ዋልሽ ” አሉዋት ።

“ እግዚአብሔር ይመስገን ። አንተስ እንዴት ዋልህ ? ” አለቻቸው ።

“ እርቦኛልና እስቲ እንጀራ ስጭኝ ” አሉዋት ። ባልቴትዋም

“ ለመሆኑ አንተ የማን ወታደር ነህ ?” አለች ።

ቴዎድሮስም “ የተድላ ጓሉ ነኝ እንጂ የማን ብለሽ ? ” አሉዋት ። ሴትዮዋ ይህን እንደሰማች ተነስታ እንጀራ በእርጐ አድርጋ ሰጠቻቸው ። ቴዎድሮስ የሰጠቻቸውን እንጀራ በእርጐው እየማጉ መብላት ሲጀምሩ ሴትዮዋ ወደ አጠገባቸው ቀረብ ብላ ተቀምጣ “ብላ ” ትላቸው ጀመር ።

ሴትዮዋ ንጉሡ አጤ ቴዎድሮስ መሆናቸውን አላወቀችም ። ቴዎድሮስም እንዲታወቁ አልፈለጉም ነበርና ከሴትዮዋ ጋር ጭውውት ጀመሩ ። “ ያ እብድ ንጉሥ ወዴት ደረሰ ይባላል ? ወሬውን አልሰማችሁም ? ” አሏት ።

ሴትዮዋም የንጉሡን መሰደብ ስትሰማ ተናደደችና “ እብዶችስ የተድላ ጓሉ ወታደሮች ናችሁ እንጂ የተቀባ ንጉሥ እብድ



አይባልም ። አሁን ሸዋ መሔዱን ብትሰሙ አገር ለማጥፋት ደስ ብሏችኋል ። ያ እብድ የምትሉት ንጉሥ ቢዘልቅባችሁ ደግሞ ደምጣችሁን አጥፍታችሁ ከአምባ ለመሽጐጥ ነው ” አለች ።

ቴዎድሮስም ቆጣ ብለው “ ምነው ትሰድቢናለሽ ። እንጀራሽን አንሺ አሉዋት ። ሴትዮዋም ምነው አትጐርሰውም” ብትላቸው “ ይበቃኛል ፡ ደህና ሁኝ ” ብለው ወጡ ።

ተድላ ጓሉ ከምሽጋቸው አልወጣ ብለው ስላስቸገሩ አጤ ቴዎድሮስ ጉጃም እንዲዘረፍ አዘው ወታደሩ በሚዘርፍበት ጊዜ የዚያች ሴትዮ ቤትና ንብረት እንዳይዘረፍ ዘብ አቁመው እንድትጠበቅ አዘዙ ። ዘረፋው ጋብ ሲል ቴዎድሮስ ያቺን ሴትዮ አምጡ ብለው አዘዙ ።

የታዘዙ ወታደሮችም ሴትዮዋን ይዘው ወደ ቴዎድሮስ ሲሔዱ ሴትዮዋ ከመፍራትዋ የተነሳ እያለቀሰችና እየተንቀጠቀጠች ቴዎድሮስ ዘንድ ደረሰች ። ቴዎድሮስም ቆጣ ብለው “ በይ አንቺ ሴት ! ትናንትና የተድላ ጓሉ ወታደሮች ከቤትሽ ገብተው ነበር ? ስምቻለሁና እውነቱን ንገሪኝ ። በቀረ ከሳሽ ሊመጣብሽ ነው ” አሏት ።

ያልታወቀው ኢትዮጵያዊው ደራሲ ሩቢላ ባሳተሙት መጽሐፍ ላይ የሴትዮዋን መልስ ሲገልፁ እንዲህ ይላል ። “ እግዚር ያሳይዎ ጃንሆይ ። ከንጉስና ከእግዚር ፊት እውነት መናገር ነው መልካም ። ትናንትና እውነት በሀሰት አለውጥም ። አንድ ጉበዝ ከቤቴ መጥቶ እባክሽ እርቦኛልና እንጀራ ስጭኝ አለኝ ። የማን ወታደር ነህ ብዬ ብጠይቀው የተድላ ጓሉ ነኝ እንጂ የማን ልታደርገኝ ነው አለኝ ። እኔም ፈርቼ እንጀራ በእርጐ አቀረብሁለትና አልበላውም እንኳ አልሞጽሙጾ ጥሎልኝ ሔደ ። የተናገረውንስ ለራሱ ይጥቀመው ፤ እኔ አልናገረውም ። እኔ ግን የተቀባ ንጉሥ ሲመጣ ድምጣችሁ ሊጠፋ ዛሬ ንጉሱ ሸዋ ሔደው ስምታችሁ ድሃ ለማጥፋት ደስ ብሏችኋል ብዬ ተናገርሁትና ደህና ሁኝ ብሎኝ ጦሩን አንስቶ ወጥቶ ተጓዘ ። ከዚህ ሌላ የተናገርሁት የለኝም ። ካለ አንድ ጉበዝ ሌላ የገባብኝም የለ ። ከሳሽ ይቁምብኝ ” አለችና እጅ ነሳች ።

ቴዎድሮስም ስለእሳቸው የተከራከረችውን አስበው አምሳ ላምና አምሳ በሬ ሰጥተዋት “ እስከ ሕይወቴ ፍጻሜ ድረስ አትከሰስ ፤ አትወቀስ ” ብለው አዘዙላት ።

አጤ ቴዎድሮስ የሸፈተባቸውን አገር እየዘረፉና ሰውንም እየቀጡ በጌምድር ገቡ ። የቴዎድሮስን ጐንደር መግባት ተድላ ጓሉ ሲሰሙ ከጅብላ ምሽጋቸው ወጥተው ንጉሡ በጐጃም ላይ የሾሙዋቸውን ራስ እንግዳን ለመውጋት ተሰለፉ ። ጉሊት ከተባለው ቦታ ላይ ሁለቱም ወገኖች ጦርነት ገጥመው ራስ እንግዳ ድል አድርገው ። ደጃች ተድላም ፈረሳቸው ላይ እንደሆኑ እየተዋጉ ውጊያውን ይመሩ ነበርና በመጨረሻው ጊዜ በሽጉጣቸው ተኩሰው ቢስቱ ሽጉጣቸውን አምዘግዝገው በመወርወር አንድ ሰው ገደሉና በፈረሳቸው እየጋለቡ አምልጠው ጅብላ ገቡ ። የጐጃም አዝማሪም " ደጃች ተድላ መች ገንዘብ ወደደ ፤ ተኩሶ አምዘግዝጐ ጥሎላቸው ሔደ " ብሎ ገጠመላቸው ። ራስ እንግዳም ከተድላ ጓሉ ሠራዊት ብዙ ሰው ማርከው ነበርናምርኮኛውን ሁሉ በነፃ ለቀቁት ። የምርኮኛውን በነፃ መለቀቅ ቴዎድሮስ ሲሰሙ ተቆጡ ። ራስ እንግዳንም " እንዴት ሳትቀጣ ትለቃለህ " ብለው አስጠርተው አሰሩዋቸውና በእሳቸው ቦታ ራስ ውቤን ሾመው ሰደዱ ።

በ1849 ዓ.ም. በታህሣሥ ወር የእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ወደ ኢትዮጵያ መጡ ። አጤ ቴዎድሮስም በታላቅ ክብር ተቀበሏቸው ። ሊቀ ጳጳሱ የመጡበት ዋናው ምክንያት አጤ ቴዎድሮስና በኢትዮጵያ የተሾሙት ጳጳስ አቡነ ሰላማ ስምምነት አልነበራቸውም ። ከጳጳሱ ጋር ብቻ ሳይሆን ከቀሳውሱትም ጋር ጠብና ክርክር ስለነበር ይሄን ነገር በሰላም ለመፍታትና ለማስማማት ብለው ነበር ይባላል ። ቴዎድሮስን ከቀሳውስት ጋርም ሆነ ከየመኳንንቱ የሚያጣላቸው ጳጳሱ አቡነ ሰላማ ነበሩ ። አቡነ ሰላማ ጠባያቸው የመንፈሳዊነት ሳይሆን ዓለማዊነት ያጠቃው ነበር ። ከቴዎድሮስም በፊት ከእቴጌ መነን ጋር ከፍተኛ ጠብ ተጣልተው ነበር ። እቴጌ መነን በጳጳሱ አድራጐት ተናደው "ጳጳስ ባርያ ነው ። በወርቅ ተገዝቶ መጥቷልና ። ደግሞ ባርያ ጌታው ፡ እመቤቱ የወደዱትን ፡ ያዘዙትን ይሠራል እንጂ የርሱ ፈቃድ አይሆንም ' ብለው ወቀሷቸው ። ጳጳሱ አቡነ ሰላማም እኔ ባርያ ሆኜ በወርቅ በሺ ብር ተገዛሁ ። አንቺ ግን በአገሬ እስር ብርም አታወጭ" ብለው መሰሉላቸው ። ይህን የጳጳሱን የስድብ መልስ ስንመለከት ከዓለማውያን እንደበት እንጂ ካንድ መንፈሳዊ አባት ሊነገር የማይገባው ነበር ። የጳጳሱን ታሪክ ወደፊት አቡነ ሰላማ ከሚለው እርእስት ሥር ይመለከቱታል ።





የጐንደር ከተማ እይታ

አጤ ቴዎድሮስ ምንም እንኳን ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ቢደከሙም የሚሸፍተው እየበዛ አልሳካላቸው አለ ። በጐጃም አል በገርም ብለው ያስቸገሩት ደጃዝማች ተድላ ጓሉ ፣ በሸዋ መሸሻ ሰይፉ ፣ በስቆጣ ዋግሹም ገብረ መድህን ፣ በትግሬ ደጃዝማች ንጉሴ ፣ በአጠገባቸው በጐንደርም ጋረድ ከንፋንና ግንባሮ ካሣ ሸፍተው ቴዎድሮስን እረፍት አሳጥተዋል ። ከእነኚህ ከታወቁት ታላላቅ ሰዎች ሌላ በየጉጡና በየአምባው እየሸፈተ ያስቸገራቸው ባላባትም ብዙ ነው ። እነኚህ ሁሉ ቴዎድሮስ እምነው የሾሙዋቸው ሹማምንቶቻቸው ነበሩ ።

ከዚህም ሌላ በጳጳሱ በአባ ሰላማና በቀሳውስቱም ጭቅጭቅ ቴዎድሮስ ሰላም አላገኙም። ቀሳውስቱ የሚወጣባቸውን ደንብ በመቃወም ሁልጊዜ አቤቱታ ያቀርባሉ ጳጳሱ አባ ሰላማ ጥቅማቸው በታነካ ቁጥር በተራው ነገር ሁሉ ቴዎድሮስን ይገዘቷቸዋል። የመኳንንቱ መሸፈት ፣ የቀሳውስቱ ጭቅጭቅ የአባ ሰላማ ግዝት ፣ ከሌላው ከድሃው አቤቱታ ጋር ተዳምሮ ቴዎድሮስን የነገር ብዛት በጥብጧቸዋል። ቤተ ክህነትና መኳንንቱ መሬቱን ተካፍሉ በመያዙና የሚያርሰውና የሚያመርተውም ለየራሱ በመሆኑ ቴዎድሮስ ጦረኛ ሠራዊታቸውን የሚቀልቡት በማጣት መቸገራቸው ሌላው የቴዎድሮስ ችግር ነበር። ሠራዊታቸው ዘርፎ እንዲበላ ሲያዙም ባላገሩ ይነሳባቸዋል። ይህን የመሳሰለው ችግር ተደራርቦ የደረሰባቸው ቴዎድሮስ ፣ መኳንንቱ እንዲገብር ፣ ቤተ ክህነት የያዘው መሬት ተቀንሶ በይዞታውም እንዲገብር በማድረጋቸውና መሬትን በመውረሳቸው ሸፍታውም ሆነ በጥባጩ እየበዛ ሔደ። ቴዎድሮስም እልህ ለእልህ ተያይዘው አዋጃቸውን ሁሉ በኃይል ለማስፈጸም ቢጥሩም ቅጣታቸውን ፈርቶ ከሚገብርላቸው ይልቅ የሚሸፍተው እየበዛ ሔደ። "ሰዎችን ከማጥፋት ሰዎች የሚጠሉብህን አጥፋ" የሚለው ምሳሌም በቴዎድሮስ ዘንድ ትክክለኛ አባባል አልነበረም። ሁሉን በኃይል ፣ ሁሉን በግድ የሚሉት ቴዎድሮስ የግዛት ዘመናቸው እየረዘመ በሔደ ቁጥር ችግራቸውም እየበዛ ሔደ።

ከችግራቸው በመጠኑ ብንመለከት በ1849 ዓ.ም. ካህናት ተሰብስበው ከቴዎድሮስ ዘንድ ቀርበው "ጃንሆይ ፣ ለሕዝቡ እንደ አባትህ ብለው እንዳወጁት እኛንም እንደ ጥንት እንደነገሥታቱ ያኑሩን" ብለው አቤቱታ አቀረቡ። አቤቱታው የቀረበበት ምክንያት የጣሉባቸውን ግብር እንዲያነሱላቸውና የወሰዱባቸውን መሬት እንዲመልሱላቸው ነበር። ይህን አቤቱታ የሰሙት አጤ ቴዎድሮስም "እኔ ምን ልብላ ? ሠራዊቱንስ ምን ላብላው ? እኩሌታውን የመስቀል መሬት ፣እኩሌታውን እሪም ገዳም እያላችሁ ወሰዳችሁት" አሏቸው።

የቀሳውስቱ አፈጉባኤም (ተናጋሪ) "አራት ወር በጐንደር ተቀምጠው አርማጨሆን ፣ ጠገዴን ፣ ወልቃይትን ፣ ሰሜንን ትግሬን ይብሉ። አራት ወር በእሪንጐ ተቀምጠው በጌምድርን ፣ ላስታን ፣ የጁን ወረሂመናን ፣ ወሎን ፣ ሸዋን ይብሉ። አራት ወር ይባባ ላይ ተቀምጠው ሜጫን ፣ አገውን ፣ ዳሞትን፣ ጐጃምን ይብሉ። እንደ ጥንቱ እንደ ነገሥታቱ ይሁን" አሏቸው። ይህን አባባል ስንመለከተው ንጉሡ ከቀሳውስቱ ራስ ላይ ተነስተው ባላገሩ ራስ ላይ እንዲሠፍሩ የሚጠይቅ ነው።



አጤ ቴዎድሮስም ለቀሳውስቱ ጥያቄ ሲመልሱ በሴት አጣራር እየተናገሩ "እኔ ብቻዬን በሆንሁልሽ ጊዜ እንደ አጤ ኢያሱ በሻሽ እንቀሽ ልትገድሊኝ ነው ?" አሉና በፍትሐ ነገሥት እንዲወስን አዘዙ። ፍትሐ ነገሥቱ በቀሳውስት የተዘጋጀ የሕግ መጽሐፍ በመሆኑ ለቀሳውስት ያደላልና የፍትሐ ነገሥቱ ውሳኔ ለቀሳውስት ሆነ። ይህን የሰሙት ቴዎድሮስም "እንድሽ እንባቢ ፣ እንድሽ ተርጓሚ" ብለው ተቆጥተው "የወደዳችሁትን ባልጋው አስቀምጡበት። እኔ እንደጋሎች እየዘረፍሁ እበላለሁ" ብለው ለመሄድ ከተቀመጡበት ጃንተከል ከተባለው ግንብ ሥር ተነሱ። ቴዎድሮስ ተነስተው መንገድ ሲጀምሩ በዚያ የነበረው ሕዝብ በሙሉ ተነስቶ ተከተላቸው። ይህም ነገር ለካህናትና ለጐንደር ከፍ ያለ መከራ እንደሚያመጣ የተገነዘቡት የአገር ሽማግሌዎች በቴዎድሮስ እግር ላይ ወድቀውና ለምነው መለሱዋቸው። ከጳጳሱና ከካህናትም ጋር አስታረቋቸው። ቴዎድሮስም ካህናት ፈሰስ እንዲገብሩና የዳኝነት ገቢ ለንጉሡ እንዲሆን ሌላው እንደጥንት እንዲያድሩ ብለው አወጁላቸው።

ወደ መኳንንቱ ብንመለስ ቴዎድሮስ ሁሉንም ተራ በተራ ለማስገበርና የከዳቸውንም ለመቅጣት ተዘጋጁ። በመጀመሪያም የላስታውን ዋግሹም ገብረ መድህን ለመምታት ከመነሳታቸው በፊት በግብር ላይ ለሚያዘምረው አዝማሪ

"ጐጃም ብንቆጣው በአባቱ ተቀጣ ፣
ወሎን ብንቆጣው በነፍጡ ተቀጣ ፤
ይብላኝ ለወራሄ ይብላኝ ለሰቆጣ"

ብለው ራሳቸው ግጥም ነገሩ። ከዚህም በኋላ ወደላስታ ተጓዙ። ዋግሹም ገብረ መድህንም ተጋጥመው ከተዋጉ በኋላ ዋግሹም ድል ሆነው ተማረኩ። ከአባቸውም ጋር ቢትወደድ ብሩና አባ ጫጉ የተባሉት የጦር መሪዎች ተያዙ። ቴዎድሮስም ሶስቱን መኳንንት አስረው ጦረኛውን የወጋቸውን ሠራዊት ግን ማሩት። መኳንንቶቹን ማለት ዋግሹም ገብረ መድህንን ፣ ቢትወደድ ብሩንና አባ ጫጉን ፣ ከጐጃም የተያዙትን እስኔ ደረሰን ፣ ጉለም ወልደሚካኤልን ፣ማሩ ሰሎሞንንና ሌሎች ሶስት ሰዎች በጠቅላላው ዘጠኝ መኳንንቶችን ረጅም ግራር ከሚባለው ሥፍራ በግንቦት ወር 1850 ዓ.ም. ለመቀጣጫ ብለው እጅና እግራቸውን እየቆረጡ ሰቀሉዋቸው። ቴዎድሮስ በስቅላት ብቻ ለመቀጣጫ ማድረጉ ሲበቃቸው ብዙውን ጊዜ ሰዎችን በስቅላት የሚገድሉት በመጀመሪያ እጅና

እግራቸውን ካስቆረጡ በኋላ ነበር ። ይህም ምሕረት የሌለውና ድርብርብ ቅጣታቸው በቴዎድሮስ ላይ ጠላት አበዛባቸው እንጂ አል ጠቀማቸውም ።

ወደፊት እንደምናነበው ይህን የቴዎድሮስን ጭካኔና መጥፎ አቀጣጥ የሚያዩትና የሚሰሙት ሚስታቸው እቴጌ ተዋበች ብዙውን ጊዜ ጭካኔያቸውን እንዲተውና ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲያድርባቸው ይመክሩዋቸው ነበር ። ቴዎድሮስ ግን የሚስታቸውን ምክር በሰላሙ ጊዜ ተቀብለው በንዴታቸው ጊዜ ይረሱታል ። ቢሆንም እቴጌ ተዋበች በሕይወት በነበሩበት ጊዜ የሚቀጡት ቅጣት እቴጌ ተዋበች ከሞቱ በኋላ እጅግ በጣም የተለየ የበረታ ቅጣት በመጀመራቸው ቴዎድሮስን በምክር ይዘዋቸው የነበሩት እቴጌ ተዋበች እንደነበሩ ሕዝቡ ሁሉ አወቀ ።

አጤ ቴዎድሮስ የከዱ ጠላቶቻቸውን ረጅም ግራር ከተባለው ሥፍራ ከሰቀሉ በኋላ ወደ ጎንደር ተመለሱ ። በሸዋ የሾሙዋቸው የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ አቤቶ ሰይፉ በቴዎድሮስ ላይ ሸፍተው ምሥራቅ ሸዋ ነፃ መውጣቱን አውጀው አንኮበር ተቀመጡ ። ይህን የሰሙት ቴዎድሮስም በግስጋሴ ወደሸዋ ዘመቱ ። አቤቶ ሰይፉም ሠራዊታቸውን ይዘው ሙቅምድር ከሚባለው ቦታ ጦርነት ተጀመረ ። ጦርነቱ እንደተጀመረ የሸዋ ሠራዊት በርትቶ በመዋጋቱ የቴዎድሮስ ጦር ወደ መሸነፉ አዘንብሎ ነበር ። በኋላም አቤቶ ሰይፉ ከቴዎድሮስ የተማረከ አንድ ሰው አስቀርበው ሲጠይቁ ዘማቹና ተዋጊው ቴዎድሮስ መሆናቸውን ነገራቸው ። አቤቶ ሰይፉ መጀመሪያ የተዋጉት የቴዎድሮስ ሹም ከሆነው ከአፀ በዛብህ ጋር መስሏቸው ነበር ። በኋላ ግን የቴዎድሮስን መኖር ሲሰሙ ከጦራቸው መሀል በድብቅ ወጥተው ሸ ሹ ። ሠራዊቱም የአለቃውን መሸሽ እንደሰማ እጁን ሰጠ ። አጤ ቴዎድሮስም ይህን የወጋቸውን ሠራዊት በጀግንነቱ አድንቀው 500 ያህል ሰዎችን ቀኝ እጃቸውንና ግራ እግራቸውን እየቆረጡ ጣሉዋቸው ። በዚህ ጊዜ አንዲት ባሏ የተቆረጠባት ሴት

“ አጤ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ ፣

የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነስተውት ሔዱ ” ብላ ገጠመች ። አጤ ቴዎድሮስ በሰላም እጁን የሰጠውን ሠራዊት እጅና እግሩን ይቁረጡት እንጅ የሸዋው ሠራዊትም ከእሳቸው ሠራዊት 1700 ያህል ወታደሮች ገድሎባቸዋል ።



ቴዎድሮስ ከሸዋ ድል በኋላ ወደ ጎንደር ተመለሱ ። ጥቂት ዕረፍት ካደረጉ በኋላ በወሎ ተበታትኖ የሸፈተባቸውን ባላባት ለማስገበር ከሚስታቸው ከእቴጌ ተዋበች ጋር ወደ ወሎ ጉዞ ጀመሩ ። እቴጌይቱም አሟቸው ነበርና አርብ ገበያ ከተባለው ሥፍራ ሲደርሱ ለመጓዝ አቃታቸው ። ከዚያ ጀምረው በአልጋ ላይ ተኝተው በሸክም ይጓዙ ጀመር ። ክረምት የመግቢያው ጊዜ ተቃርቦ ነበርና በሰኔ ወር ወደ መቅደላ ሲጓዙ እቴጌ ተዋበች በ1850 ዓ.ም ነሐሴ 13 ቀን ረቡዕ ማታ ግራኝ ሜዳ በተባለው ሥፍራ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ።

አጤ ቴዎድሮስም የሚስታቸውን ሬሳ ከግራኝ ሜዳ ወደ መቅደላ ለመውሰድ ጉዞ ጀመሩ ። ሠራዊታቸው ግን ጥቂት እንደተጓዘ በክረምት ውሃ ሙላት ሊያስወስዱን ነው እያለ አንጐራጐረ ። ቴዎድሮስም ይህን ሰምተው የእቴጌ ተዋበችን ሬሳ ከሠፈር አስመልሰው በሣጥን አድርገው ይዘውት የሚዞሩት ታቦት ካለበት ድንኳን ውስጥ አስቀመጡት ። አጤ ቴዎድሮስ ሚስታቸውን እቴጌ ተዋበችን በጣም ይወዱዋቸው ነበርና ከታመሙበት ጊዜ ጀምሮ ለሚስታቸው ጸሎት ይዘው አዳራቸው ከቤተ ክርስቲያን ነበር ። ምግባቸውም ሽንብራ ብቻ እንደነበረ የቅርብ ታሪክ ፀሐፊያቸው ደብተራ ዘነበ ጽፈዋል ።

አጤ ቴዎድሮስ ክረምቱ ሲወጣ የሚስታቸውን ሬሳ በሣጥን አስይዘው ደሴ ገቡ ። ሬሳውን ከደሴ አኑረው የሸፈተባቸውን አመዴ በሽርን ለመውጋት ወደ እርቄ ሔዱ ። አመዴ በሽርም የንጉሡን መምጣት ሰምተው ሸሹ ። ከዚያ ተመልሰው ተሁለደሬን ዘረፉት ። ቴዎድሮስ ተሁለደሬን ሲያዘርፉ ጎንደር በሽፍታ ተያዘ የሚሉ ወሬ መጣላቸው ። ደሴ ከሚስታቸው ሬሳ ዘንድ አቡኑንና እጨጌውን ፣ ግራዝማች ዓለሜንና ሌሎች የጦር መሪዎችን ትተው እሳቸው ጥቂት የዋድላን ጦር ይዘው ወደ ጎንደር ተመለሱ ። ጎንደርን ይዘው የነበሩት ሽፍቶችም የንጉሡን መምጣት ሲሰሙ ሸሹ ። ከዚያም በግስጋሴ ተመልሰው የወሎው አመዴ በሽር ሠራዊቱን ይዞ ቢፈታ ከተባለ ቦታ መስለፉን ሰምተው በጥቅምት ወር 1851 ዓ.ም. ደረሱበት ። አመዴ በሽርም የንጉሡን መምጣት ሲሰማ ሐተላ ወደ ተባለ አገር ሸሽቶ ሔደ ። ቴዎድሮስም ተከታትለው ቢሔዱ አመዴ በሽር ኩሉ ወደተባለ ሥፍራ ሸሽቶ አመለጠ ቴዎድሮስ ግን ባላገሩን ያለርህራሄ ፈጁት ።



የእቴጌ ጥሩ ወርቅ ሥርዓተ ቀብር



ቴዎድሮስ የሚስታቸውን ሬሳ ሳያስቀብሩ በድንኳን ውስጥ ማጥን አስቀምጠው ሁለት ወር ያህል እየተዘዋወሩ ከተዋጉ በኋላ ጥቅምት 11 ቀን 1851 ዓ.ም. የሚስታቸውን ሬሳ ግሼን አስወጥተው አስቀበሩ ።

አጤ ቴዎድሮስ የሚወዷቸውን የሚስታቸውን አስከሬን ግሼን ካስቀበሩ በኋላ ወደ በጌምድር ተመልሰው በንዘን ተቀም ጠው ሳሉ የደጃዝማች ከንፉ ልጅ ደጃች ጋረድ ሸፈተባቸው ። ጋረድ አገር እየዘረፉና ሰው እየገደሉ አስቸገሩ ። ጋረድ በሸፈቱበት ጊዜ የአጤ ቴዎድሮስ ታማኝ ወዳጃቸውንና በኢትዮጵያ የእንግ ሊዝ መንግሥት ቆንሲል የነበረው ፕላውዴን ወደ እንግሊዝ አገር ለመሔድ ከቴዎድሮስ ተሰናብቶ ጉዞ ጀመረ ። የካቲት 25 ቀን 1852 ዓ.ም. ጐንደር ከተማ አካባቢ ቀሃ ወንዝ አጠገብ ሲደርስ የደጃች ጋረድ ሰዎች በጦር ደረቱ ላይ ወግተው ያዙት ። ይህንንም ቴዎድ ሮስ እንደሰሙ ሕይወቱን ለማዳን ብለው አንድ ሺ ብር ለጠላታ ቸው ለጋረድ ከፍለው ቁስለኛውን ወዳጃቸውን ፕላውዴንን አስለ ቀቁ ። ፕላውዴንም በቃሬዛ ሆኖ ሰዎች ተሸከመውት ወደ ጐን ደር መጣ ። በጦር የተወጋው ቁስሉ ከፍተኛ ነበርና ፕላውዴን ጐን ደር በደረሰ በዘጠኝ ቀኑ በተወለደ በ40 ዓመቱ ሞተ ።

የወዳጃቸውን የፕላውዴንን ሬሳ በታላቅ ስነ ሥርዓትና ክብር በጐንደር ከተማ ካስቀበሩ በኋላ ደሙን ለመበቀል ሠራዊታቸውን አስከትተው ወደ ጋረድ ዘመቱ ። ደባርቅ ከሚባለው አካባቢ ጦር ነቱ ተጀመረ ። ጦርነቱ ተፋፍሞ ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰዎች ወደቁ በዚህ መሀል ደጃች ጋረድ አጤ ቴዎድሮስን ነጥለው ለመግደል እያደቡ ሲደርሱ አጤ ቴዎድሮስ አጠገብ ቤል ዮሐንስ የተባለው እንግሊዛዊ ነበርና ጋረድን በጠመንጃ መትቶ ጣላቸው ። ጋረድ ወዲያውኑ ሲሞቱ ይህን ያየው የጋረድ ወንድም ደግሞ የወንድ ሙን ገዳይ ሊቀ መኳስ ቤልን ወዲያውኑ ገደለው ። አጤ ቴዎድ ሮስ ደግሞ የወዳጃቸውን የሊቀ መኳስ ቤልን ገዳይ የጋረድን ወን ድም ገደሉ ። ይህ ከሆነ በኋላ የጌታውን መሞት ያወቀው የጋረድ ሠራዊት መሸሽ ሲጀምር የቴዎድሮስ ሠራዊት እያባረረ ይገድልና ይማርክ ጀመር ። ከሞተው በስተቀርም 1500 ያህል የጋረድ ሰዎች ተማረኩ ። አጤ ቴዎድሮስም ይህን የተማረከውን ሠራዊት ከደባ ርቅ ከተማ አስገብተው በሙሉ አስገደሉዋቸው ። ማስገደሉ ብቻ ሳይበቃቸውም ጭንቅላቱን እያስቆረጡ እንደ ካብ እንዲካብ አዘዙ ። ጭንቅላቱ በሚካብበት ጊዜም እየተቆጠረ ስለተካበ 1500 ጭን

ቅላት ተቆጥሮ መካቡን አለቃ ወልደ ማርያምና አለቃ ተክለ ኢየሱስ ጽፈዋል ።

አጤ ቴዎድሮስ ደጃች ጋረድን ድል ካደረጉ በኋላ ሌላውን ሽፍታ ደጃች ብሩ ጎይሉን ሊወጉ ወደ ጣና ሔዱ ። ብሩ ጎይሉ ጣና ሐይቅ ደሴት ውስጥ ገብተው ቴዎድሮስ ሲርቁ እየወጡ እየዘረፉ ፣ ቴዎድሮስ ወደ አካባቢያቸው ሲቀርቡ ደግሞ ከደሴት እየገቡ አስቸግረው ነበር ። በዚህ ድርጊት ቴዎድሮስ በጣም ይናደዱና ይበሳጩ ነበር ። በአሁኑ ጊዜ ቴዎድሮስ ብሩ ጎይሉ የሚያዙበትን ብልሃት አዘጋጅተው ወደ ጣና ዘመቱ ። በጣና አካባቢ ያሉትን ጀልባዎች ሁሉ ሰብስበው በ500 ጀልባዎች ሠራዊታቸውን ገመድ ጦርና ጐራዴ እያስያዙ በየጀልባው ላይ አሳፈሩት ። የብሩ ጎይሉም ሠራዊት በየጀልባው እየሆነ ወደ መጣበት ጠላት ወደ ቴዎድሮስ ሠራዊት ተጓዘ ። የሁለቱም ሠራዊት በባሕር ላይ ተገናኝቶ ውጊያ ጀመረ ። የቴዎድሮስ ሠራዊት እንደተመከረውና እንዳጠናው በጦሩ ላይ ገመድ እያሰረ ጦሩን ወርውሮ የጠላቱን ጀልባ ይወጋል ። ጀልባው በጦር ሲወጋ ገመዱን እየጐተተ ጀልባውን ከነሰዎቹ በማቅረብ በጦርና በጐራዴ እየደበደበ የብሩ ጎይሉን ሠራዊት በዚህ ዓይነት ዘዴ ፈጀው ። ብሩ ጎይሉም ድል ሆነው ተያዙ ።

አጤ ቴዎድሮስ በአሁኑ ጊዜ የቀራቸው ኃይለኛውና ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር የወዳጅነት ውል እየተዋዋሉ ያስቸገሩዋቸው የትግራዩ ደጃዝማች ንጉሤ ናቸው ። ደጃዝማች ንጉሤ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ እያሳደሙ ከውጭ አገር መንግሥት ጋር እንዴት ይዋዋሉ እንደነበረ ወደፊት በምዕራፍ 6 ውስጥ በሚነበበው በደጃች ንጉሤ ታሪክ ውስጥ ያገኙታል ።

አጤ ቴዎድሮስ ደጃች ንጉሤን ለማጥፋት እየደጋገሙ ቢዘምቱም ሊያገኙዋቸው አልቻሉም ። የደጃች ንጉሤን ከፈረንሳይና ከኢጣሊያ መንግሥታት ጋር አገር ቆርሶ የሚሰጥ ውል መዋዋላቸው አጤ ቴዎድሮስ እንደሰሙ ይህ ውል በሥራ ላይ ሳይውል ለማጥፋት በማስጋሴ ተጉዘው ትግራይ ገቡ ። የአጤ ቴዎድሮስ በድንገት መምጣት እንደተሰማም በትግራይ ሕዝብ ዘንድ ድንጋጤን ፈጠረ ። ደጃዝማች ንጉሤንም ከፈረንጆቹ በተሰጣቸው ተስፋ ተማምነው ለጊዜው ባላቸው መሣሪያና ሠራዊት ቴዎድሮስን ለመጣም አክሱም አጠገብ ሳጋሞ (?) ከተባለ ቦታ ሠራዊታቸውን አሰልፈው ቴዎድሮስ ጠበቋቸው ። አጤ ቴዎድሮስም ከቦታው ደርሰው ጊዜው መሽቶ ነበርና የሁለቱም ሠራዊት ፊት ለፊት ተሰላልፎ ለበነጋታው ውጊያ አሰፍስፎ ይጠባበቅ ጀመር ።



ከአጤ ቴዎድሮስ ሠራዊት መሀል ሰባኪዎች ወጥተው ከደጃች ንጉሤ ሠፈር በስውር ገቡ ። እንደገቡም "ንጉሡ አጤ ቴዎድሮስ እናንተን ወታደሮቹን ምረዋችኋል ። ድሮም ቢሆን በግድ ታዛችሁ የወጣችሁ በመሆናችሁ በእናንተ ላይ ቂም የለም ብለዋልና ወደ ንጉስ ሠፈር በሰላም ግቡ" እያሉ ሰበኩ ። ይህን የሰሙት የደጃች ንጉሤ ወታደሮችም ሌሊቱኑ ከደጃች ንጉሤ ሠፈር እየከዱ ወደ ቴዎድሮስ ገቡ ።

ደጃች ንጉሤ በማግስቱ ሠራዊታቸው እየከዳ መሔዱን ሰምተው አዘኑ ። በተረፉቸው ሠራዊትም ቴዎድሮስን ለመግጠም እንደማይችሉ ገምተው ወደ ቴምቤን ተራራ ሸሹ ። አጤ ቴዎድሮስም ተከታትለው ደረሱባቸውና ጥቂት ውጊያ ከተደረገ በኋላ ንጉሤ ድል ሆነው ተማረኩ ። አጤ ቴዎድሮስም ደጃች ንጉሤንና ወንድማቸውን ሌላውንም ተባባሪ መኳንንት ሁሉ እጅና እግሩን እየቆረጡ ጣሉዋቸው ። አለቃ ወልደ ማርያም ከድሉ በኋላ ስለነበረው ወይም ስለ ደጃች ንጉሤ አሟሟት ሁኔታ ሲፅፉ ". . . .ከወደቁበት አህል ውሃ የሚሰጥ አልነበረምና ውሃ ጥም ቢጠናበት አገው ንጉሤ ይህን የወርቅ ድሪዬን ሰጥቼ አንድ ዋንጫ ውሃ ባገኘሁ ብሎ ተመኘ ። ወንድሙም ሰምቶ ላትተርፍ ምን ያደክምሃል ብሎት ወዲያው ሁለቱም ሞቱ ። እንዲህም በተደረገ ጊዜ ንጉሡ እጅግ ደስታ አድርገው በምገዛው አገር ሁሉ ያልዘፈነልኝ ጠላቴ ነው ብለው አዋጅ ነገሩ ። በዚህም አዋጅ ቃል እሰይ ንጉሡን ቀናዎ እያለ ያልዘፈነ የለም . . ." ብለዋል ።

እርግጥ ደስ የሚያሰኝና የሚያዘፍንም ነበር ። ምክንያቱም ቴዎድሮስ ከተነሱባቸው ጠላቶች ሁሉ ከውጭ መንግሥት ጋር ተዋውሎ የውጭ ጦር ሊያመጡባቸው የተዘጋጁት አገው(ደጃች) ንጉሤ ነበሩ ። ሌላው ምክንያት ደግሞ የግል ጠላታቸውን ወይም የሥልጣን ተቀናቃኛቸውን ለመጣል በማሰብ ለውጭ አገር መንግሥት አገር ቆርሶ መስጠት በአገር ላይ የሚፈጸም ትልቅ በደል ስለሆነ ነው ።

አጤ ቴዎድሮስ አገው ንጉሤን ድል አድርገው በታላቅ ደስታ ወደ ጐንደር ሲመለሱ ከደጃች ውቤ ደብር ደረስጌ ላይ ሠፈር አደረጉ ። በዚያም ሠፈር አድርገው ሳለ አንድ ወታደር የደጃች ውቤን

ልጅ ወጣትዋን ጥሩነሽን አየ ። ያም ወታደር በጥሩነሽ ውበት ተደ ንቆ ወደ አጤ ቴዎድሮስ መጥቶ "ጃንሆይ ለእርስዎ ለንጉስ የተገባች መልካ እንደፀሐይ የምታበራ ሴት አገኘሁ" ብሎ ነገራቸው ። አጤ ቴዎድሮስም ደህና ደፀና ሰዎች ልከው ጥሩነሽን አስመጥተው ሲያዩ በውበቷ ደነገጡ ። እንደ አሊቃ ወልደ ማርያም አጻጻፍ ከእ ግር እስከ ራስ ቆጥረው አይተው ይህቺስ ጥሩ ወርቅ ናት አሉ ከዚህ በኋላ በሕግ አገቡዋቸው ። ስማቸውም ጥሩነሽ መሆኑ ቀርቶ ቴዎድሮስ ባወጡት ጥሩ ወርቅ ተባለ ።



ምዕራፍ 6

# ደጃች ተድላ ጓሉ አቡነ ሰላማ ወይዘሮ ተዋበች አሊ ፕላውዴን ዮሐንስ ቤልና ደጃች ንጉሤ

## ተድላ ጓሉ

ተድላ ጓሉ የራስ መርድ የልጅ ልጅ ናቸው ። ደጃች ብሩ በጐጃም ሆነው ስማንኛውም መስፍን ወይም የበላይ ነኝ ባይ እል ገብርም እያሉ በተቀመጡበት ጊዜ አንድ መነኩሴ "አልጋህን የሚወርሰው ተድላ ጓሉ ነው" ብሎ ነገራቸው ። ያንጊዜ ተድላ ጓሉ ደረበጌ ይማሩ ነበር ። የመነኩሴውን ትንቢት የሰሙት ደጃች ብሩ ከደረበጌ ትምህርት ቤት ተድላ ጓሉን አስይዘው ጳሚ ጨርቅ በሚ ባል እምባ እሠሩዋቸው ።

ተድላ ጓሉ እንደታሠሩ ያ በፊት ትንቢት የተናገረው መነ ኩሴ ወደ ደጃች ብሩ ዘንድ መጥቶ "ብታስረውም ፣ ብትገርፈውም የክርስቶስ ትእዛዝ አይቀርምና ይልቅ ፍታው" ብሎ ነገራቸው ። ደጃች ብሩም ተድላ ጓሉን ፈትተው "እኔ በምገዛበት አገር እንዳ ትቀመጥ" ብለው አባረሩዋቸው ። ተድላ ጓሉም ወደ አማራ ሳዳ ንት ሔደው ከደጃች ትኩ ዘንድ አሽከርነት ገቡ ። ይህን ነገር ደጃች ብሩ እንደሰሙ "ጠላቴን ደብቀህ እኑረሃል አሉ ። እሺ ብትል አባረው ፣ እምቢ ብትል ታጠቅ መጣሁ" ብለው ለደጃች ትኩ ላኩባቸው ። ደጃች ትኩም ፈርተው ተድላ ጓሉን አባረሩዋ ቸው ።

ተድላ ጓሉ ወደ ደራ ሔዱ ። ደራ ሔደውም ከኦሮሞዎቹ ከነ ቦሩ ቱሬ ዘንድ ገቡ ። ደጃች ብሩም ይህን ሲሰሙ የፊተኛውን ዓይ ነት የማስፈራሪያ ቃል ለቦሩ ቱሬ ላኩ ። ቦሩ ቱሬም ፈርቶ ተድላ ጓሉን ከባላባትነቱ ግዛት ውስጥ አባረረ ።

ተድላ ጓሉ ወደ ጃርሶ ሔዱ ። ከጃርሶም ከኦሮሞው ባላባት ከነገዎ ገመዳ ዘንድ ገቡ ። ይህን የተድላ ጓሉን ጃርሶ መግባትና

ነገዎ ገመዳ ዘንድ መጠጋታቸውን ደጃች ብሩ ሲሰሙ ያንኑ የማስፈራሪያ ቃል ለነገዎ ገመዳ ላኩበት ። ነገዎም የተድላ ጓሉን ጉዳይ ሲያጠና ደጃች ብሩ የሚያባሩዋቸው ንግርት ስላለ መሆኑን አጠና ። ነገዎ ገመዳ ጉልበት ያለውና እንደ ደጃች ብሩ ሁሉ ትዕቢተኛ ነበርና ደጃች ብሩ ለላኩበት መልከት "አትችለኝምና አትምጣ ። ግድ ያለህ እንደሆነ የምትወደውን ፣ የምታምነውን ሎሌህን አስቀድመህ ሰደህ የሠራዊቴን ብዛት የልቤን ብርታት አሰልለህ ናብኝ ። ብሎ መልሱን ላከ ።

ደጃች ብሩ መልሱን እንደሰሙ ወደ ነገዎ ገመዳ አገር ሰላይ ወይም ተመልካች ላኩ ። ነገዎ ገመዳም የተመልካቹን መምጣት እንዳወቀ የሰላሌንና የጃርሶን አሮሞ በሙሉ በሜዳ ላይ አሰልፎ ጉግስ ጨዋታ በማስመሰል የፈረሱን ፣ የጦሩን ብዛትና አወራወር አሳየ ። ከደጃች ብሩ የተላከው ሰላይ ተመልሶ "አንችለውምና እንቅር" ብሎ ነበረ ። ደጃች ብሩም "እኔ የዳምጠው ጌታ የጋላ ፈረስ ነወይ ከፊቴ የሚቆም ? ቂጥ ለቂጥ ነው የማማታው" ብለው ፎከሩ ። የጐጃም መኳንንቶችም "አሳዳጅ አስከ ደጅ አንሁን በከንቱ ሰዎቻችን አይለቁ" በማለት መከረው ደጃች ብሩን ከውጊያው አስቀሩ ።

ተድላ ጓሉ ከነገዎ ዘንድ ከከረሙ በኋላ ደጀን ካሉት ዘመዶቻቸው ጋር መላላክ ጀመሩ ። ከዘመዶቻቸውም መልካም ምላሽ እንዳገኙ ነገዎ ዘንድ ቀርበው "አገሬ ናፈቀኝ ። ዘመዶቼን ለማየት ልሂድ" ብለው ፈቃድ ጠየቁ ። ነገዎም በአሳቡ ተስማምቶ አስከ አባይ ወንዝ ድረስ በሸኚ አደረሳቸው ፣ ተድላ ጓሉ ከዘመዶቻቸው አገር አሳይ ዳርቻ ቢደርሱም የቆሳው ሕዝብ ደጃች ብሩን ፈርቶ ተድላ ጓሉ እንዳይገቡ ከለከለ ። በዚህም ምክንያት ቆለኛና ደገኞቹ ተጣሉ ። በረብሻውና በግልግሉ መሀል የቅርብ ዘመዶቻቸው ተድላ ጓሉን በድብቅ ወስደው ፊታውራሪ ፀጋ ቤት አስቀመጡዋቸው ። ይህም ነገር ሚስጥሩ እያፈተለከ የተድላ ጓሉ መደበቅ ተሰማ ። አድገህ ንጉሤ የሚባሉት ሰው ከሳሽ ሆነው ተነስተው "የደጃች ብሩን ጠላት ደብቀህ አኑረሃል" ብለው ፊታውራሪ ፀጋን ከስሰው ስለረቱ አንድ ሺ አሞሌ ጨው እንዲከፍሉ ተበየነባቸው ። ፊታውራሪ ፀጋም የተፈረደባቸውን ቅጣት በሙሉ ከፈሉ ። በዚህም ጊዜ በደጃች ብሩ ላይ ራስ አሊ ጦር ስላወጁባቸው የተድላ ጓሉ ጉዳይ ቀዘቀዘ ።



ደጃች ብሩ ከደጃች ካሣ (ቴዎድሮስ) ጋር ተዋግተው ድል ሆነው መያዛቸውን ተድላ ጓሉ ሲሰሙ ከተደበቁበት ከደጀን ወጥተው ለደጃች ካሣ አሽከርነት ገቡ ። ቅድም እንደተባለው ደጃች ካሣም የደጃች ጓሉ ልጅ መሆናቸውን ባወቁ ጊዜ የጐጃም ጦር አዛዥ አድርገው ሾሙዋቸው ። በበላያቸው ግን ባላምባራስ ወልታን የጐጃም ምስለኔ ብለው ሾሙ ።

ተድላ ጓሉ በሰላም መኖር እንደጀመሩ በፊት እንደተባለው አዝማሪው ሊቀ መኳስ መርሻ በገጠሙላቸው ግጥም ምክንያት በካሣ ላይ ሸፈቱ ። መንቆረር (በዛሬው ደብረ ማርቆስ) ላይ ሆነው ራሳቸውን ደጃዝማች ብለው ደጃች ካሣ የሾሙዋቸውን ሰዎች እየሻሩ የእሳቸውን ወገኖች ይሾሙ ጀመር ።

የተድላ ጓሉን ሹም ሽር አንዳንዱ የጐጃም ክፍል አልቀበል አለ ። ተድላ ጓሉ በበረንታና ሸበል ላይ የሾሙዋቸው ፊታውራሪ ወንድ አወክ የተባሉትን ነበር ። ሕዝቡ ግን አንቀበልም ብሎ ባንድነት ተነስቶ ፊታውራሪ ወንድ አወክን አባሮ ጋትአነስ ከተባለው ቦታ አድርሷቸው ተመለሰ ሲመለስም ።

"ስርጉደው ስርጉደው ስርጉደው በጨሬ ፣
ግድ ብሎ ተመጣ ባገሬ ።
ፊታውራሪ ወንድ አወክ የጨስ ጨው ወዳጅ ፣
የጐበዝ ሚስት ወዳጁ ፣
አፈረሰው አፈረሰው በጁ" እያለ ጨፈረ ።

ግጥሙ ፊታውራሪ ወንድ አወክ እንደተሾሙ በሕዝቡ ላይ የጨስ ጨው ግብር እንዲከፍል አውጀውበት ስለነበርና የሰው ሚስት መቀማት በመጀመራቸው የተገጠመባቸው ነው ። የጨስ ጨው ማለት በመኖሪያ ቤት ሁሉ አንዳንድ አሞሌ ጨው ግብር መቀበል ወይም መክፈል ነው ። ተድላ ጓሉ ለጉብያ ሕዝብ ደግሞ ኃይሌ ወልደዮሐንስን ሾመው ነበርና የዚያም አገር ሕዝብ አንቀበልም ብሎ ኃይሌ ወልደዮሐንስን አባረረ ። በተራውም

" እንደ ሊበን እንደ ኮሳሴ
እኛ አንከፍልም ፈሰሴ " እያለ ዘፈነ ። ፈሰሴ ግብር ነው ። በደጀን ሕዝብ ላይ የተሾሙት ደግሞ ባላምባራስ አድገህ ንጉሤ ነበሩ ። የደጀን ሕዝብ በባላምባራስ ላይ አድሞ ተነስቶ አባረራቸው በእሳቸውም ላይ

"ያውለኛል ፣ ያውለኛል ጦሬ ፣
አድገህ ንጉሴ የተድላ ጓሉ አትድረስ ባገሬ

እንደቅማቱ እንደ እያቱ
ደጀን ነው ሞቱ ” እያለ ዘፈነ ። ይህን ሁሉ የሰ
ሙት ደጃዝማች ተድላ ጓሉ ተናደዱ ። መጀመሪያም በበረንታና
ሸበል ላይ ዘመቱ ። የበረንታና ሸበል ቀለኞችም ተሰባስበው ሜን
ፈቆ በተባለ ሜዳ ላይ ከተድላ ጓሉ ጋር ተጋጥመው ተድላ ጓሉ
ድል አደረጉ ። በዚህም ጦርነት ላይ የተማረከውን ሁሉ ተድላ ጓሉ
ቀኝ እጁንና ግራ ጆሮውን እያስቈረጡ ለቀቁት ። የተድላ ጓሉ
ወታደርም ብድሩን ለመመለስ ሲዘፍን

“ ሰርጉድ በርጉድ ብሎ ሰርጉድ መነመኑ ፣
ቀኝ እጁን ገብሮ በግራው ለመኑ ” እያለ በተራው በበረንታና
በሸበል ሕዝብ ላይ ዘፈነበት ። ተድላ ጓሉም ከዚያ አልፈው በረጭ
በሚባል ቦታ ሠፍረው የጉብያን ሕዝብ “ ግባ ” ብለው አወጁ ።
የጉብያ ሕዝብም በበረንታ ላይ የደረሰውን ያውቃልና በጥሪው
መሰረት በብዛት ተሰልፎ

“ ቢገዛን መች ጠላሁ የራስ ኃይሉ ልጅ
የኋላውን ካማ ብፈራው ነው እንጂ ” እያለ እየዘፈነ ገባ
ታላቁ ራስ ኃይሉ የተድላ ጓሉ እያት ናቸው ። ደጃች ተድላም የጉ
ቢያን ሕዝብ በሰላም ካስገበሩ በኋላ ወንታ ሔደው ሰፈሩ ። በዚ
ያም ሆነው የደጀንን ሕዝብ ግባ ብለው ላኩበት ። የደጀንም ሕዝብ
በበረንታና ሸበል የደረሰውን ሰምቷልና በነቂስ ወጥቶ ገበረላ
ቸው ። ቆታር ከተባለ ሠፈር ሲደርሱም የጁቤና የገሞ ሕዝብ በሕ
ብረት ሆኖ ወጋቸው ። ደጃች ተድላ ድል አደረጉ ። ከዚያም ምር
ኮኛ አሰባስበው በሙሉ ገርፈው ለቀቋቸው ።

ቀረር ኤውስጣጤዎስ በተባለው እምባ የአሞራው ኃይሉ
ልጆች ፣ የደጃዝማች ዘውዴ የአጐት ልጆች ዶሪ ኃይሉ ፣ ጀምበሬ
ኃይሉ ፣ ወሌ ኃይሉ የሚባሉ ጀግኖች ነበሩና ተድላ ጓሉ ደንበጫ
ላይ ሠፍረው “ እታመልጡኝምና ግቡልኝ ” ብለው ላኩባቸው ።
መልዕክተኛው ፊርሶ ይህን መልዕክት ሲነግር ዶሪ ኃይሉ ተነስቶ
ፎከረ ። ወዲያውም አቅራሪ አስጠርቶ

“ ላሚቱ አንበሳ ፣ ጥጃውም ትኩላ ነው ፣
አላቢዋ ዘንዶ ጋሻውም እባብ ነው ፣
ቀጨሞን ተሻግሮ መካሪው ሰው ማነው ” ብሎ
ግጥም ገጠመ ። ጋሻ ማለት ላሞች ሲታለቡ እግራቸው የሚታሠር
በት ጠፍር ነው ። የዶሪ ኃይሉን ግጥም የሰሙት የዶሪ ኃይሉ
እግቾች የሆኑት ጀግናው ጓሉ አደሩ የተባሉት ደግሞ



ከተምጨ ወዲህ እንዳትሻገሩ ፣
አፋው ነብር ነው የጓሉ አደሩ ፣
እንደ ዶጋን ምት ካንገት ካንገቱ ፣
የጓሉ አደሩ ባፉ እመታቱ ። እያሉ ግጥም ነገሩ ።
ባፉ ማለት የጉራዴ ስም ነው ። ይህን ቀረርቶ ከአባባቂ የሰ
ሙት ተድላ ጓሉ ፎክረው ዘመቱባቸው ። ዶሪ ኃይሉም በተ
ድላ ጓሉ ሠራዊት ላይ ሌሊት አደጋ ጥለው ብዙ ሰው ፈጅ
ተው እሳቸውም በዚያው በጦሩ ሜዳ ሞቱ ። ወንድሞቻቸው
ጀንበሬ ኃይሉና ወሌ ኃይሉ ግን አመለጡ ። ደጃዝማች ተድላም
የዶሪ ኃይሉን ሬሳ እንዳይቀበር ከልክለው ከመንገድ ላይ ተጥሎ
ሕዝብ እንዲያየው አደረጉ ።

ይህን የሰሙት የዶሪ ኃይሉ ሚስትም
“ ተውት አትቅበሩት ይኑር ከመንገዱ
ምን ወንዝ አብቅሎታል እያሉ ይሂዱ ” ብለው
እንጉራጉሩ ። እገው ያሉት የዶሪ ኃይሉ ወንድሞች የወንድማቸ
ውን ድል መሆንና እሟሟት ሰምተው በእገው ውስጥ ተፈሩና
ታዋቂ የሆነውን ሽፍታ አቶ እርጥቦ ወልደ አምላክ የሚባለውን
በገንዘብ ገዝተውና ሌላም ኃይል ጨምረው ተድላ ጓሉን ሊወጉ
ተጓዙ ። የፎዳ ከሚባለው ሥፍራ ላይም ከደጃች ተድላ ሠራዊት
ጋር ጦርነት ገጥመው ተድላ ጓሉ ድል አደረጉ ። አዝማሪው
“ እገው የወቁትን ያንን መብላት ትተው ፣
እርጥቡን አጨዱት ደጃዝማች ቸኩለው ። ”
ብሎ ገጠመላቸው ።

ተድላ ጓሉ መንቆረር ተመልሰው ቤት ያሠሩ ጀመር ። ወታ
ደራቸው ግን ባለመሸለሙና ባለመሾሙ ቅሬታ ተሰምቶት በያለ
በት ያማቸው ጀመር ። የወታደራቸውን ማጉረምረም የሰሙት
ደጃች ተድላም በግብር ላይ ለቆመው አዝማሪ
“ አታንገራግር ወታደር ፣
መልአክ በፈታው ጦር ” ብለው ግጥም ነገሩ ።
ይህም ቢሆን ደጃች ተድላ በወታደር እያያዛቸውና በግብር እበላላ
ቸው ሠራዊቱ ይወዳቸው ስለነበር በጉጃም ላይ ተንበራፍተው
መቀመጥ ጀመሩ ።

አጤ ቴዎድሮስ ሸዋን ወግተው ወደ ጐንደር ለመመለስ አባ
ይን ሲሻገሩ ተድላ ጓሉ ከመንቆረር ወጥተው ከምሽጋቸው ገቡ

ቴዎድሮስም ጅብላንብሬ ተድላ ጓሉን ሳልይዝ አልሔድም ብለው መንቀረር ላይ ሠፈር አደረጉ ። የጅብላ ምሽግም ባለመሰበሩ ቴዎድሮስ በአገሩ ላይ ራስ እንግዳን ሾመው ጐንደር ገቡ

ቅድም እንዳነበብነው ቴዎድሮስ ራስ እንግዳን ሽረው ለጐጃም ራስ ውቤን ሾሙ ። ቴዎድሮስ ራስ ውቤን ይዘው ወደ ጐጃም ሔደው ግዛቱን አደላድለው ተድላ ጓሉን ለመያዝ መንገድ ሲጀምሩ የእንግሊዙ መልዕክተኛ ሚስተር ራሳም በመምጣቱ ቀሩ ።

የደጃች ጐሹ ልጅ ደጃች ተሰማ አርባ አምባ ከሚባል ቦታ ታስረው ነበርና ልጃቸውን አዳልን አደራ ሰጥቼሃለሁ ብለው ለደጃች ተድላ ላኩባቸው ። ልጅ አዳል በኋላ በአጤ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተባሉት ናቸው ። ደጃች ተድላም ልጅ አዳልን ተቀብለው ከልጃቸው ከንጉሤ ጋር ይማር ብለው ጅብላ አስቀመጡዋቸው ። በጅብላም ከሊቀ ካህናት ወርቄ ዘንድ እየተማሩ ዳዊት ከደገሙ በኋላ ከደጃች ተድላ ቤት መኖር ጀመሩ ።

ደጃች ተድላ ወይዘሮ ጉዳዩ የተባሉት ቁባት (ውሽማ) አሉዋቸው ። ልጅ አዳል ዕድሜያቸው ከጉርምስና ሲደርስ ተሸሽገው ከወይዘሮ ጉዳዩ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈፀሙ ። ደጃች ተድላም ሰምተው ተቆጡ ። ሲያስሩዋቸው ሲሉም ይህን ሐሳባቸውን የሰማ ፈንታ ወዳጆ የሚባል ሰው ልጅ አዳል ዘንድ ሔዶ “ ልጅ አዳል ነህ እንዴ ? ምነው እስታሁን ? እረ ወዴያ ፣ እረ ወዴያ ” እያለ ተናገረ ። ልጅ አዳልም ፈንታ ወዳጆ እንዲሸሹ መምከሩ መሆኑ ገብቷቸው ያሏቸውን አሽከሮች አስከትለው ከደጃች ተድላ ቤት ጠፍተው ሔዱ ። ጠለዛም ከሚባል አገር ገብተው ከብላታ ከብረ አብ ዘንድ ተቀመጡ

ከብላታ ከብረ አብ ቤት የተቀመጡት በግልጽ ሳይሆን ቀን ቀን ከጫካ እየዋሉ ማታ ለእዳራቸው ከብላታ ቤት ያድሩ ነበር ። ወይዘሮ ጉዳዩንም ደጃች ተድላ ገርፈው ብዙ ሥቃይ አሳዩዋቸው ። ልጅ አዳልንም ሲያስፈልጉ አጡዋቸው ። ደጃች ተድላ የሸፈቱባቸውን ግላቴ ኮልባንና ተሰማ ደረሶን ሊይዙ ወደ ሜጫ ዘመቱ ። የደጃች ተድላን መዝመት ልጅ አዳል ሲሰሙ የጓደኛ አሽከሮቻቸውን መርሻ ፀዳሉንና ተሰማ አሉላን ፣ አጽቂ ደረሶን ፣ መሸሻ እንግዳን ወደ መንቀረር ላከው ወይዘሮ ጉዳዩን አስመጡ ። ጉዳዩን በእጃቸው ካደረጉ በኋላ የደጃች ተድላን ከተማ መንቀረርን አቃጠሉት ።



ደጃች ተድላም የከተማቸውን መቃጠል ፣የቁባታቸውን መወሰድ ሲሰሙ ተናደዱ ። ዘራፊዎቹ ያሉበትንም ቦታ ሲጠያይቁ ደግሞ በረሃ መሆናቸውን አወቁ ። ከሜጫ ተነስተው በደጋ ዳሞት ወጥተው በደገም ጫካ ውስጥ ወራሪ(ቀዳሚ ጦር) ሰደዱበት ። ልጅ አዳልና ወይዘሮ ጉዳዩ ሲያመልጡ ተሰማ አሉላ ግን ዝንብል ከሚባል ደን ውስጥ እንደተደበቁ ተያዙ ። ደጃች ተድላ ፣ ተሰማ አሉላን ሀብትና ንብረት በሙሉ ከወረሱ በኋላ “ ከተማዬን ባቃጠልህበት ፣ እቁባቴን በወሰድህበት ተፋረደኝ ” ብለው የተለያየ ፍርድ አስፈረዱባቸው ፣ ደጃች ተድላ ግን ገርፈው ጅብላ አሰሩዋቸው ። ወይዘሮ ጉዳዩ ከልጅ አዳል ከበፊቱ በስርቆሹ ጊዜ ፀንሰው ነበርና ወንድ ልጅ ወለዱ ። የተወለደው ልጅ በዛብህ ተባለ በዛብህ በኋለኛ ዘመን ራስ በዛብህ የተባሉት የራስ ኃይሉ ታላቅ ወንድም ናቸው ።

ደጃዝማች ተድላ በየጥቃቅኑ ሽፍታ ቢረበሹም ብዙውን ጊዜ በሰላም አሳለፉት ። አጤ ቴዎድሮስም የደጃች ተድላን መረጋጋት ሲያውቁ በሐምሌ ወር ሌትና ቀን ገስግሰው እጅባራ ከሚባል ቦታ ላይ ደርሰውባቸው ደጃች ተድላ ለጥቂት ሲያመልጡ ሠራዊታቸውን ግን ቴዎድሮስ ፈጁባቸው ። ከባለገሩም ሆነ ከወታደሩ የተማረከው ስምንት ሺህ ያህል ሰው ነበርና አጥር አሳጥረው ያን ሁሉ ሠራዊት በአጥር ውስጥ አጉረው በጐራዴና በጥይት ጨረሱት ።

ደጃች ተድላ ጓሉ 12 ዓመት ገዝተው በ1860 ዓ.ም. ሕዳር 6 ቀን ሞቱ ። አጤ ቴዎድሮስም የተድላ ጓሉን መሞት ሲሰሙ አዘኑ ፣ ደነገጡም ። ምክንያቱም አዋቂዎች “ ተድላ ጓሉ ሲሞት አንተ ተከትለህ ትሞታለህ ” ብለዋቸው ስለነበር ነው ። ተድላ ጓሉ በይፋ አልተቀበሩም ። በይፋ የተቀበሩ እንደሆነ ቴዎድሮስ መጥተው ይወጉናል በሚል ፍራቻ በድብቅ የውሽ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ።

አልቃሽም “ አጥር ቀደው ወጡ ነውረኛ መስለው ፣<br>
እረኛ ሳይሰጡት ለዚህ ሁሉ ሰው ።<br>
ተንግዲህ ወዲህ የልቤን ልናገር ፣<br>
አባ መላክ ተድላ ጠጁ ውሃ ነበር ።<br>
በሸዋ ተላከ ዋናው ሲመጣ ነው ፣<br>
በጐንደር ተላከ ዋናው ሲመጣ ነው ፣<br>
ተድላ ጓሉ ሞቶ ጐጃም ሲፈታ ነው ።

አልሞተም ይሉናል ደጃዝማች ተድላን ፣
አሁን እሑድ ሲቀር የምናውቀውን*
እሻሻ ነው እንጂ የእሥራኤል ሞት ፣
እንዲያልቅ ሰው ተድላን ለምን ቀበሩት” አሉላቸው ።

# አቡነ ሰላማ

ደጃች ውቤ ታላላቅ ሊቃውንቶችን መርጠው አለቃ ሀብተ
ሥላሴን የበላይ አድርገው ከግብጽ ጳጳስ እንዲያመጡላቸው ወደ
ካይሮ ላኩዋቸው ። መልዕክተኞቹ ከመሔዳቸው በፊትም ደጃች
ውቤ “...ሃይማኖቱን ከዚያው ወስናችሁ ፣ በማናቸውም ተስማ
ምታችሁ ፣ከዚህ እንደ ቀድሞ ጠብ እንዳይሆን ቀዋሚ ነገር ይዛ
ችሁ ፣ ጳጳሱንም የተገባ ባለ አእምሮ ሰው መርጣችሁ ይዛችሁ
ኑ” ብለው መከረውና አስጠንቅቀው ሰደዱዋቸው ። ደጃች ውቤ
ጳጳሱ እንዲመጣላቸው የፈለጉበት ምክንያት ራስ አሊን አሸን
ፈው እሳቸው የመንገስ ፍላጐት ስለነበራቸው ነው ።

አድዋ ላይ ይኖር የነበረውን ኢዘንበርግ የተባለውን ሚስዮ
ናዊ በሃይማኖት ሰብከት ምክንያት ደጃች ውቤ ተጣልተውት
ካገር እንዲወጣ አድርገውት ነበር ። ኢዘንበርግ በዚህ ጊዜ የሚኖ
ረው ካይሮ ነበር ። የደጃች ውቤ መልክተኞች መላካቸውን በሰማ
ጊዜ ወደ ሊቀ ጳጳሱ ዘንድ ሔዶ 1700 ብር (አንዳንዶቹም 7000
ይላሉ )እጅ መንሻ ሰጥቶ አንድራዎስ የሚባለው የ25 ዓመት
ወጣት ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ያደርጉ ዘንድ ለመናቸው ።ኢዘን
በርግ ይሄን ያህል ስጦታ የሰጠበት ምክንያት ወጣቱ አንድራዎስ
ወደ ኢትዮጵያ ቢላክ የበለጠ ገንዘብ እንደሚከፍለው ስለሚያው
ቅና ስለተነጋገሩም ነው ። ሊቀጳጳሱም በኢዘንበርግ ሐሳብ ተስ
ማሙ ።

ኢትዮጵያውያኖቹ መልክተኞች ከሊቀ ጳጳሱ ዘንድ ቀርበው
የተላከውን እጅ መንሻ ከሰጡ በኋላ ሊቀጳጳሱ ከአንድራዎስ አገ
ናኝተው “እሱን ነው የምሰጣችሁ” አሏቸው ። የአባ አንድራዎስን

---

* እሁድ እሁድ ግብር ያበሉ ስለነበረ ነው ።



የመጀመሪያ ታሪክና ሁኔታ ብቀወውም በዚያ ባሉ መነኮሳት
ዘንድ በመጥፎ ምግባር የታወቀ ሰው ነበሩና አንዳንድ መነኮሳት
በምስጢር ለደጃች ውቤ መልዕክተኞች የተመራጩን ጳጳስ ታሪክ
ነገሩዋቸው ። መልዕክተኞቹም ከሊቀ ጳጳሱ ዘንድ ቀርበው “....
የ25 ዓመት ወጣት እንዴት አቡን ሆኖ ያንን ሁሉ ሕዝብ ሊመራና
ሊጠብቅ ይችላል ።....40 ዓመት የሆነው ሌላ ሙሉ ሰው ይፈ
ልጉልን ..ብለው አመለከቱ ። ሊቀ ጳጳሱም አሰብበታለሁ ብለው
መለሱዋቸው ።

ከደጃች ውቤ በተላኩት መልዕክተኞች መሐል ያለመግባባት
ተነሳ ። ከመልዕክተኞቹ አንዱ የሆኑት አለቃ ኩላሊት ኪዳነ ማር
ያም “ ይህን ወጣት ጳጳስ ብንወስድ ልጅ ነውና ብዙ ዘመን ይቆ
ይልናል ” የሚል ሐሳብ አቀረቡ ። የመልዕክተኞቹ መሪ አለቃ
ሀብተ ሥላሴ ደግሞ “ ሞት በሰው እጅ ሆነንን ! አርጌ ሳለ ልጅ
ሲሞት አላየህምን ? ” ብለው መለሱ ። ይህ ያለ መግባባት በመል
ዕክተኞቹ መሐል እንዳለ ወደ ሮም ሊሄዱ ተነሱ ። መልዕክተኞቹ
ወደ ሮም የሚሔዱበት ምክንያት ገና ከትግሬ ከመነሳታቸው
በፊት ደጃች ውቤ በትግራይ ይኖሩ የነበሩትን ካቶሊካዊውን አባ
ያዕቆብን አስጠርተው “ እነዚህን መልዕክተኞቼን ጠብቀህ ውሰድ
ልኝ ” ቢሏቸው አባ ያዕቆብ በነገሩ ተስማምተው እባቸውም በተ
ራቸው “ ይህን ከታዘዝሁ እኔም አንድ ነገር ልለምንዎ ። በዘመ
ዶቼ ዘንድ ከፉ እንዳይሆንብኝ እነዚህ ሰዎች ከጴጥሮስ መቃብር
ከጳውሎስ ዝህር ሮማ ደርሰውልኝ ይምጡ ቢሏቸው ደጃች ውቤ
“እሺ ይድረሱልህ ። እኔም አገሬ ቢያዩልኝ እወዳለሁ” ብለው ሮማ
ሄደው አገር አይተው እንዲመጡ አዘዋቸው ስለነበረ ነው ።

መልዕክተኞቹ ወደ ሮማ ለመሔድ መርከብ ተከራይተው
ገንዘብ ከፍለው ከጨረሱ በኋላ የአንድራዎስን ጳጳስ መሆን የተስ
ማሙት አለቃ ኩላሊት ኪዳነ ማርያም በመጨረሻዋ ሰዓት ላይ
ወደ ሮማ አልሔድም ብለው ቀሩ ። ሌሎቹ ግን በመርከብ ተሳፍ
ረው ወደ ሮም ሔዱ ። የመልዕክተኞቹን ወደ ሮም መሔድ ያረጋ
ገጡት አለቃ ኩላሊት ኪዳነ ማርያም ከሊቀ ጳጳሱ ዘንድ ቀርበው
“ ይህን የተባላውን ሰው ወደነዋልና ጳጳስ አድርገው ይስጡን ”
ብለው ስለጠየቁ ሊቀ ጳጳሱ እሺ ብለው አንድራዎስን የጵጵስና
ስማቸውን ሰላማ ብለው ሾመው ሰጡዋቸው ። ወደሮም ሔደው
የነበሩት መልዕክተኞችም ከሮም ተመልሰው ጳጳሱ እንዲሰጣቸው
ሊቀጳጳሱን ቢጠይቁ “ ያንኑ እናንተ የጠላችሁትን ወንድሞቻችሁ

ተባብረው ወደው ስለመረጡት እርሱን ሾሜ ሰድጃለሁና ሒዱ ተከተሉ ” አሏቸው ። አቡነ ሰላማ በዚህ ዓይነት የመጡ ሰው ናቸው ። ይህን ታሪክ እዚህ ያመጣሁት አጤ ቴዎድሮስ አባ ሰላማን ማሰሩና መፍታታቸው ፤ ማጉላላታቸው ብቻ በአገራችን ስለተጻፈ አንዳንድ ሰዎች ያለቦታው የቴዎድሮስን ክፋት እያጋነኑ በማውራታቸው እውነተኛውን ለማሳወቅ ያህል ነው ።



አቡነ ሰላማ




ሰላማ ተብለው ከእስክንድርያ የመጡት ግብጻዊ ጳጳስ ገና እስመራ ሲደርሱ ከውቤም ሳይተዋወቁ “ አሊን ያልወጋ ውጉዝ ነው ” እያሉ ሕዝቡን አወገዙ ። ራስ አሊና ደጃች ውቤ ጦርነት ተጋጥመው ራስ አሊ ድል ሲያደርጉ አቡነ ሰላማ ተማርከው ከራስ አሊ ዘንድ ቀረቡ ። ራስ አሊም “ ፍየል ከመድረስዋ ቅጠል መበጠስዋ ። ዛሬ በእንግድነት ይህን የሠራህ ቆይተህስ ምን ትሠራ ይሆን ። ጳጳስ ታረቁ ፤ አትዋጉ እያለ ለምና ገዝቶ ያስታርቃል እንጂ ተዋጉ ብሎ ያስተላልቃልን ። እኛን ለማዋጋት ማነው የላከህ ። ሰላማስ ብሎ ማነው የሰየመህ ። ሰላም አጥፊ የሰላም ጠር እንጂ ። ወየው አቡን ባልሆንክ ፤ እንደ ግብርህስ ሞት ይገባህ ነበር ። ምንም ሥራህ የሰይጣን ቢሆን ስምህ ጳጳስ ነውና አንተን ገድዬ ስሜን አላከፋም ። አሁን ጐንደር ወርደህ ከአቡን ቤት ተቀመጥ ። ከዚህ አትናወጥ ” ብለው መውቀሳቸውን አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ጽፈዋል ።

ራስ አሊ የያዙባቸውን ቂም ለማሻር በዚያን ጊዜ ለራስ አሊ ይገብሩ እንጂ ራሳቸውን ችለው የሚኖሩበትን የሸዋውን ንጉሥ ሣህለ ሥላሴን አቡነ ሰላማ ማውገዝ ጀመሩ ። “ ሣህለ ሥላሴ ውጉዝ ነው ” እያሉ በይፋ በአደባባይ ይናገሩ ጀመር ። ይህን የሰሙት ንጉሥ ሣህለ ሥላሴም ከየአድባራቱ ሊቃውንት ሰብስበው የሊቃውንቱም የበላይ መሪ አለቃ አሥራትን አድርገው ጠይቁ ልኝ ብለው መልዕክተኞቻቸውን ወደ ጐንደር ላኩ ። መልዕክተኞ ቹም ከራስ አሊ ዘንድ ቀርበው “ ንጉሣችን በምን ምክንያት ይወገዛሉ ። ይዳኙን ። ” ብለው አመለከቱ ። ራስ አሊም “ ነገር እንዳለው በሥርዓት ይባባል ፤ ያከራክር ። እንደሌላውም ግዝቱን ይፍታ ለው ብለው ጨምረው ወ/ሮ እናታቸው ወደ እቴጌ መነን ሰደዱዋቸው ።

እቴጌ መነንም ጳጳሱን “ቀርበህ ተባባል ። ወይም ግዝት ፍታ” ቢሏቸው አልዳኝም ብለው ተከታዮቻቸውን ጦር አስነስተው ብዙ ሰው አለቀ ። ከዚህ በኋላ ራስ አሊ እንዲህ ያለ ጳጳስ አያስፈልገኝም ብለው ከጐንደር እንዲወጡ አደረጓቸው ። ያንጊዜ ደጃች ውቤ ከራስ አሊ ጋር ታርቀው በግዛታቸው ነበሩና አባ ሰላማ እንደገና ተመልሰው ወደ ደጃች ውቤ ገቡ ። በዚህ ጊዜም የጐንደር ሊቃውንት በእኚሁ በጳጳሱ በሃይማኖት ምክንያት ቂም ይዘው ነበርና

“ ግድግዳው ቤታችሁ ያው ይሻላችኋል ፤
ካቡን አትጠጉ ይናድባችኋል ።
መናዱ እንኳ ቢቀይ ከዚህ ከእርጉዝ ካብ ፤
እይታጡምና ዳሞትራና አባብ ” እያሉ ገጠሙባ



ንጉስ ሣህለ ሥላሴ

ቸው ። የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ መልዕክተኞችም ከጐንደር ተመልሰው አንኮበር ሲገቡ ደብተራ ጉልቴ የተባሉት ሊቅ

" እንዳሥራት ማን አለ የሚያውቅ ድኀውን
ትግሬ መርቶት መጣ ያን ረኸም አቡን " ብለው ገጠሙ ።

አጤ ቴዎድሮስ ገና በሽፍትነት ሳሉ ራስ አሊን ድል ካደረጉ በኋላ የደጃች ካሣን ኃይል መበርታት ያዩት አቡነ ሰላማ ከደጃች ውቤ ዘንድ እንደሆኑ " እኔን ብትቀበለኝ ቀብቼ አነግስሃለሁ " እያሉ በምስጢር ይላላኩ ጀመር ። ደጃች ካሣም ደጃች ውቤን ድል ሲያደርጉ በቃላቸው መሠረት አቡነ ሰላማ ደጃች ካሣን ቴዎድሮስ ብለው ቀብተው አነገሱ ።

አቡነ ሰላማ በጐንደር ሊቃውንቶች ዘንድ እንደማይወደዱ አጤ ቴዎድሮስ ያውቁ ነበርና የጐንደርን ሊቃውንቶች ሰብስበው " አባቴን ተቀበሉልኝ ፣ ታረቁልኝ " ብለው ለመኑ። ሊቃውንቱም " የሃይማኖት ነገር በሥርዓት እንጂ በልመና አይሆንም ። የእግዚአብሔርን ሃይማኖት ሰው ብሎ በሰው ልመና መካድና ማበካድ ለኛም ለእርሶዎም አይገባምና በዚህ ነገር እሺ ልንልዎ አንችልም ።"



ብለው መለሱ ። በዚህ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ተናደው በአጠገባቸው የቆሙቱን ወታደሮች " በል በልልኝ " ብለው አዘዙ ። ወታደሩም የሊቃውንቱን ልብስ እየገፈፈ ጥምጥማቸውን እያወለቀ በሚጫወትባቸው ጊዜ አቡነ ሰላማ ከዚያም ነበሩና በአድራጐቱ ተደስተው ሊቃውንቱን የሚያስቃየውን ወታደር " እግዚአብሔር ይፍታህ " አሉት ። ይህን የአቡነ ሰላማን " እግዚአብሔር ይፍታህ " ማለት የሰማው ወታደር የሊቃውንቶቹን ቀሳውስት ቤት ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ጭምር ከተማዋን በሙሉ ዘረፋት ።

አቡነ ሰላማ ከግብጽ አገር ሲመጡ የተከፈለው አሥር ሺ ብር ነው ። የዋሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ያህል ገንዘብ ከፍሎ ጳጳስ ማስመጣቱ በያገሩ እየዞሩ ድቁናም ቅስናም እየሰጡ ሃይማኖቱን እንዲጠብቁለትና እንዲያስፋፉለትም ነበር ። ቴዎፍሎስ ዋልድ ሜየር እንደጻፈው አባ ሰላማ ግን አገር ላገር አልንከራተትም ብለው ትንፋሻቸውን በስልቻ እየሞሉ ለሸዋና ለጐጃም ይልኩ ነበር ። አንድ ሰው ለመቅሰስ በሚፈልግበት ጊዜ ከስልቻው መጠነኛ ትንፋሽ በራሱ ላይ ይነፋበትና ቄስ ሆነ ይባል ነበር ።

ከአጤ ቴዎድሮስ ጋርም ቢሆን በፍቅርና በሰላም አልኖሩም ። የጠብ መነሻ የሆነውም ሚስዮናውያኖቹ ከራፍ እና ፍላድ የመጡ ጊዜ ነው ። እነኚህ ሁለት የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ከኢትዮጵያ እንደገቡ ደብረ ታቦር ሔደው ከራሳቸው ጳጳስ ከጉባት የተጻፈላቸውን ደብዳቤ ይዘው አቡነ ሰላማ ዘንድ ቀረቡ ። አቡነ ሰላማም በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት ሚስዮናውያኖቹ ስብከታቸውን እንዲሰብኩ ፈቀዱላቸው ። በማግስቱም ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ሲያገናኙዋቸው አጤ ቴዎድሮስ " የምፈልገው ጥበበኛ የጅ ሥራ አዋቂ ነው ። ጠመንጃና ሌላም የሚሠራ እንጂ ሰባኪ ለአገሬ ምን ይጠቅማታል " ቢሉ አቡነ ሰላማ " በሥራዬ በሃይማኖት ጉዳይ አትግባ " ብለው ቴዎድሮስን ገሰጡዋቸው ። ቴዎድሮስም ከዚያን ቀን ጀምሮ ቂም ያዙ ።

አባ ሰላማ ከቴዎድሮስ ጋር በነበሩበት ጊዜ የጐንደርና የጐጃም ፣ የሸዋም ቀሳውስት ጳጳሱን አይወዱዋቸውም ነበር ። ከክህነት በስተቀር ለጳጳሱም አይታዘዙም ነበር ። ይህን የቀሳውስቱን ያለመታዘዝና መጥላት ያወቁት አባ ሰላማም ቁጭታቸውን በቴዎድሮስ በትር ለማስመታት እያሉ ቀሳውስቱ ሥርዓት የሌለው በመሆኑ በሥርዓት እንዲያድር እንዲያደርጉ ለቴዎድሮስ ይነግሩዋቸው ነበር ።

አጤ ቴዎድሮስም እውነት እየመሰላቸው ከቀሳውስቱ ጋር በየጊዜው ይጣሉ ነበር ። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተሰምቶ የማይታወቅ ትእዛዝም ቀሳውስቱን ያዙ ነበር ።

በ1849 ዓ.ም በመስከረም ወር አጤ ቴዎድሮስ ማንኛውም ቄስ ጥምጥም ጠምጥሞ ከእሳቸው ዘንድ እንዳይቀርቡ የሚል አዋጅ አወጡ ። ይህን ምን ጊዜም ተደርጎ የማያውቅ ነገር ነውና ካህናቱ ጥምጥም ማውለቅ የከብራቸው መዋረድ መሆኑን አውቀው ከንጉስ ዘንድ ቀርበው " ጃንሆይ ጥምጥም ክብራችን ነውና ይበይኑልን " ብለው አመለከቱ ።

አጤ ቴዎድሮስም " ከታቦት በገባችሁ ጊዜ ስለምን ጥምጥማችሁን ታወልቃላችሁ ? ቢሏቸው እግዚአብሔር አድሮበታል ብለን ነው " አሏቸው ፡ ንጉሱም " በኔ እግዚአብሔር አላደረብኝምን ። እግዚአብሔር በኔ አድሮ አይደለም የሚያስገዛኝ ? " አሏቸው ። ካህናቱም አዎን አሉ ። ቴዎድሮስም " እንግዲያው ምነው እኔ ሥራት አስተምራችሁ ብዬ ነው ። ጠምጥሙ " ብለው አዋጁን ሻሩላቸው ። ይህ አዋጅ ቴዎድሮስ አምነውበት ያወጁት ያለመሆኑን ብዙም ሳይቆይ በመሻራቸው ያስታውቃል ። በኋለኛው ዘመንም ቴዎድሮስ በቀሳውስት ዘንድ ከፍተኛ ጥላቻ መነሳቱን ካወቁ በኋላ ለዚህ ያበቋቸውን ጳጳሱን አባ ስላማን መቅደላ ወስደው አሰሩዋቸው ።

የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ኢትዮጵያ መጥተው በነበረ ጊዜ ከኢትዮጵያው ጳጳስ ከአቡነ ስላማ ጋር ተማክረው ለንጉስ ቴዎድሮስ ሳያማክሩ ወደ ግብጽ መሪ ሠራተኛ እንዲልክ ደብዳቤጽፈው ነበር ። የደብዳቤውን መጻፍ ቴዎድሮስ እንደሰሙ " ከኔ ሳትማከሩ እኔ ሳልፈቅድ እንዴት ለግብጽ ንጉሥ ደብዳቤ ጻፋችሁ ? "ብለው ቢጠይቋቸው ሁለቱም ኃይለ ቃል ተናገሩዋቸው ። በዚህ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ የሁለቱንም ጳጳሳት ቤት በእሾህ አጥር አሳጥረው ከዚያ እንዳይወጡ በዘበኛ እንዲጠበቁ አደረጉ ። አጤ ቴዎድሮስ እንኳን ከውጭ አገር መንግሥት ጋር መጻጻፍ ቀርቶ በአገር ውስጥም ቢሆን ሁሉን ነገር ለማወቅ የሚፈልጉ በመሆናቸው ሁለት የግብጽ ጳጳሳት በራሳቸው ሥልጣን በሰው አገር ጉዳይ በምስጢር መጻጻፋቸው ጥፋት ነበር ። ሆኖም ቀሳውስትና የአገር ሽማግሌዎች በነገሩ ገብተው ቴዎድሮስን ከጳጳሳቱ ጋር አስታረቋቸው ።



በ1850 ዓ.ም. የጁ ውስጥ ኢየላ ከተባለው ቦታ ሠፍረው ሳለ አንድ ሰው ወደ ንጉስ ጮኸ ። የሰውየውን ጩኸት የሰሙት ቴዎድሮስም አቡነ ሰላማን " ለምን ያስጮሁብኛል ? " ቢሏቸው አቡነ ሰላማ " አንተ በኔ ግዛት ምን አገባህ " ብለው የተገላቢጦሽ ንጉሱን ተቆጡ ። ንጉሱም ተናደው ቢቆጡ ጳጳሱ ብሰው በኃይል ተቆጥተው " ታቦት ያነሳ ፣ ይህን ሰው የተከተለ ውጉዝ ይሁን " ብለው ገዘቱ ። ንጉሱም ግዝቱን እንደሰሙ ያዘው ብለው ጳጳሱን አስያዙዋቸው ። የጳጳሱን መያዝ ያዩት ሊቀጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ግዝቱን ፈቱ ። አባ ሰላማ ግን ለምን የገዘትኩትን ይፈታሉ ብለው ከሊቀ ጳጳሱ ከቄርሎስ ጋር ተጣሉ። በእነኝህ ሰዎች መጣላት ምክንያት ታላቅ ሽብር ሊነሳ ሲል ቴዎድሮስ ነገሩን አብርደው ታረቁዋቸው ። ይህን በመሳሰለ በጥቃቅኑ ነገር ሁሉ ቴዎድሮስን የሚያበሳጯቸው ብዙ ነበር ።

አቡነ ሰላማ አምስት ዓመት ያህል በግብጽ ከሠሩ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ብዙ መንገላታት አድርሰውባቸው በመጨረሻው እንደገና ከ62 ተከታዮቻቸው ጋር ከመቅደላ ተራራ አስገብተው አሠሩዋቸው ። ከዚያም ሆነው ከሸዋው ንጉሥ ከዳግማዊ ምኒልክ ጋር በሚስጥር " ከዚህ አውጣኝና አነግስሃለሁ " እያሉ ሲጻጻፉ አራት ዓመት እንደታሠሩ በሞት ተለዩ ።

አቡነ ሰላማ ከቴዎድሮስ ቁጣና እጅ ድነው በ1860 ዓ.ም. ጥቅምት 15 ቀን ባደረባቸው የሳንባ (የሳል) በሽታ አርብ ዕለት ከቀኑ በ9 ሰዓት ሞቱ ።

## እቴጌ ተዋበች አሊ

ቀደም ብለን እንዳነበብነው እቴጌ ተዋበች ሞተው አጤ ቴዎድሮስ ሬሳውን አጅበው በሚሔዱበት ጊዜ

" እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሔድ ፣
እቴጌ ተዋበች ሚስትና ገረድ " ብለው ተቀኙላቸው ።

ትርጉሙም እቴጌ ተዋበች ሚስት ፣ እናት ፣ ገረድ ነች ለማለት ነው ።

አጤ ቴዎድሮስ ለሚስታቸው የተቀኙት ቅኔ ትክክለኛ አባባል ነበር ። ተዋበች ለቴዎድሮስ ትንከባካቢ ሚስታቸው ፣ መካሪ እህ

ታቸው ፤ አሳቢ እናታቸው እና አገልጋይ ገረዳቸው ነበሩ ። በቅርብ ሁኔታውን ያጠናው ዎልድሜየር ሲጽፍ “... ንጉሥ ቴዎድሮስን ሚስታቸው እቴጌ ተዋበች ይጠብቋቸዋል ።...እቴጌይቱ እንደ አበሾች ባህል ሁሉ ንጉሡን በምግባቸው በኩል ይንከባከቡዋቸዋል ። ንጉሱ የሚበሉትንም ሆነ የሚጠጡትን የሚቀበሉት ከእቴጌይቱ እንጂ ከሌላ ሰው አይቀበሉም ። ሴትዮዋ ብልህና ጠቢብ ስለሆኑ ንጉሱ ብዙ መጠጥ በሚጠጡበት ጊዜ ወይም እየደጋገሙ ሲጠጡ ሲያዩዋቸው “ ንጉስ እስካሬ መጠጦችን ደጋግሞ አይጠጣም ” በማለት ይመክሩዋቸዋል ። በዚህም ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ያነቡላቸዋል “ ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲያድርባቸውም ይነግሩዋቸዋል ።.....” ብሏል ።

ዶክተር ብላንክ እንደጻፈው ደግሞ “ ...ጀግናና ተወዳጅ የሆነች ሚስታቸውን አጡ ። እጅግ በጣም ታማኝ የሆነች አማካሪያቸውና እንደ እሳቸው ሰፊ ምኞትና ዓላማ የነበራት ጓደኛቸው በመሆንዋ በጣም ይወዷት ስለነበረ በሕይወታቸው ሳሉ ትዝታዋ ምንጊዜም ከአእምሮአቸው ውስጥ አልጠፋም ነበር ። በ1860 ዓ.ም አንድ ብረት ቀጥቃጭ (ሠራተኛ) የሆነ ሰው ከቴዎድሮስ ፊት ቀርቦ ሚስቱ በጠና መታመምዋን ገልጦ ለጥቂት ቀናት ለመሞት በምታጣጥር ባለቤቱ አጠገብ ለመቆየት እንዲፈቀድለት ስለጠየቀ አጤ ቴዎድሮስ በዚህ አነጋገር ልባቸው ስለተነካና የሚወዷትንም ባለቤታቸውን በማስታወስ ራሳቸውን እቀርቅረው ማልቀስ ጀመሩ . . ” ብሏል ።

ተዋበች ለቴዎድሮስ እጅግ በጣም ደግና አዛኝ ፤ አፍቃሪና አሳቢ የሆኑበት ምክንያት ነበራቸው ። ቴዎድሮስ ከመሞት ያዳኑዋቸው ፤ ሕይወታቸውን ለተዋበች ሕይወት የለወጡ ሰው ነበሩ ። ሜጀር ፖልሰን ኒው ማን የትባሉት ታሪክ ፀሐፊ እንደሚተርኩት አያታቸው እቴጌ መነን ከቱርክ ጦር መሪ ከመሐመድ አሊ ጋር ለመግጠም ወደ ወሰን ሲሔዱ ወይዘሮ ተዋበችም አብረው ሔደው ነበር ። የዚያን ጊዜ የተዋበች ዕድሜ 15 ዓመት ነበር ። በጦርነቱ ላይ ተዋበች ተማርከው ተወሰዱ ።

የዚያን ጊዜው ካሣ የኋላው ቴዎድሮስ ከእቴጌ መነን ጦር ጋር ነበሩና የተዋበችን መማረክ እንደሰሙ ብቻቸውን አሽምቀው ወደ ጠላት ሠፈር ገብተው ተዋበች ከታሠሩበት ቦታ ደረሱ ። ተዋበችም በመሐመድ አሊ ዘቦች ይጠበቁ ነበር ። ካሣ ዘቦቹን እን



ደምንም ብለው አልፈው ገቡ ። ሲገቡም ተዋበች ራሳቸውን ለመግደል አካላቸውን በጥተው (ቀደው) መርዝ ሲጨምሩ ደረሱባቸው ። ካሣም ተዋበችን ሲያዩ በውበታቸው ቢደነግጡም ቶሎ ብለው እጐንብሰው መርዝ የተደረገበትን የተበጣውን ቦታ በአፋቸው እየመጠጡ መርዙን ያወጡላቸው ጀመር ። መርዙን መጥጠው አውጥተው ከጨረሱ በኋላ ተዋበችን በድብቅ አውጥተው ጎንደር ወስደው ለወላጆቻቸው መስጠታቸውን ዘርዝረው ጽፈዋል ።

ቴዎድሮስን ከተራ ሽፍትነት ጀምሮ እስከ መንገስ ድረስ የደረሱ ተዋበች ናቸው ። እንዴት እንደሆነም ከዶክተር ብላንክ ታሪካ ጥቂት እንመልከት ። በኋላ ቴዎድሮስ የተባሉት ካሣ ገዳሪፍ ላይ ከቱርኮች ጋር በተደረገው ጦርነት ቆስለው ቁስላቸው እስኪሻላቸው ድረስ ደንቢያ ተኝተው ስለነበረ ለማገገሚያ ፍሪዳ እንዲላክላቸው ለአማቻቸው ቢልኩ እቴጌ መነን አንድ ብልት ሥጋ ከስድብ ጋር በላኩላቸው “ ...መንፈሰ ጽኑ የሆነችውና የምትወዳቸው ሚስታቸው ቆስሎ ከተኛው ጀግና ባለቤቷ አጠገብ ያልተለየች በስሆን ይህን አሰቃቂ የንግሥቲቱን ንግግር በሰማች ጊዜ ትኩስ የሆነው የጋለ ደሟ ሲፈላ ኩራት በተመላው አነጋገር ከመቀመጫዋ ተነስታ እየተንቀራጠጠች “ ደፋሮችን እወዳቸዋለሁ ፡ ፈሪዎችን ግን እንቃቸዋለሁ ” ብላ ከዚህ ሁሉ ውርደት በደሉን በደም የማይበቀሉ ቢሆን ከጐናቸው አብራቸው ለመገኘት እንደማትችል ስትገልጽላቸው ጥቃት የማይወደውን የካሣን ልብ የመበቀል ሀሳቡ ጠነሰሰችበት። ወዲያው ቁስላቸው እያገገመ ሲሔድ ወደ ቋራ ተመልሰው ነፃነታቸውን በግልጽ አወጁ ።. . ” ይላል በሌላ ጊዜ ደግሞ “ . . .ካሣ ከጠነከሩ የበላይነቱን ቦታ ለማግኘት ምንም የሚያቆማቸው ነገር ያለመኖሩን ሚስታቸው ደጋግማ ስትገፋፋቸው የጥርጣሬ መልክ ስላሳዩዋት አሁንም በዚህ ሐሳብ የማይቀጥሉ ከሆነ አብራ ለመኖር እንደሚያዳግታት ስላስፈራራቻቸው ወደ ጉጃም ቀጥለው ሁሉንም ድል መቱት . . . ” በማለት ጽፈዋል ።

# ፕላውዴን (ዎልተር ቺቺሊ ፕላውዴን)

እ.ኤ.አ. ሰገስት 3 ቀን 1820 ዓ.ም ተወለደ ። በኛ አቆጣጠር ሐምሌ 27 ቀን 1812 ዓ.ም. መሆኑ ነው ። በ19 ዓመት ዕድሜው ወደ ሕንድ ሔዶ ካልካታ ውስጥ ካር ታጉር ከተባለ ኩባንያ ዘንድ ተቀጠረ ። እ.ኤ.አ. በ1843 ዓ.ም ከሕንድ ወደ እንግሊዝ አገር ለመመለስ ጉዞ ጀምሮ ስዊዝ ሲደርስ ከቢል ጋር ተገናኙ ። በዚያም ሆነው የአባይን ምንጭ እንፈልጋለን በማለት ተስማምተው ወደ ኢትዮጵያ መጡ ። በዚህ ጊዜ የፕላውዴን ዕድሜ 23 ዓመት ነበር ።

በኢትዮጵያ ውስጥ እስከ 1847 ዓ.ም. ድረስ አራት ዓመት ቆይቶ ወደ አገሩ ተመለሰ ። በእንግሊዝ አገርም ለእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሎርድ ፖልመር እስቶን የእንግሊዝ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ ቆንሲል ቢያቋቁም ጠቃሚ እንደሚሆን አሳወቀ ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩም በአሳቡ ተስማምተው "አገሩንም ፣ ሕዝቡንም ፣ ቋንቋውንም ታውቃለህና አንተው ሁን" ብለው ፕላውዴን በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል አድርገው ሾሙት ።

ፕላውዴን ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሾመበትን ደብዳቤ ይዞ በ1848 ዓ.ም ምጽዋ ደረሰ ። ከዚያም መሀል አገር ገብቶ ከራስ አሊ ጋር የቆንሲልነቱን ሥራ ጀመረ ። ራስ አሊና ደጃች ካሣ በሚዋጉበት ጊዜ ፕላውዴን ታሞ ስለነበረ ወደ እንግሊዝ አገር ለመሔድ ምጽዋ ነበረ ። በምጽዋም ሕመሙ ስለጠናበት እስኪሻለው ድረስ በዚያው ቆየ ። ሕመሙን ሻል ሲለው ራስ አሊ በደጃዝማች ካሣ ድል መሆናቸውን ሰማ ። ይህም ለውጥ እሱን የሚመለከተው በመሆኑ የእንግሊዝ አገር ጉዞውን አቋርጦ ወደ አዲሱ ንጉሥ ወደ ቴዎድሮስ ዘንድ ተመለሰ ።

ፕላውዴን ወደ ጎንደር እንደተመለሰ ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ተገናኝቶ ከራስ ጋር የነበረው የሰላም ውል እንዲጠና ቢጠይቃቸው ቴዎድሮስ በውሉ ውስጥ ያለው የእንግሊዝ መንግሥት የፍትህ ጠባቂነት የሚለው ቃል እያለ ውሉ አይጠናም ብለው እምቢ አሉ ። ፕላውዴንም ይህን የውል ቃል አስቀርቶ በውሉ ቴዎድሮስ ሲስማሙ የእነሱንም ቆንሲልነት አወቁለት ። ቆንሲልነቱን ለማወቃቸውም ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለእንግሊዝ መንግሥት ጻፉ ።



ዛቲ፡ ጦማር፡ ዘተፈነወት፡ እምኀበ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡
ቴዎድሮስ፡ ዘኢትዮጵያ።
ትብጻሕ፡ ኀበ፡ ንግሥተ፡ እንግሊዝ፡ ብክቶርያ።
እንዴት፡ ነዎ፡ ደኅና፡ ነዎን።
እኔ፡ እግዚአብሔር፡ ይመስገን፡ ደኅና፡ ነኝ።
አቶ፡ ቡላዴንን፡ የእርስዎ፡ መላክተኛ፡ ነው፡ ብዬ።
በፍቅር፡ በወዳጅነት፡ ተቀብየው፡ ሰሰሁ።
እስተ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ያለ መላክ፡ ባላርፍ፡ ባይረጋልኝ፡ ነው።
አሁንም፡ እርስዎም፡ የክርስቶስ፡ ልጅ፡ ነዎ።
እኔም፡ የክርስቶስ፡ ልጅ፡ ነኝ።
ስለ፡ ክርስቶስ፡ ፍቅር፡ ወዳጅነት፡ ፈልጌ፡ ሰሰሁ።
አሁንም፡ ክርስቶስ፡ ደሥ፡ ቢአሠኘኝ።
ሥኀረጋ፡ ደሥታየን፡ ሁሉ፡ ሺ፡ ማጣሴ፡ ለመ፡ ጤምሬ።
ከቶ፡ ቡላውዴን፡ ጋራ፡ እልካለሁ፡ አብሮ፡ ደስ፡ እንዲለን።



ፕላውዴን የበፊት ሕመሙ ሲሻለው ከፈረስ ወድቆ እግሩ ተሰበረ ። ጥቂት ቀን ቆይቶ ለመታከም ወደ አገሩ ለመሄድ ከጎንደር የካቲት 25 ቀን 1852 ዓ.ም. ተነስቶ ጉዞ እንደጀመረ ጎንደር ከተማ አጠገብ ቀሃ ከሚባለው ወንዝ ሲደርስ በድንገት የደጃች ጋረድ ሰዎች ደርሰው ደረቱ ላይ በጦር ወጉት ። ማርከውም ወሰዱት ። ቴዎድሮስም ከሽፍቶቹ ጋር በተደረገው ድርድር መሠረት አንድ ሺ ብር ከፍለው ፕላውዴንን አስለቀቁት ። ፕላውዴንም በጦር የተወጋው ከፋኛ ነበርና በቃሬዛ ሆኖ ጎንደር ገባ ። በጎንደርም ለዘጠኝ ቀናት በሕመም ሲሰቃይ ቆይቶ በጥር ወር 1853 ዓ.ም. ሞተ ።

የፕላውዴን ሬሳም ነገሥታት ከሚቀበሩበት ሥፍራ የጎንደር ሕዝብና መኳንንት ባለበት ጉዞ ፍታት ተፈትቶ ተቀበረ ። በጎንደር ያሉት ዕቃዎችም ለወንድሙ ትሬቫሊስ ቺቺሊ ፕላውዴን ተሰጠው ። ከዕቃውም ጋር ፕላውዴን በሕይወት—በነበረ ጊዜ በደረቅ እርሳስ ይጽፈው የነበረው ማስታወሻና የመጽሐፍ ረቂቅ ድርሰቱ

ተገኝቶ ለወንድሙ ተሰጠ ። ይህም ደርሰቱ ፕላውዲን ከሞተ ስምንት ዓመት በኋላ ወንድምየው "ትራቭልስ ኢን አቢሲኒያ ኤንድ ጋላ ከንትሪ" በሚል ርእስ አሳተመው ።

ፕላውዲን እንዳሁኖቹ አምባሳደሮች ወይም ቆንሲሎች የሚሠራው ሥራ አልነበረውም ። ራሱ በመጽሐፉ እንደገለፀው "በስም ብቻ ቆንሲል ነኝ ። የቆንሲልነት ተግባር ግን የለኝም ። የውጭ ንግድ ጉዳይ የለም ። የንግድ ትርፍም ጉዳይ የለም ። የምጠብቀውም የእንግሊዝ መንግሥት ነገር የለም" ብሏል ።

አጤ ቴዎድሮስ ፒላውዲንን የገደሉትን ሰዎች እነጋረድን ከነወታደሩ ካጠፉ በኋላ የሟቹን የፕላውዲን ደም መበተላቸውን የፕላውዲን ረዳት ወይም ምክትል ሆኖ ምጽዋ ለተቀመጠው ለራሱኤል ባርኒ የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉ ።

በስሙ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡
ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ቴዎድሮስ፡ ይድረስ፡፡ ከእት፡ በረኒ
"እንደ ተ፡ ሠነበትህ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ ይመስ
ገን፡ ደኅና፡ ነኝ፡፡ የምሥራች፡ በእግዚአብሔር፡ ኀይ
ል፡ ቀናሻ፡፡ ወደ ፪ ቅኝ ... ገን፡ ዮሐንስን፡ የገደ
ሉን፡ ሠዎች፡ ፈጀኋቸው፡ በእግዚአብሔር፡ ኀይል
፡ ከሚቱ፡ በቀር፡ ከሠልፋ፡ ያገኘሁትን፡ ሁሉ፡ ፈጀሁት
እንድ፡ እሌተ ውሁም፡፡ ወዲያው፡ ተከታትሎ፡ ተሸጎ
ሩ፡ ሌበ፡ ንጉሢን፡ በእግዚአብሔር፡ ኀይል፡ ከነሠራዊ
ቱ፡ ፈጀሁት፡ አኾለም፡ ከሜዳው፡ ላይ፡፡ አግተም፡ ቆ
ሉ፡ ኖልኝ፡፡ ከዕንግሊዝ፡ ንግሥት፡ ከወዳጄ፡ እግዚ
አብሔር፡ ያደረገልኝን፡ የደሥታዬን፡ ወሬ፡ የምልክ፡
ሠው፡ የምሠድ፡ ነኝና፡ ቶሎ፡ ኖልኝ፡ ይዘህልኝ፡ የም
ትዊድ፡ ነህና፡፡ የሊቀ፡ መኳስ፡ ዮሐንስን፡፡ የአቶ፡ ቡላዲን
ን፡ ሠዎች፡ እስታሁን፡ ያቆየኋቸው፡ ከእኔ፡ ሠው፡ ከንቱ፡ጋ
ራ፡ ይሂዱ፡ ብዬ፡ ነው፡፡



ይህን ደብዳቤ መቼ እንደጻፉት ቀኑ ባይገለጽም ለራሱኤል ባርኒ የደረሰው ግን እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 23 ቀን 1863 ነው በኛ አቆጣጠር ጥር 15 ቀን 1855 ዓ.ም መሆኑ ነው ።



## ቤል/ሊቀ መኳስ ዮሐንስ

ጆን ቤል በሞቱበት ጊዜ ስለነበረው የቴዎድሮስ ሁኔታ ዱፍተን ሲጽፍ "....ከጐናቸው ሆኖ ይዋጋ የነበረውን የወዳጃቸውን ሬሳ ባዩ ጊዜ እጅግ በጣም አምርረው አለቀሱ ። ወዳጄ ቤል ፣ ደሃው ቤል ፣ በወዳጅነት ከፍያ ህይወቴን ያዳንኸው" እያሉ ሬሳው ላይ ተደፍተው ጮሁ ። ከሬሳው ላይ ሲነሱም የገዳዩም ሬሳ ከዚያ ወድቆ ነበርና "አንተ ፣ አንተ የማትረባ ከወዳጄ ፣ ካንዱ ወዳጄ የለየኸኝ" ብለው የያዙትን ጦር በሬሳው ላይ ሰኩበት ።..." ብሏል ።

ጆን ቤል በእንግሊዝ ባህር ሀይል ውስጥ የመቶ አለቃ ነበር ። በኋላም ጊዜ በቱርክ ቅኝ ግዛትነት ስር በነበረችው አሌፖ በተባከችው የአረብ አገር የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ሆኖ ተሹሞ ነበር ። ከዚያ በኋላ ግን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ለራስ አሊ አሽከርነት አደረ ። ራስ አሊም የባሻነት ማዕረግ ሰጥተውት ነበር ። ጆን ቤል በራስ አሊ ዘንድ አይወደድም ነበር ፤ መኖርም የቻለው በፕላውዲን ደጋፊነት ነበር ። ቤል አንዲት ኢትዮጵያዊት አግብቶ ሁለት ሴቶችና አንድ ወንድ ልጅ ወልዳለታለች ፤ ሴቶች ልጆችም በኋለኛው ጊዜ ሁለት የቴዎድሮስን ጥበበኛ ፈረንጆችን አግብተው ከባሎቻቸው ጋር በቴዎድሮስ እጅ ታስረው ነበር ። እስረኞቹ ሲፈቱም አብረው ተፈትተው ከባሎቻቸው ጋር ወደ ኤሮፓ ሄደዋል ። አንዲቱ ልጅ ያገባችው ዎልድሜየርን ነበር ።

ራስ አሊና ደጃች ካሣ ( በኋላ ቴዎድሮስ) የመጨረሻውን ጦርነት በተጋጠሙ ጊዜ ቤል ከራስ አሊ ወገን በመሆን ተዋግቷል ። ራስ አሊ ድል ሲሆኑም ጆን ቤል ካንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተደብቆ ሳለ ቴዎድሮስ ይህንኑ ሰምተው ምህረት አድርገውለት ወደ ቴዎድሮስ ገባ ። ቤል በኑሮውም ሆነ በአለባበሱ ከኢትዮጵያኖች የተለየ አልነበረም ። የሚለብሰው ልብስ አበሾች የሚለብሱትን ሲሆን ስእግሩ ጫማ ስራሱ ባርኔጣ አያደርግም ነበር ።

አጤ ቴዎድሮስን በጥሩ ሁኔታ ስለሚመክሯቸውና በተለይም በፍርድ ጉዳይ መልካሙንና እውነተኛውን መንገድ ስለሚመራቸው ቤልን ይወዱትና ያከብሩት ነበር ። በሕዝቡም ዘንድ በዚሁ በምክሩና በአማላጅነቱ የተወደደና የተከበረ ሰው ነበር ። የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል የሆነው ፕላውዲን እንኳን በአጤ ቴዎ

ድሮስ ሞገስ ዘንድ አግኝቶ በኢትዮጵያ መኖር የቻለው በጆን ቤል ድጋፍ እንጂ ቴዎድሮስ ፕላውዲንን አይወዱትም ነበር ። ብዙ ጊዜም ከመታሰርና ከመጉሳሳት የዳነው በቤል አማላጅነትና ስለሱ መልካም ነገር በመናገሩ ነበር ።

## ደጃዝማች ንጉሴ ወልደ ሚካኤል

ደጃዝማች ንጉሴ በአባታቸው የአገው ትወላጅ ስለሆኑ ብዙ ጊዜ አገው ንጉሴ እየተባሉ ይጠራሉ ። ደጃች ውቤ ድል ሆነው ሲያዙ ደጃች ንጉሤ የአጐታቸውን የደጃች ውቤን ሥልጣን ለመያዝ ወራሽ ነኝ ብለው በቴዎድሮስ ላይ ሸፈቱ ። ደጃች ንጉሤ የደጃች ውቤ እህት ልጅ ናቸው ደጃዝማች ንጉሴ በትግራይ ውስጥ ሸፍተው ሲነሱ ብዙ ተከታይ በማግኘታቸው አቅማቸው ወዲያውኑ ደረጀ ።

ደጃዝማች ንጉሤ በቴዎድሮስ ላይ የሸፈቱት እንደሌሎቹ ጠላቶቻቸው ሁሉ ራሳቸውን ችለው አልነበረም ። የካቶሊኩን መነኩሴ አባ ያዕቆብን ወዳጅ አድርገዋቸው ስለነበረ በአባ ያዕቆብ አገናኝነት ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር መወዳጀት ጀመሩ ። አባ ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር የመጣሁ ነኝ በማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው ለእግራቸው ጫማ ሳይኖራቸው ፍፁም ባህታዊ መስለው የሚሰሩ ነበሩ ። በዚህም ተግባራቸው በሕዝቡና በመኳንንቱ ዘንድ ሁሉ የተከበሩ ስለነበሩ ደጃች ንጉሴ እንደ ሸፈቱ ፈረንሳዊው አባ ያዕቆብ ወዳጅነታቸውን አጠናክረው ከመንፈሳዊነቱ ወደ ዓለማዊነቱ አዘነበሉ ።

የእንግሊዝ መንግሥት ቀደም ብሎ በራስ አሊ የምስፍንና ዘመን በዲፕሎማቲክ ደረጃ ከኢትዮጵያ ጋረ ወዳጅነት መሥርቶ ፕላውዲንን ቆንሲል አድርጎ በመሾሙ ለአገራቸው መንግሥት ይቆረቆሩ የነበሩት አባ ያዕቆብ የእንግሊዝ መንግሥት በኢትዮጵያ ያለውን ተፈላጊነት አስጥለው በምትኩ የፈረንሳይ መንግሥት እንዲሆን ያስቡ ነበርና ደጃዝማች ንጉሤ በቴዎድሮስ ላይ ሸፍተው ሲነሱ ‘‘የቴዎድሮስን መንግሥት ለመጣል የበለጠ ኃይል መያዝ አለብዎት ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ግንኙነት ቢጀምሩ የፈለጉትን ያህል የጦር መሣሪያ ማግኘት ይችላሉ ’’ ስላሉዋቸው ደጃዝማች ንጉሤ ለፈረንሳዩ ንጉሥ ናፖሊዮን 3ኛ ደብዳቤ ጻፉ ።



ሰኔ 2 ቀን 1848 ዓ.ም. ለናፖሊዮን የተጻፈው ደብዳቤ ‘‘. . . አባቴ ይሁኑ እኔም ልጅዎ እሆናለሁ ። አሁን አንድ ሽፍታ ንጉሥ ተነስቶ እኔን በማጥቃት ላይ ነው ። ክርስቲያኖችም እያጠፋ ነው ። እንደ እውቅትዎ ይርዱኝ ። ቢቻል በነሐሴ ፣ ባይቻልም በመስከረም ። እስከዚያም እቆያለሁ ከወዲያ ወዲህ እያልኩኝ ። አቡነ ያዕቆብን አባቴ አድርጌአለሁ ። የእርስዎንም ፈቃድ የማልጥስ ነኝ ’’ የሚል ነበር ።

ይህ የደጃች ንጉሤ ደብዳቤ በተጻፈ በዘጠኝ ቀኑ ለፈረንሳይ መንግሥት ደረሰ ። የፈረንሳይ መንግሥትም ደብዳቤውን ካየ በኋላ የሚጣሩ ነገሮችን እንዲያጣራ ምጽዋ የተቀመጠውን ጉዳይ ፈጻሚውን ቢላርድን አዘዘ ። ቢላርድም ለፈረንሳይ መንግሥት በላከው መልስ ደጃዝማች ንጉሤ እስካሁን ድረስ ከመሐል ኢትዮጵያ የሚባረሩትን ካቶሊኮች እያሰባሰቡ ማስጠጋታቸው ፣ ካቶሊኩን ፈረንሳዊ አባ ያዕቆብንም (ጃኮቢስ) ኢትዮጵያ ጳጳስ ብለው መሾማቸውን የፈረንሳይ መንግሥት ባንዲራም በደጃች ንጉሤ ትእዛዝ በትግራይ ምድር እንዲውለበለብ መፍቀዳቸውን ሁሉ ዘርዝሮ አሳወቀ ።

ይህ የፈረንሳይ መንግሥት ባንዲራ በኢትዮጵያ ምድር መስቀል ወይም መውለብለብ በዚያን ጊዜ በነበረው እስተሳሰብ ከፍተኛ የፖለቲካ ስሜት ነበረው ። አጤ ቴዎድሮስም የማንኛውም የውጭ አገር መንግሥት ባንዲራ በኢትዮጵያ ምድር እንዲውለበለብ አይፈቅዱም ነበር ። በቴዎድሮስ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ዱፍትን ሲጽፍ ‘‘. . .ጋፋት ደረስን ። ከዚያም ሙሴ ሌዠን ተቀበለን ። . . .ሙሴ ሌዠን በድንጋይ ላይ ሶስት ቀለም የሆነውን ባንዲራውን ሰቅሎ ነበር ። እንዲህ ዓይነቱ ነገር ንጉሡ እንደማይወዱ ከተነገረው በኋላ ቶሎ አነሳው ። . . .የሱ ሀሳብ በዚያ ማዛት ቆንሲል በመሾሙ የቆንሲሉን መመሥረት ለማሳወቅ ነበር ። የንጉሡ አሳብ ደግሞ በዚያ አገር ማንኛውም ኃይለኛ መንግሥት እንዲገባ አይፈልጉም ። . . .ብሏል ። የአንድ የውጭ አገር መንግሥት ባንዲራ በኢትዮጵያ ምድር ላይ እንዳይተከል ወይም እንዳይውለበለብ የሚፈልጉት መሪዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ሕዝቡም ጭምር ነበር ። ዶክተር ብላንክ በመጽሐፉ እንዲህ ይላል ።‘‘ . . .አንድ ጊዜ ሚስተር ፕላውዴን የአገሩን ሰንደቅ ዓላማ ለመስቀል (ራስ አሊን) ፈቃድ ቢጠይቃቸው በደስታ መፍቀዳቸውን አረጋግጠው . . .እንድጠብቅልህ አትጠይቀኝ ። እንደዚህ ስላለው ነገር

እኔ ብዙ አልጨነቅበትም ። ዳሩ ግን ሕዝቡ የሚወደው አይመስለኝም ስላሉ ፕላውዴን በቆንስላው ግቢ የእንግሊዝን ሰንደቅ ዓለማ በቅሎ ማውለብለብ እንደጀመረ ከጥቂት በዓት በኋላ ቁጥሩ የበዛ ሕዝብ መጥቶ ሰንደቅ ዓላማውን አውርዶ ቀዳዶ ጣለው ። ይህን ሁኔታ ራስ አሊ ሰምተው ከፕላውዴን ጋር ሲነጋገሩ "አል ነገርኩህም ነበርን" የሚል ቃል ብቻ ነበር ። . . ." በእንዲህ ዓይነቱ ዘመንና ወቅት ነው ደጃች ንጉሤ የፈረንሳይ ባንዲራ በትግራይ ምድር እንዲውለበለብ ያደረጉት ።

ቢላርድ ሪፖርቱን ያቅርብ እንጂ አባ ያዕቆብና ቢላርድ ተበግምተው ሌሎች የሚጣሩ ነገሮችን ከደጃች ንጉሤ ዘንድ ሔደው እንዲጋነገሩ ኢትዮጵያዊውን ካቶሊካዊ መነኩሴ አባ እምነቱ (እምነት ማርያም) የተባሉትን ላኩዋቸው ። አባ እምነት ማርያም (እምነቱ) ወደ ደጃች ንጉሤ የተላኩበት ሌላው ምክንያት የደጃች ንጉሴ የቅርብ ዘመድ ስለነበሩ ነው ። አባ እምነቱም ከደጃች ንጉሴ ዘንድ አንድ ወር ያህል ከርመው ሲመለሱ ንጉሤ የትግራይ ሙሉ ገዥ መሆናቸውን ያላቸውም የጦር መሣሪያ ከሶስት እስከ አራት ሺ ጠመንጃ ብቻ በመሆኑ በዚህም መሣሪያ ቴዎድሮስን ለመቋቋም እንደማይችሉ አሰረዱ ። የዚያን ጊዜ የትግራይ ገዥ ወሰኑ እስከ ቀይ ባህር ድረስ ነበር ።



ጥንታዊት የአክሱም ከተማ

ከፈረንሳይ መንግሥት የተጠየቀው የጦር መሣሪያ እርዳታ በመዘግየቱ ደጃች ንጉሤ ቢላርድንና አባ ያዕቆብን ይጠይቁ ጀመር ። ምንም እንኳ መልሱ ከፓሪስ ባይመጣ የንጉሤን ተስፋ ላለማ



ጨለም ቢላርድ በካቶሊክ ቀሳውስት ታጅቦ 15 ጠመንጃ ስጦታ አስይዞ ከንጉሤ ጋር ለመገናኘት ከምጽዋ ወደትግራይ መጣ ። ከደጃች ንጉሤም ጋር ተገናኝተው በሚነጋገሩበት ጊዜ ደጃች ንጉሤ የፈረንሳይ መንግሥት መድፎች እንዲሰጣቸውና ወደ ደምቢያ እንዲዘምቱ አሁን ያላቸው ወታደር ግን አራት ሺ ያህል ጠመንጃ ያዙና አስር ሺህ ያህል ጦረኛ ሠራዊት መሆኑን አሳወቁ ። ከዚያም በቀር ስለንግድና በሌላም ጥቃቅን ነገሮች ተነጋግረው ቢላርድ ወደ ምጽዋ ተመለሰ ።

የፈረንሳይ መንግሥት ጉዳዩን እንዳጠናው ደጃዝማች ንጉሴ የጦር መሣሪያ የሚሰጣቸው ሰው ሆነው አላገኛቸውም ። ቢላርድም ሆነ አባ ያዕቆብ በዚህ ጉዳይ ቃል እንዳይገቡ ትእዛዝ ተላለፈላቸው ። ይህ ከሆነ በኋላ አባ ያዕቆብና ቢላርድ ተነጋግረው ጉዳዩን የሚያስረዳ የመልክተኛ ቡድን ወደ ፓሪስ እንዲላክ ተስማሙ ። የሚላኩትም ሰዎች አባ እምነቱና ልጅ ጠጋዬ እንዲሆኑ ተወሰነ ። ፈረንሳዊው ለፔር ደግሞ ፀሀፊና አስተርጓሚያቸው ሆኖ አብሮ እንዲሄድ ተመረጠ ። ይህ ካለቀ በኋላ ደጃዝማች ንጉሤ ደብዳቤ ጽፈው ለመልክተኞቹ ተሰጥቶ መልክተኞቹ ጉዞአቸውን ጀመሩ ።

መልክተኞቹ ከመሔዳቸው በፊት ከነአባ ያዕቆብ ጋር በምክር ይደጋገፉ የነበሩት ካቶሊካዊው የአላዛሪስቱ ሚስዮን መሪ የነበሩት አባ ጁሴፔ ሳፔቶ በዚሁ ጉዳይ ለሮማው ፓፓ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ለፈረንሳይ ንጉሥም በላኩት መልዕክት የፈረንሳይ መንግሥት የንጉሴን ጥያቄ ቢፈጽም ንጉሥ ንጉሴ ካገራቸው ዳርቻ ለፈረንሳይ መንግሥት ግዛት ለመስጠት መዘጋጀታቸውን ፥ በኢትዮጵያ የሚኖረው የፈረንሳይ ቆንሲል በሁሉም ነገር ባለሙሉ ሥልጣን እንደሚሆን ፥ በአድዋም ለቆንሲሉ መቀመጫ ከ500 እስከ 600 ሰዎችን ሊያኖር የሚችል መሬት ለመስጠት መወሰናቸውን አሳውቀው ነበር ። የያኔው የትግራይ ዋና ከተማ አድዋ ነበር ።

ደጃዝማች ንጉሤም ለፈረንሳይ መንግሥት መሪ ለንጉስ ናፖሊዮን የጻፉት ደብዳቤ " . . . . .የአገሬን ነፃነት እንዲጠብቁልኝ እለምናለሁ ። ከዘራፊውና ከዓመፀኛው ከቴዎድሮስ እጅ ይጠብቁኝ ። ይህንንም ለማድረግ ሁለት ነገሮች ያስፈልጋሉ ። መጀመሪያ ከናንተ ተወካይ ቢላክ ከዚህ በፊት እንደጠየቅሁት ይጠብቁኝ ። ይህ በአገሬ ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ እንዲመለከት ።እሱንም በአገሬ እንደራሴ አድርጌ እጠብቀዋለሁ ። የፈረንሳይንም ባንዲራ

እተክላለሁ ። ሁለተኛ የምፈልገው ሁለት መድፎች ከተኳሾቻቸው ጋር ነው ። ለአደረጉልኝና ለአገሬም ለሚያደርጉት እርዳታ ከባህር ዳርቻ ራስ ዱሜራ የሚባል ዙላን እሰጥዎታለሁ ” የሚል ነበር ። ደብዳቤው የተጻፈው ጥቅምት 22 ቀን 1851 ዓ.ም ነው ።

በፈረንሳይ በኩል ያለውን በዚህ አናቁመውና መልክተኞቹ እነ አባ እምነቱ ወደ ኤሮፓ በሚሔዱበት ጊዜ በአባ ጁሴፔ ሳፔቶ ውትወታ ስኢጣሊያ መንግሥትም ደብዳቤ እንዲፃፍና ይዘው እንዲሔዱ ተደርጐ ነበር ። ኢጣሊያዊው አባ ጁሴፔ ሳፔቶም በኢጣሊያ አገር ስለው ጉዳይ እንዲረዱ ተብሎ ወደ ሮም ሔደው ነበር ። መልክተኞቹ ሮም ደርሰው በኢጣሊያው ንጉሥ ለዳግማዊ ቬቶር አማኑኤልና ለፓፓው የተፃፈውን ደብዳቤ ሰጡ ። መልክተኞቹ ወደ ፓሪስ ሲሔዱ ጁሴፔ ሳፔቶ ቀርተው እሳቸው ለአገራቸው ለኢጣሊያ የሚበጀውን ይሠሩ ጀመር ። የተላኩት መልክተኞችም ተመልሰው የማይጨበጥ ተስፋ ይዘው ኢትዮጵያ ገቡ ።

የኢጣሊያ መንግሥት ጉዳዩን ለመጨረስ መልክተኞች ወደ ኢትዮጵያ እንደሚልክ ሲነግራቸው የፈረንሳይ መንግሥት ደግሞ ጉዳዩን አጥንቶ መልሱን እንደሚሰጥ ነግሮአቸው ተመለሱ ። የኢጣሊያ መንግሥት በገባው ቃል መሠረት መልክተኞቹን አፋጥኖ ወደ ደጃች ንጉሤ ዘንድ ላከ ። የተላኩትም መልክተኞች ከደጃዝማች ንጉሤ ጋር ተገናኝተው የጦር መሣሪያውን ለመስጠት ድርድር አቀረቡ ። በቀይ ባሕር ዳርቻ በዙላና በአንፊለ መሀል ያለውን አንዳዳ የተባለው አገር እንዲሰጣቸው ጠየቁ ። ደጃዝማች ንጉሤም በአሳቡ ተስማምተው የኢጣሊያ መንግሥት መልክተኞች ወደ አገራቸው በሚመለሱበት ጊዜ ለኢጣሊያው ንጉሠ ነገሥት “ . . የተጠየቀውን ጉዳይ ሁሉ ተስማምተንበታል ። ይህንንም ስምምነት በአስቸኳይ እንድንፈራረም እጠይቃለሁ . . . . ” የሚል ደብዳቤ ጽፈው ላኩ ።

የኢጣሊያው ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ቬክቶር አማኑኤልም ለደጃዝማች ንጉሤ በላኩት ፌብራሪ 10 ቀን 1859 በተጻፈ ደብዳቤ ሲመልሱ “...የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ በመስማቴ በጣም ተደስቻለሁ ። በዚህም ላይ ወዳጅነታችንን አጠንክረን የንግድን ጉዳይ ሁሉ እንመሠርታለን ። አሁንም የእርስዎ ወኪል በፍጥነት ይምጣና ይህን ጉዳይ በቶሎ እንጨርስ ።. . . ” አሉ ። ይህ ደብዳቤ ሉጥሪማ ጉየራዴ. አፍሪካ (የአፍሪካ የመጀመሪያው ጦርነት) በተባለው መጽሐፍ



ክገጽ 58 66 ላይ አለ ። ከዚህም ሌላ ጁሊዮ ባሳተሙት ኢትዮፒያ ማር. ሮቦ (የኢትዮጵያ ቀይ ባህር) በተባለው ቮሊዩም 1 ገጽ 56 ላይ ይገኛል ።

ይህ የኢጣሊያው ንጉሠ ነገሥት ደብዳቤ ለደጃዝማች ንጉሤ ሲደርሳቸው ተደሰቱ ። ጁሴፔ ሳፔቶ ስለዚሁ ጉዳይ በመጽሐፋቸው ሲገልፁ “ . . . .ደጃች ንጉሤ. . .ማህተሜን ይውሰዱ ። የፈለጉትን ጥሩ ነው የሚሉትን ነገር ሁሉ ጽፈው ያትሙበት ።ልቤን ከፍቼልዎታለሁ . . አሉ ፡ . . . ” ብለዋል ። የኢጣሊያ አገር ጋዜጦችም በኢትዮጵያ ያሉ ካቶሊኮች ችግር ስለደረሰባቸው የኢጣሊያ መንግሥት አስቸጋሪውን ንጉሥ ጥሎ ተስማሚውን ለማንገስ ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ ነው እያሉ ይጽፉ ጀመር ። ይህን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የርበ በርስ ሽብር የሰሙ የኢጣሊያ ነጋዴዎችም የጦር መሣሪያ ለደጃች ንጉሤ ለመሸጥ ሩጫ ጀመሩ ። ከኢጣሊያ መሣሪያ ነጋዴዎች አንዱ የሆነው ባሮኒ የተባለው ሰው አፕሪሌ 24 ቀን 1859 ለወዳጁ ለኮግላን በጻፈው ደብዳቤ “. . .ለዚህ የካቶሊክን እምነት ለሚያበፋፋው ቅዱስ ጦርነት ከአስር ሺህ እስከ ሃያ ሺ ጠመንጃ አቀርባለሁ . . . ” የሚል ቃል ነበረበት ።

በኢጣሊያ በኩል ያለው የደጃዝማች ንጉሤ ጉዳይ ተፋፍሞ ሳለ የፈረንሳይ መንግሥት ደግሞ በአልጄሪያ የፈረንሳይ መንግስት ተወካይ የሆነው ኮንት እስታንሌ ሩሴል ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ለፈረንሳይ መንግስት ወደብነት የሚጠቅመውን ሥፍራ ከምፅዋ እስከ ታጁራ ድረስ እንዲያጠና ታዘዘ ። ሩሴል በታዘዘው መሠረት ታህሳስ 2 ቀን 1853 ዓ.ም. ምፅዋ ሲደርስ አባ ያዕቆብና አባ እምነቱ ተቀበሉት ። ወዲያውም ሐውዜን ለነበሩት ለደጃዝማች ንጉሤ የሩሴል መምጣት ተነገረ ። ሩሴልም አስር ሹማምንት በሚመሩዋቸው የባህር ኃይል ወታደሮች ታጅቦ በአባ ያዕቆብና በአባ እምነቱ መንገድ መሪነት የወደብ ፍለጋ ጉዞ መጀመራቸውን ራሱ ሩሴል በጻፈው ኡን ሚስዮን በሚባለው መጽሐፉ ገልጦታል።

የሁለቱ መንግሥታት በኢትዮጵያ ዘልቆ መግባትና ከንጉሤ ጋር መዋዋል ለቴዎድሮስ ሚስጥር አልነበረም ። አጤ ቴዎድሮስ ደጃች ንጉሤን ለማጥፋት ቢዘምቱም ሆነ ቢያደፍጡ ሊያገኙዋቸው አልቻሉም ። ይህን የንጉሤን ሁኔታ የሚያጠናውና የሚመለከተው አገሩን የሚወደውና ለባዕድ እሳልፎ ላለመስጠት ሲዋጋ የኖረው የትግራይና የሐማሴን መኳንንት ተማክረው ባስነሱት አድማና ስብከት የደጃች ንጉሤ ሠራዊት እየከዳ በመለየቱ መነመነ ።

የሩሲል ምፅዋ መግባት ለደጃዝማች ንጉሤ እንደተነገረ ደጃዝማች ንጉሤ በአንድ ከፍተኛ ሹም የሚመራ ሠራዊት ልከው በእሳቸው ስም ታላቅ አቀባበል ተደረገለት ። ይህም የተላከው ሠራዊት ሩሲል ከኢትዮጵያ እስኪወጣ ድረስ ከማንኛውም አደጋ እንዲጠብቀው የታዘዘ ነበር ። ደጃች ንጉሤ ይህን ሠራዊት ለጥበቃ ያዘዙበት ምክንያት ቅድም እንደተባለው አገር ወዳዱ መኳንንት ሩሲልን ይዞ ለቴዎድሮስ ለማስረከብ መስማማቱን ደጃች ንጉሤ አውቀው ስለነበረ ነው ። ሩሲልም ቢሆን ይህን የመኳንንቱን አድማ ሰምቶ ሰግቷል ። ይህን ስጋቱን ያወቁት አባ ያዕቆብም ምንም ነገር እንደማይደረግ እኔ ኃላፊ እሆናለሁ እያሉ የመኳንንቱን ኃይል እያንቋሸሹ ቢነግሩትም ሩሲል ግን ሁሉም ነገር ገብቶት ነበርና ለሲት የጀመረውን የወደብ ፍለጋ ጉዞ አቋርጦ ምፅዋ ገባ ።

ሩሲል ምፅዋ እንደገባ የደጃች ንጉሤ ተወካይና ባለሙሉ ሥልጣን ከሆኑት ከአባ እምንቱ ጋር ውል ተዋዋለ ። አባ እምንቱ ውሉን ሊዋዋሉ የቻሉት ከደጃች ንጉሤ የተሰጣቸውን ባለሙሉ ሥልጣን ወኪል መሆናቸውን የሚያስረዳ ባለማህተም ደብዳቤ ካሳዩ በኋላ ነበር ። ከውሉ ውስጥ አንዳንዱን ለመጥቀስ የፈረንሳይ መንግሥት ዙላንና የዲሴን ደሴቶች ፣ ከዊዳ እስከ ዘይላ ድረስ ያለውን የኢትዮጵያን ቀይ ባህር በር እንዲይዝ የሚል ነበር ። በውሉ አንቀፅ 5 ላይ ደግሞ በደጃች ንጉሤ ስም "....ይህ ለእናንተ የሰጠሁት ስጦታ ለፈረንሳይ ንጉስ እስከ ልጅ ልጅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል ። ከባህር የሚመጣብኝን ፣ ከአገር ውስጥ የሚነሳብኝን ጠላት (የፈረንሳይ መንግሥት) እስከ ልጅ ልጅ ድረስ ይጠብቁኛል..." የሚል ነበር ።

የኢጣሊያና የፈረንሳይ መንግሥታት ሁለቱም ከደጃች ንጉሤ ጋር ባደረጉት ውል የኢትዮጵያን ቀይ ባህር ዳርቻ መሬቶች ተከፋፍለው ቴዎድሮስ የሚጠፉበትን የጦር መሣሪያ ለደጃች ንጉሤ ለመስጠትና ለማድረስ በሚዘጋጁበት ወቅት እጤ ቴዎድሮስ ቀደም ብለን እንዳነበብነው ደጃች ንጉሤን ድል አድርገው ቆራርጠው ጣሉዋቸው ። ደጃች ንጉሤ ሲሞቱም ሃያ ዓመት ያህል የተለፋበት የባህር በር የመያዙ ጥንስስ ተደፋ ።



ምዕራፍ 7

# የቴዎድሮስ ሰውነት—ጠባይ—ርህራሄ ፣ ጭካኔና—ፍርድ

ቴዎድሮስ እንዴት ያሉ ሰው ነበሩ? ብንል ሁሉንም ጠባይ አሟልተው የያዙ ሰው እንደነበሩ እንረዳለን ። ይህም ማለት ደግ ናቸው ፣ ክፉም ናቸው ። ሩህሩህ ናቸው ፣ ጨካኝም ናቸው ። ፍርድ አዋቂ ናቸው ፣ ፍርደ ገምድልም ናቸው ። ሁሉንም በየተራቸው እናነባለን ። ቀድመን ግን አካላቸው ምን ዓይነት ወይም እንዴት እንደነበር እንመልከት ።

ያያቸው ዱፍተን ሲፅፍ "....ወደ ጥቁረቱ የሚያደሉ ናቸው። ጥንቅላ ግን አይደሉም ።....ራሳቸው ጥሩ ቅርፅ ያለው ነው ። ጠጉራቸው ከግንባራቸው ወደኋላ የተጐነጐነ ነው ። ግንባራቸው ወጣ ያለ ነው ።....

"ዓይናቸው ጥቁር ነው ።....አፍንጫቸው በመጠኑም ቢሆን የሮማውያን ቅርፅ አለው ።....አፋቸው ውብና ፈገግተኛ (ሳቂታ) ነው ።....ጢማቸውም ሆነ ረዛቸው በጣም ትንሽ ነው ። ጠባያቸው ደስ የሚልና ትሁት ናቸው ።....ኤሮፓውያኖች ሠራተኞች ለመጨረሻ ጊዜ የሚሠሩትን መድፍ ለመመልከት ንጉሡ መጡ ። በራሳቸው ላይ ምንም የለም ። እግራቸው ባዶ ያለጫማ ነው ። በዚህ እሾህና ቁጥቋጦ በበዛበት መጥፎ መንገድ ባዶ እግራቸውን ኮረብታውን ወጡ ።....እሳቸው በእግራቸው እየሄዱ እኛን በየበቅሎአችን ላይ እንድንቀመጥ ነገሩን ። እኛም ለክብራቸው ስንል እምቢ ብለን እሳቸው እሔዱበት ድረስ በእግራችን አብረን እንጓዝ ጀመር ።

"....ታቦር ተራራ ሥር ስንደርስ ቴዎድሮስ ፈረሳቸው ላይ ተቀመጡ ። ፈረሱ ላይ በወጡበት ጊዜ ከመሬት ዘለው ተቀመጡበት እንጂ እርካብ አልረገጡም ። በፈረስ ግልቢያና አቀማመጥ ጥሩ

የሩሴል ምፅዋ መግባት ለደጃዝማች ንጉሤ እንደተነገረ ደጃዝማች ንጉሤ በአንድ ከፍተኛ ሹም የሚመራ ሠራዊት ልከው በእባቸው ስም ታላቅ አቀባበል ተደረገለት ። ይህም የተላከው ሠራዊት ሩሴል ከኢትዮጵያ እስኪወጣ ድረስ ከማንኛውም አደጋ እንዲጠብቀው የታዘዘ ነበር ። ደጃች ንጉሤ ይህን ሠራዊት ለጥበቃ ያዘዙበት ምክንያት ቅድም እንደተባለው እገር ወዳዱ መኳንንት ሩሴልን ይዞ ለቴዎድሮስ ለማስረከብ መስማማቱን ደጃች ንጉሤ እውቀው ስለነበረ ነው ። ሩሴልም ቢሆን ይህን የመኳንንቱን አድማ ሰምቶ ሰግቷል ። ይህን ስጋቱን ያወቁት አባ ያዕቆብም ምንም ነገር እንዳይደረግ እኔ ኃላፊ እሆናለሁ እያሉ የመኳንንቱን ኃይል እያንቋሸሹ ቢነግሩትም ሩሴል ግን ሁሉም ነገር ገብቶት ነበርና ለሊት የጀመረውን የወደብ ፍለጋ ጉዞ አቋርጦ ምፅዋ ገባ ።

ሩሴል ምፅዋ እንደገባ የደጃች ንጉሤ ተወካይና ባለሙሉ ሥልጣን ከሆኑት ከአባ እምነቱ ጋር ውል ተዋዋለ ። አባ እምነቱ ውሉን ሊዋዋሉ የቻሉት ከደጃች ንጉሤ የተሰጣቸውን ባለሙሉ ሥልጣን ወኪል መሆናቸውን የሚያስረዳ ባለማህተም ደብዳቤ ካሳዩ በኋላ ነበር ። ከውሉ ውስጥ እንዳንዱን ለመጥቀስ የፈረንሳይ መንግሥት ዙላንና የዲሴን ደሴቶች ፣ ከዊዳ እስከ ዘይላ ድረስ ያለውን የኢትዮጵያን ቀይ ባህር በር እንዲይዝ የሚል ነበር ። በውሉ አንቀፅ 5 ላይ ደግሞ በደጃች ንጉሤ ስም "....ይህ ለእናንተ የሰጠሁት ስጦታ ለፈረንሳይ ንጉስ እስከ ልጅ ልጅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል ። ከባህር የሚመጣብኝን ፣ ከእገር ውስጥ የሚነሳብኝን ጠላት (የፈረንሳይ መንግሥት) እስከ ልጅ ልጅ ድረስ ይጠብቁኛል..." የሚል ነበር ።

የኢጣሊያና የፈረንሳይ መንግሥታት ሁለቱም ከደጃች ንጉሤ ጋር ባደረጉት ውል የኢትዮጵያን ቀይ ባህር ዳርቻ መሬቶች ተከፋፍለው ቴዎድሮስ የሚጠፋበትን የጦር መሣሪያ ለደጃች ንጉሤ ለመስጠትና ለማድረስ በሚዘጋጁበት ወቅት አጤ ቴዎድሮስ ቀደም ብለን እንዳነበብነው ደጃች ንጉሤን ድል አድርገው ቆራርጠው ጣሉዋቸው ። ደጃች ንጉሤ ሲሞቱም ሃያ ዓመት ያህል የተሰፋበት የባህር በር የመያዙ ጥንስስ ተደፋ ።



ምዕራፍ 7


# የቴዎድሮስ ሰውነት—ጠባይ—ርህራሄ ፣ ጭካኔና—ፍርድ

ቴዎድሮስ እንዴት ያሉ ሰው ነበሩ? ብንል ሁሉንም ጠባይ እሟልተው የያዙ ሰው እንደነበሩ እንረዳለን ። ይህም ማለት ደግ ናቸው ፣ ክፉም ናቸው ። ሩህሩህ ናቸው ፣ ጨካኝም ናቸው ። ፍርድ አዋቂ ናቸው ፣ ፍርደ ገምድልም ናቸው ። ሁሉንም በየተራቸው እናነባለን ። ቀድመን ግን አካላቸው ምን ዓይነት ወይም እንዴት እንደነበር እንመልከት ።

ያያቸው ዱፍተን ሲፅፍ "....ወደ ጥቁረቱ የሚያደሉ ናቸው። ቯንቅላ ግን አይደሉም ።....ራሳቸው ጥሩ ቅርፅ ያለው ነው ። ጠጉራቸው ከግንባራቸው ወደኋላ የተጐነጐነ ነው ። ግንባራቸው ወጣ ያለ ነው ።....

"ዓይናቸው ጥቁር ነው ።....አፍንጫቸው በመጠኑም ቢሆን የሮማውያን ቅርፅ አለው ።....አፋቸው ውብና ፈገግተኛ (ሳቂታ) ነው ።....ጢማቸውም ሆነ ሪዛቸው በጣም ትንሽ ነው ። ጠባያቸው ደስ የሚልና ትሁት ናቸው ።....አሮፓውያኖች ሠራተኞች ለመጨረሻ ጊዜ የሚሠሩትን መድፍ ለመመልከት ንጉሱ መጡ ። በራሳቸው ላይ ምንም የለም ። እግራቸው ባዶ ያለጫማ ነው ። በዚህ እሾህና ቁጥቋጦ በበዛበት መጥፎ መንገድ ባዶ እግራቸውን ኮረብታውን ወጡ ።....እሳቸው በእግራቸው እየሄዱ እኛን በየበቅሎአችን ላይ እንድንቀመጥ ነገሩን ። እኛም ለክብራቸው ስንል እምቢ ብለን እሳቸው እሔዱበት ድረስ በእግራችን አብረን እንጓዝ ጀመር ።

"....ታቦር ተራራ ሥር ስንደርስ ቴዎድሮስ ፈረሳቸው ላይ ተቀመጡ ። ፈረሱ ላይ በወጡበት ጊዜ ከመሬት ዘለው ተቀመጡበት እንጂ እርካብ አልረገጡም ። በፈረስ ግልቢያና አቀማመጥ ጥሩ



አጤ ቴዎድሮስ (በጦር ልብስ)



ችሎታ አላቸው ። ፈረሱ እየጋለበም ከፈረሱ ላይ መውረድ ይችላሉ ።. . . .”

ዶክተር ብላንክ ጽፎት አቶ ዳኜ ወልደ ሥላሴ እንደተረጐሙት ደግሞ “. . . . በ1852 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስን ስንገናኝ ዕድሜያቸው 48 ዓመት ይሆን ነበር ። መልካቸውም ከብዙዎቹ አበሾች ጠቆር ያሉ ጠይም ፣ አፍንጫቸው ደፍጣጣ ፤ አፋቸው ሰፊ ከንፈሮቻቸው ትንንሽ ጠጋጋ ፤ ቀጠን ያሉ ፣. . . . በፈረሰኛነታቸው ፣ በጦር አወራወር ስልታቸውና በወታደርነታቸው የተመሰገኑ ፤ ጠንካራ የሆነውን ጭፍራቸውን ለማሸነፍ ችሎታ ያላቸው ሰው ነበሩ ። ጐድጐድ ያሉት ጥቋቁር ዓይኖቻቸው እገላለጥ አስደንጋጭ ሲሆኑ በሰላም ጊዜ ደስ የሚያሰኙ ፣ የሰውን ፍቅር የሚያስገኙ ፣ ለስላሳ ሆነው በተቆጡ ጊዜ ደግሞ በርበሬ መስለው የሚያስደነግጡና የሚያሸብሩ እሳተ ገሞራ የሚወረውሩ ነበሩ ። በድንገት ሲቆጡ መላ አካላቸው የሰውን ልጅ ከፍ ካለ ድንጋጤ ላይ ይጥላል ። ጠይሙ ገላቸው ሲኮስኩስ ፣ ስሱ ከንፈራቸው ሲንቀሳቀስና ጡራቸው ሲቆም በጠቅላላው ሰውነታቸው የአንበሳነት ጠባይ የያዘ አስደንጋጭ ይሆናል ።

“. . . . በተከታዮቻቸው ለመወደድ የሚችሉ የጦር ዘዴና መላ ያላቸው ሰው ነበሩ ። ሕይወታቸው ከማለፉ ከጥቂት ቀናት በፊት ባገኘናቸው ጊዜ ሙሉ የመረነት ባሕሪያቸውና ክብራቸው ፣ ከመልካም ቤተሰብ የወረሱት ባሕል ያልተለያቸው የመኳንንት ጠባያቸው አብሯቸው ነበር ። ከአንደበታቸው የሚወጡት ቃላት የሚጣፍጡ ፣ ሲስቁ የሚማርኩ ለዛ ያላቸውና በጠቅላላው ደስ የሚያሰኙ ክብር የተመላቸው ንጉስ መሆናቸውን ለመረዳት አዳጋች አልነበረም ቴዎድሮስ በሚያደርጉት በደልና የጭካኔ ሥራ ሁሉ ተገቢ ነው ተብሎ እንዲደገፍላቸው የሚጥሩና ምክንያት የሚፈጥሩ ሰው ነበሩ ። . . . .” ይላል ።

ብላንክ እንዳለው ሰውነታቸው የአንበሳነት ጠባይ ያለው ብቻ ሳይሆን ቴዎድሮስ የሚያጫውቷቸው ለማዳ አንበሶችም ነበሩዋቸው ። ራሳም በሁለተኛው ቮልዩም መጽሐፉ ላይ በደብረታቦር ስላየው ስለአንበሶቹ ጉዳይ ሲገልፅ “. . . . አንድ ቀን አራት አንበሶች አስይዘው እንድመለከታቸው ወደ አለሁበት መጡ ። ከአጠገቤም ሲደርሱ የአንበሶቹ ጠባቂ አንበሶቹን እየፈታ እንዲለቃቸው አዘዙትና ‘ምን ያህል ለማዳ እንደሆኑ እያቸው’ አሉኝ ። እነኚህ አንበ

ሶች ሲስቀቁ ውሎአቸው ከከብቶች ጋር ነው ። ሁልጊዜም ፈረሶችን እየተከተሉ ይሔዳሉ ። ንጉሡ ጥቂት ቆይተው ለአንበሶቹ ጠባቂ ምልክት ቢሰጡት ጠባቂው ሁሉንም ጠራና በማሰሪያቸው ያዛቸው ።. . . .” ብሏል ። አንዳንድ ሰዎች ቴዎድሮስ በአንበሶች መሀል ሆነው የተሳሉትን ስዕል ሲያዩ በአሊው በልበወለድነት የሳለው የሚመስላቸው አሉ ። ነገሩ ግን እርግጥ ነበር ።



አጤ ቴዎድሮስ ከአንበሶቻቸው ጋር

## ጠባይ

አጤ ቴዎድሮስ ጠባያቸው ተለዋዋጭ ነበር ። በማያስቆጣ ነገር ይቆጣሉ ፣ ይበሳጫሉ ፣ ይቀጣሉ ። በሚያስቆጣው ነገር ደግሞ ይስቃሉ ፣ ይምራሉ ፣ ወይም ዝም ይላሉ ። አለቃ ተክለ ኢየሱስም “. . . የአጤ ቴዎድሮስ ነገር ያስቸገረ ነበረ ። ስምሕረት የተባለው ለመዓት ፣ ለመዓት የተባለው ለምሕረት ይሆን ነበረ” ብለው ይጽፉና ይህንኑ ሲያብራሩት “አንዱ ያልታሰበ መዓት በመቅደላ የነበረውን እስር ገደል ሲጥል ከርስቶስ የፈረደበት አንድ መነኩሴ አላገደደው መጥቶ ይህን ታሪክ አይቼ ልሂድ ብሎ በንጉሡ ትይዩ ቆመ እርሱ ሊመከር አስቦ ነበረ ። ንጉሡ ግን ተቋጥቷልና እርሱንም



አብረህ ጣለው አሉ ። ደግሞ የተበደለ ሰው ቢጮህለት ፍርድ አዛብቶ ባፉ አረደው ። የዚህ ጊዜ ሚስቱ ስታለቅስ

“አንተ እየተሟገትህ ዳኛው እያደላ ፣
ባፋረዱህ እንጂ እኔ ምን ልበላ” አለች ። ደግሞ ያልታሰበ ምሕረት እናት አባትዋ እት ወንድሟ በአሳት ተቃጥለውባት የቆጫት የነደዳት አበራሽ የምትባል ሴት ስታለቅስ

ሺ ፈረስ በኋላው ሺ ፈረስ በፊቱ ፣
ሺ ነፍጥ በኋላ ሺ ነፍጥ በፊቱ ፣
ይህን ሳታይ ሞተች ኮሶ ሻጭ እናቱ ።
በሸዋ በትግሬ የተቀመጣችሁ ፣
በጐጃም በላስታ የተቀመጣችሁ ፣
አንድ ዛላ በርበሬ መንቀል ቸግሮአችሁ ፣
በሉ እንዲህ ቆጥቁጦ ስብልቦ ይፍጃችሁ ። ብላ ተሳደበች ። ይህን ስድብ ንጉሡ በበማ ጊዜ ፈከረ ። ካሣ አንድ የናቱ ። የሀበሻ ባል የኢየሩሳሌም ውሽማ እለና አስመጣት ። እርስዋም ተጨነቀች ። ተንቀጠቀጠች ። ስውም ልትቀጣ ነው ብሎ ቁርጥ አወቀ ።

እርስዋ ግን አይሰማም ብዬ እንዴት በጉድ ወጣሁ ፣
መንጠልጠያ ባገኝ ከሰማይ በወጣሁ ፣
መውረጃ ባገኝ ከምድር በገባሁ እያለች አለቀሰች። ምሕረት የታዘዘበት ቀን ሆኖ ማራት ። ወዲያው ሸለማት ። ብርም ባርያም ሰጣት ።. . . .በማለት ጽፈዋል ። አለቃ ወልደ ማርያም ይህንኑ የቴዎድሮስን የጠባይ መለዋወጥ ባጭር ቃል ጽፈው ሲያስረዱ “. . . .ሰውም ከሰው ተጣልቶ ከቴዎድሮስ መዓት ይጣልህ እያለ ሲረግም ፣ ሲመርቅም ከቴዎድሮስ በረከት ይክፈልህ ይል ነበር. . .” ብለዋል ።

አለቃ ወልደ ማርያም ስለዚሁ ስለቴዎድሮስ ጠባይ ሲገልጡ “. . . . በጉዞ ሲሄዱ በጭንቅ ሥፍራ ከመንገድ ላይ ወታደር ከባልደረቦቹ ብቻውን ተለይቶ አንድ ፈረስ ሁለት አህያ ሲነዳ ፈረስ ለብቻ ወደቀ ። አህያ ጭነቱን ጣለ ። ይህን ጊዜ ያ ወታደር ለማናቸው ይሁን? ተቸግሮ ጨንቆት ፈጣሪውን ሲያማርር ንጉሡ በኋላው ደርሰው ቢሰሙት ‘ለምን ፈጣሪህን ታማርረዋለህ። ይህን ንጉስ ግደልልኝ እንዳርፍ ብለህ ለምነው እንጂ’ አሉት ። እርሱም ሲመልስ ‘ጃንሆይ ፣ አልሰማም አለኝ እንጂ እኔስ ሁልጊዜ ለመንሁት’ አለ ። ቴዎድሮስም እውነትህን ነው ብለው ዝም ብለውት

ሒዱ ።....” በማለት ጽፈዋል ። የእንግሊዝ ቆንሲል ፕላውዲንም “....መጥፎ ባህሪያቸው ሳይታሰብ ድንገት ቱግ ብለው የሚቆጡት ነው ።....” ሲል ጽፏል ።

አንዲት ሴት ባሌ ሽፈታ ብላ ብትነግራቸው ተናደው “ስት ማከር ከርማ ነውኮ ። መቶ አምሳ ግረፍልኝ” ብለው አስገረፏዋት። ከዋድላ አንድ የሽፍታ አለቃ ከሁለት ተከታዮቹ ጋር ተይዞ መጥቶ፣ ሽፍቶቹ ይቅር ይበሉን እያሉ ሲለምኑ ገበያ ላይ በጥይት አስደበደቡዋቸው ። ሚስቶቻቸውም ከወንብ በላይ ራቁት ሆነው ለግርፍ በወታደሮች ተይዘው ቀርበው ሊገረፉ ሲተኙ ቴዎድሮስ “ተው አትንካቸው ። ሚስቶች ምን ያውቃሉ ። ጥፋተኞቹ ባሎቻቸው ናቸው” ብለው በነፃ መልቀቃቸውን ራሳም ጽፏል ።

የቴዎድሮስን ጠባይ መለዋወጥ ያዩት አሜዋቻቸው የነበሩት ብላታ በቀቱ የተባሉት ሰው ፈርተው ከቴዎድሮስ አጠገብ መጠጋቱን ተዉ ። ቴዎድሮስም አንድ ቀን ወደ ብላታ በቀቱ መላከተኛ ልከው “ምነው እንደወትሮህ አታጫውተኝም ፣ ምነው ጠፋህ” ብለው ቢልኩባቸው ብላታ በቀቱ ሲመልሱ “ቀድሞ በዋዛው ጊዜ አውቅ ነበረ ። አሁን ግን ረሳሁት” አሉ ።

ዶክተር ብላንክ ጽፎት አቶ ዳኜ ወልደ ሥላሴ ከተረጐሙት ደግሞ “....አጤ ቴዎድሮስ በከተማ የሚኖሩትን ሁሉ ይጠሉዋቸዋል ። በልዩ ልዩ ቦታ እየሠፈሩ የሜዳዎችን ንፁህ አየር ማግኘት ስለሚወዱ በሚመርጡት ኮረብታ ላይ ሠራዊቱ ዙሪያውን ይሰፍራል ።....ውብ በሆነ በአበሻ አገር አየር በየሌሊቱ መንቀሳቀስን ይመርጣሉ ።

“....ቴዎድሮስ በቤተ መንግሥታቸው ውስጥ ለቅርብ አገልጋይነት አዘውትረው የሚቀጥሩዋቸው ከኤሮፓውያን ጋር የሠሩትን ሰዎች ነበር ። ....ዘወትር በአጠገባቸው ከማይለየው አሽከራቸው ሌላ ብዙ ጊዜ የቴዎድሮስን ጠመንጃ ፣ ጐራዴ ፣ ጦርና ጋሻ በጥንቃቄ የሚጠብቁ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የሚኖሩ የቤት አሽከሮች ነበሩ ።

“....አጤ ቴዎድሮስ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ንጉሥ መሆናቸው ቢታወቅም በብዕራቸው ከማንም ሰው ጋር ተጻጽፈው አያውቁም ። ነገር ግን በማንኛውም ጊዜ ብዙ ፀሐፊዎች ስለሚያስከትሉ ደብዳቤ ለመጻፍ ሲያስቡ በቃላቸው እየነገሩ ያፅፏቸዋል ። የቴዎድሮስ አንጐል አስገራሚ በሆነ ሁኔታ የማስታወስ ችሎታ ስላለው የደብዳቤዎች መልስ በሚፅፉበት ጊዜ ከሳምንት ፣ ከወር ፣ ወይም ከብዙ ዓመታት በፊት ለደረሷቸው ደብዳቤዎች መልስ መስጠት ባስፈለጋቸው ጊዜ የተደረገውንና የሆነውን ሁሉ በትክክል እያስታወሱ የሚፈለገውን መልስ መስጠት ይችላሉ ።

“....አጤ ቴዎድሮስ በጀግንነታቸው የማይጠረጠሩ ንጉስ ቢሆኑም በሚሠፍሩበት ጊዜ ሙሉ ጥንቃቄ እንዲደረግ ያዛሉ ። ድንኳኑ የሚተከልበት ኮረብታ ሁልጊዜ የተጣራ ነፍጥ በያዙ ወታደሮች ሲጠበቅ ያድራል ። ቴዎድሮስም ሽጉጣቸውን ከትራሳቸውና ብዙ የተለጐሙ መሣሪያዎች ከአጠገባቸው ሳያስቀምጡ እንቅልፍ አይወስዳቸውም ።....መርዝ ከምግብ ጋር ተቀላቅሎ እንዳይሰጣቸው እጅግ ስለሚፈሩ ማንኛውንም ዓይነት ምግብ ንግሥቲቱ ወይም ምትኳ እንዲሠሩትና በሚቀርብላቸውም ጊዜ ብዙ ሴቶች ቀምሰው የምግቡን ንፁህነት ማሳየት ይኖርባቸዋል ። የሚጠጣውም ሁሉ ውሃም ይሁን ጠጅና አረቄ በዚሁ ዓይነት መንገድ መጠበቅ ስላለበት መጠጥ የያዘውን ዋንጫ ወይም ብርሌውን የሚያቀርበው አሳላፊ ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀምሶ ማረጋገጥ አለበት ።

“....አጤ ቴዎድሮስ በጣም ቀናተኛ የሆኑ ባል ነበሩ ።....ለንግሥቲቱ በጣም ስለሚጠነቀቁ ምንጊዜም ቢሆን ከሠራዊቱ ጋር አብረው እንዲጓዙ አያደርጓቸውም ። ንግሥቲቱ ደህና ሆነው ተሸፋፍነው በሌሊት በብዙ ጃንደረባዎች ታጅበው መጓዝ ይኖርባቸዋል ። በጉዞ ላይ ሳሉ ዓይናቸውን በንግሥቲቱ ላይ የሚያሳርፍ ወንድ ከፍ ካለ መከራ ላይ ይወድቃል ። አንድ ቀን ንግስቲቱን አጅቦ የሚጓዝ ወታደር ወደ ንግስቲቱ ድንኳን ተደብቆ ከተጠጋ በኋላ ድንገጡሯ (ገረዲቱ) ጠጅ እንድትሰጠው ለምኖ ሲጠጣ ባለመታደል አንድ ጃንደረባ ስላየው ተከሶ ከንጉስ ነገስቱ ፊት ቀርቦ ወንጀሉ ከተነገረ በኋላ ቴዎድሮስ በመልካም ስሜት ላይ ስለነበሩ ወታደሩ ጠጅ ይወድ እንደሆነ ስለጠየቁት በፍርሃት ይርበደበድ የነበረው ወታደር የጠጅ ዓመልተኛ መሆኑ ስለተረጋገጠ ንጉሱ ሁለት ዋንጫ ጠጅ እንዲሰጠውና እንዲደሰት ከፈቀዱ ለት በኋላ አከታትለው ለወደፊቱ ወደ ንግሥቲቱ ድንኳን እንዳይጠጋ ትምህርት እንዲሆነው እምሳ ጅራፍ እንዲገረፍ አዘዙ ። አንድ ቀን መቅደላን በጐበኙ ጊዜ የአምባው አዛዥ ባቀረበው ክስ አንዱ የአምባው መኰንን ከሚስቱ መኖሪያ ቤት ገብቶ መያዙን ስለገለፀ ቴዎድሮስ ስቀው “ምን ቂል ነህ ። እኔ ንጉስ ነኝ ፣ ነገር ግን ሚስቴን በሚገባ አልጠብቅምን?” ሲሉ ተናገሩ ።

“....ማልደው መነሳት ይወዱ ነበር ። በመጡኑ እንቅልፍ ይወዳሉ ። ከቀኑ ሁለት እስከ አሥር ሰዓት ድረስ የሚቀርብላቸውን ጉዳይ ሁሉ እያጠኑ ይፈርዳሉ ። ከሰዓት በኋላ ጠባያቸው የሚለወጥ ስለሆነ በተለይም የቤተ ክህነት ሰዎች በሚቻላቸው ሁሉ ከፊታቸው ይሠወራሉ ። ቴዎድሮስ የጥንት ልማዳቸውን ያልረሱ ሰው ስለነበሩ ሊነጋጋ ወገግ ሲል ብቻቸውን ከድንጋይ ላይ ተቀምጠው በአሳብ ባህር እየዋኙ በፀጥታ ሲፀልዩ ይታዩ ነበር ። በምግብ በኩል ብዙ የማይስገበገቡና በቀን አንድ ጊዜ ብቻ መብላትን የሚወዱ ፣ በጾም ጊዜ እንጀራና የእህል ወጥ ፣ በፍስክም ቀን እንጀራና የአሳ ወይም የስጋ ወጥ ይበላሉ ።

“....አጤ ቴዎድሮስ ተራ የሆኑ ልብሶችን ኩታና በአገር ውስጥ የተሠራ ሱሪና እጀጠባብ ይለብሳሉ ። ጫማና ባርኔጣ ግን አይወዱም ። በጣም ረጅም የሆነው ጠጉራቸው በሶስት ረድፍ ተሠርቶ ከአንገታቸው ላይ ይደርስ ነበር ። ወደ መጨረሻው ግን ስለ ጠጉራቸው የነበራቸውን ጥንቃቄና መንከባከበ በመተዋቸው ጠጉራቸው ብዙ ተጉሳቁሎ ይታይ ነበር ። በህዝቡ ብስጭት ምክንያት የተሰማቸውን ሀዘን ለመግለፅ ሲሉ በአበሻ ልማድ መሠረት ቅቤ በመቀባት የሚያደርጉትን የጠጉር መንከባከብ ትተው ነበር ። አንድ ቀን ሲያነጋግሩን ልብሳቸው በጣም ተራ በመሆኑ ይቅርታ ጠይቀው ለጥቂት ጊዜ አገራቸውን አበሻን በሰላም ሊገዙ ችለው ስለነበረ ለንጉስ የሚገባውን የክብር ልብስ እየለበሱ ንጉስነታቸውን ይገልፁ እንደነበረ አንስተው አሁን ግን በሕዝቡ ብስጭት ምክንያት በየጊዜው ለጦርነት ተሰናድተው ስለሚኖሩ እንደ አንድ ተራ ወታደር መልበስ መምረጣቸውን አስረዱን ። ቢሆንም ቴዎድሮስ የዘመነ መንግሥታቸው ፍፃሜ እንደተቃረበና የሚወድቁ መሆኑን ስለተገነዘቡት ብዙ ጊዜ በንጉሳዊ ልብሳቸውና ጌጣቸው እያሸበረቁ መታየት ጀምረው ነበር ። ይህንንም ማድረጋቸው ለሕዝቡ በስልጣን ላይ መኖራቸውን ለማሳየት አስበው ይሆናል....” በማለት ፅፈዋል ።

ዱፍተን ደግሞ “....እኛ የደረስን ጊዜ ንጉሱ አልነበሩም። ወደ ደቡብ የሶስት ቀን ጉዞ ሄደው ነበረ ። ከሳምንት በኋላ ይሆናል ደብረታቦር ተመልሰው መጡ ።....ባልደረባዬ ዎልድሜየር ንጉሱን እንኳን ደህና መጡ ብሎ እጅ ከነሳ በኋላ አንድ ወጣት እንግሊዛዊ ከእርስዎ ጋር ለመገናኘት ከውጭ ይጠብቃል ብሎ ነግሮልኝ ኖሮ ተጠራሁ ። እንደታዘዝሁት ባርኔጣዬንና ጫማዬን አው



ልቄ ከደጅ አስቀምጬ ገባሁ ።....ዝነኛው ቴዎድሮስ የታወቀውን ጦረኛ ፣ የታላቁ አገር የበላይ ፣ ከጥጥ የተሰራ ሸሚዝና ሱሪ ለብሰዋል ። እነሱም ቢሆኑ በጣም ንፁህ አይደሉም ። በዙፋን ላይ አልተቀመጡም ፣ ከመሬት አንድ ጫማ ያህል ከፍ በምትል ድንክ ላይ ተቀምጠዋል ። በመጀመሪያ ጊዜ ንጉሱ አይደሉም ብዬ አስቤ ነበር ። እጅ የነሳሁትም ያለቦታው ለሌላ ሰው ነው ብዬ ነበር ። እንድቀመጥ አዘዙኝ ። እግሬን አጣምሬ ተቀመጥሁ ። በመጠጥ በኩል አረቄና ጠጅ መጥቶ በሚገባ ተጋበዝን ። በምግቡም በኩል የጤፍ እንጀራና ስጋ እንደ ቁርስ ተብሎ በልተናል ። ንጉሱም እየደጋገሙ አረቄ ይጠጣሉ ።....ይህን ያህል አብዝተው ጠጪ አይደሉም ። ደጋግመው ይጠጡ እንጂ ካንድ የተወሰነ ደረጃ ሲደርሱ ያቆማሉ ። አብዛኛውን ጊዜም የሚጠጡት ከቴምርና ከማር የሚሠራውን የሱዳን አረቄ ነው ።....” ብሏል ።

በሌላ ጊዜ ስለሆነው ሁኔታ ዱፍተን ሲፅፍ “....በማግሥቱ ለፈረንሳዩ ቆንሲል ለሌዣን ይፋ አቀባበል አደረጉለት ። ለአቀባበሉም ስርዓት መድፍ ተተኩሶ በዙፋናቸው ተቀምጠው ተቀበሉት። የተቀበሉበትም ቤት ግድግዳው ረጅም ሆኖ የሚያማምሩ ምንጣፎችና ዥንጉርጉር ጨርቆች ተደርገውበታል ። መሬቱም እንደዚሁ ሙሉውን ተነጥፏል ። ከናፖሊዮን የተላከውንም የወዳጅነት ደብዳቤ ከሌዣን እጅ ተቀበሉ ።

“....ሌዣን አሽከሩን የስጦታውን እቃ እንዲያቀርብ አዘዘ ። ሽጉጦች ፣ ውብ የሆኑ እቃዎች ፣ በብዙ ሳጥን የተያዙ የሀር ልብሶችን አቀረበ ።....ለስጦታው ንጉተው በተመስጦ አይመለከቱም። ....እንዱ ብቻ አንዱን ሽጉጥ አነሱና ወደ አይናቸው አስጠግተው እያነጣጠሩ ተመለከቱ ። ምንም ነገር ሳይናገሩም እጠገባቸው ለቆመው አሽከር ሰጡት ። ሀር ጨርቆቹንማ መለስ ብለውም አላዩዋቸውም ። ከሳጥኑ መጨረሻ ያለው እስኪወጣም አልጠበቁም ። “እንዲህ ዓይነቱ ነገር የሴት ስለሆነ ለእቴጌይቱ ይሁን” አሉ ። ከሀሩ ልብስ ይልቅ በሳጥኑ መከደኛ ላይ የተለበዱት ባለቀለም ስእሎች ስሜት ሰጡዋቸው.... በማለት ፅፏል ።

ቴዎድሮስ በሴት በኩል ያላቸው ጠባይ እንደ አብዛኛው ወንድ ሁሉ መሀከለኛ ቢሆንም እንደሌላው ጠባያቸው ሁሉ ቆንጆ ካዩ የማታመልጣቸውና የሚንቁም ወንድ ነበሩ ። በዚህ በኩል ያላቸውንም ጠባይ እንዲህ ዓይነት ናቸው ብሎ ለመደምደም አስቸጋሪ ነው ። እንዳንዱን ሁኔታ እንመልከት ።

ወይዘሮ የተመኙ የየጁ ተወላጅ ሲሆኑ ባላቸውም የየጁ ኦሮሞ ነበር ። ወይዘሮ የተመኙ በእስልምና ሃይማኖት የሚያምኑ ሴት ነበሩ ። ቴዎድሮስ የእኚህን ሴት ቁንጅናና ዘንፋላነት እንደሰሙ ከባላቸው ነጥለው አስመጡዋቸው ። ክርስትና አስነስተውም ስማቸውን የተመኙ ብለው አስቀሩዋቸው ። ባልዬውም ይገሉኛል ብሎ አገር ጥሎ ጠፋ ። ቴዎድሮስ ግን እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ የተመኙን ወድደዋቸው ይኖሩ ነበር ።

ቴዎድሮስ የደንቢያዋን ወይዘሮ ሒሩትን በቁንጅናቸው አድንቀውና ወደው ቁባት አድርገው አስቀምጠዋቸው ነበር ። ወይዘሮ ሒሩት በቴዎድሮስ ተግባር ይበሳጩና ያዝኑ ስለነበር ጠፍተው ከጣና ደሴት ደቅ ከሚባለው ገዳም ገብተው ተደበቁ ። ቴዎድሮስም በያለበት አስፈልገው ስለጠፉባቸው አዝነው ተቀመጡ ። አቶ ገሪማ ታፈረ እንደጻፉት ይህን ሚስጥር የሚያውቀው የቴዎድሮስ አዝማሪ በግብር ላይ ሲዘፍን "ወድቃ ተሰብራ ያለ ውሉ ፣

ሒሩት ደቃለች አሉ" ብሎ በቅኔ ግጥም በመናገሩ ቴዎድሮስ ወይጦዎችን ሰብስበው በጀልባ ሰው ልከው ወይዘሮ ሒሩትን አስይዘው አስመጡዋቸው ።

ይህን የመሳሰለውን ስናይ ቴዎድሮስ ለውበት ያላቸውን አድናቆትና ፍቅር እንረዳለን ። በሌላው ሁኔታዎች ደግሞ ያን የመሰሉት ውበት አፍቃሪ ወንድ ፣ መነኩሴ መስለው እናገኛቸዋለን ።

በጐንደር ከተማ አቅራቢያ ቀሃ ወንዝ አጠገብ አጤ ሰቀላ ከተባለው ኮረብታ ላይ ቴዎድሮስ የቁንጅና ውድድር እንዲደረግ አዘዙ ። ቴዎድሮስ ትእዛዙን ይስጡ እንጂ ነገሩ የመጣው ከኤሮፓውያኖቹ ከነቤል ይመስላል ። የምርጫው ወይም የቁንጅና ውድድሩ ሊቀ መናብርት ኢትዮጵያዊው ገብርዬና እንግሊዛዊው ጆን (ዮሐንስ) ቤል ነበሩ ።

ራሳቸው አጤ ቴዎድሮስ ባሉበት የቁንጅናው ውድድር ተካሒዶ 1ኛ ጣይቱ ይልማ ሆነች ። ጣይቱ ይልማ ለውድድር የቀረበችው ከሰቀልት ወረዳ ከመቋሚያ ማርያም ሲሆን ፣ የደጃዝማች ይልማ አሰፋ ልጅ ናት ። 2ኛ/ የወጣችው ወይዘሮ ተዋበች የተባለች ናት ። ተዋበች እስላም ስትሆን ባልዋም መሐመድ ኩርማን ይባል ነበር ። ተዋበች 2ኛ. ለመውጣት የቻለችው በጠጉርዋ ማማር፣ በቁንዳላዋ አወራረድና በሹርባዋ አረዛዘም ነበር ። እነኚህን የመሳሰሉ ከማንም የሚበልጡ ውብ ሴቶች ተመርጠውላቸው ሳለ ቴዎድሮስ



ከጉዳይም ሳያገቡዋቸው ተዋቸው ። አቶ ቢወጣ ኪዳኑ በዘመኑ በያዙት ማስታወሻ እንደገለጡት ጣይቱ ይልማን በጋፋት የመድፍ ሠራተኞቹ አለቃ የነበረው ወርመር (ኦርማኤል) አግብቷት ብዙ ልጆች ወልዳለታለች ።

## ርህራሄ (ደግነት)

ቴዎድሮስ ደግ ሰው ነበሩ ። ወዳጃቸው የነበረው ዎልድሜየር ሲጽፍ "....አንድ ቀን ከንጉሥ ቴዎድሮስ ጋር በየባላገሩ ስንዘዋወር አንዲት ድሃ ሴት አጋጠመችን ። ሴትዮዋ ምንም ልብስ ያለ ለበሰች ፈፅማ ራቁትዋን ነበረች ። ንጉሱ ከበቅሎአቸው ወረዱና የለበሱትን ሸማ ከላያቸው ላይ አንስተው ሴትዮዋን አለበሷት ። ከዚያም በኋላ ገንዘብ ሊሰጧት ፈልገው ገንዘብ አጡ ። ወደኔም ዞር ብለው እስቲ ጥቂት ብር እንዳለህ አበድረኝ አሉኝ ። እኔም 'እሺ ጃንሆይ ፣ አሁን ለግዜው አምስት ብር አለኝ ። እሱን ልስጦት' ብዬ ሰጧቸው ። እሳቸውም ገንዘቡን ከኔ ወስደው ለድሃይቱ ሴትዮ ሰጧት ። ሴትዮዋም ደስ ብሏት ሄደች ። ማታ በሠፈር ንጉሱ አንድ መቶ ብር ሰጡኝ ። እኔም 'ጃንሆይ እኔ የሰጠሆት አምስት ብር ነው ለምን 95 ብር አስበልጠው ይሰጡኛል?' አልኳቸው ። እሳቸውም 'የመለስኩልህና የሰጠሁህ እንደ ንጉስነቴ ነው ።' አሉኝ ። አመስግኜም እኔም እየተደሰትኩ ወደ ቤቴ ሄድሁ.... ብሏል ።

በሌላ ቀን ስለሆነው ነገር ደግሞ ይሄው ዎልድሜየር ሲጽፍ ".... አንድ ቀን ከንጉሱ ጋር በጋማ ከብት ተቀምጠን በአገር ውስጥ እንዘዋወር ነበር። አንድ ሰው ከመንገዳችን ላይ ቆመና ጃንሆይ ጃንሆይ እያለ ጮኸ ። ንጉሱም 'ምን ሆነሃል ተናገር' አሉት ። ሰውየውም 'ከመንገድ ላይ ሃያ ብር አገኘሁ ። ይህ ገንዘብ የማን እንደሆነ እኔ አላውቅም ። በዚህ ምክንያት ገንዘቡን ወደ ጃንሆይ አመጣሁት' አላቸው ። ንጉሱም 'ይሄ ያንተ የዋህነት ነው ። አሁንም ገንዘብ የጠፋው ሰው እስቲገኝ ድረስ ገንዘቡን አንተጋ አስቀምጠው ። ስላንተ ታማኝነት ግን እኔ ሌላ ሀያ ብር እሰጥሃለሁ' ብለው ሰጡት ። ሰውየውም እየተደሰተ ሔደ ። ይህን ወሬ አንድ ሌላ ሰው ሰምቶ እንዲህ በቀላሉ ገንዘብ የሚገኝ ከሆነ የቀበርኩትን አርባ ብር አውጥቼ ለንጉሱ ላቅርብ ብሎ ይዞ መጣና 'ጃንሆይ ፣ ይሄንን ገንዘብ ከመሬት አገኘሁት ። የማን ገንዘብ እንደሆነ ስለማላውቅ

ወደ እርስዎ አመጣሁት’ አላቸው ። ንጉሡም የሰውየው አታላይነት ገብቷቸው ‘ገንዘቡን ወስደህ ለኔ ገንዘብ ያዥ ስጥ’ አሉት ። ሰውዬውም እያዘነ ገንዘቡን ለንጉሡ ገንዘብ ያዥ አስረክቦ ወደ ቤቱ ሔደ. . .’ በማለት ጽፏል ።

ዱፍተን ለለ ቴዎድሮስ አዛኝነት ሲጽፍ “. . . .ድሆችን እራሳቸው እየተቆጣጠሩ ይጠብቃሉ ። ድንኳናቸው በተተከለበት ቦታ ሁሉ የድሆችን አቤቱታ መስማት ይወዳሉ ። ሁልጊዜ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የድሆችን ጉዳይ ይሰማሉ ። በጉዞም ላይ በሳምንት በሺዎች የሚቆጠር ብር ለድሆች ይሰጣሉ ። ይህንንም ስጦታ በሚሰጡበት ጊዜ “ድሆችን ባልረዳ ለእግዚአብሔር ያሳጡኛል ። እኔም እራሴ ድሃ ነበርኩ ይላሉ ።. . . .” ብሏል ።

ፕላውዴን እንደጻፈው ደግሞ “. . . .አንድ ቀን ለጉዞ ልንነሳ ስንል ስጦታ ሰጡኝና አልቀበልም ብላቸው ‘ አንተ ልጄ ነህ ። ከኔ የምትፈልገውን ነገር ስሰጥህ ለምን አትቀበልም?’ አሉኝ ። እኔም የታዘዝኩት ምን እንደሆነ ብነግራቸው ‘ግድ የለም ። መልክተኞች ሁሉ ከመንግሥታቸው እንደሚከፈላቸው አውቃለሁ ። አገሬ ግን እንግዶችን እንድንቀበል ትጠይቀናለች ። የእንግዶችን እግር ማጠብ ይገባናል ።. . . .ክፍያ የምከፍልህ አይደለም ። የምሰጥህ ለእህልና ለውሃ ነው ። መቀበል አለብህ ። ከኔ የበለጠ ሀብታም መሆንህን አውቃለሁ ። ይሄ ግን አሁን ብድር ነው ። አንተ ደግሞ በተግባር ትከፍለኝ ይሆናል ። ባንተም ረዳትነት ብዙ ቤቶችን እገነባለሁ።’ አሉኝ ። እኔም ‘ ምንም አይደለሁም ። ለእርሶ የሚጠቅሙ የኔ ንግሥት ናቸው’ ። አልኳቸው ። እሳቸውም ‘ስማኝማ ። ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የምድር ነገሥታት ሁሉ በኔ ላይ ተቃውመው ለመነሳት አይችሉም ። ስለዚህ አልፈራቸውም ። ግን ያንተ ንግሥት አንተን ወደኔ ልከውልኛልና ክርስቲያን ናቸው ። እምነታችንም ያስተሳስረናል ። ክርስቶስ ወዳጅነታችንን ፈቅዷል ። እግዚአብሔር በዚህ መልካም መንገድ ይምራኝ’ አሉኝና ለብቻዬ ወስደው አንድ ሺ ብር ሰጡኝ ። ከዚያም እጄን ይዘው ሰው ሁሉ ሟች ነው ። አንድ ነገር በኔ ላይ ቢደርስ ልጄ ፣ ወዳጄ ሁነኝ ። ወደ አገርህም ሁላችሁንም የሚወድ ሰው ነው ብለህ ጻፍ ።. . . .እወድሃለሁ ። አምንሃለሁ ። በል ሂድ ። ደህናዋል አሉኝ. . . ” ብሏል ።

ፕላውዴን ጁን 25 ቀን 1855 ወደ አገሩ ባስተላለፈው ሪፖርት “. . . .ንጉሥ ቴዎድሮስ በዕድሜ ወጣት ናቸው ።. . . .ትሁ



ትና ደስተኛ ናቸው ። የባርያ ንግድን አጥብቀው የሚቃወሙ ናቸው ። የተሸጡትን ባርያዎች እሳቸው እንደገና የተገዙበትን ዋጋ እየከፈሉ በማስለቀቅ ነፃ ያወጡዋቸዋል ።. . . . ወታደሩም ከሚከፈለውና እየሠራ ከሚያገኘው ገቢ በስተቀር ከገበሬው ዘንድ እንዳይደርስ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥተዋል ።. . . .” በማለት ለሕዝቡ ያላቸውን ርህራሄ ገልጿል ።

ዎልድ ሜየር ስለ ባርያዎች ጉዳይ በጻፈው በጐንደር አካባቢ ባርያ ነጋዴዎች የሚወስዷቸውን አስጥለው በብዙ መቶ የሚቆጠሩትን በነፃ ከለቀቁ በኋላ ጥቂቶቹን ለዎልድሜየር ሲልኳቸው በጻፉት ደብዳቤ ‘‘. . . .እነኚህን ወጣት ልጆች ጥበብና ሃይማኖቶች እንድታስተምራቸው ይሁን ። እንደእነኚህ ያሉትንም ያልታደሉ ፍጥረቶች ባገኘሁ ጊዜ ሁሉ እልክልሃለሁ ። ደስ እንዲላቸው ። የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ የምችለው እኔ ነኝ. . . . ” ብለውታል ።

ቀደም ብለን እንዳነበብነው የደጃዝማች ከንፉ ልጆች መኰንንና ይልማ የጐጃሙን ገዥ ብሩ ጐሹን ቸንቲ በር ከተባለው ሥፍራ በተዋጉ ጊዜ ያን ጊዜ ካሣ ይባሉ የነበሩት ቴዎድሮስ ፣ ከደጃች ከንፉ ልጆች ጋር አብረው ነበሩ ። የደጃች ከንፉ ልጆች ድል ሆነው ጦራቸው በተበታተነ ጊዜ የያኔው ካሣም አምልጠው አለፋ ላይ ካንድ ሰው ቤት ተደብቀው ወር ሙሉ መቀመጣቸውን አንብበናል ። ብዙ ቆይቶ የያኔው ካሣ ከእቴጌ መነን ጋር ተዋግተው ድል ካደረጉ በኋላ ሠራዊታቸውን በየባላገሩ ቤት ምሪት ሰደዱት ። ምሪት ከገባባቸው ባላገሮች መሀል ያ ድሮ በውሮ ወር ሙሉ ከደበቃቸው ሰው ቤት 12 ወታደሮች ገብተው ሠፈሩበት ። ይህ ሰው ሊቀለቡ የገቡበት ሰዎች ስለበዙበት በሌሊት ተነስቶ ወደያኔው ካሣ ዘንድ ሔዶ ጮኸ ። ደጃች ካሣም ሰውየውን በድምጡ አውቀው ወታደር ልከው አስይዘው አስመጡት ። እንደመጣም አንተ እገሌ የምትባለው ሰው አይደለህም? ብለው ቢጠይቁት አዎን ነኝ አለ ። ከዚያም የሠራላቸውን ውለታ ሁሉ ነግረው ከእልፍኝ አስገብተው ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ተዋበች ጋር አስተዋውቀው ጋበዙት ። በመጨረሻም አንድም ወታደር እንዳይገባበት አድርገው ሃያ ብር ፣ ስምንት በሬ ፣ ስምንት ላም ፣ ሴትና ወንድ ባርያዎች ሰጥተው አገሩንም የሱ ግዛት ጉልት አድርገው ሰጥተው ሰደዱት ። ይህም ቴዎድሮስ አስታዋሽ አእምሮና ብድር መላሽ መሆናቸውን ያሳያል ።

በሽፍትነት ዘመናቸው ስማቸውም ካሣ በነበረበት ጊዜ ከወዳጃቸው ከሌላው ሽፍታ ከእንድሪስ ጋር ሆነው አምበለይ ከሚባል

ከሻንቅላ አገር ዘመቱ ። ከዚያም ብዙ ዘረፋ አግኝተው 600 የሚ
ሆን ሻንቅላም ተማረከ ። የተዘረፈው ፍየልና በግም ለቁጥር አስቸ
ግሮ ነበር ። ይህ ሁሉ ሲሆን ከካሣ በኩል ሁለት ወታደሮች ሻን
ቅላ ሲያባርሩ በጦር ተወግተው ወድቀው መቅረታቸውን ካሣ
ሰሙ ። እንደሰሙ ሰባት ያህል አሽከሮቻቸውን አስከትለው ሁለት
ወታደሮቻቸው ወደ ወደቁበት ቦታ ሔዱ ። ከቦታውም ሲደርሱ
ሁለቱ ወታደሮች ከፉኛ ተወግተው ወድቀው አገኙዋቸው ። አን
ዱን የቆሰለ ወታደር አሽከሮች ሲሸከሙ አንዱን ግን እሳቸው ተሸ
ከመው ይጓዙ ጀመር ። በጉዞው ጊዜ ካሣ የተሸከሙት ወታደር
ከሚፈሰው ደም ብዛት የተነሳ ደሙ በካሣ ጀርባ እየተንቆረቆረ
በእግራቸው እያለፈ ይወርድ ጀመር ። አለቃ ዘነበ እንደፃፉት በደም
የተበከለው የልጅ ካሣ እግር "....በክረምት እንደሚሔድ ሰው
ብዙ ጭቃ አነሳ" ። ካሣ እንዲህ ለፍተው ከሠፈር ያደረሱዋቸው
ሁለቱ ወታደሮች ከሠፈር ሲገቡ ሞቱ ።

ወሎ ውስጥ ለጋምቦ ላይ ጮቄ ጨሜ በተባለው ቦታ ሠፍ
ረው ሳለ በኤሮፓ እንደሚዘንበው በረዶ አይነት ወይም እንደ
አመድ የሚበን በረዶ ዘነበ ። ይህም በሰውም በከብቱም ላይ ሁሉ
እየወረደ እንደ ጭቃ እየተመረገ ተቀመጠ ። አቅመ ቢሶችና ሕመ
ምተኞች በበረዶው ምክንያት ብዙዎቹ ሞቱ ። በዚህ ጊዜ ቴዎድ
ሮስ ድንኳናቸው ውስጥ ነበሩ ። መጠጊያ ወይም መከለያ የሌለው
ሕዝብ በበረዶው መመታቱን ያዩት ቴዎድሮስ ሕዝቡ በእንደዚህ
ያለ ሥቃይ ላይ ሆኖ እኔ ከድንኳን ውስጥ ተጠልዬ አልቀመጥም
ብለው ከደጅ ወጥተው በረዶው ከሚወርድበት ውስጥ ቆሙ ። ሠራ
ዊቱንም እግዚኦ በሉ ብለው አዘው እግዚአታው ሲጀመር በረዶው
ቆሞ ፀሐይ ወጣ ።

## ጭካኔ

አጤ ቴዎድሮስ የበፊት ሚስታቸው እቴጌ ተዋበች ከሞቱ
በኋላ ጠባያቸው ተለዋውጦ ጨካኝ ሆኑ የሚሉ አሉ ። ፈረንጅ
ፀሐፊዎችም መካሪያቸው ጆን ቤል ከሞተ በኋላ መካሪ በማጣት
የጭካኔ ሥራ ጀመሩ እያሉ ፅፈዋል ። እንደተባለው የተዋበችና
የቤል መሞት ቴዎድሮስን ከብስጭት ላይ ቢጥልም አጠቃሎ የቴ
ዎድሮስን ጠባይ ለወጠ ለማለት አይቻልም ። ገና በሽፍትነት ሳሉ



ቀደም ብለን እንዳነበብነው በህብረት እየዘረፉ አብረው ሊበሉ
የተስማሙዋቸው ሽፍቶች ለየራሳችን ያገኘነውን እንብላ ቢሏቸው
ተቆጥተው የተያዙትን ሰባት ሽፍቶች ጉልበት ጉልበታቸውን
ቆርጠው ጣሉዋቸው ። ከእንዲህ ዓይነቱ ቅጣት መግደል የተሻለ
ነው ። ከዚያም ሌላ የሱዳኑን ወዳጃቸውን የእንድሪስን ጠላቶች ድል
አድርገው ከማረኩ በኋላ የእሳቸው መጨረስ እንሶ 210 ኢትዮጵ
ያውያኖችን በፈለገህ መንገድ ግደላቸው ብለው ለእንድሪስ ሰጡት ።
እንድሪስም ሁሉንም በሰይፍ ፈጃቸው ። ራሳቸው ካሳም በዚሁ ጊዜ
ከተማረኩት ሰዎች መሀል አምሳዎቹን ሁለት ሁለት ጆሮአቸውን
እያስቆረጡ ግፍ ከሰሩ በኋላ ለቀቁዋቸው ። ይህን የመሳሰለውን
ቅጣታቸውን ስናይ ቴዎድሮስ ጨካኝነታቸው ከመጀመሪያው
ጀምሮ እንጂ ከተዋበችና ከቤል ሞት በኋላ አይደለም ።

ወይዘሮ ተዋበችን ካገቡም በኋላ ቢሆን ብዙ የጭካኔ ተግባሮ
ችን ፈፅመዋል ። ቀኛዝማች ወንድይራድን ራትና ምሳህ ኮሶ ይሁን
ብለው በእንስራ ሙሉ የተበጠበጠ ኮሶ ሰጥተው እያጠጡ በጭካኔ
የገደሉዋቸው ወይዘሮ ተዋበች ሳይሞቱ በፊት ነው ። ጊምባ ላይ
የተማረኩ 47 ኦሮሞዎችን ሁለት ሁለት እጃቸውን እየቆረጡና ቁራ
ጩን በያንገቱ ላይ በገመድ እያሰሩ አገርህ ግባ ብለው የሰደዱት
እቴጌ ተዋበችም ቤልም እያሉ ነው ። ይህን የመሳሰለውን ብዙ
ቅጣት ስናይ ቴዎድሮስ ከተዋበችና ከጆን ቤል ሞት በኋላ ጠባ
ያቸው ተለወጠ የሚባለው አባባል ትክክል አይመስልም ። ምናል
ባትም ከሁለቱ ሰዎች ሞት በኋላ የበለጠ ጨካኝ ሆኑ ቢባል
ይሻላል ።

አለቃ ገብረ ሥላሴ እንደፃፉት ደግሞ ቴዎድሮስ ጭካኔ ያበ
ዙት የሸዋው ምኒልክ ካመለጡ በኋላ ነው ይላሉ ። ይህንንም ሲያ
ብራሩ "....ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ጋር....
ከዕለታት ባንድ ቀን ሲነጋገሩ "አባቴ በሀገርዎ ሳሉ የኔን ወሬ
ይሰሙ ኖርዋልን ?' ብለው ጠየቋቸው ። እሳቸውም 'ቸር ነህ ፣
ጀግና ነህ ይሉሃል ። ነገር ግን የሸለመውን የሾመውን ያስራል ፣
ይገድላል ፣ ይቆርጣል ይሉሃል' አሏቸው ። አጼ ቴዎድሮስም መለሱ
'በሽፍትነቴ በረሃ ለበረሃ ስሔድ መነኩሴ አገኘሁ ። ያም መነኩሴ
ትነግሣለህ ፣ ነገር ግን ያሳደግኸው ሰው ከቤትህ የወጣ ዕለት መን
ግሥትህ ያጥራል ብሎ ነገረኝ ። ይህን የማደርገው ስለዚህ ነው"
አሏቸው ። አቡነ ቄርሎስም 'እግዚአብሔር የሚያነግሰውን ሽፍኖ
ይጠብቀዋል እንጂ አንተ መቼ ታገኘዋለህ'....አሏቸው...."

ይላሉ ይህም እውነት ቢሆን እንኳ ቴዎድሮስ ጭካኔ የጀመሩት ምኒልክ ከመማረካቸው በፊት ገና በሽፍትነት ሳሉ ነው ።

አንዳንድ ሰዎች ቴዎድሮስ ጨካኝ የሆኑት የአገሪቱን አንድነት ለማስከበር ሲሉ ነው ይላሉ ። ይህም እውነት ቢመስልም ሕዝብ የሚያብረው በሰላም መንገድ እንጂ በኃይልና በጭካኔ አይደለም ። የኃይል ሥራ ለጊዜው ላይ ላዩን መልካም ውጤት የሰጠ ቢመስልም ውስጡ ግን የሚያመረቅዝ ነው ። ለቴዎድሮስም በሰላም የገቡላቸው ሁሉ የኃይል ሥራቸውን በመመልከትና በመስማት ነግ በኔ እያለ ከዳቸው እንጂ ለጥ ሰጥ ብሎ አልተገዛላቸውም ። ኢትዮጵያን አንድ አድርጌ እገዛለሁ ያሉት ቴዎድሮስ በመጨረሻው ሰዓት የእንግሊዝ ጦር በመጣ ጊዜ ሰላምጌ ላይ ሆነው "....ወደ እምባው አመልክተው 'ግዛቴ ያ ብቻ ነው ። ስለዚህ ከዚህ እቆያችዋለሁ ። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ያለው ይሆናል..."ብለው መናገራቸውን ዶክተር ብላንክ ጽፏል ።

የቴዎድሮስን የአስተዳደር ሁኔታ እያየ ሠራዊቱና መኳንንቱ ባይከዳቸው ኖሮ የኢትዮጵያ ወሰን ለእንግሊዝ ጦር ክፍት ሊሆን ለት ባልቻለ ነበር ። እንግሊዞችም ቢሆኑ እስረኞቻቸውን ለማስፈታት ለመግባት የደፈሩት የመኳንንቱን መለያየት በማየትና ምቹ ክፍት ጉዳና በማግኘታቸው ነው እንጂ በጉልበታቸው ብቻ ተመክተው ቢመጡ ኖሮ ምናልባትም በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍ ያለ የደም መፋሰስ ይደርስ ነበር ። ግን የሁሉም በቴዎድሮስ ላይ ማደምና የሁሉም መከፋፈል የቴዎድሮስን መንግሥት አዳከመ ። ዶክተር ብላንክ ሲጽፍ "....አጤ ቴዎድሮስ ከጥቂት ወራት በፊት ይገዙት የነበረው ግዛት ሁሉ ቀረና በጣም ትንሽ እርሷንም ሊከላከሉዋት የማይችሏት መሬት ቀረቻቸው ። በሰኔ ወር 1859 ዓ.ም. ያለ ግዛት ንጉስ ፣ ያለ ጦር ሠራዊት ጀኔራል ሆኑ ። መቅደላና ዙር አምባ በእርሳቸው ወታደሮች እንደተጠበቁ ነበሩ ። ከእነዚህ ቦታዎች በስተቀር ግን የኔ ነው የሚሉት አንድም ቦታ አልቀረ...." ብሏል ። ያኔ በቴዎድሮስ ጉን ጥሩ አማካሪዎች ቢኖሩና ቴዎድሮስም ተቀባይ ቢሆኑ ኖሮ የቴዎድሮስ መንግሥት ቶሎ ለመውደቅና በየጊዜው ከመዋጋት ባልደረሱ ነበር ። ነገር ግን ዙርያቸውን የከበቧቸው ወዳጆቼ የሚሉዋቸው ሁሉ የእለት ጥቅማቸውን ፈላጊዎችና መስሎ አዳሪዎች በመሆናቸው ለቴዎድሮስ አወዳደቅ መሰላል ዘር ጣጮች ሆኑ ። ቴዎድሮስም ቢሆኑ "የሚጠሉህን ሰዎች ከማጥፋት ይልቅ የሚጠሉብህን ነገር አጥፋ" የሚለውን የምሥራቃውያንን ምክር አልተከተሉም ።



ቴዎድሮስ ከሠሩዋቸው የጭካኔ ተግባሮች ጥቂቶቹን እንመልከት ። የሸፈተባቸውን ቾኮልን ለመውጋት ወደ ደንበጫ ሔደው ሳለ ቾኮል አመለጣቸው ። ከአሽከሮቹም ሰድስት ሰዎች ተማርከው ስለ ነበረ እነሱን በገበያ ላይ ሰቀሉዋቸው ። አንደኛው ከቴዎድሮስ አሽከር ጠመንጃ ሲቀማ ተይዞ ነበርና ያንን ሰው ከመድፍ እፍ ላይ አስጠግተው አስቁመው የመድፉ ጥይት እንዲተኮስ አዘዙ ። ሲተኮስም ሰውየውን ብትንትኑን አውጥቶ ገደለው በማለት ጸሐፊ ትእዛዛቸው አለቃ ዘነበ ጽፈዋል ። ከአለቃ ዘነበ መጽሐፍ የምናነበው ሌላም አለ ።

ግራዝማች ዓለሜ የሸፈቱ ጊዜ አንዱ አሽከራቸው ተይዞ መጣ ። ከንጉሱ ችሎት በቀረበ ጊዜም ቴዎድሮሰ የሞት ፍርድ ካስፈረዱበት በኋላ "....መቅደላ ፣ ወረሂመኖ ፣ ደላንቴ ፣ ዳውንቴ ፣ ዋደሌ ጦርህን ከዚህ ሰው ደም ያላስነካህ ጠላቴ ነህ ...." ብለው በመናገራቸው ያ ሁሉ ሕዝብ በንጉሱ ትእዛዝ መሠረት ሁሉም በጦር ሲወጋው ብትንትኑ ወጥቶ ለምልክት እንኳ የሚታይ ሥጋው ከመሬት ላይ ጠፋ ።

አለቃ ወልደ ማርያም እንደጻፉት ደግሞ ቲዝባ ከሚባለው አገር ሕዝብ መሀል ጥቂቶቹ ከቴዎድሮስ ዘንድ ቀርበው "ጃንሆይ ፣ ሁሉንም እንደ አባትህ አደር ብለውታል ። እኛም ያባታችን ማደሪያ ሌሊት ገስግሰን በረት ከፍተን ፣ ላም ነድተን ፣ ሰው ሲተኛ ግድግዳ ምሰን ፣ ያገኘነውን ወስደን እንኖራለንና ይሄው ይፈቀድልን ብለው አመለከቱ ። ቴዎድሮስም "አሁን ያላችሁት ጥቂቶች ናችሁና ሁላችሁም አንድ ሁናችሁ ንገሩኝ" ብለው በቀጠሮ መለሱዋቸው ። በቀጠሮው ቀን ሽማግሌና ሕፃን ሁሉ ሳይቀር ሕዝቡ በሙሉ መጣ ። ቴዎድሮስም በለው ብለው ሲያዙ ወታደሩ ያን ሁሉ ሕዝብ በጦርና በጉራዴ ፈጀው ። በፊት የቀረቡት ተንኮለኞች ወይም አላጋጮች ብቻ መቀጣት ሲገባቸው ምንም የማያውቀውን ባላገር ሁሉ በማሰ ጉምጀት አሰብስበው ማስፈጀቱ መልካም ድርጊት አልነበረም ።

ደጃች ተድላ ጓሉን ለመያዝ አጤ ቴዎድሮስ ገስግሰው በድንገት ደርሰው በተዋጉ ጊዜ ስምንት ሺ ሰዎችን ማረኩ ። ይህን ሁሉ ምርኮኛ እንጅባራ ላይ ሰብስበው ራሱን ሲያስቆርጡ ውለው ጊዜው ሲመሽ የተረፈው ሰው ተቆጥሮ አደረ ። ሲነጋጋ ንጉሱ ተነስተው ያደሩትን ሰዎች አምጣ ብለው አስቀርበው ሁሉንም አስደብድበው ፈጁት ። ያን ሁሉ ከምር ሬሳ እየተዘዋወሩ ሲያዩ ከሬሳዎቹ መሀል እንዱ አልሞተ ኖሮ ሲንፈራገጥ አዩት ። ቴዎድሮስም "ሁሉንም

እንዲሁ ሳትገድሉ ነው የጣላችኋቸው'' ብለው ያን የሚንፈራገጠውን ራሳቸው ገድለው ሌላው ሁሉ እየታየ ያልሞተው እንዲገደል አዘዙ ። ሁሉም ካለቀ በኋላ "ይህን ሁሉ ጠላቴን በጄ ጥሎ እንዲህ አስተኝቶ ያሳየኝ እግዚአብሔር ይመስገን'' ብለው መሬት ሰመው ከድንኳናቸው ገቡ ። አልቃሽም

"እንጥረኛው ብዙ ከንጉሱ ቤት
ባል አልቦ አደረጉት ይህን ሁሉ ሴት'' ብላ ገጠመች ።

በ1859 ዓ.ም. የአማራ ሳይንት ሰዎች ሊከዱ ነው ብለው ስለነገሩዋቸው ቴዎድሮስ ከአማራ ሳይንት መኳንንት 400 ሰዎች አስይዘው ሁሉንም በጐራዴ አስደብድበው ፈጁዋቸው ። አንድ ሰው ከዋድላ ሰዎች ጋር ቢጣላ ከቴዎድሮስ ዘንድ መጥቶ ዋድሎች ሊከዱዎት ነው ብሎ ነገራቸው ። ቴዎድሮስም "ለዋድላ ሰዎች ገንዘብ እሰጣለሁና ሁሉም ተሰብስቦ ይምጣ'' ብለው አዋጅ አስነገሩ ። ይህንንም አዋጅ የሰማው ሕዝብ እረኛ እንኳ ሳይቀር በሙሉ ተሰብስቦ መጣ ። አጤ ቴዎድሮስም በራስ አዲሉ የሚመራውን የየጁን ጦር ዙሪያውን አስከብበው ስድስት መቶ ሰዎችን በጐራዴ አስደብድበው ፈጁዋቸው ። ይህን የግፍ አገዳደል ያዩት ራስ አዲሉ ለሊቱን አምልጠው መሸፈታቸውን አለቃ ተክለ ኢየሱስ ጽፈዋል ። ከአለቃ መጽሐፍ ሌላም እናንባለን ።

የሜጫና የአገው ሰዎች ሊሸፍቱ ነው ብሎ አሳባቂ ነገራቸው። ቴዎድሮስም አራት መቶ የሜጫና የአገው መኳንንት ሰብስበው ዙሪያውን በሾህ አጥር አጥረው ሱሪ ብቻ እየሰታጠቁ ራቁታቸውን እንደ ከብት አጐሩዋቸው ። እህልና ውሃም እንዳይሰጣቸው አዘዙ ። በረሃብና በውሃ ጥም የሚሰቃየው ሕዝብም ከአሥር ቀን በኋላ መሞት ጀመሩ ። በ15ኛው ቀን ግን ሁሉም በረሃብና በውሃ ጥም አለቁ ። ወሰን ቢሰውር የሚባሉት የሜጫ መኰንንም "ጃንሆይ ፡ አምስት መቶ ብር ልክፈልና አንድ ዋንጫ ውሃ ይስጠኝ '' ቢሏቸው ቴዎድሮስ ሰምተው ዝም ብለውት አለፉ ። ወሰን ቢሰውር ከሞቱም በኋላ ሚስትየዋ "ጌታ የጌታው ልጅ ወሰን ቢሰውር
ውሃ ልግዛ ይላል በአምስት መቶ ብር ''
ብላ ገጠመች ።

ቴዎድሮስ ቃሮዳ ከሚባል አገር ሔዱ ። ቃሮዳ በአትክልት አብቃይነቱ በተለይ በወይን ሰብል የታወቀ አገር ነበር ። ቴዎድሮስ ቃሮዳ እንደደረሱ ሕዝቡን ሰብስቡልኝ ብለው ሕፃናት ሳይቀሩ



1700 ሰዎች ተሰበሰቡ ። ይህን ሁሉ ሰው ቤት አስከቻለ ድረስ በየቤቱ እያስገቡ ሁሉንም በእሳት እያቃጠሉ መጨረሳቸውን አለቃ ወልደ ማርያም ፅፈዋል ። ሌላም አለ ።

ማህደረ ማርያም በወረዱ ጊዜ ካህናቱ ንጉሱን ለመቀበል ከለቻ ከሚባል ሜዳ ላይ ቆመው በፀናፅልና በከበሮ እያመሰገኑ እቀባበል አደረጉላቸው ። ይህን ያዩት ቴዎድሮስ በልልኝ ብለው ወታደሩን አዝዘው 450 ካህናት በጐራዴ ተደብድቦ አለቀ ። ከዚያ ተመልሰው ደብረታቦር በወጡ ጊዜ ከርብ ጀምሮ እስከ ፍርቃበር ወታደራቸውን አሰማርተው ሲቆፍርም በመንገድ ሲሔድም የተገኘውን ሁሉ 7700 ሰዎችን አሰበሰቡ ። ይህን ሁሉ ሰብስበው በየቤቱ ውስጥ እያጐሩ የታጐሩበትን ቤት በማቃጠል ሲያስፈጁዋቸው ዋሉ ። ሰዉ ተቃጥሎ ሲያልቅ ጊዜው ስለመሸ ተራፊውን ከሜዳ ላይ እየተጠበቀ ራቁታቸዉን እንዲያድሩ አዘዙ ። ለሊቱንም ዝናብ ስለዘነበ ሕፃናትና እመጫት ሳይቀሩ በዝናብ ሲደበደቡ አደሩ። በማግስቱ ቴዎድሮስ ያደረውን ሕዝብ ለማቃጠል መጥተው ሰዉ ከሚቃጠልበት ቤት እየተከፈለ ሲገባ አንድ የአምስት ዓመት ልጅ እናቱን እየጐተተ "ነይ እንደትናንቱ ዝናብ እንዳይመታን ቶሎ ከቤት እንግባ'' እያለ ሲያለቅስ ፣ እናቱም ስታለቅስ ቴዎድሮስ አይተው "ለምን ያለቅሳሉ'' ብለው ጠየቁ ። ልጁ የተናገረውን ቢነግሯቸው "ፈጣሪዬ ምነው እንዲህ ታደርገኛለህ ። ወይ እኔን ቶሎ ግደልና ፍጥረትህ ይረፍ ብለው አልቅሰው ሊቃጠሉ የቀረቡትን ሁሉ ማሩት ። ይህ ከሆነ በኋላ ጣና ሐይቅ ውስጥ ከምትገኘውና ምፅርሐ ወደምትባለው ደሴት ሔደው በደሴቲቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች በሙሉ በቤት ውስጥ እያስገቡ ቤቱን በማቃጠል ጨረሱት ።

ዶክተር ብላንክ ስለቴዎድሮስ የጭካኔ ተግባር ጽፎት አቶ ዳኘ ከተረጐሙት ብንመለከት " ህዳር 21 ቀን 1859 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ አጤ ቴዎድሮስ የተመረጡ ጥቂት ፈረሰኛና እግረኛ ወታደሮች አስከትለው ጐንደርንና ከጐንደር ግንብ ውስጥ እየተደበቁ የሚያስቸግሩዋቸውን ሽፍቶች ለማጥፋት መገስገስ ጀምረው አስራ ስድስት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሰማንያ ማይልስ ርቀት ያለውን ጐዳና አንድ ጊዜ ስንኳ ሳይቆሙ ሲኀዙ አድረው ወገግ ሲል የጐንደር ከተማ ከሚገኝበት ተራራ ሥር ደረሱ ። ምንም እንኳን በድንገት ለመድረስ አቅደው የመጡ ቢሆንም የጐንደር ነዋሪ ሕዝብ ወሬውን ሰምቶ ስለነበረ በመጨነቅና በመሸበር ሴቶች

ወጥተው በእልልታና በደስታ ሲቀበሉዋቸው በፋሲል ግምብ ውስጥ ተሰግስጐ የነበረውም ሽፍታ ሸሽቶ ከጐንደር ወጣ ። ወዲያውም ሽፍቶችን ለማግኘት ሠራዊቱ ቤቱንና ቤተ ክርስቲያኑንም ሳይቀር መበርበር መዝረፍ ያዘ ። ዳሩ ግን ሽፍቶቹ ባለመገኘታቸው ከአስር ሺህ በላይ የሆነውን የከተማውን ነዋሪ ሕዝብ እንደ ከብት ሰብስበው ነዱት ። ከዚህም በኋላ የጥፋት ሥራቸውን ጀምረው ሕዝቡን ፣ ቤቱን ፣ ቤተ ክርስቲያኑንና ቤተ መንግሥቱንም ጭምር በእሳት አቃጠሉት ። ከቀሳውስት መካከል እንዳንዶች የደፈሩ እጉረምርመው የንጉሠ ነገሥቱን አፈጻጸም በግልፅ ተቃውመው በላወገዙ ብዙ መቶ ሽማግሌ ቀሳውስት ወደ እሳቱ ተወርውረው ተቃጠሉ ። የማቃጠሉ ነገር ከዚህ ላይ ባይቆም "እልል እያሉ የተቀበሉት ሴቶችስ የት አሉ? እነርሱ እልል ባይሉ ኖሮ ሽፍቶቹ መምጣታችንን የት ያውቁ ነበር?" በማለት ሴቶቹ ሁሉ ተይዘው እንዲመጡ አጤ ቴዎድሮስ በማዘዛቸው ሁሉም ከነ ሕይወታቸው ወደተቃጠለው ቤት እየተወረወሩ ነደዱ ።. . . ." ብለዋል ።

ይህን የመሳሰለውን የቴዎድሮስን የጭካኔ አስተዳደር ስንመለከት ቴዎድሮስ ጠላት ሳይኖርባቸው በራሳቸው ላይ ጠላት የሚፈጥሩና የሚያበዙ ሰው ነበሩ ። ብዙ ፀሐፊዎች እንደጻፉት ቴዎድሮስ የሚፈፅሙት የጭካኔ ተግባር ሁሉ በትክክል የተፈፀመ ትክክለኛ ተግባር ይመስላቸው ነበር ። ሲናገሩም "ለአገሬ እድገት ብዬ ነው" ይሉ ነበር ። ወዳጃቸው ፕላውዴን እንደጻፈው ". . . . ባንድ አጋጣሚ ንጉሱ ሲያጫውቱኝ "አንተና ቤል ብቻ ትወዱኛላችሁ ። አበሾች ግን የሚገዙት በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ። ግን ገና ብዙ የምሠራው አለ ። ዛሬ ማታ ብሞት ወይም ብመነኩስ እንኳ ይህ የሚሆነው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ። በዚህ ቤት ሙሉ ወርቅ ብትሰጠኝ ጥቅሙ ምንድነው? እምመኘው ጥበብን ነው ። ቅጣት የማበዛውም አገሬ በሥርዓት እንድትተዳደር ለማድረግ ነው ።. . . ለእኔ ለአንድ ደሃ ይህን ዙፋን የሰጠኝ እግዚአብሔር ጥበብን ደግሞ ይሰጠኝ" አሉ ።. . . ." ብሏል ። ቴዎድሮስ በንዴት ወይም በሌላ ጊዜ የጭካኔ ተግባራቸውን ይፈፅሙ እንጂ በጥሞናው ጊዜ ባለፈው ተግባራቸው ይፀፀቱ እንደነበር ብዙዎች ጽፈዋል ። ብዙ ንፁሃን ሰዎች ፈጅተው ከጨረሱ በኋላ "እኔን ግደሉኝና ሠራዊትህ ይረፍ" እያሉ ይፀልዩ ነበር ። ፕላውዴንም ". . . .ባንድ አጋጣሚ ደግሞ እንደሚወዱኝ ነግረውኝ እግዚአብሔር ጥሩ ልብ እንዲሰጣቸው እንድፀልይላቸው ለመኑኝ. . . ." ይላል ።



አጤ ቴዎድሮስ ሁሉን ነገር በኃይል አስፈጽማለሁ ፣ ወይም በኃይል ሥራ ፀጥታውን አስከብራለሁ እያሉ ነገሩን ሁሉ አበላሹት እንጂ ለአገራቸው ፈጣን እድገት አሳቢና ለሥራውም ታታሪ ነበሩ። በተለይም ወይዘሮ የተመኙን ቁባት ካስቀመጡ በኋላ ከወይዘሮ የተመኙ ዘንድ እየቆዩ ብዙ አረቄ መጠጣት ስላበዙ በሞቅታ በሚሰጡት ፍርድና ተፈጻሚነት ጠላታቸው እየበዛ ሔደ ። ይህ ባይሆንና ቴዎድሮስ ሁሉንም ነገር በጥሞና ነገር በመቻልና በማሳለፍ አገሪቱን ቢመሩ ኖሮ ለአገሪቱ የፈለጉት እድገትና ሥልጣና ሁሉ በሰላም በተከናወነላቸው ነበር ።

## ፍርድ

ቴዎድሮስ ከነገሱ በኋላ በ1846 ዓ.ም. ደብረ ወርቅ ላይ ሠፍረው ሳለ ሁለት ሰዎች ተከሰው ለፍርድ ቀረቡላቸው ። ከሳሽ ሹምዬ ጃሎ ሲባል ተከሳሽ ደግሞ ጠቦ ወልደ ሚካኤል ይባላል ። ሹምዬ ጃሎ አንድ ፈረስ ለጠቦ ሰጥቶታል ። ሹምዬ ጃሎ የራስ አሊ አሽከር ነበረና ከራስ አሊ ጋር ሆኖ ካሣን የወጋ ሰው ነው ። አሊ ድል ሲሆኑ ሰዋቸው ሲዘረፍ ሹምዬም ልብሱን ሳይቀር ተገፎ ከባድ ድህነት ላይ ወደቀ ። ሀብት ባለው ጊዜ ፈረስ ከሰጠው ወዳጁ ከጠቦ ዘንድ ሔዶ እባክህ ልብሴን የምገዛበት አንድ ብር ስጠኝ ብሎ ለመነው ። ጠቦም አልሰጥህም አለው ። ውለታውን ቆጥሮ ቢለምነውም እምቢ አለው ።

ከዚህ በኋላ አቶ ሹምዬ የደህና ቀን ወዳጁን ጠቦን ከስሶ ከቴዎድሮስ ዘንድ አቀረበው ። ከዚያም ቀርበው ሲሟገቱ ሹምዬ በደህናው ቀን ፈረስ መስጠቱን አመልክቶ አሁን ተዘርፎ ድህነት ሲጫነው ለልብስ መግዣ አንድ ብር ቢለምነው እምቢ ማለቱን አመለከተ ። ጠቦ ወልደ ሚካኤልም ነገሩን ሸፈጠና ፈረስ አልሰጠኝም ብሎ ካደ ። ሹምዬ ጃሎ ሲመልስ ፈረስ " ለመስጠቴ ምስክር አለኝ ። ምስክሬም እግዚአብሔር ነውና እግዚአብሔርን ምስክር እጠራብሃለሁ" አለው ። የዚህ ጊዜ ጠቦ ወልደ ሚካኤል ደነገጠና "እግዚአብሔርን ምስክር ከጠራህስ አዎን ሰጥተኸኛል" ብሎ አመነ ። ይህን እግዚአብሔርን መፍራቱን የሰሙት ቴዎድሮስ "እግዚአብሔርን ፈርተህ እውነቱን ስለተናገርክ እኔ እከፍልልሃለሁ" ብለው ለሹምዬ ጃሎ አስር ብር አንድ ፈረስ አንድ በቅሎ ሰጥተው ገላገሉዋቸው ።

ቴዎድሮስ ጋይንት ላይ ሠፍረው ሳለ ወታደሮቻቸውን በባላገሩ ላይ ተሰሪ አገቡ ። ባላገሩ እንዲቀልብ በየቤቱ ማስገባት ማለት ነው ። ተሰሪ ከገቡት ወታደሮች መሀል አንዱ ወታደር አንዱን ባላገር ገደለው ። የሟች ወገንም ከቴዎድሮስ ዘንድ መጥቶ አመለከተ ። ቴዎድሮስም ወታደራቸውን ሁሉ አፈርሳታ አስቀምጠው ገዳዩን አውጣ ብለው ያዙ ። ወታደሩም በመላው አድሞ ገዳዩን እሳየንም እያለ በቄስ እየተገዘተ ወጣ ። የሟች ገዳይ ወታደር በመጥፋቱ ቴዎድሮስ ተናደው "ወታደር ብላ ፣ ባላገር አብላ ያልሁ እኔ ነኝ ። ደመኛህም እኔ ነኝና እኔን ግደል" ብለው ተነስተው ለከሳሹ ነገሩት ። ከሳሹም "እኔ ንጉስ መግደል አይቻለኝም" አለ ። ቴዎድሮስም እንግዲያውስ ደም በከንቱ አይቀርም ብለው ለሟቹ ወገን የደም ገንዘብ ዋጋ ሰጥተው ሸኙት ።

አቶ ገሪማ ታፈረ አንዳንድ የቴዎድሮስን ፍርዶች ጽፈዋል ። አንድ ጊዜ ቴዎድሮስ አንድ ታማኝ ወታደራቸውን ጠርተው "በፍርቃ በር በኩል እርጉዝ ሴት እንኳ ብትሆን እንዳታልፍ ጠንክረህ ጠብቅ" ብለው አዘዙት ። በሌላ ቀን ደግሞ ሌላውን ወታደር ጠርተው "ፈረስ እያለዋወጥህ ይህን ወረቀት የጁ ሰጥተህ በአስቾኳይ በስድስት ቀን ውስጥ ተመልሰህ እንድትመጣ ብለው ላኩት ። ይህ የታዘዘ ወታደር በፈረስ እየጋለበ ሔዶ ፍርቃ በር ደረሰ ። የፍርቃ በሩ ጠባቂ ዘበኛ አታልፍም ብሎ ከለከለው ። የተላከው ወታደር ደግሞ "ከንጉሱ ተልኬ ነው ። በስድስት ቀንም የጁ ደርሼ እንድመለስ ስአስቾኳይ ጉዳይ ልከውኛልና ልለፍ" አለ ። ዘበኛውም "ከተላከህ አትከልክሉት የሚል ማህተም እንዳለህ አሳየኝና ታልፋለህ እንጂ ያለዚያ አታልፍም" ብሎ ከለከለው ። የተላከው ወታደር በግዴታ አልፋለሁ ብሎ መንገድ ሲጀምር ዘበኛው ጥይት ተኩሶ ገደለው ።

የሟች ወገኖች የንጉሱ መልክተኛ ወንድማቸው ንጉሱ ልከውት ሲሔድ በመገደሉ ጉዳዩን ከስሰው ቴዎድሮስ ዘንድ አቀረቡት ። ቴዎድሮስም ችሎት አስችለው ፍርድ እንዲፈረድ አደረጉ ። በችሎቱ ላይ የተቀመጠው ፈራጅ ሁሉ እየተነሳ ገዳዩን "በደለኛ ነህ ። እምቢ አልፋለሁ ቢልህስ ለንጉስ ታስማ ነበር እንጂ ራስህ ፈርደህ እንዴት የንጉስ መልክተኛ ትገድላለህ? አሁንም ስትሞት ይታየናል" እያሉ ፈረዱ ። አንድ ፈራጅ ግን ከተቀመጡበት ተነስተው "....ማየት የሚገባን በመጀመሪያ ከንጉሱ የተሰጠውን ትእዛዝ ነው ። አንዱን ጠርቶ በዚህ በር ያለኔ ፈቃድ ወንድ ይቅ



ርና የፀነሰች ሴትም ብትሆን እንዳታልፍ ብሎ ማዘዝ ፤ እንደገና ሁለተኛውን ወታደር ጠርቶ ቀንና ለሊት ሳታርፍ በስድስት ቀን የጁ ደርስህ እንድትመለስ ብሎ ማዘዝ አግባብ ስላልሆነ ጥፋቱ የሚመለከተው ንጉሠ ነገሥቱን ነው ። ነገር ግን ብርሃን ናቸውና ምን ይደረግ" ብለው ተቀመጡ ።

አጤ ቴዎድሮስ ይህን ንግግር ሲሰሙ ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው "እንዲህ ነው መሸምገል ፣ ሁለት ጠጉር ማብቀል ። በደለኛው እኔ ነኝ ። ፍረዱብኝ" ብለው በተከሳሹ ወታደር ቦታ ወርደው ቆሙ ። ወዲያውም ፈራጆች በፈረዱት ፍርድ መሠረት ለሟች ወገኖች 500 ብር የደም ዋጋ ቴዎድሮስ እንዲከፍሉ ተፈርዶ በስምምነት አለቀ ። ለዚያን ዘመን ዋጋ በቴዎድሮስ ላይ የተፈረደው 500 ብር አጠፌታ ዋጋ መሆኑ ነው ።

አንድ ቀን ደግሞ አንድ ሌባ ከአንድ ሀብታም ቤት ሊሰርቅ ገባ ። ከበረት ገብቶ ሲያንኰዳጉድ ባለቤቱ ነቃና ወጣ ። ባለቤቱ ሲወጣ ሌባው ሸሸ ። ሰውዬውም ሌባውን እያባረረ ሲደከመውና መድረስም ሲያቅተው "በቴዎድሮስ አምላክ ቁም" ብሎ አወገዘው ። ይህን ሲሰማ ሌባው ቆሞ ጠበቀው ። ሀብታሙ ሰውዬም ከሌባው ዘንድ እንደደረሰ በያዘው አንካሴ ሌባውን ደጋግሞ ወጋውና ጥሎት ሄደ ።

ሌባው አልሞተ ኖሮ እየተንኰተተ እርዋ ሚካኤል ደብር ገብቶ ተኛ ። ሌባው ሻል ሲለው ቴዎድሮስ እንፍራንዝ መጥተው መስፈራቸውን ሲሰማ እያዘገመ ሔደ ። ታሪኩን ለቴዎድሮስ ተናገረ ። ቴዎድሮስም ታሪኩን በጥሞና አዳምጠው "የለሊት ጅብ ፣ ከሰው በረት ምን ልታደርግ ገባህ? አበጀ ። ደግ አድርጓል" ብለው አስደነገጡትና በሚስጥር ሀብታሙ ሰውዬ ተይዞ እንዲመጣ አዘዙ ።

ሀብታሙ ሰውየ እንደመጣም ቴዎድሮስ በፈገግታ "እህእ አንተ ጐበዝ ፣ ይህን ሌባ እንዴት አድርገህ ወጋኸው?" ብለው እየሳቁ ጠየቁት ። ሰውዬውም ደስ ብሎት "በረቴን ከፍቶ ገብቶ ከብቶቼን ሊነዳ ሲል ነቃሁና ምዝራጤን (አንካሴየን) ይዤ ልወጋው ስል ኮቴዬን ሰምቶ አብለከ አለ (ሮጠ) እኔም ተከታትዬውብሮጥ የማልደርስበት መሆኔን ስላወቅሁ በቴዎድሮስ አምላክ ብለው መሮጡን ትቶ ቀጥ ብሎ ቆመልኝ ። እንደ ደረስኩም በያዝኩት ምዝራጥ ወደወድኩት(ወጋሁት) ብሎ ተናገረ ።

አጤ ቴዎድሮስ የሰውየውን ንግግር በምተው ሲጨርሱ

“ወንጀለኛ ነህ ። እንዴት በስሜ ቆሞልህ ትገድለዋለህ ። መሞት ይገባህ ነበር ። ግን ምሬሃለሁና ያለህን ሀብትና ንብረት በሙሉ ለወጋኸው ትለቃለህ” ብለው ፈረዱ ።

አንድ ነጋዴ ወገራ ዳና ክትባለ ገበያ ውሎ ሲመለስ አንድ አይጠማሽ ከሚባል ቦታ ሲደርስ ወንበዴ ቀማኛ ይዞ ይደበድበው ጀመር ። ነጋዴውም “ገንዘቤን ውሰድና ልቀቀኝ ። እየነገድሁ ልጆቼን ላሳድግበት ተወኝ” እያለ ቢለምነውም እምቢ ብሎ ገደለው። ይህን ነገር ተደብቆ ይሰማ የነበረ ሰው ሁኔታውን ለሟች ሚስት ነገራት ። የሟች ሚስትም ለቴዎድሮስ አመለከተች ። ወንበዴው ተይዞ ሲመጣ ቴዎድሮስ በሽማግሌ ይታይለት ብለው አዘዙ ። ሽማግሌዎቹም ሰማንያ ብር ካሣና አርባ ብር የዳኝነት በወንበዴው ላይ ፈረዱበትና ውሳኔውን ለመንገር ቴዎድሮስ ዘንድ ቀረቡ ። ቴዎድሮስ ውሳኔውን ሰምተው ሴትዮዋን ቢጠይቋት በውሳኔው መስማማቷን ነገረች ። ቴዎድሮስም “ወይ ሴት መሆን? ገንዘቤን ውሰድና ለቀኸኝ ልጆቼን ላሳድግ ሲለው በጭካኔ የገደለውን ሰው በገንዘብ ትታረቂያለሽ?” ብለው ሰማንያውን ብር ከራሳቸው ሰጥተው ወንበዴውን አሰቀሉት ።

አንድ ገበሬ ሞተ ። ሚስቱ የቤቱን ኃላፊነት ወሰዳ ስታስተዳድር ያላት አንድ ወይፈን ብቻ ነበርና ወይፈኑ ሴት ፍለጋ እያለ አላርስ አለ ። የመንደርዋን ሰዎች አኮላሹልኝ ብላ ብትለምንም የመንደሩ ሰዎች የወይፈኑን ቁመና አይተው ለርቢ ስለሚሆን ለጥቅማቸው ሲሉ እምቢ አሏት ። ከዚህ በኋላ ያ ወይፈን እየዞረ የሠፈሩን ላሞች ሁሉ ሲያስወልድ ከረመ ። አንድ ቀን ካንድ በሬ ጋር ሲዋጋ ያን በሬ ገፍቶ ገደል ጨመረውና በሬው ሞተ ። በሬው ገደል የገባበት ሰው የወይፈኑን ጌታ ያቺን ሴት ከሰሳት ። “ተዋጊ በሬህን ፣ ተናካሽ ውሻህን ያዝ ይላልና የበሬዬን ዋጋ ትከፍይኛለሽ” አላት ።

ሴትዮዋ በሽማግሌዎችም በዳኞችም ስለተፈረደባት ቴዎድሮስ ዘንድ ሔዳ ጮኸች ። ቴዎድሮስም “ሕጉ ያዛልና መክፈሉን ትከፍያለሽ” ብለው ፈረዱና “ለመሆኑ ከዚህ ወይፈንሽ የተወለዱትን ከብቶች ታውቂያቸዋለሽ?” ቢሏት አዎን አውቃቸዋለሁ ብላ መለሰች ። ቴዎድሮስም አጋፋሪያቸውን ጠርተው “ንሳማ ፣ እሷ የምታሳይህን ከብቶች ሁሉ እየያዝህ አንድ ለሷ ፣ አንድ ለባለ ላም እያደረግህ አካፍላቸው” ብለው አዘዙ ። ሴትዮዋም በአንድ ጊዜ ሀብታም ሆነች ።



ከደብረ ታቦር ተነስተው ሲሔዱ ጊዜው ብርድና ንፋስ ሆኖ አላስኬድ ስላለ ጉና ከሚባለው ሠፈር ሲደርሱ ሠፈር ሆነ ። ቴዎድሮስ የሚያድሩበት ቤት አልነበረምና ከድንኳን ይሻላል ተብሎ ካንድ ቄስ ቤት ገብተው አደሩ ። ለሊቱን የዚያ ቄስ ቤት ትኋን ሲበላቸው አደረ ። በማግስቱ ቴዎድሮስ ከውጭ ሆነው የቤቱን ጌታ ቄሱን አስጠርተው ከአልጋህና ከመቀመጫህ በስተቀር ሌላውን ዕቃህን አውጣ ብለው አዘዙና ዕቃው እንደወጣ ቤቱ እንዲቃጠል አዘዙ ። ቤቱ ሲቃጠልም እያዩ “ትኋን እንዳንገበገብሺኝ አንገበገብኩሽ እያሉ ቆይተው ለቄሱ ቤት ሥሩለት ብለው አዘዙ ። ወዲያውም ሠራዊታቸው ተረባርቦ በጣም ደስ የሚያሰኝ ቤት ባንድ ቀን ተሠርቶ ተሰጠውና ዕቃውን አስገባ ።

አንድ ሴትዮ አርባ ክንድ ርዝመት ያለው መቀነት አሠርታ ለቴዎድሮስ ስጦታ ሰጠች ። ቴዎድሮስም ስጦታውን ተቀብለው “እንዴት በአርባ ክንድ መቀነት ወሰንሺኝ ። እንደተራ ሰው ቆጥረሺኝ ነው? ” ቢሏት “አይደለም ጃንሆይ ። ድሃ ብሆን ነው እንጂ ለእርስዎ መቶ ክንድም አይበቃዎ” አለቻቸው የሴትዮዋን መልስ የሰሙት ቴዎድሮስ ተደስተው ሸልማት ሸልመው ሰደዷት ።

ይህን ታሪክ የሰማች ሌላ ሴት ለዚያች መልክ ጥፉ ያን ያህል የሸለሙ የኔንማ ቁንጅና ሲያዩ የበለጠ ይሸልሙኛል ብላ ከቴዎድሮስ ዘንድ ቀርባ እጅ ነሳች ። ቴዎድሮስም “ሙያሽ ምንድነው እቱ?” ብለው ጠየቋት ። ሴትዮዋም “የከተማ ቅሬ (ሴትኛ አዳሪ) ነኝ እንጂ ሥራ የለኝም” ብላ መለሰች ። ቴዎድሮስም “እግዚአብሔር ሁለት እጆች የፈጠረልሽ እንድትሠሪባቸው ነበር ። ለመብል ብቻ ከሆነ አንድ እጅ ይበቃሻል” ብለው አንድ እጅዋን አስቆረጧት።

የዘመኑ ዘፋኞችም

“ማረስ ይሻላል መገበር ፣
እጅ እግርን ይዞ ለመኖር ።
አላርስም ያሉ አልነግድ
ተመለመሉ እንደ ግንድ ።” እያሉ ይዘፍኑ ነበር ።

ምዕራፍ 8

# የአረቦች ጥንስስ

ግራኝ መሀመድ በኢትዮጵያ ላይ በሽፍትነት ተነስቶ በአረቦች
በተለይ በቱርኮች እርዳታ በመላ ኢትዮጵያ ከተንሰራፋ በኋላ ቱር
ኮች በኢትዮጵያ ዳርቻ በተለይ በምፅዋና ባካባቢዋ፣አገር መያዝና
መስፈር ጀመሩ ። የቱርኮች ኃይል በሚደከምበት ጊዜ ግብጾች እየተ
ረከቡ በመፈራረቅ ይይዙ ጀመር ።

ይህን የአረቦችን በኢትዮጵያ ዳርቻ ላይ መስፋፋት የኢትዮ
ጵያ ነገሥታት በነገሩ ቢቆጩበትም የባህር ላይ መዋጊያ መርከብ
ሸለሌላቸው ብቻ መርከብ ላላቸው መንግሥታት እያመለከቱ ውጤ
ቱን ይጠባበቁ ጀመር ። የሚጠበቀው የባለ መርከብ አገር እርዳታም
ውጤቱ አጥጋቢ ባይሆንም በየጊዜው የተነሡ ነገሥታትና መሳፍ
ንት ከመለመን ያቋረጡበት ጊዜ አልነበረም ። እንዲያውም ከአረ
ቦች መስፋፋት ይልቅ ሌላ ክርስቲያን የሆነ መንግሥት ቢይዘው
ይመኙ እንደነበረ ለማስረጃ ያህል ከትግራዩ መስፍን (ገዢ) ከደጃዝ
ማች ሰባጋዲስ ደብዳቤ መረዳት እንችላለን ።

በ1820 ዓ.ም. ግድም ዊልያም ኮፊን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ
ወደ አገሩ በሚመለስበት ጊዜ ለእንግሊዙ ንጉሥ ለጆርጅ 4ኛ
ደጃዝማች ሰባጋዲስ አንድ ደብዳቤ ልከው ነበር ። ደብዳቤውም
“....የምፅዋን ወደብ እርስዎ ይውሰዱና ለኛ ይሰጡናል ። ባይሆ
ንም ደግሞ በእርስዎ በንጉሥ እጅ ቢሆን ይሻለናል....” የሚሉ
ቃላት ይገኙበት ነበር ።

ከዚያም በፊት የትግራይ ገዥ (መስፍን) የነበሩት ራስ ወልደ
ሥላሴ በ1802 ዓ.ም. ግድም በሚያዝያ ወር ለእንግሊዛዊው ለሶልት
ሲያጫውቱት “.... በመሬት ላይ ስላለው ጉዳይ አታስቡ ። ምፅ
ዋን ስለያዙት ቱርኮች ግን አስቡበት ። እንግሊዞች ምፅዋን ቢይዙና
መርከቦቻቸው አካባቢውን ቢጠብቁ ከዳርቻው ወዲህ ላለው አገር
እኔ ጠባቂ እሆን ነበር....” ማለታቸውን ራሱ ሶልት ፅፎታል ።



መሐመድ አሊ ግብፅን ማስተዳደር እንደጀመሩ በግራኝ
መሀመድ ጊዜ በጀሃድ ጦርነት እስከ ሰሜን ኢትዮጵያ ድረስ በአረ
ቦች (በእስላሞች) ተይዞ እንደነበረ አስታውሰው አረብን ሁሉ አጠ
ቃልዬ እገዛለሁ በሚለው ሐሳባቸው መሠረት ኢትዮጵያንም ደር
በው ለመያዝ ፈለጉ ።

መሐመድ አሊ ግብፅን በገዢነት ይያዙ እንጂ በትውልድ
ግብፃዊ አልነበሩም ። ቱርካዊ ናቸው ። መሐመድ አሊ በ1769
ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ከቱርክ ወላጆቻቸው ቱርክ ውስጥ ተወለዱ ።
የቱርክ ጦር በ1799 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ግብፅ ሲገባ መሐመድ አሊ
ገና የሰላሳ ዓመት ጐረምሳ ስለነበሩ በፈቃደኛነት ከጦሩ ጋር ዘም
ተው ግብፅ ምድር ገቡ ። ግብፅ ምድር በገቡ በአራተኛው ዓመት
ማለት በ1803 ዓ.ም. የግብፅን መንግሥት ያዙ ። የግብፅን መንግሥት
አመራር ሲይዙ በቀላል ሁኔታ አልነበረም ። አስር ሺ አልባናውያን
ወታደሮችና ሌሎችም ነበሩዋቸው ። እነዚህንም ወታደሮች በበላይ
ነት የሚመሩላቸው ከ95 ልጆቻቸው መሀል ከመጀመሪያ ሚስታቸው
የተወለዱትን ሦስቱን ልጆቻቸው ማለት ኢብራሂም ፣ ቱኩን ፣ እስ
ማኤል የተባሉትን የጦር ትምህርት አስተምረው የወታደሩ የበላይ
አድርገዋቸው ነበር ።

መሐመድ አሊ ተቃዋሚዎቻቸውን እያጠፉ ሥልጣን ቢይዙም
ሥልጣን ከያዙም በኋላ ብዙ ተቃዋሚዎቻቸው ኃይለኛዎቹ ማምሉ
ኮች ከባድ ምሽግ እየሠሩ የማይገብሩና የማይበገሩ ሆኑባቸው ።
እነኝህንም ማምሉኮች በእርቅና በሰላም ለመስማማት ብለው ሰላም
ከመሠረቱ በኋላ ታላቅ በዓል አዘጋጅተው 500 የማምሉክ አለቆች
በበዓሉ ላይ እንዲገኙ ጥሪ አደረጉ ። ማምሉኮቹም እውነት ሰላም
የወረደ መስሏቸው በ1811 ዓ.ም. በዓሉን ለማክበር ካይሮ ተሰበሰቡ ።
በዓሉ ተከብሮ ካለቀ በኋላ በትልቁ ልጃቸው በኢብራሂም የሚታ
ዘዙትን ወታደሮች አዘው አምስት መቶዎቹን ማምሉክና ብብዙ
ሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን በጥይትና በሰይፍ አሳርደው ባንድ ቀን
ሁሉንም ፈጁዋቸው ። ይህ ከሆነም በኋላ በዚሁ በኢብራሂም የሚታ
ዘዘው ወታደር እስከላይኛው አባይ ድረስ ዘምቶ የተረፉትን ማም
ሉኮች ሁሉ ጨረሳቸው ።

ተቃዋሚዎቻቸውን በዚህ ሁኔታ ከጨረሱ በኋላ መሐመድ አሊ
ታላቁን ሕልማቸውን እውን ለማድረግ አሰቡ ። የመጀመሪያ አሳባ
ቸው ቀይ ባህርን ከዳር እስከዳር መያዝ ነበር ። ቀይ ባህር ከተያዘ

የአረብን አገር በሙሉ ለማስገበርና የባህሩም መንገድ ለንግድ እስከ ሕንድና ሩቅ ምሥራቅ ድረስ እንደሚያዘልቃቸው በማሰብ ነበር ። ሁለተኛው ሕልማቸው ወይም አሳባቸው በጥቁርና በነጭ አባይ(ናይል) ሸለቆ ያሉትን አገሮች በሙሉ ለመያዝ ነበር ። እነኝህም አገሮች በሚያዙበት ጊዜ ወደሰሜን ኢትዮጵያ ገብቶ ጣናን ለመያዝ ጐንደር መድረሻ በመቀጣ በኩል እንዲሆን ተወጠነ ።

በዚያው ዘመን የነበረው ዋዲንግተን ያን ሐሳብ ሲተነትን '....የመሐመድ አሊ አሳብና ምኞት በናይል አካባቢ ያሉ አገሮችና ደሴቶች ሁሉ በእጁ እንዲገቡለት ነው ። ከአበሻ ምድር ጀምሮ እስከ ሜዲትራንያን ባህር ድረስ ያሉ የናይልን ውሃ የሚጠጡ ሰዎች ሁሉ የእሱ ተገዢ ሆነው እሱ ጌታቸው እንዲሆን ነው ።.... በማለት ጁርናል ኦፍ ኤ ቪዚት ቱ ሰም ፓርትስ ኦፍ ኢትዮጵያ በሚል ርእስ ገልጾታል ።

በዚህ ሐሳብና ውጥን መሠረት መሐመድ አሊ 3ኛ ልጃቸውን እስማኤልን በ25 ዓመት ዕድሜው አባይን ለማስገበር ሾሙት ። አባይ ስል የኛን ጥቁር አባይ ነው ። ናይል ግን ከነጭ አባይ እስከ ሜዲትራኒያን ባህር ድረስ ያለው የኛንም አባይ ጨምሮ ነው ።

የአባይ ዳርቻን እየያዘ ኢትዮጵያ ድረስ ለማስገበር የታዘዘው እስማኤል ወታደሮቹን በሚገባ አደራጀ ። የቱርክና የአልባኒያ ተወላጆች የሆኑት ወታደሮቹ ቀይ ወይም አረንጓዴ ባርኔጣ ያደርጉና ወርቃማ ክፈፍ ያለው አጭር ኮት ይደርባሉ ። በወገባቸው ላይ ነጭ ሐር ታጥቀው ቁምጣ ሱሪ የሚለብሱ ነበሩ ። ጫማቸው ቀይ ነበር ። እነኝህንም ወታደሮች እያንዳንዳቸውን አንድ ባርያና አንድ አህያ እንዲከተላቸው ይደረጋል ። ሌሎቹ ወታደሮቹም ቢሆን እንደነኝህ በጣም ያጌጡ አይሁኑ እንጂ አለባበሳቸው አንድ ዓይነት ነበር ። ከእነኝህ ከታወቁት ወታደሮች ሌላ ለዝርፊያና ለምርኮ ሲል ብቻ የሚዘምተው ሲቪል ሕዝብ በጣም የበዛ ነበር ።

እስማኤል ጦሩን አዘጋጅቶ ለመዝመት በሚነሳበት ጊዜ አባቱ መሐመድ አሊ ጦሩን እንዲያሰናብቱለት አደረገ ። መሐመድ አሊም ጦሩን በሚያሰናብቱበት ጊዜ አንድ የሰው ጆሮ ላመጣ ወታደርም ሆነ ሲቪል የዘመኑን ገንዘብ 50 ፒያስተር እሰጣለሁ ብለው አወጁ ። እስማኤል መሐመድም ጦሩን እየመራ ወደ ላይኛው አባይ ወደ ሱዳን ጉዞውን ጀመረ ። አቅም ያላቸው የሱዳን ባላባቶችም መጠነኛ ቁርቁስ እያደረጉና እያለቁ የእስማኤል ወታደር ተጓዘ ወደ ኢትዮ



ጵያ ጠረፍ በሚቃረብበት ጊዜ ግን ሻጊያዎች ያላቸውን ጦር አዘጋጅተው በሴትዋ ሜህራ አቡድ መሪነት ተሰልፈው ጠበቁ ። በ1822 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) የእስማኤል ወታደሮች ቆርቲ (ኮርቲ) ከሚባል ቦታ ሲደርሱ ሜህራ ከግመልዋ ላይ ሆና ጦርዋ እንዲገጥም አዝዛ ታላቅ ጦርነት ተደረገ ። 800 ያህል የጥቁሮች ሬሳም በቆርቲ ሜዳ ላይ ወደቀ ። በጦርነቱ ጊዜ አብሮ የነበረው ዋዲንግተን እንደጻፈው በጦሩ ሜዳ የወደቁት 800 ጥቁር ሬሳዎች አንዳቸውም ጆሮ አልነበራቸው ። ከቆርቲ ጦርነት በኋላ በነበረው ዘረፋና ግድያ ሶስት ሺ ጆሮዎች ባንድነት ሆነው ወደ ካይሮ ተላኩ ። አምሳ ፒያስተር ለማግኘት ጆሮዎቹ የሚቆረጡት ከሞተ ሰው ላይ ብቻ ሳይሆን በሕይወት ካለም ሰው ላይ ነበር

የእስማኤል ወታደሮች በሱዳን ውስጥ ታላቅ ድል ካገኙ በኋላ የሱዳኑ ንጉስ (ሜክ) ኒምር የመጣበት ጠላት እንደማይበገር አውቆ ሰላም እንዲወርድ በእርቅ ለመግባት ተስማማ ። ይሄው የኒምር አሳብ ወደ ካይሮ ተልኮ ከመሐመድ አሊ የመጣው መልስ 30,000 ጥሬ ብር ፣ ስድስት ሺ ባርያዎችን በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ እንዲገብር ፣ ካልገበረ ግን ጦርነቱ እንዲቀጥል የሚል ሆነ

ኒምር ሥልጣን የያዘው በ1806 ዓ.ም. ግድም ነው ። ቁመቱ 6 ጫማ ርዝማኔ ያለው ሲሆን የላይ ልብሱ የነብር ቆዳ ነው ። ይህም የአባይ ዳርቻ ሹማምንት ምልክት ነበር ። ወደ ውጭ ሲሔድም ታላቅ ግንጥላ ተይዞለት ነው ። ጠባቂዎቹም ሶስት መቶ ፈረሰኞች ይሁኑ እንጂ ያላቸው ጠመንጃ ከሃያ አይበልጥም ። ከሻጊያዎች ጋር ሁልጊዜ በውጊያ ስለሚኖር የእስማኤል ጦር ጉረቤቶቹን ሻጊያዎችን እያረደ ሲጨርስ ኒምር በሱ የማይደርስ መስሎት ሳያግዝ ቀረ ። ሻጊያዎች ድል ሲሆኑ ሻጊያዎችን የደበደበው በትር ወደሱ ሲዞር ከሻጊያዎች ባገኘው ትምህርት ልገብር አለ ።

ኒምር ከካይሮ ከመሐመድ አሊ የመጣውን የግብር ጥያቄ ለሕዝቤ ላስረዳ ብሎ በእስማኤል እጅ ከወጣ በኋላ ሕዝቡን ሰብስቦ አማከረ ። ሕዝቡም እንኳን ባንድ ቀንና ለሊት በመትም ቢሆን ያን ያህል ግብር ለመስጠት ባለመቻሉ ከመገበር ይልቅ ተዋግቶ መሞቱን መረጠ ። ሌሊት ሲሆንም ሕዝቡ እስማኤል የሠፈረበትን ሠፈር በእሳት አቃጠለው ። እስማኤልም ከዚያ ለመውጣት ሞክሮ ሳይሆንለት ቀርቶ ሞተ ። የአሁኑ ትረካ በመተማ በኩል ስላለው ብቻ ነው ።

እስማኤል እንደሞተ በቦታው መሐመድ ቤይ ተተኩቶ ሱዳኖችን ፈጁዋቸው ። በተለይ የቂም ሥቃይ ለማሳየት በማለት ወንዱን እየሰለቡ ፤ ሴቶቹን ጡታቸውን እየቆረጡ ለቀቁዋቸው ። ኒምርም ሸሽቶ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ገብቶ በተራሮች ውስጥ ተደበቀ ። እነ መሐመድ ቤይም ወደፊት እየገፉ መተማ ድረስ መጥተው ኒምርን ቢያጡ መተማ ከተማን አቃጠሉት ። በጠቅላላው አምስት ሺ ሱዳኖችንም ገደሉ ።

ይሄው ከግብፅ የመጣው ጦር የኢትዮጵያን ወሰን አልፎ ገባ። ለአገባባቸው ሰበብ ያገኙት ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ የተደበቀውን ኒምርን እንይዛለን በማለት ነው ። የግብፅም ጦር ከኢትዮጵያ ምድር ገብቶ ማስገበር ጀመረ ። ይህን ነገር ደጃች ውቤ እንደሰሙ የግብፅን ጦር ከኢትዮጵያ ምድር ለማስወጣት አስበው ትግራይ ውስጥ በተነሳባቸው የተቃዋሚዎቻቸው የሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት ሳይዘምቱ ቀሩ ። ኒምር ግን ወልቃይት ሆኖ የተቻለውን ያህል የግብፅን ጦር አላስገባ ብሎ ሲከላከል ቆየ ። በኋላም የደምቢያ ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ክንፉ ደርሰውለት የግብፅን ጦር ከወሰን አርቀው አባረሩ ።

ደጃዝማች ክንፉ ይህን ወሰን አልፎ ገብቶ የነበረውን ጦር አባርረው ወደ ግዛታቸው ሲመለሱ በሱዳኑ ቅኝ ገዥ በአህመድ ቃሲምና ከካይሮ በመጣለት ረዳቱ በረሺድ የሚመራ ጦር ባንድነት መጥቶ በኢትዮጵያ ግዛት ለመግባት እየዘረፉና እያስገበሩ ስላስቸገሩ ደጃዝማች ክንፉ እንደገና በ1829 ዓ.ም. በሚያዝያ ማለቂያ ዘምተው ዋድ ቃልተቡ በተባለ ሥፍራ ጦርነት ገጥመው ታላቅና ዝነኛ ያደረጋቸውን ድል አገኙ ።

የደጃዝማች ክንፉ ድል ማድረግ በካይሮ ከተማ በተሰማ ጊዜ አሊ ቀርሽድ ፓሻ የሱዳን ገዥ እንዲሆን ተሹሞ ጥሩ መሣሪያ የያዘ አዲስ ጦር ይዞ በግስጋሴ ድል ለሆነው ሠራዊት ደረሰለት ። ይህም አዲስ ጦር መተማ አካባቢ ደርሶ ወሰን ሳያልፍ ሠፈረ ። ደጃች ክንፉም እንደገና ጦራቸውን ይዘው ለመዝመት ሲሉ ወሬው ከግብጾች ዘንድ ስለደረሰ በአስቸኳይ ኢትዮጵያን ለመውረር ያለ ምጣታቸውንና አሁንም የሰፈሩት ወሰን ሲያልፉ መሆኑን የሚነገር መልክተኛ ልከው ደጃች ክንፉን ከመዝመት አስቀሩዋቸው ። ከዚህ የተረፈው በቴዎድሮስ ትረካ ውስጥ አለ ። ትንሽ ለመጨመር ቢያስፈልግ አጤ ዮሐንስ ሕይወታቸውን እስከ መሰዋት የደረሱት በዚሁ ወሰን በኩል ከመጣው የአረብ ጦር ጋር ሲዋጉ ነው ።



ምዕራፍ 9

# ልማት

አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው የነበሩትን ፈረንጆች አሰባስበው ለኢትዮጵያ እድገት የሚሆን ተግባር በውዴታ ብቻ ሳይሆን በግዴታም ጭምር እንዲሠሩ አደረጉ ። እነኝህም ሚስዮናውያን እና ለአገር ጉብኝት የመጡት ፈረንጆች በእጅ ጥበብ በኩል እምብዛም እውቀት ስላልነበራቸው የቴዎድሮስን ፍላጐት እንደምኞታቸው ሊፈፅሙላቸው አልቻሉም ።

ከሚስዮናውያኖቹ አብዛኛዎቹ ደጃች ውቤ ትግራይን በሚገዙበትና በራስ አሊ የምስፍንና ዘመን ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ናቸው ። የፕሮቴስታንቱ ጳጳስ ጐባት በ1823 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የአገሪቱን ሁኔታ ካጠኑ በኋላ ወደ አገራቸው ተመልሰው ሔዱ ። በ1827 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ሲመጡ ሶስት የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያንን ማለት ክራፍ ፣ ኢሰንበርግ እና ብሎምሐርት የተባሉትን ይዘው ገቡ ። እነኝህም ሚስዮናውያን ከቀሳውስት ጋር በተነሳው ያለመግባባትና ጭቅጭቅ ምክንያት ትግራይን ለቀው እንዲወጡ ታዘዙ ። ሔንሪ ዱፍተን በደቡብ ኢትዮጵያ ያሉትን ሕዝቦች ወንጌል ለማስተማር የመጣ ነበር ።

ሚስዮናውያኖቹ ከትግራይ ወጥተው ወደሸዋና ጐንደር በሔዱበት ጊዜ ማለት በ1830 ዓ.ም. የታወቀው የጀርመን የተፈጥሮ ተመራማሪ ሩፔል ከፍራንክፈርት ተነስቶ ኢትዮጵያ ገባ ። ከሩፔልም ቀጥሎ ጀርመናዊው የእፅዋት ተመራማሪ ዶክተር ሺምፐር ለእፅዋት ምርመራና ጥናት ተግባር ወደ ኢትዮጵያ መጣ ። ከ1831---1835 ባለው ዘመንም ለፈብሬዢር እና ፔቲ የተባሉት ሳይንቲስቶች ለሳይንስ ምርመራና ጥናት ተግባር ኢትዮጵያ ገቡ ።

ፈረንሳዊዎቹ ኢንጂነሮች ፌሬ እና ጋሊነየር በምጽዋ በኩል አድርገው በትግራይ አልፈው ጐንደር ገቡ ። ማንስፊልድ ፓርኪንስ ከ1835 ጀምሮ እስከ 1840 ትግራይን እየጐበኘ የኢትዮጵያን ታሪክ ሲያጠና የቆየ ሰው ነበር ። አጤ ቴዎድሮስ እነኝህንና ሌሎ

ችንም አሰባሰበው ያለ እጠቀታቸው የእጅ ሥራ እንዲሠሩ አዘዙ ዋቸው ። እነኝህ ሰዎች ግን ጥቃቅን ነገሮችን ከመሥራት በስተ ቀር የቴዎድሮስን ሐሳብ ሊያሟሉ አልቻሉም ።

ከሚስዮናውያኖቹ አንዱ ፍላድ የሚባለው ታሞ ስለነበረ ወደ ውጭ አገር ሔዶ ታክሞ እንዲመለስ ቴዎድሮስን ፈቃድ ጠየቀ። ፍላድ ለቴዎድሮስ ወዳጅ ነበርና ሕመሙን ታክሞ በሚመለስበት ጊዜ የጅ ሥራ አዋቂዎች ይዞላቸው እንዲመጣ ቴዎድሮስ ለመኑት ። ፍላድም ፈቃደኛ ሆኖ በመገኘቱ አጤ ቴዎድሮስ አድራሻ የሌለው ለፍላድ የምስክር ወረቀት የሚሆን ፡ የእሳቸው መልክተኛ መሆኑ ንና ጠቢባን እንዲያመጣላቸው መታዘዙን የሚገልጽ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ሰጡት ።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡
፩አምላክ። የእግዚአብሔር፡ፍጡር፡በርያ
ው፡የዳዊት፡የሰሎሞን፡ልጅ። ንጉሠ፡ነገ
ሥት፡ቴዎድሮስ። ዘኢትዮጵያ ።አቶ፡
ፍሳጥን፡በአይሮጳ፡ልኬ፡ሰድጄዋለሁ ።ብ
ልህ፡ሠራተኛ፡ፈልጌ አለሁ። ከኔ፡ዋሀዊ ጠማ
ን፡ሠራተኛ፡ሁሉ።በደስታ፡እቀበለዋለሁ፡
ቢኖርም፡ደስ፡አሰኝቸ፡እኖረዋለሁ።ብ
ልሀትኛም፡አስተምሮ፡ወደ፡አገሬ፡እሰደ
ሰለሁ፡ቢላ።ደመወዙን፡ሠጥቼ፡ደስ፡አ
ሰኝቸ፡ሸኝቼ፡እሰደዋለሁ።በእግዚአብሔ
ር፡ኃይል።የእግዚአብሔር፡እምነት፡ይሁንብኝ።



ክርስቶስ፡በተወለደ፡በሺህ፡ተ፰፻፶፰ ዘመ
ን፡በዘመነ፡ማርቆስ፡በመጋቢት፡በ፲ቀን፡ዘጊ
ሳይ።ተፃፈ።



ፍላድ ይህን ደብዳቤ ይዞ ወደ ኤሮፓ ሔደ ። ሕመሙን ድኖ ሚስት አግብቶ በዓመት ከመንፈቁ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ዋልድሜየር ፡ ቤንደር ፡ ኪንስለ ፡ ሜየር ፡ ሳልሙለር እና እስኮርዝ ከነልጁ ሆነው አብረውት መጡ ። ዋልድማየር ለወንጌል ስብከት ሥራ ከጳጳስ ጐባት የተላከ ቢሆንም ሌሎች ግን የእጅ ሥራ ሞያ የነበራቸው ነበሩ ። ሆኖም በጉዞ ላይ እንዳሉ የእስኮርዝ ልጅ ሞተ። ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው ወጭኔ ላይ ሲደርሱ መንገ ደኞቹ በሙሉ ታመሙ ። ከጥቂት ቀናት በኋላ እስኮርዝ በያዘው ሕመም ምክንያት ሲሞት ሌሎቹ ድነው በስላሳ ሁለት ግመሎች የተጫነውን ጓዛቸውን ይዘው ጐንደር ገቡ ። ከግመሎቹ ጭነት አብዛኛው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር ።

በጆን ቤል አማካይነት ከቴዎድሮስ ጋር ተገናኙ ። አጤ ቴዎ ድሮስም በደስታና በአክብሮት ተቀበሉዋቸው ። በመንገድ ስለሞ ቱት ሰዎችም በጣም ማዘናቸውን ገልፀው “ እግዚአብሔር የኔን ኃጢአት ቆጥሮ ነው እነዚህን ሰዎች ከኔ የወሰዳቸው ” ማለታቸ ውን ዋልድሜየር ጽፏል ። ከዚያም የእያንዳንዳቸውን ችሎታ ጠይ ቀው በችሎታቸው መሠረት እንዲሠሩ አዘዙ ። ቴዎድሮስ የሚመጣውን የውጭ አገር ሰው ሁሉ ሲገናኙ ዋናው ጥያቄያቸው “ ምን ሥራ ታውቃለህ ? ” ማለት ነበር ።ምንም አላውቅም ካለ ዳግመኛ አያነጋግሩትም ። ፈጥኖም ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ያዛሉ ።

ለምሳሌ ኸንሪ ዱፍተን የመጣ ጊዜ ከቴዎድሮስ ጋር ተገናኘ ራሱ ኸንሪ ዱፍተን እንደጻፈው "የባሩድንና የእርሳሱን አሠራር ትች ላለህ ?" ቢሉት "የለም ። እንዲህ በማለቴ አዝናለሁ እንጂ አላው ቅበትም ። በአገሬም ቢሆን በኀምሩክ ጸሐፊነት እሠራ የነበር ኩኝ ነኝ" አላቸው ። አጤ ቴዎድሮስም "ይሄም መልካም ነው ። አንድ የእንግሊዘኛ ፀሐፊ እንዲኖረኝ ብዙ ጊዜ አስብ ነበር ። አሁን አንተ በዚያ በኩል ታገለግለኛለህ" አሉት ።



የጋፋት መንደር (ደብረታቦር)

ቴዎድሮስ የሰበሰቡዋቸውን ፈረንጆች መቅደላ አስቀመጡዋ ቸው ። በዚያም ያለው ብርድና ሌላውም ሁኔታ ለፈረንጆች አል መች ስላለ ጆን ቤል ከቴዎድሮስ አስፈቅዶላቸው ከመቅደላ ተራራ ላይ እንዲወርዱና ጋፋት እንዲኖሩ አስደረገ ። ጆን ቤል በዚህ ልመና የገባው ከኢትዮጵያዊት የወለዳት ሴት ልጁ ዎልድ ሜየርን አግብታ ከባሏ ጋር መቅደላ ስለነበረች በሷም ውትወታ ጭምር ነው ። ከቴዎድሮስ ፈቃድ እንደተገኘም በሰኔ ወር 1852 ዓ/ም ፍላድ ከነሚስቱ ፣ ዎልድሜየር ከነሚስቱ ፣ ቤንደር ፣ ሳልሙለር ፣ ኰንዝላን፣ሜየር ከነሚስቱ፣ (ቴዎድሮስ በትርጉሙ ከንቲባ ይሉት ነበር) ወደጋፋት ሔዱ ። በዝናብና በጭቃው ምክንያት እየተጉላሉ ከሰባት



ቀን በኋላ ጋፋት ደረሱ ። በዚያም በህብረት እየሆኑ 12 ትናንሽ ቤቶች ሠሩ ። በህብረት ሥራውም አንዱን ቤት ሠርተው የሚጨ ርሱት በአምስት ቀን ነበር ። በዚህ ዓይነት የህብረት አሠራር እያን ዳንዳቸው ሁለት ጐጆ አገኙ ። አንዱ ቤት የመኝታና እልፍኝ (ሳሎን) ሲሆን አንደኛው ማድቤት ነበር ። ጋፋትም የኤሮፓውያን ሠፈር ሆነ ።

አንድ ቀን ንጉሱ ዎልድሜየርን "እናንተ የኤሮፓ በዎች በጣም ብልሆች ናችሁ ። ግን ችሎታችሁን ደብቃችኋል ። አሁን በጣም ትልቅ የሆነ መድፍ እንድትሠሩልኝ እፈልጋለሁ ። መሥራቱን እና ውቅበትም ብትሉ ሁላችሁም ዋሾዎች መሆናችሁን አረዳለሁ ። አነኝያን ያናደዱኝን ምን እንዳደረግኋቸውም ታውቃለህ" ብለው በድንገት ማዘዛቸውን ራሱ ዎልድሜየር ጽፎታል ።

ዎልድሜየር ስለራሱ አስተሳሰብ ሲጽፍ "አናውቅበትም ብል ሁላችንንም ይገድሉናል ። እናውቅበታለንና እሺ እንሠራለን ብልም ካልሠራን ያው መገደላችን ነው ብዬ ጥቂት አሰብኩና ለመሥራት የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ እንሞክራለን አልኳቸው" ብሏል ። ቴዎድሮስ በዎልድሜየር አመላለስ ተደሰቱ ። ሥራው እንዲጀመርም አዘዙ ። አንዳንድ ሰዎች እየመጡ "ንጉሱ መድፉ ከተሠራ በኋላ እነኚህን ባርያዎች ደብረ ታቦር ተራራ ላይ እገላቸዋለሁ ሲሉ ሰማን" እያሉ ለፈረንጆቹ ይነግሩዋቸዋል ። ፈረንጆቹም ንጉሡ ምን ዓይነት ተለዋዋጭ ጠባይ እንዳላቸው ያውቃሉ ። ከፈረንጆቹ ጋር ሆነው ተማሪዎችን ያስተምሩ የነበሩትን ደብተራ ሣህሉን ያለምንም ጥፋትና ጥየቃ ጠርተው እጅና እግራቸውን ቆርጠው ጥለዋቸዋል ይህ ከፈረንጆቹ አእምሮ አልጠፋም ። የፈረንጆቹንም አሽከሮች እያስጠሩ አስገድለዋቸዋል ። አስረዋቸዋልም ። ይህን ሁሉ የሚያው ቁት ፈረንጆች ሰዎቹ እንደነገሩዋቸው መድፉ ከተሠራ በኋላ ይገድ ሉናል ብለው ቢሰጉም ፣ ባይሠራም ደግሞ ያው መገደላቸው ስለሆነ ሥራውን ሞክረው የሚመጣውን መጠባበቅ እንደሚሻል ወሰኑ ። በውሳኔያቸው መሠረትም የመድፉን ሞዴል በወረቀት ላይ ሠር ተው ዎልድ ሜየር ለቴዎድሮስ አቀረበ ። ንጉሱም ስዕሉን አይተው ከተስማሙ በኋላ በአስቸኳይ እንዲሠራ አዘዙ ። የጉልበቱን ሥራ የሚረዱዋቸውም በሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን ሰጡዋቸው ።

ኸንሪ ዱፍተን በመጽሐፉ ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልፅ እንዲህ ይላል ። ". . . . ለዚህ ለመድፉ ሥራ ምንም ዓይነት ችሎታ ቀርቶ

አሳብም የሌላቸው ስለነበረ. . . .ከንጉሱ ዘንድ ቀርበው መድፍ መሥራት ቀርቶ ሁኔታውን እንደማያውቁ አስረዱ ። በእንግሊዝ ፤ በጀርመን ወይም በፈረንሳይ አገር በፋብረካ ስለሚሠራ በንግድ ልውውጥ ማስመጣት ስለሚቻል በዚያ በኩል አጠያይቀው ለማስፈፀም እንደሚችሉ ነገርናቸው ። ንጉሱ በዚህ መልስ አልተደሰቱም ። ምኞታቸው በአገራቸው ውስጥ መሥራት እንደሚቻልና ከሌላ ጥገኝነት ለመውጣት መሆኑን ተናገሩ ። ኤሮፓውያኖቹ እያቅማሙ ስላስቸገሩ የኤሮፓውያኖቹን አሽከሮች በሙሉ ሰብስበው በሰንሰለት አሠሩዋቸው ። ይህም ጌቶቻቸው የንጉሱን ምኞት አስከፈፀሙ ድረስ መሆኑ ተነገራቸው ።

". . . .ከሁሉም የተሻለ እውቀት ያለው ሞርዝ ነው ። የብረት ማቅለጫውም ምድጃ ከሸክላ እንዲሠራ ተወሰነ ።. . . .ከዚያ ስለሚቀጥለው ሥራ እውቀት የላቸውም ነበርና እየተሰበሰቡ ራሳቸውን ገጥመው ከየመጽሐፉ መረጃ ይፈልጉ ጀመር ።. . . በአሸዋ በተደባለቀ አፈር ሸክላ(ጡብ) ሠርተው ምድጃውን ካበጁ በኋላ አፈር ለማቅለጥ ቢሞከሩ ብረቱ ቢቀልጥም አልወርድ አለ ። አሁን የቀራቸው ዕድል እንደገና በሌላ ዘዴ መሞከር ነው ። በየባላገሩ እየዞሩ ለሸክላ መሥሪያ የሚሆን ጥሩ አፈር ይፈልጉ ጀመር ። አፈሩን አግኝተው በዚያ አፈር ሸክላ እንደገና ምድጃው ተሠራ ። አሁን ከማቅለጫው ብረቱ እየቀለጠ ይወርድ ጀመር ። አሁን ሁሉም ተደሰቱ ። ንጉሱም እየተመላለሱ በማየት ውጤቱን ይጠባበቁ ነበርና ከዚያ ወዲያ ልጆቼ እያሉ ይጠሩዋቸው ጀመር ።. . ." ይላል ። ሞርዝ በፊት የራሽያ ወታደር የነበረና በኋላም የፖላንድ ወታደር የነበረ ነው ። ወደ ኢትዮጵያም የመጣው ለጉብኝት አገር ለማየት ነበር ።

ምንም እንኳን ኸንረ ዱፍተን እንደገለፀው በብረቱ መቅለጥ ምክንያት ገና በውጥኑ ቴዎድሮስ ቢደሰቱም በዚያን ጊዜ የእንግሊዝ ጦር እስረኞቹን ለማስለቀቅ ወደ ኢትዮጵያ ሊመጣ ነው እየተባለ በሰፊው ይወራ ነበርና ቴዎድሮስ እየተበሳጩ ብዙ ሰዎችን ይገድሉ ጀመር ። ይህን የግድያ ብዛት ያዩት ፈረንጆችም በፍርሃት ሥራቸውን ያጣድፉ ጀመር ። ቴዎድሮስም በየቀኑ እየተመላለሱ የምድጃዎቹን የብረት ማቅለጥ ሥራ ይመለከታሉ ፤ ይቆጣጠራሉም ። አለቃ ተክለ ኢየሱስ እንደጻፉት ". . . .መድፉ የተሠራው ከጐንደር በተዘረፈው ንዋየ ቅድሳት ነቅሳ ባለው መስቀልና ቃጭል ፤ በሰንና በብረት ነሐስ ነው. . . ." ይላሉ ።



ብረቱ በብዛት ቀልጦ ከመጨረሻው ደረጃ በደረሰበት ጊዜ ቴዎድሮስ መጥተው ከሁለቱ ምድጃዎች መሀል ከቆሙት ፈረንጆች አጠገብ ሆነው የዎልድሜየርን እጅ ያዙና "አሁን ምን እንደማደረግ ንገረኝ ። ትእዛዝ እንድሰጥላችሁ" አሉት ። ዎልድሜየር ራሱ እንደጻፈው ንጉሱ በድንገት እጄን ሲይዙት በጣም መደንገጡን ገልጿል ። ከምድጃው ይጨምሩኛል ብሎ አስቦም ነበር ። በዚያን ጊዜ ደግሞ ዎልድሜየር ሥራው ባይሳካም ". . . .ብረቱን ካቀለጡት ምድጃዎች ውስጥ ይጨምሩናል. . . ." እያለ ያስብ ነበር ።

ብረቱ ደህና ሆኖ መቅለጡን ያየው ዎልድሜየር ወደ ቴዎድሮስ ጠጋ ብሎ የምድጃዎቹ በዮች እንዲከፈቱ እንዲያዙ ነገራቸው። በቴዎድሮስ ትእዛዝ ሲከፈትም የቀለጠው የብረት ወንዝ ሃያ ደቂቃ ያህል ከወረደ በኋላ የሞዴል ጉድጓድ ሞላ ። ንጉሱም ተደስተው የመድፉን ስም ሰባስቶፖል ብለው ሰየሙት ። ብረቱ ቀልጦ የገባበት ሞዴል ቦታ ከሶስት ቀን በኋላ ሲከፈት ጥሩ ፎርም ይዞ ተገኘ ።

ይህ መድፍ ተሠርቶ ካለቀ በኋላ ስላለው ሁኔታ ዎልድሜየር በጻፈው መጽሐፍ እንዲህ ይላል ። ". . . ሠርተን እንደጨረስን አንዱ ሹማቻው 'ጃንሆይ ፤ አሁን የምንፈልገውን ሁሉ አገኘን እርስዎም ትልቅ ታሪክ መሠረቱ ። እንዲህ ያለ ነገር ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ አልተሠራም ። ለመሥራት የበቃው በእርስዎ ዘመነ መንግሥት ነው ። ከእንግዲህ ወዲያ ከእነኝህ ነጮጭ አህዮች የምንፈልገው የለም' አላቸው ።. . . ." ይላል የሰውየው አስተሳሰብ ፈረንጆቹን ለማስገደል ነበር ። ቴዎድሮስ ግን ዎልድሜየር እንደጻፈው ". . . . ይቆዩ ። በፊት ለመድፉ መሔጃ ጋሪ ይሥሩ" አሉ ። በመድፉ ሥራ ላይ ለተካፈሉት ኤሮፓውያንም የክብር ቀሚስ ፤ በወርቅና በብር ዕቃ ያጌጠ ፈረስና በቅሎ ሸለሙዋቸው ። ለእያንዳንዳቸውም አንዳንድ ሺህ ብር ሰጡዋቸው ። የመጡበትንም የሚስዮን ሥራ እንዲሠሩና እንዲያስተምሩ እየተሰበሰቡም እንዲፀልዩ ፈቀዱላቸው ።

ቴዎድሮስ ፈረንጆቹን በሽልማት ካስደሰቱ በኋላ ለመድፉም ሆነ ለሌላ ዕቃ ማጓጓዣ የሚሆን ጋሪ እንዲሠሩ ጠየቁዋቸው ። እነሱም ተረባርበው አስራ አራት ጋሪዎችን ሠሩ ። የጋሪዎቹን ሥራ ከጨረሱ በኋላ ቴዎድሮስን ወደ መጥፎ ተግባር ከሚመሩዋቸው አወዳድ ባይ ሰዎች አንዱ ቀርቦ "ከእንግዲህ የምንፈልገው ነገር የለ

ምና እነኝህ ነጭ አሀዮች ይገደሉ” ብሎ እንደገና ቢያስታውሳ
ቸው “ጅል ። መድፉ የሚሔድበትን መንገድ ማን ሊያሠራው ነው?”
ብለው መለሱለት ።

ቴዎድሮስ መድፉ ተተኩሶ ምን ያህል ርቀት ለመምታት እንደ
ሚችል ለማየት ፈለጉ ። መድፉና ጥይቱ በሚሞከርበት ቀን ቴዎድ
ሮስ ወደ ጋፋት መጡ ። ከደብረታቦር እስከ ጋፋት ያለው የመንገድ
ርቀት አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ይሆናል ። ስለመድፉ አተኳኮስ
ሁኔታ ዱፍተን ሲናገር “. . . .እኛም ሚስተር ሳልሙለር ግቢ ሆነን
ተቀበልናቸው ። ግቢው አርቆ ለማየትም አመቺ ነበር ። ምንጣፍ
ወጥቶ ተነጠፈና ንጉሰ ነገስቱ ተቀመጡ ። ሙሴ ሌዝሮን አጠገባ
ቸው እንዲቀመጥ ፈቀዱለት ሌሎቻችንም በያገኘንበት ቦታ ተቀ
መጥን ። . . .ይህ ጥይት በተተኮሰበት ጊዜ ንጉሱ በአሳብ ተመስጠው
ነበር ። ራሳቸውንም ደፍተው ከማንም ጋር አይነጋገሩም ነበር ።
እስተነአካቴውም ከንፈራቸው እንኳ ሲከፈት አላየሁም ።. . . .
ሁኔታቸው ተኩሱ እስቲሳካ ድረስ አልተለወጡም ። ከተተኮሰ በኋላ
ዙሪያቸውን ተመለከቱ ። አጠገባቸዎ በተቀመጠውም ላይ ዓይና
ቸው ፈዝዞ ቀረ ። ኤሮፓውያኖቹም ፈዘዙ ። ንጉሱም ከዚህ የበላጠ
ጥይት እንዲሠራላቸው ጠይቀው የተሻለ ትልቅ መሥሪያ ቤት እንደ
ሚሠራና የፈለጉትን ነገር ሁሉ እንደሚቀርብላቸው ነገሩዋቸው ።
ይህ ሁኔታ በሚካሔድበት ጊዜ ቴዎድሮስ ከምንጣፉ ላይ ካጠገ
ባቸው ከእሳቸውና ከሙሴ ሌዝሮን መሀል ከተቀመጠው ከሙሴ
ቡርጋርድ ልጅ ጋር ይጫወቱ ነበር ። ይህም እንግዳ ነገር ነበር ።
. . . .የዚህ ጦረኛ ሰው ከንድ ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን የገደለ፡
አስር ሺህ ሰዎችን ያህል ገደል የጨመረ ክንድ ካንድ ትንሽ የነጭ
ልጅ ጋር ሲጫወት ማየት ድንቅ ነገር ነው. . . .” ብሏል ።

አለቃ ወልደ ማርያም እንደጻፉት ደግሞ “. . . .በተጨረሰም
ጊዜ ንጉሱ ሠሪዎቹን እንዎልድሜየርን ተኩሱትና ድምፁን ልስ
ማው ፣ የአረሩንም መንገድ ልየው ቢሉ እነዚያም በተንኮል ጥበብ
ሲያታልሉ አሁን ብንተኩሰው በከተማ ሀገር መካከል የድምፁ
ኃይል የቀረበች እርጉዝ ያስወርዳል ። የደከመ በሽተኛ ይገድላል
እያሉ እውነት አስመስለው ሳይተኩስ ቀርቶ. . . .ከደብረ ታቦር
ተነስቶ በሰባት ወር በብዙ ድካም ሰውም እየሞተበት እስከ መቅ
ደላ ደረሰ ይላሉ ።

እዚህ ላይ ዱፍትን ተተኩሶ መልካም ውጤት አሳየ ሲል
አለቃ ወልደ ማርያም ደግሞ የሙከራው ተኩሰ ያለመተኮሱን



ይገልጻሉ ። ግን ማንኛውም ገማች እንደሚገምተው ቴዎድሮስ ያንን
ያህል በጉጉት የጠበቁት ለአገሬ ትልቅ ሥራ እሰራላታለሁ ብለው
ያሰቡለትና ያሠሩት መድፍ ሥራው ካለቀ በኋላ ሳይሞከር ቀረ
ብሎ ለመገመት አስቸጋሪ ነው ። ቴዎድሮስን የመሰለ ሰው ቀርቶ
ሌላውም ቢሆን ያን የመሰለ ሥራ አሠርቶ ለእርጉዝና ለበሽተኛ
አስቦ አይሞከር የሚል የለም ። ዶክተር ብላንክ እንደጻፈውም
“. . . .በሚገባ በመተኮሱ አጤ ቴዎድሮስ በጣም ተደስተው ለሠራ
ተኞቹ የሚያስደስት ሽልማት ሰጦታ አድርገው መድፉን ከእሳቸው
ጋር ይዘው ለመሔድ መሰናዳት ጀመሩ. . . .” ይላል ። ይህም አስ
ተማማኝ የሆነ ምስክርነት ነው ። ምክንያቱም የእንግሊዝ ጦር መጣ
እየተባለ በሚወራበት ጊዜ ቴዎድሮስ ያን መድፍ ሲያስሞክሩ
የእንግሊዝን ጦር ሊገጥሙበት ወደ መቅደላ እፉፍ በብዙ ችግር
አያስግዙትም ነበር ። ተተኩሶ በውጤቱ ባይደሰቱም ኖሮ እንድ
ሙቀጫ የመሰለ ድብልብል ከባድ ብረት በታላቅ ችግርና መከራ
ወደ መቅደላ ባልተጓዘ ነበር ። የመድፉ ክብደት 80 ኩንታል ወይም
8000 ኪሎ ግራም ነው ።

የእንግሊዝ ጦር ዙላ ወደብ መከማቸቱን ቴዎድሮስ ሰሙ ።
ይህን እንደሰሙም ያን፡ ያሠሩትን ታላቅ መድፍ ወደ መቅደላ ለማ
ስጓዝ ጀመሩ ። ወደ መቅደላ የሔዱበት ዋናው ምክንያት መቅደላ
ተራራ በርያውን ሙጥጥ ያለ ገደል በመሆኑ ጠላት ከዚያ ቦታ
በቀላሉ ለመድረስ እንደማይቻል ታስቦ ነው ። ወደ ተራራው ለመ
ውጣትም ያለው በር አንድ ብቻ ነው ። ይህም በመሆኑ አጤ ቴዎድ
ሮስ የእንግሊዝን ጦር መቅደላ ተራራ ላይ ሆነው ለመግጠም አስ
በው ነው ።

መስከረም 21 ቀን 1860 ዓ.ም. መድፉ በጋሪ ላይ ተጭኖ
የመቅደላው ጉዞ ተጀመረ ። ከጋፋት እስከ መቅደላ ድረስ ያለ
የመንገድ ርቀት 320 ኪሎ ሜትር ያህል ይሆናል ። ይህ ርቀት
ደግሞ እንኳን 8000 ኪሎ ግራም የሚከብድ መድፍ የጫነ ጋሪ
የሚጎተትበትና ሌጣ የሆነ ሠራዊት የሚጓዝበት መንገድ የለም ።
ይህን ሁሉ ቴዎድሮስ ያውቃሉ ። በመንገዱ ምክንያት ችግር እንደ
ሚደርስም ተገንዝበውታል ። ቢሆንም ቴዎድሮስ ደፋርና ችኩል
በመሆናቸው ሠራዊቱ እየቀደመ መንገድ ሲሠራ መድፉ ከኋላ
እንዲከተል አዘዙ ።

መንገዱን ለመድፉ መጎተቻ የሚሆን ገመድ ከጭራና
ከበግ ሰንበር በወፍራሙ ሲገመድ ከርሟል ። ጋራው በቁልቁለት




የቴዎድሮስ መድፍ (ሰባስቶፖል)

እንዳይሽከረከር ፣ በዳገት ወደኋላ እንዳይመለስ ማገጃ ወይም የፍጥነት መቆጣጠሪያ አለው ። ብዙ ገመዶች ከጋሪው ፊት ከታሠሩ በኋላ 800 ጋሪ ጐታች ሰዎች ተመደቡ ። አብዛኛው ክፊት እየጐተተ ጥቂቱ ከኋላ እየገፉ ያ ታላቅ አስቸጋሪ ጉዞ ተጀመረ ። ችግሩ የመንገዱ ብቻ ሳይሆን በዚያን ጊዜ ቴዎድሮስን ብዙ ሰዎች ክድተዋቸው ስለነበረ መንገዱ በሙሉ በሽፍቶች የተሞላ ነበር ። ስለዚህም ጉዞው መንገድ እየሠሩ መድፍ የተሸከመውን ጋሪ መጐተት ብቻ ላይሆን ከሽፍቶች ጋር ጦርነት እየገጠሙ መንገዱን ማስለቀቅም ነበር ። በዚህ ምክንያት በቀን ውስጥ ረጅም ጉዞ ተደረገ የሚባለው የሶስትና የአራት ኪሎ ሜትር ርቀት ብቻ ነበር ። ሌላው ችግር ደግሞ ጊዜውገና ሰብል ያልተሰበሰበበት ወቅት በመሆኑ ለሠራዊቱ በቂ ስንቅ አልነበረውምና ደክሞ እየዋለ የምግብ ችግር ሠራዊቱን ያጋጥመው ነበር ። ይህን ችግር ለመፍታትም አጤ ቴዎድሮስ ያገኙት ዘዴ ራሳቸው በሰብል መሀል እየገቡ እሸት እየቆረጡ በመመገብ ለሠራዊታቸው አርአያ ሆኑ ።

እስከ ጨጨሆ ድረስ ያለው መንገድ እምብዛም አስቸጋሪ ባይሆንም ከዚያ በኋላ ግን ያለው መንገድ የተራራ መውጣት ነበር ።



በዚያም ከባድ የሆነ የመንገድ ሥራ ችግር አጋጠመ ከን[illegible] ጀምሮ እስከ ምሽቱ ድረስም ሠራዊቱ በሙሉ መንገድ በመ[illegible]ት ይውላል ። የአገሬው ባላገርም እየታዘዘ በመውጣት ይረዳል ። አጤ ቴዎድሮስም ከሠራዊቱ መሐል ሳይለዩ ድንጋይ በመፈንቀልና አፈር በመደልደል ሥራ ሲያግዙ ይውላሉ ። ይህን መንገድ ከመነሻው



አጤ ቴዎድሮስ በመንገድ ሥራ ላይ

እስኪ መድረሻው ሔጀበት እንዳየሁት በዚያ ዘመን በእንደዚያ ያለ ጥሩ ምሕንድስና ይሠራል ተብሎ የማይታሰብ ነው ። ምንም እንኳን እኔ በበቅሎ በምጓዝበት ጊዜ መንገዱን ጢሻ ወርሶት አንዳንዱም ዘንድ ጐርፍ በርብሮ ያበላሸው ቢሆንም የአግድመት አያያዝና የመጠምዘግያው ፕላን ለኔ አስደንቆኛል ።

ጓዙ ተንታ በደረሰ ጊዜ ወዳጃቸውና የሚወዱት ዎልድሜየር ከእንግሊዝ ጦር ጋር መዋጋቱ እንዲቀርና ነገሩ በሰላም እንዲያልቅ ወደናፒር መልክተኛ እንዲላክ አጤ ቴዎድሮስን አማከሩቸው ። ቴዎድሮስ ባቀረበው አሳብ ተናደው ሽጉጣቸውን መዝዘው ዎልድ ሚየርን ሊገድሉት ካነጣጠሩበት በኋላ ሽጉጡን መልሰው ከቦታው ከተቱ ። ወዲያውም የያዙትን ጦር ቢወረውሩበት ጦሩ ለጥቂት ስቶት ከመሬት ገብቶ ተቀረቀረ ። ከዚህ በኋላ ለዎልድሜየር ይቅርታ ቢያደርጉለትም ዳግመኛ በቴዎድሮስ ፊት የሰላም ሁኔታን የሚያነሳ ጠፋ ። ባዚያን ጊዜ ግን የእንግሊዝ ቀዳሚ ጦር ከበሽሎ ሸለቆ ደርሶ ነበር ። አንድ ቀንም ቴዎድሮስ ዎልድሜየርን ጠርተው የሩቅ ማመልከቻ መነጥራቸውን ሰጡትና "....የበሽሎን ወንዝ አካባቢ ተመልከትበት እነኝያ እኔን ለመግደል የተላኩትን መልክተኞች ታያቸዋለህ? የለበሱትን ቀይ ልብስኝ በማየቴ ተደስቻለሁ ። የተደሰትኩበትም ዋናው ነገር ያ ቀጣፊ ካሜሮን ያመጣልኝን መልስ ለማምጣት የእንግሊዝን አገር በሙሉ በማንቀሳቀስ ነው" አሉት ።

መድፉ ከስድስት ወር ተኩል ጉዞ በኋላ ሰላምጌ ደረሰ ። ሰላምጌ ከመቅደላ ግርጌ ያለ ሰፊ ያለ ቦታ ነው ። ወደፊትም ቢሆን ስማቸው የሚጠሩት ፋላ ፣ እርጌ ፣ ሰላሴ እነኝህን የመሳሰሉት ሁሉ በመቅደላ ተራራ ወገብ ላይ የቦታዎች ስም ናቸው ።

መድፉ እየተጐተተ ሰላምጌ ከደረሰ በኋላ ስለነበረው ሁኔታ ዶክተር ብላንክ ሲፅፍ "...መጋቢት 16 ቀን 1860 ዓ.ም. ጋሪዎቹን መድፎቹንና አዳፍኔውን ይዘው ሰላምን ተራራ ሥር ሠፈር አድርገው ወደ አምባው ለመውጣት የሚያስፈልጋቸውን መንገድ ማሠራት ጀመሩ ።...ከሰላምጌ ተራራ ላይ የተሠራው መንገድ በፊ ሆኖ ቀጥ ያለ ተራራና ከግማሽ መንገድ ላይ በኃይል ስለሚጠመዘዝ ምናልባት ከባድ ጋሪዎችን ለማዞር የሚያስቸግር መስሎን ሰጋን ። አጤ ቴዎድሮስ የሥራውን አካሄድና አመራር አተኩረው ይመለከቱ ስለነበረ ብዙ ንግግር አላደረጉም ። ኋላ ግን ትልቁ አዳፍኔ መድፍ እየተጐተተ ብቅ ሲል አንድናዶ አመልክተው የሚስተር ራሳምን አስተያየት ጠየቁ ። ይህ ትልቅ ነገር ሁላችንንም አደነቅ ነው ። ሚስተር ራሳምም አድናቆቱን ከሠራተኛ ጋር ከገለፀላቸው በኋላ በቅርቡ የመጡት ሰዎችም ተመልክተው እንደሚያደንቁት ስለተናገረ ።.... አጤ ቴዎድሮስ ቆቀው ... ዎልድሜየር እንዲወርድና ራሳም ያለውን እንዲነግረው አዘዙት ።...ከዚህ በኋላ



አጤ ቴዎድሮስ አስቸጋሪ ቀጥተኛ ወደሆነው ቦታ ወርደው ሠራተኞቹን መምራት ያዙ ።... ያን የመሰለ ከባድ ዕቃ እንደዚያ ካለ ተራራና ገደል ሥፍራ ጐትቶ ለማውጣት ከቴዎድሮስ አመራር በስተቀር ሌላ ሰው ሊያደርገው እንደማይችል በፍፁም አምናለሁ ... መጐተቻው መጫኛ ጠፍሩ ብዙ ጊዜ የሠራ በመሆኑ አሁንም ቅድምም ስለሚቆረጥ በዚህ በመጨረሻው ሰዓት ላይ አደጋ ደርሶ ይህ የደከሙበት ትልቁ ሰባስቶፕል ገደል ገብቶ ግርማዊነታቸውን ሊያበሳጭና ሊያሳዝናቸው እንደሚችል በመገመት ሁኔታው እኛንም ከአደጋ ላይ ሊጥለን ስለሚችል እግዚአብሔር በሰላም እንዲያወጣው መፀለይ ግድ ሆነብን ። አጤ ቴዎድሮስ ከአንድ ትይዩ ከሆነ ድንጋይ ላይ ጦራቸውን ተደግፈው ቁመው በሥራው ላይ ሆነው ጠፍሩን ለሚስቡት አምስትና ስድስት መቶ ለሚሆኑ ሰዎች መልክት እየላኩ ሥራውን መምራት ያዙ ። አንዳንድ ጊዜ የሠራተኞቹ ድምፅ ሲበዛ ወይም መምሪያ ለመስጠት ሲፈልጉ እጃቸውን ወደ ላይ ብድግ ባደረጉ ጊዜ ያ ሁሉ ድምፅ ባንድ ጊዜ ፀጥ ስለሚል ከዚህ በኋላ ግልፅ በሆነ ድምፃቸው መናገርና መምራት ይጀምራሉ።



“በመጨረሻ ትልቁ አዳፍኔ መድፍ በሰላም ሰላምጌ ደረሰ ።
በፍጥነት ወጥተን ግርማዊነታቸው ላከናወኑት ትልቅ ሥራ ምሥ
ጋናችንንና አድናቆታችን እንደገለፅን ወደ መድፉ ሒደን እንድን
መለከት ታዘዝን ። ሶስታችንም ከመድፉ መጐተቻ ጋሬ ላይ ወጥተን
አድናቆታችንን በቃለ አጋኖ ስለገለፅን በዙሪያው የነበሩት ሁሉ
ተገረሙ ። ግርማዊነታቸውም ያስደሰታቸውን መሣሪያ እኛም ስላ
ደነቅንላቸው ከተቀመጡበት ከሰላምጌ አፋፍ ላይ ቀረብ ብለን እን
ድንቀመጥ አዘዙን ።. . . .” በማለት ሁኔታውን ገልጿል ።

ዶክተር ብላንክ እንደጻፈው “ሶስታችንም” ብሏል ። እነሱም
ራሳም ፣ ራሱ ብላንክና ፕሪዲውክስ ነበሩ ። ብላንክ እንደጻፈው
ሶስቱም ከቴዎድሮስ አጠገብ እንደተቀመጡ ቴዎድሮስ ወደራሳም
ዞወር ብለው ስለ እንግሊዞች መድፍ ሁኔታ ይጠይቁ ጀመር ።
ጥያቄያቸው የመድፎቻቸው ኃይል ምን ያህል ነው ? ምን ያህል
ርቀትስ ይተኩሳሉ ? ወታደሮቻቸውስ እንዴት ናቸው ? እያሉ
ነበር ። ራሳምም ራሱን ከመከራ ለማዳን ሲል ባጭሩ ስለወታደር
ነገር ምንም እንደማያውቅ መናገሩን ራሱ ጽፎታል ። አጤ ቴዎድሮስ
የራሳምን መልስ ችላ ብለው “. . . .እነኝህን የኔን የማይረቡ ወታደ
ሮች እንዴት አድርጌ የእናንተን ጥሩ የለበሱትን ወታደሮች ላላያ
ቸው እችላለሁ?. . . እንድ ጊዜ ኃይለኛ እንደነበርኩበት ጊዜ ቢሆን
ኖሮ በእርግጥ የእናንተን ወታደሮች ለመገናኘት ካረፉበት ከጠረፉ
ቦታ ድረስ እሔድ ነበር ። ወይም ደግሞ መልክተኛ ልኬ በአገሬ
ውስጥ ምን እንደሚፈልጉ እሰጠይቃቸው ነበር ። ሆነና አሁን አበ
ሻን በሙሉ አጥቻለሁ ። እሁን የቀረኝ ይሄ ድንጋይ ብቻ ነው ።
አሉት ። ያን መድፍ ያሠሩትም እንግሊዞችን ለመውጋት ሳይሆን
የአገራቸውን ሽፍታ ለማጥፋት እንደነበረ ገለፁለት ።

ምንም እንኳ በዘመናቸው ባለሞተር መኪና ቀርቶ ሕዝብ
የሚመላለስበት ሠረገላ እንኳ በኢትዮጵያ ውስጥ ባይኖርም ቴዎድ
ሮስ ኢትዮጵያን በሙሉ በመንገድ ለማገናኘት ከፍተኛ ምኞትና
ሐሳብ ነበራቸው ። ሽንሪ ዱፍተን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ሚስዮ
ናውያንን መንገድ እንዲሠሩ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ረዳት መንገድ
ሠሪዎች መስጠታቸውን በመጽሐፉ ይገልፅና ይህም ሊሆን የቻ
ለው ሚስዮናውያኖቹ “. . . .አንድ ቀን ከንጉሱ ጋር በአጀብ
ሲሔዱ ብዙ ድንጋይና ቋጥኝ ካለበት ቦታ ደረሱ ። በዚያም ሆነው
ኤሮፓውያኖቹ በኤሮፓ መንገድ ላይ እንዲህ ያለ መሰናከል ያለመ
ኖሩንና መንግሥት መንገድ ማሠራቱን ነገሩዋቸው ። ቴዎድሮስም



ወዲያው ከበቅሎአቸው መውረዳቸውንና ድንጋይ ማንሳታቸውን
ያየ ሁሉ ከበቅሎና ከፈረሱ እየወረደ ድንጋዮቹን ያነሳ ጀመር
ወዲያውንም ድንጋዮችም ሆኑ ቋጥኞች ተነስተው ጥቂት ማይሎች
ርዝመት ያለው ሥፍራ ጥሩ መንገድ ሆነ ።“. . . .አንድ ቀን ደግሞ
በመንገድ ሲሔዱ መሬቱ ተሰነጣጥቆ ፈረስና በቅሎ አላስኬድ
ሲል ተመልከተው ያንጊዜ በእግራቸው ነበርና የሚጓዙት ቆም
ብለው በያዙት ጦር መሬቱን እየቆፈሩ ሲያስተካከሉ ያየው ሠራዊት
ባንድ ጊዜ መንገዱን ደልድሎ ጥሩ መንገድ አደረገው ።. . . .”ይላል
እንዲያው ለአብነት ያህል ይህን ጠቀስኩት እንጂ የቴዎድሮስ የመ
ንገድ ሥራ በዚህ የተገታ አልነበረም ።

መኪናም—ሆነ ሠረገላ በሌለበት አገር መንገድ ለመሥራት
ቴዎድሮስን ምን አሳሰባቸው ?። ቴዎድሮስን መንገድ ለመሥራት
ያሳሰባቸው ።“. . . .መንገዱ ሁሉ በያቅጣጫው በየዱሩ ውስጥ
በመሆኑ ሽፍታውና ሌባው ነጋዴዎችን እየዘረፉ በማስቸገሩ ደንበኛ
መንገድ በሚስዮናውያኖቹ ለማሠራት ፈለጉ ። ዋናውን ከተማቸውን
ደብረ ታቦር አድርገው መንገዶች ሁሉ ከደብረ ታቦር ጋር እንዲ
ገናኝ ለማድረግ ወጠኑ ። ከጐንደር ከጐጃምና ከመቅደላ ጋር በአ
ውራ ጐዳና ለመገናኘትና ከእነዚህም መንገዶች ቅርንጫፍ ከሌሎች
ከተሞች ጋር እንዲያገናኝ እንዲደረግ ፕላን አወጡ ።” ሲል ሽንሪ
ይገልጣል ። ቴዎድሮስ ወደ ዋድላ ሲሔዱ ከሚስዮናውያኖቹ አንዱ
ሳልሙለር የሚያሠራውን የቤተሐራን መንገድ ሊጐበኙለት ሔዱ ።
ከዚያም እንደደረሱ ሳልሙለር “የሚረዳኝ አጥቼ ብቻዬን ሆንኩ”
ብሎ ለአጤ ቴዎድሮስ አመለከተ ይህን የሰሙት ቴዎድሮስ በጣም
ተቆጥተው “ይሄ ከሩቅ አገር መጥቶ ሲሠራ ያገሬ ሰው እምቢ
ሲል” ብለው የዋድላውን ምስለኔ ይመር ጐዳና የተባሉትን ገር
ፈው እንዲታሠሩ ማድረጋቸውን አለቃ ዘነበ ጽፈዋል ። ለሳልሙለ
ርም የራሳቸውን የሚቀመጡበትን በቅሎ ከነሙሉ ዕቃው ሸለሙት።
የጨጨሆን መንገድ ለሚሠሩት ለፍላድ 300 ብር ፣ ለቤንደር ፣ ለኪስሌ
እና ለዎልድሜየር 600 ብር ቀሚስ ፣ ድርብ እያለበሱ ሸለሙዋቸው።
ይህን ስናነብ ቴዎድሮስ ለአገራቸው እድገት ምን ያህል አሳቢ
እንደነበሩ እንገምታለን ።

ሚስዮናውያኖቹን በግዴታ ይዘው ያሠሩዋቸው በነበረ ጊዜ
ለ ሚስዮናውያኖቹ ረዳት የሚሆኑ በብዙ ሺህ የ ሚቆጠሩ ኢትዮጵያ
ውያኖችን ሰጥተዋቸው ነበር ። ሚስዮናውያኖቹም መንገድ ከመሥ
ራታቸውም ሌላ በሠሩት መንገድ ዕቃ የሚያመላልስ ጋሪም ሠር

ትው ነበር ። ይህም ብቻ ሳይሆን በውሃ ኃይል እየዞረ ልዩ ልዩ መንኮራኩሮችን የሚያዞር መኪናም ተሠርቶ ነበር ። በዚያን ዘመን የቅጥቀጣና ልዩ ልዩ ሞያ አላቸው የሚባሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በሚስዮናውያኖቹ ዘንድ ተሰብስበው እንዲሠሩና እንዲማሩም ተደርገው ነበር ። ሳልሙላር እና ዋልድሜየር ኢትዮጵያውያንን በ ጊገባ የጅ ሥራ በማስተማራቸው ቴዎድሮስ ተደስተው በየጊዜው ሥራው ወደ ሚሠራበት ወደ ጋፋት እየተመላለሱ ይጐበኙዋቸው ነበር ። አዳዲስ ሥራዎች ተሠርተው በሚያዩበት ጊዜም ዋልድሜየር እንደጻፈው “ የሚያላዝኑ እጆች ። አሁን እነኝህንም አፈር ይበላቸው ይሆናል ” እያሉ የዋልድሜየርን እጅ ይስሙ እን ነበረ ጽፍዋል ።

ወዳጃቸው የነበረው ፕላውዴን እንደ ኤሮ[illegible] አቆጣጠር ሰኔ 25 ቀን 1855 ዓ.ም. ወደ እንግሊዝ ወዳገሩ ባስተላለፈው ሪፖርት ላይ ሲገልጽ “....የአበሾችን አለባበስ እንኳ ላመለወጥ ጀምረዋል ። ሰዎቻቸው ሁሉ ከጋሎች በወሰዱት አለባበስ ግማሽ ራቁት መሆናቸው ቀርቶ ሙሉ ልብስ እንዲለብሱ አዘዋል ።... በያውራጃው ያለውን ወታደር ሁሉ ባንድ አዛዥ ሥር እያደረጉ ለመፍረድና ለመቅጣት ሥልጣን በሌላቸው በታማኞቻቸው ሥር እንዲታዘዝ አድርገዋል ።...ለወታደሩም ግንዘብ በመስጠት በደሞዝ እንዲተዳደር ወስነዋል ። ለሹማምንትም እንደየደረጃቸው ከመቶ ብር እስከ ሺህ ብርጳሚ ክፍያ ወስነውላቸዋል ።... ይህም ቢሆን እንደሚያስቡት በ ጊገባ ሆኖ አልተቋቋመላቸውም ።... ወታደሩም በጠመንጃ ብቻ እንዲበሰፍ እንጂ በጦርና በጐራዴ እንዳይሆን ያስባሉ ። ጦርና ጐራዴንም ወደማረሻነት ለመለወጥ ይመኛሉ ።... ” ብሏል ።

መጋቢት 6 ቀን 1858 ዓ.ም ቴዎድሮሰ ለራሳም በጻፉት ደብዳቤ “ .. ቱርኮች አገሬን ይዘውብኝ ባላንጋራ ሁነውኛልና መርከብ የለኝ በባህር አልችላቸውም... ” ብለው ነበር ። በዚህ ምክንያት የእንግሊዝ እስረኞችና ሚሲዮናውያኖቹ መርከብ እንዲሠሩላቸው ትእዛዝ ሰጡ ። ስለዚሁ ጉዳይ ዶክተር ብላንክ ሲጽፍ “... የጋፋት ሰዎች መርከብ መሥራት እንዲጀምሩ ቢታዘዙ ስለመርከብ ሥራ ምንም እንደማያቁ ገልፀው ፣ ነገር ግን ችሎታ ያለው ሰው ከመራን ለመሥራት ፈቃደኛ ነን ብለው በተጨማሪም ለመርከብ ሥራ ችሎታ ያለው ሰውና መሣሪያ ከእንግሊዝ አገር



ሚስተር ራሳም እንዲያመጣላቸው እንዲጠይቁት. . .የሚጠይቁትንም ሚስተር ራሳም በደስታ እንደ ሚፈጽም አረጋገጡ ።

“ . . .ከጥቂት ቀናት በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ለሚስተር ራሳም ደብዳቤ ጽፈው የመ[illegible]ከብ ሠራተኞች ከእንግሊዝ አገር እንዲያስመጣላቸውና ሠራተኞ[illegible] እስኪመጡ ድረስ እንዲቆይ ስለጠየቁት. . . ሚስተር ራሳምም . . .ወደ እንግሊዝ አገር ቢመለስና የግርማዊነታቸውን ፍላጐትና ጥያቄ ለንግሥቲቱ አስረድቶ ለማስፈፀም የሚቀለው መሆኑን ከስረ[illegible] በኋላ ግርማዊነትዎ ከዚሁ እንዳለሁ ደብዳቤ እንድጽፍ ከ[illegible]ም ልጻፍ ሲል መልስ ሰጠ ።

ቴዎድሮስ በዚህ የረጅም ጊዜ ሐሳብ አልተስማሙም ። የእንግሊዝ እስረኞችም ተጠይቀው መርከብ መሥራት ያለመቻላቸውን ገልፀዋል ። ሚስዮናውያኖቹም እናውቅበትም ብለዋል ። ለዚህ [illegible]ኃኒት ወይም መፍቻው ቁልፍ ራሳቸው ቴዎድሮስ በመሆናቸው ለመስራት ሥራውን መጀመር እንዳለባቸው ተገንዝበው ቴዎድሮስ የመርከብ ሥራቸውን ጀመሩ ። ሐሳባቸውም፡ እሳቸው ሥራውን ቢጀምሩ ሌሎች አ[illegible]ውያንም ስለሚረዱ ሥራው ከፍጻሜ እንደሚደርስ በመ[illegible] ብላንክ ሲጽፍ “ . . . . ራሳቸው ወርደው መርከብ [illegible] ጀመሩ ። . . . . ” ይላል ። ሌሎችም አ[illegible]ውያን በመ[illegible] ታላቅ መርከብ ተሠራ ። “ እንዲያውም ” ይላል [illegible] እንዲያውም [illegible] ድል እስቲመር ፈልሰፈው ሠርተው ነበር ። [illegible] ኮማቲሽ ሳይሠራ ቀረ ።. . .ጀልባዋን የሚያንቀሳቅሰው [illegible] መንኮራኩር በጣም ትልቅ ስለነበር ወደ ውሃው ውስጥ [illegible] እንዲገባ ለማድረግ በመቶ የሚቆጠር ሰው ያስፈልገው [illegible] ጀልባ ሥራ መንፈሳቸው በጣም [illegible] ሰጦ በነበረ [illegible] ሰለዚህ ትግባር ስላዋሉት ከሠራቸው አራት [illegible] ከሚገኝ ሥፍራ ላይ ኃይለኛ ጠላት ተነስቶ [illegible] . . ይላል ።

ይህ በኢትዮጵ[illegible] የመጀመሪያ ጊዜ በሞተር የሚንቀሳቀስ ጀልባ የተሠራው [illegible]58 ዓ.ም. በሚያዝያ ወር ነበር ። ራሳም ስለነዚሁ መርከቦች ሥ[illegible] ሲገልጽ “ . . . በሥራው ቴዎድሮስም ተካፋይ ነበሩ ። 60 [illegible] ርዝማኔና 20 ጫማ ስፋት ያላቸው ሁለት ጀልባዎች ተሠሩ ። [illegible] እነዚህ 2 ጀልባዎች እያንዳንዳቸው አንድ መቶ ሰዎች [illegible] ጀልባዋ ወደባህሩ ውስጥ ያዘቀጠችው አራት ኢንች ያህል [illegible] ነበር ።. . . ሚስዮናውያኖቹና ሕዝቡ ተሰ

ብስቦ በአድናቆት ጀልባዎቹን ሲመለከት ቴዎድሮስ ደግሞ በጣም
ደስ ብሏቸው ነበር ። ጀልባዋ በምትሞከርበት ጊዜ እኛን ይዘውን
አልሔዱም ። መልክተኛ ልከውም እናንተን የተውኩበት ምክን
ያት ምናልባት ጀልባዋ የሰጠመች እንደሆነ ውሃ ውስጥ ትገቡና
ትበሰብሳላችሁ (ትረጥባላችሁ) ብዬ ነው አሉን ።. . . በደህና ከተመለ
ሱም በኋላ እንደ የባህር ኃይል እንድናጃቅም ጠየቁን ።. . . . .
ብሏል ።

በቴዎድሮስ ታሪክ ውስጥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ጉልቶ
የሚታየው መድፍ ማሠራታቸው ብቻ ነው ። ግን ብዙ ሥራ አሠር
ተዋል ።



ምዕራፍ 10

# ፈረንጆቹ ለምን ታሰሩ?

አጤ ቴዎድሮስ ፈረንጆቹን ያሰሩበት ምክንያት ምንድነው ?
በእብሪት ተነሳስተው ነው ወይስ ምክንያት አላቸው ? የአንድን
መንግሥት ያውም በዚያን ዘመን የሚፈራውን የእንግሊዝን መን
ግሥት ቆንቢል የሆነውን ሰው ማሠር የማይገባ ቢሆንም ቴዎድ
ሮስ ያሠሩበት ዋናው ምክንያት ግን በኢትዮጵያ ላይ ጠላት ስለበ
ዛና ኤሮፓውያንም እየናቋቸው ስላስቸገሩዋቸው ነው ።

ቱርኮችና ግብጾች ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት ለመያዝ በያ
ለበት ይራወጣሉ ። በባህርም ሆነ በምድር የኢትዮጵያን ወሰን
እያለፉ አገር ይዘዋል ። በዚህ ላይ የካቶሊክ ሚስዮናውያን በእባ
ቸው ላይ ሌላ ፕሮፓጋንዳ ይሠራሉ ። ፈረንሳዮች ከኢትዮጵያ ጠላ
ቶች ጐን ተሰልፈው ለኢትዮጵያ ጠላቶች የመሣሪያም ሆነ የማበ
ረታታት ዕርዳታ ያደርጋሉ ። ፈረንሳዮች ለኢትዮጵያ ጠላቶች የሚ
ረዱበት ዋናው ምክንያት የኢትዮጵያ ኃይል ሲዳከም በደከመ ው
ጉልበት ላይ በአዲስ ኃይል ዘምተው ኢትዮጵያን ለመያዝ ባላቸው
ጉጉት ነው ። ይህም ጉጉት በቴዎድሮስ ዘመን የተጀመረ ሳይሆን
የቆየ ነው ።

ቴዎድሮስ ገና ከመንገሳቸው በፊት ደጃች ካሣ ይባሉ በነበ
ረበት ጊዜ የሮማ ካቶሊክ ሚስዮን የላካቸው ያዕቆብ(ጃኮቢስ)
በአገር ጉዳይ እየገቡ በብከትና ስለላ ስለጀመሩ ከኢትዮጵያ እን
ዲወጡ አዘዙዋቸው ። ያኔ የካሣ ግዛት ኢትዮጵያን በሙሉ አይጠ
ቃልልም ነበርና ካሣ ያባረሩዋቸው አቶ ያዕቆብ ወደ ትግራይ
ሔደው ከደጃች ውቤ ዘንድ ተቀመጡ ። ቴዎድሮስ ደጃች ውቤን
ድል አድርገው ከነገሡ በኋላ አባ ያዕቆብ ኢትዮጵያን ትተው ወጡ ።

አባ ያዕቆብ የደረሰባቸውን በደል እየጨማመሩ በቫቲካን [illegible]
የካቶሊክ ሊቀ ጳጳስ አመለከቱ ። [illegible] አንድ ዜጋችን ያለ [illegible]
ንያት ስለተፈረደ [illegible] ይታይልኝ ሲሉ ለኢጣሊያ መንግሥት

አመለከቱ ። የኢጣሊያ መንግሥትም በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል እያለ አለሁ አለሁ ለሚለው ለፈረንሳይ መንግሥት ጉዳዩን አመልክቶ ግብጽ አገር ባለው አምባሳደርና ምጽዋ በተቀመጠው የፈረንሳይ ቆንሲል አማካይነት ጉዳዩ እንዲ[illegible]ስ ጠየቀ ። በኢትዮጵያ እግራቸውን ለማስገባት ይመኙ የነበሩት ፈረንሳዮች ይህን ምክንያት በማግኘታቸው የቴዎድሮስን መንግሥት መቃወማቸውን በይፋ ገለፁ ።

አባ ያዕቆብ ቴዎድሮስን ለመጣል እነእከሌን [illegible] እያሉ የኢትዮጵያን መኳንንት ስም እየጠሩና ከቴዎድሮስ ጋር ያላቸውን ጥል እያጋነኑ ለፈረንሳይ መንግሥት ይጽፉ ጀመር ። [illegible] ቀርቶ ፌብሩዋሪ 24 ቀን 1856 ለሳልሳዊ ናፖሊዮን በጻፉት ደብዳቤ ከቴዎድሮስ በፊት በራስ አሊ ጊዜ የነበሩትን አጤ የ[illegible] እንደገና ወደ ዙፋናቸው ቢመለሱ በካቶሊክ ሃይማኖት ሊገቡ ቃል ገብተውልኛል እያሉ ጻፉ ። በዚህና በሌሎች ምክንያቶች ቴዎድሮስ የውጭ አገር ሰዎችን እየጠሉ የሚስዮናውያንንም [illegible]ት ከለከሉ ።

አጤ ቴዎድሮስ ሚስዮናውያንን በኢትዮጵያ ው[illegible] መንፈሳዊ ስብከት [illegible]ስብኩ የከለከሉት የካቶሊክ እም[illegible]ቶችን ሚስ[illegible] ብቻ አይደለም ። የፕሮቴስታንት እ[illegible]ችም [illegible] መንፈሳዊ ስብከት እንዳይሰብኩ ከልክለ[illegible] እንደ[illegible] አንድ ጊዜ በሌጀንና በባርዶል [illegible]ንደር ውስጥ [illegible] ተደርጎ ጉዳዩ በሚመረመርበት ጊዜ [illegible] ቴዎድሮስ [illegible] "... በሚገባ አውቃለሁ ።...የኤሮፓ [illegible]ሥታት አንድ [illegible] ለመያዝ ሲፈልጉ መጀመሪያ ሚስ[illegible] ይልካሉ ። [illegible]ም ሚስዮናውያኖቹን የሚያጠናክር [illegible] ይሸኛሉ ። [illegible] በኋላ ቆንሲሉን የሚጠብቅ [illegible] ጦር ወታደሮችን ይልካሉ ። እኔ እንደ ሒንዱስታን ራ[illegible] ሆኜ እንደዚያ እንዲደረግ የምፈቅድ አይደለሁም ።. . ." [illegible] ።

አጤ ቴዎድሮስ እንዳሉት ሁሉ ፈረንሳዮችም [illegible] እንግሊዞች ፣ ኢጣሊያኖችም ጭምር ስለሚስዮናውያኖቹ ኑሮ ጉዳይ የሚከራከሩበት በእርግጥ ለእግዚአብሔር መንግሥት የወንጌል ትምህርት እንዲስፋፋ ብለው አይደለም ። አብዛኛዎቹ ሚስዮናውያን አንድ አገር የሚገቡት ለወንጌል ስብከት ሥራ ሳይሆን የአገሩን [illegible] ፣ የመንግሥቱን ጥንካሬና ድክመት ለመሰለል [illegible] ነው ።



ውስጥ ምሥጢሩን ግን በወንጌል ልባስ ይሸፍኑታል ። ይህም ሁሉም እንዲህ ያደርጋሉ ማለት ሳይሆን እንዲያ የሚያደርጉ እንዳሉባቸውም ለማሳወቅ ነው ።

ለምሳሌ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የሆኑት ሉዊስ ክራፍ እና ሔንሪ እስተርን ለወንጌል ሥራ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው ኖረው ከወጡ በኋላ የጻፉዋቸውን መጽሐፍት ብንመለከት የኢትዮጵያ ብሔረሰብ የሚያደርገውን የርስ በርስ ግጭት ፣ በመንግሥት ላይ ያየሉትን ሽፍቶች ታሪክና ዝና ፣ የትኛው አገር ለምና የትኛው በረሃ ክፍል እንደሆነ ፣ በጠቅላላው አገሪቱን ቁልጭ አድርጐ የሚያሳይ ትረካ ነው የንጉሡን ወይም የየመኳንንቱን ደካማና ጠንካራ ጐን ሁሉ ይጠቅሳሉ ። ይህ እንግዲህ ከወንጌል ሥራ ወይም ትእዛዝ ጋር የማይገናኝ ነገር ነው ።

በተለይ እስተርን አጤ ቴዎድሮስን ለካራም ናቸው ፣ ሴሰኛ ናቸው ፣ የእንዲት ተራ የኮሶ ሻጭ ልጅ ናቸው እያለ በመስደብ የጻፈባቸው የትኛው ወንጌል ነው ሐሜታ እሙ ወይም ተሳደቡ የሚል ? ወደፊት እንደምናነበው አጤ ቴዎድሮስን ከመጠን በላይ ያናደዳቸውና ሚስዮናውያኖችን ያስጠላቸው አንዱም የእስተርን አጻጻፍ ነው ። እነኝህ ሰዎች ለወንጌል ሥራ ሳይሆን ለታሪክ ፀሐፊነት ገብተው እንደዚያ ያለ ቢጽፉ ባልተነቀፉ ነበር ። ወንጌልና ስድብ አብረው አይሄዱም ።

ወደ እንግሊዞች ብንመለስ ወደ ኢትዮጵያ እግራቸውን ለማስገባት ባሰቡበት ጊዜ መጠቀሚያ ወይም መንገድ ቀዳጅ አድርገው መጀመሪያ የላኩዋቸው የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያንን ነበር ። ይህን ያወቁት ቴዎድሮስም ሚስዮናውያኖቹ ከኢትዮጵያ እንዲወጡ አደረጉ ። ይህንንም የቴዎድሮስን ውሳኔ ለማስለወጥ የእንግሊዝ መንግሥት ቴዎድሮስ የሚወዱትን የጦር መሣሪያ ሊልክላቸው አሰበ ። ይህንንም ሐሳብ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አፕሪል 8 ቀን 1858 በተጻፈ ደብዳቤ ለፕላውዲን ገለፀለት ።

ፕላውዲን ይህ ደብዳቤ እንደደረሰው መልሱን ኖቬምበር 15 ቀን 1858 ጻፈ ። በጻፈውም መልስ ቴዎድሮስ ትግራይን እስኪይዙ ድረስ የሚላከው መሣሪያ ኤደን እንዲቀመጥ ፣ ቴዎድሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ሐሳብና ፍላጐት መሠረት እንዲሠሩ እንዲደረግ ፣ ፈቃደኛ ሆነው ተባብረው ባይሠሩ ግን "...የማብፁ ገዥ ባለው ኃይል ስነ ሥርዓት እንዲያስተምራቸውና ሥልጣኔ እንዲያሳያቸው ቢደረግ

ይሻላል. . .ይህም አዲስ ገና የተቋቋመው ሕፃን መንግሥት ማንኛ ውንም ኃይል መቋቋም የሚችል አይደለም ። ስለዚህ ግብጾች ቢመ ቱዋቸው ጉዳዩ ቀላል ይሆናል. . .'' ብሎ ነበር ።


ፕላውዴን እንዳመለከተው ቴዎድሮስ እየተደጋገሙ ቢጠየቁና ብዙ ማስፈራሪያ ቢቀርብላቸውም ኤሮፓውያንን የሚፈልጉዋቸው ሀገሪቱን በማልማት በኩል ብቻ መሆኑን እየገለፁ ያውም ቢሆን በእሳቸው ትእዛዝ መሠረት እንጂ ማንንም በበላይነትም በስብከትም እንደማይቀበሉ አስታወቁ ። ይህንንም የቴዎድሮስን ገታራነት ያየው ፕላውዴን ጉዳዩን እየዘረዘረ ወደ አገሩ አስታወቀ ። የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም ያሰበውን ለማድረግ እንዲያመቸው መጀ መሪያ ቆንሲሉን ማንሳት ስላለበት ጃንዋሪ 1860 ለፕላውዲን በጻ ፈው ደብዳቤ ፕላውዲን ከኢትዮጵያ እንዲወጣ አዘዘው ። ፕላውዲ ንም በታዘዘው መሠረት በሕመም እሳቦ ከኢትዮጵያ ለመውጣትና ወደ አገሩ ለመሔድ ጉዞ ሲጀምር በጋረድ አሽከሮች በጦር ተወግቶ ተያዘ ። ፕላውዲንም ከሞተ በኋላ ቴዎድሮስ ለንግስት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ ". . .እነ አቶ ቡላዲን ፣ እነ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ . . . የጠሉኝ ሰዎች እኔን ይከፋው ሲሉ ገደሉዋቸው ። እኔም በእግዚአብ ሔር ኃይል ደመኞቼን አንድ ሳልተው ፈጀኋቸው ። የገዛ ዘመዶቼን በእግዚአብሔር ኃይል የርስዎን ዝምድና ስፈልግ. . ." በሚሉ ቃላት ለጊዜው ይነሳ የነበረውን የእንግሊዝን ድንፋታ ገቱት ።

ቴዎድሮስን ከውጭ መንግሥት ጋር በማበር እጅግ ያበሳጩ ዋቸው የነበሩት የካቶሊክ ወይም የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ብቻ አልነበሩም ። የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ደግሞ አገርዎን ይልቀቁ በሚለው እሳብ ከሁሉ የበለጠ ያሳዝኑዋቸውና ያበሳጩዋቸው ነበር ። የፈረንሳይ መንግሥት ለደጃች ንጉሴ ዕርዳታ ሰጥቶ አገር ለመ ቀበል ከመስማማቱ በፊት ሌላ ውጥን ነበረው ። የአሌክሳንድርያው የኦርቶዶክስ ሊቀ ጳጳስ ወይም ፓትርያርክ የሆኑት አቡነ ቄርሎስ ወደ ሃይማኖት ልጆቻቸው ወደ ኢትዮጵያ ሔደው መሔድም ባይችሉ መልክተኛ ልከው የኢትዮጵያውን ግብጻዊ ጳጳስ አቡነ በላማንና ቴዎ ድሮስን መክረው የካቶሊክ ሚስዮናውያን በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ፈለጉ እንዲሰብኩ እንዲያስደርጉ ጠየቁ ። አቡነ ቄርሎስም እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 2 ቀን 1853 በተጻፈ ደብዳቤ አቡነ ሰላማ የካቶሊክ ሚስ ዮናውያንን እንዳይቃወሙ አዘዙዋቸው ። ይህም ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሚስዮናውያን ጥላቻ አልበርድ አለ ።

ይህን የአማላጅነት ምክንያት ያገኙት አቡነ ቄርሎስ እንደ ጁሌፔ ሁሉ እሳቸውም ለአገራቸው ለግብፅ ማሰብ ወይም ንጉሱን ማዘር



መሩ ። ቴዎድሮስ ከመንገሳቸው አንድ ዓመት ያህል ቀደም ብሎ ሐመድ ሰይድ ፓሻ የግብፅ ገዢ ሲሆን በሱዳን በኩል ያለው ኔታ ተለወጠ ። መሀመድ ሰይድ ፓሻ በሱዳን በኩል ከኢትዮጵያ ር ያለውን ወሰን አልፎ ሰናር ፣ በጐስ ፣ መንሳ ፣ ሐልመሐል ፣ ሐባ ብና ሌሎችም የግብፅ ግዛት ናቸው ብሎ አወጀ ። ይህንንም ለማስ ፀም በወሰን ላይ ከኢትዮጵያውያን ጋር ብዙ ጦርነቶች ተደርገው ኢትዮጵያውያን እያሸነፉ የግብፅን ጦር መልሰዋል ።



ግብጻዊው ፓሻ

ይህን የሚያውቁት የኦርቶዶክሱ ሊቀ ጳጳስ ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ በፈረንሳይ በኩል ለአማላጅነት ሲመረጡ ይህን የወሰን ጉዳይ በሰላም ለማስጨረስ መንገድ ለማዘጋጀት እንደሚሹ ለመሐመድ ሰይድ ፓሻ አመለከቱ ። ሰይድ ፓሻም ለፈረንሳይ አማላጅነት አስመስለው ይህን ጉዳይ ለማስፈጸም ወደ ኢትዮጵያ እንዲሔዱ ጠየቃቸው ። እሳቸውም ጥያቄውን በደስታ ተቀብለው በታህሳስ ወር 1849 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጡ ። ምናልባት የማያውቁ አንባቢዎች ቢኖሩ በዚያን ጊዜም ሆነ ከዚያን በፊት ለኢትዮጵያ ጳጳስ የሚመጣለት ከግብፅ አገር ግብፃዊ የሆነ ሰው በፓትርያርኩ እየተሾመ ነበር ። ስለዚህ የፓትርያርኩ የአቡነ ቄርሎስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ክበሬታ ነበረው ።

አቡነ ቄርሎስ እንደመጡ አጤ ቴዎድሮስና ሕዝቡ ታላቅ አቀባበል አደረጉላቸው ። ከአቀባበሉም ስነ ሥርዓት በኋላ አቡነ ቄርሎስ ከግብፁ ገዥ ከመሐመድ ሰይድ ፓሻ ለአጤ ቴዎድሮስ የተላከውን ደብዳቤ አቀረቡ ። የመጡበትም ምክንያት በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል የጠበቀ ወዳጅነት ለመመሥረት እንደሆነ በማስታወቃቸው ቴዎድሮስ በጣም ተደሰቱ ። ይህንንም የሁለቱን አገር ወዳጅነት ቴዎድሮስ በጣም እንደሚፈልጉት ገልፀው ለሰይድ ፓሻ የሚላከውን የወዳጅነት ደብዳቤ መልስ እንደሚፅፉ ገለፁላቸው ።

አቡነ ቄርሎስ ለሰይድ ፓሻ የሚላከውን የወዳጅነት ደብዳቤ ቀደም ብለን ታሪካቸውን ካነበብነው ከግብፃዊው የኢትዮጵያ ጳጳስ ጋራ ለማዘጋጀት ቢፈቅድላቸው ለማዘጋጀት ፈቃደኛ መሆናቸውን ለቴዎድሮስ ገለጡ ። አጤ ቴዎድሮስም ጉዳዩን በቅን ልቦና ተመልከተው በቴዎድሮስ ስም የሚላከውን ደብዳቤ እንዲያዘጋጁ ፈቀዱላቸው ።

በሁለቱ ጳጳሳት የተረቀቀው ደብዳቤ ለአጤ ቴዎድሮስ ቀረበ ። አጤ ቴዎድሮስም የደብዳቤውን ረቂቅ ቃሉን ሰምተው ጉዳዩን በጉባኤ ለማስፈቀድ መኳንንቱና ሕዝቡ እንዲሰበሰብ አዘዙ ። መኳንንቱና ሕዝቡ በተሰበሰበበት ጉባኤ ለሰይድ ፓሻ የተፃፈው ደብዳቤ ተነበበ ። ደብዳቤው ባጭሩ የሚለው ጥበበኞች እንዲላኩላቸው ፣ በሶስት የቱርክ መኮንኖች የሚመሩ የግብፅ ወታደሮች በኢትዮጵያ ገብተው የኢትዮጵያን ወታደር እንዲያሰለጥኑ ፣ በኢትዮጵያ ያሉት የእንግሊዝና የጀርመን ዜጎችም እንዲወጡ የሚልና ወሰኑንም በሰላም





አቡነ ቄርሎስ

በፓሻው አስተሳሰብ ለመጨረስ ፈቃደኛ መሆናቸውን የሚገልፅ ነበር ። ይህም አስተሳሰብ ኢትዮጵያ ባዶዋን ሆና ከውስጥ የቱርክና የግብፅ ወታደሮች ገብተው ማንኛውንም የኃይል ሥራ ለመሥራት እንዲችሉ የታሰበ ነበር ። አጤ ቴዎድሮስ ደብዳቤውን ካስነበቡ በኋላ ፓትርያርኩ በቃል የነገሩዋቸውን ጭምር ለተሰበሰበው ሕዝብ ነግረው "የእግዚአብሔርን መንገድ ማስተማር ትታችሁ ለገዢያችሁ ለሰይድ ፓሻ አሽከር ከሆናችሁ እኔም በአገሬ ገዢያችሁ ነኝና በመንገዴ አስራችኋለሁ" ብለው ፓትርያርኩንም ጳጳሱንም አብረው

አለፉዋቸው ። የዚያን ዘመን ኢትዮጵያውያን ታሪክ ፀሐፊዎች የቤተ ክህነት ሰዎች በመሆናቸው ክአቡነ ቄርሎስና ከአቡነ ሰላማ መታሰር ላይ ሲደርሱ የታሰሩበት ምክንያት ብዙ ነው እያሉ ያል ፉታል ። አንዳንዶችም ቴዎድሮስ ስለባዱ ነው ይላሉ ፡ ቴዎድሮስ ግን እንደዚያ የሚያደረጋቸው የአገር ፍቅር እንጂ እብደት አል ነበረም ።

ቅድም እንደተባለው ቱርኮች እስከ ባብ ኤልመንደብ ያለው የኢትዮጵያ የባህር ጠረፍ ለኛ ይገባል እያሉ በያለበት የኢትዮ ጵያን የባህር ጠረፍ ይዘዋል ። ግብጾች በሰሜናዊ ምዕራብ ያለው የኢትዮጵያ ግዛት ለኛ ይገባል እያሉ አደጋ በመጣልና በመያዝ ላይ ናቸው ። ሕዝቡንም በሃይማኖት ስብከት ገብተውታል ። ወሰን እያለፉም ይዘርፋሉ ፡ ቤት ያቃጥላሉ ። ቤትና ወንዱን እየማረኩ ባርያ ያደርጋሉ ። በቁርአን ትምህርት ያላመነውንም በሰይፍ ይቀጣሉ ። አጤ ቴዎድሮስ ይህን ሁሉ በመመልከትና ዙርያውን የከበቡት ጠላቶችም በመሣሪያ በኩል ከአቅም በላይ በመሆናቸው ክርስቲያኑን የእንግሊዝ መንግሥት እርዳታ ጠየቁ ።

የቴዎድሮስ የእርዳታ ጥያቄ የደረሰው የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ሎርድ ከላሬንዶን ግብጽ አገር ላለው የእንግሊዝ አምባሳደር ደብዳቤ ጻፉ ። ጁን 30 ቀን 1854 የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለግብፁ አምባሳደር በጻፉት ደብዳቤ “. . . ለፓሻው አጥብቀህ የምትነግረው . . በማንኛውም ነገር ቢሆን በወደብም ሆነ በማንኛውም የአበሻ ወሰን እንዳይደርሱ ። የግርማዊት ንግሥት መንግሥት በዚያ አገር ያሉትን ክርስቲያ ኖች ለመጠበቅና [illegible] ይጻደዳል ። ስለዚህ [illegible] ጉራባች ያሉት [illegible] ተግባር እንዲታገሡ እድርግ . . . ” [illegible]

[illegible] ይህ በዚህ [illegible] ሚኒስትር ሆና [illegible] ተብሎ ነው ። [illegible]



ድ ውቅያኖስ ላይ የበላይነቱን ቦታ ይዛ ቅቆጣጠር ጀመር ። ያኔ ስዊዝካናል ስላልተከፈተ ዋናው የመርከቦች መንገድ ሕንድ ውቅ ያኖስ ነበር ። አፍሪካን ከሚከቡ ውሃዎች ከሚዋሰኑት አገሮች አን ዲቱ ኢትዮጵያ ስለሆነች የእንግሊዝ መንግሥት መልክተኞችን ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት በመላክ ወዳጅነት መሥርቶ ቀይ ባህ ርን ይቆጣጠር ነበር ።

በቴዎድሮስም ጊዜ እንግሊዞች ይሄው በቀይ ባህር ላይ ያላቸ ውን የበላይነት ሌላ መንግሥት ገብቶ እንዳያደናቅፋቸው በማሰብ ከአዲሱ የቴዎድሮስ መንግሥት ጋር ወዳጅነታቸውን ለመቀጠል ፈለጉ ። በራስ አሊ የምስፍንና ዘመን በአበሻ አገር ቆንሲል ተብሎ ተሹሞ የነበረውን ፕላውዴንን በቆንሲልነት ቴዎድሮስ እንዲቀ በሉት አደረጉ ። ፕላውዴን ከሞተ በኋላ እንግሊዞች የባህር ጥበቃ ቸውን ለማጠናከርና ኢትዮጵያ ከሌላ ከእንግሊዝ ተቀናቃኝ መን ግሥት በተለይም ከፈረንሳይ ጋር ተወዳጅታ የበላይነቱን እንዳያጡ ያኔ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት በነበረችው በሕንድ አገር ይሠራ የነበ ረውን ካፕቴን ቻርልስ ዱንካን ካሜሮንን የኢትዮጵያ ቆንሲል ብለው ሾሙት ።

ካሜሮን በ1852 ዓ.ም. ጐንደር ገባ ። ካሜሮን በመጣበት ጊዜ ቴዎድሮስ ደጃች ተድላ ጓሉን ለመውጋት እየፈለጉዋ ቸው ይዟዟሩ ስለነበር ጐንደር አልነበሩም ። ካሜሮንም ቴዎድሮስ እስቲመለሱ ድረስ ክረምቱን ጐንደር ላይ አሳለፈው ቴዎድሮስ ጐንደር በተመለሱ ጊዜ ታላቅ የክብር አቀባበል አደረጉለት ። ካሜሮንም ከእንግሊዝ መንግሥት የተላኩ ናቸው በማለት አንድ ጠመንጃና ሁለት እጀታቸው ብር የሆኑ ሽጉጦችን በስጦታ አቀ ረበ ። “ ለአበሻው ንጉሥ ለቴዎድሮስ ከእንግሊዝና ከአይርላንድ ንግሥት ለአሽከርዋ ለፕላውዴን ለተደረገለት ቸርነት የተሰጠ ። 1861 ” የሚል የእንግሊዝኛ ጽሑፍ ያለበት ሥጦታም ሰጠ ።

አጤ ቴዎድሮስ በተላከላቸው ስጦታና በተለይ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የጠበቀ ወዳጅነት በመመሥረቱ ተደሰቱው [illegible] ከተኞቻቸውን በቅርቡ ወደ እንግሊዝ አገር ልከው [illegible] ምኞትና አሳብ ለእንግሊዝ ንግሥት እንዲሚያሰሙ ተናገሩ ። ከካሜሮንም ጋር ፈረንሳዊው ባርዴል [illegible] ነበርና ቴዎድ ሮስ ከፈረንሳይ መንግሥትም ጋር [illegible] ለመመ ሥረት ፍላጐቱ እንዳላቸው ተናገሩ ። [illegible] ንግ

ሥት መልክተኞች እልካለሁ በማለታቸው ካሜሮን ተገረመ ። " አንድ የአፍሪካ ትንሽ ንጉሥ እንዴት ዓለምን ከምታስተዳድር ከእንግሊዝ ንግሥት ጋር መልክተኛ ልኮ ለመነጋገር ያስባል ? " በማለት ተገርሞ ጉዳዩን ናቀው ።

በራስ አሊ የምስፍንና ዘመን ፕላውዴን በእንግሊዝ መንግሥት ስም ሆኖ የተዋዋለውን ውል እንደገና እናድስው ብሎ ካሜሮን አጤ ቴዎድሮስን ጠየቀ ። አጤ ቴዎድሮስም "ቆይ ላስብበት " አሉት ። ካሜሮን ግን በየቀኑ እየደጋገመ በመጠየቅ ውትወታ ስላበዛ አጤ ቴዎድሮስ አንድ ቀን ቀቆጥተው " ቆይ ስልህ ቆይ ። እኔ ቴዎድሮስ እንጂ አሊ አይደለሁም ። ስለመንግሥቴም ላስብበት " ብለው ቁርጡን ስለነገሩት ካሜሮን የመጣበት ቁም ነገር እንዳይባለሽበት ቁጣና ኩራቱን ትቶ ወደ መለማመጡ አዘነበለ ።

ፕላውዴን በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል በነበረ ጊዜ በአገሩ መንግሥት ስም ከራስ አሊ ጋር ያደረገው ውል የኢትዮጵያና የእንግሊዝ መንግሥታት በወዳጅነት በንግድ ልውውጥና የሁለቱም አገር ዜጎች አንዱ በሌላው አገር ውስጥ እንደፈለገው የመዘዋወርን ነፃነት የሚሰጥ ነበር ። ይህም ውል ከ1841 እስከ 1847 ወይም እ.ኤ.አ. ከ1849 እስከ 1855 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ ነበር ።

ውሉ የሁለቱን መንግሥታት ወዳጅነትና የንግዱ ልውውጥ የሚጠቅም ቢሆንም የአንዱ አገር ዜጋ በሌላው አገር እንደፈለገው የመዘዋወር መብት መስጠቱ ግን ጥቅሙ ለእንግሊዞች ብቻ እንጂ በዚያን ዘመን ለነበሩ ኢትዮጵያውያን እንግሊዝ አገር ውስጥ ገብተው እንደፈለጉ ሊዘዋወሩ አይችሉም ። እንደዚያ ለማድረግ እውቀቱም ገንዘቡም የላቸውም ። እንግሊዞች ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው ሊዘዋወሩ ይችላሉ ። ገንዘብም እውቀትም ያላቸው ናቸው ። ከዚህም ሌላ በስለላ ወይም እርስ በርስ ለማጋጨት ተግባር ሊገቡ ይችላሉ ። እንግሊዞች አብዛኛዎቹን ቅኝ ግዛቶቻቸውን የያዙትም በዚሁ ዓይነት ዘዴ ነበር ።

አጤ ቴዎድሮስ በራስ አሊ ዘመን ምስፍና የነበረውን ውል ላጥናው እያሉ ያቆዩት ከላይ በተተነተነው አኳኋን መሆን ያለመሆኑ አይታወቅም ። በኔ አስተያየት ግን ካሜሮን ውሉን እናድስ እናድስ በሚልበት ጊዜ ባርዴል ደግሞ የጦር መሣሪያ ነጋዴ ነበርና አጤ ቴዎድሮስ ዘንድ እየቀረበ ለራሱ ንግድ እንዲያመቸው ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር ቢወዳጁ የጦር መሣሪያ የሚፈልጉትን ያህል መግዛት ይችላሉ እያለ ይነግራቸው ስለነበር አጤ ቴዎድሮስ የሁለቱንም መንግሥት ወዳጅነት ለመፈለግ አስበው ይሆናል ። ባርዴል አጤ ቴዎድሮስን ምን ያህል ይጨቀጭቃቸው እንደነበረ ወዳገሩ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ገልጾታል ። ባርዴል የታወቀ የጦር መሣሪያ ነጋዴ ቢሆንም በውጭ ግን ሊያስወራ ራሱን የካሜሮን ረዳት አድርጎ ነበር ።

ሌላውም ምክንያት ካሜሮን ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ሶስት ወር ያህል ከቆየ በኋላ ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሩሴል ዘንድ ፌብሩዋሪ 22 ቀን 1862 ዓ. ም. የተጻፈ ደብዳቤ መጣለት ለቴዎድሮስም በተጻፈው የሰላምታ ደብዳቤ ላይ አድራሻው " ለክቡር ቴዎድሮስ " የሚል ስለነበር ምናልባትም ቴዎድሮስ የእንግሊዝ ንግሥት ንጉሥነታቸውን አውቀው " ንጉሥ ቴዎድሮስ " እያሉ ሲጽፉ አንድ የበታች ሚኒስትር " ለክቡር " ብሎ በመጻፉ ቴዎድሮስ ቂም በመያዛቸው ሊሆን ይችላል ።

አጤ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ንግሥትና ለፈረንሳዊው ሳልሳዊ ንጉሥ ለቻርልስ ሎዊስ ናፖሊዮን ቦናፓርት የወዳጅነትና የእርዳታ መጠየቂያ ደብዳቤ ጽፈው ካሜሮን ወደ እንግሊዝ አገር ፡ ባርዴልን ደግሞ ወደ ፈረንሳይ አገር ላኩዋቸው ። አጤ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ንግሥት የጻፉት ደብዳቤ ፣ ዘመኑን የአጻጻፍ ስልት ለማሳየት ከእንግሊዝኛው ትርጉም ጋር የሚከተለው ነው ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ
በንድነት ፡ በሶስትነት ፡ እግዚአብሔር ፡ መርጦ ፡ ያነ
ገሰው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘኢትዮጵ
ያ ፡ ይድረስ ፡፡ ከዕንግሊዝ ንግሥት ፡ ቢክቶሪያ ፡፡
እንዴት ፡ አሉ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደኅ
ና ፡ ነኝ ፡፡ አስተ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አባቶቼ ፡ ነገሥታት ፡ ፈጣሪ
ለችነን ፡ ቢበድሉት ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለጋሎች ፡ ለቱር
ክ ፡ አሣልፎ ፡ ሰጥቶባቸው ፡ ነበረ ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ከተወ
ለድሁ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ካሠድ ፡ አንስቶ ፡ ኃይል ፡ ሰጥቶ ፡ ባባ
ቶቹ ፡ መንግሥት ፡ አቆመኝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል
፡ ጋሎችን ፡ አስለቀቅኋቸው ፡ ቱርኮች ፡ ግን ፡ ያባቴን ፡

መሬት፡ ለቀቁ፡ ብላቸው፡ እምቢ፡ ብለዉኝ፡ በእግዚ
አብሔር፡ ኃይል፡ ይኸው፡ ልታገል፡ ነኝ፡፡ እነአቶ፡ ቡ
ላጂን፡ እነሊቀመኳስ፡ ዮሐንስ፡ የክርስቲያን፡ ንጉሥ
ታላቅ፡ ሰው፡ ክርስቲያን፡ የሚወዱ፡ ለሉ፡ እናስተዋ
ውቀህ፡ አለን፡ እያሉኝ፡ እጅግ፡ አወዳቸው፡ ነበረ፡ የር
ስዎን፡ ወዳጅነት፡ ያገኘሁ፡ እየመሰለኝ፡፡ ሞት፡ አይቀ
ርምና፡ የጠሉኝ፡ ሰዎች፡ እነኝ፡ ይክፉው፡ ሲሉ፡ ገደሉ
አቸው፡ እኔም፡ በእግዚአብሔር፡ ኃይል፡ ደመኞቸን፡
፩ ሳልተው፡ ፈጀኋቸው፡ የገዛ፡ ዘመዶቸን፡፡ በእግዚ
አብሔር፡ ኃይል፡ የርስዎን፡ ዝምድና፡ ሥፈልግ፡
ቱርኮች፡ ከባህር፡ ላይ፡ ሁነው፡ መልክተኛየን፡ አናሳል
ፍም፡ ብለው፡ ቸግሮኝ፡ ሳለ፡ ቈንስል፡ ኪምሮን፡
መጣልኝ፡ ወረቀትና፡ የፍቅር፡ በረከት፡ ይዞ፤
በእግዚአብሔር፡ ኃይል፡ እጅግ፡ ደስ፡ አለኝ፡
ደህንነትዎንና፡ ፍቅርዎን፡ ብሰማ፡፡ የሠደ
ዱልኝንም፡ የፍቅር፡ በረከት፡ ተቀበልሁ፡ እግ
ዚአብሔር፡ ይሥጥልኝ፡፡ አሁንም፡ መልክተኛ
የን፡ ከቈንስል፡ ኪሜሮን፡ ጋራ፡ የፍቅር፡ በረከት
ይዞ፡ እንዳልሰደው፡ ቱርኮች፡ በባህር፡ ላይ፡ የማ
ያስተላልፉልኝ፡ ሆነ፡ አሁንም፡ እንዲህ፡ ሠለ፡ ሰፍ
ራ፡ እከሌ፡ ይቀበለው፡ ብለው፡ ይላኩልኝ፡፡ ም
ላሹን፡ ቈንስል፡ ኪሜሮን፡ ይዞልኝ፡ ይምጣ፡፡

እናንተም፡ ተገፉልኝ፡ ክርስቲያኖን፡ እስላም፡ አጠቃህ
ኢ ለኝ፡፡ ተጻፈ፡ ብ፳፱፡ ተ፲፰፻፶፭ ዘመን፡ በሉቃስ፡ በወርኃ፡ ጥቅምት
፡ በ፳፱ ቀን፡ ጐጃም፡ በደባባ፡ ከተማ፡፡

አጤ ቴዎድሮስ ይህን ደብዳቤ ለካሜሮን ሰጥተው እሱም ለእንግሊዝ መንግሥት አቅርቦ ከዚያ የሚያገኘውን መልስ ይዞላቸው እንዲመጣ አዘዙት ። በፈረንሳዩ ንጉስ ለ፫ኛ ቻርለስ ሎዊስ ናፖሊዮን ቦናፓርትም ተመሳሳይ የሆነ ደብዳቤ ጽፈው ባርዴል እንዲያ



ደርስና መልሱን ይዞ እንዲመጣ ላኩ ። ሁለቱንም በሚልኩበት ጊዜ ለሁለቱም ለመንገዳቸው ስንቅ የሚሆን ገንዘብ ሰጥተው ነው ።

ባርዴል ምጽዋ ሲደርስ በመርከብ ተሳፍሮ በግብጽ በኩል አድርጐ ወደ ፈረንሳይ ሔደ ። ካሜሮን ምጽዋ ሲደርስ ደብዳቤ ስለያዘ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲመጣ እንዲፈቀድለት የአገሩን መንግሥት ቢጠይቅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎች አንድ ትንሽ መንግሥት የታላቁን የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ለመላክ በማሰቡ ተገርመውና ስድብ ነው ብለው ካሜሮን ደብዳቤውን እንዲልክላቸውና እሱ ግን ወደ ሱዳን ግዛት ሔዶ በዚያ ያለውን የጥጥ አዝመራ እንዲያይና የባርያ ገበያውን ሁኔታ እንዲያጠና ትእዛዝ ደረሰው ። የጥጥ አዝመራውን እንዲያይ የታዘዘበት ምክንያት እንግሊዝ ጥጥ የምትገዛው ከአሜሪካ ነበርና በዚያን ጊዜ በአሜሪካ አገር በተነሳው የርስ በርስ ጦርነት ምክንያት የጥጥ ገበያ በመቋረጡ ጥጥ ተወዶ ስለነበረ ነው ።

ካሜሩን እንደታዘዘው ደብዳቤውን ወደ እንግሊዝ አገር ልኮ ቦጐስ ፣ መንሳ ፣ ከረንና ወደሌሎችም ቦታዎች ሊጐበኝ ሔደ ። ቴዎድሮስ በባርያ ገበያ ላይ ባላቸው የከልከላ አመራር ምክንያት በሱዳን ውስጥ በግብጽ የሚቃወሙዋቸው ባርያ ፈንጋዮች ነበሩና ካሜሮን ከእነሱም ጋር ተገናኝቶ ተነጋገረ ። ቴዎድሮስ የካሜሮንን ሂደት ይከታተላሉ ። አብሮህ ይሂድ ያሉትን ፀሀፊያቸውን አቶ ሣሙኤልን ምጽዋ ላይ እንዲቀር አድርጐ እሱ ወደ ሱዳን መሔዱን ሰምተዋል ። ሱዳን ውስጥ ገብቶ ከጠላቶቻቸው ከባርያ ፈንጋዮችና ከሌሎቹም ሹማምንቶች ጋር ተገናኝቶ መነጋገሩ ወሬው ደርሷቸዋል ። “. . . ወዳጅ ነኝ ብሎ እንዴት ወደ ጠላቶቼ ይሔዳል ? ” እያሉም አጠገባቸው ላሉት መኳንንቶችና ፈረንጆች ያወራሉ ። በፈረንጆች ላይም ያላቸው እምነት በቋፍ ሆነ ።

ካሜሩን አጤ ቴዎድሮስ ለላኩት ደብዳቤ የሚመጣውን መልስ ሲጠብቅ ቆየ ። የደብዳቤው መልስ ግን አልመጣለትም ። የደብዳቤው መልስ በመዘግየቱና በሱዳን አገርም የወባ በሽታ መነሻው ጊዜ ስለተቃረበ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ ። የደብዳቤው መልስ ያልመጣለት ምክንያት የእንግሊዝ መንግሥት ደብዳቤውን በመናቅና በተለይ አንድ ትንሽ መንግሥት የእንግሊዝን ቆንሲል እንደ አሽከሩ በመላኩ ተናደው ስለነበር ክብራቸውን ለመግለጽ ሲሉ መልሱ እንዳይጻፍ ወሰኑ ። ንግስቲቱ ቪክቶሪያ ግን ለደብዳቤው መልስ እንዲሰጥ ፈልገው ነበር ። ምክር ቤቱ ባለመስማማቱ ቀረ ።

ካሜሩን ከአጤ ቴዎድሮስ ሲገናኝ የደብዳቤ መልስ ያስመጣቱን ተናገረ ። አጤ ቴዎድሮስም ተበሳጩ ። መበሳጨታቸውን ያየው ካሜሮንም "ጃንሆይ ። እስከ ሁለት ወር ድረስ የደብዳቤዎ መልስ ይመጣል ። ባይመጣ ግን አንገቴን እሰጣለሁ ( I WILL GIVE MY HEAD) አላቸው ። ቴዎድሮስም እሺ ብለው ሲጠብቁ የደብዳቤው መልስ ሳይመጣ የቀጠሮው ጊዜ ሁለት ወር አለፈ ። ከዚህ በኋላ በቴዎድሮስና በኤሮፓውያን መሀል የመጀመሪያ ጠብ ( ያስመጣባባት ) ተፈጠረ ።

ሁኔታው በዚህ ላይ እንዳለ ፈረንሳዊው ሙሴ ጉላሜ ሌዠን የፈረንሳይ መንግሥት መልክተኛ ነኝ ብሎ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የንግድ ሁኔታ ሊያጠና መጣ ። ቴዎድሮስም ሌዠንን በክብርና በደስታ ተቀበሉት ። ሌዠንም ለቴዎድሮስ ያመጣውን ስጦታ አቅርቦ ሲጨዋወቱ ቴዎድሮስ "... በዓለም ላይ ካለው ስጦታ ሁሉ ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር መወዳጀቱ የበለጠ ነገር ነው.." አሉ ሌዠን ስለመጣበት ጉዳይ ከቴዎድሮስ ጋር ተነጋግሮ ካበቃ በኋላ "ከዚህ ከኔ አገር ከኔ ጋር ትቆያለህ ወይስ ፈጥነህ ትሔዳለህ ?" ብለው ጠየቁት ።

ሌዠንም "ጃንሆይ ከተፈቀደልኝ መቆየት እፈልጋለሁ ብሎ መለሰ ።

"ጥሩ ብለሃል" አሉ ቴዎድሮስ "የአገርህን ሰው ወዳጄን ሙሴ ባርደልን ወዳገሬህ መንግሥት ስወዳጅነት ነገር ስለላክሁት እሱ እስኪመለስ ድረስ መቆየት አለብህ" አሉት ። ሌዠንም ይህን የቴዎድሮስን መልስ በደስታ ተቀበለው ።

ሶስት ሳምንታት ከቆየ በኋላ የቴዎድሮስ ዓይነውሃ አላምር ያለው ሌዠን ከቴዎድሮስ ዘንድ ቀርቦ ወደ አገሬ ለመመለስ እፈልጋለሁና ይፍቀዱልኝ ብሎ ጠየቃቸው ። ቴዎድሮስም "ሙሴ ባርደል እስኪመለስ ድረስ ቆይ ብየሃለሁና ቆይ" አሉት ። ሌዠንም "ጃንሆይ ። ባርደል የማይረባ ቀጣፊ ሰው ነው ። እሱ ወደዚህ አገር አይመለስምና ለኔ ፈቅደውልኝ ልሒድ" አላቸው ። ንጉሱም "ቀጣፊው ግን እንደሆነ ለማረጋገጥ ይበጀኛልና ባርደል እስኪመለስ ድረስ ከዚሁ ቆይ ። አትሔድም" አሉት ።

ሌዠን የመቆየቱ ጉዳይ አስግቶት ወደ አገሩ ለመሔድ እንዲፈቀዱለት ክርክር ሊጀምር ሲል ቴዎድሮስ አቋርጠውት "...ያገሬህ መንግሥት ለፍቅርና ለወዳጅነት ነገር ልኮህ እንደሆነ በኬን



ዘለንና በልጆቼ* ፊት ነግሬሃለሁ ። ባርደል እስኪመለስ ድረስ አርፈህ ተቀመጥ ። ለጭቅጭቅ ፡ ለድብድብ መጥተህ እንደሆን ንገረኝ ። እሰማሃለሁ ።' ብለው ሲቆጡት ሌዠን ደንግጦ አንገቱን አቀርቅሮዝም አለ ።

ሙሴ ባርደል በመስከረም ወር 1856 ዓ.ም. ተመልሶ መጣ ። ባርዴል ሲመጣ ቴዎድሮስ ለፈረንሳዩ ንጉሥ ሳልሳዊ ናፖሊዮን ቻርልስ ቦናፓርት ለጻፉት ደብዳቤ ከፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሙሴ ድሩይን የተጻፈውን የምላሽ ደብዳቤ ይዞ መጣ ። የመጣው መልስ ቴዎድሮስን አላስደሰታቸውም ።

የመጣው የደብዳቤ መልስ ባጭሩ የሚለው 1ኛ. የፈረንሳይ መንግሥት በዓለም ያሉትን ካቶሊካውያንን ሁሉ የመጠበቅ ኃላፊነት ስላለበት የእነሱን መልካም ሁኔታ ከመስማት የበለጠ የሚያስደስተው ነገር ያለመኖሩን ይገልፅና ፪ኛ ቴዎድሮስ በመጥፎ አማካሪዎች ምክር እየተገፋፉ ምንም በማያገባቸው ጉዳይ ከጎረቤቶቻቸው ኃይለኛ መንግሥት ጋር ጦርነት መጀመራቸው የማያዋጣቸው መጥፎ ነገር መሆኑን የሚገልፅ ነበር ። ይህ ደብዳቤ እንኳን በዚያን ዘመን በወቅታዊው ሁኔታ ላይ ላሉት ቴዎድሮስ ይቅርና በሐሳብ ወደዚያ ዘመን ለምንሔደው ሰዎች እንኳ የፈረንሳይ መንግሥት አመላለስ የሚያናድድ ነው ። ቴዎድሮስ የጠየቁት ስለአገር እድገት ጉዳይ እንጂ ስለሃይማኖት የቱ ይሻላል የሚል ጥያቄ አልነበረም ። ለካቶሊክ የክርስቲያን ሃይማኖት ጋሻ ሆኜ የቆምኩ ነኝ የሚለው የፈረንሳይ መንግሥት እስላም በላጠቃኝ የመሣሪያ እርዳታ ስጡኝ ላሉት ለቴዎድሮስ ምን አግብቶዎት ይናጋሉ ፡ ያገርዎንም ወሰን አርፈው ይልቀቁ የሚል መልስ መስጠቱ የሚያሳዝን ነው ።

ቴዎድሮስም ቢሆኑ የዋዛ ሰው አልነበሩም ። ከፈረንሳይ መንግሥት የተላከው ደብዳቤ ኤሮፓውያኖቹ በሙሉ ባሉበት ሜዳ ላይ ጉባኤ ተደርጐ ከተነበበ በኋላ "ይህን የወዳጅነት መልስ ነው ብዬ አልቀበለውም ። የፈረንሳይ መንግሥት ለጻፍኩለት ደብዳቤ ምላሽ እንዳልሰጠ አድርጌ እቆጥረዋለሁ" ብለው ደብዳቤውን ከመሬት ላይ ጣሉትና ከላዩ ላይ ቆመው እየረጋገጡ በእግራቸው አሽተው መቅደዳቸውን ሩቤንሰን ጽፎታል ። ደብዳቤውን በእግራቸው

* ልጆቼ የሚሉት በጋፋት ያሉትን ሚስዮናውያን ፈረንጆችን ነው ።

አሻሽተው ሰላዩ እንደቆሙም ከፈረንሳይ ጋር ሲያደርጉት የወጠኑት ወዳጅነት መቅረቱን ገልፀው የጎንደሩን ጉባኤ በተኑ ።

የባርዴልን መመለስ በናፍቆት ፣ ይጠባበቅ የነበረው ሌዣን ከቴዎድሮስ ዘንድ በሌላ ቀን ቀርቦ ወዳገሩ ለመመለስ እንዲፈቅዱለት ጠየቀ አጤ ቴዎድሮስም "ባርዴል አይመጣም ፣ ውሸታም ሰው ነው ብለኸኝ ነበረ ። አሁን እሱ ስለመጣ ውሸታምና ቀጣፊው አንተ መሆንህን አወቅሁ ። በአገሬ ደግሞ ብዙ ውሸታሞች ስላሉ እነሱ ይበቁኛልና አንተ ካገሬ ውጣልኝ " ብለው ወቅሰው ወደ አገሩ እንዲሔድ ፈቀዱለት ። ሌዣንም ከኢትዮጵያ ወሰን ሲደርስ ከንጉሱ እጅ ማምለጡን ስላወቀ መጥፎ የስድብ ደብዳቤ ፅፎ ለቴዎድሮስ ላከላቸው ። ይህም የስድብ ደብዳቤ ቴዎድሮስ በኤሮፓውያን ላይ የነበራቸውን ጥላቻ እያባባሰው ሔደ ።

ቴዎድሮስ ኤሮፓውያኖችን እንዲጠሉ ያደረጋቸው እነኝህ ምክንያቶች ብቻ አይደሉም ። የዶክተር እስተርንና የአቶ ሮዚንታልም ጉዳይ አለበት ። ሮዚንታል ለወንድሙ በጻፈው ደብዳቤ "ኢትዮጵያውያን በራሳቸው ጨካኝ ንጉሥ ከሚገዙ ይልቅ በባዕድ በግብጾች ቢገዙ ይሻላል " የሚል አስተያየቱን ጽፎለት ደብዳቤው ተያዘ። ደብዳቤውንም አቶ ሣሙኤል ጊዮርጊስና አቶ ብሩ ጴጥሮስ ለቴዎድሮስ ተርጉመው ስድባቸውን አሰሙዋቸው ።

ሚስዮናዊው እስተርን በሃይማኖት ስብከት ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ጎንደር አጠገብ ካሉት ፈላሻዎች ዘንድ ከርሞ አገሩ ሲመለስ ዎንደሪንግ አሞንግ ዘ ፈላሻስ ኦፍ አቢሲኒያ በሚል ርእስ አንድ መጽሐፍ አሳተመ ። በመጽሐፉ ውስጥ ባለፈው ገጽ እንዳልኩት ቴዎድሮስን የሚሰድቡ ቃላት አሉበት ።

እስተርን ይህን መጽሐፉን ካሳተመ በኋላ እንደገና ተመልሶ ወደ ኢትዮጵያ መጣ ። በሰላም በመኖር ላይ እያለ ካሽከሮቹ ጋር በተፈጠረው ያለመግባባት ተከሶ ከአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ ቀረበ ። በዚያም በሙግት ላይ እንዳሉ እንደ ዎልድሜየር አጻጻፍ በንዴት በንጉሱ ፊት አሽከሮቹን ስለተማታ ንጉሱን ደፈረ ተብሎ እንዲታሠር ተደረገ ። በታሠረ በማግስቱ ሙሴ ባርዴልን አስጠርቶ "ዎንደሪንግ አሞንግ ዘ ፈላሻስ ኦፍ አቢሲኒያ የተባለው መጽሐፌ ከሣጥኔ ውስጥ ስላለ አባክህ አምጣልኝ ። ይህ መጽሐፍ በመኖሩ የተገኘብኝ እንደሆን ብዬ ፈርቻለሁ ። ምናልባት በንጉሱ የተገኘብኝ



እንደሆነ ንጉሱን የማያስደስት ነገር አለበት ብሎ አሜወተውና ሰውሮ እንዲያመጣለት ለመነው ።

ባርዴል በተለመነው መሠረት መጽሐፉን ከደራሲው ከእስተርን ሣጥን ውስጥ አውጥቶ እንደተጠየቀው ለእስተርን በመስጠት ፈንታ እያነበበ ንጉሱን ቴዎድሮስን የሚነካውን ክፍል ይተረጉም ጀመረ ። ሲጨርስም ያን የተረጐመውን ስድብ ከነመጽሐፉ ለአጤ ቴዎድሮስ አቀረበው ። አጤ ቴዎድሮስ ስድባቸውን ሲሰሙ እንደገና በባሰ ሁኔታ ተበሳጩ ። በፈረንጆች ላይ ያላቸውም ጥላቻ በዛ ። የእስተርን አጻጻፍም ባጭሩ ቴዎድሮስ የኮሶ ሻጭ ልጅ እንጂ የነገሥታት ዘር የሌላቸው መጥፎ ሽካካ ፣ እንደ ዱር አውሬ ደም የጠማቸው መሆናቸውንና ሌላ ሌላ ሁሉ የሚገልፅ ነበር ።



አጤ ቴዎድሮስ በእስተርን ላይ ሽጉጥ ደግነው

ይህ የእስተርን የስድብ ጽሑፍ ከደረሳቸው በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ጉዳዩ በችሎት እንዲታይ ወሰኑ ። በችሎቱ እለት በሺ የሚቆጠሩ ተመልካቾችና በኢትዮጵያ ያሉ ፈረንጆች ሁሉ ቀረቡ ። አጤ ቴዎድሮስም ችሎቱ ላይ "....እናንት የኤሮፓ ሰዎች ወደ አገሬ

ሲትመጡ አፍቅሬ ፡ አክብሬ ፡ እቀበላችኋለሁ ። አኖራችኋለሁም ። ይህንንም የማደርገው የኤሮፓ ሰዎች ሁሉ እንደምወደው እንደ ዮሐንስ ቤል እየመሰለኝ ነው ። እሱ እውነት ተናጋሪ ነበር ። እናንተ ግን ውሸታሞች ፡ ቀጣፊዎች ናችሁ ። መልክም ሳደርግላችሁ እናንተ ግን በመጥፎ መለሳችሁልኝ ። ወደ አገራችሁ በምታስተላልፉት ነገር ሁሉ እኔን የሚያጥላላ ነገር ትናገራላችሁ ። ትጽፋላችሁም ። በዓለም ላይ መጥፎ ስም አሰጣችሁኝ ። በእኔና በእናንተ መሀልም እግዚአብሔር ፍርዱን ይስጥ'' ብለው ችሎቱን አስጀመሩ ።

ችሎቱ የተሰበሰበው ጐንደር ከተማ ውስጥ ከሰፊ ሜዳ ላይ ነበር ። ወዲያው ክርክሩ ከተሰማ በኋላ ሊቃውንቶቹ ፍትሐ ነገሥቱ ምን እንደሚል እንዲያነቡ ተጠየቀ ። ፍትሐ ነገሥቱ ከተነበበ በኋላ ችሎቱ በአንድ ድምፅ አቶ እስተርንና አቶ ሮዜንታል በስቅላት እንዲቀጡ ፈረደ ። ወዲያውም የመስቀያው እንጨት ተሰቃዮቹ እየተመለከቱ ይዘጋጅ ጀመር ።

አጤ ቴዎድሮስ የሚወዱትና የሚያከብሩት ሚስዮናዊው አቶ ፃልድሜየር በኀዘንና በትካዜ ወደ ንጉሡ ዘንድ ቀርቦ ተንበርክኮ እያለቀሰ ምሕረት እንዲደረግላቸው ንጉሡን ለመነ ። ቴዎድሮስም የፃልድሜየርን እጅ ይዘው ከተንበረከከበት አስነሱትና ''አይዞህ አትፍራ ወዳጄ ። ላንተና ለዮሐንስ ቤል ስል አልገድላቸውም ።. . . አንተ ወዳጄ ነህ ። ይህቺን ጣቴን እንኳን ቆርጠህ ስጠኝ ብትለኝ እሰጥሃለሁ ። ምክንያቱም እውነተኛ ሰው ነህና እወድሃለሁ ።'' አሉት ።

ከዚህ በኋላ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ሰዎች ፍርዱ በእስራት ተለውጦላቸው አቶ እስተርንና አቶ ሮዜንታል ወዲያውኑ በእግር ብረት ታሠሩ ። ቴዎድሮስ በኤሮፓውያን ላይ የነበራቸው ፍቅርና አክብሮት ተሟጦ ስለነበረ ቂም የያዙባቸውን ፈረንጆች ሁሉ እንዲታሠሩ አደረጉ ። ማርቲን ፍላድ ፣ እስቲገር እና ብራንዲስ ወዲያውኑ በሰንሰለት ታሠሩ ።

ጥቂት ቀደም ብለን እንዳነበብነው ቴዎድሮስ የጐንደሩን ችሎት ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር ''ወደ አገራችሁ በምታስተላልፉት ነገር ሁሉ እኔን የሚያጥላላ ነገር ትናገራለች ።. . .'' ያሉት እንዲያው ከልባቸው አቅንተው ወይም ሳይሆን አይቀርም በሚል አስተሳሰብ አይደለም ። ምፅዋ ይኖሩ የነበሩት ሚስዮናዊው አባ (ጎድሬ) ዴልሞ የተባሉ ሰው የእንግሊዝና የፈረንሳይ ጋዜጦች ስለ



ኢትዮጵያና ስለቴዎድሮስ የሚፅፉትን ሁሉ ጋዜጣውን ለቴዎድሮስ ይልኩ ነበር ። ለአጤ ቴዎድሮስም ጋዜጣውን እየተረጐመ የሚያነብላቸው ባርዴል ስለነበረ ሁሉንም ነገር አጣርተው ያውቁታል።

በካሜሮን እጅ የተላከው ደብዳቤ ዓመት ካለፈው በኋላ በ1856 ዓ.ም. ኬራንስ የተባለ የአይርሽ ሰው ለካሜሮን ከእንግሊዝ መንግሥት የተጻፈውን ደብዳቤ ይዞ ጥቅምት 21 ቀን ጐንደር ገባ ። ቴዎድሮስም የደብዳቤያቸው መልስ መጥቶ እንደሆን ቢጠይቁ የእሳቸው ደብዳቤ መልስ ያለመምጣቱን አስረዳ ። ኬራንስ ይዞ የመጣው ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለካሜሮን የተፃፈለትን ትእዛዝ ነበር ።

ደብዳቤውም ''. . .በመሀል ኢትዮጵያ የግርማዊት ንግሥት ወኪል ሆነህ ብትቀመጥ ምንም የሚጠቅም ነገር የለም ። ወደ ነበርክበት ወደ ምፅዋ ብትመለስ ግን የተሻለና የበለጠ ሥራ መሥራት ትችላለህ ።. . .ይህንንም ፈጥነህ አድርግ ። ሌላ ትእዛዝ እስኪመጣልህ ድረስም በምፅዋ እንድትቆይ . . .'' የሚል ነበር ። በሩቅ ላለው ለእንግሊዝ መንግሥት ጉዳዩ ቀላል መስሎ ቢታየውም በቅርብ ላለው ለካሜሮን ግን ይህን ትእዛዝ ተቀብሎ ለቴዎድሮስ ማሳወቅ ጭንቁ ነበር ።

ካሜሮን ከዚህ በፊት ከአገሩ በደረሰው ትእዛዝ መሠረት ሱዳን ውስጥ ገብቶ በመስንበቱ ቴዎድሮስ ከጠላቶቼ ከደርቡሾች ጋር ቆየህ በማለት ከፉኛ ቂም ይዘውበታል ። አሁን ደግሞ ቱርኮች ከኢትዮጵያ አስለቅቀው ወደ ያዙት ወደ ምፅዋ ለመሔድ ከቴዎድሮስ ፈቃድ መጠየቅ በሕይወቱ ላይ መፍረድ ነበር ። ካሜሮን ይህን ሁሉ በማመዛዘንና በመፍራት የመንግሥቱን ትእዛዝ ቻል ብሎ ቆየ ። የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ግን እየደጋገመ ትእዛዙን አስቀላለፈለት ።

ያሁኑ ጊዜ ደግሞ ቴዎድሮስን ያዘናና ጥሩ ጊዜ አልነበረም ። ግብጾች ከፈረንሳዮች ጋር ተባብረው በሱዳን በኩል ወደ ኢትዮጵያ ለመዝመት የመዘጋጀታቸው ወሬ ይወራ ነበር ። ወሬም ብቻ ሳይሆን ከንት ራውል ዱ.ቢሶን ከሱዳን ወይም ከኢትዮጵያ የጥጥ መትከያ መሬት እንድፈልግ ታዝዤ መጥቻለሁ እያለ ካርቱም ገብቷል ። ከእሱም ጋር 400 ጠመንጃና አራት መድፎች ያለው የፈረንሳይ ጦር ሠራዊት አጅቦታል ''. . .በሱዳን ውስጥ የጥጥ መትከያ ሰፊ መሬት የማይገኝ ቢሆን ከኢትዮጵያ ውስጥ ገብቼ እንድፈልግና

## ምዕራፍ 11

# የራሳም መልዕክተኛነት

በሚስተር ራሳም የሚመሩት የእንግሊዝ መልክተኞች ምፅዋ ከደረሱ በኋላ ብላንክ ስለነበረው ሁኔታ በመጽሐፉ ሲገልጥ “. . . ንጉሠ ነገሥቱን ለማግኘት የጓጉለትና ስዎቹንም ለማሠር ምክንያት የሆነውን የንግሥቲቱን ደብዳቤ ለማድረስ የነበረው ጥረት ብርቱ ነበር ። የአበሻው ንጉሠ ነገሥት ለእንግሊዝ ንግሥት ልከውት ለነበረው ደብዳቤ መልስ የያዙ መልክተኞች ምፅዋ መግባታቸውን ለግርማዊነታቸው የሚያስታውቁ መልክተኞች ለማግኘት ምፅዋ በደረስንበት ቀን ወዲያውኑ ሙከራ ጀመርን ። ነገር ግን የአጤ ቴዎድሮስን ስምና ዝና የስማ ሁሉ ፈጽሞ የሚሸበር ስለሆነ ለዚህ ተግባር የምናውላቸው ስዎች ለማግኘት ከፍ ያለ ችግር ገጠመን ። ብዙ የገንዘብ ስጦታ እንከፍላለን በማለት ተስፋ ስጥተን ማግኘት ቻልን ..” ይላል ። ትርጉም እቶ ዳኘው ወልደ ሥላሴ

ራሳም በጻፈው መጽሐፍ ላይ እንደሚገልጠው ለቴዎድሮስ የተጻፈው ደብዳቤ በአረብኛ ፊደልና ቋንቋ ነበር ። ደብዳቤውም “. . . .ትናንት ከዚህ ወደብ መድረሱን ለግርማዊነትዎ ሳስታውቅ ክብር ይሰማኛል ። የመጣሁትም ግርማዊት የእንግሊዝ ንግሥት ለግርማዊነትዎ የጻፉትን ደብዳቤ ለማድረስ ነው ። ይህንንም ያመጣሁትን ደብዳቤ በእጅዎ ለመስጠት እችል ዘንድ መልስዎን እጠባበቃለሁ ።

“. . . .ክብር አግኝቼ እርስዎን ለማየትና ከታላቁ ችሎትዎ ለመቆም በጉጉት እጠብቃለሁ ፡ በዚህም ምክንያት ከከተማዎ የሚያደርሰኝ አጃቢ እንዲላከልኝ ፈቃድዎን እጠይቃለሁ ። የዝናሙ ወራት ደርሶ መንገዱ አስቸጋሪ ከመሆኑ በፊት ፈቃድዎ ይፈጸምልኛል ብዬ እመኛለሁ ። ቆንሲል ካሜሩንንና ሌሎቹንም እስረኞች በፈቃድዎ ፈትተው እዚህ ቦታ ድረስ እንደሚልኩልኝም ባለሙሉ ተስፋ ነኝ ።



“ይህ ከሆነም ግርማዊነትዎ የሚመኙትን ምኞት ሁሉ የሚያስፈጽም አንድ የመልዕክተኛ ቡድንዎ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲሔድ እናደርጋለን ። ንግሥታችንም መልዕክተኛዎን ለመቀበል ደስተኛና ፈቃደኛ ናቸው ። ወደ ኤደን ከመመለሴ በፊትም ይህ የሚላከው ቡድን ቢመጣ እንግሊዝ አገር ድረስ በኔ ጠባቂነትና ኃላፊነት አደርሰለሁ ። ከዚህም ደብዳቤ ጋር ሶስት ደብዳቤዎችን ልኬአለሁ ። አንደኛው ከግብፅ የኮፕት ፖትርያርክ ለግርማዊነትዎ የተጻፈ ነው ። ሁለቱ ግን ለኢትዮጵያው ጳጳስ ለአቡነ ሰላማ የተላኩ ናቸው ። . . . ለነዚህም የሚሆን መልስ ቢልኩ እኔ ተርጉሜ በየአድራሻው ለማድረስ እችላለሁ ፡ ግርማዊነትዎ በመልስዎ እንደሚያስደስቱኝ ተስፋ አለኝ ።. . .” የሚል ነው ።

ሚስተር ራሳም ለአጤ ቴዎድሮስ የጻፈውን ይህን ደብዳቤና ለእስረኛው ለካሜሩን ስንቅ የሚሆን ገንዘብ ጨምሮ ላከና ምላሽ እስኪመጣ ምፅዋ ሆነው ይጠባበቁ ጀመር ። የደብዳቤው ምላሽ ሳይመጣ በመዘግየቱ መልክተኛው በሽፍታ ተገድሎ ወይም ተወርሶ ይሆናል ተብሎ ስለታሰበ ለሁለተኛ ጊዜ አክቶበር 17 (በኛ ጥቅምት 7) ቀን አሁንም በአረብኛ ቋንቋ የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፈ ።

“. . . .እዚህ ከደረስኩ አሁን ሶስት ወር ገደማ እንደሆነኝ በግርማዊነትዎ ይታወቅልኝ ። የመጣሁትም ከታላቋ የእንግሊዝ ንግሥት ለግርማዊነትዎ ለተላከው ደብዳቤ ለማድረስ ነው ። እዚህ እንደደረስኩም ይህንኑ ለግርማዊነትዎ የሚያስታውቅ ደብዳቤ ጽፌ በሁለት መልክተኞች ልኬ ነበር ። መልክተኞቹም መሐመድ አባዋስ እና መሐመድ ስኡድ ይባላሉ ። እስካሁን ድረስ ግን አንዳችም መልስ አላገኘሁም ።. . .

“እዚህ ስለቆየሁበት ምክንያት በየቀኑ የተለያዩ ወሬዎችን እሰማለሁ ። አንዳንዱ ወሬ መልዕክተኞቹ ከእርስዎ ዘንድ ባይደርሱ ነው ይሉኛል ። ይኸውም በመንገድ ላይ ከእርስዎ ዘንድ እንዳይደርሱ የሚያደርጉ አስቸጋሪ ስዎች እንዳሉ ይነግሩኛል ። አንዳንዱም ወሬ ደብዳቤው ለሌሎች ሰዎች ተሰጥቶ እነኛ ስዎች ለግርማዊነትዎ ሳያደርሱት ጥለውት ይሆናል የሚል አለ ። በእነዚህ ምክንያቶች አሁን እንደገና ይህን ደብዳቤ ጻፍኩልዎ ። ከዚህም ጋር ከዚህ በፊት ጽፌልዎት የነበረውን ደብዳቤ አልደረስዎት ይሆናል ብዬ ግልባጭ ጨምሬ ልኬአለሁ ።. . .

“ናእብ መሐመድ ቢን አብዱልራህማን ለግርማዊነትዎ ታማኝ


ወዳጅ መሆኑን ስለነገረኝ ይህን ደብዳቤ በእርሱ በኩል ላኩልዎት ። . . . .እርሱም በደህናና በሰላም እንደሚያደርስልዎ ተስፋ አለኝ ። መልሱን በቶሎ በመላክ እንዲያከብሩኝ እለምንዎታለሁ ። ከእንግሊዝ መንግሥት ለተላኩበት መልዕክትም የግርማዊነትዎ አስተያየት ምን እንደሆነ ባውቅ ደስ ይለኛል ። በሁሉም ነገር የግርማዊነትዎ ፍጹም ታዛዥ ነኝ. . .”

ራሳም ይህን ደብዳቤ ከጻፈ በኋላ ለኤሮፓውያኖቹም ደብዳቤ ጽፎ ነበር ። እንግሊዛውያኖቹ ሳይሆኑ ሌሎች የተያዙት ኤሮፓውያኖች ምን ዓይነት ቋንቋ ይናገሩ እንደሆነ ስላልታወቀ እነራሳም በእንግሊዝኛ ፣ በፈረንሳዊኛና በጀርመንኛ ቋንቋዎች ደብዳቤ ጽፈው እስረኞችን ለማስፈታት የሚቻልበትን የተሻለ መንገድ እንዲያማክሩዋቸው ጠየቁ ።

ሁለተኛውም ደብዳቤ ቢሆን ውጤት አልነበረውም ። በምፅዋ ሐኑር ይቃጠል የነበረው ብላንክ “. . . .የተላኩት ሰዎች ከልዩ ልዩ ክፍል ከተራው ወገን ፣ ከናይብ ተከታዮችና የንጉሡ ነገሥቱ ታማኝ አሽከርና ዘመድ የተባለ ሰው ሁሉ ቢሆንም ውጤቱ አንድ ሆነ ። ችግሩ ከንጉሡ ነገሥቱ መልስ መምጣቱ ሳይሆን እንዳቸውም ሳይመለሱ መቅረታቸው ነበር ። . . . .” ይላል ። በዚህም ምክንያት እንደገና ለሶስተኛ ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ደብዳቤ ጻፈ ። ራሳም ሶስተኛውን ደብዳቤ በእንግሊዝኛ የጻፈበት ምክንያት በአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ እንግሊዝኛና አማርኛ የሚያውቁ ኤሮፓውያንና ኢትዮጵያውያንም መኖራቸውን ስለሰማ ነው ። ይህን ሶስተኛውን ደብዳቤ የላከው ኢብራሂም በተባለ ሰው እጅ ነበር ። ኢብራሂም የተመረጠበትም የንጉሡ ባለሟል የሳሙኤል ወንድም ነኝ ብሎ ስለተናገረ ነበር ። ማርች 30 በኛ መጋቢት 21 ቀን የተጻፈው ሶስተኛው ደብዳቤም እንደሚከተለው ይላል ።

“ . . .ግርማዊነትዎ እስረኞቹን ይቅርታ አድርገውላቸው በነፃ እንደሚለቋቸው በዚህ ለሶስተኛ ጊዜ በጻፍኩልዎት ደብዳቤ ስገልጽልዎ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል ። ከስምንት ወሮች በፊት በጻፍኩልዎ ደብዳቤ ከእንግሊዝ መንግሥት የተጻፈልዎትን ደብዳቤ ለማድረስ ተልኬ መምጣቴን ገልጬ ነበር ። ሶስት ወር ሙሉ መልሱን ስጠብቅ ከቆየሁ በኋላ የመጀመሪያዎቹ ሁለት መልዕክተኞች ባያደርሱልኝ ይሆናል በማለት እንደገና በሐረርጌው ናእብ በኩል ጽፌልኬ ነበር ።





ናእቢ ሐሰን

“ ለመጀሪያውም ሆነ ሁለተኛው ጊዜ ለጻፍኩልዎ ደብዳቤ እስከአሁን መልስ አላገኘሁም ።እንደማስበውና እንደምገምተውም ሁለቱም ደብዳቤዎች እንደደረሰዎት አድርጌ ነው ። ነገር ግን የእርስዎ ዝም ማለት እኔን በጣም አሳስቦኛል ።

“ ለግርማዊነትዎ ለመግለጽ የምወደው የመጣሁበት ዋና ተግባር ከንግሥታችን የተጻፈልዎትን ደብዳቤ ለግርማዊነትዎ ለማድረስ ነው ። ይህን ደብዳቤ ለእርስዎ ከማቅረብ ሌላ የማደርገው ምንም ነገር የለም ።. . . .

“ ከፉ አሳቢ ሰዎች የእንግሊዝና የኢትዮጵያ መንግሥት በመልካም ወዳጅነት እንዳይገናኙ ስለሚመኙ የተላኩበት ሥራ እንዳይሳካ የሚያደርጉ አሉ ። የእንግሊዝ መንግሥት የጠበቀ ወዳጅነት እንደሚፈልግ አረጋግጥልዎታለሁ። በሁለቱ መንግሥታት መሀል የሚደነቀረውን መሰናከል እያስወገድን መልካም ግንኙነት እንዲኖረን እንጥራለን ።

“ የመዘግየቱ ጉዳይ የበለጠ እያሳሰበኝና እያስጨነቀኝ ሔደ ። ምክንያቱም ለላከኝ መንግሥት ምን መልስ ልመልስ እያልኩ

ነው ። ሌላው ደግሞ የዝናቡ ወራት አሁን መቃረቡ ነው ። ስለ ዚህ ግርማዊነትዎ ፈቃድዎ ሆኖ መልስ ፈጥነው ካላኩልኝ ወደ ሥራ ቦታዬ ወደ ኤደን ለመመለስ የምገደድ መሆኔን አገልጣ ለሁ ።

አጤ ቴዎድሮስ የሚጽፉላቸው ደብዳቤዎች ሳይደርሳቸው ቀርተው ሳይሆን ሁሉም ደርሰዋቸዋል ። መልሱን ፈጥነው ለመስ ጠት ግን የእሳቸው ደብዳቤ መልስ እንደተናቀ እሳቸውም የንግ ሥቷን ደብዳቤ በመናቅ ብድር ለመመለስ ብለው ነው ። ለራሳም ደብዳቤ መልስ መከልከል ብቻ ሳይሆን የተላኩት መልክተኞች እንኳ ተመልሰው እንዲሔዱ አልፈቀዱላቸውም ነበር ።

ከመልዕክተኞቹ አንዱ አቶ ወልደ ማርያም የሚባለው ከመቅ ደላ ተመልሶ ምጽዋ ገባ ። ከእሱም ጋር በመቅደላ የታሠሩት የትግ ራይ እስረኛ የደጃች መርድ ሁለት አሽከሮች አብረውት መጡ ። እነኝህም ሰዎች ከቴዎድሮስ የተጻፈ ደብዳቤ ባይዙም ከቆንሲሉ ከካሜሩንና ከወንጌላዊው እስተርን የተጻፈ ደብዳቤዎች ይዘው መጡ ። ካሜሩን ለራሳም በጻፈው ደብዳቤ "....ምክሬን ልለግ ስህ ፣ የተከበርከው ራሳም ሆይ ...ይህን ነገር ከመፍትሔ ለማድ ረስ ጠንከር ያለ ደብዳቤና ተግባር ያስፈልጋል ። እንዳሁኑ ያለው ልመና አያዋጣም ። እርግጥ ይህ ይደረግ ብለን መንግሥታችንን መጫን እንደማይገባን እናውቃለን ። የእንግሊዝ መንግሥት ጥቅምና የአገሬቱ ደህንነት በቅድሚያ ትኩረት የሚገባው ነው ።

"....እሳቸው ነገሩ በሰላም እንዲያልቅ ይፈልጋሉ ። ግን እን ዴት እንደሚሆን አያውቁም ። እባክህ ስለ እግዚአብሔር ብለህ ወደዚህ እንዳትመጣ ። እንደሚያስሩህ እርግጠኛ ነኝ ። እንደሚያ ስቡት እኛ በእጃቸው እስካለን ድረስ ምንም ጥቃት እንደማይደር ስባቸው ይገምታሉ ። እንዳንተ ያለው ደግሞ ሲጨመርላቸው ለእሳቸው የበለጠ መልካም ነገር የሚሆንላቸው ይመስላቸዋል ። እንደ እሳቸው አስተያየት ማለቴ ነው ።..." የሚሉ አረፍተ ነገ ሮች ነበሩበት ።

ራሳም እነኝህን ከመቅደላ የመጡትን ሰዎች ስለቴዎድሮስ ሁኔታና ስለእስረኞቹ ይዞታ ሲጠይቃቸው ንጉሡ የውጥር መያዛ ቸውን ነገሩት ። ሸዋ ዘምተው ሲመለሱ ወታደራቸው በረሃብና በበሽታ እንደተጐዳባቸው ፤ የወሎ ሰዎች ሸፍተው ማስቸገራቸ ውን ፤ የወልቃይቱ ጣሰው ጐበዜ ዋናው ከተማ ጐንደርን መያ



ዙን ፤ ምስራቃዊው አውራጃ ላስታ ፣ አገውና ተምቤን እስከ ትግሬ ድረስ በዋግሹም ጐበዜ እጅ መሆኑን ፣ ዋግሹም ጐበዜም ለቴዎ ድሮስ ዋና ጠላታቸው መሆኑን ሁሉ ነገሩት ።

ከራስም ዘንድ እየተላኩ የሔዱት ሰዎች ሁሉ ለምን መልስ ይዘው አልመጡም ? ለምንስ በዚያው ይቀራሉ ? እነኝህን የመሳ ሰሉ የእንባቢ ጥያቄዎች ይኖራሉ ። ለእነኝህ መልስ መጠነኛ ማብ ራሪያ የሚሰጠን የመሐመድ ሰይድ ደብዳቤ ነው ። መሐመድ ሰይድ ሐምሌ 17 ቀን 1856 ዓ.ም. የመጀመሪያዋን የሚስተር ራሳምን ደብዳቤ ለአጤ ቴዎድሮስ ለማድረስ የተላከ መልዕክተኛ ነው ። መሐመድ ሰይድ የቆየበትን ምክንያት ሪፖርት እንዲያቀርብ ራሳም ባዘዘው መሠረት የጻፈው ደብዳቤ (ሪፖርት) እንዲህ ይላል ።

"...እኔና ጓደኛዬ መሐመድ አባዋስ ወደ አበሻው ንጉስ ዘንድ ተልከን በ16 ቀናችን ደረስን ። ጐንደር እንደደረስን ወዲያውኑ ደብዳቤውን ለንጉሱ በእጃቸው ሰጠን ። እሳቸውም ደብዳቤውን ከማንበባቸው በፊት "ይሄን ደብዳቤ የሰጣችሁ ባሻ የሚባለው ምን ዓይነት ሰው ነው? አብረውትስ ወታደሮች አሉ? ብለው ጠየ ቁን ። ምንም የለም ብለን መለስንላቸው ። ደብዳቤው እንዲነበብ አረብኛ ማንበብ የሚያውቅ እንዲጠራ አዘዙ ፣ ሌላ ሰው ደግሞ ጠርተው ለኛ ምግብና ማረፊያ እንዲሰጠን አዘዙት ።

"በማግስቱ መልክተኛ ልከው አስጠሩን ። እንደደረስንም ይህን ወረቀት የሰጣችሁ ሰው ወደዚህ ለመምጣት የሚፈልግ ነው? ብለው ጠየቁን ። እኛም አዎን ወደዚህ ለመምጣት በጉጉት ይጠባበቃል ብለን ነገርን ። እሳቸውም በአርባ ቀናት ውስጥ መልሱን ይዛችሁ ትሔዳላችሁ ። አሁን ሂዱና ጠብቁ ብለው ንጉሱ አሰናበቱን ። በሣ ሙኤል በኩል መልዕክተኛ ተልኮ መልሱን እስቲነግረን ድረስ ሳን ፈራ እንድንቆይ ተነገረን ።

ከሁለት ወር በኋላ ንጉሱ ወደ ደብረ ታቦር ሔዱ ። ኤሮፓው ያን ሁሉ ተሰብስበው ቆንሲል ካሜሩንንና ሌሎቹንም እስረኞች እንዲፈቱ ለመኑዋቸው ። ንጉሱም ነገ ኑ ብለው መለሱላቸው ። ማታ ውኑ መልክተኛ ልከው ልመናቸውን እስቲፈጽሙላቸው ድረስ ከፊ ታቸው እንዳይቀርቡ አስነገሩዋቸው ። እኛም ሣሙኤል እንደገና ወደ ንጉሱ እንዲያቀርበን ጠየቅነው ። ወደ ምፅዋ ለመመለስ አስበን ነበርና ነው ። የኛ ሥራ ደብዳቤውን አምጥተን መስጠትና መልሱን

ይዘን መመለስ ነው አልነው ። በማግስቱ ወደ ንጉሱ ድንኳን ተወሰድን ። ወደ ድንኳኑ ከመግባታችን በፊት ሣሙኤል መጥቶ ጥቂት ቆዩ ብለዋችኋል ብሎ ነገረን ።

“ከሐረር ጊጎ ናአቢ የተላኩት የእርስዎን ደብዳቤ የያዙት ሌላዎቹ መልዕክተኞች መቅደላ መድረሳቸውን ሰማን ። የያዙትንም ደብዳቤ ተቀብለው ከተነበበና ጉዳዩን ከሰሙት በኋላ መልዕክተኞቹ ከኛ ጋር እንዲቀላቀሉ ታዘው እኛ ወዳለንበት ሠፈር መጡ ።



ኢማር አብዱላሂ

“ንጉሱ እኛን ያኖሩን ልክ የእሳቸውን ተከታዮች እንደሚይዙት ነበር ። የሚያስፈልገንን ሁሉ እየጠየቅን በየጊዜው ይሟላልናል ። ይህም በጦርነት ላይ ከሚውሉበት ቀን በስተቀር ነው ። የጐንደሩ ነጋዴ ወልደ ሥላሴ ጉበዜ በሐምሌ ወር መጀመሪያ ገደማ ከምፅዋ መጣ ። ከንጉሡ ዘንድ ቀርቦም ስለኛ መቆየት አመለከተልን። እሱም ከእርስዎ ጋር መገናኘቱን ገልጾ የዘገዩት የሚሰጣቸውን መልስ ሲጠብቁ ነውና ሲሆን መልሱን ይዘው ፣ ያለዚያም እንደዚሁ እንዲሔዱ ቢደረግ መልካም ነው አላቸው ። ይህን በሚናገርበት ጊዜ ጓደኛዬ መሐመድ አባዋሶ ከዚያው ቆሞ ነበር ። ንጉሱም ፈጥነው እንደሚመልሱን ተስፋ ሰጥተዋል ተብሎናል ።



“ሰኔ 27 ቀን ረቡዕ ዕለት ኢብራሂምና መሐመድ ሺሃዊ ሶስተኛውን የእርስዎን ደብዳቤ ይዘው መጡ ። በማግስቱ ሁላችንም ከንጉሱ ዘንድ ተጠራን ። ያንጊዜ በመቅደላ ምሽግ ነበሩ ። እዚያም እንደደረስን ወደ ምፅዋ ለመመለስ ዝግጅት እንድናደርግ ተነገረን ።





እሥረኞች

በዚያም ቦታ የንጉሱን የአማርኛና የአረብኛ ፀሐፊዎቻቸውን አየና
ቸው ። ሙአሊም ማታና (ማታ የአባቱ ስም ነው ጨለመ መሸ ለማ
ለት አይደለም) ። አለቃ ተክሌ ናቸው ። እነሱም ለእርስዎ የሚላ
ከውን ደብዳቤ ይጽፉ ነበር ።

"ንጉሱ በየትኛው መንገድ ወደ ምፅዋ ለመመለስ እንደምን
ፈልግ ጠየቁን ። እኛም በላስታ በኩል ያለው መንገድ ሰላማዊ (ደህና)
መሆኑን ነገርናቸው ። ደብዳቤዎቹ ለሣሙኤል ተሰጡት ፣ እኛም
ወደሰፈራችን ሔደን እንድንዘጋጅ ተነገረን ። በመጨረሻው ደብዳቤ
ዎቹ ለኢብራሂምና ለመሐመድ ሲሃዊ ተሰጡ ። በዚያው ቀን በተሰ
ያት ገደማ መቅደላን ለቀን የምፅዋ መንገዳችንን ቀጠልን ።

"ከንጉሱ ዘንድ ተሰናብተን ከሔድን በኋላ ቆንሲል ካሜሩን
መፈታቱን ሰማን ። ኢብራሂምና መሐመድ ሲሃዊ እግር ብረቱ በሚ
ወልቅበት ጊዜ ከዚያው ከአጠገቡ ነበሩ ። እኔና ጓደኛዬም ቆንሲሉን
ብዙ ጊዜ እይተናቸዋል ። አንድ ጊዜ ልብሳችንን የምንገዛበት ገን
ዘብ ልከውልናል ። ከተፈቱ በኋላ ግን ለማየት ጊዜ አልነበረንም ።
ለምፅዋው መንገዳችን ተቻኩለን ነበርና ነው ። ከምሽት በደረስን
ጊዜ የንጉሱ ኃይል ብዙ ነበር ። እየቀነሰ ሔዶ አሁን የበፊቱን
ግማሽ ያህልም አልቀራቸውም ። ግማሹም በመኮብለል ሌላውም
በየቦታው ከሽፍቶች ጋር በሚያደርገው ውጊያ እየሞተ አልቋል ።
እኛ መቅደላን በለቀቅንበት ጊዜ እንኳን ንጉሱ ትልቁን አመፀኛ
ዋግ ሹም ጎበዜን ለመውጋት ሊዘምቱ ነው እየተባለ ይወራ ነበር ።
ተክሌ ወንዝ ስንደርስ እንዳየነው የንጉሱ ሹማምንት ለዘመቻቸው
ስንቅ የሚሆን በግና የቀንድ ከብት ይሰበስቡ ነበር ።

"ጓደኛዬ አባዋሰ ተምቤን አጠገብ ፋናራ ስንደርስ ተለያይተን
በሰራዊ ውስጥ ጉዱ ፈላሴ ያሉትን ዘመዶቹን ለማየት ብሎ ሔደ ።
ምፅዋ ላይ እንገናኝ ብሎን ቀረ ።"

ለሶስተኛ ጊዜ ራሳም ለአጤ ቴዎድሮስ የጻፈውን ደብዳቤ
መጋቢት 21 ቀን 1857 ዓ.ም. ይዘው የሔዱት ኢብራሂም ወለድ
ሹም እና መሐመድ ሲሃዊ በደብዳቤ ያቀረቡት ሪፖርት ደግሞ
እንዲህ ይላል ።

"ከእርስዎ እንደተለየን ወደ አበሻው ንጉስ ዘንድ ለመሔድ
በትግሬ ፣ በተንቤንና በላስታ አድርገን ጉዞ ጀመርን ። በጉዞውም ከመ
ጨረሻው ቦታ ለመድረስ አንድ ወር ያህል ፈጀብን ። የምንጓዘውም



ፍቶችን እየፈራን በሌሊት ነበር ። አንዳንዴም አንድና ሁለት ቀን
ህል ጉዞአችንን እያቋረጥን ውሎ እናደርግ ነበር ። ሰቆጣ ስንደርስ
ሰቆጣና በደብረ ታቦር መሃል ያለው መንገድ ሰላማዊ ባለመሆኑ
ብዙ ቀን ተቀመጥን ።

"ደብዳቤውን በሣሙኤል በኩል ለመስጠት አሰብን ። እሱም
ንጉሱ ባለሟል ነው ። ሰቆጣ እንደደረስን ስንጠያይቅ እሱ ያለው
ብረ ታቦር መሆኑን አጣራን ። እኛም የመጣንበትን ጉዳይ ገልፀን
ን ዲረዳን መልዕክተኛ ላክንበት ። እሱም ግድ የለም እንድትመጡ
ሊል ላከብን ። እኛም በቀጥታ ወደ ደብረ ታቦር ተጉዘን በ12 ቀና
ችን ደረስን ። እሱም የንጉሱን የጦር መሣሪያዎች ጠመንጃዎችንና
ጥይቶችን ወደ መቅደላ በማስጫን ሥራ በዝቶበት አገኘነው ። በዚ
ያውም አስር ቀናት ከቆየን በኋላ ሳሙኤል ቀድሞን ወደ መቅደላ
ሔደ ። እኛንም ለንጉሱ ከሚጫነው ጓዝ ጋር እንድንሔድ አደረገን ።

"ጁላይ 4 (ሰኔ 27) ቀን በዘጠኝ ቀናችን ረቡዕ ዕለት መቅደላ
ደረስን ። ደብረ ታቦር ሆነን ሳሙኤል ስላመጣነው ደብዳቤ ለንጉሱ
ሊነግርልን ተስፋ ሰጥቶን ነበርና መቅደላ ካለው ከሳሙኤል ቤት
እንደደረስን መልዕክተኛ ሠጥቶ ከንጉሱ ዘንድ እንደምንፈለግ ነገረን።
እኛም ፈጥነን ጉዞ ጀመርን ።

"ደብዳቤውን ለግርማዊነታቸው ከመስጠታችን በፊት ማን
እንደላከን ጠየቁን ። እኛም እርስዎ እንደላኩን ተናገርን ። እሳቸውም
'ይሄን የሽፍታውን አገር እንዴት አለፋችሁት!'' ብለው ቢጠይቁን
እኛም 'በእርስዎና በእንግሊዝ መንግሥት ውቃቤ ልናልፈው ቻልን'
ብለን መለስን ። ደብዳቤ ይዞን እንደሆነና የተጻፈውም በምን ቋንቋ
እንደሆነ ጠየቁን ። አንደኛው የተጻፈው በአረብኛ ሲሆን ሌላው
ደግሞ በእንግሊዝኛ ነው አልናቸው ።

"ደብዳቤውን ከመቀበላቸው በፊት የምንናገረው ሌላ መል
ዕክት እንዳለ ጠየቁን ። እኛም 'ጃንሆይ መጀመሪያ ደብዳቤው ይነበ
ብና ከዚያ በኋላ የምንናገረው ይኖረናል' አልናቸው ። እሳቸውም
'ግድ የለም ። ደብዳቤውን በኋላ እነበዋለሁ ። በመጀመሪያ የምትና
ገሩት እንዳለ ልስማው' አሉን ። እኛም 'የእንግሊዙ ወኪል ለእርስዎ
ከፍተኛ ሰላምታ እንድናደርስ ነግሮናል ። የመጀመሪያዎቹ ደብዳቤ
ዎች ሞገስ እንዳላገኙ ሰግቷል ። በዚህም በእንግሊዝኛ በአበሻ መሀል
መልካም ወዳጅነት እንዳይኖር የሚፈልጉ ሰዎች እንዳሉ ጠርጥሯል።
እሉ የመጣቡትንም ጉዳይ እያጣመሙ የሚያስረዱ እንዳሉ አድርጎ

ያስባል ። የእንግሊዝን መልካም ወዳጅነት ግን ግርማዊነትዎ ተመራ ምሮ እንዲደርስበት ይመኛል ። ይህንንም ከእንግሊዟ ንግስት ለግር ማዊነትዎ በተጻፈው ደብዳቤ ላይ ያገኙታል ። የያዘውንም ይህን ደብዳቤ ለግርማዊነትዎ ለመስጠት ቸኩለዋል’ ብለን ተናገርን ።

‘‘እሳቸውም ‘ለመምጣት ከፈለገ ለምን ከእናንተ ጋር አይመጣም ነበር ?’ አሉን ። እኛም ስንመልስ ‘እንዴት አድርጎ ያለ ግርማዊነትዎ ፈቃድ መምጣት ይችላል ?’’ ስንላቸው ሳቁና ‘እሺ ያንን የምትሉ ትን ፈቃድ እልክለታለሁ’ አሉን ። ከዚያም ወደ ሠፈራችን እንድን ሔድና ደብዳቤውን ካነበቡ በኋላ እንደሚያስጠሩን ነገሩን ።

‘‘ወደሠፈራችን እንደተመለስን ራሳቸው ንጉሡ ከሚበሉት ምግብ ተላከልን ። ከበላንም በኋላ እንድንመጣ ተነገረን ። ከፊታቸው ስንቀርብም ሶስቱን ደብዳቤዎች ፀሐፊያቸው ሙአሊም ማታ እንደ ገና እንዲያነባቸው ነገሩት ። እሳቸው ከመጀመሪያው ደብዳቤ ይልቅ ሁለተኛው የተሻለ መሆኑን ፣ ከሁለተኛው ደግሞ ፫ኛው ደብዳቤ የተ ሻለ መሆኑን ተናገሩ ። በተለይ ፫ኛው ደብዳቤ በጣም እንዳስደሰ ታቸው ገለጹልን ። ሲናገሩም እንግሊዝና አበሻ ወዳጅ ከሆኑ ጊዜው የቆየና አሁንም ወዳጅ መሆናቸውን ተናግረው ቆንሲሉ ግን በሁ ለቱ አገሮች መሀል እንዳለው ወዳጅነት ያለመሥራቱን ፣ አሁንም አንተ ሁሉንም እንደምታስተካከል ተስፋ እንዳላቸው ነገሩን ።

‘‘ከዚህ በኋላ ወደ ሠፈራችን እንድንመለስ ተነገረን ። በሠ ፈራችንም ምንም ነገር እንዳይጐድልብን አስፈላጊያችን ሁሉ እንዲ ደረግልን ሣሙኤልን አዘዙት ። እኛም ‘ንጉሥ ሆይ በእርስዎ ታላቅ ቸርነት በምግብ በኩል ምንም የጐደለብን ነገር የለም ። ነገር ግን የምንጠብቀው በታላቁ ቸርነትዎ መልሱን ሰጥተውን ወደ ምፅዋ እንድንመለስ እንዲያደርጉን ነው’ አልናቸው ። እሳቸውም መንገዱ አስቸጋሪ መሆኑና ይህንንም ለማስተካከል በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ትግሬ እንደሚዘምቱና እኛም ጥቂት እንድንቆይ ቆንሲሉንም እንደሚፈቱ ነገሩን ። እኛም ስንላክ በአርባ ቀን እንደምንመለስ ተስፋ ሰጥተን ነበር ። ከዚህ የበለጠም መቆየት እንፈልግም አልናቸው ።

‘‘እሳቸውም ሳቅ አሉና በፈገግታ ‘የእንግሊዙ ወኪል በእር ግጥ ወደዚህ ለመምጣት ፈልጐ እንደሆነ እንዴት አድርጎ በሸፈተው አገር ውስጥ ሊያልፍ ይችላል ?’ ሲሉ ሳሙኤል በዚያው ነበርና ጣልቃ ገብቶ በመተማ በኩል መልካም (ሰላማዊ) መንገድ መኖሩን



ተናገረ ። ንጉሱም በአሳቡ ተስማሙ ። እኛንም አሁን ሂዱና ነገ እንድትመጡ አሉን ።

‘‘በማግስቱ ማለዳ ጁላይ 5 (ሰኔ 28) ቀን ንጉሱም እኛንም ፣ ሣሙኤልንም ፣ የአማርኛና የአረብኛ ፀሐፊዎቻቸውንም አስጠሩን ። የአረብኛውን ቋንቋ ደብዳቤ ሙአሊም ማታ ጻፈው ። የአማርኛው ደብ ዳቤ ደግሞ በአንድ ፀሐፊ ተጻፈ ። ለእኛም አጃቢ እንደሚሰጡ ንና እነሱም መተማ ድረስ እንደሚሸኙን ነገሩን ። አንተም እዚያ በምትደርስበት ጊዜ ተቀባይና አጃቢ ሳይልኩልህ አይቀርም ። ከም ፅዋ ስትነሳም እንድትጽፍላቸው ነግረውናል ። ይህም መተማ ያለው እንደራሴያቸው እንዲቀበልህ ለማዘዝ ነው ።

‘‘ከዚህ በኋላ ካንተ የተላኩት የበፊተኞቹ መልክተኞች ሁሉ ከኛ ጋር አብረውን እንዲመለሱ እንዲነገራቸው አዘዙ ። ለእያንዳን ዳቸውም 5 አምስት ብር እንዲሰጣቸው ተናገሩ ። ለኛ ግን ምንም አልሰጡንም ። ነገር ግን ካንተ ጋር ተመልሰን በምንሔድበት ጊዜ እንደሚሸልሙን ተስፋ ሰጥተውናል ። ወደ አንተ የተላከውን ደብዳቤ እንዳልፈረሙበትና ማህተምም እንዳልተደረገበት ነግረውናል ። ምክንያቱም በቆንሲል በጣም ስለተናደዱ ነው ። እሱንም እኛ ከሔ ድን በኋላ እንደሚፈቱት ነገሩን ። እኛም ‘ንጉሥ ሆይ ታላቁን ደግነትዎን የምንለምነው ለላከንም ለአቶ ራሳም ቆንሲል ተፈትቶ አየነው ብለን ለመንገር እንድንችል ከመሔዳችን በፊት ቆንሲሉን ፈትተው ልባችንን በደስታ እንዲሞሉት ነው ። አልናቸው ። እሳቸ ውም ይሁንላቸው ። ለአቶ ራሳም ወዳጅነትና ስለ እናንተም መቸገር ቆንሲል ተለቆ ታዩታላችሁ’ አሉን ።

‘‘ከዚህ በኋላ አቶ ሣሙኤልንና ዋናውን የጦር አዛዦቸውን ራስ እንግዳን አዘው እኛ ከእነሱ ጋር እንድንሔድና ቆንሲሉን ከፊ ታችን እንዲፈታ ፣ እኛም መፈታቱን ማየታችንን ላንተ እንድንነግር አዘዙን ። ቆንሲሉ ከፊታችን ከተፈታ በኋላ ላንተ የሚላክ ደብዳቤ እንዲሰጠን ጠየቅነው ። ሣሙኤል ግን ንጉሱ ካላዘዙ በስተቀር ይኼ ነገር ፈጽሞ አይቻልም አለን ። እኛም ጉዞ በጀመርንበት ጊዜ ቆን ሲሉ ተፈትቶ ነበር ። ይህንንም ታላቅ ቸርነታቸውን ተመልሰን ለማ መስገን አስበን ፈርተን አልሔድንም ። ከዚህ በኋላ ጉዞአችንን ቀጥ ለን በ12ኛው ቀናችን ምፅዋ ገባን ። የቆየነውም በመንገዱ ፀጥታ ማጣት ነው ።’’

እነኚህ የመልዕክተኞቹ ሪፖርቶች በራሳም መጽሐፍ በመጀመሪ ያው ቮልዩም ላይ ይገኛሉ ።

በመጨረሻው እነራሳም ምፅዋ በገቡ በዓመቱ በነሐሴ ወር 1857 ዓ.ም. የፈቃዱ ደብዳቤ ከቴዎድሮስ ዘንድ መጣላቸው ። ከአጼ ቴዎድሮስ ዘንድ ለሚስተር ራሳም የተጻፈው ደብዳቤ ቀጥሎ ያለው ነው ።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩አምላክ። ሰሚን፡እግ ዳሓጥፍላህ፡አቡነ፡ሰላሚ፡ኮከብ፡የሚባል፡ፈሳሽ። ቁንሰል፡ ኀበሳችሁ፡የሰደዳችሁቱ፡ኬምሮን። ከገዘ፡ከተማየ፡በእግዚአ ብሔር፡ኀይል፡በፍቅር፡አስቀምጣቸው፡ሳሉ፡ሰደዱኝ። የእንግሊዝን፡ንግሥት፡ፍቅር፡ለፈልግ። ቡላዲን፡ዮሐንስ፡የ ሚባሉ፡የእንግሊዝ፡ሰዎች። ከገሬ፡ሊደበደቡ።በእግዚአብ ሔር፡ኀይል፡የነዚያን፡ደም፡ኀበመላስ። በዚኸውም፡ነፍሰ፡ገ ዳይ፡ኀበሰው፡በደሉኝ። ቁንሱሉ፡ኬምሮን፡የሚባለው፡የንግ ሥት፡ሎሌ፡ነኝ፡ቢለኝ። ያገሬን፡ጊጥ፡ሸለሚ፡ሠንቁን፡ሠ ጥቼ፡ከንግሥት፡ወዳጅ፡አደርገኝ፡ኀበየ፡ኀበሰደው። ከቱርኮች፡ ጋራ፡ሰንብቶ፡ተመልሶ፡መጣ። ደብዳቤየን፡ኀበሰው፡እሏ ተመ ለሰላኝም፡አለኝ። ምን፡ባደረግሁ፡ጠሉኝ፡ኀበየ፡በጌታዬ፡ ኀይል፡ዝም፡አልሁ።

ይድረስ፡ከሆርሙዝ፡ራሳም። አሁንም፡ትግሬ፡ሽፍታ፡ወጥ ቶአልና። በእግዚአብሔር፡ኀይል፡ዙረህ፡በመተማ፡ና፡ መተማ፡ስትደርስ፡ሳክብኝ፡በእግዚአብሔር፡ኀይል፡ተ ቀባይ፡አሰድልሀለሁ።

ሰኔ፡በባተ፡በ፳፱ ተጻ፡ረቡ፡ተማ ፈ።

ደብዳቤውም ማህተም አልነበረውም ። ለራሳም የተጻፈበት ደብዳቤ ከዚህ በላይ ያነበብነው አማርኛው ብቻ ሳይሆን ይህ የአማ ርኛው ደብዳቤ በአረብኛ ተተርጉሞ በአንድነት ከአማርኛው ጋር



ተልኮለታል ። ምናልባትም ለአንባቢዎች ወይም ለተመራማሪዎች ጠቃሚ ይሆን እንደሆነ በማለት እንደ አማርኛው ሁሉ ማህተም የሌለበትን አረብኛ ደብዳቤ ፎቶ ኮፒ ከዚህ ቀጥሎ አስገብቼዋለሁ ።

بسم الاب والابن والروح القدس الاله الواحد له المجد الى الاباد امين

علم كتاب اسمي اليك فهو ابونا سلامه وكوكب اليهودي الذي يدعا والذي اذ عينتموه قنصل

الذي يدعى كمرون المرسل منكم قد اجلستهم في مدينتي المخصوصه بعناية الله بالمجد وبينما انا معهم بالمحبه

تتعوقني فيما انا راغب في محبة الملكه الانكليزيه بلودين ويوحنا المدعوين الناس ابطلين

لما ان سفك دمهم في بلادي فبقوة الله لما اهتممت مع اوليك من قاتليهم فلهذا قالوا انه قاتل النفوس

شتموني بكرين الذي يدعا قنصل ادعا انه خادم الملكه ونحن نعدنا زيناه بزينة ملبوس بلادنا وقد اعطيناه

زادا للطريق وقلت له اجعلني ان اكون حبيب الملكه لما ارسل بهذا الامر فتوجه وجلس مده مع الترك ور

جع الينا وقد كلمناه عن جهة جواب المرسل منا على يده الى الملكه فقال الى الان لم وصلني الجواب ولاره فقلت ماذا

ماذا عملت عدوني ويبغضني بقوة سيدي خالقي سكت

يصل الى هرمز رسام = ايضا نعلمك ان في هذا الوقت قد صار واحد في بلاد التري على بقوة الله قدر

الى الطريق المؤديه الى المته واحضر وهين حضرتك الى تلك النواحي ارسل اليك بقوة الله ارسل اليك الذي يقبلك

ራሳም ይህ ማህተም የሌለበት የፈቃድ ደብዳቤ እንደደረሰው ከምፅዋ ወደ መተማ ለመሔድ ያለበትን ችግር ሁሉ ያወጣና ያወርድ ጀመር ። ከረምት ስለገባ ከምፅዋ መተማ ለመድረስ የተዘጋጀ መንገድ በሌለበት አገር የማይታሰብ መሆኑን አወቀ ። ሁለተኛው ነገር ደግሞ በዚያው ጊዜ ሱዳን ውስጥ ኃይለኛ በሽታ ገብቶ ሕዝቡን ይጨርስ ስለነበረ በቀጥታ ሄዶ ከዚያ በሽታ ውስጥ መግባትም አስፈራው ። ስለዚህ እንደገና ወደ አጤ ቴዎድሮስ ችግሩን ገልጾ ደብዳቤ ጻፈላቸው ። "ጃንሆይ ። . . . አንድ ነገር እንድገልጽልዎት እለምናለሁ ። በከሰላና ባካባቢው በገባው በሽታ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ እርስዎ እንዳሉኝ በመተማ ዞሬ ለመምጣት የማይቻል ነው . ." ብሎ አሳወቀ ።

ራሳም ይህን ደብዳቤ ከጻፈ በኋላ የከረምቱን ወራት ካይሮ ላይ ለማሳለፍ በመርከብ ተሳፍሮ ወደ ካይሮ ሔደ ። ወደ ካይሮ የሔደበት ዋናው ነገር ክረምቱን በዚያ ለማሳለፍ ብቻ ሳይሆን የእንግ



የጥንታዊት አዱሊስ ከተማ

ሊዝ መንግሥት በራሳም ምትክ ፖልግራብ የተባለውን ሾሞ ምጽዋ ድረስ ሰዶ ስለነበረ ስለዚሁ ጉዳይ በቴሌግራፍ ለመጠየቅና ለመነጋገር ነው ። ካይሮ ደርሶ የቴዎድሮስን የፈቃድ ደብዳቤ መድረሱንና ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ ይመከራቸው የነበረው ካሜሮንም አሁን ግቡ የሚለው የንጉሱ ደብዳቤ ከደረሳቸው በኋላ ቢቀሩ በእስረኞቹ ላይ አደጋ እንደሚደርስ ገልጾ የጻፈለትንም ጨምሮ ለእንግሊዝ መንግሥት በቴሌግራፍ አስታወቀ ። የእንግሊዝ መንግሥት ጉዳዩ እስከዚህ ደረጃ ከደረሰ በራሳም ምትክ ወደ ቴዎድሮስ እንዲሔድ ታዞ የመጣው ፖልግረብ ባለበት በዚያው በካይሮ እንዲቆይ ሆኖ ራሳም ግን በደረሰው የፈቃድ ደብዳቤ መሰረት ከነተከታዮቹ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ የሚል ትእዛዝ አሳለፈ ። ከዚህ በኋላ ራሳም ከእንግሊዝ አገር ሲነሳ ለአ ጤ ቴዎድሮስ የሚሰጥ የያዘው ስጦታ እጥጋቢ መስሎ ስላልታየው አንዳንድ ስጦታዎችን ገዛ ። እስከ መስከረም ድረስ ካይሮ ከቆዩ በኋላ መስከረም 28 ቀን 1858 ዓ.ም. ተመልሰው ምጽዋ ገቡ ።



እነራሳም ምጽዋ እንደገቡ ጊዜ ሳያጠፉ ጥቅምት 6 ቀን 1858 ጓዛቸውን በተከራዩዋቸው ስልሳ ግመሎች ላይ ጭነው በቀጠሯቸው በብዙ ሰዎች ታጅበው የመተማ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። ከምጽዋ መተማ ድረስ ያለውን ረጅም ጉዞ በመሬት በመጓዝ 704 ኪሎ ሜትር ተጉዘው ከምጽዋ በተነሱ በወር ከሰባት ቀናቸው ሕዳር 12 ቀን መተማ ገቡ ። ጐንደር ለመድረስ ግን ገና 160 ኪሎ ሜትር ያህል መንገድ ይቀራቸዋል ።

መተማ ድረስ ስለነበረው የጉዞ ሁኔታ ብላንክ ሲጽፍ “.. በሠፈርንበት ቦታ ሁሉ የእንበሶች ጬኸት ጆሮአችንን ያደነቁረው ነበር ። የአገሩ ሙቀት ከመጠን በላይ ኃይለኛ አስቃቂ ስለነበረ የቀኑን ሐሩር ለመሸሽ ስንል በጧት እየተነሳን መጓዝን እንወድ ነበር ። ከሁሉም ይልቅ ማታ ማታ ጨረቃ ቢኖርም ባይኖርም ከቀኑ ሐሩር ይሻላል በማለት መጓዝን እንመርጣለን ። እንደዚህ ባለ ከባድ ሁኔታ የምንገሰግሰው የመንግሥታችንን ትእዛዝ ለማክብርና በሰንሰለት የታሠሩት ወገኖቻችን ወደሚገኙበት አገር በመድረስ ተግባራችንን ለመፈጸም ግዴታችን ስለነበረ ነበር። የምንጠጣው ውሃ በፍየል አቅማዳ የተያዘውን ሙቅና ቆሻሻ ውሃ ስለነበር በፀሐይ የተቃጠለውን አካላታችንን ለማለስለስና ድካማችንንም ለማውጣት መንገድ አልነበረንም ። የደረሰብንን መጐሳቆል በሱዳን ላይ ለማቋረጥ የገጠመን ችግርና መከራ ከባድ ቢሆንም በጥንቃቄ አንድ ሰው በሞት ሳይለየን በሰላም መተማ ደረስን ። አብረውን የተጓዙት የአገሬው ሰዎችና ተከታዮቻችን ሚስተር ራሳምም ሳይቀር በወባ በሽታ መሰቃየታቸው ባይቀርም ሁሉም በሕይወታቸው ላይ አደጋ ሳይደርስባቸው ድነዋል . . . . ” ብሏል ።

መተማ እንደደረሱ ቴዎድሮስ መተማ ስትደርስ ላከብኝ ባሉት መሠረት ራሳም ወደ አጤ ቴዎድሮስ መተማ መድረሱን በደብዳቤ ጻፈላቸው ። አጤ ቴዎድሮስም የፍቃድ ደብዳቤ ፣ ተቀባይና አጃቢም ላኩላቸው ። ለመተማው ገዢ ለሸህ ጁማ አጤ ቴዎድሮስ በጻፉለት ደብዳቤም “ . . . . . የምወደው ወዳጄ አቶ ኽርሙዝድ ራሳም የሚባል የእንግሊዝ ሰው አሁን እንተጋ መተማ አለ ። እሱንም አጅበህና በደህና አድርገህ ጭልጋ እንድታደርሰው ይሁን ። ከዚያም የኔ ሰዎች ይቀበሉታል ። በዚህ ጉዳይ እንድትበረታበት ። ምክንያቱም የምወደው ወዳጄ ነውና ። እንድታከብረውም ይሁን ። . . . ” ይላል ።

እነ ራሳም እንደ ቴዎድሮስ ትእዛዝ ሁሉ ታጅበው ጭልጋ ሲደርሱ 1400 የሚሆኑ ከአጤ ቴዎድሮስ የተላኩ ተቀባዮች ተቀ ብለዋቸው ይጓዙ ጀመር ። ጥር 20 ቀን 1858 ዓ.ም በጌምድርንና ዳሞትን ከሚያዋስነው ቦታ እኩለ ቀን ላይ ሲደርሱ ራስ እንግዳ ብዙ ሰው ይዘው አቀባበል አደረጉላቸው ። ከዚህ ቦታ አጤ ቴዎ ድሮስ ዘንድ ለመድረስ የሚቀራቸው መንገድ ሃያ ደቂቃ ያህል የሚ ያስኬድ ነው ።

በዚያ ቦታ ስለነበረው አቀባበል አብሮ ይጓዝ የነበረው ዶክተር ብላንክ ሲገልጽ "...ተራራማ ቦታ ላይ የአጤ ቴዎድሮስ ወታደሮች የጦር መሣሪያና ጦር በያዙ... ባጌጡ ሰዎች ተሞልቶ ነበር ።.. ቁጥራቸው አስር ሺህ የሚሆኑ ሰዎች በሁለት ረድፍ ተሰል ፈው ስለጠበቁን በመካከላቸው ስናልፍ ፣ በቀኝ በኩል የተሰለ ፉት በተንቆጠቆጠ ልብስ አጊጠው በብር ያጌጠ ጋሻና ጦር ይዘው ፣ ፈረሶቻቸው ባማረ መሣሪያ ተሸላልሞ ፣ የንጉሠ ነገሥቱ መ ኮንኖ ችና የቤት አሽከሮች በሚያማምሩት ፈረሶቻቸው ላይ በንቃት ተቀ ምጠው ነበር ። በግራ በኩል የተሰለፈው ፈረሰኛ ሠራዊት ...ጥቅ ባለ ሁኔታ በብዛት የቆመ ሲሆን የቀኙ ክፍል ደግሞ ...ቷየ ነበር ።..." ብሏል ።

ከዚህ አቀባበል በኋላ ለራሳም መሔጃ ከአጤ ቴዎድሮስ በተ ላከች ውብ ሆና ባጌጠች በቅሎ ራሳም ተቀምጠ በደመቀ አጀብ ከቴዎድሮስ ሠፈር ደረሱ ። ከሠፈሩም የመንገደኞቹ ድንኳን እስቲ ተከል ድረስ ለመቀበያ ተብሎ ከተተከለው ከአጤ ቴዎድሮስ የግል ቀይ ድንኳን ውስጥ ገብተው አረፉ ። ግብር ገብቶላቸው በሚዝና ኑበት ጊዜ ከአጤ ቴዎድሮስ በአረብኛ የተጻፈ ደብዳቤ ለራሳም ደረሰው ። ደብዳቤው እንዲህ የሚል ነበር ።

بسم الاب والابن والروح القدس الاله الواحد له الحمد سرمدياً امين

ملك الملوك ... السلطان تادوروس



بحول بقوة الله حيث انك حضرة طالب لنا بيل المحبة محبنا هرز رسا...

في هذا اليوم ... لا ... البيات والراحة وفي بال المواجهة ولكن قد صرنا جالسين

في بلاد قد أكلت مستنضرين حضورك فالمال والجيوش قد صاروا جميعا

فقد صار الامر اليوم بالمواجهة ... وفي بال السر فالان احضر



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ አሜን
ከንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ በእግዚአብሔር ኃይል ፣ ይድረስ
ከወዳጅ ወዳጅነቱን ከሚፈልገው ሀርሙዝ ራሳም ።

የዛሬውን ሌሊት አርፈህ ብታሳልፈው የተሻለ ይሆንልህ ነበር ። ነገ ጧት ብንገናኝም ጥሩ ነበር ። ነገር ግን እኔ በዚህ አገር ያንተን መምጣት ስጠባበቅ ብዙ ቆይቻለሁ ። ስንቅ በማለቁ ምክንያት ወታ ደሩ ምግብ ፍለጋ ላይ ነው ። በዚህ ምክንያት ስኔና ባንተ መሀል የሚደረገው ንግግር ዛሬ ቢጀመር መልካም ነው ። ነገ ጧት ጉዞ እንጀምራለንና አሁን መጥተህ እንገናኝ ።"

ከዚህ በኋላ በራስ እንግዳ እየተመሩ ከንጉሡ ድንኳን አካባቢ ሲደርሱ በሩምታ ጥይት ተተኩሶ አቀባበል ተደረገላቸው ። ከድን

ኳኑ ውስጥ ሲገቡም አጤ ቴዎድሮስ በዙፋናቸው ተቀምጠው በግራና በቀኝ ሹማምንቶቻቸው ቆመው ነበር ። ቴዎድሮስ የለበሱት ያገር ልብስ ሲሆን ራሳቸውን ተከናንበዋል ። በእፍንጫቸውም ላይ የኩታቸውን ጠርዝ አድርገዋል ። እነ ራሳም ገብተው ከተጻፈ ዓመት ከመንፈቅ የሆነውን የንግሥት ቪክቶሪያን ደብዳቤ ለመስጠት ራሳም ሲጠጋ ከንብንባቸውን አወረዱ ።

ራሳም የንግሥቲቱን ደብዳቤ ለአጤ ቴዎድሮስ ከሰጠ በኋላ ከዚያው ከፊታቸው ቆሞ “እጅግ በጣም ከተከበሩት የእንግሊዝ ንግስት የተጻፈውን ይህን ደብዳቤ ለግርማዊነትዎ ሳቀርብ ታላቅ ክብር ይሰማኛል” በማለት ንግግር አደረገ ። ቴዎድሮስም “ደብዳቤውን የምቀበለው በደስታ ነው ። እተንም በደህና በማየቴ ተደስቻለሁ” ብለው መልስ ሰጡ ። ደብዳቤውንም በሶስተኛው ካለው መከዳ ላይ አስቀመጡት ። ወደ ተነጠፈው ሥጋጃ እያሳዩም “ተቀመጡ” አሏቸውና ተቀመጡ ።

ከንግሥቲቱ በእንግሊዝኛ የተጻፈውን ደብዳቤ ወደ አማርኛ ለመተርጐም አስተርጓሚ አቶ ወልደ ገብርኤል ቀረቡ ። አቶ ወልደ ገብርኤል ትውልዳቸው ሸዋ በመሆኑ ለሸዋው ንጉሥ ለምኒልክ ረድተው ነገር ያበላሻሉ ብለው አጤ ቴዎድሮስ ውጣ ብለው ከድንኳኑ አስወጧቸው ። ስለዚህ ደብዳቤውን በቀጥታ ወደ አማርኛ የሚተረጕመው ስላልተገኘ ራሳም ወደ አረብኛ እየተረጐመ አቶ ሣሙኤል ደግሞ ከአረብኛ ወደ አማርኛ ቃል በቃል ይተረጉመው ጀመር ።

ከንግሥቲቱ በተጻፈው ደብዳቤ ላይ “. . . . ግርማዊነትዎ ሚስተር ራሳምን በመልካም እንደሚቀበሉት ስለምናምን ስለኛም የሚነግርዎትን ሁሉ ዋጋ እንደሚሰጡት እምናለሁ ።. . . . “የሚለውን አረፍተ ነገር አቶ ሣሙኤል ሲያስተረጉሙ “. . . . ሚስተር ራሳም የሚፈልጉትን ሁሉ ያደርጋል . . . ብለው ተረጐሙት ይህን “ራሳም የሚፈልጉትን ያደርጋል” የሚለውን የተሳሳተ ትርጉም የሰሙት ቴዎድሮስ በጣም ደስ አላቸው ። “. . . .ከእንግዲህ ወዲህም እንዲህ ያለ ሰው ካገኘሁ በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መሀል ያለው የቆየ ወዳጅነት እንደገና ይታደሳል ። ከእነኝያ ኤሮፓውያን እስረኞች ሁሉ ይህ ሰው የበለጠ ነውና ወዳጄ ሚስተር ራሳም ከኔ ጋር የሚቆይ ከሆነ እነኚያ ወደፈለጉበት ይሂዱ ። ልቀቋቸው . . .” አሉ ።

በዚህ በአጤ ቴዎድሮስ መልስ ራሳም ተደሰተ ። ራሳም እንደ መሰለው አጤ ቴዎድሮስ እስረኞቹ እንዲፈቱ ያዘዙት ከንግሥቲቱ



በመጣው ደብዳቤ ተደስተው መሰለው እንጂ “ከኔ ጋር የሚቆይ ከሆነ” የሚለውን አረፍተ ነገር አላጤነውም ። ከዚህ በኋላ በተደረገው ጭውውት ቴዎድሮስ ለራሳም ኤሮፓውያን እንዴት እንዳስቀየሙዋቸው ፤ በተለይ አቡነ ሰላማ ፤ ቆንሲል ካሜሩንና ቄስ እስተርን እንድነት ሆነው የበደሏቸውን ሁሉ ነገሩት ። ካሜሩን የሰጡትን ለእንግሊዝ ንግሥት የጻፉትን ደብዳቤ ይዞ ምፅዋ በመሔድ ፈንታ ወደ ከሰላ ሔዶ ከጠላቶቻቸው ከቱርኮች ጋር ሲማከር መቆየቱን ፤ ከቱርኮችም ጋር በተገናኘ ጊዜ በተደረገለት የእራት ግብዣ ላይ ይዞ የሔደውን የአበሻ አሽከር እየሸለለ እንዲፎክር ቢያዘውና እምቢ ቢለው አስገድዶ ማሸለሉን ፤ ቱርኮችም እየሳቁ “ትልቁ ንጉሣችሁ ወታደሮች የሚያዋጋው እንደዚህ ነው” እያሉ ማላገጣቸውን ሁሉ ነገሩት ።

እስተርንም አቡነ ሰላማ የነገሩትን ይዞ የኮሶ ሻጭ ልጅ ብሎ መጻፉንና እናታቸው ያደረጉትን ውለታ ሁሉ ለራሳም አጫወቱት ። ድካማቸውም አገሪቱን በአንድ ንጉሥ የምትገዛ ሰላማዊ አገር ለማድረግ መነሳታቸውን ሁሉ አጫወቱት ። “. . . .ወደ ደቡብ ስሔድ በሰሜን ያለው ሕዝብ ይሸፍታል ። ወደ ምዕራብ በምሔድበት ጊዜ ደግሞ በምሥራቅ ያሉት ይሸፍታሉ . . .” እያሉ ነገሩት ። ቱርኮች በሱዳን በኩል ገብተው ከኢትዮጵያ ግዛት ሰናርን ቆርሰው መውሰዳቸውንና በአሁኑም ጊዜ ለጦርነት መዘጋጀታቸውን ሁሉ ነገሩት ። ራሳምም የሚነግሩትን ሁሉ በጥሞና አዳመጠ ። በመጨረሻውም አጤ ቴዎድሮስ ለነሚስተር ራሳም ባልደረባ እንዲሆናቸው ፀሐፊያቸውን አቶ ሣሙኤልን ሰጡዋቸው ። እነ ራሳምም ባልደረባቸውን ከተቀበሉ በኋላ ከቴዎድሮስ ድንኳን ጥቂት ራቅ ብሎ ከተተከለላቸው የማረፊያ ድንኳን ውስጥ ገቡ ።

ለነሚስተር ራሳም ለሚያስፈልጋቸው ወጭ አጤ ቴዎድሮስ 10000 ብር (15000 የሚሉም አሉ) ሰጡዋቸው ። በየቀኑም አንድ ሺ እንጀራ ፤ ሁለት የቀንድ ከብት ሃያ ዶሮ 500 እንቁላል ፤ አስር ገንቦ ወተትና አሥር ገንቦ ማር እንዲሰጣቸው ድርጐ አዘዙላቸው ። መቅደላ ያሉት እስረኞችም ተፈትተው ለነራሳም እንዲሰጡ ተፈቅዶ መልክተኛ ወደ መቅደላ ተላከ ።

## ምዕራፍ 12

# እሥረኞች ተፈትተው ታሠሩ

አጤ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የሚላክ የሚከተለውን ደብዳቤ ጽፈው እስረኞቹ ወደ አገራቸው በሔዱበት ጊዜ እንዲላክ አዘዙ ።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩አምላክ፡የእግዚአ
ብሔር፡ፍጡር፡ባርያው፡የዳዊት፡የሰሎሞን፡ልጅ፡ንጉሠ፡ነ
ገሥት፡ቴዎድሮስ፡ይድረስ፡ለእግዚአብሔር፡ከሰው፡ሁሉ፡መር
ጦ፡አልቆ፡ካነገሠሽ፡ሃይማኖት፡ፍቅር፡ከሚወዳ፡የታጠቃ
ጀሀ፡ከሚጠብቁ፡ከዕንግሊዝ፡ንግሥት፡ከቪክቶርያ፡ሕር
ምክር፡ስለሆነ፡በኬምሮን፡ጉዳይ፡ሠርጄዋለሁ፡ያሉኝ
ን፡እንኳን፡እርስዎ፡የባርያዎ፡ባርያ፡ቢልክብኝ፡እምቢ፡እላ
ለሁ፡አሺ፡ብዬ፡ጀልዎ፡ለበሁ፡ለኢያ፡ግን፡ቋቋለ፡ነኝ፡ብሎ፡ከመ
ጣ፡ግብጥ፡ጋራ፡ሁነው፡ያደረጉኝን፡እግዚአብሔርን፡ከሚ
ፈሩ፡ሰው፡ጠይቀው፡ያግኙት፡ስለ፡ክታላቂቱ፡ከርስዎ፡ጋራ
መላለክ፡ተገብቶኝ፡አይደሰም፡ዳሩ፡ግን፡ተላቅ፡ሰውና፡ባለ
ር፡እንድ፡ነው፡ሁሉን፡ይችላል፡እኔን፡የኢትዮጵያን፡ደንቆር
ሰስ፡እግዚአብሔር፡ብሰው፡ይቻሉኝ፡፡ለኔሬ፡እቸው፡የነበሩ
ቶችን፡ያሞፈሩኝ፡የሰደቡኝ፡ጋሉ፡ገዞች፡የእስራኤል፡ልጅ፡ጠ
ቶቹ፡ለተላቆች፡እነ፡ነኝ፡እግዚአብሔር፡ብቻ፡ነውና፡ሁሉ
ሠተ፡ኃይሉ፡ሠጥቶኝ፡መሰሰልኝ፡፡የኢትዮጵያን፡ሰዎች
ደንቆር፡ነታቸ፡ነን፡ዕውር፡ነታቸ፡ነን፡ሣይሰሙት፡አስፈቀ
ዳቸው፡ያማረ፡መለሱኝ፡ደፍረ፡የለክሁ፡ብዬን፡ከቁትብ
ኛቢገኝ፡ይሞክሩኝ፡እንጂ፡አይክፉብኝ፡እግዚአብሔር፡የ
መረጠዎ፡ንግሥት፡ዓይንዎ፡የበራ፡ነውና፡፡

ዓለም፡ተፈጠረ፡በ፯ሺ፫፻፶፰አመት፡በጥር፡በ፳፪ቀ
ን፡ተጣፈ፡፡ጌታ፡ከተወለደ፡በ፲፰፻፶፰ አመት፡





ይህም ለንግሥት ቪክቶሪያ የተጻፈ ደብዳቤ ወደ እንግሊዝኛ ተተረጒመው ጋር ሲተያይ አንዳንድ ስህተቶች አሉበት ። ይህም የሆነው ከተርጓሚው ብዛት ይመስላል ። አማርኛው በአቶ ሣሙኤል ጊዮርጊስ ወደ አረብኛ ከተተረጓመ በኋላ ራሳም ራሱ ከአረብኛ ወደ እንግሊዝኛ ስለተረጒመው ነው ። ወይም ደግሞ ራሳም በእንግሊዝኛ እትሙ ላይ የፈለገውን ቃል ጨምሮ ይሆናል ራሳም ስለተርጓሚው አቶ ሣሙኤል በመጽሐፉ እንደጻፈው“አቶ ሳሙኤል አረብኛና አማርኛ በጥሩ ሁኔታ ያውቃሉ . . .” ይላል ። አቶ ሳሙኤል ግን ትግሬ ሰው በመሆኑ አማርኛ 2ኛ ቋንቋው እንጅ የራሱ ቋንቋ አይደለም ። ስምሳሌ “...በኬምሮን ጉዳይ ሰድጄዋለሁ ... ”የሚለው አማርኛው አረፍተ ነገር በእንግሊዝኛው ላይ “. . . በሁሉም ኤሮፖው ያ ጉዳይ . . . ” የሚል ተጨምሮበታል ። በአማርኛው ። . . . .ስለ እግዚአብሔር ብለው ይቻሉኝ . . . “የሚለው አረፍተ ነገር ራሳም በተረጒመው እንግሊዘኛ ላይ “. . . . በስህተቴ ይቅርታ ያድርጉልኝ . . . ”ይላል ። በውጫሌ ውል በትርጉም ስህተት ኢጣሊያኖች እንደመጡ ሁሉ በቴዎድሮስም ዘመን በትርጉም ስህተት እንግሊዞች መጡ ። በቴዎድሮስ ደብዳቤ ላይ “. . ጋላ ገዞች . . .”ያሉት እነራስ አሊን ነው ።

እነራሳም ጥቂት ቀናት አረፍት ካደረጉ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ወደ ጣና አካባቢ ለመሔድ ሲነሱ እነራሳም አገር እንዲያዩና እንዲላመዱ ብለው እብረው ይዘዋቸው ሔዱ ። ጣና ሐይቅ ሲደርሱም ራሳም መቅደላ ያሉት እስረኞች ተፈትተው እስኪመጡ ድረስ ዘጌ ደሴት ላይ ሆኖ እንዲጠባበቅ ትተውት አጤ ቴዎድሮስ ወደ ሜጫ ሔዱ ። ከሜጫም ራሳምን ለማስደሰት ብለው ወታደሮች ከጫካ የያዙዋቸውን ሁለት የአንበሳ ግልገሎች በልጅ ካሣና ብልጅ አብተው ላኩለት ። የአንበሳ ግልገሎቹን በላኩለት ጊዜም የሚከተለውን የሰላምታ ደብዳቤ ጻፉለት ።

ጸ ከሀዐ፡ አብ፡ ወወ ል ድ፡ ወመ ን ፈ ስ፡ ቅ ዱ ስ፡ ፩ አ ም ላ ክ፡
ን ጉ ሠ ነ ገ ሥ ት፡ ቴ ዎ ድ ሮ ስ፡ ይ ድ ረ ስ፡ ከ ቶ፡ ሕ ር ም
ዝ ር ስ ም፡ እ ን ደ ም ን፡ ሰ ነ በ ት ህ፡ እ ኔ፡ እ ግ ዚ አ ብ ሔ
ር፡ ይ መ ስ ገ ን፡ ደ ኅ ና፡ ነ ኝ፡ ወ ን ድ ሞ ች ሽ ን ም፡ እ
ነ ሀ ኪ ም ን፡ እ ን ዴ ት፡ ሰ ነ በ ታ ች ሁ፡ እ ለ፡ በ ል ል ኝ፡
በ ፈ ጣ ሪ የ፡ ኃ ይ ል፡ ካ ን ተ፡ ከ ተ ለ የ ሁ፡፡ ፪ ያ ን በ ሣ

ልገሎች። ዕየወረቦ፡ልጅ፡ ማርኪ፡ ሠድጀልሃለሁ፡ የናንተን፡ ደህና፡ መ ባበት፡ አዳምጠ ለሁ፡ ብዬ፡ ጣፎ፡ ከሚባል፡ አገር፡ ሳይ፡ መጥቶ፡ ሠፍሬአለሁ። እግዚ አብሔር፡ቢል፡ እንገናኛ ለን፡በ ቃ ጓኪ፡መሸገር፡ አምሮ ኛል፡፡



የአንበሳ ግልገሎቹና ይህ የአጤ ቴዎድሮስ ደብዳቤ እንደደረሰው ራሳም የሚከተለውን ዲብዳቤ ጻፈላቸው “. . . ትናንት የተከበረ ደብ ዳቤዎን ስቀበል ክብር ተሰምቶኛል ። . . . በደብዳቤው ላይም የግር ማዊነትዎን ጤንነት በማወቄ በጣም ተደሰትሁ ። እግዚአብሔር በረከቱን እንዳሳይረብዎት ሁሉ ወደፊትም እንዲሁ እንዲቀጥል እፀ ልያለሁ ። . . . . የላኩልኝ የአንበሳ ግልገሎችና ሚዳቋ በደህና ደረ ሉኝ ። ስለነዚህና በአገርዎ ከገባሁ ጀምሮ ቶሎ ተደረገልኝ አከብሮት ከፍ ያለ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። በደግነትዎ ከዋንጂ ተነስተን በሐይቁ ላይ አድርገን ባለፈው ሐሙስ ከዚህ ስንደርስ አቶ ካሣና አቶ ወንዴ ከፍተኛ አቀባበል አደረጉልን ። እስካሁንም ያለነው ከእነሱ ቤት ነው ።. . .”

እስረኞቹ ቀስ በቀስ እያሉ ራሳም ዘንድ ቆራጣ ከተባለው መን ደር ተሰባሰቡ ። እነኝህም ለመጀመሪያ ጊዜ ራሳም ዘንድ የመጡት የፖለቲካ እስረኞች ሳይሆኑ ሚስዮናውያኖቹና ሌላዎቹ አገር ለመ ጐብኘትና ለጥናት የመጡት ነበሩ ። ራሳም ለቴዎድሮስ በጻፈው የሰላምታ ደብዳቤም ላይ የሌሎቹን እስረኞች ከሱ ዘንድ መድረስ ጠቅሶ የመቅደላ እስረኞች ያለመድረሳቸውን ገለፀላቸው ። አጤ ቴዎድሮስም ለራሳም መልስ የሚከተለውን ደብዳቤ ጽፈው በልጅ አብተውና በከንቲባ ኃይሉ እጅ ላኩለት ።



በስመ፡ አብ፡ ወወልድ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ቴዎድሮስ፡ ይድረስ፡ ከአቶ፡ ሕርምዝ፡ ረስአም፡ እንዴት፡ ሰነበትህ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር ይመስገን፡ ደህና፡ ነኝ፡ ሐኪሞ፡ ብሎ ማ ኔን፡፡ አቶ ጥሬ ደን፡ ወነ ድሞችህን፡ እንዴት፡ ሰነበታችሁ፡ እሰ፡ በልልኝ፡ ደህ ና፡ መማባታችሁን፡ ቆራጣ፡ መ ድረሳችሁን፡ ሰምቸ፡ በፈጣሪ አችን፡ ኃይል፡ እ ጅግ፡ ደስ፡ አለኝ። አሁንም፡ እደዘአችሁ፡ እጋፋ ራ፡ ጉለምን፡ ሠድጄዋለሁ፡ እስሮችን፡ እስፈ ትተህ፡ ና፡ ብየ፡ በቶሎ፡ አገራችሁን፡ እሠዳች ኋለሁ። ፬ቱን፡ ፪፪ት፡ አፋ፡ ተራዘሚዎች። ፲ ቱን፡ ፪፪ አፍ፡ የወገብ፡ ጠበንጆች፡ ከነማፍሰሻቸ ው፡ የሰጠኸኝን። ። አቶ፡ ቢርግ፡ እኔ፡ ከወገድሚ ልኬ፡ ሳንተ፡ በረከት፡ ያስመጣሁት፡ ነው፡ ብሎ፡ እ ለኝ። እኔም፡ ለአቶ፡ ቢርግ፡ ፬ሺህ፡ ብር፡ ዳረግሁት፡ ክትባሬው፡ ነጋድራስ፡፡ ፡፡ አቶ፡ ምስኒጂር፡ አጥብ ቆ፡ ይወድሃል፡ ብለህ፡ የነገርኸኝን፡፡ የፍቅር፡ በረከ ት፡ ጆት፡ ስትሂድ፡ የምሠድሰትን፡ የሚወደውን፡ ለክብኝ፡ በእግዚአብሐር፡ ኃይል፡ አስቤ፡ እንዳቶ ይ።



ራሳም ከመጣም በኋላ የፈረንጆች ቅጥፈት ቴዎድሮስን ያስገረ ቸው ጀመር ። ራሳም ለቴዎድሮስ አራት ባለ 2 አፈሙዝ ጠመንጃ ዎችን (እንደረሽ ያሉ) እና በዘመኑ ምርጥ የተባሉት ሁለት አፈ ሙዝ ያሳቸው ስምንት ሽጉጦችን በስጦታ መልክ ሰጠ ። ራሳም ከቴዎድ ሮስ አጠገብ ሲርቅ ሙሴ ቡርጋድ የተባለው ፈረንሳዊ ጠመንጃ ሠሪ እኔ ከወንድሜ ዘንድ ልኬ ያስመጣሁሎት ነው ብሎ ከቴዎድሮስ 4,000 ብር ተቀብሎ አሁን በዚህ ደብዳቤ እንዳነበብነው ቴዎድሮስ ጠመንጃዎችንና ሽጉጦቹን ራሳም እንዳልሰጣቸውና እሳቸው መግ ዛታቸውን እንዲያውቁ ለራሳም በደብዳቤ ገለፁለት ። ይህ ደብዳቤ ለራሳም የካቲት 11 ቀን ሲደርሰውም ደነገጠ ።

በደብዳቤያቸው ላይ የጠቀሱት ሞዚንጀር የስዊስ ተወላጅ ነው ። እሱም እ.ኤ.አ በ1864 በምፅዋ የፈረንሳይ ተጠባባቂ ቆንሲል ሆኖ ነበር ። በኋላም በምፅዋ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ሆኖተሾመ ። ይህ ሰው ወደፊት እንደምናነበው የእንግሊዝን ጦር እየመራ መቅደላ ያደረሰ ነው ። ከቴዎድሮስም በኋላ አጤ ዮሐንስንና ንጉሥ ምኒል ክን ሲያጣላ የኖረ ነው ። በመጨረሻው በ1867 ዓ.ም ኢትዮጵያ ውስጥ አፋሮች ገደሉት ።

አጤ ቴዎድሮስ እስረኞቹን በሙሉ አስፈትተው መጋቢት 3 ቀን ከራሳም ዘንድ ከተሰበሰቡ በኋላ አሁን ወደ ራሳቸው ጉዳይ ተመ ልሰው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለሚስተር ራሳም ጻፉለት ።

በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ቴዎድሮስ፡ ይድረስ፡ ካቶ ህርምዝ ረስአም፡ እንዴት፡ ሰነበትህ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ ይመስገን፡ ደህና፡ ነኝ፡፡ ሀኪም፡ ብሎ፡ ማኖን፡ እቶ ጥሬ ዩን፡ ወንድሞችኸን፡ እንዴት፡ ሰነበታች ሁ፡ አለ፡ ■ልልኝ፡፡ በእግዚአብሔር፡ ቸርነት፡ በኔ ና፡ በንግሥቴቱ፡ በቢክቶርያ፡ ሀብት፡፡ ወዳጅ፡ ፍታልኝ፡ ያሉኝን፡ ሰዎች፡ በእግዚአብሔር፡ ኃ ይል፡ ደህና፡ መምጣታቸውን፡ ከናንት፡ መገና



ኘታቸውን፡ ሰምቸ፡ እጅግ፡ ደስ፡ አለኝ፡፡ እኔ፡ ወ ደጄ፡ ንግሥቲቱ፡ የላኩብኝን፡ ፈቃድዎን፡ አደረግ ሁ፡ በእግዚአብሔር፡ ኃይል። አሁንም፡ ወዳጄ፡ ንግ ሥቲቱ፡ የሠደዱልኝ፡ ደብዳቤ፡ እንዲህ፡ ይላል ለቶ፡ ሕርምዝ፡ ረስአምን፡ የአደን፡ ሹም፡ የነበረው ን፡ አማኛ፡ ሎሌየን፡ ወዳጅን፡ ሠድጄዋለሁና፡፡ ከኛ፡ የምትፈልገውን፡ ሁሉ፡ ጉዳይ፡ ከርሱ፡ ጋር ፡ ተማክር፡ እርሱ፡ ያረግልሃል ብለው ኛል፡፡ አሁን ም፡ እኔ፡ የምፈልገው፡ እውር፡ ነኝና፡ ዓይኔ፡ እንዲ በራ፡ ጥበብ፡ ነው፡፡ ፡፡ አሁንም፡ አንተን፡ ደስ፡ እን ዳለህ፡ እኔንም፡ ደስ፡ እንዲለኝ፡ በእግዚአብሔ ር፡ ኃይል፡ ብልህ፡ ልክህ፡ አስመጣልኝ፡፡ ፡የን ግሥቲቱንም፡ ቃል፡ ገልብጠህ፡ የሠጠኸኝን፡ ሠድጄለሁ፡ እንድትሰሙት፡ ብዬ፡፡ ፡፡ እኔህን፡ ያ ስፈታሀቸዉን፡ ሰዎች፡ በእግዚአብሔር፡ ኃይል፡ እውነት፡ አዋረዳችሁትን፡ አላዋረዳችሁትም፡ ብለህ፡ ጠይቃቸው፡ ወንድሞችኸን፡ ይዘህ፡ እነ አቶ፡ ዋልድ፡ ማየርን፡ ብሌምረ ህ፡

ዓለም፡ ከተፈጠረ፡ በ፯ሺ፡ ከ፫፻፶፰ ዓመት፡ ጌታ፡ ከተወለደ፡ በሽ፡ ከ፰፻፶፰ ዓመት፡ በዘመ ነ፡ ማርቆስ፡ በወርሀ፡ መጋቢት፡ በ፪ ቀን፡ ተ ጣፈ፡፡



ይህ ደብዳቤ ከደረሰው በኋላ ራሳም በጣም ደነገጠ ። በተጻፈለት ደብዳቤ ላይ "ወዳጄን" የሚለውን ቃል በቅንፍ ከቦ የኤክስ ምልክት አደረገበት ። ምክንያቱም ንግስቲቱ ራሳምን "ወዳጄን" ብለው እንዳልጻፉና ሊሉትም እንደማይገባቸው ስለሚያውቅ ነው ። ቀጥሎ "ከኛ የምትፈልገውን ሁሉ ጉዳይ ከርሱ ጋር ተማከር ። እርሱ ያረግልሃል" የሚለውንም አረፍተ ነገር እንደዚሁ በቅንፍ ከብቦ ከደብዳቤው ሕዳግ ላይ (No INSTRUCTION THUS) የሚል ጽፎ ኽርሙዝ ራሳም ለማለት H.R ጻፈበት ። ይህም አረፍተ ነገር ንግስቲቱ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ስላልነበረ ታላቅ የትርጉም ስህተት መፈጠሩ ግባው ።

ራሳም የተፈቱትን እስረኞች በድንኳኑ ውስጥ ሰብስቦ ከቴዎድሮስ የተጻፈውን ደብዳቤ አነበበላቸው ። የተፈቱትም ሰዎች ምንም ጥፋት እንዳልሠሩ ተናግረው በመጨረሻው ለንጉሡ ክብር ሲባል ብቻ ጥፋተኞች ነን እንዲሉ ተደርጐ ራሳም ይህንኑ በደፈናው ጥፋተኛነታቸውን ብቻ ገልጾ ለቴዎድሮስ ጻፈ ። አጤ ቴዎድሮስም የተበደሉት በደል በዝርዝር ባለመነገሩ አዝነው የተበደሉበትን ሁኔታ ለራሳም ለማስረዳት የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉለት ።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩አምላክ፡
ንጉሠ፡ነገሥት፡ቴዎድሮስ፡ይድረስ፡ካቶ፡ህርሞዝ፡ር
ስአም፡እንዴት፡ሰነበትህ፡እኔ፡እግዚአብሔር፡ይመስገን
ደህና፡ነኝ፡፡ሀኪም፡ብሎ፡ማናን፡አቶ፡ጥሬ ደን፡ወንድሞ
ችኽን፡እንዴት፡ሰነበታችሁ፡ስለ፡በልሖኝ፡፡ ፡፡ኮንሱል
ነኝ፡ብሎ፡ያለው፡የኪምሮንም፡ነገር፡እንዲህ፡ነው፡፡በ
ርደልን፡ወኪል፡አርጎ፡እርሱ፡አይነተኛ፡ሁኖ፡የንግሥት
፡መልክተኛ፡ችንመጥቶ፡ናልኝ፡ተቀበለኝ፡ብሎ፡ሳክብ
ኝ፡፡እኔም፡በእግዚአብሔር፡ኃይል፡ደስ፡ብሎኝ፡ምጥ
ዋ፡ድረስ፡ሰው፡ሰድጄ፡አስመጣሁት፡ሚጪ፡ደብረ፡መ
ይ፡ከሚባል፡ሠፈሬ፡ቢደርስ፡መኳንንቶቼ፡ወጥተው
፡ተቀበሉት፡ጠድፍ፡አስተክስሁ፡፡እንደገሬ፡ሥራት፡አን
ጥሬ፡ተገናኘሁት፡በእግዚአብሔር፡ኃይል፡፡የንግሥ
ት፡ደብዳቤ፡ነው፡ብሎ፡ሰጠኝ፡፡ደብዳቤውን፡በነበ



ው፡፡፪አፍ፡ተራዛሚ፡፩ነፍጥ፡፡፪ት፡፪፪አፍ፡የወገብ
ጠበንጃ፡የንግሥት፡በረከት፡ነው፡ብሎ፡ሠጠኝ፡፡እግ
ዚአብሔር፡ይሥጥልኝ፡ብዬ፡እጅ፡ነስቼ፡ተቀበልሁ፡፡
ቀረ፡ግን፡የደብዳቤው፡ቃል፡ወዳጅ፡እንሁን፡ዘመድ፡እ
ንሁን፡አንተም፡እንዳፈቀርኽን፡እንደወደድኽን፡ሰም
ተናል፡በነቡላዲን፡ነገር፡ካገርህ፡ሰው፡ጋራ፡የተደረገኽ
ውን፡ጥንትም፡ኢትዮጵያና፡እንግሊዝ፡አንድ፡ነው፡
ፍቅር፡ነው፡፡ዘሬም፡የኛ፡ቍንስል፡ካንተ፡አገር፡እንዲ
ቀመጥ፡፡አዳኝ፡እንዲአድን፡ነጋዴ፡እንዲነግድ፡እንዲ
መላለስ፡፡የኛ፡ሰው፡ያንተ፡ሰው፡ነውና፡ጠብቅልኝ፡
አለኝ፡፡ያንተም፡ኰንሱል፡ከኛ፡አገር፡መጥቶ፡እንዲ
ቀመጥ፡አዳኝህ፡እንዲአድን፡ነጋዴህ፡እንዲነግድ
በእግዚአብሔር፡ኃይል፡እንጠብቅልሃለን፡ብሎ፡አለኝ፡
፡እሺ፡ብዬ፡ደስ፡ብሎኝ፡፡እንደአገሬ፡ሥራት፡ደስ፡የሚለ
ኝን፡ሁሉ፡አድርጌለት፡ሰበር ደሕም፡ሰርቶም፡፡ቴ፫ከች
፡አገሬን፡ይዘው፡ብኝ፡በላንጋራ፡ሁነው፡ኛልና፡መርከብ
የለኝ፡በባህር፡አልችላቸውም፡በእግዚአብሔር፡ኃይ
ል፡የምሠደው፡በረከት፡ሎሌየን፡የሚቀበለኝ፡

ሰው፡ይሰደዱልኝ፡ብዬ፡የፍቅር፡ደብዳቤ፡ሠጥቼ፡
ሰደድሁት፡፡ከወዲያ፡ተሳክሁ፡ብሎ፡የመጣበትን፡ክ
ዚህ፡ተማክሮኝ፡የፄደበት፡ጉዳይ፡ትቶ፡ከቱርኮች፡
ከማይወዱኝ፡ሰዎች፡ሂደ፡ሲአዋርዱኝ፡ሲንቁኝ፡ሰ
ንብቶ፡መጣ፡፡የሠበሁህ፡የፍቅር፡ደብዳቤ፡ምላሹ
፡ፄት፡አለ፡ምን፡ይዘህ፡መጣህ፡ብዬ፡ብጠይቀው፡እንጃ

፡እሳዉቅም፡ አለኝ፡ እንግዲህ ለየወዳጅም፡ ሎሌ፡ አይደለህ፡ ግቤ፡ በፈጣሪየ፡ ኃይል፡ አሠርሁት፡፡ ይኸን፡ እሱ፡ ቢልህ፡ በቃሉ፡ ጠይቀው፡

የባርደራም፡ ነገር፡ ከፈረንሲስ፡ ንጉሥ፡ ሳይተዋውቅህ፡ ብሎኝ፡ እሺ፡ ብየ፡ ብሠደው፡ አስከልክሎ፡ እምቢ፡ ብሎ፡ ሠደደኝ፡ ብሎ፡ ሀዐጠ፡ ብሸው፡ እግዚአብሔር፡ አለኝ ብዬ፡ ዝም፡ ብየ፡ ተቀምጬ፡ ሣለ፡ ፈረንሲስ፡ ነውና፡ መክረርኝ፡ ፍታ፡ አለኝ፡፡ ከወዲያ፡ ሳስተዋውቅህ፡ ብለህ፡ ሂደህ፡ አስከልክሎ፡ ሠደደኝ፡ ለሐህ፡ የማን፡ ወዳጅ፡ ብየ፡ ነው፡ የምፈታው፡ አይሆንም፡ አልሁት፡ በዚህ፡ ተቆጥቶ፡ ከደባባዬ፡ ሸማዉን፡ ታጥቆ፡ የነበረዉን፡ ፈትቶ፡ ተከናነበ፡፡ በዚህ፡ ተቆጥቶ፡ አሠርሁት፡ በጌታየ፡ ኃይል፡ ለሱ፡ ቢልህ፡ ጠይቀው፡፡ ይህን፡ ሁሉ፡ የሚሠድቡኝ፤ አልሠሙም፡ አልነገሩአቸዉም፡ ብዬ ወዳጅ፡ ጋሽ፡ ነውና፡ በመከተሉኝ፡ በእግዚአብሔር፡ ኃይል፡ ብየ፡ ነው፡ የጠላኋቸው፡

ታንም፡ በእግዚአብሔር፡ ኃይል፡ ንግሥትኙየ አገር ምን፡ ው፡ እናንተን፡ እየወደድሁ፡ እኔ ነኝ፡ እንደገና፡ ተመልሼ መጠላቸው፡ ነኝ፡ ከንጀት፡ እስ[illegible]ርቱኝ፡ በድየ፡ እንደሆ እዩብኝና፡ ልክስ፡ ተበድየ፡ እንደሆነ፡ የፍቅር፡ ካሣ፡ አስሉኝ፡፡



ከዚህ ደብዳቤ በኋላ እስረኞቹ በሙሉ ጥፋተኞነታቸውን በማመናቸው ቴዎድሮስ ተደስቱ ራሳምም ጥፋት ከእስረኞች እንጅ ከቴዎድሮስ ዘንድ ያለመኖሩን በደብዳቤ ገለፀላቸው ። አጤ ቴዎድሮስም ሳም ደብዳቤ ከደረሳቸው በኋላ ለእስረኞቹም ሙሉ ምህረት ማድቸውን በሚከተለው ደብዳቤ ለራሳም አሳወቁ ።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩አምላክ፡ንጉሠ
ነገሥት፡ቴዎድሮስ፡ይድረስ፡ካቶ፡ሕርምዝ፡ረስአም፡፡እንዴ
ት፡ሰነበትህ፡እኔ፡እግዚአብሔር፡ይመስገን፡ደህና፡ነኝ፡፡ሀኪም
፡ብሎግን፡፡አቶ፡ፕሬደን፡ወንድሞችሽን፡እንዴት፡ሰነበታች
ሁ፡አለ፡በልልኝ፡፡የነኪምርንንም፡ነገር፡ወደጆች፡ብዬ፡ሳ
ቅ ሳምጣቸው፡በድለውኝ፡መገኘታቸውን፡እንኳ፡እናን
ት፡አወቃችሁልን፡እንጂ፡፡ከእግዚአብሔር፡በታች፡
ሥለታላቂቱ፡ንግሥት፡ሥለወዳጄ፡ሥለ፡ቢክቶር
ያ፡ይቅር ምንተ፡እግዚአብሔር፡ታርቄአለሁ፡፡በእግዚአ
ብሔር፡ኃይል፡ደስ፡አሠኝተህ፡የላክህብኝን፡ቃሉ፡
እጅሽን፡እግርሽን፡ዝቅ፡ብዬ፡የምሠምህ፡ነኝና፡መ
ጥታችሁ፡ተገናኙኝ፡እንድንመካከር፡፡፡ የነኪምርን፡
ታከረው፡የነበሩት፡እናት፡ምሽት፡ዘመዶች፡አጠቅሠ
ው፡የላኩብኝን፡በእግዚአብሔር፡ኃይል፡ሥለታላ
ቂቱ፡ንግሥት፡ሥለወዳጄ፡ሥለቢክቶርያ፡ታርቂ
ላቸዋለሁ፡ሁሉንም፡በፈጠረአችን፡ኃይሉ፡ሠ
ንገናኝ፡እንመካከራለን

በመጋቢት፡በ፲ቀን፡አሁድ፡ተጣፈ፡፡



አጤ ቴዎድሮስ ምህረት ማድረጋቸውን በዚህ ደብዳቤ ብቻ ሳያቆሙ እንግሊዝ አገር ላሉት ለእስረኞቹ ቤተሰቦች የሚላክም የሚቀጥለውን ደብዳቤ ጽፈው ለራሳም ላኩለት ።



መ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩አምላክ፡ንጉሠ
ሥት፡ቴዎድሮስ፡ይድረስ፡ካዘንተኞች፡ሁሉ፡፡
ዴት፡ሰነበታችሁ፡እኔ፡እግዚአብሔር፡ይመስገ
ደህና፡ነኝ፡፡
ቶኞች፡መቀደሳ፡ታሠሩብን፡ያላችሁት፡፡በእግ
ብሔር፡ኃይል፡በንግሥቲቱ፡በቢክቶርያ፡ወዳጅ
ፈትቸ፡ለአቶ፡ህርምዝ፡ረስአም፡ሠጠሁላችሁ
ስ፡ይበላችሁ፡፡



አጤ ቴዎድሮስ ዘጌ ከመጡ በኋላ የተለቀቁትን እስረኞች ለስን
ቅ ዘጌ ድረስ የሚያመጣቸው ጀልባዎች ላኩላቸው ። በከንቲባ ኃይሉ
ታዘዙት ጀልባዎች እንደደረሱ ራሳም እስረኞቹ የነበሩትን ሁሉ
ወደ እሳቸው እንዲመጣ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጻፉለት ።

መ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩አምላክ፡ንጉሠ
ሥት፡ቴዎድሮስ፡ይድረስ፡ካቶ፡ህርምዝ፡ረስአም፡እንዴ
ሰነበትህ፡እኔ፡እግዚአብሔር፡ይመስገን፡ደህና፡ነኝ፡
ኪም፡ብሎግንና፡አቶ፡ፕሪደን፡ወንድሞችሽን፡
ንዴት፡ሰነበታችሁ፡አለ፡በልልኝ፡፡በእግዚአብሔር
ይል፡በደህና፡ተመልሼ፡ከቤቴ፡ገባሁ፡ፈረሶችን፡ካገር
ነበሩትን፡ልቀበል፡ሂጄ፡ነበረ፡አሁንም፡እግዚአብ

ሐ ር፡ በጤና፡ ከወዳጆቹ፡ ከናንተ፡ ጋራ፡ ለመገናኘት
ያብቃን፡፡ ሬት፡ ስማልወዳቸው፡ አስሬአቸው፡ ለነበር
ሁ፡ ሰዎች፡ ከናንተ፡ እስቲገናኙልኝ፡ ድረስ፡ ከፈጣሪ
አችን፡ ጤና፡ ሠጥቶህ፡ አድርሥልኝ፡ እያልሁ፡ እለ
ምን፡ ነበረ፡፡ ዛሬ፡ ግን፡ ከሳይ፡ ለንግሥቲቱ፡ ለወደ
ጇ፡፡ ከዚህ፡ የደሥታ፡ አበባ፡ ስያዛችሁልኝ፡ ለናንተ
እዮሚና፡ ጤና፡ ሥጥሐኝ፡ እያልሁ፡ እለምናለሁ፡፡
፡እኔን፡ የሚወዱበት፡ ልቦና፡ ሥጥልኝ፡ እያልሁ
እለምናለሁ፡ ፈጣሪአችንን፡፡ እኔ ግን፡ እንግሊ
ዞችን፡ እወዳችሁም፡ እጠላችሁም፡ በዮሐንስ
ና፡ በቡላዲን፡ ጠይቃችሁ፡ እግኙት፡፡ በተቻለኝ፡
እንደገሬ፡ እንዳቀሚ፡ ማቆሰመጤን፡ መውደዴን፡ አል
ተውሁም፡ ነበረ፡፡ እኒያን፡ መውደዴ፡ ማቆሳመጤ፡
የንግሥቲቱን፡ የናንተን፡ ፍቅር፡ አገኝ፡ ሥል፡ ነው
፡፡ አሁንም፡ ወትሮ፡ እፈልገው፡ የነበረ፡ ፍቅራችሁ፡
ተገኘልኝ፡ መስሎኝ፡ በፈጣሪአችን፡ ኃይል፡ እጅግ
ደስ፡ ብሎኛል፡፡ ታንከኞች፡ ሠዶጀሳችኋለሁ፡ ከ
ስቃ፡ እንግዳ፡ ጋራ፡ ኑና፡ እንድንማክር፡ እነከንቲ
ባዎ፡ እናንተም፡

በመጋቢት፡ በ፲፭ ቀን፡ ዛርብ፡ ተጣፈ፡፡



እስካሁን ባነበብናቸው ደብዳቤዎች ሁሉ አጤ ቴዎድሮስ ሰም ጠሩ ብሎግና የሚሉት ብላንከን ፕሪዶን የሚሉት ፕሪዲውክስን ው። በኋላም የመጡት እንግሊዞችና የበፊተኞቹም እስረኞች ጭምር ቶላኩላቸው ጀልባዎች ሆነው ወደ ዘጌ ሔዱ። ቴዎድሮስ ከእስረ ቹ ጋር እንሰነባበት ያሉትን ሀሳብ ራሳም አልወደደውም። ምክን ቱም ቴዎድሮስ የሚጠሉዋቸውን ሰዎች ሲያዩ ምናልባት ይናደዱና ር ይበላሻል ብሎ ነው። ራሳም በዚህ ሐሳብ ላይ እያለ ከቴዎ ሮስ የተጻፈ ደብዳቤ ደረሰው።

ስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡
ጉሠ፡ ነገሥት፡ ቴዎድሮስ፡ ይድረስ፡ ካቶ፡ ሀርም
፡ ረስአም፡፡ እንዴት፡ ሰነበትህ፡ እኔ፡ እግዚአብሔ
፡ ይመስገን፡ ደህና፡ ነኝ፡ ሀኪም፡ ብሎ፡ ግን፡፡
ቶ፡ ፕሪዶን፡ ወንድሞችኽን፡ እንዴት፡ ሰነበ
ቻችሁ፡ አስ፡ በልልኝ፡፡ ሰላሰትና፡ ደህና፡ መግ
ቻችሁን፡ የሚጠይቅ፡ ደብዳቤ፡ ሠደኝ፡ ነበረ፡
ሳ፡ ግን፡ እነልጅ፡ አባተ፡ ደህና፡ መግባታችሁን
ጥተው፡ ነገሩኝ፡፡ በእግዚአብሔር፡ ኃይል፡ እ
ግ፡ ደስ፡ አለኝ፡፡ የነከንቲባ፡ ጉዳይ፡ ያዘዝኋ
ው፡ ደርሰላቸው፡ እንደሆነ፡ እንድትሰናበ
፡ ተሰናድታችሁ፡ ቆዩ፡ በእግዚአብሔር፡ ኃ
ል፡

መጋቢት፡ በ፳ ፪ ቀን፡ አርብ፡ ተጣፈ፡



ይህ ደብዳቤ እንደደረሰው የተጨነቀው ራሳም ለመስማመጥና በቴዎድሮስ ዘንድ ያለውን ፍቅር ላለማጣት ብሎ ካለችው ቅርስ እጀጠባብ ለቴዎድሮስ ላከ ። የራሳም ጭንቀት የቴዎድሮስ ጠባይ ተለ ዋዋጭ መሆኑን እስረኞቹ ነግረውታል ። አሁንም በመፈታታቸውም እርግጠኛ ሆነው አልተደሰቱም ። ምክንያቱም ቴዎድሮስ ከፉ ባላ ቸው ቀን መልሰው እንደሚያስሯቸው ስለሚያውቁ ነው ። ራሳምም ይሆን ሁሉ ለሚነግሩት እስረኞች ምንም አደጋ እንደማይደርስ ቢነ ግራቸውም እስረኞቹ አላመኑም ነበር ። ስለዚህ የራሳም ሥጋት እየበዛ በመሔዱ ለመስማመጥ ብሎ እስረኞቹ የሰጧቸውን እጀጠባ ቦች በሥጦታ መልክ አቀረበ ። አጤ ቴዎድሮስም ለተደረገላቸው ስጦታ ምሥጋና ሲያቀርቡ እንዲህ ብለው ጻፉ ።

በስመ፡ አብ፡ ወወልድ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡
ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ቴዎድሮስ፡ ይድረስ፡ ከአቶ፡ ሆረ
ሙዝ፡ ራስአም፡ እንዴት፡ ሰነበትህ፡ እኔ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ይመስገን፡ ደህና፡ ነኝ፡፡ ሀኪም፡ ብሉ
ንን፡፡ አቶ፡ ፕሪዶን፡ ወንድሞቼንን፡ እንዴ
ት፡ ሰነበታችሁ፡ እሰ፡ በሐልኝ፡፡ የሠደድህል
ኝ፡ እጀ፡ ጠባብ፡ በወና፡ ሞሀመድ፡ እጅ፡ ደረሠልኝ
፡ እግዚአብሔር፡ ይሥጥህ፡፡ ምነው፡ ዘሬማ፡ የ
ኔ፡ ሰንጋዳ፡ አይደለኸም፡ በተቻለኝ፡ እኔ፡
ልጨርሰ ነቀልህ፡ እንደ፡ አንተ፡ ለምን፡ ታሠባ
ለህ፡፡ እግዚአብሔር፡ ቢረዳህ፡ በምፈልገው፡
ጉዳይ፡ ትጨርስ ነቀልኝ፡ እንደ፡ እንግዲህ፡ በገ
ንዘብ፡ አትጨርሰ ነቀልኝ፡ አይረሱኸን፡ ወንድሞቺ
፡ ወገሬ፡ ጨጊፍ፡ አምባጨጊሬ፡ ሰይ፡ ጠፈነ ተ
ኞችን፡ ሣጠጡ፡ የኔ፡ ሰዎች፡ ይዘው፡ ደብዳ
ቤአቸውን፡ ቀምተው፡ ሰዎቹን፡ አስረው፡
፡ ደብዳቤውን፡ ሰደዱልኝ፡ በየሀ፡ የፈረን
ጅ፡ ጠሃፊነትም፡ ሆነ፡ ያገት፡ እንደሆነ፡ ብየ፡ ሣ



ልፈታ፡ ሠድጀልሃለሁ፡፡ ያገት፡ የሆነ፡ እንደ
ሆነ፡ ሰውየዉን፡ የማያስፈታ፡ ሠድጀልሃለሁ
፡፡ ያገት፡ ያልሆነ፡ እንደሆነ፡ ደብዳቤዉን፡ ምሠ
ለህ፡ ሥደድልኝ፡፡ እስረኞችም፡ ወደኔ፡ እንዲ
መጡት፡ አረጋለሁ፡፡ የኛንተ፡ ፋሲካ፡ ወደሬት፡
ሀየነን፡ ሣላው፡ እንደኛው፡ ፋሲካ፡ ነው፡ መ
ሰለኝ፡ ፍረዳ፡ ሠጡ፡ ብየ፡ ሐኬ፡ ነበረ፡ በወቅሁ
፡ የፋሲካችሁ፡ ለት፡ እንድታከብሩ፡ አረግ፡ ነበረ፡
መነው፡ ሣት ነገረኝ፡ ቀረህ፡ በእግዚአብሔር፡ ኃ
ል፡ በገዛ፡ ቤትህ፡ በገዛ፡ ወደጅህ፡ በገዛ፡ ወንድ
ምህ

## መጋቢት፡ በ፳፩ ቀን፡ ሰኞ፡ ተጣፈ፡፡



በደብዳቤው ላይ ራሳም የላከው አንድ እጀ ጠባብ ይመስላል ራሳም እንደሚገልፀው ግን 12 ያህል እጀ ጠባቦችና ሸሚዞችን ነው የላከላቸው ። መጋቢት ወር አልፎ ሚያዝያ እስቲገባ ማንኛ ውም ነገር በሰላምና በፍቅር ሲካሔድ ቆየ ። በሚያዝያ ወር እስረ ኞች የነበሩት በሙሉ ወደ አገራቸው እንዲሄዱ ተወስኖ ነበር ። ኤሮ ፓውያኖቹም ወደ አገራቸው ለመመለስ ጓጉተዋል ። ዘመዶቻቸው ንም ለመገናኘት ናፍቀዋል ። የበፊተኞቹ የቆዩት እስረኞች ቀር ተው በኋላ የመጡት እንኳ መናፈቃቸውን ብላንክ ሲጽፍ "... በውስጣዊ መንገድ የነበረውን ሁኔታ ስላልተረዳነው ማንኛውም ችግርና እንቅፋት የተወገደልን መስሎን ፍርሃታችንን ቀንሰን በአ

የር ላይ ግንብ መሥራት ጀመርን ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ አገ ራችን ተመልሰን ዘመድ ወዳጆቻችንን ለመገናኘት ንጉተን ሱዳን በረሃ ስናልፍ የሚገጥመንን ደካም ስንፈራ በድንገት ፕሮግ ራማችንና ፍላጐታችን በጭካኔ ተደምስሶ ሁኔታው ተለወጠ”ይላል፡፡ ብላንክ እንዳለው ሁኔታው ተለውጧል ፡፡ የሁኔታውንም መለ ወጥ ያጠራጠራቸው አጤ ቴዎድሮስ በድንገት የጻፉላቸው ደብ ዳቤ ነበር ፡፡

ከ ስመ፡ አብ፡ ወ ወል ድ ፡ ወመ ን ፈ ስ፡ ቅ ዱ ስ፡ ፩ አ ም ላ ክ፡
የ እ ግዚ አብሔ ር፡ ፍጡ ር፡ባር ያው፡ የ ዳ ዊ ት፡የ ሰ ሎ
ሞ ን፡ ል ጅ፡ን ጉ ሠ፡ ነገ ሥ ት፡ ቴ ዎ ድ ሮ ስ፡ ይ ድረ ስ፡
ከ እ ን ግ ሊ ዝ፡ን ግ ሥ ት፡ ሎ ሌ ፡፡ ከ ወ ዳ ጅ፡ ከ ግ ካ
ሬ የ፡ ካ ቶ፡ ህ ርም ዝ፡ ረ ስ አ ም፡ የ ምፈ ል ግ ው፡ የ ም ት
ል ክ ል ኝ፡፡ መ ድ ፍ፡ ሠ ሪ፡፡ ነ ፍ ጥ፡ ሠ ሪ፡፡ ብ ረ ት፡ እ ቀ
ላ ጭ፡፡ ቡ ም ባ፡ ተ ኳ ሽ፡፡ መ ድ ፍ፡ ተ ኳ ሽ፡፡ እ ኒ ህ፡ ሁ
ሉ፡ ሠ ራ ተ ኞ ቹ፡ አ ሣ ይ ተ ው ኝ፡ እ ን ዲ መ ለ ሱ፡ ክ ነ
መ ሣ ሪ ያ ቸ ው፡ ይ ም ጡ ል ኝ፡ በ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር፡
ኃ ይ ል፡፡ ይ ህ ን፡ ጥ ፈ ህ፡ ሳ ክ ል ኝ፡ በ እ ግ ዚ አ ብ
ሔ ር፡ ኃ ይ ል፡፡



አጤ ቴዎድሮስ እንደገና የሠራተኞቹን ጉዳይ ካነሱ ሠራተኞቹ እስቲመጡ ድረስ እነኝህንና እንደመያዣ ሆነው እንደሚቆዩ ገባቸው ፡፡ እንዳንዶቹም ምህረት ተደርጐልን ስለተሰቀቅንና እንድ ንሔድም ስለተፈቀደልን የደብዳቤው ጥያቄ ከሔድን በኋላ የሚፈ ፀመውን ነው በማለት ተናገሩ ፡፡



ለእስረኞቹ የተፈቀደላቸው የመሔጃ ጊዜ ስለደረሰ እስረኞች በሩት ሰዎች በሙሉ ከቴዎድሮስ ሳይሰናበቱ ጉዞ እንዲጀምሩ ርጐ ራሳም ግን ቴዎድሮስን ተሰናብቶ እንደሚደርስባቸው ገለ ሌሎቹ ጉዞአቸውን ጀመሩ ፡፡ ራሳምና አብረውት የመጡት የኋለ ው ጊዜ መልከተኞች ግን ለመሰናበት ከቴዎድሮስ ፈቃድ ጠይ ውና ተቀብለው ወደ ዘጌ ሔዱ ፡፡

እርብ ዕለት ዘጌ ሲደርሱ ከፍ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው ፡፡ እንግዳ ከሌሎች መኳንንቶችና ሠራዊት ጋር ሆነው በዘጌ ወደብ በሉዋቸው ፡፡ ከዚያም ምርጥ በሆነ ዕቃ ባጌጡ በቅሎዎች ተቀም ው ወደ ንጉሱ ሠፈር ሔዱ ፡፡ ከቴዎድሮስ አዳራሽ ደርሰው ሲገቡ ዳራሹ ውስጥ ብዙ ወታደሮችና መኳንንት ቆመዋል ፡፡ ቴዎድ ግን የሉም ፡፡ ፈረንጆቹም ለቴዎድሮስ ዙፋን እጅ ነስተው ቆም ዳሉ ወታደሩ እየተነባበረ እነራሳምን እያነቀ ያዛቸው ፡፡ ታጥቀ ት የነበረውንም ዝናርና ጐራዴ ፈትተው ወሰዱባቸው ፡፡ ልብ ውም ተቀዳደደ ፡፡ ከመሬት ላይ አስተኝተው ያዙዋቸው ፡፡ ከጥቂት ሽብር በኋላ ይቀመጡ ተብለው እጅ እጃቸውን ከያዛቸው ወታ ጋር ከመሬት ከተነጠፈው ምንጣፍ ላይ ተቀመጡ ፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ መጥተው ከዙፋቸናው ላይ ቀምጠው “እስረኞቹ የታሉ? ለምን ወደኔ አልመጡም? እኔ ሳልፈቅድ ስደድ አይገባችሁም” እያሉ ጠያይቀው በመጨረሻው “ወንድ ቻችሁን ለማስመጣት ልኬአለሁና እነሱ ከመጡ በኋላ የሚሆረገ ን እነግራችኋለሁ” አሉዋቸውና ጥቂት እልፍ ብሎ ከተተከለላ ው ድንኳን ውስጥ እንዲገቡ አዘዙላቸው ፡፡

ወዲያውኑም ሌሎቹ እስረኞች የነበሩት ኤሮፓውያን ተይዘው ንዲመጡ ለቢትወደድ ተድላ ደብዳቤ ተጻፈላቸው ፡፡ ደብዳቤውም በመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ንጉሠ ሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ከቢትወደድ ተድላ ፡፡ እንዴት ከርመ ል ፡፡ እኛ ደህና ነን ፡፡ ከወዳጆቻችንና ወደ አገራችን እንሔዳለን ሉት አይሮጳውያን ጋራ ተቀያይመናል ፡፡ እሱም ገና እርቅ ባለማ ኃችን ነው ፡፡ በነገሩ መከረን የምናደርገውን እስከ ወበንን ድረ ሰዎቹን ያዟቸው ፡፡ ግን ጉዳት እንዳይደርስባቸውና እንዳይፈሩ ሁን” የሚል ነበር ፡፡

እስረኞች የነበሩት እንደገና ተይዘው ሚያዝያ 9 ቀን 1858 ዓ.ም. ሰኞ ዕለት ዘጌ ደረሱ ፡፡ እንደደረሱም ሁሉም በአንድነት

ሆነው ከቴዎድሮስ ችሎት ቀረቡ ። አጤ ቴዎድሮስም "እኔን ለምን ሳትሰናበቱና ሳታስፈቅዱኝ ከአገሬ ለመውጣት ሞከራችሁ?" ብለው ጠየቁ ። እስረኞቹም ግርማዊነትዎ ለሚስተር ራሳም ስለሰጡን ሚስተር ራሳም ባዘዘን መሠረት ነው የሔድነው ብለው መለሱ ።

"ታዲያ ለምንድነው ረምሀዝ ወደኔ አምጥቶ እንዳያስታርቃችሁና እንዳያስናብታችሁ ያልጠየቃችሁት?"ብለው ወደራሳም ዞር አሉና "ይህ ከሆነ ጥፋቱ ያንተ ነው ። ከነዚህ ሰዎች ጋር እንድታስታርቀኝ ነግሬህ አልነበረምን ? ለምንድነው በዚህ መሠረት ያልፈፀምከው?"ብለው ጠየቁት ። ራሳምም "ከእነዚህ ሰዎች ፍርድ በኋላ በላኩልኝ የይቅርታ መጠየቂያ ደብዳቤ እርቁ የተፈፀመ መስሎኝ ነው" አላቸው ።

አጤ ቴዎድሮስም "ለእነዚህ ሰዎች መጓጓዣ የሚሆን በቅሎና ለስንቃቸውም ገንዘብ ልስጣቸው ብልህ በቅሎም ገዝቼላቸዋለሁ ። ለስንቃቸውም በቂ ገንዘብ አለ አላልከኝም? እነዚህን ሰዎች ከአበሻ አገር በልዩ መንገድ ለማውጣት ፈልገህ ከነገርከኝ ቀን ጀምሮ ባንተ ላይ ጥርጣሬ አድሮብኛል ። አገርህ ስትገባ እነዚህን ሰዎች በሰላም አሰፈትተህ የወሰድካቸው መሆኑን ትተህ በተንኮልና በዘዴ እንዳወጣሃቸው አድርገህ ለመፎከር መሰለኝ ።...." አሉትና ያለምንም ውሳኔ የተሰበሰበውን ጉባኤ በትነው ተነሱ ።

በማግስቱ ሁሉም የታሰሩበት ሰንሰለት እንዲወልቅላቸው ተደርጎ ከአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ ቀረቡ ። በዚህኛው ችሎት አጤ ቴዎድሮስ ፈረንጆቹን ሁሉ ቀረብ በሉ ብለው እንዲቀመጡ ከፈቀዱላቸው በኋላ" .... በእናንተ ላይ እንድናደድና በጥላውዲን ጊዜ በኔና በእንግሊዝ መሀል የነበረውን መልካም ወዳጅነት እንዲበላሽ የሚያደርገው ሰይጣን ነው ። ከልጅነቴ ጀምሮ ኤሮፓውያኖችን እወዳለሁ ። በተለይም እንግሊዞችን ። እግዚአብሔር በሚያውቀው ከጧት እስከ ማታ የማስበው ከእንግሊዝ ሕዝብ ጋር ያለኝን ወዳጅነት ለማጠንከር ነው ። የማይካደው ነገር ቱርኮችን እዋጋለሁ ። ነገር ግን እንግሊዞችን ለመዋጋት ፈፅሞም በአእምሮዬ የለም ። የምመኘው እንዲወዱኝና ወዳጆቼ እንዲሆኑ ነው ።

"አቶ ኮከብ (አስተርን) የዋህ ገራገር ሰው ነህ ። አንተ አይደለህም የሰደብከኝ ። የሰደበኝ እሱ ነው ። አቶ ፍላድም እግዚአብሔር በሚያውቀው በሱ ላይ መጥፎ ሐሳብ የለኝም ። ከኔ ጋር የሚያቀያ



ሙው አንድም መጥፎ ነገር አልሠራም ። አቶ ራሳም በሕይወቴ ካጋጠሙኝ ጥሩ ሰዎች አንዱ አንተ ነህ ። እንድቆጣ የሚያደርግ ምንም የሠራኸው ነገር የለም ። እርግጥ አንድ ቀን በነገርህ ግልፍ ብሎኛል ። ይህንንም ያደረገው ሰይጣን ነው ። አሁን እንግዲህ ሰላም እንመሠርታለን ። ያለፈውን ነገር እንርሳው ። በፍቅር ወዳጅነታችንን እናድሳለን" .... ብለው ተናገሩ ።

አጤ ቴዎድሮስ ይህን ንግግር ካደረጉ በኋላ ከዙፋናቸው ተነስተው ይቅርታ ጠየቁ ። እስረኞቹም ተጠያቂዎች ሳይሆኑ እነርሱ ይቅርታ እንዲያረግላቸው ለመኑ ። አጤ ቴዎድሮስ ግን ኤሮፓውያኖቹ ይቅርታ እንዲያደርጉላቸው ወጥረው ስለያዙ ፈረንጆቹ እንደ አገራችን ባህል "ለእግዚአብሔር ብለን ይቅር ብለናል" ብለው ተናገሩ ። ይህንንም ብለው ወዲያው ሁሉም ተንበርክከው ለሥሩት በደል አጤ ቴዎድሮስ ይቅርታ እንዳያደርጉላቸው ለመኑ ። እሳቸውም "ለእግዚአብሔር ብዬ ይቅር ብያለሁ" አሉና ቀቀመጡ አሏቸው ።

ከዚህ በኋላ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ንግሥት የሚላከውን ደብዳቤ መጻፍ ጀመሩ ።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አ
ምላክ። የእግዚአብሔር፡ፍጡር፡ባርያው፡የጸ
ዋት፡የሰሎሞን፡ልጅ፡ንጉሠ፡ነገሥት፡ቴዎ
ድሮስ። ይድረስ፡እግዚአብሔር፡ከሰው፡ሁሉ፡
መርጦ፡አልቆ፡ካነገሣቸው። ሃይማኖት፡ፍቅር፡ከሚ
ወዱ። የተጠቃ፡ድሀ፡ከሚጠብቁ። ከእንግሊዝ፡ን
ግሥት፡ከቤክቶርያ። ። እቶ፡ህርምዝ፡ረስእምን፡
ሉሌዎን። በኬምሮን። ኍዳይ፡ሰድድዋስሁ። ደሉ
ኝን፡እንኳን፡እርሰዎ፡የባርያዎ፡ባርያ፡ቢልክብኝ።
እምቢ፡እላለሁ። እሺ፡እነሆ፡በእግዚአብሔር፡ኀይ
ል። እቶ፡ኬምሮንን፡ፈትቸ፡በሉሌዎ፡ለእቶ፡ህር
ምዝ፡ረስእም፡ሰጠሁ። የአይሮጳ፡ሰዎች፡ሁሉ፡የ
ታሰሩትን። ፍታልኝ፡ያሉኝን። በእግዚአብሔር፡ኃይል፡ፈ.

ትቸ፡ሃንዱ፡ሠጠሁ፡፡የእዮሮጳግ፡ሰው፡ሁሉ፡፡ወዴ፡
አገሩ፡መመለስ፡የሚኔምረውን፡በእግዚእብሔር፡
ኃይል፡፡እሺ፡ሠጠሁ፡፡እቶ፡ሀርምዝ፡ረስአምን፡ኩ
ሌምሃ፡ያስነበትሁት፡ከኛ፡የምትፈልገውን፡ሁሉ፡
ጉዳይ፡ከርሱ፡ጋራ፡ተማከር፡ባሉኙ፡ረሃዴ፡፡ከርሱ፡
ጋራ፡እየተማከርሁ፡፡እልክብዎ፡ብየ፡ነው፡፡ ፡፡የኢ
ትዮጵያ፡ሰዎች፡እውር፡ነንና፡ዓይናችነን፡ያብሩል
ን፡፡እግዚአብሔር፡በሰማይ፡ያብ●ራስዎ፡፡ ፡፡ ፡፡
በ፯ሺ ተ፫፻፶፰ ዘመን፡ዓለም፡ከተፈጠረ፡፡

ክርስቶስ፡በተወለደ፡በሺ፡ተ፰፻፶፰ ዘመን፡
በዘመነ፡ማርቆስ፡በወርኃ፡ሚያዝያ፡በ፲ ቀን፡፡
ዘጊ፡ሳይ፡ተጣፈ፡፡ ፡፡



በደብዳቤው እንዳየነው አጤ ቴዎድሮስ ራባምን ለማስቀረት ወስነዋል ፡፡ “ . . . . እውር ነንና ዓይናችንን ያብሩልን . . . . ”ባሉት መሠረት ኢትዮጵያውያን በዘመኑ ከዓለም ሥልጣኔና ጥበብ ተለይተው ሳያዩም ሳይሰሙም ይኖሩ ስለነበረ በዓለም ያለውን ጥበብ በራስም አማካይነት በእንግሊዝ መንግሥት ረዳትነት ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት አስበው ነው ፡፡ ሆኖም ይህ ድርጊት ወይም የራሳም በኢትዮጵያ መቅረት በትርጉም ስህተት የመጣ እንጂ ንግሥት ቢክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ ራሳም በኢትዮጵያ ቀርቶ ጉዳይ ፈፃሚ ይሁን አላሉም ፡፡ ራሳምም ቢሆን የሚያውቀው የንግሥቷን ደብዳቤ አድርሶና እስረኞቹን አስፈትቶ መመለስ እንጂ የመቅረቱን ጉዳይ በውኑም በሕልሙም አላሰበውም ፡፡ አጤ ቴዎድሮስም ከበፊቱ እንዲህ ዓይነቱን የመቅረት ነገር እንስተውበት ቢሆን ምናልባትም ኣንድ ስምምነት ወይም የመግባቢያ ቋንቋ ሊፈጠር በቻለ ነበር ፡፡



አጤ ቴዎድሮስ ለንግስት ቢክቶሪያ ደብዳቤ የጻፉ ዕለት ራሳምም ለእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አንድ ደብዳቤ ጻፈ ፡፡ እፕሪል 18 (በኛ ሚያዝያ 10) ቀን 1866 (በኛ 1858) ዓ.ም. ራሳም የጻፈው ደብዳቤ እንዲህ የሚል ነበር ፡፡

“ . . . . ከዶክተር ብላንክና ከሚስቶር ፕሬደውክስ ጋር ሆነን ጃንዋሪ 28 ቀን ከአበሻው ንጉሠ ነገሥት ዘንድ ደረስን እንደደረስንም ንጉሠ ነገሥቱ በታላቅ ክብር ተቀበሉን ፡፡ በመንከባከብና በቸርነትም አቆዩን ፡፡ የንግሥትንም ደብዳቤ በአክብሮት ተቀበለው በመንከባከብና በቸርነትም አቆዩን ፡፡ የንግሥትንም ደብዳቤ በአክብሮት ተቀብለው የከበረ መልስም ጽፈዋል ፡፡ . . . . ”ብሎ የተደረገውን አቀባበልና መስተንግዶ ከገለፀ በኋላ “ . . . . ንጉሠ ነገሥቱ ስለጉዞዬ ወጭ 10,000 ብር ሰጡኝ ፡፡ በደግነትና በእንክብካቤም ይዘውኛል ፡፡ . . . . የልዑላኖች በቅሎ ኮርቻ ፣ ጋሻ ፣ ጐራዴና ጦር ሰጥተውኛል ፡፡ አብረውኝ ላሉትም ጋሻ ጦርና የተለያዩ ሥጦታዎችን ሰጥተዋቸዋል ፡፡ በተጨማሪም አምስት በቅሎዎች ሰጥተውናል ፡፡ . . . .

“ንጉሠ ነገሥቱ ከጥቂት ዓመታት በፊት ጀምሮ ጠቢባን ሰዎችን ከእንግሊዝ አገር ለማስመጣት ይፈልጋሉ ፡፡ ትናንትናም ስንነጋገር ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች እንዲመጡላቸውና መድፍ ፣ ጠመንጃና ጥይት እንዴት እንደሚሠራ ፣ ብረት እንዴት እንደሚቀልጥ ሰዎቻቸውን እንዲያስተምሩላቸው መፈለጋቸውን ነገሩን ፡፡ እንዳሉትም እነኚህ ሰዎች ሲመጡ የሚያስፈልገውን ዕቃና መሣሪያቸውን ሁሉ ይዘው እንዲመጡና ሰዎቻቸውን ካስተማሩም በኋላ በደህና ወደአገራቸው እንደሚመለሱ ነገሩኝ ፡፡ . . . . ለክቡርነትዎ የማሳስበው . . . . ከዚች አገር ጋር ለወደፊቱ ጥሩ ወዳጅነት እንድንመሠርት ነው ፡፡

“የግርማዊት ንግሥት መንግሥት ፈቃዱ ሆኖ አንድ መቶ ሺ የተለያዩ ጥይቶች ጥቂት ባለሁለት አፍ ጠመንጃዎች ፣ ሽጉጦች ፣ ንጉሱ በባሕሮች ላይ የሚሔዱበት አንድ ጀልባና የሚሆነውን ነገር ሁሉ ይህን ደብዳቤ ባመጣው በሚስተር ፍላድ እጅ እንዲላክልኝ አሳስባለሁ ፡፡

“የግርማዊት መንግሥት ጠቢባኖቹን ለመላክ ፈቃዱ ከሆነ ሰዎቹ እዚህ በሚመጡበት ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱ ሠራተኛ ሆነው

ቢያንስ አንድ ዓመት እንደሚቆዩ. . . . ሲነግራቸው መልካም ነው . . . . የሚል ነበር ።

ይህንና አጤ ቴዎድሮስ ለንግስት ቪክቶሪያ የጻፉትን ደብዳቤ አቶ ፍላድ እንዲያደርስና መልሱን ይዞ እንዲመጣ ተመርጧል ። ፍላድ ደብዳቤዎችን ይዞ ከመሔዱ በፊት ከንጉሱ ለመሰናበት ከራሳም ጋር ሆነው ወደ አጤ ቴዎድሮስ ድንኳን ሳይታሰቡ ከራሳም ዘንድ መጡ ። እንደመጡም ከራሳም ድንኳን ሲገቡ የራሳም ድንኳን ምንጣፍ የሌለበት ሸለነበረ በአስቸኳይ ምንጣፍ እንዲመጣ አዘዙ ። ምንጣፉ እንደመጣም ከራስ እንግዳና ከአቶ ሳሙኤል ጋር ሆነው ራሳቸው ቴዎድሮስ ምንጣፎቹን አነጠፉ ። ምን ያህል ትሁት ንጉሱ መሆናቸውንም ለፈረንጆቹ አሳዩ ። የብላንክና የፕሪዲውክስ ድንኳኖችም እንዲነጠፉ አዘዙ ። ጥቂት ተጨዋውተውና ፍላድን ተሰናብተው ሲሔዱ ሲነሱ ራሳም ቀረብ ብሎ እስከ ቤታቸው ለመሸኘት እንዲፈቅዱለት ለመናቸው ። ቴዎድሮስም "ማለፊያ ነው ፤ በልና" ብለው እጅ ለእጅ ተያይዘው ይጓዙ ጀመረ ።

ከራሳም ጋር እጅ ለጅ ተያይዘው እየተጫወቱ ሲሔዱ ከፈረንጆች ሠፈር ሲወጡ ሲሉ የፈረንጆቹን ጠባቂ ራስ ወልደ ማርያምን ቆመው አገኙዋቸው ። ቴዎድሮስም ቆም አሉና "ምን ታደርጋለህ?" ብለው ጠየቋቸው ። ራስ ወልደ ማርያምም "እየጠበቅሁ ነኝ" ብለው መለሱ ። ቴዎድሮስ ይህን መልስ እንደሰሙ ቆጣ ብለው "ምን! ወዳጄን ራሳምን ነው የምትጠብቀው? በል አሁን ከዚህ ሂድ ። እሱን የምፈራበት ምንም ነገር የለኝም "ብለው በእጃቸው ወደራሳቸው አፍ እየጠቆሙ" እየው ። እዚህ ውስጥ የሽጉጥ አፈሙዝ ሲያስገባ እንኳ አልጠረጥረውም" አሏቸው ። ጥበቃው ግን ላላ እንጂ ጨርሶ አልተነሳም ።

አቶ ፍላድ እንግሊዝ አገር ሔዶ መልሱን ይዞ እስኪመጣ ድረስ ኤሮፓውያኖቹ በሙሉ በመያዣ ስም እንደሚቆዩ ተነግሮአቸዋል ። ፍላድም ቀደም ብለን ያነበብናቸውን ደብዳቤዎች ይዞ ሚያዝያ 20 ቀን 1858 ዓ.ም. የእንግሊዝ አገር ጉዞውን ጀመረ። መጀመሪያ ወደ ኤደን ሔደ ። በዚያም ሲመካከር ቆይቶ በሐምሌ ወር እንግሊዝ አገር ገባ ።

የዚያን ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት ከከባድ ችግር ላይ የወደቀበት ዘመን ነበር ። የፑርሲያና የኦስትሪያ ጦርነት በመነሳቱ የእ



ግሊዝ መንግሥት ተወጥሯል ። በእንግሊዝ አገር ላይም በደረሰው
ንዘብ ችግር ከከባድ ፈተና ወድቋል ። ይህ ብቻ ሳይሆን እንግሊዝ
ር ከባድ የከብት እልቂት የደረሰበት ዘመን ነበር ። በእነዚህ
ሉ ችግሮች ለተዘፈቀችው እንግሊዝ ከቴዎድሮስ የተላከው አቶ
ላድ ተመልካችም ሆነ ጉዳዩ ከብደት አጣ ። ቢሆንም ፍላድ ጣልቃ
ገባ ራሳምም ሆነ ሌሎቹ እስረኞች ተለቀው በጥሩ ሁኔታ
 እንደሚገኙ እያስረዳ እንደገና ነገሩ ከመበላሸቱ በፊት የቴዎ
ሮስ ጥያቄ እንዲሟላ ይወተውት ጀመር ። በመጨረሻውም የእን
ሊዝ መንግሥት መሪ የሆነው ሎርድ ደርቢይ በቴዎድሮስ የጠ
ቡን መላክ ጥያቄ ተስማምቶ በንግሥቲቱ ስም ደብዳቤ እንዲፃ
 ቴዎድሮስ የጠየቋቸውም የጅ ሥራ አዋቂዎች እንዲላኩላቸው
በነ ።

ፍላድ በውሳኔው ተደስቶ የመመለሻ ጉዞውን በሚያዘጋጅበት
 ተለቀው የነበሩት እስረኞች እንደገና ደብረ ታቦር ላይ በሙሉ
ሩ የሚሉ ወሬ እንግሊዝ አገር ደረሰ ። ይህም ወሬ ደህና አዝ
ሚያ የያዘውን የፍላድን ጉዳይ አደፈረሰው ። ኤሮፓውያኖቹም
ምልሰው እንደገና በቴዎድሮስ መታሰራቸው ወሬ ሳይሆን እርግጥ
ላድ ነበር ።

አጤ ቴዎድሮስ ፈረንጆቹን መልሰው ያሠሩበት ምክንያት ኢየ
ሌም ደርሰው የሚመለሱም ሆኑ በዚያው በኢየሩሳሌም የሚ
 ሰዎች በሚልኩላቸው መልዕክት ወይም በሚነግሩዋቸው ዜና
ንግሊዞች ከሱአኪን ከሰላ ድረስ የባቡር ሐዲድ እየዘረጉ ናቸው።
ም እንግሊዞች ከቱርኮች ጋር መስማማታቸውንና ወዳጅነታቸ
 ያሳያል ። ተባብረውም ሊወጉዎት ነው" እያሉ ይነግሩዋቸው
ር ። ከዚህም ሌላ ምፅዋ የሚኖረው ወዳጃቸው የሆነው ፈረንጅ"
 ራሳም ተላከሁ የሚለው ውሸት ነው እንጂ እውነት አይ
ም ። እንግሊዞችም ቢሆኑ የሚፈልጉት የተያዙባቸው ሰዎች እንዲ
ቁላቸው ነው እንጂ ስለእርሶ ጉዳይ ሐሳብም የላቸው" ብሎ
ጻፈላቸው ነበር ።

ተለቀው የነበሩት እስረኞችም ፍላድ እስኪመለስ በሰላምና
ቅር እንዲያውም በቅሎ ከነጌጠቻቸውና ሌላም ሽልማት ተሸ
ው በሰላም ጋፋት ሔደው መኖር ሲጀምሩ ቴዎድሮስ እንዲህ
 ወሬ በመስማታቸው ሰኔ 18 ቀን 1858 ፈረንጆቹን ከጋፋት
 ደብረ ታቦር ጠሩዋቸው ። ደብረ ታቦርም ከአጤ ቴዎድሮስ

ሠፈር እንደደረሱ በአንድ ድንኳን ውስጥ እንዲያርፉ ተደረገ ። ጥቂት ቆይቶም ራስ እንግዳ ፣ ከንቲባ ኃይሉና አቶ ሣሙኤል ወደ ፈረንጆቹ ዘንድ ተልከው መጥተው የቴዎድሮስን የመልዕክት ጥያቄ አቀረቡ ። ጥያቄውም "ቱርክ በእንግሊዝና በፈረንሲስ መንግሥት እየተረዳች እገሬን ለመውጋት አስባ በሱዳን በኩል የባቡር ሐዲድ የተዘረጋው በእንግሊዞች እጅ አይደለምን ። ቆንሲል ኪምሮን ለእን ግሊዝ ንግሥት እንዲያደርሱልኝ የጻፍኩትን ደብዳቤ ከሰጠሁት በኋላ መልስ ሳይዝልኝ ተመልሶ የመጣውስ በዚያው አይደለምን ? በጻፍኩትም ደብዳቤ የእንግሊዝ መንግሥት የሳቀበት መሆኑን አቶ ሮዚንታል ፣ ነግሮኛል ። ስለዚህ እኔ ወዳጅነታችሁኝ ስፈልግ እና ንተ ጠላቴ እየሆናችሁ ከጠላቶቼ ጋር ከተባበራችሁ በእጃችሁ ያለ ውን የጦር መሣሪያ ስጡና ከዚሁ እንድትቆዩ ብለዋችኋል"ብለው ነገሩዋቸው ። ፈረንጆቹ ደብረ ታቦር ላይ በእስር ስም እንዲቆዩ ተደ ረገ ። ስሙ እስር ይባል እንጂ የደብረ ታቦሮቹ እስከ ጋፋት ድረስ እየሔዱ ጋፋት ከቀሩት ፈረንጆች ጋር ሲጫወቱ እንዲውሉ ተፈ ቅዶላቸው ነበር ። በኋላ ግን በአመላቸው እስራታቸው ጠበቀባቸው።

አንድ ቀን በሰኔ ወር ማለቂያ ገደማ አጤ ቴዎድሮስ በጋፋት የሚሠራውን ሥራ ለማየት ወደ ጋፋት ሔዱ ። በጋፋት ያለውንም ብረት ማቅለጫ ሲጐበኙ ፈረንጆቹም አጅበው እየተከተሉ ይሔዱ ነበር ። ፈረንጆቹ በሙሉ ባርኔጣቸውን አውልቀው በእጃቸው ይዘው ሲጓዙ ሁለቱ ፈረንጆች ግን ባርኔጣቸውን እንዳደረጉ ይከተሉ ነበር ። ቴዎድሮስም ፈረንጆቹን ስለ ጤንነታቸው ሁሉ እየጠየቁ ተጓዙ ። ከብረት ማቅለጫው ቤት ሲገቡ በዚያው ያሉት ሁሉ እጅ ሲነሱ ሮዜንታል እጅ ሳይነሳ ቀረ ። ይህን ሁሉ ድርጊት ቴዎድሮስ ያላዩ መስለው አይተዋል ። ግን ምንም አልተናገሩም ።

የብረት ማቅለጫውን ጐብኝተው ሲወጡ አንድ ሰው"ጃንሆይ። እነኝህ ፈረንጆች ጌቶቼ ሁል ጊዜ ይረዱኛል ። ደጐች ናቸው ። እር ስዎም ካለሁበት ችግር እንድወጣ ይርዱኝ" ብሎ ለመናቸው ። የዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ ክፉኛ ተቆጥተው "እንዴት ከኔ ሌላ ሌሎች ንም ሰዎች ጌቶች ይላል? በሞቴ በልልኝ" ብለው ያን ደሃ አስደ በደቡት ። ከዚያም ጥቂት እርምጃዎች ሔድ ብለው በድንገት ቆሙና ወደ ሮዜንታል ዞር ብለው ያዘው" ሲሉ ወታደሮቹ ሮዜ ንታልን ተረባርበው ያዙት ። ሌሎች ደግሞ በዚያው በአጠገባቸው ያገኙትን ዶክተር ብላንክን ወጥረው ያዙት ።



አጤ ቴዎድሮስ ወደ ሮዜንታል እየተመለከቱ "አንተ አህያ ለምንድነው የድሃ ቤት ልጅ ነው ያልከኝ" ብለው በቁጣ ጠየቁት። ሮዜንታልም በፍርሃት እየተንቀጠቀጠና የውጥር እንደተያዘ "ጃን ሆይ ። እርስዎን በድየና አዋርጄ ከሆነ ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ እለምናለሁ ።"አለ ። ሮዜንታል ፈርቶ የሚንቀጠቀጥበት ምክንያት ቴዎድሮስ ጥያቄ ባቀረቡበት ጊዜ ጦራቸውን በእጃቸው ይሰብቁ (ይነቀንቁ) ስለነበረ ነው ።

ሮዜንታልን ከጠየቁና የሚለውን ከ ሰሙ በኋላ ወደ ሌሎቹ ኤሮፓውያን ዞር ብለው "እናንት ባሮች ። በገንዘቤ አልገዛኋችሁ ምን ። እረ እናንተ እነማን ናችሁ ጌቶች ተብላችሁ የምትጠሩት ። ተጠንቀቁ" አሏቸው ። ከዚያም ባርኔጣ አድርገው ወደ ተከተሏቸው ፈረንጆች ዞር ብለው"ኩራት አልተሰማችሁምን ። ባሮች ፣ ሴቶች አህያዎች ። ከኔ ጋር እየሔዳችሁ ባርኔጣችሁን ታደርጋላችሁ ? እኔ አብሬአችሁ እንዳለሁ አላያችሁምን ፣ ደግሞስ ሐኪሙ (ዶክተር ብላንክን ነው) ባርኔጣውን በእጁ ይዞ ሲያጅብ አላያችሁምን ።

እኔ አይደለሁም እንዴ ሀብታም ያደረግኋችሁ ። እናንተማ ድሆች አልነበራችሁምን? " ብለው ከወቀሷቸው በኋላ ሁሉም በወታደር እንደተያዙ እየተገፉና እየተጐተቱ ጉዞው ወደ ደብረታቦር ቀጠለ ። ባርኔጣውን በእጁ ይዞ ላጀባቸው ለዶክተር ብላንክ ግን የከንቲባ ኃይሉን በቅሎ አስጥተው በማዕረግ እንዲከተላቸው አደረጉ ።

ደብረ ታቦር እንደገቡ አቶ ራሳምና በዚያ የነበሩት ኤሮፓው ያኖች ከሜዳ ላይ እንዲሰበሰቡ አድርገው እሳቸውም ከአንድ ድን ጋይ ላይ ቁጭ አሉ ። ዙሪያውም በመኳንንትና በወታደሮቻቸው ተከበቡ ። አጤ ቴዎድሮስም በያዙት ጦር ጀንፎ (እጀታ) ድንጋ ዩን እየደበደቡና እየሰባበሩ ወደ እስተርን እየተመለከቱ "የክርስ ቲያንን የአረመኔ ወይስ የይሁዲ ባህል ነው እንድትሰድበኝ የሚ ፈቅድልህ ? ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሆነ በየትኛው ሥፍራ ላይ ነው ሰውን እንድታዋርድ የሚፈቅድልህ? እንዲያው ለመሆኑ መጽሐፉን ስትፅፍ ፈቃድ የሰጠህ ማነው? እረ እንዲያው ማነው! ይህን እኔን የሚያንቋሽሽ ታሪክ የነገረህ? በል ንገረኝ"አሉ ። እስ ተርን ለመመለስ ሲዘጋጅ ቴዎድሮስ ወደ ራሳም ዞር አሉና "አን ተም ብትሆን በድለኸኛል" ብለው ሊነግሩት ሲጀምሩ ራሳም ክፉኛ ደንግጦ ከንግግራቸው መሀል ገባና "እኔ? ጃንሆይ እኔ " አላቸው ።

አጤ ቴዎድሮስም "አዎን አንተ እንተው ራስህ ። ያውም የበ

ደልኸኝ አራት ጊዜ ነው ። ስማኝ ልንገርህ ። መጀመሪያ ነገር አቶ
ኮከቤ እኔን ሰድቦና አዋርዶ የጻፈውን መጽሐፍ አነበብክው ።
ሁለተኛው ነገር ከእስረኞቹ ጋራ ሳታስታርቀኝ ከአገር እንዲወጡ
አድርገህ ልታስወጣቸው ነበር ። ሶስተኛው በደል ያንተ አገር
መንግሥት ኢየሩሳሌም ቁርኮች እንደተያዘች እንድትቆይ ፈቃዱ
ሆነ አራተኛው ምን ነበር ! ይሁን ብቻ አሁን ረስቸዋለሁ ። ግን
የምልህ ኢየሩሳሌም የኔ መሆኗን ታውቃለህ በዚያም ያለው ጽላት
በቁርኮች መያዙንም ታውቃለህ? ወይስ አላውቅም ልትል
ነው ። ''ብለው ለጥቂት ጊዜ ዝም አሉ ።

ከዚያም አስተርጓሚውንና ፀሀፊያቸውን አቶ ሣሙኤልን "እነ
ዚህን ወዳጆችህን ባስራቸው ምን ታስባለህ" ብለው ጠየቁት ።
አቶ ሣሙኤልም "ጃንሆይ ። እርስዎ ያውቃሉ እንጂ እኔ ደግሞ ምን
አውቃለሁ ። ምንስ አስባለሁ ። አዛዣችን እርስዎ አይደሉምን"
ብሎ መለሰ ። ከዚህ በኋላ ማሰሪያውን አምጣልኝ ብለው እግር ብረ
ትና ሰንሰለት ቀረበ ። ከቀረበ በኋላ ወደ አንዱ የጦር መኰንናቸው
ዞር ብለው "እነኝህን ሰዎች በድንኳናቸው ውስጥ ሆነው ልት
ጠብቃቸው ትችላለህ ወይስ አትችልም ።" ብለው ጠየቁት ።
ሰውየውም "ጃንሆይ ። ከድንኳን ይልቅ በቤት ውስጥ ሆነው ቢ ጠ
በቁ ይሻላል" ብሎ ስለመለሰ "መልካም ነው "ብለው ወዲያው
ካንድ ከቤተ መንግሥቱ ቅርብ ከሆነ ቤት ተወስደው እንዲታሠሩ
አዘዙ ።

የታሰሩበት ቤት አየር መግቢያ መስኮት እንኳ የሌለው
ስለነበረ አቶ ራሳም ተበሳጭቶ አንድ መልክተኛ ወደ አጤ ቴዎ
ድሮስ ሲልክ "በጃንሆይና በእንግሊዝ መንግሥት መካከል ወዳ
ጅነት እንዲፈጠር ለማድረግ በቻልኩት ሁሉ ደክሜአለሁ ።
አሁን ግን በኛ ላይ የደረሰውን በደል የእንግሊዝ መንግሥት በሚያ
ውቅበት ጊዜ በሚመጣው ነገር ጃንሆይ እንዳይወቅሱኝ ብለህ ንገ
ራቸው" ብሎ ላከ ። አጤ ቴዎድሮስም ለራሳም መልስ ሲልኩ"
በመጥፎም ሆነ በመልካም ብይዛችሁ እንግሊዞች ጠላቶቼ በመሆ
ናቸው አጉላላቸው ማለታቸው አይቀርምና ምንም አይደለም አር
ፈህ ተቀመጥ" ብለው ላኩበት ።

የቴዎድሮስ ጠባይ ተለዋዋጭ ነው ተብሏል ። በጠባያቸው መለ
ዋወጥም እጅግ በጣም ክፉ የሆኑት ሰው የዚያኑ ያህል ደግሞ
እጅግ በጣም ደግ ሰው ሆነው ይገኛሉ ። እንዲያ ተጣልተውና ሰድ
በው ካሠሩዋቸው ፈረንጆች ዘንድ አንድ ቀን ማታ ጠጅና አረቄ



አስይዘው እስረኞቹ ካሉበት ቤት ገቡ ። ከዚያም ተቀምጠው ጠጅና
አረቄው እየተጠጣ ሲጫወቱ "ሚስቴ እንኳ በአሁኑ ጊዜ ከቤት
እንዳልወጣ አጥብቃ ብትነግረኝም እናንተን በእንደዚህ ያለ ኃዘንና
ችግር ላይ ጥያችሁ ለመቅረት ደስ ስላላለኝ አብሬአችሁ ለመ
ጠጣትና ለመጫወት መጣሁ ''አሏቸው ።

ከራሳም ጋር ሲጫወቱ ራሳም በእንግሊዝ አገር ስላለው
የቀረጥ አቀራረጥ ጉዳይ አጫወታቸው ። ቴዎድሮስ በእንግ
ሊዝ አገር ስላለው ከነጋዴ ስለሚቀረጠው ቀረጥ ሰምተው
ኩት ብለው ሳቁና "ስማኝ እንጂ ራሳም ። የአገሬ ሰው
በገንዘቡ እንደመነገድ ከመሬት ውስጥ ይቀብረዋል ። ይህን የሚያ
ደርገውም ለኔ የሚገባኝን ቀረጥ ላለመክፈል ሲል ነው"አሉት ።
እንደገና ራሳም በፈረስና በበቅሎ በቤት ሠራተኛም ስለሚቀረጠው
ቀረጥ ቢያጫውታቸው "አይ አቶ ራሳም ። አንተኮ የአበሾችን ነገር
አታውቅም ። አሁን እኔ በበቅሎው ፣ በፈረሱ ፣ በእንሰሳው ቀረጥ
ልቀበልህ ብለው ማንም ሰው ፈረስና በቅሎ የሚኖረው የለም ።
በአሽከርህ ቀረጥ ክፈል ። ብለውም ሁሉም የየራሱ አሽከር ይሆናል"
አሉት ። ይህን የመሳሰለውን ሲጫወቱ ቆይተው ለመሔድ ሲነሱ
"....ፊቴን ሳያዩና ሰውም የሚናገረውን ሰምታችሁ ሳትገምቱት
በልቤ ውስጥ ያለውን ስሜት ብትመለከቱት ለአገሬ ጥሩ አላማ ያለኝ
ሰው ነኝ" ብለዋቸው ሔዱ ።

አንድ ቀን ደግሞ ከደብረ ታቦር ወደጋፋት መጥተው ሥራ
ውን ከጐበኙ በኋላ ከውጭ መቀመጥ ፈልገው ቀይ ሐር የተነ
ጠፈበት ወንበር ተደርጐላቸው ተቀመጡ ። ራሳም በአጨዋወቱ ያስ
ደስታቸው ነበርና የንግስተ ሳባን ታሪክ አጫወቱት ። ቀጥሎም
አንድ ጊዜ የጐንደር ከንቲባ ሆነው ተሹመው የነበሩት ከንቲባ ኃይሉ
የኤሌክሳንደርን (እስክንድርን)ታሪክ እንዲናገሩ አዘዋቸው ያወሩ
ጀመር ። ታላቁ አሌክሳንደር ከኢትዮጵያ ልዕልት ልጅ ማስወለዱ ፣
እስከ ገነት (መንግስተ ሰማያት) ድረስ ሔዶ መመለሱን ሁሉ ከን
ቲባ ኃይሌ መጽሐፍ ይዘው ስዕሉን እያሳዩ ለራሳም ተረኩለት ።

ራሳም ባፉ ባይናገርም በነገሩ አላመነም ። በታሪክ መጨረሻ
ላይ ቴዎድሮስ ወደ ራሳም ዞር ብለው "የእስክንድርን ታሪክ ወደ
ድከው ወይም ጠላኸው? ''ብለው ጠየቁት ። ራሳምም "ጃንሆይ ፣
እውነቱን ለመናገር አሌክሳንደር ወደ ገነት ለመሔድ በመመኘቱና
በመሔዱ በጣም ብልህ ሰው ነው ወደ መሬት ተመልሶ በመምጣቱ

ግን በጣም ሞኝ ሰው ነው ። እኔ በሱ ቦታ ብሆን ኖሮ አንድ ጊዜ ተፈቅዶልኝ መንግሥተ ሰማያት ከገባሁ ከዚያው እቀር ነበር "ሲላቸው ከተቀመጡበት ከትንሿ ወንበር ተፈንግለው እስ ኪያዘሙ ድረስ ሳቁ ሲበቃቸውም ወደ እራሳም እያዩ "እኔ በእ ንዲህ ዓይነቱ ግብስብስ ነገር ሁሉ የማምን ይመስልሃል? "ቢሉት "አይመስለኝም ጃንሆይ ። ግርማዊነትዎ የበለጠ እውቀት እንዳለዎ እርግጠኛ ነኝ ። "አላቸው ። በዚችም ቦታ ተቀምጠው ሁለት ሰዓት ያህል ሲጫወቱ መቆየታቸውን ራሱ ራሳም ፅፎታል ።

ኤሮፓውያኖቹ በሙሉ መቅደላ ተወስደው እንዲታሠሩ በታ ዘዘው መሠረት ፈረንጆቹ በሙሉ የመቅደላውን የእስራት ዘመና ቸውን ለመጀመር ሐምሌ 5 ቀን 1858 ዓ.ም. መቅደላ ገቡ ።





ምዕራፍ 13

# የእሥረኞች የመቅደላ ኑሮ

ማርከሃም ስለመቅደላ ተራራ ሲፅፍ "....በዓለም ካሉ ቦታ ዎች ሁሉ ጤናማ አየር ያለበት ሥፍራ ነው ። ...." ይለዋል ። መቅደላ ተራራ ዙሪያውን ሙጥጥ ያለ ገደል ነው ። ከእናቱ ለመ ድረስ ያለው መንገድና በር አንድ ብቻ ነው ። ከላዩ ላይ ከተወጣ በኋላ ግን እጅግ በጣም ሰፊ የሆነ ሜዳ ነው ። መቅደላ ተራራ በተ ፈጥሮ አቀማመጡ አመች በመሆኑ ከጥንት ጀምሮ የእስረኞች ማስ ቀመጫ ነበር ። አጤ ቴዎድሮስም የመቅደላን ተራራ ለእስረኞች ማኖ ሪያ ብቻ ሳይሆን የንብረታቸውም ማስቀመጫ አድርገውት ነበር ።

ጭልጋ ውስጥ ማር አምባ ከተባለ ቦታ የነበሩት የፖለቲካ እስ ረኞች ወደ መቅደላ ከተዛወሩ በኋላ በመቅደላ አምባ ዘጠኝ ሹሞች ተሾሙበት ። ከዚያ በፊት ግን የአምባው ሹም አንድ ሰው ብቻ ነበር ። በዚያም የሚሾመው የእስረኞች ጠባቂ ማዕረጉ ደጃዝማች ነበር ። ኤሮፓውያኖቹ እስረኞች ወደ መቅደላ ከተወሰዱ በኋላ ግን የአምባው አዛዥ ማዕረግ ከደጃዝማችነት ወደ ራስነት ከፍ አለ ። ዋናው አዛዥ ራስ ሲባል የሌላዎቹ ዘጠኝ ሹማምንት ማዕረግ ግን ቢትወደድ ነበር ።

ፈረንጆቹ መቅደላ የገቡ ጊዜ ዋናው የአምባው አዛዥ የበጌ ምድሩ ተወላጅ ራስ ኪዳነ ማርያም ነበሩ ። ራስ ኪዳነ ማርያም በራስ አሊ ዘመነ መንግሥትም ያገለገሉ ታላቅ ሰው ናቸው ። በጠ ባያቸውም ጨዋ ፣ አዛኝ ፣ እውነተኛ ስለነበሩ ፈረንጆቹ ይወዱዋቸው ነበር ። ራስ ኪዳነ ማርያም ያለ ንጉስ ትእዛዝ ምንም ዓይነት መጥፎ ነገር እንዳይደረግ የሚቆጣጠሩና የማይፈልጉም ሰው ነበሩ ። ምኒ ልክ ከመቅደላ ካመለጡ በኋላ ራስ ኪዳነ ማርያም ግንኙነት አላ ቸው ተብለው በሰንሰለት ታሠሩ ። የተረፈ ዘመናቸውንም በሰን ሰለት እንደታሰሩ ደብረ ታቦር ጨረሱት ።

መቅደላ በሽሎ እና ጀዳ በተባሉ ወንዞች መሀል የሚገኝ ተራራ ነው ። በተራራው ወገብ ላይ ያለው ሰላምጌ የሚባለው ቦታ ሰፊ

በመሆኑ በዚያን ጊዜ በዚያ ቦታ በእርሻ ተግባር የሚኖሩ ብዙ ሰዎች ነበሩበት ። አራሾቹም የሚያርሱት ለንጉሱና ለመቅደላ ሹማምንት ነበር ። ይህ ብቻ ሳይሆን በተራራው ጫፍ የታሰሩ የታላላቅ ሰዎች አሽከሮች በዚያው በሰላምጌ ፣ ቦታ እየተሰጣቸው ቤት ሠርተው ከብት እያረቡ ስንቅ በማቀበል የሚኖሩም ነበሩበት ። ከሰላምጌ ጐን ደግሞ ሥላሴ እየተባለ የሚጠራ ሜዳ አለ ። ሜዳው ሥላሴ የተባለበት የሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ስላለበት ነው ። በዚያም በየሳምንቱ ቅዳሜ የገበያ ቀን ስለሆነ ብዙ ሕዝብ ይሰበሰብበት ነበር ።

በመቅደላ ተራራ ላይ ስላሉት ቤቶች ዶክተር ብላንክ ሲገልፅ "...የአፄ ቴዎድሮስ ቤትና ጐተራ የተሠራው ከአምባው ማዕከላዊ ቦታ ላይ ነው ። ከቤቱ ፊት ለፊት ሰፊ ለአደባባይነት እንዲያገለግል ክፍት ቦታ ያለው ሲሆን በጀርባ በኩል የንጉሡ ነገሥት መ ኳንንቶች መኖሪያ ሠፈር ይሆንና በስተቀኝ በኩል ደግሞ ቤተ ክርስቲያኑ ፣ እሥር ቤቱና የወታደሮች ሠፈር .... (አሰ) መቅደላ ላይ ያሉት የአጼ ቴዎድሮስ ቤቶች ሰፋ ባለ ሁኔታ እንደሌሎቹ የአበሻ ቤቶች የተሠሩ ናቸው እጤ ቴዎድሮስ ግን በጠቅላላው በቤት



ዶብረታቦር: መድኃኔ ዓለም



ስጥ ከመኖር በድንኳን መኖርን ስለሚወዱ በአምባውም ውስጥ ተው መዘጋትን ስለማይፈልጉ ሲመጡ ሰላምጌ ላይ ድንኳናቸውን ተለው ይሰነብታሉ ። በእነዚህ ቤቶች ብዘም ኑረውባቸው ውቁም ። ..." ብሏል ።

ስለ እስር ቤቶቹ ሁኔታ ሲገልፅ ደግሞ ".... የፖለቲካ ፣ ስ ገዳይና ሌቦችም የሚታሰሩባቸው አምስት ትልልቅ ቤቶች ሩ ። በዙሪያቸው የሀብታሞቹ እስረኞች አሽከሮችና ዘበኞች ይኖ ። ቤቶቹ በጥብቅ አጥር የተከበቡ ናቸው ። እኛ በተያዝን ጊዜ ዚህ ቤቶች ውስጥ ቁጥራቸው 600 የሚሆኑ እስረኞች ይገኙበት ር ። ከዚሁም ውስጥ 80 በትኩሳት በሽታ ሲሞቱ 175 ተፈቱ ። ..307 ተገደሉ ። የእሥር ቤቱ አጠባበቅ በአንድ በኩል በጣም ቅ ሲሆን ባንድ በኩል ደግሞ ልል መስሎ ይታያል ። ፀሐይ ጠልቅ እስረኛው ሁሉ ወደ እሥር ቤቱ አጥር ግቢ እንዲገባ ዘዝና ሲገባ አንድ ባንድ እየተቆጠረ ሰንሰለቱም ያልተፈታ ሆኑን ከበራፉ ላይ ዘበኞች ቁመው ይፈትሻሉ ።

"ከዚህ ቀደም ሴቶች እስረኞች ከወንድ እስረኛ ጋር በአ ድ ቤት ውስጥ ይታሠሩ ስለነበር ኋላ ግን ተሻሽሎ ለብቻቸው ት ተሰጥቷቸዋል ። እስር ቤቱ በጣም ሞልቶ ብዙ መጨናነቅና ታፈግ ስላለ አበሻዎችንም ያሳዝናቸው እንደነበር ይገልፃሉ ። ንበዴው ፣ ከብዙ የጦር ግንባር ድል የተጐናፀፈው ጀግና ፣ ጠቅላይ ው ፣ ልዑሉ ሁሉም በጠቅላላው የተለየ ቦታ ሳይኖራቸው እጃ ውና እግራቸው በሰንሰለት ተፈድኖ በዚያች ጠባብ ቦታ ላይ ጐን ጐን እየተጋፉ ይተኛሉ ። ከእስር ቤቱ መካከል ላይ ዘበኞቹ እሳ ቸውን እየሞቁና እየተጫወቱ ሲጠብቁ ያድሩና ከጧቱ በ12 ሰዓት እስር ቤቱን ከፍተው እስረኛውን ስለሚያስወጡት በችግር ጐዳው እስረኛ የእለት ምግቡን ለመለመን ወይም የታደለና ከሮቹ ሀብቱን ይዘው በዙሪያው የሚጠብቁት ከሆነ ስንቁን በመ ል በጠቅላላው ምግብ ለማግኘት ሲጥር ይውላል ። ...." ግለት ጽፍዋል ። (ትርጉም ዳኜ ወ/ሥ)

ራስ ኪዳነ ማርያም የመቅደላ ሹም የነበሩ ጊዜ እስረኞቹ ፈረ ጆች መቅደላ ገቡ ። ከመቅደላ እንዴት ተደርገው በእግር ብረት ንደታሠሩ ዶክተር ብላንክ ሲድፍ ".... እግረሙቁ ቀርቦ ተራ ተራ እየቀረብን የመታሰሩ ተግባር ተጀመረ ። የፊተኞቹ ኤሮፓው እስረኞች በከባድ እግረሙቅ ቀድመው ታሠሩ ። በመጨረሻው

የኔው ተራ ደረሰና እንድቀመጥ ከተደረገ በኋላ ሱሪየን ከፍ ከፍ
አድርገው ቀኝ እግሬን ከአንድ ለዚሁ ተግባር ከቀረበ ድንጋይ ላይ
አስቀመጡት ። የሰንሰለቱን ቀለበት ከቀኝ ቁርጭምጭምቴ በላይ
ካጠለቀ በኋላ ሰንሰለቱን ለመግጠም ሲሉ በመዶሻ መደብደብ ያዙ።
ብረቱን ሲደበድቡ መዶሻው በትክክል ስለማይመታ ለሰውነቴ ሁሉ
አስቃቂ የሆነ ጉዳት ተሰማኝ ። የመጀመሪያዋን ቀለበት ለማጥ
ለቅ አሥር ደቂቃ ጊዜ ወሰደባቸው ። በዚሁ ሁኔታ ከግራ እግሬ
ላይ ሰንሰለቱን አጠለቀልኝ ። የአሰራሩ ሁኔታ በሚከናወንበት ጊዜ
ሰንሰለቱን የሚያጠብቋቸው ቀጥቃጮ ብረቱን ሰቶ እግሬን ያነኩ
ተዋል በማለት ከባድ ሰቀቀን ጥሎብኝ ነበር ። የግራውን እግሬ
ሙቅ አጥብቀው ወደ መጨረሱ ገደማ ሳሉ ቀለበቱ ስለተሰበረ
ሰውነቴ በድንጋጤ አረገደ ። በዚህም ምክንያት ሥራው እንደገና
ተጀምሮ በሚገባ ስለተፈፀመ ቀጥቃጩና የወህኒ ቤቱ አዛዥ ተደ
ሰቱ ። ....”ይላል (ትርጉም ዳኜ ወ/ሥ)

የእስረኞቹ የእስራት ዘመን እንዴት እንደተፈፀመ ከማወቃ
ችን በፊት እሰረኞቹ መቅደላ ተራራ ላይ አንድ ዓመት ከመንፈቅ
ሲቆዩ እንዴት ይኖሩ እንደነበረ ማወቁ ይጠቅም መሰለኝ ። ራሳም
በሁለተኛው ቮሊዩሙ መጽሐፍ ሲገልጥ“ ....የመቅደላ መሬት
ለአትክልት ተሰማሚ ነው ። ችግሩ በድርቅ የወራት ውሃ በመስኖ
ለማጠጣት ውሃ ያለማግኘቱ ብቻ ነው ። መቅደላ እንደ ደረስን ከግ
ብፅ አገር የያዝኩት የቲማቲም ዘር ነበረኝና ከጕጆዬ ፊት ለፊት
ተከልኩት ። በወሩ ልክ እንደ ወይን ሐረግ አደገ ። ከጥቂት ተጨማሪ
ሳምንታት በኋላ በብዛት አድጐ በሥሩ 6 ሰዎች ያህል የሚያሰቀ
ምጥ ዳስ (መጠለያ) )ሆነ ። የቤቱንም መግቢያ ሁሉ ከላይ አለበ
ሰው ። ዓመቱን ሙሉ ፍሬው ባለማቋረጡ የቲማቲም ወጥና ኮቴ
ሌት እየሠራን ለመብላት ቻልን ። ጥቂት ፍሬዎችም ዘራሁና ችግኙ
እንደ ደረሰ ለአገሬው ሰው ሁሉ አደልኩ ። የእንግሊዝ ጦር መጥቶ
እስከንወስድ ድረስ ቲማቲም አላጣንም ነበር ። አንድ ጊዜ አንዱን
የቲማቲም ሐረግ ለከቼው ርዝመቱ 18 ጫማ ከግማሽ ሆነ ። ....”
ብሏል ። ቲማቲም ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተከሎችንም ይተክሉ ነበር።
ይህ የቲማቲም ተከል በኢትዮጵያ የመጀመሪያው እንደሆነ ይገ
መታል ።

ራሳም ጊዜውን የሚያሳልፈው በአትክልት ተከላ ብቻ አልነ
በረም ። ብዙ የዱር ወፎችን አላምዶ ቤቱ ነፃ በተለቀቁ ወፎች
የተመላ ነበር ። አጤ ቴዎድሮስ በዚህ በወፍ ማላመዱ እየተ



ደሰቱ ያደንቁለት ነበር ። የሰላምታ ደብዳቤ በሚፅፉለት ጊዜ“ ....
ልጆችህስ እንዴት ናቸው ....”እያሉ ስለወፎቹ ይጠይቁት ነበር ።
ከራሳም ዘንድ የመጣ ሰው ሲያገኙም “የራሳም ልጆች እንዴት
ናቸው?” እያሉ መጠየቃቸውን ራሳም ጽፏል ።

ራሳም ስለመቅደላ ኑሮአቸው ሲገልፅ“ ....ዳቦ እንጋግራለን።
የምንመገብበት ጠረጴዛችን ሁልጊዜ ልብስ አለው ። አንዳንዴም
የአፍ መጥረጊያ ፎጣ(ናፕኪን) ይኖራል ። ....ምግብ የምንመገ
በው ከሾርባ ጀምረን ነው ። አንዳንዴም አሣ እናገኛለን ። ....እው
ነቱን ለመናገር አንድ ባለሚሊዮን ብር ጌታ ከኛ የተሻለ ኑሮ አይ
ኖርም ። ....ትንሽ ምቾታችንን የምታበላሽብን የታሰርንባት
ሰንሰለት ብቻ ናት ። ....ሌላው ደግሞ በከር ጫፍ ስለተንጠለጠለ
ችው ሕይወታችን እንሰጋለን ።

“የሚጠይቁን ከአምባው ብዙ ሰዎች ይመጣሉ ። ....እንደ
ደንብ አድርጌም ለሚመጣው እንግዳ አንድ ሲኒ ቡና አንድ ወይም
ሁለት መለኪያ አረቂ እሰጣለሁ ። ጠጅ ግን በቤቴም እንዲገባ አል
ፈቅድም ነበር ። ....ከሹማምንቱ ጋር ሁሉ ስንጨዋወት እናመ
ሽለን ። እኔም ሳስቃቸው አመሻለሁ ። ....አንዳንዴም ሹማምንቶቹ
የሚማከሩትና ስብሰባቸውን የሚያካሔዱት ከኔ ቤት ነው ። ....
የማታ ጐብኝዎቼ ብዙውን ጊዜ ሴቶች ናቸው ። እነኝህም ባሎ
ቻቸው በፖለቲካ የታሠሩባቸው ናቸው ። እነሱም የባሎቻቸውን ወሬ
ይዘው ይመጡና ስንጫወት እናመሽለን ። ....ድምፃቸውን ሲሰ
ሙት ግሩም ቃና ያለው ነው ። የአበሻ ሴቶች ሲናገሩ ሳይጮሁና
ረጋ ብለው ነው ። .... ያዝኑልኛል ፣ ያፅናኑኛል ም ። የእግዚአብ
ሔርን ምሕረት እንድጠብቅ ይነግሩኛል ። ....ሲያፅናኑኝም ያን
ተንና የጓደኞችህን እስተሳሰር ከኛ ባሎች ጋር ብታስተያየው የእናንተ
ሰንሰለት መታሰር አይባልም ። እነሱ እኮ እጃቸውንና እግራቸውን
ባንድነት በሰንሰለት ታስረው ነው ያሉት ። አንተ ከመምጣትህ
በፊት ከኛ ሰዎች ጋር ታስረው የነበሩትን ወንድሞችህን እስቲ ጠይ
ቃቸው ። ይነግሩሃል ። ያኔ ያንተን እስርና የኛን ባሎች አስተሳሰር
ልታመዛዝን ትችላለህ ይሉኛል ።

“. አንድ የፎቶግራፍ አልበም ነበረኝና እሱን እያገላበጡ
ማየት ይወዳሉ ። ወደየቤታቸው ከተመለሱም በኋላ ላከልን እያሉ
የስወሰዱታል ። ለሌሎች ለማሳየት እያሉ ነው ። አንዳንዴም
ሳይመልሱልኝ እስከ 15 ቀን ድረስ ይቆያል ። ....አንድ ጊዜ

ከእንግሊዝ አገር የአንዲት ወዳጇ የጅ ስዕል ካርድ ደረሰኝ ። ይህ አዲስ ስዕል እንደ ደረሰኝ ለሁሉም እንግዳ ሆነባቸው አንዳንዶቹ የሚስቴ ወይም የወዳጇ ይመስላቸዋል ። እነኝያ ቅዱሳን ነፍሳት ስዕሉን እያዩ ያስቅሳሉ ። ስዕሉን እየሳሙም 'አቶ ራሳም እንዲህ በስንሰለት መታሰሩን ስትሰሚ አላለቀሽም? እግዚአብሔር ብርታቱን ይስጥሽ' ይላሉ ። ....ብሏል ።

ከመቅደላ የጥበቃ ኃላፊነት ራስ ኪዳነ ማርያም ከተነሱ በኋላ ምክትል አዛዥ የነበሩት ቢትወደድ ቢሰውር ራስ ተብለው የመቅደላ ሹም ሆኑ ። ቢሰውር በደምቢያና በበጌምድር መሀል ያለው የእንፍራንዝ ተወላጅ ናቸው ። አባታቸውም የእንፍራንዝ ገዥ ነበሩ። አባትዬው የቴዎድሮስን አክስት አግብተው ቢሰውርን ወለዱ ። በዚህ ምክንያት ቢሰውር በቴዎድሮስ ዘንድ የሚታመኑ ሰው ነበሩ። ራስ ቢሰውር በአርሻና በከብት እርባታ የታወቁ ሀብታም ነበሩ ። በወይን ተክልም በኩል በብዛት ስለነበራቸው በጐንደርና በሌላም በሌላ አገር እየተላከ ይሸጣል ። ቴዎድሮስ ራስ ቢሰውርን ስለሚያምኗቸውና ስለሚመኩባቸውም ቁባቶቻቸውን እንኳ የሚያስጠብቁት ራስ ቢሰውርን ነበር ። በኋላ ግን የቴዎድሮስ አመራር እየተለወጠና ግራ እየገባቸው ስለሔደ ፈርተው ከመቅደላ ጠፍተው ከዱ።

ይህ የፈረንጆቹ እንደገና መታሰር እንግሊዝ ውስጥ በተሰማ ጊዜ ታላቅ ውዝግብ ፈጠረ ። በሰላም ሊያልቅ የነበረው ጉዳይም እንደገና እሰር ገብቶ ክርክር አስነሳ ። ኮሎኔል ሜርዌዘር በክርክሩ መሀል ገብቶ "የሚሻለው ጦር ማወጁ እንጂ ከአንግዲህ ወዲያ መለማመጡ የእንግሊዝን መንግሥት ማዋረድ ነው" የሚል አሳብ አቀረበ ። ቢሆንም ጉዳዩ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲጠና ስለታዘዘ ምክር ቤቱ ጉዳዩን በዝርዝር አጥንቶ አጤ ቴዎድሮስ ለጻፉት ደብዳቤና ጥያቄ መልስ ሰጥቶ ቢሞክር ይሻላል በሚለው ሐሳብ ላይ ረጋ ። ወሰነ ።

ከዚህ በኋላ ታልቦት የሚባል ሲቢል ኢንጂነርና ስድስት የጅ ሥራ አዋቂዎች ከነመሣሪያቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲሔዱ ለፍላድ ተሰጡት ። ለንጉሱ የሚሆን ስጦታ ይዞ በጥቅምት ወር 1859 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ጉዞውን ጀመረ ። በታህሣሥ ወር ምፅዋ ገብተው ለአጤ ቴዎድሮስ ምፅዋ መግባቱን የሚገልፅ ደብዳቤ ላከ ። ፍላድ ከእንግሊዝ አገር ከመነሳቱ በፊት ምፅዋ ሲደርስ መድረሱን ለቴዎድሮስ አሳውቆ እስረኞቹ ተልከውለት ምፅዋ ላይ ሳይረከባቸው



ጅ ሥራ አዋቂዎችን እንዳይልክ ወይም ይዞአቸው እንዳይገባ ታዞ ነበርና ይህንኑ ገልጾ ለቴዎድሮስ ጻፈ ።

ፍላድ ለአጤ ቴዎድሮስ ከጻፈው የራሱ ደብዳቤ ጋር ከእንግሊዝ ንግሥት የተላከላቸውንም የደብዳቤ ትርጉም ጨምሮ ልኮት ነበር ። ደብዳቤውም "ለመልካም ወዳጃችን" በሚል አድራሻ ይጀምርና "....ግርማዊነትዎ እንደጠየቁት ሁሉ በአበሻ ውስጥ እንዲሠሩ የሚፈልጓቸውን ጠቢባን ሰዎች ልከንልዎ ፍላድ ይዞ ሊመጣልዎት ቢል ለአሽከራችን ለራሳም ያደረጉለትን መልካም ድርጊት ሁሉ ትተው ከአሽከራችን ከካሜሮንና ከሌሎቹ ኤሮፓውያን ጋር እንደገና ማሠርዎን ሰማን ። ከግርማዊነትዎ ግን ይህ የሆነበትን ምክንያት የሚያስረዳ ምንም ነገር አላገኘንም ።

"ይህም ቢሆን ፍላድን እንዲያው በከንቱ በማቆየት ጊዜ እናጠፋም ብለን ለግርማዊነትዎ የጻፍነውን ደብዳቤ ሰጥተን ልከነው ። ግርማዊነትዎም የገቡትን የተስፋ ቃል እንደሚፈጽሙ እየተማመን የታሠሩትን እስረኞች አሽከራችንን ራሳምን ከአሽከራችን ከካሜሮንና ከሌሎቹ ኤሮፓውያን ጋር እንደሚለቁዋቸው ተስፋ እናደርጋለን ። ....በወዳጅነታችን ላይ የጋረደው ጥቁር ደመና ፍላድ ከእርስዎ ዘንድ በደረሰ ጊዜ ተገፎ እንደሚጠፋ ሙሉ እምነት አለን...."የሚል ረጅም ደብዳቤ ነበር ።

አጤ ቴዎድሮስ ም ከዚህ ደብዳቤ ጋር ከፍላድ የተፃፈው ማስታወሻ ከደረሳቸው በኋላ መልሱን ለፍላድ በመጻፍ ፈንታ መቅደላ ላይ በእስር ላለው ለራሳም ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጻፉለት ።

በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡
ጉሠ፡ ነገሥት፡ ቴዎድሮስ፡ ይድረስ፡ ከቶ፡ ኒር
ዝ፡ ረስአም፡ እንዴት፡ ሰነበትህ፡ እኔ፡ እግዚአብ
ር፡ ይመስገን፡ ደህና፡ ነኝ፡፡ ሃኪም፡ ብሎንማን
ቶ፡ ፕሪደን፡ እነአቶ፡ ኬምሮንን፡ እነከክብን፡
ንዴት፡ ሰነበታችሁ፡ ስለ፡ በሰላሜ፡፡ አሽከርህን
መተማ፡ ሰደድልኝ፡ ደሐኘኝን፡ ሠደድሁልህ፡፡
ስተወህኒ፡ በማመል፡ ከዚያ፡ ወደዚህ፡ በሰው፡ ተ
ኪ ከማችሁ፡ አሃምጡልኝ፡ ብዬ፡ አገዝጋ ሠድጃስ
ሁ፡ በእግዚ አብሔር፡ ኃይል፡፡ እቶ፡ ፍላጥ፡ ተ

መልስ፡መጥቶ፡ምጥዋ፡ላይ፡ሁኖ፡ ይህነን፡ደብ
ዳቤ፡ ሠዩልኛ ል፡ አይተህ፡ እንብበህ፡ ቶሎኝ፡
፡፡እኔ ም፡ በእግዚ አብሔር፡ኃይል፡ ልመጣ፡ነኝ
ተመክሬን፡ምላሹን፡ እንድንልክ፡፡



ይህ ደብዳቤ ታህሣሥ 21 ቀን 1859 ዓ.ም. መቅደላ ላለው ለራሳም ደረሰው ። በዚያ ያሉት ኤሮፓውያን እስረኞች ሁሉ የፍላድን መመለስና ምጥዋ መድረስ በመስማታቸው ከፍተኛ ደስታ አደረጉ ። የቴዎድሮስ ደብዳቤ ራሳም ጉዳዩን እንዲያጠናው የተላከ እንጂ መልስ መጻፍ ስለሚያስፈልገው ራሳም ደብዳቤውን ይዞ ጉዳዩን እያጠና ቆዩ ።

ፍላድ ለጻፈው ደብዳቤ መልስ ሳያገኝ ስለዘገየበት እንደገና ያንኑ የመጀመሪያውን ደብዳቤ ግልባጭ ጽፎ መልሱ የዘገየበት መሆኑንም ገልጾ ለአጤ ቴዎድሮስ ከምጥዋ ጻፈላቸው ። አሁንም አጤ ቴዎድሮስ ለፍላድ መልስ በመስጠት ፈንታ ስለሁለተኛውም ደብዳቤ ሁኔታ ለእስረኛው ለራሳም ጻፉለት ። ደብዳቤውም ቀጥሎ ያለው ነው ።



በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡፩ አምላክ
ንጉሠ፡ነገሥት፡ ቴዎድሮስ፡ ይድረስ፡ ከአቶ፡ሬሰእ
ም፡ እንዴት፡ ሰነበትህ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ይመ
ስገን፡ ደህ ና፡ ነኝ፡ ሀኪም፡ ብሎንግን፡ አቶ፡ ፕሪ
ደን፡ አቶ፡ ኬምሮንን፡ እነአቶ፡ ከከብን፡ እንዴ
ት፡ ሰነበታችሁ፡ አለ፡ በሉልኝ፡፡ ደግሞ፡ አሁን፡
ሁለተኛ፡ አቶ፡ ፍላጥ፡ ላከብኝ፡፡ ላንተም፡
የሠደደውን፡ ደብዳቤ፡ ሠድጄልሃለሁ፡፡ አ
ሁንም፡ የውነት፡ የናንተና፡ የኔ፡ ዝምድና፡
መገናኛ፡ ምልክት፡ እነዚህ፡ የመጡ፡ ሠራተኞች
ብልሆችም፡ በመተማ፡ ከቶ፡ ፍላጥ፡ ጋራ፡ እንደ
መጡ፡ አርገህ፡ ላክልኝ፡፡ ከዚያ፡ ወዲያ፡ ጠላ
ቱን፡ ጠላት፡ ወዳጁን፡ ወዳጅ፡ ካደረጋችሁልኝ፡ በ
ኋላ፡ የናንተን፡ ዝምድና፡ የጠላሁ፡ እንደሆነ፡
፡ በእግዚአብሔር፡ እገናኛ፡፡ ለሎሞን፡ እንኳ
የዳዊት፡ ልጅ፡ ታላቁ፡ ንጉሠ፡ የእግዚአብሔር
፡ ፍጥረት፡ የእግዚአብሔር፡ ባርያ፡ ቤተ፡ መቅ
ደስን፡ ሲሠራ፡ እጅግ፡ ቸግሮት፡ ነበረ፡፡ ከኪሮስ፡
ንጉሠ፡ ከኪራም፡ እቁ ላ ም ጠ፡ ከፍሪማ ው፡ ሀ ጅ ፉ፡
ሰምና፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ ብልህ፡ ተቀብሎ፡ አም
ጥቶ፡ አሠራ፡፡ አሁንም፡ እኔ፡ ከታላቂቱ፡ ከእንግሊ
ዝ፡ ንግሥት፡ ከመኳንንቶችዎ፡ ሁሉ፡ ተአገርዎ፡
ሰው፡ ከሠራዊትዎ፡ ሁሉ፡ ከፍሪማው፡ ወ ዩ ፉ፡ እ
የታጠቅሁ፡ እየፈታሁ፡ ሣቆ ሳም ሞ፡ እነአቶ፡ ከከ
ብ፡ ሠዩበውኝ፡ አሻርሂወኝ፡ አገኘሁ፡፡ ቀጥሎ፡
አቶ፡ ኬምሮን፡ ከእንግሊዝ፡ ንግሥት፡ ከተላላ
ኩ፡ ሃይማኖትና፡ የተጠቃ፡ ደሀ፡ ከሚበዛብቁቱ፡ ከእግዚ
አብሔር፡ ወዳጅ፡ ከእግዚአብሔር፡ ባለምዋል፡ ከቢ
ክቶርያ፡ የፍቅር፡ ደብዳቤ፡ ብሠድ፡ ሆሆ ለኸ፡ነሰኝ፡

አንተ፡ አቶ፡ ረስአም፡ ቀጥለህ፡ ከንግሥቲቱ፡ ተልኬ አለሁ
፡ብለህ፡መጣህ፡እኛ፡ብዬ፡በተቻለኝ፡ጉልበቴ፡በፍቅር
፡ተቀበልሁህ። የሠጠኸኝን፡ደብዳቤ፡ግዜ፡ያውሮ
ጳን፡ሰዎች፡ሁሉ፡የተጣላሃቸዉን፡ያሠርሃቸዉን፡
ፍታልኝ፡ማርልኝ፡የሚል፡ቃል፡አገኘሁኝ፡እኔ
ም፡ካንተ፡ፊት፡፩ቀን፡ሣላሣድር፡እኛ፡ብዬ፡ል
ኪ፡አስፈቶቻ፡አመጣሁልህ፡በፈጣሪ አቾን፡
ኋይል፡፡ ከኔ፡ሣይደርሱ፡አስመጥቸ፡ላንተ፡ሰጠ
ሁህ። ወደ፯ን፡ንግሥቲቱን፡ከነመኳንንቶችዎ፡
ደስ፡ይበልዎ፡ብዬ። አንተ፡ግን፡ምንስ፡በድላቹሁ
ነው፡የታሠራችሁ፡ብለህ፡ሣትጠይቃቸው፡በድ
ሎ፡ተገኝቶ፡እንደሆነ፡ሣልክስ፡ተበድሎ፡ተገኝቶ፡እን
ደሆነ፡ከንግሥቲቱ፡ወረቀት የገ፡እንደገኝ፡ሣታ
፡ገኝ፡ከኔ፡ሣታገናኝ፡ሠደድሃቸው። ቀጥሎ
እንግሊዝና፡ቱርክ፡፩ሆነው፡ጠሉህ፡ብሰው፡
በማሁ፡በዚህ፡አገሬ፡ዝም፡ብዬ፡ተቀምጬ፡
ሣለሁ። አቶ፡ፍሳጥ፡የደስታ፡የፍቅር፡ደብዳቤ፡
ሳክብኝ፡፡ እሁ ንም፡ ስሉዋንን፡በፍቅር፡ከኪራ
ያ፡ጨዋማ፡እንደወደቀ፡እኔም፡ከእግዚአብሔር፡በ
ታች፡ከንግሥቲቱ፡ከመኳንቶችም፡ከወዳጆች
ም፡ሁሉ፡ጨዋማ፡ወድቄ፡አለሁ፡የኖበብ፡ብል
ሃቶ፡እንዲአሣዩኝ፡በመተማ፡እንዲመጡል
ኝ፡አርገህ፡ላክ፡፡ ይህ፡ከሆነ፡በኋላ፡ደስ፡እሠ
ኛቸ፡አሺኛቸ፡አሰደቹኋለሁ፡በእግዚአብሔር፡
ኋይል፡፡

…ሎቃ ስ፡በወርቁ፡
ተሐሣሥ፡በ፳ቀን፡ተጻ…
ተ…፡፡





በዚህ ደብዳቤ ላይ እንዳነበብ ነው ታላቁ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሊያሠራ ባሰበ ጊዜ ከኪሮስ ጫማ ወድቆ ለመነ ብለዋል ። ይህን ማለታቸው በዘመኑ ከሁሉ ታላቅ የነበረው ሰሎሞን የሚፈልገው ጉዳይ እስቲሟላለት ከበታቹ ከኪሮስ እግር ላይ ወደቀ ። እኔም ጉዳዩ እስኪሞላልኝ ድረስ ብቻ የማይገባኝን ከንግስቲቱ ጫማ ወድቄ እለምናለሁ ማለታቸው ነው ። የሚለማመጡት ጉዳያቸው እስኪፈፀምላቸው ድረስ ብቻ መሆኑን መግለጣቸው ነው ። የንቀት አጻጻፍ ነው ።

ዋናው ቁም ነገር በቴዎድሮስ ሁለት ደብዳቤዎች ላይ እንዳየነው እስረኞቹ ከመለቀቃቸው በፊት ፍላድ ጥበበኞቹን ይዞ ይምጣ ይላሉ ። ራሳምም በዚህ ሐሳብ ተስማምቶ ለፍላድ እንዲፅፍለት ጠይቀዋል ። ምጥዋ ያለው ፍላድ ግን ማንም ቢጥፍለት እስረኞቹ ተለቀው ምጥዋ ላይ በእጁ እስኪገቡ የመጡትን ጥበበኞች ወደ ቴዎድሮስ የሚልክ ሰው አይደለም ። ምክንያቱም ከዚህ በፊት እንዳነበብነው እስረኞቹን ሳይቀበል ጥበበኞቹን እንዳይልክ ከእንግሊዝ መንግሥት ታዟልና ነው ። ደግሞም የቴዎድሮስ ጠባይ ተለዋዋጭ መሆኑን ስለሚያውቅ ምናልባትም ሁሉንም ባንድነት ያስሩዋቸው ይሆናል የሚል ሥጋትም አለበት ። ፍላድ በሁለቱ መንግሥታት መሀል ባለው የመልክተኛነት ጉዳይ ከእጣብቂኝ ውስጥ የገባ ሰው ነው ። የእንግሊዝ መንግሥት የራሱ መንግሥት ስለሆነ የመንግሥቱን ትእዛዝ መቀበልና ማክበር ግዴታ ነው ። ምጥዋ ላይ የማደሪያ ቤቱ ቢሆንም ቴዎድሮስ ሚስቱን በመያዣነት የያዙበት በመሆኑ ስለ ሚስቱ ሕይወት ያሰባል ፣ ይጨነቃልም ።

አጤ ቴዎድሮስ ለራሳም የጻፉት ደብዳቤ እንደደረሰው ራሳም በንጉሡ ሐሳብ እንደሚስማማ ገልጦ ለንጉሡ ጻፈላቸው ። አጤ ቴዎድሮስም የራሳም ደብዳቤ ሲነበብላቸው በጣም ተደሰቱ ። ደብዳቤውንም ላመጣው ሰው አንድ በቅሎ ከነሙሉ ዕቃው ሸለሙት ። እነ ራሳምም ሆኑ ሌሎቹ ኤሮፓውያንን እስረኞች የእርቁን ጉዳይ እያስመሰሉ ከፍላድ ጋር ምጥዋ ላለው ለኰሎኔል ሜርዌዘር የሚፅፉለት ጉዳይ በጦር ኃይል መፍትሔ እንዲያገኝ እያሉ ነበር ። የእንግሊዝ ጦር ወደ ኢትዮጵያ ቢመጣ ቴዎድሮስ እንደሚፈጁዋቸው እስረኞቹ ያውቃሉ ። ግን በእስር መጉላላቱ ስልችቷቸው ስለነበረ ከዚያ ኑሮ መሞታቸውን መርጠው ነው ። ይህን ያላወቁት አጤ ቴዎድሮስ ግን ራሳም በአሳባቸው እንደሚስማማ ገልጦ በጻ

ፈላቸው ደብዳቤ ተደስተው ፍላድ ለሶስተኛ ለጻፈላቸው ደብ ዳቤ ለራሳም ቀጥሎ ያለውን ጻፈለት ።

ወመልድ ፡ ወመንፈስ ፡
በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ቴዎድሮስ ፡ ይድረስ ፡ ከአቶ ፡ ረሳአም
እንዴት ፡ ሰነበትህ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር
ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡፡ ሀኪም ፡ ብሩ
ሎንባን ፡ አቶ ፡ ፕሪደን ፡ እነአቶ ፡ ኪምሮንን ፡
እነአቶ ክከብን ፡ እንዴት ፡ ሰነበታችሁ ፡ አለ ፡ በል
ልኝ ፡፡ አቶ ፡ ፍላት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ላከብኝ ፡ ቀድሞ
አቶ ፡ ረስአምን ፡ ከነኬምሮን ፡ ነገር ፡ ወዳንተ ፡ በላክ
ነው ፡ ጊዜ ፡ በመልካም ፡ ዓይን ፡ በፍቅር ፡ ተቀበልኸው
ብለው ፡ ለማኝ ፡ እኛም ፡ ያልኸ ነን ፡ ሁሉ ፡ እሺ ፡ ብለን
ለፍጥ ፡ ለጥተን ፡ ሠደን ፡ ነበረ ፡፡ ኋላ ግን ፡ የወትሮ
ው ፡ ፍቅሩ ፡ ተለወጠበት ፡ ብሎ ፡ ወሬ ፡ ለማኘ ፡፡ ዳሩ
ግን ፡ ይህን ፡ ሥለ ለማኝ ፡ ያንቱና ፡ የኛ ፡ ፍቅር ፡ ይ
ለወጣል ፡ ያለማለት ፡ ተከፋ ፡ አለኝ ፡ ብለው ፡ ላኩ
ብኝ ፡፡ እኔም ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ምላሽ ፡ አምልክ ፡ ነኝ ፡
፡ ጥንት ፡ እንግሊዝ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ወዳጅ ፡ ዘመድ ፡
ነበረ ፡ አሁ ፡፡ ዐኔም ፡ የጥንቱን ፡ ነገር ፡ እየሰማሁ
፡ እጅግ ፡ እጥብቂ ፡ እ ወዳቹ ኋለሁ ፡፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ነቀ
ርክ ፡ ጋራ ፡ አመውህ ፡ ጠሉህ ፡ ብ ሰው ፡ ቢነግሩኝ ፡ እ
ውነትን ፡ ይሆን ፡ ብዬ ፡ ልቤ ፡ አወላወለብኝ ፡፡ ዳሩ
ግን ፡ በእንግሊዝና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሠማካከል ፡ መከ
ፋት ፡ አለ ፡ አይመስለኝም ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ፡ ፍቅር ፡



ንሆን ፡፡ እንግሊዝን ፡ የሚአማ ፡ የሚጠላ ፡ እኛ
ወደዉም ፡፡ እኛንተዋ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚአ
ን ፡ የሚጠሳን ፡ አትውደዱብኒ ፡፡ እነአቶ ፡ ረስ
ምን ፡ ወደኔ ፡ የላካችኋቸዉን ፡ መቅደላ ፡ ኪቤቴ ፡
ከተማየ ፡ መልካም ፡ አርጌ ፡ አስቀምጫቸዋ
ሁ ፡
ንተን ፡ ወዳጅነትና ፡ ፍቅር ፡ እስታገኘው ፡ ብዬ ፡፡ የኔን
ል ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ አምልክነኝ ፡ ካቶ ፡ ፍላት ፡ ድረስ ፡፡ አን
ሃ ፡ ዝም ድ ናችሁን ፡ ወዳጅነታችሁን ፡ እንዳገኝ
ሁ ፡ አርገሕ ፡ እንዳላክህ ፡ ላክልኝ ፡ በእግዚአብ
ር ፡ ኃይል ፡፡ የምትለደው ፡ ሰው ፡ ደብዳቤኸን ፡ ጨ
ረህ ፡ ቶሎ ፡ ከኔ ፡ ድረስ ፡ ስደድልኝ ፡፡ እቶ ፡ ፍላትን
ቶሎ ፡ ይዘት ፡ እንዲደርስ ፡፡



አጤ ቴዎድሮስ መልስ በመስጠት ፈንታ አዲሱን የፍላድን ትእዛዝ ካልታዘዘውና ሊሽርም ከማይችለው ከራሳም ጋር ሲፃፃፉ ቆዩ ። ፍላድም አራት ጊዜ ለአጤ ቴዎድሮስ ፅፎ ከእላቸው መልስ ባለማግኘቱና እንደታዘዘው እስረኞቹ ተለቀው ምፅዋ ባለመግባታቸው ፍላድ አብረውት የመጡትን የጅ ሥራ አዋቂዎች ወደ አገራቸው መልሶ ሰድዶ እሱ ወደ መሀል አገር ገብቶ ደምቢያ ላይ ከቴዎድሮስ ጋር ተገናኘ ።

ፍላድ ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር እንደተገናኘ "ሠራተኞቹ የታሉ" ብለው ጠየቁት ። ፍላድም ከእንግሊዝ መንግሥት የታዘዘውን ትእ

ዛዝ ነግር "ጃንሆይ እስረኞቹን ለቅቀው ምዕዋ ድረስ ባለመላከዎ
በትእዛዙ መሠረት መልሼ ወደ አገራቸው ሰደድኋቸው" ብሎ
ተናገረ። ቴዎድሮስም "ለመሆኑ ከንግሥቲቱ ጋር ተገናኘህ" ብለው
ጠየቁት "አዎን ጃንሆይ ተገናኝቻለሁ ። እንዲያውም የቃል መል
ክትም ልከውኛል" ብሎ መለሰ ።

"ምንድነው መልክቱ" አሉት ።

"የእንግሊዝ ንግስት ለግርማዊነትዎ እንዳደርስ ያዘዙኝ መል
ክት እነዚህን በአገርዎ ውስጥ ያለፈቃዳቸው ያስቀመጧቸውን ሰዎች
በሚያስችኩል ከአገርዎ አሰወጥተው ካላኳቸው ለወደፊቱ ከእኛ
ጋር በወዳጅነት ለመኖር የማይቻል ነው ብለዋል"አለ ።

አጤ ቴዎድሮስም ለጥቂት ጊዜ በፀጥታ ቆይተው አሰቡና
"ሰማ ። የወዳጅነት ምልክት እንዲያሳዩኝ ጠይቄ መልስ አልተሰጠ
ኝም ። መጥ ፡ ው መዋጋት ከፈለጉ ይምጡ ። ድል ባላደርጋቸው
ደግሞ ሴት ብለህ ጥራኝ "ብለው አሰናበቱት ።

በማግሥቱ ፍላድ ከእንግሊዝ ንግሥት የተላከውን ስጦታ አቀ
ረበ ። በስጦታው መሀል የሩቅ ማያ መነጥር (ቴሌስኮፕ) ነበረበት ።
ይህም መነጥር በዘመኑ ከነበሩት ምርጥ መነጥሮች አንደኛው ነበር።
አጤ ቴዎድሮስ መነጥሩን ተቀብለው አዩበትና ". . . . መጥፎ መነ
ጥር ነው የተላከልኝ ። በዚህም ምንም ነገር ለማየት አልቻልኩም ።
እንካ አስቲ አንተ እይበት"ብለው ላንዱ ወታደራቸው ሰጡት
ወታደሩም አይቶበት ጥሩ የሚያሳይ መነጥር መሆኑን ተናገረ ።

አጤ ቴዎድሮስም ወታደሩን "ወይድልኝ ወዲያ ። ከጥቂት
ዓመታት በፊት መቶ አለቃ ፊጠነ (ለስፒዲ) እነዲት ትንሽ
ቁራጭ ምነጣፍ ቢጤ ባቶ ኬሬንስ እጅ ላከልኝ ። በእግዚአብሔር
ኃይል ያቺን ምንጣፍ ያመጣልኝን ሰው አሠርኩት ። አሁንም ይሄ መነ
ጥር የመጣልኝ ለደህና ነገር አይደለም ። ስለዚህ ባለፈው ጊዜ እንዳደ
ረግሁት የመሰለ ነገር ባምጪው ላይ አደርጋለሁ ። "አሉት ።

ፍላድም ነገሩን ለመለወጥና ለማብረድ ሲል "ጃንሆይ ። እነ
ኚህን እስረኞች ካለቀቁ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ወዳጅነት ያለ
አይመስለኝም ። ነገሩም እየከረረ መሔዱ ነው ። "አላቸው ።

"ይምጡ ብየሃለሁ" አሉት ። ቴዎድሮስ "በኃይሌ አልመ
ካም ። ኃይሌን ያደረግሁት በእግዚአብሔር ላይ ነው ። የሰናፍጭ



ንጣት ታህል እምነት ያለው ተራራዎችን ማዘዝ ይችላል"አሉት ።
ፍላድ ይለቀቁ እያለ የሚከራከርላቸው እስረኞች በዚህ ጊዜ 61
ዎች ነበሩ ። ይህም ቁጥር የኤሮፓውያኖችን ሚስትና ልጆች ጨምሮ
ው ። ከፍላድ ክርክር በኋላ ግን የእስረኞቹ ብዛት 62 ሆነ ። ይህን
ጥር ያበዛው የራሱ የፍላድ መታሰር ነው ።

ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ መካ የሚሔዱ ኢትዮጵያውያን ምዕ
ምናን በየደረሱበት አገር የአበሻ ንጉሥ የእንግሊዝን ንግሥት አሽ
ሮች በሰንሰለት አስሮ ካስቀመጣቸው አራት ዓመት አለፈ እያሉ
ማውራታቸው ወሬው እየተዛመተ በመላው ዓለም ተዳረሰ ። የእ
ግሊዝ መንግሥትም ይህ ወሬ እንዳይሰማ ቢያብቅም ወሬው እየ
ሰፋፋና እየገነነ ሔደ ። ሄንሪ ዱፍተን እንደጸፈው ". . . . ከጀዳ
ስከ ቻይና ግንብ ፣ ከኬፕ ጋርዳፊ እስከ ጐልድ ኮስት ተዳረሰ
. . . "ይላል ። ያኔ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር ይተዳደሩ የነበሩት
ገሮች ይህን ወሬ ሰምተው የእንግሊዝን መንግሥት ይከማ ነው
ያሉ እንግሊዞችን ካገራቸው ለማስወጣት ይዶልቱና ያስቡ ጀመር።
እንግሊዞች በየደረሱበት ሁሉ ይሰደቡና ይናቁ ጀመር ። በያሉበትና
በየደረሱበትም በማፈር አንገታቸውን ያቀረቅሩ ጀመር ። በእነዚህ
እስረኞች ምክንያት ኢትዮጵያ በማትታወቅበት አገር ሁሉ
ዝነኛ ሆነች ። እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያ በኤሮፓውያኖች ምክ
ያት በመላው ዓለም ላይ ስሟ የተጠራው ሁለት ጊዜ ነው ። አንደ
ኛው የቴዎድሮስ ኤሮፓውያኖችን ማሠር ሊሆን ሁለተኛው
ግማዊ አጤ ምኒልክ በኤሮፓውያን ላይ አድዋ መንደር ውስጥ
የስገኙት ድል ነው ።

የእንግሊዝ መንግሥት ከቴዎድሮስ ጋር ያለውን ግንኙነት በሰ
ላም ለመጨረስ እንደማይቻል ካወቀ በኋላ የጦር አዋጅ አወጀ ።
የጦሩ አዋጅ ቢወሰንም እስረኞቹን በደህና ለማስለቀቅ እንዴት ይቻ
ላል የሚለው ጥያቄ ክርክር አስነሳ ። በምክር ቤቱ ካሉት አማካ
ሪዎች መሀል ሰር ኸንሪ ቡልወር እና ሰር ሳሙኤል ቤከር ባቀረ
ቡት አሳብ የእንግሊዝ መንግሥት ከግብጾች ጋር ተስማምቶ ቴዎ
ድሮስን ቢያጠቃ ይሻላል አሉ ። በተለይ ሰር ኸንሪ ቡልወር የተባ
ሉት ፓል ማል ጋዜጣ ላይ ሲፅፉ ". . . . ዘመናዊ የሆነው የእን
ግሊዝና የሴፓይ (የሕንድ ፈረሰኛ) ጦር ባንድነት ሆኖ ከግብፅ ጦር
ጋር ተባብሮ ቢጋጠም ዛሬ ቴዎድሮስ ዜጐቻችንን ባሠረበት ሰን
ሰለት ነገ እሱን እንሰቅልበታለን ሲል የግብፅ ቶኸር ነግሮኛል. . . ."
ብለው አወጡ ። ሐሳቡ የእንግሊዝና የሴፓይ ጦር በቀይ ባህር

በኩል ገብቶ ወደ መቅደላ ሲገዝ የግብፅ ጦር ደግሞ በመተማ
በኩል ቢገባ የኢትዮጵያን ኃይል ከፋፍሎ በመውጋት የመሀል ግን
ኙነታቸውን ጥሩ ውጤት ይሰጣል የሚል ነው ። ለዚህ አስተሳሰብ
መልስ ተገኘለት ። መልሱም የአበሻ ሰው ደርቡሾች የሚላቸውን
በአገሩ ላይ ካየ እንኳን ሰንቅ ማቀበል ቀርቶ ከንጉሱ የተጣላው
ሽፍታም ቢሆን ይዋጋል የሚል ነበር ። በዚህም ምክንያት አሳቡ
ወደቀ ።

ኰሎኔል ሜርዌዘር ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ያጠናውን ጥናት
አቀረበ ። የሜርዌዘር ጥናት የአገሪቱን ለምለምነት ገልጾ የኢትዮ
ጵያ ሕዝብም ከዳር እስከ ዳር በንጉሱ ላይ ሸፍቶ መነሳቱን አስ
ረድቶ አገሪቱ ብትወረር ሕዝቡ እንግሊዞችን በደስታ ይቀበላል
ብሎ አሳመነ ። በዚሁ ላይም ኢጣሊያዊው አባ ማስያስ ከቴዎድሮስ
ተነጋግረው እስረኞቹን እንደማይገሉ ቃል የገቡላቸው መሆኑን
የሚያስረዳ የጻፉለትን ደብዳቤ አሳየ ።

ሜርዌዘር ያቀረበው አሳብና ጥናት ትክክለኛ ነበር ። አለቃ ተክ
ለ ኢየሱስ በዚያን ዘመን ስለነበረው የአገር መናወጥ ሁኔታ ሲገልጡ
" . . . ደብረ ታቦርን ከተማ ካደረገ በኋላ ታቦቱ መድኃኔ ዓለም
ተክለና ቤተ ክርስቲያኑን አሳምሮ ሠርቶ ባጡን በብረት ማገረው።
ሥራውን ከጨረሰ በኋላ የእስር ቤት አደረገው ። ከዚህ በኋላ የቤ
ጌምድር ሰው ይሄስ የደህንነትም እያደል እያለ አመል አወጣ ። አገር
ተናወጠ ። ንጉሡን ተጣላው ። በተራራ ላይ እየቆመ . . . . ተላደበ ።
. . . ንጉሡም ሕዝቡ እንደጠላው አውቆ ጠላት ገብቶ እንዳይገድ
ለው ከተማውን የእሾህ አጥር ዙሪያውን እያሳጠረ ይሠፍር ጀመር።
ባላገርና ወታደርም በከተማ እርስ በርሱ ይጋደል ጀመር ። ረሀ
ብም ሆነ ። እመጫት ልጅዋን እስክትጥል ድረስ ። ያንጊዜም ረሃብ
የሆነበት ምክንያት . . . . አጤ ቴዎድሮስ የበጌምድርን እህል ዘርፎ
ደብረታቦር አስገብቶ ለፈረስ ፣ ለበቅሎ ፣ ለአህያ ፣ ቀለብ ይሁን ።
ለከብት ሣር አትስጡ ብሎ አውጆ ነግሮ ነበርና ነው ። ያን ጊዜ
ያን ሶስት ወር ሙሉ ከብት እንደሰው እህል ሲበላ ባጀ ።
አንድ ቀን ቁና እህል አንድ ብር ተሸመተ ። . . . . ከአጤ ፋሲል
ጀምሮ ጥንት ከተማ የነበረውን ጐንደርን ነቅሎ ዘረፈው ። . . . .
ከቤተ ክርስቲያንም እየወጣ የገሊላት መስቀል እያወረደ ወሰደ
. . . ሁሉንም በዘበዘ ። . . . . ''በማለት ያዩትን ዕፈዋል ።

የወሎዋ ገዥ ወይዘሮ መስተዋት ከጐበዜ ጋር ተስማምታ
የመቅደላን አምባ ደምሰሳ ለመያዝ አቅዳለች ። መቅደላ ላይ ያለውን



ቴዎድሮስን ሠራዊትም በረሃብ ለማዳከምና ለመፍጀት ከመቅደላ
ምባ ሥር በየሳምንቱ አንድ ቀን ከሚውለው ገበያ ማንኛውም
ሱዋ ሰው የሆነ የወሎ ኦሮሞ ገበያው ላይ ምንም ዓይነት ሸቀጥ
ዞ እንዳይሔድ በአዋጅ አስከለከላለች ። በደላንታ በዳሞት የሚገ
ው ሠራዊትም እያደፈጠም ይሁን በግልፅ የቴዎድሮስን ሠራ
ት እንዲያጠቃ አዛለች ። እንዲያውም የሸዋው ምኒልክ ለባላን
ዋ ለወርቂት አግዘው የመስተዋትን ሠራዊት ባይወጉ ኖሮ መቅ
ላን ከቴዎድሮስ ሠራዊት አላቃ ለመያዝ ቀላል ሆኖላት ነበር ።

የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ መቅደላን ወርረው ለመያዝ ዘምተው
መቅደላ አካባቢ ከደረሱ በኋላ የጊዜውን ሁኔታና ያላቸውን ኃይል
ምተው ተመልሰዋል ። ምኒልክ ከራሳም ጋራ በምስጢር ባደረጉት
ምምነት መሠረት እስረኞቹን ከመቅደላ ማስፈታት ቢችሉ ኖሮ
እንግሊዝ መንግሥት የእላቸውን ንጉሰነት ሊያውቅላቸው እንደሚ
ል ቃል ተገብቶላቸው ነበር ። ምንም እንኳ ምኒልክ መቅደላ
ይዩ ድረስ ቢዘምቱም በጊዜው ቴዎድሮስ መቅደላ አልነበሩ
ና እቴጌ ጥሩነሽ ሊከዳቸው የነበረውን የቴዎድሮስን ሠራዊት
ንዲመለስ በማድረጋቸው መቅደላ ሳይያዝና እስረኞቹ ሳይፈቱ
ሩ ።

ሌላው የቴዎድሮስን ኃይል የቀነሰውና ብዙ ተከታይ ያገኘው
ዋግሹም ጐበዜ መሸፈት ነበር ። የዋግሹም ጐበዜ አባት ዋግሹም
ብረመድኅን ለአጤ ቴዎድሮስ ተወዳጅ ባለሟል ነበሩ ። አጤ ቴዎ
ድሮስ አንድ ቀን ተቆጥተው እንዲገደሉ አዘዙ ። የዚያን ጊዜ
ጳሱ አቡነ ሰላማ ነበሩና አማልደው ዋግሹም ገብረ መድህንን
መገደል አዳኑዋቸው ። ዋግሹም ገብረ መድህንና ልጃቸው ወጣቱ
ጐበዜ ጊዜ ጠብቀው ሲመቻቸው ከቴዎድሮስ ከድተው ትውልድ
ገራቸው ላስታ ገቡ ። በላስታም ሆነው ላስታ ከቴዎድሮስ የተ
የ ራሱን የቻለ ግዛት ነው ብለው አወጁ ።

ዋግሹም ገብረ መድህን ሸፍተው ላስታ ገብተው ማወጃቸውን
ሰሙት አጤ ቴዎድሮስ የዋግሹም ገብረ መድህንን ወንድም
ፈረን ዋግሹም ብለው ሾመው ላስታ ሰደዱዋቸው ። ዋግሹም
ፈረም ላስታ ዘምተው ወንድማቸውን ዋግሹም ገብረ መድህ
ን በጦር ኃይል ድል አድርገውና ማርከው አምጥተው ላጤ ቴዎ
ድሮስ ሰጡ ። በዚያን ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ዋድላ ላይ ነበሩና ምር
ኛው ዋግሹም ገብረ መድህን እንደደረሷቸው ሠራዊቱ እንዲያያ
ው ከደንኳናቸው ፊት ለፊት ካለ ዛፍ ላይ አሰቀሉዋቸው ።

ጐበዜ ምንም እንኳ ከአባታቸው ጋር ቢማረኩም ጠፍተው
ከቴዎድሮስ እጅ አመለጡ ። ከዚያም ተደብቀው ሲኖሩ በአሁኑ
ጊዜ የቴዎድሮስ ኃይል መዳከሙንና ሕዝቡ ጠልቶ መሸፈቱን
ሲሰሙ ከተደበቁበት ወጡ ። የአባታቸውን አሽከሮች አሰባስበው
"በደልህን ልወጣልህ ተነስቻለሁና ተከተለኝ" ብለው አወጁ ።
የላስታም ሕዝብ አዋጃቸውን በደስታ በለተቀበለው ላስታ ከቴዎ
የላስታም ሕዝብ አዋጃቸውን በደስታ በለተቀበለው ላስታ ከቴዎ
ድሮስ ሥልጣን ሥር ወጣ ። እንዲያውም የጐበዜ ኃይል በመበር
ታቱ እስከ ትግራይ ድረስ ዘምተውና አስገብረው ግዛቱን ለሚስታ
ቸው ወንድም ለደጃዝማች ካሣ (በኋላ አጤ ዮሐንስ ለተባሉት)
ሰጥተው ተመለሱ ።

ዋግሹም ጐበዜ ከራሳም ጋር ግንኙነት ስለነበራቸው በሚስ
ዮር ባደረጉት ስምምነት ጐበዜ መቅደላን ቢይዙና እስረኞቹን ቢፈ
ስፈቱ የእንግሊዝ መንግሥት የአበሻ ንጉሥነታቸውን እንደሚያው
ቅላቸው በለተነጋገሩ በ1859 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ መቅደላን ለመያዝ
አስበው ነበረ ። ነገር ግን በመጀመሪያ የሚሻላቸው ቴዎድሮስን
መውጋት መሆኑን አምነውበት የመቅደላን መያዝ ተውት ። ወደ
አጤ ቴዎድሮስም ቢዘምቱ የቴዎድሮስ ታማኝ የሆኑት ተሰማ እን
ግዳ የተባሉት የጋይንት ባላባትና ገዥ ድል አደረጓቸው ። በትግራይ
የሾሙዋቸው ደጃች ካሣ ጐበዜን ከድተዋቸው ነፃነታቸውን አወጁ ።
እንዲህ ዓይነቱ መከፋፈል ባይኖር ኖሮ ቴዎድሮስ በእንግሊዝ ጦር
አይደፈሩም ነበር ።

ቴዎድሮስ አብዛኛው ሠራዊታቸው ይከዳቸው ጀመር ። እለት
በዕለትም የሠራዊታቸው ብዛት እየቀነሰ ሔደ ። ከጦር አዛዦቻቸው
መሀል የታወቁት ራስ ዕድሉ የተባሉት ቀን በቀን ከቴዎድሮስ ከድ
ተው ሠራዊታቸውን አስከትለው ሔዱ ። ቴዎድሮስም በመላከ
ተኛ ጦር ለማስወጋት ፈልገው መላከተኛውም ጦር አብሮ እንዳ
ከዳ ብለው ተውት ።

የጋይንቱ ባላባትና ጀግናው የሠራዊቱ መሪ ዘለለው የተባለው
ከቴዎድሮስ ከድቶ 200 ያህል ፈረሰኞች አስከትሎ አገሩ ጋይንት ገባ ።
የጋይንትንም ሕዝብ በስሩ ሰብስቦ ቴዎድሮስ ቢመጡ ለመዋጋት
ተዘጋጅቶ ተቀመጠ ። የዳሞትና ደላንታም ሕዝብ በዚያ ይቀለብ
የነበረውን የቴዎድሮስን ሠራዊት ፈረሰኛ በቅሎ ማርኮ ሸፈተ ።
ብላንክ እንደሚለው "..... በሰኔ ወር 1859 ዓ.ም. ያለግዛት
ንጉሥ ያለ ጦር ሠራዊት ጀኔራል ሆኑ ። ...." ለመቅደላ



ቅራቢያ የሆኑትን አንዳንድ መንደሮች ባሏቸው ወታ
ሮች ወግተው ለመያዝ ሲዘምቱ ሕዝቡ ጠንከሮ በመዋጋቱ በለው
ያሉ ሠራዊታቸውን ያበረታቱ የነበሩት ቴዎድሮስ ሠራዊታ
ቸውን ሸሸ ከማለት ደረጃ ደረሱ ።

1859 ዓ.ም. ለቴዎድሮስ የመከራ ዘመን ነበር ። ይህንንም መከራ
መጣባቸው ጭካኔያቸውና በኃይል አገዛለሁ ማለታቸው ነበር ።
ሸፈተባቸው መኳንንት ቀርቶ ተራው ሽፍታ ሁሉ ቴዎድሮስ በሠ
ሩበት አካባቢ እየመጣ አደጋ ይጥልባቸው ጀመረ ። ሠራዊታ
ቸውም በየቀኑ እየከዳቸው በመሔዱ ቴዎድሮስ ሠፈራቸውን
አጥር እያሳጠሩ ሠራዊቱን ያስጠብቁ ጀመር ። ይህም ሁሉ ሆኖ
ቴዎድሮስ ርህራሄ አላሳዩም ። የሚማረኩትንም ሽፍታ ሆነ ታማኝ
ወታደራቸውን በየጥቃቅኑ ጥፋት ሁሉ እጅና እግር ማስቆረጣቸ
ውና በእሳት ማቃጠላቸውን አልተው አሉ ። በዚያን ጊዜ ለቴዎ
ድሮስ መጠነኛ እርዳታ ያደረገው የባላገሩ ሕዝብ ነበር ። ይሄውም
ቴዎድሮስ ሠራዊት እየከዳ በሚሔድበት ጊዜ ብድሩን ለመመለስ
ያለ ባላገሩ ይፈጀው ጀመር ። ስለዚህ የቴዎድሮስ ሠራዊት ቢከዳ
ባላገሩ እንደሚገድለው በማወቁ ከዳቱ ጋብ አለ ። ቢሆንም ከመቶ
ሺህ በላይ ወታደር ያስከትሉ የነበሩት ቴዎድሮስ በአሁኑ ጊዜ
የቀሩዋቸው ስድስትና ሰባት ሺ የሚሆን ወታደሮች ብቻ ናቸው ።

አንድ ቀን ብስጭትጭት ያሉት ቴዎድሮስ ከቀሩዋቸው ሠራ
ዊታቸው መሀል ሆነው "ሁላችሁም እንደጠላችሁኝና ለመከዳ
ትም እንደምትፈልጉ አውቄአለሁ ። ከዚህ ሁሉ ነገር ለምን እኔን
አትገድሉኝም፤ እናንተ በሺ የምትቆጠሩ ናችሁ ። እኔ ግን ብቻየን
ነኝ ። ግደሉኝና እረፉ" ብለው ተናግረው በፀጥታ ቆሙ ። ከወታ
ደሩም ምንም መልስ ስላላገኙ "መልካም ነው እናንተ የማትገ
ድሉኝ ከሆነ እኔ ሁላችሁንም አንድ ባንድ እያልኩ እገላችኋለሁ"
አሉ ።

ይህን የመሳሰለውን ሁሉ ነው ሚርዌዘር አጥንቶ ለእንግሊዝ
መንግሥት ያቀረበው ። የሚርዌዘርም ሐሳብና ሪፖርት በእንግሊዝ
መንግሥት ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ በቴዎድሮስ ላይ የጦር አዋጅ
ታወጀ ።

ምዕራፍ 14

# ጦር መጣ


እንግሊዞች በኢትዮጵያ ላይ የጦር እዋጅ ካወጁ በኋላ ዘማቹ ጦር የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት የነበረው የሕንድ ጦር እንዲሆን ተመ ረጠ ። የሕንድ ጦር የተመረጠበት ምክንያት ለእንዲህ ዓይነቱ መን ገድና ለሌላውም ጦርነት ልምድ ያለው ሠራዊት በመሆኑና በቀላሉም ቀይ ባህር ለመድረስ ስለሚችል ነው ።

ለዚህ ለሚዘምተው ጦር መሪም አዝማቹ ጄኔራል ናፒር እን ዲሆን ተወሰነ ። ጄኔራል ናፒር ለዚህ ውጊያ አዝማችነት የተመረ ጠበት ብዙ ምክንያቶች አሉ ። ናፒር በትምህርቱ ላቅ ያለውን ሥፍራ የያዘው በኢንጂኔርነቱ ነው ። በሕንድ ጦር ሠራዊት ውስጥ እያለ በሕንድ አገር ብዙ መንገዶች (ቦዮች) ድልድዮችና የመሳ ሰሉት ሁሉ በሱ ኢንጂኔርነት ተሠርተዋል ። በጦር ሜዳም ቢሆን በማዋጋት ብቻ ሳይሆን በመዋጋትም ጭምር የታወቀ ሰው ነው ። ሁለት ጊዜ የተቀመጠበት ፈረስ ከሥሩ እየተገደለበት በተአምር የዳነ ሰው ነው ። ብዙ ጊዜ በጦር ሜዳ ላይ ቆስሎ ለቁስሉ ሳይጨነቅ ወይም ጥግ ሳይዝ ወይም ወደኋላ ሳይመለስ ትኩስ ቁስሉን እንደ ያዘ ብዙ ጊዜ የተዋጋና ያዋጋ ሰው ነው ። የእንግሊዞች ጦር ቻይናን በወረረ ጊዜ ናፒር በድል አድራጊነት ቀድሞ ፔኪንግ የገባው እሱ ነው ። ከዚያም ተመልሶ በሕንድ አገር ያለው የቦምቤይ ጦር ሠራዊት አዛዥ ሆነ ። በጨዋታው ፥ በቀልደኛነቱ ፥ በደግነቱና በፍ ርድ አሰጣጡ ወታደሩ ሁሉ ይወደዋል ። ያከብረዋልም ይህ የሱ ጦር ወደ ኢትዮጵያ እንዲዘምት የተወሰነው ።

ናፒር ወደ ኢትዮጵያ ለሚዘምተው ጦር አዝማች መሆኑ ከተ ነገረው ቀን ጀምሮ ስለኢትዮጵያ ማጥናት ያዘ ። ኢንጂኔሮቹንና የጦር መኰንኖቹን ሰብስቦ ከጀምስ ብሩስ ጀምሮ ስለኢትዮጵያ የተ ጻፉትን መጽሐፍት ሰብስበው እንዲያነቡና ስለኢትዮጵያ እውቀት እንዲኖራቸው አዘዘ ። ይህም ብቻ ሳይሆን በዚያ ዘመን በሕይወት የሚገኙትን ስለኢትዮጵያ የሚያውቁ ሚስዮናውያንና ሌሎችም ለን



ን ተሰብስበው ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን አንድ ጥናት ንዲያቀርቡ አደረገ ። ይህ በዚህ እንዳለ በኤደን የፖለቲካ ኃላፊ የነው ሜርዌዘር ቀይ ባህርን ተሻግሮ ለእንግሊዝ ጦር ማረፊያ ሚሆን ቦታ መርጦ እንዲያዘጋጅ አዘዘው ።



ጄኔራል ሮበርት ናፒየር

በአገሪቱና በሕዝቡ አጠናን በኩል ናፒር ይህን ካደላደለ ኋላ እሱ ደግሞ በ1859 ዓ.ም. በነሐሴ መግቢያ ላይ የሚያስፈል ውን የወታደር ብዛትና መሣሪያ ለእንግሊዝ መንግሥት አቀረበ። ቀረበውም መጠይቅ 12,000 ተዋጊ ወታደሮች ፥ 20,000 በቅሎ ችና የማጓጓዣ እንሰሶች ፥ በያይነቱ መድፎችና በተለይ ከፍተኛ ተራራ መድፎች ፥ ጦሩን የሚያጓጉዝበት 280 መርከቦችና ከብት ሚነዱ ተራ ሰዎች እንዲሰጠው ጠየቀ ።

ለመዋጊያ የሚያስፈልገውን መጠይቅ ጽፎ ከጨረሰ በኋላ ጦሩ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ደግሞ በዝርዝር አቀረበ ። ህም ያቀረበው መጠይቅ ከባዶቹን መድፎች የሚሸከሙ 44 ዝሆ ች ፥ በኢትዮጵያ ምድር ከገቡ በኋላ ከወደብ ጀምሮ የሚዘረጋ 2 ኪሎ ሜትር ወይም ሃያ ማይልስ ርቀት የሚሆን የባቡር ሐዲድ


መስመር ፥ የባቡሩ ጋሪዎችና ጉታቾች ፡ ወደብ ላይ የሚተከሉ ታላላቅ ባውዛ መብራቶች ፡ ለመጋዘን መሥሪያ የሚሆኑ የተለያዩ ዕቃዎች ፥ የባህሩን የጨው ውሃ ጨውን ለይተው የሚያጣሩና ንፁህ ውሃ የሚያስገኙ ሁለት ኮንደንሰሮች ፥ ብዙ ሙቶ ማይል ርዝማኔ ያለው የቴሌግራፍ ሽቦ በጠቅላላው ያዙታቸው ሆስፒታል የሆኑ ሶስት መርከቦች ከበረዶ መሥሪያ ዕቃዎቻቸው ጋር ሆነው የተሟላ የሕክምና መሣሪያ ያላቸው እንዲሰጡት ጠየቀ ። ይህም ብቻ ሳይሆን በዘመኑ በኢትዮጵያ መገበያያ የነበረው ማርትሬዚያ ብር 500.000 እንዲዘጋጅለት አሳሰበ ።

ለወታደሩም ለእያንዳንዱ ነጭ ወታደር ሁለት ሁለት ተለዋጭ ቧት ጫማ ፥ አንድ የብረት ቆብ ፥ አንድ ከሐር የተሠራ ቀበቶ ፥ አንድ ጥንድ የጅ ሹራብ (ጓንት) ፥ ለእያንዳንዱ የበላይ መኰንን ሁለት ሕንዳዊ አሽከሮች ፥ እንዲሰጡትና አንዱ ለሰውየው ሲያገለግል ሌላው ለፈረስ ጠባቂነትና ቀላቢነት የሚሆን ፥ ሕንዳዊ ለሆኑት ወታደሮች ደግሞ ለእያንዳንዱ ወታደር ለወር 5,833 ሩፒ ወይም 580 ፓውንድ ሂሳብ ወጭ እንዲሆን ሲጠይቅ በምግብ በኩል ደግሞ 50,000 ቶን የሚመዝን የተለያየ ምግብና 30.000 ጋሎን ሩም የተባለው መጠጥ እንዲሰጠው ጠየቀ ።

ናፒር ይህ ሁሉ እንዲሰጠው ከጠየቀ በኋላ በእስቸኳይ በመንግሥት በኩል እንዲጠና ታዞ ጥናቱ ተፈፀመ ። በተጠናለትም መሠረት 13,000 ተዋጊ ወታደሮች ፥ እነዚህም 4,000 ኤሮፓውያንና 9,000 ሕንዳውያን እንዲሆኑ ፥ 19.000 አሽከሮችና ከብት ነጂዎች በጠቅላላው በሰው በኩል 32,000 ኃይል እንዲሰጠው ተወሰነ ። ለዕቃና ጦር መሣሪያ ተሸካሚነት በጠቅላላው 55.000 እንሰሳት እንዲዘጋጁለት ታዘዘ ። የጠየቃቸውም መርከቦች በሙሉ እንዲሰጡትና ለእነዚህም መርከቦች ኪራይ የሚከፈል ግማሽ ሚሊዮን ፓውንድ ተፈቀደለት ።

የኪራይ መርኮቦቹ ከካልካታ ፡ ከቦምቤይ ፡ ከሊቨርፑል ፥ ከለንደንና ከሌላም ቦታ ሁሉ ተሰበሰቡ ። መድፍ ይሸከማሉ የተባሉት ዝሆኖች በመርከቦቹ ግድግዳ ዙሪያ እየታሠሩ ተጫኑ ። ሌላው ዕቃና የጦር መሣሪያ ሁሉ ሲጫን ከረመ ። ወደ ኢትዮጵያ ጠረፍ ተልኮ የማረፊያ ቦታ እንዲያጠና የታዘዘው ኰሎኔል ማ~ዌዘር እስቲመለስና ጥናቱን እስቲያቀርብ ጓዙ አይነሳም ነበርና ሜር ዌዘር ጥናቱን ፈፅሞ ገባ ።





የአምባአላጌ ተራራ

ሜርዌዘር ጥናቱን ፈፅሞ ናፒር ዘንድ እንደደረሰ ለኀዙ ወይም ለጦሩ ማሳረፊያ የተመረጠው ቦታ ወደብ ዙላ መሆኑን ተናገረ ። ዙላ የተመረጠበትም ምክንያት ከጥንቱ የኢትዮጵያ ወደብ ከአዶሊስ አቅራቢያ በመሆኑና ወደ መሀል አገር ለሚደረገውም ጉዞ የጥንት ግሪካውያን ነጋዴዎች ከአዶሊስ ወደ አክሱም ይጓዙበት በነበረው መንገድ ለመጓዝ አመቺ መሆኑ ስለታመነበት ነው ። ሌላው ለምርጫ ያበቃው ደግሞ ያንጊዜ ዙላ በግብጾች እጅ የተያዘ በመሆኑ በዚያ ያሉ ግብፃውያን ሹማምንት የእንግሊዝን ጦር ለመርዳት ቃል ስለገቡም ነው ። ሌላው ደግሞ አባ ዘካርያስ የሚባል ኢትዮጵያዊ ሮም የተማረ የካቶሊክ እምነት ተከታይ "ከዙላ በሰንዓፌ በኩል ቢታለፍ መንገዱ በጣም ቀና ነው" ብሎ ስላማከራቸውም ጭምር ነበር ። ዙላ ከመመረጡ በፊት በኰሎኔል ሜርዌዘር የሚመራው አጥኚ ቡድን እስከ ታጁራ ድረስ በመሔድ ብዙ ወደቦችን አጥንተው ነበር ።

የወደቦቹ ጥናት በሚካሔድበት ጊዜ ከአጥኚው ቡድን ጋር አብሮ የነበረው ሙዚንጀር እስከ ታጁራ ድረስ በመሄድ አጥንቷል። ሐንፊላ ደሴት ለቅርበቱ ለወደብነቱም ተመርጦ ነበር ። ግን በጉዞ ጊዜ የጨው መሬት ስላሰው ለእግረኛው ወታደር አስቸጋሪ መሆኑ ታስቦ ቀረ ። ምጥዋ ጥሩ ወደብ ሆኖ ሳለ በግብጻዊ ያለ መስማማት ምክንያት ቀረ። ታጁራ ተመርጦ ከወደቡ በኋላ 200 ማይልስ ያህል የሚርቅ ውሃ የሌለበት የበረሃ መንገድ ስላለው ቀረ ።


የመጀመሪያው ቀዳሚ ጦር 10ኛው የቦምቤይ ተወላጆች እግረኛ ጦር የሚባለው ጥቅምት 11 ቀን 1860 ዓ.ም. ዙላ አጠገብ ሙልቅጦ ከተባለችው ባህር ዳርቻ ወረደ ። ይህ በመሐንዲሶችና በሠራተኞች የተመላው ቀዳሚው ዘማች ከሙልቅጦ እንደወረደ ወዲያውኑ ሥራውን ጀመረ ። ሥራውም በወደቡ አካባቢና እስከ ዙላ ድረስ ለሚመጣው ጦር ማረፊያ ማዘጋጀት ነበረ ።

በጥቅምት ወር መጨረሻ ገደማ ከባህሩ ውስጥ እበከ መሬት ድረስ ያለ የመርከቦች ማስጠጊያ እና የዕቃ ማራገፊያው ጄቲ (ግንብ) ተሠርቶ አለቀ ። በግምቡ (በጂቲው) ላይም የባቡር መሔጃ ሐዲድ ከባህሩ መሀል እስከ ምድር ድረስ ተዘረጋ ። ይህ ግንብ በባህር ላይ የመጡት መርከቦች ይጠጉትና ጭነቱ የሚራገፍበት ነው ። ይህም ሚሠራው መርከቦቹ ከመሬቱ ዳርቻ ድረስ ለመውጣት ስለ



ማይችሉ ነው ። ይህም ጄቲ እስከነሐዲዱ ፈራርሶ ሐዲዱም ዝጉ አይቼዋለሁ ።

ጊዜያዊ ቤቶችም በባህሩ ዳርቻ ተሠሩ ። ሠራተኞቹም ሕንዶች ፣ ርዶያኖች ፣ ግብጾችና ኢትዮጵያውያኖች በሠፈሩ በመብዛታቸው ያ ውድማ የነበረው ሜዳ ከተማ መሰለ ። እኔ እንዳየሁትም ዛሬም ተመልሶ ውድማ ቢሆንም አንድ ከግንብ የተሠራ ሕንፃ ከባሕሩ ዳርቻ አጠገብ ቆሞ በመጠኑ ቢፈራርስም ለመታሰቢያነት ያህል ይታያል ።



27ኛው የቦምቤይ እግረኛ ወታደር

በሕዳር ማለቂያ ሌላው ሁለተኛው የመርከብ ማስጠጊያ ጄቲ ተሠርቶ አለቀ ። የዚህኛው ጄቲ የባህር ውስጥ ርዝመት 3000 ሜትር ያህል ነበር ። በሱም ላይ የባቡር ሐዲድ ተዘርግቶ ስላለቀ ባቡር መመላለስ ጀመረ ። ከዚህ ለባቡር መስመር መዘርጋት ሥራ በሞያው ጥሩ ችሎታ ያላቸው 176 ቻይናውያን መጥተው ስለነበረ እነሱ ናቸው የሠሩት ። በዚያ አካባቢና ዙላ ድረስ (ዙላ ከወደቡ

ትንሽ ራቅ ይላል) ተመላላሹ ሠራተኛ በመብዛቱ የዙላ ሰዎች አንዳንድ ሱቆችን መክፈት ጀመሩ ።

ሆስፒታሎች ተሠሩ ። ታላላቅ መጋዘኖችና በጣም ሰፋፊ የሆኑ የእንስሳ በረቶችም ተበጁ ። ከባህሩ ጫፍ ከጀቴው መነሻ አጠገብ የቃተከሉት ሁለቱ የውሃ ማጣሪያ ኮንዴንሰሮች በቀን 160 ቶን ከጨው የተጣራ ውሃ ማውጣት ጀመሩ ። ይህም ድጋፍ በየቀኑ በመርከብ ከኤደን እየተጓዘ ለተጠራቀመው በሚሊዮን ቶን ለሚገመተው የተጣራ ውሃ ድጋፍ ሰጭ ሆነ ።

ሥራው እያለቀ በመሔድም ጦሩና የጦር መሣሪያዎቹ መግባት ጀመሩ ። ከግብፅ አገር የተገዙት 11.000 ፈረሶች ፣ በቅሎዎች፣ አህያዎችና ግመሎች ገቡ ። ከሕንድ የሚነሳው ጦርም በየቀኑ ከመርከብ እየወረደ ይሠፍር ጀመር ። በዚህ መሀል በዙላ በሠፈረው ሠራዊት ላይ ያልታሰበ ድንገተኛ አደጋ መጣበት ። የከብት ወረርሽኝ በሽታ ገባ ። በበሽታው የተለከፉ ፈረሶና በቅሎዎች በየቀኑ በመቶ የሚቆጠሩ ያልቁ ጀመር ። ከእንስሶቹ ማለቅ ሌላ ደግሞ ሬሳቸው ከባሕሩ ዳርቻ ይጣል ስለነበር ከባድ በሽታ ያመጣል ተብሎ አሰጋ ዙላ እንደ ቆላ በመሆኑ ሜርዌዘር አሉ ያላቸው የውሃ ጉድጓዶች ሁሉ ስለደረቁ የውሃ እጥረት የሚያሰጋ ሆነ ። የኮንዴንሰሮቹም ማጣራት በየቀኑ ከሚገባው ሰውና እንስሳ ጋር አልመጣጠን አለ ። ይህ ከሆነ በኋላ ጦሩ ተከፍሎ ቀዳሚ ጦር ወደ ሰናፌ እንዲሔድ ታዘዘ ። ሰንአፌ ዋናው ጦር ከሠፈረበት ከባህሩ ዳርቻ 40 ማይልስ ያህል ይርቃል። የቀደመው ጦርም በመሀንዲሶች የተሞላ ስለነበረ የሚጓዘው ለተከታዩ ጦር መንገድ በመሥራት ነበር ።

ይህ ቀዳሚ ጦር ከግብጾች የመሬት ይዞታ ወጥቶ ከደጃዝማች ካሣ (በኋላ አጤ ዮሐንስ ከሆኑት) ግዛት ሲገባ ጦሩን የሚመራው ሜርዌዘር ለደጃዝማች ካሣ ደብዳቤ ፅፎ የማለፊያ ፈቃድ ጠየቀ ። በጻፈውም ደብዳቤ የሚጓዘው በመቅደላ ያሉትን ኤሮፓውያን እስረኞች ለማስፈታት ብቻ መሆኑን ገልጾ በሰላም እንዲያሳልፉት የሚጠይቅ ነበር ። ሜርዌዘር ለጻፈው ደብዳቤም ደጃች ካሣ መልሱን በፅሁፍ አሳወቁት ። ደጃች ካሣ በጻፉት ደብዳቤ ከራስ ወልደ ሥላሴና ከሰባጋዲስ ጋር እንግሊዞች የነበራቸውን ወዳጅነት እሳቸውም እንደሚፈልጉት ገልፀው ይህንንም ወዳጅነት ለማደስ ሁኔታውን ለመነጋገር መርጫ ወርቄን መላካቸውን የሚገልጽ ነበር ።

መርጫ ወርቄ ከደጃች ካሣ የተላከውን ደብዳቤ ለሜርዌዘር ሰጥቶ ሲጨዋወቱ ሜርዌዘር "የመጣነው እስረኞች ወገኖቻችንን





የዙላ ሰፈርና ወደብ

ከመቅደላ ለማስፈታት ነው ። ሕዝቡን ለመንካት ወይም አገሪቱን ለመውረር አልመጣንም . . . . "አለው ። መርጫ ወርቄም የቴዎድሮስን መሸነፍ እነሱም እንደሚፈልጉት ገልጾ ከዚያ በኋላ አገሪቱን ለቀው እንዲወጡ በሚለው ሐሳብ ሁለቱም ወገኖች ተስማምተው ተለያዩ ።

ሜርዌዘር ከደጃዝማች ካሣ የማለፊያውን ፈቃድ ካገኘ በኋላ ከካሣ ግዛት ሲወጣ የሚጠብቀው የዋግሹም ጉበዜ ግዛት በመሆኑ ለእባቸውም ያንኑ የመሰለ ቃል ፅፎ ላከላቸው ። ዋግሹም ጉበዜም በሰጡት መልስ የቴዎድሮስን መውደቅ እንደሚፈልጉ ገልፀው ለዚህ ጉዳይ ብቻ ከሆነ የማይቃወሙ መሆናቸውን ጻፉለት ። የሸዋው ምኒልክ በጦሩ መንገድ ላይ ምንም ግዛት ስለሌላቸው ሜርዌዘር በአሁኑ ጊዜ ደብዳቤ አልጻፈላቸውም ። ኤደን በነበረ ጊዜ ግን የእንግሊዝ ጦር ሊዘምት መዘጋጀቱንና በሚዘምትበትም ጊዜ ምንም ተቃውሞ እንዳያነሱ ፅፎላቸው ተስማምተዋል ። ሜርዌዘር ሰነአፌ ላይ ሆኖ ከታላላቆቹ ገዢዎች ጋር በቃልም በፅሁፍም የመጓዣውን መንገድ ጥርጊያ አሳመረ ።



ናፒየር ከሹማምንቶቹ ጋር

ሜርዌዘር ይህን ካደረገና ካጠናቀቀ በኋላ ለአጤ ቴዎድሮስ በናፒር ስም ደብዳቤ ጻፈላቸው ።

ለቴዎድሮስ

የአበሻ ንጉሥ

"በእንግሊዝ ንግሥት ትእዛዝ በእጅዎ ያለምክንያት የተያዙትን እስረኞች ለማስለቀቅ መጥቻለሁና እስረኞቹን በሙሉ ለቀው እንግሊዝ ሠፈር ከደረስንበት ድረስ እንዲልኳቸው ይሁን ። ግርማዊነትዎ ይህን ትእዛዝ የማይስማሙበት ቢሆን ግን ከግርማዊነትዎ ግዛት በኃይል እንድገባ ታዝዤአለሁ ። ይህንንም የመጣሁበትን እስክፈፅም ምንም የሚያቆመኝ ኃይል የለም ።

"በግዛትዎ ውስጥ የማደርገውም ሆነ የምፈልገው ነገር የለኝም ሥልጣንዎንም አልቀናቀንም ። ዋናው ጉዳይ የተያዙት ሰዎች እንዲለቀቁ መሆኑን አሳውቆታለሁ ።

"ግርማዊነትዎ ይህን የመጣውን አደጋ እስረኞቹን ቶሎ በመልቀቅ ሊመልሱት ይችሉ ይሆናል ። ነገር ግን እስረኞቹ በሰላም



እጄ ካልገቡ ፣ ቢጉላሉ ፣ ወይም አንዳንድ ጉዳት ቢደርስባቸው ኃላፊነቱን የሚወስዱት በግል ግርማዊነትዎ ብቻ ነዎት ። ይህ ከሆነም ለወደፊቱ ምንም ዓይነት ወዳጅነት አይኖረንም ።

አር.ናፒር ሌ/ጄኔራል
የቦምቤይ ጦር ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ ።

ይህን ደብዳቤ ይዞ የሚሔደውን ሰው ከመንገድ ላይ ሽፍቶች አግኝተው ያዙት ። መልእክተኛውም የቴዎድሮስን ስም አንዳይጠራ ፈርቶ እንግሊዞች ለራሳም የጻፉትን ደብዳቤ ይዞ እንደሚሔድ ገለፀ ። ሽፍቶቹም በራሳቸው መልእክተኛ ደብዳቤውን ለራሳም ላኩለት ። ራሳምም ደብዳቤው እንደደረሰው አንብቦ ለቴዎድሮስ በመድረስ ፈንታ ለሱ በመድረሱ በጣም ተደሰተ ። ለቴዎድሮስ ደርሶ ቢሆን ኖሮ በራሳም አስተሳሰብ እስረኞች የተባሉትን ሁሉ እንደሚፈጅዋቸው ስለገባው ደብዳቤውን ደብቆ አስቀመጠው ።

ይህ ሁሉ በሚሆንበት ጊዜ የእንግሊዝ ጦር ዋና አዛዥ ጄኔራል ናፒር ወደ ኢትዮጵያ ገና አልመጣም ነበር ። ናፒር ጦሩንና ጓዙን በሙሉ አስቀድሞ ከላከ በኋላ ታህሣሥ 25 ቀን ሙልቅጦ ገባ ። ጄኔራል ናፒር ከቦምቤይ ወደብ አክታቪያ በተባለች መርከብ ከተከታዮቹ መኰንኖች ጋር ሆኖ ሙልቅጦ ወደብ አካባቢ መርከቧ ስትደርስ ያሉዋት መድፎች በሙሉ ተተኰሱ ። ከመሬት ለአቀባበሉ የተዘጋጁት የጦር መድፎችም አጠፋውን በመተኮስ መለሱ ።

መርከቢቱ ከተዘጋጀው ጄቲ አጠገብ ቆመች ። ጄኔራል ናፒር ከመርከቧ ብቅ ሲል የተሰለፈው ጦር ሙዚቀኞች የወታደር ማርሽ ማሰማት ጀመሩ ። ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቁ የወታደር ሙዚቃ በሚሰማበት ጊዜ ለወሬ የተሰበሰበው የዙላና የአካባቢው ሕዝብ ሴቱ በእልልታ ወንዱ በሆታ በባህሩ ማዕበል ጋር መሬቲቱን በጩኸት አደበላለቋት ። በቀይ ኮት ያጌጠውንና የተሰለፈው የክብር ዘብም በብረት ሰላምታ ሰጠ ። ናፒር የመጣው ወደኋላ ከቀሩት 19 ዝሆኖች ጋር ስለነበረ የዝሆኖቹ በሰልፈኛው መሀል መንጐማለል ለሰልፉ የበለጠ ድምቀት ሰጠው ። እነኚህ ለመቅደላ ጦርነት የመጡት ለማዳዎቹ የኤስያ ዝሆኖች ከታላቁ አሌክሳንደር በኋላ ለአፍሪካ ምድር የመጀመሪያዎቹ ዝሆኖች ነበሩ ። ናፒርም ለሶስት ሳምንታት ያህል በዙላ የተሠራውን በመመልከትና የጐደለውንም በማሟላት ቆይቶ ዘማቹንና ከወደብ የሚቀረውን ጦር ካደላደለ በኋላ ጥር 17 ቀን ወደሰንአፌ ሔዱ ።

ናፒር አስቀድሞ የላከውና በኋላም ይዞት የመጣው ጦርና ስንቅ 32,062 የሰው ኃይልና 27,747 የጭነትና የምግብ እንስሳት ነበሩ። ዝርዝሩን ለማወቅ ካስፈለገ እንደሚከተለው ነው ።

10,231 እግረኛ ወታደር
983 መድፈኛ ወታደር
2,064 ፈረሰኛ ወታደር
2,306 ረዳት ዕቃ ያዥ ወታደር በጠቅላላው 16,18' ተዋጊ ወታደሮች ሲሆኑ ከብት ነጂና ጠባቂው ደግሞ 12,640 ሰዎች ነበሩ ። ለመኮንኖች ተከታይ የሆኑ አሽከሮች ደግሞ ብዛታቸው 3,233 ነበር ።

ይህ ሁሉ ሠራዊትና ጓዝ የመጣው በ669 መርከቦች ነው ። ለመርከቦቹም የተከፈለው የኪራይ ገንዘብ 433,028 ፓውንድ ነበር ። በጓዝ በኩልም መርከቦቹ ጭነው ያጋዙት 306,524 ቶን የሚከብድ ዕቃና መሣሪያ ነበር ። በእንስሳት በኩል ሙልቅጦ የገባው ።

4,189 ፈረስ
16,022 በቅሎ
1,759 አህያ
5,733 ግመል
44 ዝሆን ሲሆን ለወታደሩ ስንቅና ቀለብ እንዲሆኑ የገቡት የሥጋ ከብቶች ደግሞ 7,071 በሬና 12,839 በጐች ነበሩ ።

ጄኔራል ናፒር ይህን ሁሉ ጓዝና ሠራዊት አስቀድሞ እሱ ኢትዮጵያ ምድር ከገባ በኋላ ስመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚነገር አንድ አዋጅ አወጣ ።

"ለገዥዎች፣ ለባላባቶች ፣ ለሃይማኖት መሪዎችና ለአበሻ ሕዝቦች በሙሉ ።

"የአበሻው ንጉሥ ቴዎድሮስ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል የሆነውን ካሜሮንን የእንግሊዝ ንግሥት መልክተኛ ራሳምንና ሌሎችንም ብዙዎችን ኤሮፓውያኖች ከሰለጠነው ዓለም ሕግ ውጭ አስረው መያዛቸውን ሁላችሁም ታውቃላችሁ ። እንዲለቋቸውም በወዳጅነት የተደረገው ድካም ሁሉ አልሆነም ። በዚህም ምክንያት መንግሥቴ አንድ ጦር እንድመራና እስረኞቹን እንዳስለቅቅ አዞኛል ።



"ለእስረኞቹ ወዳጅ የሚሆነው ሁሉ ወይም ነፃነታቸውን እንዲያገኙ የሚያደርግ ሁሉ ይሸለማል ። እንዲጎዱ የሚያደርጉ ግን ያለ ምህረት ይቀጣል ።


"የእንግሊዝ ጦር ሠራዊት በአገራችሁ ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ አስታውሱ ፣ የአበሻ ሕዝብ ሆይ ። የእንግሊዝ መንግሥት ከእናንተ ጋር ጠላትነት የላቸውም ። አገራችሁንም ሆነ ነፃነታችሁን ለማጥፋት ምኞትም የላቸው ። ሃይማኖታችሁ እንደተመሠረተ ፣ ሰዎቻችሁና ሀብታችሁ ሁሉ በጥንቃቄ ይጠበቃል ። ለወታደሮቼ የምታቀርቡት ምግብ ሁሉ ዋጋው ይከፈልበታል ።

"የእንግሊዝ መንግሥት ኃይል ወደ አበሻ ምድር የመጣው የግርማዊት ንግሥትን አሽከሮችና ሌሎችንም ያለፍርድ የተያዙትን ኤሮፓውያኖች ለማስለቀቅና ነፃነታቸውን ለማስገኘት ነው ። ይህ ከሆነ በኋላ በተቻለ ፍጥነት አገራቱን ለቀን እንወጣለን ። ከአበሻ ምድር ውስጥ ምንም ዓይነት ግዛት ለመፈለግ ወይም በአገራችሁ የመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ ልንገባ አልመጣንም"

ናፒር በጉዞው ላይ መጀመሪያ ከሚያገኛቸው ከደጃች ካሣ ጋር በቃል መነጋገሩ ጠቃሚ መሆኑን አወቀ ። በዚህም ምክንያት ይህንኑ ግንኙነታቸውን የሚያዘጋጁና የሚገናኙበትንም ቦታ የሚያስወስኑ መልክተኞች ከሰንአፌ ወደ ደጃች ካሣ ተላኩ ። በኩሎኔልነት ሲያገለግል የኖረው አሁን ብርጋዲየር ጄኔራል ሆኖ የተሾመው ሜርዌዘር የመልክተኞቹ መሪ ሲሆን በውስጡም ጀምስ ግራንት እና የኢትዮጵያን መኳንንት እስከ አጤ ዮሐንስ ዘመን ሲያበጣብጥ የኖረው ሙዚንጀርም አብሮ ነበር ። በጠቅላላው 13 መልክተኞች የሉበት ቡድን ጥር 18 ቀን ከሜጀር ጄኔራል ናፒር ተልኮ ወደ ደጃች ካሣ ሔደ ። ጥር 23 ቀንም ከደጃች ካሣ ዋና ከተማ አድዋ ገባ ።

መልክተኞቹ አድዋ እንደደረሱም በመርጫ ወርቄ ወንድም ገብሩ ወርቄ ባልደረባነት በገቡ በማግሥቱ ከደጃች ካሣ ጋር ተገናኙ ። ገብሩ ወርቄ ከሕንድ አገር ቦምቤይ የተማረ በመሆኑ እንግሊዝኛ በሚገባ ይችላል ። ለባልደረባነት የተመረጠውም በዚሁ ምክንያት ነበር ።

ደጃች ካሣ የሸሬውን ገዥ ጉግሣን ፣ አማካሪያቸውን የፀራገብረ ሚካኤልን ፣ የሰላዋውን ገዥ ኃይሉ ማርያምን ፣ የገራልታውን ሐጐስን ፣ የአክሱሙን ንቡረዕድ ገብረ ውበትን ፣ ሹም ተምቤን እን



ራስ ካሣይ በአዲግራት ከእንግሊዝ ጦር ሲደርሙ




ን፣ ሹም አጋሜ ጥርሶን ፣ የሰባጋዲስን ልጅና ሌሎችንም መኳንንት ይዘው ተቀበሉዋቸው ። መልእክተኞቹም የመጡበትን ጉዳይ ሳይ ሆን የወዳጅ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ታላቅ ግብር ተደረገ ። በማግስቱ የመጡበት ጉዳይ ንግግር ተጀምሮ ከናፒር የተጻፈውን ደብዳቤ መልእክተኞቹ ለደጃች ካሣ ሰጡ ። ደብዳቤው ተነቦና ተተ ርጉሞ እንዳበቃም ደጃች ካሣ ሲናገሩ “. . . . አባቶቼ ከእንግሊዝ ጋር ወዳጅነት እንዳበጁ ሁሉ እኔም ወዳጅ በመሆን ከብትና እህል በማቅረብ እረዳለሁ . . . . ”አሉ ።

በዚህና ከናፒር ስለሚገናኙበትም ቦታና ጊዜ ተስማምተውና ምስነው የናፒር መልእክተኞች ጥር 27 ቀን ከአድዋ ተነስተው ጉዞ ኣቸውን ጀመሩ ። ከመልእክተኞቹም ጋር ሊቀ መኳስ ይልማ ብረው እንዲሔዱ ተደርጎ ነበር ። ሊቀ መኳስ የአድዋ አዋሳኝ ጐንደብታ ገዢ ናቸው። እናታቸው የሰባጋዲስ ልጅ ሲሆኑ አባታ ቸው ሊቀመኳስ ደስታ ይባላሉ ። ደስታ ደግሞ የጐንደብታው የፊ ተውራሪ ገብረ አምላክ ልጅ ናቸው። ከመልእክተኞቹ ጋር ሊቀ መኳስ ይልማ ዋና ሆነው አብረው እንዲሔዱ ይላኩ እንጂ ቀሳ ውስት ፣ አርባ ያህል ጦር የያዙና ሃያ ጠመንጃ የያዙ ተከታዮች ብረው ነበሩ ።

እነኝህ መልእክተኞች ከናፒር ሠፈር መድረሳቸው እንደተሰማ ፒር ከፍተኛ አቀባበል እንዲደረግላቸው አዘዘ ። ከዚያም የመ እክተኞቹ የሁለቱም ወገን ቡድን ከናፒር ጋራ ተገናኝተው ሰፊው ከተነጋገሩ በኋላ በማግስቱ ኢትዮጵያውያኖቹ መልእክተ ኞች አንድ ወጥ ልብስ (ዩኒፎርም )በለበሱ ወታደሮች አጃቢነት ተሸኝተው ወደ አድዋ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። ሁለቱም ወገኖች የተ ስማሙት የትግራዩ ገዥ ደጃች ካሣና የእንግሊዙ ጦር አዛዥ ሌተና ጄኔራል ናፒር ሐራማት ውስጥ ማይ አደብ ከተባለው ቦታ እንዲገናኙ ተወስኖ ነበር ።

በቀኑ ቀጠሮው ናፒር በ450 ወታደሮች ታጅቦ የካቲት 18 ቀን ማይ አደብ ሲደርስ ደጃች ካሣ አራት ሺህ ከሚሆኑ ጠመንጃና ጦር ከያዙ ወታደሮቻቸው ጋር በዚያው ሠፍረው ነበር ። ቀይ መልክ ያለው የካሣ ድንኳን ተተክሏል ። ከካሣ ሠፈር ማዶ ከትይዩ ቦታ ናፒር ሠፈር ሆኖ ድንኳኑ ተተከለ ። የድንኳኑ ተከላ ሥራ አልቆ ጥቂት ከቆየ በኋላ ካሣ በወታደሮቻቸው ታጅበው ናፒርን ለመገ ናኘት ወደ ናፒር ሠፈር ሔዱ ። ካሣ በአስፈሪ ግርማ ታጅበዋል።



ብርጋዴር ጄኔራል ሜርዌዘር ከካሣ ጋር ተቀምጠው




የተቀመጡባት በቅሎ ግራጫ (ነጭ) ነች ። ካሣ በራሳቸው ላይ ያሠሩት ታላቅ ጉፈር ግርማ ሞገስ ሰጥቷቸዋል ። ታላቅ ዣንጥላ በረጅም ሰው ተይዞላቸው ከበፊታቸው ነጋሪት እየተጎሰመ ፣ እምቢልታ ፣ እየተነፋ የኢትዮጵያን ባንዴራ ቀይ ቢጫ አረንጓዴ የሆነውን (ያኔ እንዲህ ነበር ።) አስቀድመው በ400 ወታደሮች ታጅበው ሔዱ ።

የካሣ መምጣት እንደታወቀ ለአቀባበሉ የክብር ዘብ ተሰልፎ፣ ራሱ ናፒር ባጌጠ ዝሆን ላይ ተቀምጦና ቀያይ ልብስ በለበሱ ዝሆን ተቀማጮች ታጅቦ ታላቅ አቀባበል አደረገላቸው ። ከዚያም ከአቀባበሉ ሥርዐት በኋላ ለመገናኘት ከተዘጋጀው ድንኳን ይዞአቸው ገባ። ጥቂት ረፍት እንዳደረጉ የወይን ጠጅ ቀረበ ። ወይን ጠጅ ለደጃች ካሣ ሲሰጥ በውስጡ መርዝ ወይም መጥፎ ነገር ያለመኖሩን ለመግለፅ ናፒር ራሱ የካሣን ብርጭቆ ተቀብሎ ቀመሰ ።

በንግግሩም ወቅት እንግሊዞች ስለሚያስፈልጋቸው ፣ ነገር ሁሉ ቀደም ብለው የሚያውቁት ሙዚንጀር እንደሚያዘጋጅላቸው ካሣ ተናግረው በእሳቸው በኩል ደግሞ ያለውን ችግር የዋግሹም ጉበዜና በአጋሜ የራስ ባርያው መሸፈት መሆኑን አስረዱ ። ናፒርም ሲመልስ በአገራችሁ የውስጥ ጉዳይ አንገባም ። መሣሪያ ግን እንረዳዎታለን ብሎ በዚህ አሳብ ሁለቱም ወገኖች ተስማምተው ካሣ ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ ። ናፒር በአገራችሁ የውስጥ ጉዳይ አንገባም ማለቱ የጨዋነት መልስ ቢሆንም ዋናው ቁም ነገር ግን ናፒር ከትግራይ ከደጃች ካሣ ግዛት ሲወጣ የሚያጋጥመው ወይም የሚገባበት የዋግሹም ጉበዜ ግዛትና ዋግሹም ጉበዜ በመሆናቸው ነው ።

ደጃች ካሣ ከናፒር ከመለየታቸው በፊት ናፒር ወደ ሠፈራቸው እንዲመጣ ጋብዘውት ስለነበረ በዚያው ዕለት ከተለያት በኋላ ናፒር ወደደጃች ካሣ ሠፈር ሔደ ። ከካሣ ሠፈር ሲደርስም የካሣ ወታደሮች ተሰልፈው እርምታ በመተኮስ ተቀበሉት ። ናፒርም ምርጥ የሆኑትን የካሣን ወታደሮች በማየቱ መደሰቱን ለደጃች ካሣ ገለጠላቸው ። ከዚያም ከካሣ ጋር ተያይዘው ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀው ድንኳን ገቡ ።

ከድንኳኑ እንደገቡም የትግራይ ቆነጃጅት ሴቶች እያባለሉ በትላልቅ ውብ ዋንጫ ጠጅ እየተቀዳ ተሰጣቸው ። ግብር ቀርቦ ምግብ ከተበላ በኋላ እምቢልታ ነፊዎችና ማሲንቆ መቺዎች



ራስ ካሣ ከናፒር ጋር ተቀምጠው ሲጨዋወቱ



ታው ጨዋታ ተጀመረ ። ካሣም ለጄኔራል ናፒር በራሱ ላይ በሳ ጐፈር አሠሩለት ። በወገቡም ላይ ሰገባው ያጌጠና የሚያ ጐራዴ አስታጠቁት ። በእጁም ጦርና ጋሻ በማስያዝ ሸለሙት ህ በኋላ ናፒር ለመሔድ በሚነሳበት ጊዜ ከድንኳኑ በራፍ ሲደ በወርቅ መረሸት ያጌጠች ግራጫ በቅሎ ቀርባ ለመጓጓዣው ጠችው መሆኑ ተነገረው ። መልካም አቀባበል እንደተደረገለት እምቢልታና መለከት ነፊዎች ቀድመው ሙዚቃ እያሰሙ መል አሸኛኘት ተደረገለት ። ናፒር ጐፈሩን አስሮ ጐራዴውን ታጥቆ ሸለማት ግራጫ በቅሎ ተቀምጦ ከሠፈሩ ሲገባ እንኳን ወታ ፥ ጓደኞቹ የሆኑት የእንግሊዝ መኰንኖች እንኳ ናፒር መሆ አላወቁም ነበር ።

ከዚህ በኋላ የእንግሊዝ ጦር የመቅደላ ጉዞውን ቀጠለ ። የእን ጦር በሚጓዝበት ጊዜ በየደረሰበት ሁሉ ሕዝቡ እየወጣ ኑቅ ይመለከተው ነበር ። ጉዞው ላይ ፈረሰኞች ይቀድማሉ። ኞቹም እረንጓዴ ልብሰ ለብሰው ውብ ባርኔጣ ያደረጉ ናቸው። ንኖቹ ግን ብርማ መልክ ያለው የብረት ባርኔጣ አድርገዋል ። ሰኞቹ ቀጥሎ የሚጓዘው እግረኛው ወታደር ነው ። ከእግረኛው ደር መሀል የሆኑት ሕንዳዊ ወታደሮች ከጉልበታቸው የሚደርስ ጓዴ ቁምጣ ታጥቀዋል ። ቀይ ኮት ደርበዋል ። አረንጓዴ ጥም ጠምጥመዋል ። ሕንዳዊ ያልሆኑት ወታደሮች ደግሞ ሱሪያቸው ላይ ሲሆን ነጭ ኮፍያ (መለዮ) አድርገው ይጓዛሉ ። ይህ ታይቶ ያልታወቀ የአለባበስና የሰልፍ ሂደት ሕዝቡ እያየ ንቅም የበለጠ ግን የሚደነቀው ታላላቆቹን መድፎች የተ ት ዝሆኖች በየራሳቸው ላይ ለ ው ተቀምጦባቸው ሲጓዙ ነበር ።

ጉዞው ላይ ናፒር በየደረሰበት ሠፈርና መንደር ሁሉ ከሠ ቹም ጋር ሰላማዊ ንግግር በሚደረግበት ጊዜ ከብሪትሽ ም ለቅርሳዊ ዕቃዎች ፍለጋ ከጦሩ ጋር የመጣው ሪቻርድ ስ ደግሞ በየቤተ ክርስቲያኑ እየገባ ለሙዚየም የሚሆኑ ችን ይፈልግ ነበር ።

ጃዝማች ካሣ ግዛት ጨርሰው ከመውጣታቸው በፊት ካለው አገር ከላስታ ገዥ ከዋግሹም ጐበዜ ጋር በሰላም ፍ መነጋገር ያስፈልግ ነበር ። ይህንኑ ጉዳይ እንዲነጋገር ጀር ተልኮ ቀድሞ ሔደ ። በዚያን ጊዜ ዋግሹም ጐበዜ በጌምድር ሔደው ነበር ። በቦታቸው ግን እኅታቸውና የጐ



የእንግሊዝ ወታደር መቅደላ አፋፍ ሲወጣ



ዜ ጦር ዋና አዛዥ ለሆኑ ደጃች መሸሻ ስለነበሩ በተከዜ ሸለቆ
ጉል ፍ ከሚባል ሥፍራ ከሙዚንጀር ጋር ተገናኙ ። ከናፒር
ተላከው መልዕክት መሠረት ደጃች መሸሻ ተስማምተው
እንግሊዝን ጦር እየመሩና እየጠበቁ ያለምንም ችግርና ኮሽታ ደላ
ታ ደረሱ ።

የእንግሊዝ ጦር ደላንታ ላይ የለንዴ በተባለ ቦታ ሠፈር
ርጐ ሳለ ናፒር ራሱ ለአጤ ቴዎድሮስ የመጀመሪያውን ደብ
ቤ ጻፈ ደብዳቤውም "…. በእንግሊዝ ንግሥት ትእዛዝ ከጦር
ራዊቴ ጋር መቅደላ አጠገብ ደርሻለሁ ። የታዘዝኩትም በእርሶ
ና የሚገኙትን መልከተኛዎን ራሳምን ቆንሲል ካሜሮንን
ኪም ብላንክንና መቶ አለቃ ፕሪዴውክስን እና ሌሎቹንም
ሉን በግርማዊነትዎ ኃይል ሥር ያሉትን አውሮፓውያኖቹን ለማ
ቀቅ ነው ግርማዊነትዎን የምጠይቀው እነኝህን ሰዎች በተ
ለ ፍጥነትና ሰላማዊ ሠፈሬ ድረስ እንዲልኩልኝ ነው …."
ጊል ነበር ።
የእንግሊዝ ጦር በዚያው የለንዴ በተባለው ቦታ እንደ
ፈሩ ለቴዎድሮስ በተጻፈው ደብዳቤ መልሱ እስኪመጣ ድረስ
ግ ጉበዜ እንጀራ እባት ከዋድላው ገዥ ከደጃች ወልደ ቂር
ለ (ኪሮስ) ከደላንታው ባላባት ልጅ አቢጋዝ ጋር ተገናኝተው
መካከር 20.000 ኪሎ ግራም ስንዴ 15.000 ኪሎ ግራም
ቄት 50.000 ኪሎ ግራም ገብስ ከዋድላ ከደላንታና ከዳ
ንት ሕዝብ ቀርቦላቸው ገዙ ። መጋቢት 29 ቀን የወሎዋ
ሥት የወይዘሮ መስተዋት ልጅ ኢማም አህመድ ከጉናቸው
ደሚሰለፍና ቴዎድሮስን ለመጣል እንዲበረቱ የሚያበረታታ
ዳቤ በእናቱና በራሱ ስም ጽፎ ለናፒር ላከ ። ናፒርም ለደረሰው
ዳቤ መልስ በእንግሊዞች በኩል ምንም የሚያውክ ነገር
ደሌለና ቴዎድሮስ ግን በሌላ በኩል ከመቅደላ አምልጠው
ዳይወጡ ሠራዊታቸውን ጠባቂ እንዲያደርጉ ጽፎ ለአረብኛ
ቋ አስተርጓሚነት አብሮአቸው በነበረው በአከበር አሊ እጅ
ላቸው ። በፊት የመቅደላ ገዥ የነበሩትና ከቴዎድሮስ ከድተው
ጡት ቢትወደድ ኃይሉ ከእንግሊዝ ጦር ዘንድ መጥተው
ቅደላን ምሽግ ሁኔታ መድፎቹ የተጠመዱበትን ቦታ ሁሉ
ዝር መረጃ ሰጡ ።

እስካሁንም ድረስ ለቴዎድሮስ የተጻፈው ደብዳቤ መልሱ
መጣላቸውም ነበር ። ቀዳሚው የእንግሊዝ ጦርም ተከዜ ወንዝ

ደረሰ ። መቅደላ ለመድረስም የቀረው 65 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ነው ። በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ ለራሳም የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉለት ። ደብዳቤውም ቀን ባይኖረውም መጋቢት 9 ቀን 1860 መጻፉን ራሳም ይገልጻል ።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩አምላክ፡
ንጉሠ፡ነገሥት፡ቴዎድሮስ፡ይድረስ፡ከአቶ፡ህ
ርምዝ፡ረሳም፡እንዴት፡ሰነበትህ፡እኔ፡እግዚ
አብሔር፡ይመስገን፡ደህና፡ነኝ፡ሀኪም፡ብ
ሎንግን፡አቶ፡ፕሪዶንን፡እነአቶ፡ኪዎሮንን፡እነ
አቶ፡ኮክብን፡ወንድሞቼኸን፡እንዴት፡ሰነበታ
ችሁ፡አለ፡በልልኝ፡እኔ፡ካንተ፡ከወደጀ፡ጠብ፡የ
ለኝም፡ቂም፡የለኝም፡፡ቀድሞም፡መቅደላ፡የሰደ
ድሁህ፡ጊዜ፡ጠብቁ፡ብየ፡ብልክ፡፡ፈርቶ፡እሰ
ር፡ነው፡ብለው፡ጠልሰው፡ላኩብኝ፡፡አሁንም
፡እኔን፡ወዳጅህን፡እግዚአብሔር፡ካመጣልህ፡
፡ወንሰለቱ፡ይውጣልህ፡ተፈታ፡፡የጌቶችኽን፡
፡ሁነታ፡እስትናይ፡ድረስ፡በንዲያው፡እንጠ
ብቅሃለን፡ ፡አቶ፡ፍላጥ፡ካገርህ፡ስንቅህን፡
አምጥቶ፡ሰጥቶኝ፡ነበረ፡አገር፡ሺ፡ፍቶብ
ኝ፡ተሺካሚ፡አጥቼ፡ተበላሸብኝ፡፡ባቶ፡ፍላጥ
ባስቋ፡አንጋዳ፡በ ሻለቃ፡ልይህ፡እጅ፡ሁለት
ሺ፡ብር፡ሰድጀልሃለሁ፡ቀቀበል፡፡ገንዘብህ፡ስለ
ተበላሸ፡፡መቶ፡በግ፡አምሳ፡ፍሪዳ፡ሰድጀልሃለ
ሁ፡ተቀበል፡፡በእግዚአብሔር፡ኃይል፡ደህና፡ስ
መድረስ፡ቢ አበቃኝ፡ዓይን፡ላይን፡ተያይተን፡
እንጫወታለን፡አይዘህ፡





ራሳም በቴዎድሮስ የደብዳቤ ትእዛዝ መሠረት ከታሰረበት ሰንሰለት ተፈታ ። ቴዎድሮስም ወደ መቅደላ ሔደው ከመቅደላ ተራራ ግርጌ ከሰላምጌ ሠፈሩ ። ሚስዮናውያኖች እስረኞች ያሉት ሰላምጌ ሲሆን የፖለቲካ እስረኞቹ ግን ያሉት ከሰላምጌ በላይ ከአ ፋፉ ከመቅደላ ነው ። አንድ ቀን ቴዎድሮስ ከሰላምጌ እንደሆኑ ልድሜርን ጠሩትና . . . . "ወደ መቅደላ እንሔዳለን ። ቢጤዎች ንም ከዚህ ያሉትን ጥራቸውና አብረን እንሄዳለን . . . . ."አሉት። ልድሜየርም ትእዛዛቸውን ተቀብሎ ለጓደኞቹ ለእስረኞቹ ፈረን ች መልክቱን በነገራቸው ጊዜ ደነገጡ ። ምክንያቱም ቴዎድሮስ ውን ከነሕይወቱ ገደል የሚጨምሩበት 135 ሜትር ያህል ርዝ ገኔ ያለው ገደል መቅደላ ላይ ስለሆነ በዚያ ገደል ይጥሉናል ብለው ርተው ነው ። ቢፈሩም የሚቀር ነገር የለምና ቴዎድሮስን ተከ ለው ወደ መቅደላ ወጡ ።

ቴዎድሮስ ከመቅደላ አፋፍ እንደወጡ እስካሁን ድረስ በሰ ሰለት የታሠሩትን እነ ካሜሮንን በታሠሩ በአራተኛ ዓመታቸው ሰንሰለት በታሠሩ በሁለተኛ ዓመታቸው ሰንሰለታቸው እንዲፈታ ቸው አዘዙ ። እስረኞቹ በሙሉ ከሰንሰለት እሥራት ተፈቱ ። እስረ ቹ ሁሉ ከሰንሰለት እስራቸው ከተፈቱ በኋላ ከእስተርንና ሮዘንታል በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ እንዲመጡ አስጠሩዋቸው ።

ፈረንጆቹ እስረኞች ከመምጣታቸው በፊትም ከሜዳ ላይ ዙ ምንጣፎች ተነጥፈው ነበር ። ፈረንጆቹም መጥተው ከዚያ ደደረሱ ቴዎድሮስም ወጥተው ሁሉም ከምንጣፍ ላይ ተቀ ጡ ። ከራሳም ጋር ከተገናኙ ሁለት ዓመት አልፏቸው ነበርና ጁን ጨብጠው ሰላምታ ሰጥተውት ተቀመጡ ። ለራሳምም የአ ር ዓመት ያህል ዕድሜ የጨመሩ ሰው መስለው ነው የታዩት ። ክንያቱም ቴዎድሮስ በዚህ ጊዜ ሸብተዋል ፣ ከስተዋል ። ተጐሳቁ ዋልም ። ከዚያም ባንድነት ሆነው በሰላምና በወዳጅነት ይጨዋ ቱ ጀመር ።

ሲጫወቱም " . . . . ስማ ራሳም ። ባንተ እተማመንብሃለሁ ። ውና ልጄን ልዑል ዓለማየሁን አደራ ሰጥቼሃለሁ ። ጠብቀው ። ትም ሁነው ። እንደማውቀው የመጨረሻዬ ቀን ተቃርቧል ። ሬሳዬ ገብም የምትቆምበት ቀን ደርሷል ። ያኔም 'አ ንጉሥ ቴዎ ሮስ ፣ ኃጢአትህ ምንኛ የበዛ ነው'ትሉ ይሆናል ። ግን እባ ሁ በኔ እንዳትፈርዱ ። ምክንያቱም በእያንዳንዳችን ላይ የሚ

ፈርደው እግዚአብሔር ነው ። እኔ እንደ ንጉሥነቴ እፈርዳለሁ ። አን ተም እንደመልከተኛነትህ ትፈርዳለህ። ዎልድሜየርም እንደሚበዮናዊ ነቱ ይፈርዳል ። ድሆች ለማኞችም እንደ ድህነታቸው ይፈርዳሉ ። እግዚአብሔር በሰማይ ምስክሬ ነው ። በምድርም ዎልድሜየርና ጓደኞቹ ሁሉ ወዳጃቸው እንደነበርኩ ይመሰክራሉ ። እግዚአብሔር የሚያደርገውን ካደረገ በኋላ እንገናኝ ይሆናል ። .... ተመልከተኝ ራሳም ። ከተሰያየን ጀምሮም እንዴት እንደሸበትሁ እየኝ "ብለው ራሳቸውን አሳዩት ። ራሳምም በትህትና " ግርማዊነትዎ ቢሸብቱም ምንም አያስደንቅም ቢጋብቻ ላይ ስለሆኑ የጋብቻ ዘመንምን በደስታ ያሳልፋሉ" አላቸው ።

ቴዎድሮስም በራሳም እነጋገር ስቀው በእጃቸው ጉንጫቸውን እያ ሻሹ "ወዳጄ ራሳም ። አሁን ገና ደሀና አድርገህ ደበደብኸኝ ። .... እንድ ቀንም ሞቼ ታየኝ ይሆናል ። ከሬሳዬ አጠገብም ትቆምና .....'ይሄን ደካማ ሰውዬ አትቅበሩት ። ሬሳው ከመሬት ላይ እን ደወደቀ ይቅር 'ብለህ ትናገር ይሆናል ። እኔ ግን በጨዋነትህ እተ ማመናለሁ" ቢሉት ራሳም እንዲህ ያለ ነገር እንዳይናገሩ ለመና ቸው ። ከዚያም ቴዎድሮስ ለራሳም ጤንነት ብለው ጠጅ የተቀዳ በትን ዋንጫቸውን እንስተው ጠጡ ። ራሳም እጤ ቴዎድሮስ ለና ፒር ደብዳቤ ጽፈው ነገሩን በሰላም እንዲጨርሱ ነግሮአቸው ነበር። ቴዎድሮስ ግን ሰምተው እንዳልሰሙ ዝም አሉት ።

ሚያዝያ 2 ቀን ጧት በ12 ሰዓት ቴዎድሮስ ዎልድ ሜየርን አስጠርተውት ሔደ ። ዎልድሜየር እንደደረሰም አዝነውና ተክዘው አገኛቸው ። ዎልድሜየርም ጥቂት ጊዜ ቆሞ እንደጠበቀ ቴዎ ድሮስ ከተቀመጡበት ተነስተው ራሳም ከነጓደኞቹ እንዲጠራ አዘው ወደ ውስጥ ገቡ ። ራሳምና ሌሎቹ ተጠርተው ሲገቡ ቴዎድሮስ የንጉሥነት ማዕረግ ልብሳቸውን ለብሰው ወጡ ። ራሳም ንም "ለዚያ ሰውየ ወረቀት እንድፅፍለት ትፈልጋለህ፣ እይሆንም ። እላደርገውም ። እንዲት ቤት ለላከችው ሰው ምንም የማደርገው ነገር የለም ። "ብለው ተቆጡ ። ዎልድሜየርም ነገሩን ለማብረድ ብሎ "ጃንሆይ ። ከእንግሊዝ ጦር አዛዥ የተላከ ደብዳቤ ያመጣ ሰው አለ"አላቸው ። እላቸውም ። "ተወው ። ደብዳቤው በመልከተ ኛው ኮሮጆ ይቀመጥ ። ቢፈልግም ወደ ላከው ጌታው ተመልሶ ሊሔድ ይችላል ። ምክንያቱም እስክ ጭራሹም ስለማልቀበለው ነው ። ሐሳቤንም ሊለውጠው ስለማይችል ነው ። አንተም ራሳም ከእን ግሊዞች ጋር ግንኙነት ብትፈጥር ከኔ ጋር ያለህ ወዳጅነት ይጨ



ረሳል ። የመልክተኛህም ደም ስራስህ ላይ ይሆናልና ተጠንቀቅ ። ....."ካሉት በኋላ ወደ ዎልድ ሜየር ዞር ብለው "ሒድ ቤተሰ ብህን ተሰናብተህ ና ። ዛሬ ከንጉሥ ጋር የክብር ሞት ትሞታለህ" አሉትና ሁሉንም አሰናበቷቸው ።

ቴዎድሮስ ሚያዝያ 2 ቀን እስረኞቹ፣ ፈረንጆች ጠርተው በሚ ያነጋግሩበት ጊዜ በዚሁ ቀን የእንግሊዝ ጦር በበሽሎ ፣ በወርቅ ውሃ ፣ ሸለቆ ፣ ከፉላ ተራራ ሥር ፣ በእሮጌ ፣ በእፍሮ ጦሩን ሲያሰል ፍና ሲያደራጅ ዋለ ።



የበሽሎ ወንዝ መቅደላ አጠገብ

ቴዎድሮስም ዎልድሜየርን ቤተሰብህን ተሰናብተህ ና ካሉት ኋላ ዎልድሜየር ከልጁና ከሚስቱ ጋር ተላቅሶና ተሳስሞ ቴዎድሮስ ዘንድ ሲመለስ ንጉሱ ከተሰበሰበው ሠራዊታቸው ፊት ፊት ከፈረስ ላይ ተቀምጠው እንደቆሙ አያቸው ። የተሰበሰበው ብት ሺ ያህል ሰው ይሆናል ። ቴዎድሮስም ለሠራዊቱ ንግግር ያደ ጉ ጀመር ።

"ልጆቼ ። እነህኘን የመጡትን የእንግሊዝ ወታደሮች አትፍሩዋቸው። እነሱ ዳዊትን እንደተጋጠሙት እንደ ፍልስጤማውያን ናቸው ። ዳዊት ግን በእግዚአብሔር ኃይል አሸንፏቸዋለሁ ብሎ ገጠመ ። እኔ የዳዊት የሰሎሞን ልጅ አይደለሁምን ። እግዚአብሔር እኔን የኢትዮጵያ ንጉሥ አድርጐ አልቀባኝምን ። በጦርነትስ ላይ የማልነካ ፤ ሁሉን የማስፈራ የእሳት ምሰሶ እየሆንኩ ያረጀሁበት ጀግና አይደለሁምን ። ....እግዚአብሓሔር በድል ላይ ድል እየጨመረ አልሰጠኝምን ። ዛሬ የእንግሊዝን ጦር አበሻ ምድር ድረስ እንዳስመጣሁት ድል ሳደርገው ደግሞ ታያላችሁ ። እንደሕጋችን ወደ ጦርነት የሚሔደውን ሰው እግዚአብሔር ይፍታ እንዳይሉ ጳጳሱ አቡነ ሰላማ ሞተዋል ። በእሳቸው ቦታ ሆኜም እኔ እፈታችኋለሁ ። በእግዚአብሔር በአብ ፤ በወልድ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም ማንኛውም ወታደር ፤ የኤሮፓውያን ጦር ተቃውሞ የሚዋጋውን ሁሉ በጦር ሜዳ ሕይወቱን ቢያጣ እግዚአብሔር ይፍታው" ብለው ንግግራቸውን ሲጨርሱ ወታደሩ እየሸለለና እየፎከረ የእንግሊዝ ጦር ወደ መሸገበት ወደ አሮጌ ወረደ ።



## ምዕራፍ 15

# ጦርነቱ ተጀመረ

ሚያዝያ 2 ቀን ከቀኑ ለአሥራ አንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን የቴዎድሮስ ሠራዊት በእንግሊዞች ላይ ተኩስ ከፈቱ ። ቴዎድሮስም ፋላ ኮረብታ ላይ ሆነው መድፎቻቸውን እንዲተኮሱ አዘዙ። የሚተኮሱትም የመድፍ ጥይቶች በእንግሊዞች ሠፈር ሠራዊት ላይ ምንም ጉዳት አላደረሱም ። እግረኛው ሠራዊትም በብዛት እየተመመ ወደ እንግሊዞች ሠፈር ይጓዝ ጀመር ። ይህንንም የቴዎድሮስን ሠራዊት በብዛት መምጣት እንግሊዞች እንዳዩ ብሉ ጃኬት የተባለው ብርጌድ ተኩስ እንዲጀምር ታዘዘ ።

በፊታውራሪ ገብርዬ የሚመራው 5000 ያህል የሚሆነው የቴዎድሮስ ሠራዊት በብዛትና ባንድነት ሆኖ በመጓዙ ለእንግሊዞቹ ተኩስ ተመቸ ። ብዙ ሰውም አለቀ ። የተረፈውም እየተፏከረ ለማጥቃት ቢሞክር ምሽግ ይዞና ተኝቶ የሚተኩሰው የእንግሊዝ ጦር አልበገር አለ ። እነፊታውራሪ ገብርየና ብዙ መኳንንቶችም በጀግንነት እየተዋጉ ሞቱ ። የተረፈው ሠራዊትም መሸሽ ጀመረ ።

ፋላ ላይ ሆነው መድፍ የሚያስተኩሱት ቴዎድሮስ ፤ የሠራዊታቸውን መሸሽ እንዳዩ ጋፋት ያሠሩት ትልቁ መድፋቸው እንዲተኮስ አዘዙ ። ሚስዮኖቹን አላምን ብለው መድፉን እንዲተኩሱ የተመደቡት ኢትዮጵያውያን ነበሩ ። መድፉ አንድ ጊዜ የሚጐርሰው የጥይቱ ክብደት 17 ኪሎ ግራም ያህል ነበር ። ኢትዮጵያውያኖቹ ተኳሾች ግን ባንድ ጊዜ ሁለት ጥይቶች አጉርሰው በመተኮሳቸው መድፉ ፤ ከበስተኋላው በኩል ተሰነጠቀ ። ከአገልግሎት ውጭ ሆነ ።

መድፉ እንዲተኮስ በታዘዘበት ጊዜ ሠሪዎቹ ሚስዮናውያኖች ከመድፉ 3 ሜትር ያህል ራቅ ብለው ቆመው ነበር ። ቴዎድሮስም ከእነሱው አጠገብ ነበሩ ። ቴዎድሮስ የመድፉን መሰንጠቅ እና ከአገልግሎት ውጭ መሆኑን ሲያውቁ ተበሳጩ ። በንዴታቸው

ብዛት ጥርሳቸውን ሲቆረጥሙ ድምፁ እጠገባቸው ለነበሩት ሁሉ ይሰማ ነበር ። ቴዎድሮስ እንዲያ እንደተናደዱ መድፉን በሠሩት ፈረንጆች ላይ እንዳችም ርምጃ አልወሰዱም ። በከፋ አስተያየት እንኳ አልገላመጡዋቸውም ። ምክንያቱም የሠሩዋቸው ሌሎቹ ትና ንሽ መድፎች በሚገባ ወደ እንግሊዝ ጦር ይተኮሱ ነበርና ነው ። ግን ጥይቶቹ ባዶ ሜዳ ላይ ከመውደቅ በስተቀር ፋይዳ አልሠሩም። ወዲያወም ነጐድጓዳማ ዝናብ በመዝነቡ ጦርነቱን ቅጥ አሳጣው።



የንጉሡ ቤት ሲቃጠል


ከጀርባ የተኩስ ሽፋን ወይም ድጋፍ የሌላቸው ኢትዮጵያ ውያን ከእንግሊዞች ምሽግ እምባና ስልሳ ሜትር ርቀት ድረስ እየ ተጠጉ ቢዋጉም ለእንግሊዞች ጥይት ተመቹ እንጂ ውጤት ሊያ ገኙ አልቻሉም ። በተለይ ደግሞ አብዛኛው የቴዎድሮስ ሠራዊት የሚዋጋው በጦርና በጐራዴ በመሆኑ ከማለቅ በስተቀር መጨረስ አልቻሉም ። ጦርነቱም ከሶስት ሰዓት ውጊያ በኋላ ምሽት ሲሆን ቆመ ። እንግሊዞች ምንም ጉዳት ባይደርስባቸው ሃያ ወታደሮች ያሀል ቆሰሉባቸው ። ከኢትዮጵያውያን ወገን ግን 700 ያሀል ሰዎች ሲሞቱ 1200 ያሀል ወታደሮች ቆሰሉ ።



አጤ ቴዎድሮስም ቢሆኑ በዚህ ውጊያ ጊዜ ሊገዱሉ ነበር ። እን
ግሊዞቹ ከሠፈራቸው ሆነው ወደ ፋላ ኮረብታ ከተኮሱዋቸው የመ
ድፍ ጥይቶች አንደኛው ቴዎድሮስን ለጥቂት ስቷቸው አጠገባቸው
ቆመውን ሰው ገደለው ። ከዚህም በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ጦራቸ
ውን ያዋጉ የነበሩት ጋሻቸውን ይዘውና መከታ አድርገው ነበር።
ኋላም መልከተኛ ልከው ከሥራቸው ያለው የሚዋጋው ሠራዊታ
ው እንዴት እንደሆነ አስጠየቁ ። መልእክተኛውም ሲመለስ ሹሞ
ቻቸው በሙሉ መገደላቸውን ነገራቸው ። አጤ ቴዎድሮስም አዝ
ው ማታውኑ የማዋጊያ ቦታቸውን ከፋላ ወደ ሰላምጌ አዛወሩ ።
ዕለቱ ውጊያ የተረፈወም ሠራዊታቸው ቴዎድሮስን እየከዳ
ወደየቤቱ ሔደ ። አንዳንዶቹም ቁስለኞችን ሲያነሱና ሲያግዙ አመሹ።
ዚያን ዕለት ውጊያ እንግሊዞች 18000 የጠመንጃ ጥይትና 219
ልዩ ልዩ የመድፍ ጥይት ተኩሰዋል ። በዚያን ዘመን ስናድር ጠመ
ንጃ ገና መፈልሰፉ ስለነበረ ለመጀመሪያ ጊዜ በጦር ሜዳ ላይ የዋ
ለው በዚህ በመቅደላው የአሮጌ ጦርነት ነው ።

ሰሊት ፍላድ እና ዎልድሜየር ከአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ ተጠሩ።
ሌሎቹ ፈረንጆች እስረኞችና ተጠሪዎችም ልንገደል ነው ብለው
ተንግጠው ነበር ። ፍላድና ዎልድሜየር ከአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ
እንደደረሱ “. . . . ተዘጋጁ ። ወደራሳም የምልካችሁ መልከት
ለ “አሉና” እንዲህ በሉት ። እኔ የኢትዮጵያ ንጉሥ ባገሬ ያለሁት
ብዝ እኔ ብቻ ነኝ እል ነበር ። አሁን ግን እግዚአብሔር ከኔ የተ
ሉና ጠንካራ ሰዎች መኖራቸውን አሳየኝ ። አሁን የምጠይቀው
ክር በኔና በእንግሊዝ ጦር አዛዥ መሀል እርቅ እንዲሆን ነው ።
አሉዋቸው ። እነሱም ወደ መቅደላ አፋፍ ወጥተው መልከቱን
ራሳም ተናገሩ ። ራሳምም ሐሳባቸውን ደግፎ “ የሰላም መልከተ
ኞች ቢላኩ ጥሩ ነው” ብሎ መለሰላቸው ። መልከተኞቹም ይህንኑ
አጤ ቴዎድሮስ ነገሩ ። ቴዎድሮስም ይህን እንደሰሙ “. . . . ወደ
እንግሊዞች ለመላክ የሚያስችኩል አይደለም ። እግዚአብሔር ደስ
የሚለውን ያድርግ ። አሁን ሒዱና ተኙ። ”ብለው አሰናበትዋቸው ።

ከለሊቱ አስር ሰዓት ሲሆን ቴዎድሮስ እንደገና አስጠሩዋቸው
ሰላሙ ጉዳይ እንዴት ሊሆን እንደሚችልም ጠየቁዋቸው ። እነ
ሱም ራሳም ያቀረበው ሐሳብ ጥሩ መሆኑን ነገሩዋቸው ። በዚህም
ብሰባ ደጃዝማች ዓለሜ ሚስተር ፍላድና ፕሪዴውክስ የሰላም
መልከተኞች ሆነው ወደ እንግሊዝ ጦር እንዲላኩ ተወሰነ ።
የማግስቱም ማለት ሚያዝያ ፫ ቀን እነኝህ መልእክተኞች በየበ



የአርጌው ጦርነት



ቅሎ ሆነው ነጭ ባንዲራ እስቀድመው ወደ እንግሊዞች ሠፈር ሔዱ ።

እጤ ቴዎድሮስ መልከተኞቹን ከላኩ በኋላ በመነጥር ቁልቁል የእንግሊዞችን የጦር ሠፈር እዩና “....እቤት በእበሻ ምድር ምን ዓይነት የሚያስገርም ነገር ይታይ ጀመር? በዛሬው ቀን የእንግሊዝ ጦር በሙሉ በእበሻ ምድር ላይ ሠፍሯል ። ....” ብለው ተናገሩ ። ከዚያም በኋላ እነደጃች ዓለሜ የሚያመጡትን መልስ ሲጠባበቁ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ቆዩ ። ደጃች ዓለሜ ከቴዎድሮስ ጋር አብረው ያደጉ ጓደኛ ሲሆኑ የእጤ ቴዎድሮስ ቁባት የሆኑት የወይዘሮ የተመኙ ልጅ እግብተው ጓደኝነታቸውን የጠና ሆነዋል ።

እነደጃች ዓለሜ ከእንግሊዞች ጦር ሠፈር ሲደርሱ በእንግሊዞች ጦር ሠፈር ነጮች በመታያቸው ጭፈራና ሁካታ ሆነ ። ሠራዊቱ የጨፈረው እስረኞቹ ተለቀው የመጡ መስሎት ነው ። የእንግሊዝ ሠራዊት ከብቦ እያየቸውና እያወካ ከናፒር ድንኳን ድረስ አደረሳቸው መልእክተኞችም የተላኩትን የሰላም መልእክት ለናፒር ነገሩ። ናፒርም በጉዳዩ ተስማምቶ ለእጤ ቴዎድሮስ የሚላከው ደብዳቤ እስኪዘጋጅ ድረስ ደጃች ዓለሜ የእንግሊዝን ጦር ዝሆኖችንና ታላላቆቹን መድፎች እንዲጎበኙ ተደረገ ። እስጎብኚውም “ትናንት የተኮስናቸው መድፎች ትናንሾቹን ነው ። እነኚህ ግን እንዱ መድፍ ላንድ ጦርነት በቂ ነው”እያለ ታላላቆቹን መድፎች እሳያቸው ። ከዚያም በኋላ የተጻፈው ደብዳቤ ተሰጥቷቸው መልከተኞቹ በሙሉ ተመለሱ ።

ደጃች ዓለሜ መልክቱን ይዘው ከመመለሳቸው በፊት በትናንቱ ውጊያ ላይ የሞቱትን የፊታውራሪ ገብርዬን ሬሳ እንዲፈልጉ እስፈቅደው ነበር ። መልእክተኞቹ ሲመለሱ እግረ መንገዳቸውን የፊታውራሪ ገብርዬን ሬሳ ፈልገው እገኙት ። ፊታውራሪ ገብርዬ የሞቱት በሰናድር ጠመንጃ ጥይት ግንባራቸውን ተመትተው ነው። ጐፈርና ለምድ ለብሰው ያዋጉ ስለነበረም እንግሊዞቹ በመጀመሪያ ጊዜ እጤ ቴዎድሮስ የሚያዋጉ መሰሏቸው ነበር እሁንም የወደቁት ከነማዕረግ ልብሳቸው ነው ። ማርክሃም ስለገብርዬ ሬሳ እገኛኘት ሲገልጥ “.... በጀርባቸው ተንጋለው ወድቀዋል ። እጆቻቸው ተዘረጋግተዋል ። ልብሳቸው ለበዓል ቀን የሚለበስው በወርቅ ዘቦ ዝምዝም ያጌጠ ሐር ቀሚስ ነው ። ፊረሳቸው ከእሳቸው እሥር እርምጃ ያህል ራቅ ብሎ ሞቶ ወድቋል ። ጠጉራቸው ሽበት የበዛ

ብት ነው ። . . . . ''ይላል ። መልክተኞቹም የፈታውራሪ ገብርዬን ሬሳ ይዘው ወደ መቅደላ ወጡ ።

ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ከአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ ደረሱ ። ንጉሱም ፊታቸውን ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አድርገው ድን ጋይ ላይ ተቀምጠው አለቃ እንግዳን ደብዳቤ ያጽፉ ነበር ። የሚያ ጽፉትም ደብዳቤ እንዲህ የሚል ነበር ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ 1 አምላክ ። በሶስትነት ባንድነቱ በክርስቶስ ያመነው ካሣ ። መቼም ያገሬ ሰዎች በእግዚአ ብሔር ኃይል እኔ ካልወረድሁላችሁ ሽሽታችሁን አትተውም ። ክር ስቲያኑን ሁሉ ጉልበት አለኝ መስሎኝ ከረመኔ አገር አግብቼው ወንድ የሌላት ቆንጆ አለች ወንድ የነበራት ቆንጆ ነበረች ። ትላንትናም የሞተባት ትኖራች ። ሽማግሌ ልጅ የሌለው ባልቴት ልጅ የሌላት እኔ የምጠራቸው ብዙ በከተማዬ አሉ ። እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ፍቀዱዋቸው ። ያረመኔ አገር ነውና ። ያገሬ ሰው ገብር ሥርዓት ግባ ብዬ ብለው እምቢ ብሎ ተጣለኝ ። እናንተ ግን በሥ ራት በተገዛ ሰው አቸነፋችሁኝ ። እኔን ወደውኝ የተከተሉኝ ሰዎች አንድ እርሳስ ፈርተው ጥለውኝ ሸሹ ። ''ከሚለው ፅሁፍ ላይ ሲደርሱ እነ ደጃች ዓለሜ መጡ ።

መልክተኞቹም ከናፒር የተላከውን ደብዳቤ ሰጡአቸው ። ደብዳቤው የተጻፈው በእንግሊዝኛ ስለነበር በዎልድሜየር አስተርጓ ሚነት ይነበብ ጀመር ።

ለግርማዊ ንጉሥ ቴዎድሮስ

ግርማዊነትዎ ትናንትና እንደ አንድ ጀግና ተዋግተዋል ። ግን በኛ ጥበብና ኃይል ድል ሆነዋል ። እንደገና ደግሞ በመሀከላችን ደም እንደማይፈስ እናምናለን ። ግርማዊነትዎ የእንግሊዝን ንግሥት ከተቀበሉ በግርማዊነትዎ እጅ ያሉትን ኤሮፓውያን እስረኞችን በሙሉ በዛሬው ቀን በሰላም ከእንግሊዝ ጦር ሠፈር ድረስ እንዲል ኩዋቸው ። ይህ ከሆነ ለግርማዊዊነትዎና ለመላው የግርማዊነትዎ ቤተሰቦች ሁሉ በክብር መልካም አያያዝ እንደሚያደርግ ቃል እገ ባለሁ ።

ጠቅላይ አዛዥ

ሮበርት ናፒር



ቴዎድሮስ ደብዳቤው ሲነበብ በጥሞና አዳምጠው ንባቡ ሊያልቅ ''. . . . ያልገባኝ ነገር አለ ። ይህ በክብር መልካም አያያዝ ሚለው ነገር ምንድነው ''ብለው ጠየቁ ። መልሰውም ራሳቸው '. . . . እንደ እስረኛ ተይዤ ነው ይዞታው ? ወይስ አገሬቱን ከሸ ፍታ ሊያነጡልኝ ነው? . . . . አውቀዋለሁ ። በእስረኛነት አድርጉ ንዴት እንደሚይዘኝ ማለቱ ነው ። እኔ ቴዎድሮስ ! እኔ ነኝ እስረኛ ምሆነው? የማይሆን ነገር ነው ። . . . . ሂዱ ከዚህ ከአጠገቤ''ብለው ሲጮሁ ሁሉም አምሳ ሜትር ያህል ርቀዋቸው ቆሙ ።

አጤ ቴዎድሮስም ያፅፉት የነበረውን ደብዳቤ ለማስጨረስ ወደ ፀሐፊው ወደ አለቃ እንግዳ ዞር አሉ ። በዚያው በተጀመረው ይ ሲያስቀጥሉ''. . . . ብታሮጡአቸው ከሮጡ ሰዎች ጋር አልነበ ሁም ። ጌታ ነኝ መስሎኝ ባልሰላ መድፍ ስታገል ውዬ ነው ። ያገሬ ው የፈረንጅ ሃይማኖት ይዞአል እስልሟል እያለ አስሩን ምክንያት ሰጠኝ ነበረ ። እኔ ከከፋሁበት እግዚአብሔር መልካም ይስጠው ። ንደ ወደደ ይሁን ። እግዚአብሔር ቢሰጠኝ ሁሉን ልገዛ አሳብ ነበረኝ ግዚአብሔር ቢነሳኝ ልሞት ሐሳቤ ይህ ነበር ። ከተወለድሁኝ እስ ሁን ወንድ እጇን ጨብጦት አያውቅም ነበረ ። ሰዎች ሲሸሹ ነስቼ ማራጋት ልማድ ነበረኝ ። ጨለማ ከለከለኝ ። ትላንትና በደ ታ ያደራችሁ ሰዎች እግዚአብሔር እንደኔ አያድርጋችሁ ። እን ን የሀበሻ ጠላቴን ኢየሩሳሌም ዘምቼ ቱርኮችን እስለቅቃለሁ ስሎኝ ነበር ። ወንድ ያቀፈው ወንድ ተመልሶ አይታቀፍም ።

ይህን ደብዳቤ አፅፈው ከጨረሱ በኋላ ምንም ሳይናገሩ ለብዙ ዜ ተቀምጠው እያሰቡ ቆዩ ። ይህንንም ደብዳቤ ለናፒር እንዲያ ርሱለት ለመልክተኞቹ ሰጧቸው ። ጊዜው ቢመሽም መልክተ ቹ እጅ ነስተው ሔዱ ።

አጤ ቴዎድሮስ በአጠገባቸው ያሉትን ሰዎች ራቅ በሉ ብለው ቻቸውን እንደተቀመጡ ተከዘው ቆዩ ። ተነስተውም ። ግንባራቸ ን መሬት እያስነኩ ሶስት ጊዜ ሰገዱ ። ከስግደቱ ሶስት ጊዜ ማተቡና የታጠቁትን ባለሁለት አፈሙዝ የሆነውን ሽጉጣቸውን ዘው ራሳቸው ላይ ደገኑ ።

ይህን ሽጉጥ መደገናቸውን ያየው ራቅ ብሎ የሚመለከተው ራዊት ተሯሩጦ ደርሶ ግማሹ ወገባቸውን ተጠምጥሞ ሲይዝ ሌላ ቹ ደግሞ ሽጉጥ የያዘውን እጃቸውን ይጐትቱ ጀመር ። በዚህ ንንቅ መሀል ሁሉም ባንድነት ወደቁ ። አጤ ቴዎድሮስም ከያዟቸው

ሰዎች ለማምለጥ ከመሬት ላይ ይንከባለላሉ ጀመር ። ከዚህም መተ ናንቅ መሐል የቴዎድሮስ ሽጉጥ ባርቆ ጥይቱ የቴዎድሮስን ጆሮ በመጠኑ አቆሰላቸው ።

ቴዎድሮስ ወጥረው ከያዙዋቸው አሽከሮቻቸው ጋር መሬት ላይ እየተንከባለሉ ከቆዩ በኋላ ሽጉጣቸውን ሰጥተው ለቀቁዋቸው ሲነሱም "የእግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆን ነው" ብለው ተናገሩ ። አጤ ቴዎድሮስ መጀመሪያውን ሽጉጣቸውን ራሳቸው ላይ ባነጣጠሩ ጊዜ ራሳቸውን ይገድሉ ነበር ። በዚያች ደቂቃ ያልሞቱበት ምክን ያት ወታደሮቻቸው ተሯሩጠው ስለያዙዋቸው ብቻ አይደለም ። ቴዎድሮስም የሽጉጡን ምላጭ ወዲያውኑ ሳይስቡት ቀርተው አይደለም ። የዚያን ዘመኑ ባለሁለት አፈሙዝ ሽጉጥም ሆነ ጠመ ንጃ ለመተኮስ ሁለት ምላጭ (መሳቢያ) አሰው ። የቴዎድሮስ ሽጉጥ የተቀባበለው በአንደኛው አፈሙዝ ሲሆን ሌላው አፈሙዝ ባዶ ነበር። ቴዎድሮስ ራሳቸውን ለመግደል የሳቡት ምላጭ የባለ ባዶውን እንጅ ጥይት ያለበትን አልነበረም ። ስለዚህ የተሳበው አፈሙዝ ጥይት የሌ ለበት ስለነበር ራሳቸውን ሳይገድሉ ቀሩ። በትንንቁ ጊዜ ግን የሌላውን የጐረሰውን አፈሙዝ ምላጭ በመሳሰባቸው ጥይቱ ሊተኮስ ቻለ ።

ሁሉም ነገር ሰላማዊ መሰለ ። ቴዎድሮስም ቤተሰባቸውን ከመቅደላ ወደ ሰላምጌ አሰጠሩ ። አምስቱ ልጆቻቸው ፣ ቁባታቸው ወይዘሮ የተመኙ ሳይቀሩ ከእቴጌ ጥሩነሽ ጋር ሰላምጌ መጡ ። በሜዳ ላይም ስብሰባ ተደረገ ። ታላቁ ጀግና ራስ እንግዳ ፣ ደጃች አቦዬ ባሻ አብተው አለቃ እንግዳ ወርቅ ፣ አሳላፊ ከንቲባና ሌሎ ችም ሆነው ተሰበሰቡ ። በተያዘውም ምክር በእስረኛነት የተያዙትን እስረኞች እንግደላቸው የሚል አሳብ ቀረበ ። አንደኛው ተናጋሪ "ሁሉ ንም ባንድነት ለመያዝ የሚችል ትልቅ የእንጨት አዳራሽ ቤት ስላለ ከዚያ አጉረን ከነሕይወታቸው እናቃጥላቸው "አለ ። ሌላው ተናጋሪ ደግሞ "የለም ። እጅና እግራቸውን እየቆራረጥን እንጣላቸውና እን ግሊዞቹ ሲመጡ ያንሷቸው" አለ ።

ባሻ አብተው በቀረበው ሐሳብ ተለዩ ። "እነዚህ እስረኞች ቢገ ደሉ በአገሪቱ ላይ ከባድ መከራ ይደርሳል ። ስለዚህ የሚያዋጣው ነገር እስረኞቹን በነፃ መልቀቅ ነው " አሉ ። በሕዝቡ መሀል ቆመው ይህን የሕዝብ ፍርድ የሚያዳምጡት ፈረንጆች ደንግ ጠው የቴዎድሮስን የመጨረሻ ውሳኔ ይጠባበቁ ነበር ። የደነ ገጡ ትን ፈረንጆች የተመለከቱት ቴዎድሮስም ወደ ፈረንጆቹ ዞር ብለው



"አይዟችሁ ፣ ተቀመጡ ። አትፍሩ ። ሁላችሁንም እንድገላችሁ ተመከሬአለሁ ። እናንተ ግን በኔ ላይ ምንም መጥፎ ነገር አላ ደረጋችሁም ። ስለዚህ አልገድላችሁም ። የኔ ሞት ግን ያለው በእጇ ላይ ነው ከኔ ቀድማችሁ እንድትሔዱ አልፈልግም ። በእግዚአብሔር ዘንድ ታስጠይቁኛላችሁ ። ሒዱ ። ወዳጆቻችሁን ሁሉ ይዛችሁ ወደ እንግሊዞች ሠፈር ሒዱ "ብለው አሰናበቷ ቸው ።

የተሰናበቱትም ፈረንጆች ወደ ሠፈር ሔደው የመለቀቃቸ ውን ዜና በሠፈር ለነበሩት ነገሩ በፈረንጆቹም ላይ ሁለት ነገር ተፈራረቁባቸው ። በመለቀቃቸው ቢደሰቱም የቴዎድሮስ ጠባይ ተለዋዋጭ በመሆኑ ምናልባት ተለቀናል ብለው ሲሔዱ ሊገድሉ ዋቸው እንደሚችሉ ተጠራጠሩ ። በማንኛውም መንገድ ቢሆን ሒዱ የሚለውን ትእዛዝ ለመፈጸም ተሰባስበው ቴዎድሮስ ወዳሉበት አቅጣጫ ተጓዙ ። ከዚህ በፊት ሳይሰናበቱኝ ሔዱ ብለው እንዳሠሩ ዋቸው ያውቁ ነበርና የሚቻል ቢሆን ቴዎድሮስን ለመሰናበት ሄዱ። ከንጉሱ ሠፈር ሲደርሱ ቴዎድሮስ ድንኳናቸው ውስጥ ያለመኖራ ቸውንና ወደ እንግሊዝ ጦር ሠፈር ከሚወስደው መንገድ ላይ እንደ ሚጠብቁዋቸው ነገሩዋቸው ።

ፈረንጆቹ ተሰባስበው ሲመጡ ቴዎድሮስ አዩዋቸው ። ወዲያ ውኑም "እባካችሁ ያን ጠላቴን ኮከብን (እስተርን) አታሳዩኝ"አሉ። ይህን የሰማው ዎልድሜየር ሮጦ ሒዶ ዶክተር እስተርንን እንዲደብቀው ለራሳም ነገረው ። ከዚህ በኋላ ሌሎቹ ተሰባስበው ቴዎድሮስ ዘንድ ደረሱ ። ቴዎድሮስ ሃያ ያህል ከሚሆኑ ሰዎች ጋር ቆመው አገኙዋቸው ።

አጤ ቴዎድሮስ ራሳምን ወደአጠገባቸው ጠሩና "ደህና ያግባህ ። ወዳጄ ዳግመኛ በሕይወት አንተያይም ። ከሞት በኋላ እንገናኝ ይሆናል ። እንደሌሎቹ ወዳጆቼ ሁሉ አንተንም አምንሃ ለሁ ። . . . . ከእንግዲህ ወዲያ የምትሰማው መሞቴን ወይም መመ ንኮሴን ነው ። "አሉትና ቀና ብለው የጀምበርዋን ሁኔታ ተመለከቱ

ቴዎድሮስ ፀሐይዋ ልትጠልቅ ማሽቆልቆልዋን ካዩ በኋላ"ወደ እናንተ ሠፈር አሁን ለመሔድ ያልመሸ ይመስልሃል? አሁኑኑ ትሔዱ ወይስ ለሊቱን ከኔ ጋር አድራችሁ ጧት በማለዳ ወደ ሰዎ ቻችሁ ልላካችሁ?" ብለው ራሳምን ጠየቁት ። ራሳምም" ጃንሆይ ።

እርስዎን ደስ እንደሚልዎት ይሁን" አላቸው ። ቴዎድሮስም "መል ካም ። አሁኑኑ ብትሔዱ ይሻላል ። ግን አንድ ጊዜ ቁጭ በልና ከመሔድህ በፊት ጥቂት እንጫወት" አሉት ። ሁለቱም አብረው ተቀመጡ ። "ታውቃለህ አቶ ራሳም ። እኔና አንተ ሁልጊዜ በመል ካም ሁኔታ ላይ ነበርን ። የልብህን ግን የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው ። እኔ ግን ባንተ ላይ ትልቅ አክብሮት አለኝ ። ባንተ ላይም መጥፎ ነገር ማድረጌ እውነት ነው ። ያንንም ያደረግሁት በመጥፎ ሰዎች ግፊት ነው ። አሁን ያለፈውን ማንሳት ምንም አይጠቅመ ንም ። እኔ የማምነው ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ተደረገ ነው ። ያለፈውን ከአእምሮህ እንድታጠፈው እፈልጋለሁ . . . . ራሴን እገላለሁ ፣ ወይም እመነኩሳለሁ ። አሁን እንግዲህ በል ደህና ሁን ። ከቻልክ ነገ መጥተህ እንድታየኝ "አሉት ።

ራሳምም ስለደግነታቸው አመስግኖ "ከተቻለ መጥቼ ጃንሆይን አይዎታለሁ" ሲላቸው ንግግሩን አቋረጡትና "እውን ነገ ትመጣ ለህ?"ብለው ጠየቁት ። ራሳምም ሁሉም ነገር በጦር አዛዡ ውሳኔ የሚፈፀም መሆኑን ነግሮ ሁለቱም ከተቀመጡበት ተነሱ ። ቴዎድ ሮስም የራሳምን እጅ ጨብጠው ይዘው እንባ እየተናነቃቸው"በል ደህና ያግባህ ። መሽቷልና እየገሰገሳችሁ ሒዱ" አሉት ።

ራሳም ከቴዎድሮስ ተሰናብቶ እጃቸውን ስሞ ሲለያቸው ሌሎቹ ፈረንጆች ካሜሮንን ጨምሮ ከሩቅ ከመንገድ ላይ ቆመው ይጠ ብቁት ነበር ። ራሳምም እየተጠራጠረ ካሁን አሁን ከኋላዩ አስተ ኩሰው ገደሉኝ እያለ ወደ ፊቱ ሔደ ። ጥቂት እንደሔደ ቆም ብሎ ወደኋላው መለስ አለና "ጃንሆይ ፣ ስለርኅራኄዎ እሠሰግንዎታለሁ ። ጓደኞቼ ግን ከኋላዩ ቀሩ" አላቸው ። ታዎድሮስም "አርፈህ ፣ ዝም ብለህ ብትሔድ ይሻልሃል" አሉት ። ራሳም እጅ ነስቶ ቀጥታ ተጓዘ አሁንም ጥቂት እንደሔደ ቆም አለና ዞር ብሎ ወደ ቴዎድሮስ አየ፣ አጤ ቴዎድሮስ ጠመንጃ ቢያዙ ሰዎች እንደታጀቡ ናቸው ።እሳቸውም ሁለት ጐራሽ ሽጉጣቸውን እያወዛወዙ ቆመዋል ። የራሳምን መቆም እንዳዩ እንዲሔድ በእጃቸው ምልክት ሰጡት ። እሱም መን ገዱን ቀጥሎ ዞር እያለ ሲያይ ጓደኞቹ ቁልቁለቱን እየወረዱ ሲመጡ አየ ።

በዚህ ጊዜ የተለቀቁት ወይም የሔዱት እስረኞች በሙሉ አይ ደሉም ። ሆኖም እነኝህ በደጃች ዓለሜና ባቶ ሳሙኤል ሽኝነት ለመ ጀመሪያ ጊዜ የተለቀቁት እስረኞች ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ከእንግሊዞች ጦር ሠፈር ደረሱ ። በዚያም ትልቅ የደስታ አቀ



ባበል ተደረገላቸው ። ዘጠኝ ኤሮፓውያን እስረኞችና አሁን የተለ ቀቁት ፈረንጆች ቤተሰቦች በቴዎድሮስ እጅ ቀርተው ስለነበረ ስለነሱ ሲመከር ታደረ ።

በማግስቱ የፋሲካ በዓል ስለሆነ አጤ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ጦር አንድ ሺህ የቀንድ ከብቶችና 500 በጎችን በፀሐፊያቸው በአቶ ሳሙኤልና በጀርመናዊው ቤንደር እጅ የሚከተለውን ደብዳቤ ጨም ረው ላኩ ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ። ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ። ይድረስ ከታላቂቷ ከእንግሊዝ ንግሥት ወዳጅ ከሎሌዎ ልኬብዎ አለሁ ። ስምዎን እከሌ ብዬ እንዳልጥፍ ባላሰብ ሁት ጉዳይ ድንገት ተገናኘን ። ትላንትና ለነአቶ ፍላፐ የሰደድሁት ደብዳቤ ከእናንተ ከወዳጆቼ ጋር በመጣላቴ ሁለተኛ የውጊያችሁን ያገራችሁን ሥራት በማየቴ ያገሬ ሰው ከትእዛዝ መውጣቱን አይቼ ብገለው ፣ ብቀጣው አልመለሰልኝ ቢል ቢነደኝ ፤ ብቀና ፤ በገዛ ጠመ ንጃዬ እሞታለሁ ብዬ ሰይጣን አሳብ አሳደረብኝ ። አይ ይህን ሁሉ ሠራዊት ዋቢ አልቦ ትቼው አልሔድም እግዚአብሔር ይጣላኛል ብዬ አጣዳፊ ከእርስዎ ሰደድሁት ። እኔ ሰሞት ሊድበለበል ቃሌ ሳይ ደርስልዎ ይቀራል ብዬ ከሰደድሁልዎ በኋላ ግን የጠመንጃዬን ቃታ ከፍቼ ካፌ አጉርሼ ብስበው ብስበው እምቢ አለኝ ። ሰዎች ሩጠው መጥ ተው ካፌ ሲመዙት ተተኩሶ እግዚአብሔር አትሙት ካለኝ ግን ብተ ርፍ ልብዎ ይሻቅላል አቶ ርስአምን ስድጀው አደርሁ ። ዛሬ ትንሳኤ ነውና ፍሪዳ እንድሰድልዎ ይፍቀዱልኝ ። ደብዳቤዎ ንም መልሼ የሰደ ድሁት በሰማይ እንጂ በምድር እንገናኛለን አላልሁም ነበር ።

ፊታውራሪ ገብርዬን የኔን ወዳጅ ሳላስነሳው ያደርሁ ከሞትሁ (እኔንም) አብረው ይቅበሩን ብዬ ነበር ። ቁሜ ከዋልሁ ግን (ልቅበረው) ይፍቀዱልኝ ።. . .

ይህ እውነተኛው ደብዳቤ ወደ መጨረሻው ገደማ ፅሁፉ የጠፋ ስለሆነ የማይነበብ ነው ። በቅንፍ ውስጥ ሆኖ ከሥሩ ሰ'ስመር ያደ ረግሁበት ከደብዳቤው ላይ ይመሳሰላሉ ብዬ ያነበብኳቸው ናቸው ። ከውጭ ቋንቋ ትርጉም እንደሚታወቀው ግን የደብዳቤው መጨረሻ ኤሮፓውያኑን መለቀቃቸውን ፤ የጅ ባለሞያዎች እንዲሳኩላቸው መጠየቃቸውን የሚገልጽ ነው ።

ደብዳቤውን ይዘው የሔዱት መልክተኞች ከናፒር ዘንድ ቀር በው አቶ ሳሙኤል ወደ አረብኛ ፣ ራሳም ደግሞ አረብኛውን ወደ

እንግሊዝኛ እየተረጐሙ ለናፒር ተነበበ ። ናፒርም በራሳም አስተ ርጓሚነት በቃሉ ለአቶ ሳሙኤል የከብቶቹን ስጦታ መቀበሉን ነግሮ በቴዎድሮስ እጅ የቀሩት እስረኞችና የሁሉም ቤተሰቦች እንዲላኩለት የሚለውን መልእክት እንዲያደርስ ቤንደርን ፥ ፍላንድ ፥ ማየርን ፥ ሳልሙለርን እና ዎልድ ሜየርን ቤተሰቦቻቸውን እንዲያ መጡ ከአቶ ሳሙኤል ጋር ላካቸው ።

እነ አቶ ሳሙኤል ተመልሰው ሥላሴ ከነበሩት ከአጤ ቴዎ ድረስ ዘንድ እንደደረሱ ቴዎድሮስ በቁጣ ቃል “ሥጦታውን ተቀ በሰ ወይስ አልተቀበሉም ?” ብለው ጠየቁ ። አቶ ሳሙኤልም እጅ ነስተው “ የእንግሊዙ ራስ የላኩት መልክት ስጦታዎን ተቀብ ያለሁ ፥ ። ብድሩን እግዚአብሔር ይክፈልዎት ብለዋል” አሉ ። ቴዎ ድሮስም ሰላም በመውረዱ ደስ አላቸው ። ወዲያውም የቀሩት ፈረ ንጆችና የሌሎቹም ሚስቶች ፥ ልጆች ሁሉ ከነጓዛቸው ጭምር እንዲ ሔዱ ፈቀዱላቸው ።

የፈረንጆቹ ጓዝና ቤተሰብ ተጠቃሎ ለመሔድ ወጣ ። ዎልድ ሜየር ሊሰናበታቸው ወደ ንጉሡ ሔደ ። ቴዎድሮስም ዎልድሜየርን ሲያዩት እንባቸው አቅርሮ “በል ደህና ያግባህ ። ወዳጄ ነህ ። ቤልን እንደምወደው ነበር አንተን የምወድህ”ብለው አሰናበቱት ። እነኝ ህም ለመጨረሻ ጊዜ የተለቀቁት ኤሮፓውያን ከተሰያት በኋላ በ9 ለዓት ከእንግሊዞች ጦር ሠፈር ደረሱ ። በጠቅላላው ከቴዎድሮስ እጅ የተለቀቁት እስረኞችና ቤተሰቦቻቸው 67 ናቸው ። እነሱም ሲዘረዘሩ እንደሚከተለው ነበር ብዛታቸው ።

ካሜሮን ከፖርቱጋላዊው ሠራተኛው ጋር ................. 2
ራሳም ካንድ ፖርቱጋላዊና ከሁለት ሕንዳዊ አሽከሮቹ ጋር . . . 4
ዶክተር ብላንክ ከሁለት ፖርቱጋላዊ አሽከሮቹ ጋር ....... 3
መቶ አለቃ ረዲውክስ ....................... 1
ቄስ ሮዜንታል ከሚስቱና ከልጁ ጋር ................ 3
ቄስ እስተርን ......................... 1
ኪራንስ ............................ 1
ዳቪድ ፔትሮ ከክልስ ልጁ ጋር ................. 2
ሪቻርድ ማክ ኪልቪ ...................... 1
ፍላድ ከሚስቱና ከሶስት ልጆቹ ጋር ............... 5
ቤንደር ከሚስቱና ከሶስት ልጆቹ ጋር .............. 5
የሟቹ የኬንዚሊን ሚስት ................... 1



ዎልድሜየር ከሚስትና ከልጁ ጋር ................ 3
አሊጋዝ ቤል .......................... 1
ሜየር ከሚስቱና ከሶስት ልጆቹ ጋር ............... 5
ሳልሙለር ከሚስቱና ከልጁ ጋር ................ 3
ወይዘሪት ሉስያ ቤል ...................... 1
ሞርዝ ሐል ከሚስቱና ከሁለት ልጆቹ ጋር ............ 4
ቡርጋውድ ከሚስቱና ከአምስት ልጆቹ ጋር ............ 7
ዛንደር ከሚስቱና ከአራት ልጆቹ ጋር .............. 6
ዶክተር ቪመፐር ከሴትና ወንድ ልጆቹ ጋር ........... 3
ማክረር ............................ 1
ብራንዲስ ........................... 1
እስቴይገር .......................... 1
ቢለር ............................. 1
ኢስለር ............................ 1

አጤ ቴዎድሮስ እስረኞቹን ካሰናበቱ በኋላ ከአንድ ትልቅ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው በሁለት እጆቻቸው ራሳቸውን ደግፈው ሲተክዙ ቆዩ ። በአጠገባቸው የነበሩት ራስ እንግዳ ቀረብ ብለው “ጃንሆይ ። ለምን ያዝናሉ ? እነዚህን ነጮች መልሰን እናምጣና ገድለናቸው እንሽሽ ። ወይም ተዋግተን እንሙት ” አሏቸው ። አጤ ቴዎድሮስም በቁጣ “አንት አህያ ። ባለፈው ሁለት ቀን ውስጥ ያስፈጀሁት ሰው አይበቃምን ። እነዚህን ነጮች እንድገድልና አበሻን በደም እንዳጥባት ነው የምትፈልገው?” አሏቸው ። ማታውኑ ደግሞ በሰው ገዳይነታቸው የታወቁት አጋፋሪ መሸሻ ከቴዎድሮስ ዘንድ ቀርበው “ የእንግሊዙ ራስ የላኩላቸውን ከብቶች ተቀበሉ የተባለው በውሸት ነው ። ከሠ ፈራቸው እንኳን እንዳይገቡ ብሎ ከሠፈር ውጭ ያስጠብቋቸዋል ።” ብለው ሲናገሩ ቴዎድሮስ የበለጠ ተበሳጩ ። ተናደዱ ። “እነዚህ ሰዎች የሚፈልጉትን አግኝተዋል ። አሁን የሚፈልጉት [illegible] ለመግ ደል ነው እንጂ ” አሉ ።

ቴዎድሮስ እንደተናደዱ ወደ ሰላምጌ ሔዱ ። ከሰላምጌም መሬት ላይ ቁጭ ሲሉ ዙርያቸውን ጦር ተተክሎ ሸማ ተጋረደላቸው ። እዚያም ሆነው “የምትወዱኝ ጦረኞች ተዘጋጁ ። ሁሉን ነገር ትታ ችሁ መሣሪያችሁን ብቻ ይዛችሁ ተከተሉኝ ። ሌላ ቤት የምንፈልግ በት ጊዜው ደረሰ” ብለው ተናገሩ ። ከተራራው ላይም ወርደው ለማምለጥ ቢያስቡም የተራራው ዙርያ በሙሉ በወሎ ኦሮሞዎች ስለተከበበ ፈፅሞ የማያስወጣ ሆነ ። ወታደሩም አብዛኛው እየከዳ

ቸው ሔደ ። ከጦር አለቆቻቸውም አንዳንዶቹ ቴዎድሮስ እንደገና እዋጋለሁ ፤ ወይም አመልጣለሁ ቢሉ እጃቸውን ይዘው ለእንግሊዝ ጦር ለመስጠት ተማከሩባቸው ። ግን እጃቸውን የሚይዘው ደፋሩ ማነው ? ከሰላምጌ ወደ መቅደላ አፋፍ ሲወጡም የተከተሏቸው አራት የጦር አለቆች ና ጥቂት ወታደሮች ብቻ ነበሩ ። ቴዎድሮስ መቅደላ አፋፍ ወጥተው በዚያ ያለውን ወታደራቸውን ሲያዘጋጁ አመሹ ። እንደገናም ወደ ሥላሴ ወርደው በዚያም ያሏቸውን ወታደሮች ሰብ ስበው "እንደገና አንድ ጊዜ ከእንግሊዝ ጦር ጋር ለመግጠም አስ ቤአለሁና ተዘጋጁ" ብለው ሲናገሩ አብዛኛው ወታደር እየከዳ የሥ ላሴን ቁልቁለት ይወርድ ጀመር ። ጥቂት ወታደሮች ብቻ በአሳባቸው ተስማምተው ከአጠገባቸው ቀሩ ።



የመቅደላ ሠፈር (መንደር)

ሚያዝያ 6 ቀን ጧት በ3 ሰዓት ገደማ ፀሐይዋ ዙርያዋን በጥቁር ክበብ ተከባ አዩና "ይህ ነገር የደም መፍሰስ ምልክት ነው" ብለው ተናገሩ ። በዚህ ጊዜም ቴዎድሮስ ከመቅደላ ተራራ አምልጠው ለመ ውጣት አስበው ነበር ። ነገር ግን እየከዱዋቸው ወደ እንግሊዞች



ጦር የገቡት የጦር አለቆቻቸው ቴዎድሮስን አምልጠው ለመጥፋት ማሰባቸውን ለእንግሊዞች በለተናገሩ እንግሊዞች የወሎን አጋማሽ የምትገዛውን የወርቂትን የጦር አለቆች ሰብስበው ቴዎድሮስን በሕይወት ወይም ሬሳቸውንም ቢሆን ላመጣ ሰው ታላቅ ሽልማት እንደሚሸለም አወጁ ። ቴዎድሮስም ከአምባቸው አምልጠው ለመጥ ፋት ማሰባቸውም ተነገረ ።

ከዚህ በኋላ በዚህ የፋሲካ ሰኞ ዕለት የእንግሊዝ ብርጌድ ጦር ወደ ፋላና ሰላምጌ ተላከ ። ቴዎድሮስም መቅደላ አፋፍ ላይ እንደ ሆኑ የእንግሊዞች ጦር ሲመጣ ተመለከቱ ። ከዚያም ከፈረሳቸው ላይ ወጥተው በመቅደላ ተራራ ሜዳ ላይ እየጋለቡ ሽጉጣቸውን ወደ ሰማይ ይተኩሱ ጀመር ። ከጥቂት ጊዜም በኋላ ከፈረሳቸው ወርደው እንግሊዞች ወደ መቅደላ አምባ እንዳይገቡ የቋቲትን በር በታላቅ ድንጋይ ያዘጉ ጀመር ። ውጊያው ከተሰያት በኋላ ተጀመረ ። የእንግሊዞች መድፍ የመቅደላን ተራራ ይደበድብ ጀመር ። በኮሎ ኔል ፊልድ የሚመራው አበረኛው የእግረኛው ብርጌድ ፋላ ኮረብታን ያዘ ። ሌላው ብርጌድ ደግሞ ሥላሴ ኮረብታን ያዘ ። በሁለቱም አምባ ዎች ላይ ያለው ሠራዊት ጠመንጃውንም ሆነ ጦሩን ፤ ጋሻውንም ሆነ ጐራዴውን ከመሬት እያስቀመጠ የእንግሊዝን ጦር በሰላም ተቀ በለ ። ሴቶችም ዕቃቸውንም እያዘጋጁና እያዘሉ ወደ አሮጌ ይጓዙ ጀመር ።

በዚህ መሀል ነገረኛ አወደድ ባይ ሰው ከናፒር ዘንድ ቀርቦ "ቴዎድሮስ አመለጡ" ብሎ ተናገረ ። ናፒርም ተናደደ ። ማህ ደረ ቃል የሚባለው ኢትዮጵያዊ የቴዎድሮስን የማምለጥንና ያለማምለጥን ሁኔታ አጣርቶ ቴዎድሮስ ያለማምለጣቸውን ለሙ ዚንጀር ነገረው ። ሙዚንጀርም ለናፒር ተናገረ ። ከዚህ በኋላ ናፒር የመቅደላ ተራራ በኃይል እንዲደበደብ አዘዘ ። ከቋቲት በር አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀው የተጠመዱት መድፎችና ሞርታሮች ያለማቋረጥ ይተኮሱ ጀመር ። የመቅደላ ሜዳ በሙሉ ይደበደብ ጀመር ። በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ አጠገብ የነበረ ጋሻ ዣግሬአቸው አቶ እማረ "ጃንሆይ ። እጃችንን እንስጥ" ብሎ ቢያማክራቸው "የሰው በሰዎች እጅ ከመውደቅ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ይሻላል" አሉት ።

ከእርስዎ ሳንለይ አብረን እንሞታለን ብለው ከቴዎድሮስ አጠ ገብ ያልተለዩት አማካሪያቸውና ጓደኛቸው ራስ እንግዳ ፤ የራስ

እንግዳ ወንድም ፡ የመድፈኞች አለቃ የሆኑት ራስ ፀጋ ፡ ቢትወደድ በቀለ ፡ መድፈኛው የአባ መርሳ ልጅ አቶ እንግዳ ወርቅ የጐጃሙ ራስ መብረቁ ፡ ባሻ ቢሰውር ፡ የቋራው ቢትወደድ ዳማሽ ፡ ማምጃ ቤታቸው ቢትወደድ ባህሪ ፡ አባላፊ ፡ ከንቲባ ፡ ደዳች አልዩ ደጃች መሸሻ ፡ የመቅደላው ጎሸ ቢትወደድ አሰኔ ፡ ጋሻ ዣግሬ አቸው አቶ አማኒ እና አሽከራቸው ወልደጋብር ብቻ ነበሩ ።




ማህደረ ቃል (በኢትዮጵያና በኤርፓ አለባበስ)

አጤ ቴዎድሮስ ውብ የሆነ በወርቀ ዘቦ ዝምዝም ያጌጠ ሐር ልብስ ለብሰዋል ። በላዩም የአንበሳ ለምድ ደርበዋል ። በወገባቸው ጐራዴና ሽጉጥ ታጥቀዋል ። ካንድ ድንጋይ ላይም ቁጭ ብለው የእንግሊዝን ጦር ሁኔታ በመነጥር ይመለከታሉ ። አንለይ ዎትም ያሏቸውም ሰዎች ሁሪያቸውን ከበው ቆመዋል ። በዚህ ሁኔታ እንዳሉ አንድ የመድፍ ጥይት በቴዎድሮስ ራስ በኩል ለጥቂት ስቷቸው አልፎ ሁለት ላሞችን ገደለ ። ይህ ከሆነ በኋላ ቴዎድ ተኩሱ የተተኮሰው በልብሳቸው ምልክት መሆኑ ታውቆ ቴዎድሮስ ልብሳቸውን ለውጠው ተራ ልብስ ለበሱ ። ከጥጥ የተሠራ ሱሪያቸውን ታጥቀው ሐር ሸሚዝ ለበሱ ። ነጭ ሸማም ደረቡበት ። በወገባቸውም ሽጉጣቸውን ታጠቁ ። እንዲህ ከለበሱ በኋላ እንደገና በመነጥራቸው የጦሩን ሁኔታ ይመለከቱ ጀመር ። አሳ



ትና ጭስ እያሳየ የሚመጣባቸውን ጥይት ራሳቸውን ዝቅ እያደረጉ ያሳልፉት ጀመር ። ከታማኝ ወዳጆቻቸው አጠገባቸው ካሉት መሐልም እየተመቱና እየሞቱ ይወድቁ ጀመር ። ታማኛቸው አማካሪያቸው ራስ እንግዳ ከወንድማቸው ጋር በአንዲት ጥይት ሞቱ ። ተኩሱ እየበረከተ ሲሔድም አንዳንድ ታማኞቻቸው እየሸሹ ሔዱ ። በቴዎድሮስ አጠገብ ቢትወደድ አሰኔ ፣ እንግዳ ወርቅና አጋፋሪ መሸሻ ብቻ ቀሩ ።



መቅደላ ሲቃጠል

አጤ ቴዎድሮስ በቋቲት በር ያለውን ወታደር ለማበረታታት ወደ ቲት በር ወረዱ ። በዚያም አንድም ሰው አላገኙም ። ለመቅደላ ከላካይነት በበሩ የቀሩትንም ወታደሮች አሥር ሰዎች ያህል ቻ መሆናቸውን አዩ ። በዚያም እንዳሉ ባሻ እንግዳና ጋሻ ዣግ አቸው አማኒ ከእንግሊዝ ጦር በተተኮሰ ጥይት ተገደሉ ። ጠመ ያዥያቸው ወልደጋብር ጠመንጃቸውን አቀባብሎ ለአጤ ዎድሮስ ሰጣቸው ። እሳቸውና የቀሩት ታማኞቻቸው በቋቲት ር ሳንቃ ቀዳዳ እያሾለኩ ይተኩሱ ጀመር ። ተስፋ የሌለው እተ ኩስ ነበር ። ስለዚህ ሁሉም ያን ቦታ ትተው ወደ ላይ ወደ ቅደላ ሜዳ ወጡ ።


መጠነኛ ከፍታ ያላትን ገደል ወጥተው 30 ሜትር ያህል በሚ ጻው ላይ እንደሔዱ ቴዎድሮስ ቆም አሉና ከታማኞቻቸው ከወል ደጋብር በስተቀር ሌላዎቹ "…. ሽሹ ። ቃል ከገባችሁልኝ መሀላ ፈትቻችኋለሁ ። እኔ ግን በጠላቴ እጅ ፈፅሜ አልወድቅም "አሏ ቸው ። እነኝያም እያለቀሱና እያዘኑ ተለይተዋቸው ሔዱ ። እንደ ሔዱላቸውም ወደ ወልደ ጋብር ዞር ብለው "እለቀ ። በእነሱ እጅ ከመውደቅ ራሴን እገድላለሁ"አሉትና ሽጉጣቸውን አፋ ቸው ውስጥ ከተቱና ተኮሱ ። ወደቁ ። ጥይቷም በላንቃቸው አልፋ በማጅራታቸው በኩል ወጣች ። ይህ የሆነው ወይም ቴዎድሮስ ራሳቸውን የገደሉት ከቀኑ 10 ሰዓት ከ10 ደቂቃ ሲሆን ነው ።

ከዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ የእንግሊዝ ጦር መቅደላ ኮረብታ ላይ ወጥቶ ነበር ። በድንጋይ የተፀጋው ቋቲት በር ባንድ መድፍ ጥይት ብትንትኗ ወጥቶ በሩ ተከፈተ ። የእንግሊዝ ጦርም ግማሹ በመ ሰላል ፣ ሌላውም በገመድ እየተጐተተ የመቅደላን ገደል ወጣው ። ውጊያው የተጀመረው ከቀኑ በ8 ሰዓት ሲሆን በ10 ሰዓት የእን ግሊዝ ጦር መቅደላ አፋፍ ገባ ። ኃይለኛ ዝናብ ይዘንብ ነበርና ቴዎድሮስ ከሞቱ ከአምስት ደቂቃ በኋላ መላው መቅደላ ተራራ በእንግሊዞች ጦር እጅ ሆነ ።

ቴዎድሮስ ራሳቸውን ገድለው እንደወደቁ አሽከራቸው ወልደ ጋብር ቀበቶአቸውንና ሽጣቸውን ይዞ ሔደ ። ከተሰባሰቡት 15 ያህል ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ሸሽተው እየሮጡ ሊያመልጡ ሲሉ የተ ራራው ዙሪያ በእርሞዎች ስለተያዘ መውጫ አጥተው ዋሻ ውስጥ ተደብቀው ተቀመጡ ። በማግስቱ ወደ መቅደላ ተመለሱ ።

ቴዎድሮስ ራሳቸውን የገደሉበት ጥይት ስትጮህ የሰሙ ሁለት የአይርሽ ወታደሮች የተኩስ ድምፅ ወደሰሙበት ቦታ ሔዱ ። ከዚያም ሲደርሱ ቴዎድሮስ በጀርባቸው ተንጋለው ወድቀው አገኙዋቸው ። ቴዎድሮስ ሕይወታቸው ገና ፈፅማ አላለፈችም ነበር ። እነኝያም የአይርሽ ወታደሮች የቴዎድሮስን ሽጉጣቸውን ከወሰዱ በኋላ ከወርቅ የተሠራ የአንገት ሀብላቸውንና የጣት ቀለበታቸውንም ሰርቀው ወሰዱባቸው ። እግራቸውንም እየጐተቱ ካንገላቷቸው ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ ሕይወታቸው ጨርሳ አለ ፈች ። ይህ የተወሰደባቸው የቴዎድሮስ የአንገት ሀብል ዛሬ በእ ንግሊዝ አገር ባንድ ወታደር ቤተሰብ እጅ ሲገኝ የጣት ቀለበታ ቸው ግን በእንግሊዝ አገር ኮሌጌት ቸርች ላንካስተር ተብሎ በሚ ጠራው ሥፍራ ይገኛል ።





የቴዎድሮስ ሞት (ራሳቸውን ሲገሉ)

በወቅቱ በሥፍራው የነበረው አሜሪካዊው ጋዜጠኛ "....ራቅ ብዬ ስመለከት ብዙ ኦፊሰሮች እንግሊዛውያን ሲቪሎች በደም የተበከለውን የቴዎድሮስን ሸሚዝ ለኔ ይገባል በማለት ሲጎተቱትና ሲጣሉበት አየሁ...." ይላል ። ይህ በደም የተለወሰው የቴዎድሮስ ሸሚዝ ዛሬ በእንግሊዝ አገር ባንክ ፊልድ ሙዚየም ውስጥ ይገኛል ። ያው ጋዜጠኛ .... "ሬሳቸው ተዘርሮ ጠጉራቸው ተሸልቶ ፣ ልብሳቸው ተገፎ በከፊል እርቃን ሥጋቸውን አየኋቸው...." ሲል ጽፏል ። ይህ ተሸለተ የተባለው ጠጉራቸው ዛሬ ሙዚየም አፍማን ካይንድ ተብሎ በሚጠራው ለንደን ሙዚየም ውስጥ ተቀምጦ ለሕዝብ ይታያል ።

ቻርልስ እስታቪሌይ መቅደላ ተራራ ላይ እንደወጣ አንድ ወታደር እየሮጠ ሄዶ የንጉሡ ሬሳ ወድቆ መገኘቱን ነገረው ። እሱም ሬሳቸውን በቃሬዛ ላይ አድርጐ እስረኞቹ የነበሩትና ቴዎድሮስን በሕይወታቸው ዘመን የሚያውቋቸው አይተው የቴዎድሮስ ሬሳ መሆኑን እንዲያረጋግጡ አደረገ ። ከእስረኞቹ መሀል አንዱ የቴዎድሮስን እጅ አንስቶ የተሰበረች ጣታቸውን አየና የቴዎድሮስ ሬሳ መሆኑን አረጋገጠ ።

ጣታቸው የተሰበረችው በወጣትነታቸው ጊዜ በጦርነት ላይ በጥይት ተመትተው ነው ። ቻርልስም የቴዎድሮስ ሬሳ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ከሬሳው አጠገብ ዞር ሲል በዚያ የነበረ ሕዝብ ሁሉ እያወካና እየጮኸ የቴዎድሮስን ሬሳ ደበደበ ፣ ፍፁም ራቁት እስኪሆኑ ድረስም ልብሳቸውን ሁሉ ቀዳደደው ቴዎድሮስም በተወለዱ በ50 ዓመታቸው በነገሡ በ15ኛው የግዛት ዘመናቸው ሞቱ ማርክሃም ሲተች "...እስፈሪው ጊዜ አልፏልና ያ አስፈሪው ሰው እንደሞተ ቀብሮ ሆነ...."ይላል ።

የቴዎድሮስ ሬሳ ወደ ኢጣሊያዊው ወደ ዴቪድ ፒየትሮ ጐጆ ተወሰደ ። ራሳም ያ የተናገሩት ሬሳዬ አጠገብ ሆነህ አትቅበሩት ይቀመጥ ትለኛለህ ያሉት ትዝ አለውና ሬሳቸውን አስለብሶ በአልጋ አስደርጐ እንዲወሰድ አደረገ ።

በማግስቱ የእንግሊዝ መልዕክተኞች ወደ እቴጌ ጥሩወርቅ ዘንድ ሔደው የቴዎድሮስን ሬሳ ታላቅ ክብር ተደርጐለት በእንግሊዞች እጅ ይቀበር ? ወይስ ለእርስዎ ሰጥተን እንደ አገራችሁ ባህል ትቀብሩ ? ብለው ጠየቋቸው ፣ ንግሥቲቱም በአገሬ ቄሶች በፀሎት ቢቀበር ይሻላል አሉ ፣ እቴጌይቱ ሬሳው እንዲሰጣቸው በመ



ጠየቃቸው ላምሰዴን ፣ ዶክተር ብላንክ እና ከኢትዮጵያውያኖች በኩል አቶ ሣሙኤል ባሉበት እንዲመረመርና እንዲሰጣቸው ታዘዘ ።



አጤ ቴዎድሮስ ራሳቸውን ገድለው እንደወደቁ

የቴዎድሮስ ሬሳ ይመርመር የተባለበት ምክንያት "ራሳቸውን ገደሉ ? ወይስ ሌላ ሰው ገደላቸው ?" ለሚለው መጠይቅ መልስ እንዲገኝ ነበር ። መርማሪዎቹ በአፋቸው የገባችው ጥይት በማጅራታቸው በኩል መውጣቷን ፣ ጥይቱን የተኮሱትም የሽጉጡን አፈሙዝ አፋቸው ውስጥ ከትተው በመሆኑ አፋቸው ውስጡ በሙሉ በባሩዱ ጭስ በመጥቆሩ ተረጋገጠ ። ቴዎድሮስ የሞቱት ራሳቸውን ገድለው እንጂ ሌላ ሰው እንዳልገደላቸው ከተረጋገጠ በኋላ ሬሳቸው ተሰጠ ።

ሬሳቸው በመጀመሪያ በጥሩ የጥጥ ልብስ ተጠቀለለ ። በዚያ ላይ በወርቀ ዘቦ ከር የተዘመዘመ ሐር ለበስ ። በመጨረሻ ውብ የሆነ ባለአበባ ጨርቅ ተደረገበት ። መቃብራቸው ቤት ክርስቲ

ያን አጠገብ ከገረገራ (ከግቢ )ውጭ ተቆፈረ ። መሬቱ ጠጣር ስለ ነበረም ቁፋሮው ብዙ ጊዜ አቆየ ። በቀብሩም ሥርዓት ላይ ማንም ሰው መካፈል እንደሚችል መፈቀዱን ሰፋሬ እየዞረ ተናገረ ። ከጥቂት ሰዎች በስተቀር ግን የመጣ አልነበረም ። ምናልባት ጥቂት ቀደም ብሎ ነጎድጓዳማ ዝናብ ዘንቦ ስለነበር ቀባሪ በብዛት ያልወጣው በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችል ይሆናል ። ምናል ባትም በጥላቻ ወይም ደግሞ በፍራቻ ሊሆንም ይችላል ።



የቴዎድሮስ ሬሳ ያረፈበት ቤት በዘብ ሲጠበቅ

ሬሳቸው ባንድ አርጌ የጠፍር አልጋ ላይ ተደረገ ። ሬሳቸው እስኪቀበር ለፀጥታው ጥበቃ የታዘዘው ከ33ኛው ብርጌድ የተውጣጡ ወታደሮች መጡ ። ከዚያም በኋላ ሬሳቸው በወታደሮች ታጅቦ ወደ መቀበሪያው ሥፍራ ተወሰደ ። በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥም ተከተተ ። በላዩም ላይ ድንጋይ ተረበረበ ። ከድንጋዩም በላይ ድቅ ድቅ እየተደቀደቀ ተደረገበት ። አቀባበሩ ፍትሐትም ሆነ ደንበኛ የቀብር ሥርዓት አልተፈፀመበትም ። ጥቂት ቄሶች ብቻ መጠነኛ ፀሎት አደረሱ ። ቀብሩ እንደተፈፀመም ታላቅ ነጎድጓዳማ ዝናብ ዘነበ ።

እንግሊዞች መቅደላን ከያዙ በኋላ በዚያ አምባ የታሠሩትን እስረኞች በሙሉ እየፈቱ ለቀቁዋቸው ። ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከ ተሉት ናቸው ።



15 ዓመታት የታሠሩ
የራስ አሊ ወንድም ደጃች ይማም ።
የጉጀሙ ደጃች ብሩ ጉሹ ከሁለት ወንድሞቻቸው ጋር ።

14 ዓመት የታሠሩ
የየጁው ባላባት ፋሪስ አሊ
የደጃች ውቤ ልጅ ካሣ ውቤ
የኢዱ ልጅ ጓንጉል ።

13 ዓመት የታሠሩ
የእንደርታው ባልገዳ አርአያ

10 ዓመት የታሠሩ
የሚጫው ባላባት ባሻ ኃይሌ

ሰባት ዓመት የታሠሩ
የአጋሜው ሹም አጋሜ አረጋዊ

አምስት ዓመት የታሠሩ
የሐራማቱ ደጃዝማች ማህሉ
" አዛዥ ንጉሴ
የጠራው ባልገዳ ሙሮ
የኢዱ ማህሌ
የሰለዋው ሹም ሰስዋ ሕዝቅያስ

አራት አመት የታሠሩ
የዋጉ ዋግሹም ተፈሪ
የበለሳው ጉሸን ወንድየ

ሶስት ዓመት የታሰሩ
የሰሜኑ አካሉ ደረሶ
አዛዥ ጋረድ
የሸዋው ራስ ልቤ

ሁለት ዓመት የታሠሩ
የሸዋው ገርማሜ
" ዳርጌ ማህስ ሥላሴ
አንዳንድ ዓመት የታሠሩ
የበጌምድሩ ራስ ወልደ ማርያም
ራስ ገብሬ

ራስ ዋሀድ ተድላ
ቢትወደድ ተድላ ከሁለት ወንድሞቻቸው ጋር
የበጌምድሩ እዛዥ ወንዴ
አዛዥ ገብረ ሥላሴ
አቶ ሠርጌ ደረሶ
የቋራው ባላባት ወሰን ይልማ
አቶ ወሰን ዳርዬ
የትግራዩ ጠእፉ እንግዳ ናቸው ።

እነኝህ ስጊዜው እየተመዘገቡ የወጡት እንጂ ብዙዎች ሳይመዘገቡ በግርግሩ መሀል ወጥተዋል ።

የአጤ ቴዎድሮስ የቀብር ሥርዓት ከተፈፀመ በኋላ እንግሊዞች እቴጌ ጥሩወርቅ ከሚኖሩበት ቤት በራፍ ላይ ዘብ አቆሙ ። ዘብ ያቆሙበት ምክንያት ማንም ሰው ገብቶ እንዳይሰድባቸው ወይም እንዳያጉላላቸው እንዲጠብቃቸው ነው ። ሚርዌይዘር እቴጌ ጥሩወርቅ ካሉበት ድረስ ሔዶ ከቤታቸው ውጭ ተቀምጦ በአስተርጓሚው በአቶ ሳሙኤል አማካይነት እቴጌ ጥሩወርቅ ምን ሐሳብ እንዳላቸው ተጠየቁ ። እቴጌይቱም ፍላጐታቸው ወደ ትውልድ አገራቸው ወደ ሰሜን ለመሔድ መሆኑን ነግረው ስለልጃቸው ስለ ዓለማየሁ ግን አባትዬው አጤ ቴዎድሮስ በመጨረሻ ጊዜ እንደተናገሩት ወደ እንግሊዝ አገር ይሂድ አሉ ። ከዚህ በኋላ እቴጌይቱ ከልጃቸው ከዓለማየሁ ቴዎድሮስና የቴዎድሮስ ቁባት ከነበሩት ከወይዘሮ የተመኙ ጋር ወደ እንግሊዝ ጦር ሠፈር ወርደው በዚያ ቆይተው የእንግሊዝ ጦር በሚመለስበት ጊዜ እስተአገራቸው መንገድ ድረስ እንዲሸኛቸው ተወሰነ ። እነሱም በዎልድሚየር እጃቢነት ወደ እንግሊዞች ጦር ሠፈር ተወሰዱ ።

ሚያዝያ 16 ቀን ወደ ማታ ገደማ ከወሎ የኦሮሞ ባላባቶች አንደኛዋ ወይዘሮ ወርቂት መምጣቸው በእንግሊዞች ሠፈር ተነገረ ። እንግሊዞችም በክብር ተቀብለው ከሰር ሮበርት ናፒየር ጋር አገናኙዋቸው ። ወይዘሮ ወርቂት ከሰር ሮበርት ናፒር ጋር ተገናኝተው በአስተርጓሚ ሲጫዋወቱ "....የቻልነውን ያሀል ከቴዎድሮስ ጋር ስንዋጋ ኖርን ። ግን ኃያልነቱ እያየለብን ብዙ ጊዜ ልንዋጋውና ልናሸንፈው አልቻልንም ። ልጄን በጥሩ ሁኔታ አሳድገዋለሁ ብሎ ወስዶ ከሰው ልጅ ርሀራሄ ውጭ በሆነ ሁኔታ ቆራርጦ መቅደላ ገደል ጣለው ። አሁን እኔ የመጣሁት የጠላቴን የቴዎድሮስን መቃብርና ልጄ የትጣለበትን የመቅደላን ገደል ለማየት ነው ..." ብለው ተናገሩ ።



ሰር ሮበርት ናፒርም በሌላዋ የወሎ ኦሮሞ ባላባት በሆኑት በወይዘሮ መስተዋትና በእሳቸው መሀል ያለው ልዩነት ቀርቶ ሰላም እንዲመሠርቱ ቢጠይቋቸው "... ሁለት ሰዎች ለመንገስ ሲተናነቁ በነሱ መሀል እንዴት ሰላም ሲኖር ይችላል? መስተዋት ከኔ ጋር ወዳጅ ለመሆን በእናንተ ፊት ዛሬውኑ ቃል ብትገባ ነገ ጠብዋን ትጀምራለች..." አሉ ። ይህን በሚነጋገሩበት ጊዜ የሰር ናፒር ወታደር ገብቶ የወይዘሮ መስተዋትን መምጣት ተናገረ ። ናፒርም ለወይዘሮ ወርቂት ስጦታ ሰጥቶ ተሰነባበቱ ። ወይዘሮ ወርቂት "ልጄን ገደለብኝ" ያሉት ምኒልክ ያመለጡ ጊዜ ወርቂት ምኒልክን በወሎ በኩል አሳልፈዋል በማለት ቴዎድሮስ ተናደው 24 የወሎ መኳንንትን ገደል እየጨመሩ ካስገደሉዋቸው መሀል አንዱ የወርቂት ልጅ ነበር ።

በዚያን ጊዜ በቦታው የነበረው ማርክሃም ስለወይዘሮ ወርቂት ሲፅፍ ".... ጀግናይቱ ወሬቂት ለብዙ ጊዜ በቴዎድሮስ ላይ አምጣቆይታለች ። የነበራትም አንድ ልጅ ተገድሎባታል ። አሁን አርጅታለች ። ልጅም የላትም ። የነበራትም ኃይል በአሁኑ ጊዜ በርዷል ። የሚደጋግፋትም የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ብቻ ነው ።...ትውልዷ ከታላላቅ ባላባቶች ነው ። ባልዋም አህመድ በሽር ከታላላቅ የወሎ ባላባቶች ዝርያ የሚወለድ ነው ። በመጨረሻም አብዛኛው የወሎ ጋላ ሌላይቱን ባላባታቸውን ወይዘሮ መስተዋትን በመደገፍ ላይ ነው ።.... ወርቂት ሁሉን ነገር የተወችው ልጅዋ ከሞተ በኋላ ነው ..." ብሏል ።

ሌላዋ የወሎ ኦሮሞ ባላባት ወይዘሮ መስተዋት ነበሩ ። እሳቸውም ወደ እንግሊዞች ጦር ሠፈር የመጡት ከልጃቸው ከኢማም አህመድ ጋር ነው ። ወይዘሮ መስተዋት የአህመድ በሽር አጐት የሊበን ሚስት ነበሩ ። ባላቸው ሊበን ስለሞቱ መስተዋትም እንደ ወርቂት ሁሉ ዓለም በቃኝ ብለው ግዛታቸውን የሚያስተዳድረው ልጃቸው ኢማም አህመድ ነው ። ወደ እንግሊዞች ጦር ሠፈር የመጡትም በጦር አዛዦቻቸው በአከበር እሊና በወታደሮች ታጅበው ነው ። የመጡ ዕለትም የወይዘሮ ወርቂት ሠራዊት ከእንግሊዞች ጦር ሠፈር ለቆ እስቲወጣና እረፍትም ለማድረግ በአቅራቢያ እደሩ ። በማግስቱ ሚያዝያ 17 ቀን ከእንግሊዞች ጦር ሠፈር ሲገቡ ለጄኔራል ናፒር "ታላቅዋ የወሎ ባላባት ከደላንታ መጡ" ብሎ ተነገረ ። ወይዘሮ መስተዋት የሚኖሩት ከመቅደላ ተራራ 10 ኪሎ ሜትር ያህል ከሚርቅ ከደላንታ ጐን ከበሽሎ አጠገብ ሉጉድ ከሚባል



ወርቂት (የወሎዋ ንግስት)

ኮረብታ ላይ ነው ፣ እንግሊዞች ወደ መቅደላ በሚመጡበት ጊዜ ሁኔታወን በመፍራት ከሎጉድ ለቀው ሰወር ብለው ነበር ። የእንግሊዞች ሁኔታ ካለቀ በኋላ አክበር አሊ ወይዘሮ መስተዋትን አፅናንተና ጉዳዩን አስረድቶ ባያፅናናቸው ኖር ወይዘሮ መስተዋት ከእንግሊዞች ዘንድ አይደርሱም ነበር ።



እንግሊዞች የመቅደላን ጦርነት ከመጀመራቸው በፊት አክበር አሊ ከእንግሊዞች ጋር ተወዳጅቷል ፤ ከእንግሊዞች ጋር ባደረገው ምክክርና በታዘዘው ትእዛዝ መሠረት ከወይዘሮ መስተዋት ዘንድ ሔዶ ሁሉንም ነገር አስረድቶ ወታደሮቻቸው ቃፊር በርገና የመቅደላን ዙርያ ቴዎድሮስ እንዳያመልጡ እንዲጠብቁ ያስደረገ አክበር አሊ ነው ። ከመቅደላ ተራራ የሚወርድ ማንኛውም ሰው ወደ ኋላው እንዲመለስ እንጅ ተራራውን እንዳይወርድ የሚወርድ ወይም በኃይል የሚጠቀም ካለም በኃይል እንዲመለስ ትእዛዝ የሰጠ አክበር አሊ ነው ። አጤ ቴዎድሮስ በመጨረሻው ሰዓት ከመቅደላ ባንደኛው በኩል ለማምለጥ ሞክረው በኃይል የመለሱዋቸው እነኝሁ ጥብቅ ትእዛዝ የተቀበሉት የመስተዋት ሰዎች ናቸው ። በኋላ ግን የታዘዙት የወይዘሮ መስተዋት ወታደሮች የታዘዙትን ትእዛዝ ትተው ዘረፋ ስለጀመሩ የአጤ ቴዎድሮስ ልጅ ደጃች መሸሻ ሳይቀሩ በቃፊር በር በኩል እየወጡ ሔዱ ።

ወይዘሮ መስተዋት ወደ እንግሊዞች ጦር ሠፈር የመጡት በቴዎድሮስ ሞት በጣም ስለተደሰቱ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት ጭምር ነበር ። ከናፒር ዘንድ ገብተው ይህንኑ ደስታቸውን ገለጡ ። ናፒርም አጤ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ የተሳለውን ስዕላቸውን ለወይዘሮ መስተዋት አሳይቶ "እኚህ አይደሉምይ የምትጠያቸው ቴዎድሮስ ?" ብሎ ጠየቀ ። ወይዘሮ መስተዋትም "እኔ እንዴት አውቀዋለሁ? ያየውስ የተጠጋውስ ማነው?" ብለው መለሱ ።

ወይዘሮ መስተዋት በኢትዮጵያ ውስጥ በጦረኛነት ከታወቁት ሴቶች አንደኛዋ ናቸው ። ወይዘሮ መስተዋት በአፍላነታቸው ዘመን እንደ ወንድ የጦር መሣሪያ እየያዙ ከወንዶች እኩል የሚዋጉ ሴት ነበሩ ። ከአረጁ በኋላ እንኳ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክና የጐጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት እምባቦ ላይ በተዋጉ ጊዜ ወይዘሮ መስተዋት ለንጉስ ምኒልክ ረድተው ጐጃሞችን ወግተዋል ። በዘመኑና በጦርነቱ የነበሩ የጐጃምና የሸዋ ሰዎች ሁሉ የወይዘሮ መስተዋትን ጀግንነትና ውጊያ አድንቀዋል ።

አቴጌ ጥሩወርቅ ፣ ልዑል ዓለማየሁና ወይዘሮ የተመኙ እንግሊዞች ጦር ሠፈር ገብተው ጥቂት ከቆዩ በኋላ የእንግሊዝ ጦር መመለሻ ስለደረሰ የቴዎድሮስ ቤተሰቦችና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን ከእንግሊዞች ጦር ጋር አብረው ሊመጓዝ ተነሱ ። ምንም ዓይነት ክብር ባልጐደለበት ጉዞ እየተጓዙ ዋድላ ሲደርሱ የተከዜን ወንዝ

ሳያቋርጡ ባንጠራ ላይ ወይዘሮ የተመኙ ተለይተው የተሰጣቸውን ስጦታ ይዘው ወደ ትውልድ አገራቸው ወደ የጁ ሔዱ ።


ወይዘሮ የተመኙ አጤ ቴዎድሮስ ከነበሩዋቸው ቁባቶች ሁሉ የሚወዷቸው ሴት ነበሩ ። ቴዎድሮስ ወይዘሮ የተመኙን የያዙት ገና እቴጌ ተዋበች ሳይሞቱ በፊት ጀምሮ ነው ። ተዋበች ሞተው ጥሩ ወርቅን ካገቡ በኋላ እቴጌ ጥሩወርቅ የቴዎድሮስን ቁባቶች ሁሉ ማየት እንደማይፈልጉ ነግረዋቸው አጤ ቴዎድሮስ ቁባቶቻቸውን ሁሉ ሲያባርሩ ወይዘሮ የተመኙን ግን አላበረሩም ነበር ። ቴዎድሮስ በወይዘሮ የተመኙ ላይ የነበራቸው ፍቅር የተለየ ነበር ። አጤ ቴዎድሮስ ራቅ ካለ ቦታ በሚሔዱበት ጊዜ ከሚስታቸው ይልቅ ለወይዘሮ የተመኙ የፍቅር ደብዳቤ ይፅፉላቸው ነበር ። በደብዳቤያቸውም ላይ "እህቴ ፣ የእናቴ ልጅ ፣ አትባቢ ፣ አይዞሽ ። በቅርቡ እደርሳለሁ ።. . . ." እያሉ ይፅፉላቸው ነበር ።

ራሳም እንደፃፈው ". . . .የተመኙ ቴዎድሮስ የሚወዷቸው እቴጌ ናቸው ።. . . .የአንድ የየጁ ጋላ ሚስት ነበረች ። ውብ ነበረችና ውበቷን (ቴዎድሮስ) ሰሙ ። ከዚያም በኋላ አስመጥተው ክርስትና አስነሱዋት ።. . . ." ይላል ። ወይዘሮ የተመኙ ወፍራምና ውብ ሴት ነበሩ ።

ወይዘሮ ጥሩወርቅ ወደ ትውልድ አገራቸው የሚታጠፉበት አካባቢ ሲደርሱ ሆዳቸው ባባ ። ትንሹን የሰባት ዓመት ልጃቸውን ዓለማየሁን ለእንግሊዞች ትተው መለየቱ አባባቸው ። በፊት የተናገሩትንም ከልጃቸው ተለይተው ወደ ትውልድ አገራቸው የመመለሳቸውን ሐሳብ ለውጠው ከልጃቸው ሳይለዩ ልጃቸው ከሚደርስበት አገር አብረው ለመጓዝ መወሰናቸውን ለእንግሊዞቹ ነገሩ ። እንግሊዞቹም በአዲሱም ሐሳባቸው ተስማምተው ወደፊት ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። መቅደላ ላይ ታስረው የነበሩት ሁለቱ ወንድሞቻቸው ካሣ ውቤና ጓንጉል ውቤ ግን እህታቸውንና እንግሊዞቹን ተሰናብተው ወደ ትውልድ አገራቸው ሔዱ ።

እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ ልጃቸውን አለማየሁን ተከትለው ከእንግሊዞች ጦር ጋር ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። እቴጌ ጥሩወርቅ መቅደላን ከለቀቁ ጀምሮ ሕመማቸው እየጠና ጤነኛ አልነበሩም ። እንጣሎ አጠገብ ሐይቅ ሐላጥ ከሚባል ሥፍራ ሲደርሱ መከረኛይቱ እቴጌ ጥሩወርቅ ሞቱ ። ሬሳቸውም ጨለቆት ባለው ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከታላቁ ከራስ ወልደ ሥላሴ መቃብር አጠገብ ተቀበሩ ።





ጨለቅት ከተማ (አዲግራት)

አባቱ የሞቱበት ሕፃኑ ዓለማየሁ ቴዎድሮስ አሁን ደግሞ እናቱ እቴጌ ጥሩወርቅ ሞቱ ። ቴዎድሮስ ከመሞታቸው በፊት ራሳምን አስጠርተው ". . . .እምነዛለሁና ልጄን ልዑል አለማየሁን አደራ እሰጥሃለሁ ። ተጠንቅቀህ ያዘው ። አባትም ሁነው ። የመጨረሻ ጊዜዬ እንደቀረበ ታውቆኛል. . ." ያሉትን በማስታወስ ራሳም ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ኤሮፓውያን ጭምር አለማየሁን በእንክብካቤና በአባትነት ያዙት ።

# ምዕራፍ 16

## እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ ፣ ልጅ አለማየሁ ቴዎድሮስ

እቴጌ ጥሩ ወርቅ የሰሜን ገዥ የነበሩት የደጃች ውቤ ልጅ ናቸው ። ራሳም እንደጻፈው ቴዎድሮስ ጥሩወርቅን ያገቡዋቸው ገና የ12 ዓመት ልጅ ሳሉ ነው ይላል ። ከእቴጌ ተዋበች በኋላ ያገቡዋቸው ሁለተኛ ሕጋዊ ሚስታቸው መሆናቸው ነው ።

አጤ ቴዎድሮስ በዚህ ጋብቻ መልካም ምርጫ አላደረጉም ። በውበቷ ተደንቀው ወደው ማግባታቸው ጥሩ ነው ። ልጅቱ ግን በግዴታ እንጂ በውዴታ በፍቅር ለታገባቸው አትችልም ። ቴዎድሮስ አባትዋን በጥብቅ አስረዋቸዋል ። አባትዋን ብቻ ሳይሆን ሁለት ታላላቅ ወንድሞቿንም ካሣ ውቤንና ጎንጉል ውቤንም አስረውባታል ። ጥሩነሽ በአባትዋ በወንድሞችዋ መታሰር በቤተሰቡ መፍረስ ያዘነች ፣ በወጣትነት ዕድሜዋ ለመመንኮስ ያሰበች ናት ።

ጥሩነሽ ከጧት ጀምራ እስከ ማታ ውሎዋ ከቤተ ክርስቲያን ነበር ። ለአጤ ቴዎድሮስ ቆንጆ ልጅ አየሁ ብሎ የተናገረውም ወታደር ልጅቱን ያየው ከቤተ ክርስቲያን ሲትፀልይ ነው ። በትጠራችም ጊዜ በግዴታ ተወሰደች እንጂ በደስታና በውዴታ አልነበረም ። ይህን ሁሉ ብናልፈው እንኳ ቴዎድሮስ ሚስታቸውን ለማስደሰትና ኑሮአቸውን በሚገባ ለመመሥረት ከፈለጉ ወንድሞችዋንም ሆነ አባትዋን ሊፈቱላት ይገባ ነበር ። ታሳሪዎቹ የሚፈሩና የሚጠረጠሩ ቢሆኑ እንኳ በአጠገባቸው አስቀምጠው በዓይነ ቁራኛ ሊያስጠብቁቸው ይችሉ ነበር ። ይህ ባለመሆኑ ሚስቲቱ ሚስት ሲሆኑ አልቻሉም የግዴታ እንጂ የደስታ ሚስት አልነበሩም ። ስለዚህ በቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ገብታ እስረኛ የሆነችው ጥሩነሽ ቴዎድሮስ እንደሰየሟት ጥሩ ወርቅ መሆንዋ ቀርቶ ጥሩ እናዳጅ ሆነችባቸው ።

ቴዎድሮስ ሚስታቸውን ለማስደሰት ስላልፈለጉ እቴጌ ጥሩወርቅም ባላቸውን ለማስደሰት አልፈለጉም ። ሌላው ቀርቶ ቴዎድሮስ ከውጭ ጥሩወርቅ ካሉበት እልፍኝ ሲገቡ እንኳ በባህላችን መሠረት



ከተቀመጡበት ብድግ አይሉላቸውም ነበር ። እነዚህን በመሳሰሉት ሁኔታዎች ሁሉ የቴዎድሮስ ኑሮ በውጭም በውስጥም ብስጭት የበዛበት ሆነ ።

ለቴዎድሮስ የቅርብ ወዳጅ የነበረው ዎልድሜየር በስለዚሁ ጉዳይ ሲጽፍ "....አዲስዋ እቴጌ እንደፊተኛዋ አልሆን አሉ ። በዚህ ምክንያት ንጉሡ ይበሳጩ ጀመር ። ከብስጭት የተነሳም ብዙ አስካሪ መጠጥ መጠጣት ጀመሩ ። ሌሎች ሴቶችንም በየቦታው ማስቀመጥና መሔድ አበዙ ።..." ይላል ዎልድሜየር እንደጻፈው ቴዎድሮስ በመቅደላ ተራራ ላይ ብቻ 28 ቁባቶች አስቀምጠው ነበር ። በዚህ ምክንያትም በአባት እንጂ በእናት የማይገናኙ ብዙ ልጆች ነበሩዋቸው ።

ዶክተር ብላንክ ስለ ወይዘሮ ጥሩወርቅ ጋብቻ ጉዳይ በጻፈው ታሪክ "....ወጣትዋ ቤተክርስቲያን ለማገልገል ስትል ገዳም ለመግባት ማቀድዋን ገልጸ ጥያቄያቸውን ሳትቀበል ቀረች ። አጤ ቴዎድሮስ ሐሳባቸውን ከፍጻሜ ሳያደርሱ የማይቀሩ ብርቱና ኃይለኛ ሰው ስለሆኑ ደጃዝማች ውቤን ይህችን ልጃቸውን በሚስትነት ቢድሩላቸው ከእስር ቤት አውጥተው በሠፈራቸው የክብር እንግዳ ሆነው እንዲቀመጡ የሚያደርጉ መሆኑን ገለጸው በበኩላቸው ልጃቸውን እንዲያሸንፉ አሳብ ስላቀረቡ በመጨረሻ ጥሩነሽ ለሽማግሌ አባትዋ ደህንነት ራስዋን ሰውታ ልትወዳቸው የማትችለውን ሰው ለማግባት ተስማማች ። አጤ ቴዎድሮስ ባለመታደላቸው ሁለተኛ ሚስታቸው እንደሟቿ በእርሳቸው ፍቅር የተነደፈች ፍጹም የሆነ ፍቅር ያላት ሴት ሳትሆንላቸው በመቅረቷ ከፍ ያለ ሃዘን ደረሰባቸው ። ወይዘሮ ጥሩነሽ በጣም ኩሩ ሴት ስለነበሩ ባላቸውን እንደ አንድ ዝቅተኛ ሰው አድርገው እየተመለከቱ እንዲያከብሯቸውና እንዲወነቁላቸው የነበራቸውን ፍላጎት በግልጽ ከማሳየት አልተመለሱም ። አጤ ቴዎድሮስ እንደልማዳቸው ከሰዓት (ከትስያት) በኋላ የደከመውን ሰውነታቸውን ለማሳረፍ ወደ ንግሥቲቱ ድንኳን ሲሔዱ አስደሳች አቀባበል ስለማያገኙና እንዲያውም በቀዝቃዛና ኩራት በተመላ መንፈስ እየተቀበሉና የተለመደውን ለንጉሠ ነገሥት ባላቸው ማሳየት የሚገባቸውን ትህትናና የክብር ሰላምታ እንኳ ይነፍጓቸው ጀመር ። አንድ ቀን ወደ ድንኳናቸው ሲገቡ ያላዩዋቸው መስለው ከመቀመጫቸው ሳይነሱላቸውና ስለጤናቸውም ሲጠይቋቸው መልስ ሳይሰጡ በእጃቸው የያዙትን ዳዊት እየተመለከቱ ዝም በማለታቸው ለምን መልስ እንዳልሰጧቸው ቢጠይቋቸው "ከእርስዎ

ከበለጠና ከሚሻል ሰው ጋር በመነጋገር ላይ ስለሆንኩ ነው።... እሷቸው። ይባላል ...” ይላል። አጤ ቴዎድሮስ በገቡት ቃል መሠረት የሚስታቸውን አባት አልፈቱላቸውም። ሽማግሌው ውቤ ከእስር የተፈቱት ከሞቱ በኋላ ሬሳቸው ነው። ወንዶች ልጆቻቸው የእቴጌ ጥሩወርቅ ወንድሞችም የተፈቱት የእንግሊዝ ጦር መቅደላን ከያዘ በኋላ ነው። በዚህ ሁሉ ምክንያት የጥሩወርቅ ኑሮ የኀዘን ነበር።

ዶክተር ብላንክ በጻፈው ታሪክ እቴጌ ጥሩወርቅ ኑሮአቸው እንዴት እንደነበር ሲገልጽ “....የዓለማየሁ እናት ወይዘሮ ጥሩነሽ የተበደሉና የተገፉ ቢሆንም ምንም ቅያሜ ሳያሳዩ ለባላቸው ታማኝ ሆነው ይኖሩ ነበር። ጊዜአቸውን የሚያሳልፉት ልጃቸውን ከጐን አስቀምጠው ብቻቸውን መዝሙረ ዳዊት የመላእክትንና የሰማዕታትን መልካ መልክ የሐዋርያትንና እጅግ በጣም የሚወዷትን የቅድስት ማርያምን ውዳሴ ማርያም በማንበብ ነበር። ምንም እንኳን ባላቸው ቴዎድሮስን ምን ጊዜም ቢሆን ወደዋቸው የማያውቁ ቢሆንም በመከራቸው ጊዜ በድፍረት አብረዋቸው ተሰልፈው የስቃያቸው ተካፋይ ሆነዋል።... አጤ ቴዎድሮስ ሲሞቱ ሁለት ቀን ሲቀራቸው ለብዙ ዓመታት የተለዩዋቸውን ሚስታቸውን አስጠርተው ከሰዓት በኋላ ከእርሳቸውና ከልጃቸው ጋር ሲጫወቱ ዋሉ።...” ብሏል። (ትርጉም ዳኜ ወ/ሥ)

ምኒልክ ሸዋ ገብተው ራሳቸውን ንጉሥ ካሉ በኋላ ካንዳንድ የመቅደላ እስረኞችና መኳንንት ጋር ተማክረው የመቅደላን አምባ ለመያዝ በመጡ ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ ዶክተር ብላንክ በመጽሐፉ ሲገልጥ “.... በዚህ ጊዜ ማድረግ የሚገባትን ፈጸመች። በልጅ ዓለማየሁ ጋባዥነት በአምባው ውስጥ ለሚገኙት የጦር አለቆች ምንም እንኳ ቀኑ ጾም ቢሆንም በጾም ወጥ ግብር አግብታ የጦር አለቆችና ወታደሮቹ ታማኝነታቸው ለቴዎድሮስ መሆኑን እንዲያረጋግጡ ስስጠየቀችና ከሐዲም ቢኖር ቅጣቱን ለመስጠት መሰናዳቷ ስለታወቀ ምኒልክን እንረዳለን በማለት ውስጥ ውስጡን ቃል የገቡ ሁሉ ፍርሃት አደረባቸውና ሁላቸውም ታማኝነታቸውን ለቴዎድሮስ ለማድረግ ቃል እየገቡ ወጡ። በዚህ ስብሰባ አንዳንድ የጦር አለቆች ከምኒልክ ጋር የነበራቸውን ስምምነት መሠረት በማድረግ ሳይገኙ በመቅረታቸውና ምኒልክንም በግልጽ የሚደግፉ ብዙ ሰዎች ባለመገኘታቸው ተጠርተው ምክንያታቸውን ሲጠየቁ የሚያዛልቃቸውን መልስ በመስጠታቸው ምክንያቱን ለጊዜው ተቀብላ የቤት መንግሥቱን አጥር እንዲያጥሩ ቀላል ቅጣት ሰጥታ ቃል ከገቡ



በኋላ አሰናበተች።.... ውስጥ ውስጡን ከድቶ የነበረው የጦር አለቃ ሁሉ ለቴዎድሮስ ታማኝነቱን በቃለ አጋኖ እየተናገረና ምኒልክንም “ወፍራም ልጅ” በሚል ቅፅል ስም ይሰድቡ ጀመር።...” ብሏል።

## ዓለማየሁ ቴዎድሮስ

አጤ ቴዎድሮስ ስድስት ልጆች ቢኖሩዋቸውም ከሕጋዊ ሚስት የተወለደው ግን ዓለማየሁ ብቻ ነው። አለማየሁ ደብረ ታቦር ከተማ በ1853 ዓ.ም. ሚያዝያ 5 ቀን በተወለደ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ተደስተው መድፍና ጠመንጃ አስተኩሰዋል። 500 ያህል እስረኞችም ፈተዋል። ያ ቴዎድሮስ ከአለማየሁ ጋር ሲጫወቱ መዋል በጣም ያስደስታቸዋል። ተናደውና ተበሳጭተው በሚመለሱበት ጊዜ እንኳ አለማየሁን ታቅፈው ሲስሙ ንዴታቸውም ሆነ ብስጭታቸው ይጠፋላቸው ነበር ይባላል።



አለማየሁ ቴዎድሮስ በሕፃንነቱ

ቴዎድሮስ አንድ ቀን ከመኳንንቶቻቸው ጋር ሲጫወቱ በድንገት በጨዋታ መሀል "በዓለም ላይ ካለ ነገር ሁሉ ሽታው እጅግ ደስ የሚልና ልብ የሚመስጥ ምንድነው፤ ብለው ጠየቁ መኳንንቱም ሁሉም የሚያውቀውን የሽቶ ዘርና ሌላም ሁሉ ተናገረ። ቴዎድሮስም ሁሉንም አላወቃችሁም ካሉ በኋላ "የሕፃን ልጅ ጠረን ነው" ብለው መለሱ ይባላል።

የቴዎድሮስ ልጅ ውቡ አለማየሁ በእንግሊዞች እጅ ገብቶ አርፓውያኖቹ በሙሉ ቢያዝኑለትና ቢንከባከቡትም ኃላፊ የሚሆነው ሰው የሚያስፈልገው ሆነ። በዚህ ምክንያት ጄኔራል ናፒር ካፒቴን እስፒዲን ለአለማየሁ ሞግዚትና አሳዳጊ አድርጎ ሾመው። ካፒቴን እስፒዲ የተመረጠበት ዋናው ምክንያት አማርኛ ቋንቋ ደህና አድርጎ መናገር ስለሚችል ነው። እስፒዲ ብቻ ሳይሆን ሁለት ኢትዮጵያውያን ሞግዚቶችና አጫዋቾችም ተመረጡለት። እነሱም አንደኛው በቴዎድሮስ ቤት መንግሥት የታወቁት አለቃ ዝርአት ሲሆኑ ሌላው አቶ ገብረ መድኅን ይባላሉ።

እቴጌ ጥሩወርቅ ሲሞቱ አትራቢያ ካፒቴን እስፒዲን አስጠርተው እጁን ይዘው "ልጄ አባት የለውም። እኔም እናቱ ልሞት ነው። በሚሔድበትም አገር ዘመድ ስለሌለው አንተ ዘመድ ሁነው። አባት ስለሌለው አንተ አባት ሁነው። ይሄን ያልኩህን ሁሉ እንደምታደርግለት በእግዚአብሔር ማልልኝ። አሉት። እስፒዲ በኋላ ጊዜ እንደጻፈው "....ከሞት አፋፍ ላሉት ለአለማየሁ እናት የጠየቁኝን ሁሉ እፈጽማለሁ ብዬ ማልኩላቸው..." ይላል።

አለማየሁ ከአዲስ አሳዳጊው ከእስፒዲ ጋር ፌሬዝ በተባለች መርከብ ላይ ሰኔ 4 ቀን 1860 ዓ.ም. ተሳፈረ። በመርከቧም ላይ ለእስፒዲና ለአለማየሁ ለብቻቸው አንድ ክፍል ተሰጣቸው። ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ሞግዚቶችም አብረውት ሆኑ። አባቱም እናቱም የሞቱበት የትናንቱ የንጉሡ ንጉሥ ቴዎድሮስ ልጅ ከሞግዚቱ ከእስፒዲ ጋር ፍቅሩን መሠረተ። እስፒዲ በመርከቧ ላይ ላንዳንድ ሥራ ሲታዘዝ አለማየሁ ሳይለየው አብሮት ይሄዳል። አለማየሁ ከአንድ ቦታ ብቅ ሲል ከኋላው እስፒዲ አለ ማለት ነው። ካፒቴን እስፒዲ ብቅ ሲል ቀጥሎ የሚመጣው አለማየሁ ነው። የሁለቱን መፋቀር ያየው የመርከቧ ላይ ሠራዊት ካፒቴን እስፒዲ ምንም ዓይነት ሥራ እንዳይታዘዝ አደረጉ።

በመርከቧ ሲጓዙ ሰኔ 8 ቀን ስለደረሰው ሁኔታ እስፒዲ እንዲህ ይላል። "....የሚጮህ ድምፅ ሰማሁ። አጨጨሁና ድምፁ



አማርኛ ስለሆነብኝ አለማየሁ ያሆናል ብዬ ደነገጥሁ። አለማየሁ ከእኔ ተለይቶ መርከቧ ሜዳ ላይ ይጫወት ነበር። ወደ ልጁ እየሮጥሁ ስሔድ ከናፒር የተላከ መልዕክተኛ አጋጠመኝና ቶሎ ና ትባላለህ አለኝ። ስደርስ አለማየሁን ናፒር ታቅፎታል። አለማየሁ ይወራጫል። እናት አባቱ የሞቱበት ያን ሕፃን ከአዛሟችን ከናፒር እጅ ስቀበል አለቃ ዝርአት ልጁ የሚጮኸው ቡዳ በልቶት ነው አሉን። ምስኪኑ አለማየሁ የያዙለትን ኢትዮጵያውያን ሞግዚቶቹን ጠልቶ እኔን ሲያይ ከኔ አንገት ላይ ጥምጥም አለ...." ብሏል።

አለማየሁ ጉዞው አልተስማማውም። በተለይ ኢትዮጵያውያን ሞግዚቶቹን ሲያይ አምርሮ ያለቅሳል ስለዚህ ጉዳይ እስፒዲ እንዲህ ይላል። "....ናፒር ጠራኝና በልጁ ላይ ያለውን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ አንተ ያዝ። ከአበሾቹ ይልቅ ልጁ አንተን ወዶሃል። አበሾቹን ሲያይ የሚያወራጨውና የሚያበሳጨው ነገር ስላለ እነሱ ሲዊዝ ስንደርስ ወደ አገራቸው ይመለሳሉ አለኝ..." ይላል።

መርከብዋ ስዊዝ ስትደርስ ለአለማየሁ የተያዙት ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ሞግዚቶች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ወደ ቦምባይ (ሕንድ) በሚሔድ መርከብ አሳፍረው ላኩዋቸው። ከዚያ በኋላ ስላለው ሁኔታ እስፒዲ ሲገልጽ "....እኔንም ቢሆን አለማየሁ አስቸገረኝ። ከኔ በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር አልለምድ አለ። ሲተኛ እንኳን ክንዴን ካላንተራስኩትና እብብቴ ውስጥ ሽጉጥ ካላስ እንቅልፍ አይወስደውም። የአበሻ ሞግዚቶቹ ስለአባቱና እናቱ አሟሟት የነገሩት የሚያስፈራራ ነገር ከአእምሮው አልወጣ አለ። ተኝቶ ይባንንና ይነቃል። ምን ሆንክ ስለው ፈራሁ ይለኛል። ሽጉጥ አድርጌ እብብቴ ሥር አይዘውና አይዞህ እኔ እያለሁ አትፍራ። ተኛ ስለው ያን ምስኪን እንቅልፍ መልሶ ያሸልበዋል። እንቅልፍ ድብን አድርጎ እስኪወስደው ድረስም ራሱን ከክንዴ ላይ አላነሳም። ለአለማየሁ ያለሁት እኔ ብቻ ነኝ። ሶስት ወር ሙሉ በእንዲህ ያለ ችግር ከረመን ..." ይላል።

አለማየሁ እንግሊዝ አገር ከደረሰ በኋላ ከእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ ጋር ተገናኘ። ንግሥቲቱ ለአለማየሁ ማንኛውም ጥንቃቄ እንዲደረግለት አዘዙ። የፍርሃቱ ነገር ከአእምሮው እንዲጠፋ ሐኪሞች ሁሉ ተባብረው እንዲያድኑት ንግሥት ቪክቶሪያ አዘዙለት። ዛሬ በእንግሊዝ ቤተ መንግሥት በሚገኘው የንግሥት ቪክቶሪያ የዕለት አጀንዳ ወይም ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ንግሥት ቪክቶሪያ

ሲፅፉ "....ምስኪኑ ልጅ (ፕር ቻይልድ) አሁንም ፍርሃቱ አለቀቀ ውም።መቅደላ በተያዘ ጊዜ በዚያ የነበረውን እልቂትና የአባቱን ሞት ስላየ ያ ነገር በአእምሮው ይመጣበታል።..." የሚል ቃል ፅፈዋል።



አለማየሁ ቴዎድሮስ እንግሊዝ አገር በተወሰደ ጊዜ

አለማየሁ ሐምሌ 11 ቀን 1868 እ.ኤ.አ. እንግሊዝ አገር ከደረሰ በኋላ እስፒዲ ፣ በአሰሌ ውስጥ ፍሬሽወተር ከሚገኘው ቤቱ ይዞት ገባ ። በዚያም እንግሊዝኛ ያስተምረው ጀመር ። ንግሥት ቪክቶሪያ የአለማየሁን ሁኔታ ይቆጣጠሩ ስለነበር እስፒዲ እየወሰደው ብዙ ጊዜ ከንግሥቲቱ ጋር ይገናኛል ። ልጁን እንዳይ ጉዳውም በእስፒዲ ላይ ልዩ ቁጥጥር አቋቁመውበታል ። ሐምሌ 10 ቀን ንግሥት ቪክቶሪያ አለማየሁን ባነጋገሩበት ጊዜ ንግሥቲቱ በዕለት ሁኔታ መመዝገቢያ ደብተራቸው ላይ ስለአለማየሁ ከጻፉት "....ጨዋና ውብ ልጅ ነው ። ኬክ መብላት ይወዳል ። የሰጠሁትን ኬክ ሁሉ በላ ። የምሰጠውንም ኬኮች ደስ እያለው በፈገግታ እየተቀበለኝ በላ...." የሚል አረፍተ ነገር አስፍረዋል ።



ጁላይ (ሐምሌ) 25 ቀን ደግሞ ንግሥቲቱ በዕለት ሁኔታ ደብተራቸው ላይ "....ዛሬ ከአለማየሁ ጋር አብረን ምሳ በላን አለማየሁ ከኔ ዘንድ የሚመጣው የአገሩን የአበሻ ልብስ ለብሶና ከአገሩ የተያዘለትን ጊጣ ጌጦች አጊጦ ነው ። ምሳ በልተን ከጨ ረስን በኋላ ለዚህ ለተከበረ ትንሽ ልጅ (ዲር ሊትል ቦይ) በእጁ ላይ ሰዓት አሠርኩለት ። በወገቡም ላይ የወርቅ ሰንሰለት አስታ ጠቅሁት...." ብለው ጽፈዋል ።

አለማየሁ ከንግሥት ቪክቶሪያ ጋር ተወዳጅቷል ። በአለማየሁ ሰበብ እስፒዲም የንግሥት ባለሟል ሆነዋል ። ብዙ ጊዜም ንግሥት ቪክቶሪያ "ለዚህ እናት ለሌለው ሕፃን እናቱ እኔ ነኝ" እያሉ ይናገራሉ። ስለ ትምህርቱ ይጠይቁታል ። ስለጤንነቱ ያጫውቱታል ። አለማየሁ በቤተ መንግሥቱ ታላቅ የብስኩት ግብዣ እየተደረገለት ከልዑላንና ልዕልታት ልጆች ጋር ሲጫወት ቢውልም እምኖት የሔደውን እስፒዲን አይረሳም ። ግብዣ ላይ እስፒዲ ከሌለ አይበ ላም ። መብላት ቀርቶ ከእስፒዲ ተለይቶ ከቤተ መንግሥት አይ ገባም ። በጨዋታ ቦታ እስፒዲ ቁጭ ካላለ አለማየሁ አይጫወትም ያለ እስፒዲ ምንም ነገር አያደርግም ።

እስፒዲ ወታደር ነው ። የወታደር ድልድሉ ደግሞ ሕንድ ውስጥ ነው ። በሥራው ላይ ባለመገኘቱ ደብዳቤ ይጻፍለት ጀመር ። በጻ እስፒዲ ጥቅምት 10 ቀን ለሕንድ ዋና አዛዥ ደብዳቤ ጻፈ ። በጻ ፈውም ደብዳቤ "...እርግጥ ልጁ ጤነኛ ነው ። በባሕር ዳር እየተ ዘዋወረ ከባሕር የሚነሳውን አየር መቀበልና በባሕሩ ውስጥ መን ቦጨረቅ ይወዳል ። በሥራዬም ላይ ያልተገኘሁት ልጁን ውሃ መዋኘት እያስተማርኩት ነኝ ። ልጁ አሁን እየተላመደ ሔድ ዋል ። ማፈርና መሽኮርመሙን ትቷል ። በሱ ዕድሜ ካሉ ልጆች ሁሉ የተለየ ጨዋ ልጅ ነው ። በእንግሊዝኛ ችሎታውም ገፍቷል ።" በማለት ሪፖርት አቀረበ ።

እስፒዲ ለአለማየሁ ሕይወቱን ሰጥቷል ። እስፒዲና አለማየሁ የሚበሉት አብረው ነው ። የሚተኙትም አብረው ነው ። አለማ የሁ የእስፒዲን ክንድ ካልተንተራሰ እንቅልፍ አይወስደውም እስ ፒዲም ከአለማየሁ መለየት አይፈልግም ። ግን ሥራው ወታደርነት ስለሆነ የወታደር ግዴታውን መፈጸም አለበት ። እስፒዲ ሚስት ስለሌለው አለማየሁን የሚያሳድገው ብቻውን ነው ። እንዲህ አይ ነቱ ኑሮ የማያዛልቅ በመሆኑ እስፒዲ ሚስት ለማግባት ወሰነ ።

“አለማየሁን እንደ ልጅዋ አድርጋ የምታሳድግ ሚስት የት ትገኛለች ?” ይል ጀመር ። ልጅ የሌላትና ልጅ የምትወድ ባልቴት ያፈላልግ ጀመር ። ወይዘሮ ኮታም ተገኘችና ከሷ ጋር ተጋባ ። ኮታም ከአለማየሁ ጋር ተላመዱ ። እንደምትወደው አለማየሁም ወደዳት ። አለማየሁ ከወይዘሮ ኮታም ጋር ብቻ ሳይሆን ከወይዘሮ ኮታ እናት ጋር ተዋደደ ።

ታህሣሥ 26 ቀን ንግሥት ቪክቶሪያ በዕለት ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ “...ዛሬ ምሣ ከመብላታችን በፊት አለማየሁ መጥቶ ነበር ። አለማየሁ ደህና ሆኗል ። ቁመቱም አድጓል ። ካፒቴን አስፒዲ ከአዲሷ ሚስቱ ጋር የሙሽርነት ሽርሽር ስለሔደ ልጁን ይዛ የመጣችው የካፒቴን አስፒዲ ሚስት እናት ናት ...” ብለው ጽፈዋል ።

ያን ጊዜ ሕንድ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር ስለነበረች የሕንዱ አገረ ገዥ የአስፒዲ አለቃ ሥር እስታፎርድ ኖርዝኮት አንድ ውሳኔ አሳለፉ ። በውሳኔያቸውም ላይ “...ካፒቴን አስፒዲ ከአለማየሁ መለየት የለበትም ። ቢያንስ አለማየሁ ራሱን እስኪችልና በደንብ እስኪላመድ አብሮት መቆየት አለበት ። አስፒዲ የአለማየሁን ቋንቋ ይችላል ። ከዚህም ሌላ የአለማየሁ እናት ሲሞቱ ሲሉ ልጃቸውን አለማየሁንና አስፒዲን እጅ ለእጅ አጨባብጠው ለአስፒዲ አደራ መስጠታቸውንና መሞታቸውን አለማየሁ ያስታውሳል። የአባትና የእናቱ ተከታትሎ መሞት ከልጁ አእምሮ ውስጥ ያልጠፋ ስለሆነና ያለአስፒዲ የሚያምነውና የሚወደው ሰው ስለሌለ አስፒዲ ከአለማየሁ ጋር እንዲቆይ ወስኛለሁ ። ለልጁ ማሳደጊያ መደጎሚያ እንዲሆንም ባመት 300 ፓውንድ ለልጁ ልብስና መጫወቻ መግዣ ደግሞ ባመት 400 ፓውንድ ፤ በጠቅላላው ባመት 700 ፓውንድ እንዲሰጠው ወስኛለሁ ...” በማለት አስታወቁ ። ይህ የተወሰነው ገንዘብ በዘመኑ ከፍ ያለ ገንዘብ ነበር ። አሁን አለማየሁ በእንግሊዝ አገር ኑሮ አንድ ዓመት ሆነው ።

1861 ዓ.ም. በሕንድ አገር ኦድ ውስጥ ባለው ሱታፑር ለሚባለው ቀበሌ የፖሊስ ኮሚሽነር ሆኖ አስፒዲ ተሾመ ። አስፒዲ እ.ኤ.አ. ጁላይ 4 (በኛ ሰኔ 27) ቀን የስምንት ዓመቱን አለማየሁንና ሚስቱን ይዞ ወደ ተሾመበት አገር ሔደ ። አስፒዲ ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት አለማየሁን እንዲያሳድግ ተፈቅዶለት ነበር ። አስፒዲ በየጊዜው የልጁን ሁኔታ ሪፖርት ማቅረብ ስለነ



በረበት ከሔደ የመጀመሪያ ሪፖርቱ እንዲህ የሚል ነበር ። “...አለማየሁ በትምህርቱ ጐብዟል ። ከትምህርቱ ሌላ የውጭ እስፖርት ይወዳል ። በተለይ ፈረስ ግልቢያ በጣም ይወዳል ። የአእምሮ ሕመሙ አንዳንዴ ይነሳበታል ። አለማየሁ ለሚጠይቀኝ ሁሉ ሳልደብቅ እውነተኛውን እነግረዋለሁ ...” ብሏል ።

የአለማየሁ የሙከራ ዘመን የተጀመረው የሊብራሉ መንግሥት ቻንስለር ኦፍ ኤክስቼከርስ ሰር ሮበርት ሎዊ ስለአለማየሁ ሐሳብ ካቀረቡ በኋላ ነው ። ቻንስለሩ ጁን 5 ቀን 1870 (በኛ ግንቦት 28 ቀን 1862) ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ያቀረቡት አሳብ “...እኔ እንደማስበውና ለልጁም ይጠቅመዋል የምለው በወታደርነት ትምህርቱን እንዲቀጥል ነው ። የኤርጋ መኮንኖች በፈረስ ግልቢያ ከሚስጥለጥኑበት ቢገባ ጥሩ ይሆናል ። ...” የሚል አሳብ አቀረቡ ። አሳቡ ለክፋት አልነበረም ። ራሱን ችሎ የሚኖር ለማድረግ ነበር ። አለማየሁ ከአስፒዲ ጥገኝነቱ እንዲወጣ ለማድረግ ነበር ።

አለማየሁ ከአስፒዲ የሚለይበት ቀን ደረሰ ። አስፒዲ ለሁለት ዓመት ብቻ ከአለማየሁ ጋር እንዲሆን የተወሰነው ቀንም ደረሰ ። የተወሰነው ጊዜ ኦገስት (ነሐሴ) 1 ቀን ከመድረሱ በፊት በየካቲት ወር 1871 አስፒዲ ሪፖርት አቀረበ ። በሪፖርቱም “...በሚመጣው ሚያዝያ ወር የአለማየሁ እድሜ አሥር ዓመት ይሆናል ። አሁን የአለማየሁ ቁመት 4 ጫማ ከ6 ኢንች ሆኗል ። ጨዋታ ይወዳል ። በተለይ ከእንስሳት ጋር መጫወት ያፈቅራል ። አለማየሁ ደብተሮቹን ከማዝረክረኩ ሌላ በጥሩ ሁኔታ አድጓል ። በዚህ አለማችን (ዩኒቨርስ) ካሉ ልጆች ጥሩው ልጅ አለማየሁ ነው ።...አለማየሁ ልባችንን የሚነካ ልጅ ነው ። ስለኛ ወላጆች ይጠይቀንና ወላጆች እንደሌሉን ስንነግረው እኔም ወላጆች ስለሌሉኝ እኩል ነን ይልና ኩራት ይሰማዋል ። የዚህ የሕንድ አገር ኑሮአችን ለአለማየሁ አልተመቸውም ። ምክንያቱም ደህና ትምህርት ቤት ስለሌለ ነው ።...” የሚል ሪፖርት አሳለፈ ።

የእንግሊዝ መንግሥትም አለማየሁ ከአስፒዲ ሞግዚትነት ሥር ወጥቶ በመንግሥት ቁጥጥር እንዲሆን ወሰነ ። በ1863 ዓ.ም. አስፒዲ ወደ ፔናንግ እንዲዛወር ሲታዘዝ አለማየሁ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲመለስ ተወሰነ ። አለማየሁ አለቀሰ ። አስፒዲ አንገት

ላይ ተጠምጥሞ “. . . . አባቴ አንተ ነህ ያለ አንተ መኖር አልች
ልም ። እባክህ ከአንተ አትለየኝ ፡ ወደምትሔድበት ሁሉ አብሬህ
ልሂድ ። ያለዚያ እሞትብሃለሁ . . . ” አለው ። በዚህ ንግግር ልቡ
የተነካው እስፒዲ ከአለማየሁ ላለመለየት ደብዳቤ ጻፈ ። የእስፒዲ
ማመልከቻ ከተጠና በኋላ የሲንጋፑር ገዥ የነበሩት ሎርድ ኮምበ
ርሌይ በኮሚቴው ስም የሚከተለውን ውሳኔ አሳለፉ ።

“. . . ካፒቴን እስፒዲና አለማየሁ አብረው ሆነው አይተና
ቸዋል ። ካፒቴን እስፒዲ ለአለማየሁ እንደአባቱ ነው ። ካፒቴን
እስፒዲ ልጅ ስለሌለው ሚስቱም እሱም አለማየሁን እንደ ልጃ
ቸው ያዩታል ። የካፒቴን እስፒዲ ሚስት ከእንግሊዝ አገር ሆና
ለአለማየሁ በቂ ጥንቃቄ ማድረግ ስለምትችል ካፒቴን እስፒዲ
ወደተዛወረበት አገር እንዲሔድና አለማየሁ ወደ እንግሊዝ አገር
እንዲመለስ ይሁን . . . ”

ብዙ ክርክር ተነሳ ። የአለማየሁ የመከራ ዘመን ተጀመረ ።
ካፒቴን እስፒዲና ሚስቱ አለማየሁን ላለመስጠት ሙግት ጀመሩ ።
መሟገቻ እንደበትና እውቀት የሌለው አለማየሁም ከካፒቴን እስ
ፒዲ ላለመለየት በእንባው ተቃውሞውን ይገልጽ ጀመር ። የእስ
ፒዲን አንገት አቅፎ እየያዘም “ አባ ፡ አባዬ ፣ እባክህ ካንተ አት
ለየኝ ። እባክህ አብረን እንሁን ። ” ይለው ጀመር ። የእስፒዲ ሚስ
ትም የንግሥት ቪክቶሪያ የግቢ ሚኒስቴር ለሆኑት ለሰር ጆን ከዌል
ደብዳቤ ጻፈች ። “ . . ከልጁ ጋር ለመለየት የተወሰነው ውሳኔ ከፍ
ተኛ ኀዘን አሳድሮብናል . . . በየቀኑ የየቀኑን ሁኔታ የሚከታተሉና
ከሚወዱት ፍቅረኛቸው የተለያዩ ሰዎች ብቻ ይህን ነገር ያውቁታል
ለአለማየሁ ጥቅም ነው የሚወሰደው ከተባለ የምንናገረው የለም ነገር
ግን ይህ ነገር እጅግ በጣም አጠራጣሪ ነው ብላ ጻፈች ።

የአርጊል ዱክ በጉዳዩ ገብተው ኖቬምበር 11 ቀን 1881 ለግ
ላንድ እስቶን በጻፉት ደብዳቤ ልጁ ከእስፒዲ ጋር ቢኖር እስማማ
ለሁ ብለው አሳወቁ ። ለዚህ ሐሳብ የኤክስቼከር ቻንስለር ሮበ
ርት ሉዊ በደብዳቤ ሲመልሱ “ . . . ነገሩ የተወሰነው በጠቅላላው
አስተሳሰብ ነው ። . . . ልጁን ማየት ያለብን እንደልጃችን አድር
ገን ነው ። ማንም ወላጅ ቢሆን ልጁን ሕንድ ውስጥ ለማሳደግ
ይፈልጋል ቢባል ቅጥፈት ነው ። . . .በዚህም አገር የሚቆይ ከሆነ
መጨረሻው የማያማር ይሆናል ። . . .እኔ አሁን ከኬልተንሃም
ኮሌጅ ከጄክስ ብላኬ ጋር ተነጋግሬአለሁ ። የተነጋገርኩትም ልጁን



በግል ቤታቸው እንዲያኖሩት ነው ። ብዙ ቤተሰብ ያላቸው ሰው
ስለሆኑ ልጁ ብቸኝነት አይሰማውም ። . . .ምናልባትም ልጁ አንድ
ቀን ከአገሩ ከአበሻ የሚገባበት ጊዜ ይመጣ ይሆናል ። . . .ስለዚህ
ይህ ልጅ የኤሮፓን ባሕል ብቻ ጠቅሎ መያዝ የለበትም . . . ”
አሉ ። ጃክስ ብላኬ የኬልተንሃም ኮሌጅ ፕሬዚዳንት ናቸው ። ሌሎ
ችም ብዙ ትምህርት ቤቶች አሏቸው ። ቄስ በመሆናቸውም በደግ
ነታቸው የታወቁ ሰው ናቸው ። የወለዷቸው ብዙ ልጆች ቢኖሩዋ
ቸውም ሌሎች ልጆችም የሚያሳድጉ የብዙ ቤተሰብ አባት ናቸው ።

ንግሥት ቪክቶሪያም ይህን ውሳኔ እንደሰሙ ከእስፒዲ ይለይ
በሚለው አሳብ አልተደሰቱም ። በጻፉትም ደብዳቤ በአሳቡ ያለመ
ደሰታቸውን ገልጸው “ . . .ቢሆንም መፈጸም ያለባቸው ሁለት
ነገሮች አሉ ። መጀመሪያ የሕክምና አዋቂዎች ልጁን እንዲመረም
ሩትና እንዲያጠኑት ያስፈልጋል ። ከሚወዳቸውና ከሚያውቃቸው
ሲለይ በአእምሮው ላይ የሚያመጣው ለውጥ መጠናት አለበት
ሁለተኛ የሐኪሞች ስብሳቢና የበላይ ወሳኝ ሰር ጄነር ለንዲ
ሆን . . ” የሚል አሳብ አቀረቡ ። ሮበርት ሉዊ ደግሞ “ . . .
የአለማየሁ የወደፊት ሕይወቱ የሚመራው ካሁኑ በሚመሠ
ረተው ስነ ሥርዓት ነው ። እውር ዕድል እንዲኖረው አያስፈ
ልግም ። በቅኝ ግዛታችን በሕንድ ቆይቶ አሁን ደግሞ እን
ዲት ወደ ፔናንግ ይሂድ እንላለን ። በ700 ፓውንድ ወጭስ ምን
ዓይነት ኑሮ ሊኖር ይችላል ። በምሥራቅ አገሮች ሆኖ የምሥ
ራቅ አገር ትምህርት ይማር የሚባል ከሆነ እኔ እንደማስበው
ልጁ ለሕንድ ገገር መሰጠት አለበት ። ግን እኛ ለትምህርት የም
ንከፍለው ገንዘብ ልጁ በሚጠቀምበት ሁኔታ ላይ መዋል አለ
በት ። ስለዚህ እኔ የማቀርበው አሳብ ልጁ ወደ እንግሊዝ አገር
መጥቶ በጥሩ ሁኔታ ማደግ አለበት . . . ” አሉ ።

በመጨረሻው አለማየሁ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲመጣ የሚ
ለው አሳብ ተወሰነ ። ጃክስ ብላኬ ልጁን ለመቀበል እንዲዘጋጁ
ተነገራቸው ። እሳቸውም ልጁን በደስታ እንደሚቀበሉት ሲገ
ልጹ “ . . . ምናልባትም የሚፈልገው ከሁሉ በፊት ርህራሄንና ስነ
ሥርዓት ያላቸውን ልጆች ይሆናል ። . . .እኛ ዘንድ ከመጣ ከወርና
ከሁለት ወር በኋላ ሁሉም ነገር ይታወቃል ። እንደ ወዳጃችን ልጅ
አድርገን እንይዘዋለን ። እናስተምረዋለን ። ግልገል ፈረሱንም
እንዲጋልብ እናደርጋለን ። የሚጠይቀንን ሁሉ እንፈጽማለን ። . . ”
በማለት አለማየሁን በኃላፊነት ለመቀበል ተስማሙ ። ከዚህ በኋላ

እስፒዲ አለማየሁን ይዞ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲመጣ ታዘዘ ። እስፒዲም አለማየሁን ይዞ ታህሣሥ 21 ቀን 1863 ዓ.ም. (ዲሴምበር 30/ 1871) እንግሊዝ አገር ሳውዝ አምተን ገባ ። ወዲያውም ከቤታቸው ፍሬሽወተር ይዞት ሔደ ። እስፒዲ የተጻፈለት ደብዳቤ አልደረሰውም እንጂ አለማየሁን ይዞ ሲመጣ የት እንዲያርፉና ለአቀባበሉም ፕሮግራም መውጣቱ ተጽፎለት ነበር ። እስፒዲ ግን ደብዳቤው ስላልደረሰው አለማየሁን ይዞ ከቤቱ ሔደ ።

የአለማየሁ እንግሊዝ አገር መግባት እንደተሰማ በንግሥት ቪክቶሪያ ስም ቶማስ ቢደልፍ አንድ ደብዳቤ ለሉዊ ጻፈ ። ደብዳቤውም "...ንግሥቲቱ በልጁ ላይ ትልቅ ስሜት አላቸው ።.. እስፒዲ ልጁን ይዞ መምጣቱን ሰምተዋል ። ቢያንስ እንኳ የልጁን መድረስ ለንግሥቲቱ ሪፖርት ማቅረብ ነበረበት ።...ንግሥቲቱ ያዘዙት ትእዛዝ አለ ። የልጁ ጤንነት በሚገባ እንዲመረመርና የእንግሊዝ አገር አየርም ለኑሮምው ይስማማው እንደሆነ በአስቸኳይ እንዲጠና አዘዋል ። ለዚህም ጉዳይ ንግሥቲቱ አሳብ ሲያቀርቡ ሰርጂነር እንዲያዩትና ስለጤንነቱም ሆነ አእምሮውን ስለሚያውከው ሕመም ሪፖርት ይቅረብልኝ ብለዋል ።..ልጁ አሁን የት እንዳለ እኔ አላውቅም ።...በፕሮግራሙ መሠረት ግን እንግሊዝ አገር በገባ በአራት ቀኑ ለጂክስ ብላኬ እንዲሰጥና ትምህርት ቤት እንዲገባ ነበር ። እስፒዲ ግን አልሰጠውም ።.." የሚል ነበር ። ለዚህ ደብዳቤም ሉዊ ሲመልሱ ልጁ በደህና እንግሊዝ አገር መድረሱን ፣ ስለልጁም ማንኛውንም ነገር ማዘጋጀታቸውን ገለጹ ። ወዲያውም እስፒዲ አለማየሁን ወደ ብሪንግተን ባለፈው ሮብ ዕለት ወስደህ ለቄስ ብላኬ እንድታስረክብ ብለው አልታዘዘልኝም ።..." ሲሉ አስታወቁ ።

የንግሥት ቪክቶሪያ ፀሐፊ ለእስፒዲ በላኩት ቴሌግራም ልጁን ብሪንግተን ወስዶ ከጂክስ ብላኬ ጋር እንዲያገናኝና እንዲያስ ተዋውቃቸው ፣ የሚቀጥል ትእዛዝ እስኪደርሰው ግን ልጁ ከሉ ጋር እንዲቆይ የሚል ትእዛዝ ላኩለት ። እስፒዲ ይህ ቴሌግራም እንደደረሰው ወዲያው ተከታትሎ ሌላ ቴሌግራም ደረሰው ። ይህን ለሁለተኛ ጊዜ የደረሰው ቴሌግራም አለማየሁ ንግሥቲቱ ሊያዩት ስለሚፈልጉ አርብ ለት ልጁን ይዘህ ወደ ዊንዲሰር እንድትመጣ የሚል ነበር ።

ንግሥት ቪክቶሪያ አለማየሁ ባንድ ጊዜ ከሚወደው ከእስፒዲ መለያየቱን አልፈለጉም ። ከቄስ ጂክሲ ብላኬ ዘንድ ሆኖ ደግሞ



እንዲማር ይፈልጋሉ ። ስለዚህ አለማየሁ ከቄስ ብላኬ ዘንድ ገብቶ ከልጆቹ ጋር እስኪለማመድ ድረስ እስፒዲ ለአንድ ዓመት ጊዜ በእንግሊዝ አገር ሆኖ እየተመላለሰ እየጠየቀ እንዲያለማምደው አዘዙ ። አለማየሁ ከቄስ ብላኬ ዘንድ በሚገባበትም ጊዜ የፈለገውን ነገር በደብዳቤ እየጻፈ ለእስፒዲ እንዲልክ የሚጽፈውንም ደብዳቤ ከመላኩ በፊት ማንም ሰው እንዳያነበው ፣ በኋላ ግን የጻፈውን ደብዳቤ በሚስጥር እየታየ የሚፈልገው ሁሉ ነገር እንዲደረግለት አዘዙ።

አለማየሁ የካቲት 25 ቀን 1864 ዓ.ም. ለቄስ ብላኬ ተሰጠ ። እስፒዲ ለቄስ ብላኬ ሊሰጠው ይዞት ሲሔድ አለማየሁ ባባ ። እስፒዲም ጥሩ ቤት መሆኑን እሱም እንደማይለየው ፣ በቤቱም ብዙ ልጆች ስላሉ ከትምሕርት መልስ ብዙ ጨዋታ እንደሚጫወት እየነገረ ወሰደው ። ቄስ ብላኬ ዘንድ ሲደርሱም ለአለማየሁ ከፍተኛና ደስ የሚያሰኝ አቀባበል ተደረገለት ። የምሳ ሰዓት ሲደርስም እስፒዲ ባለበት አብረው ከቤተሰቡ ጋር ምሳቸውን በሉ ። እስፒዲ ለዚያች ዕለት ካረፈበት ሆቴል ከአለማየሁ ጋር ለመጨረሻ ጊዜ አብረው እንዲያድሩ ቄስ ብላኬን ለመኑቸው ። ቄሱ ግን አይቻልም አሉ ። እስፒዲ "እኔ በማይመችኝም ጊዜ ባለቤቴ እየመጣች አንድ ቀየው እንዲፈቀድላት ይሁን" ብሉ ቢጠይቃቸውም ቄሱ መልስ ሳይሰጡ እያጉረመረሙ ዝም አሉ ።

በዚህ የተበሳጨው እስፒዲ ጉዳዩን ለንግሥቲቱ አሳወቀ ። ንግሥቲቱም ማንኛውም የተጠየቀው ነገር ሁሉ በትክክል እንዲፈጸም አዘዙ ። ሉዊ ሁኔታው ሁሉ መስተካከሉን ካዩ በኋላ በየካቲት ወር መጨረሻ ወይም ማርች 1 ቀን ለቢዱልፍ በጻፉት ደብዳቤ "... አሁን የአለማየሁ የታሪክ ምዕራፍ ስለተዘጋ በጣም ደስ ብሎኛል ። የንግሥታችን ምኞትና ሐሳብ ካፒቴን እስፒዲና ቤተሰቦቹ እንዲጉበኙት የሚለው ሁሉ ተሳካ..." ብለዋል ።

የካቲት 29 ቀን (ማርች 8) የተሰበሰበው የእንግሊዝ ምክር ቤት የአለማየሁን ጉዳይ አነሳው ። በምክር ቤቱ አባል የሆኑት አስታፎርድ ኖርዝኮት አለማየሁ ከካፒቴን እስፒዲ ለምን እንደተለየ ጠየቁ ። ለዚህም ጉዳይ ሉዊ ሲመልሱ "....ልጁ አሁን 11 ዓመቱ ነው ። በዚህ ዕድሜ መሠረታዊ እውቀት እንኳ አላገኘም ....በዚህም ምክንያት የመኳንንት ልጆች ካሉበት ትምህርት ቤት ከእኩዮቹ ጋር ሊማር አልቻለም ። መጻፍና ማንበብ እንደማይችልም አምናለሁ ።....ለዚህ ብለን ነው..." አሉ ። እስፒዲም ከንግሥት

ቪክቶሪያ ዘንድ ቀርቦ እስከአሁን ድረስ ለአለማየሁ ባደረጉለት ጥበቃና እንክብካቤ የመታሰቢያ ሰዓትና ሌላም ሽልማት ተሰጠው ። ወዲየውም የሱ ሞግዚትነት በማብቃቱ በመንግሥት ትእዛዝ አዲስ ወደተሾመበት አገር እንዲሔድ ተብሎ ወደ ፔናንግ ሔደ ፤

በዚህ ዘመን በግንቦት ወር ለአለማየሁ ከአገሩ ከኢትዮጵያ የተጻፈ አንድ ደብዳቤ ደረሰው ። ደብዳቤው የተጻፈው በአማርኛ ስለነበር የሚያነበው ሰው እንዲፈልግ ጂክስ ብላኬ ጉዳዩን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለሎርድ ኢንፊልድ አሳወቁ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዎልድሜየርን አፈላልጎ አገኘው ። ዎልድሜየርም ደብዳቤውን እንዲተረጉም ተደረገ ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሎርድ ኢንፊልድ ቅዳሜ ቀን ዎልድሜየርን ለማነጋገር ፈልገው ከቢሮአቸው ሆነው ስለደብዳቤው ይዞታ ተነጋገሩ ። ዎልድሜየርም ደብዳቤው ከአለማየሁ አያት ፤ ከእቴጌ ጥሩወርቅ እናት የተጻፈ መሆኑን ገለጠ ። ደብዳቤው የሚለው አለማየሁ ለምን ወረቀት እንደማይጽፍላቸው ፤ የአበሻ ሕዝብም የእሱን መመለስ በጉጉት እንደሚጠብቅ የሚናገር መሆኑን አስረዱ ። ኢንፊልድም ይህን ደብዳቤ ትርጉም ለሱዊ ላኩት ። ከዚያ በኋላ ምን እንደሆነ አይታወቅም።

የአለማየሁ ሞግዚቶችና ባለ አደራዎቹ ሥራ እንዲሠራ ወሰኑበት ። በወጣለትም የሥራ ፕሮግራም መሠረት በሳምንት 31 ሰዓት ትክል ማንኛውንም ሥራ ይሠራ ጀመር ። የእስፒዲ ሚስት ይህን ተቃውማ ለቢዱልፍ አመለከተች ። ቢዱልፍም ለሱዊ በጻፉት ደብዳቤ “. . . . አለማየሁ አንዳንድ ቀን ወደ እስፒዲ ሚስት ዘንድ እየሔደ እንዲውል ጂክስ ብላኬን ብታዘው ንግሥቲቱ ያዘዙት ትእዛዝ በመፈጸሙ ደስ ይላቸዋል ። በዚህም በሚመጣው የበጋ ወራት የእስፒዲ ሚስት ወደ ምዕራብ ከመሔድዋ በፊት ከእሷ ጋር እንዲከርም አድርግ . .” ብለው ላኩበት ።

በትእዛዙ መሠረት የእስፒዲ ሚስት እንድትንከባከበው ተፈቀደላት ። እሷም ካለበት ድረስ ሔዳ አለማየሁን ካየችውና ሲጫወቱ ከዋሉ በኋላ ለቢዱልፍ በጻፈችው ሪፖርት “. . . . ማደጉን ቁመቱ አድጓል ። መልኩ ግን ገርጥቷል ። አካላቱም ከስቷል ። ዝምተኛና ጭምትም ሆንዋል ከወንዶች ልጆች ጋርም እንዳይገናኝና ከእኩዮቹ እንዳይጫወት ተደርጓል ። ከውጭ አየወጣም እንዳይዛለል ታግዷል። ብዙ ጊዜም እየደጋገመ የምጫወታቸው ወንዶች ልጆች አጣሁ ። ቅዳሜና እሁድ ብቻ ከሌሎች ሁለት ልጆች ጋር መነጋገር ይፈቀ



ድልኛል ። እነኝህም ሲያጫውቱኝ የሚመጡት ሁለት ልጆች ሁል ጊዜ እነሱው ብቻ በመሆናቸው ተሰላችቶኛል ። በሌላ ቀን ግን የሌሎች ወንድ ልጆች እጅ እንኳ ጨብጨ አላውቅም ፤ ብሎ አጫውቶኛል ይህን የመሳሰሉት ነገሮች ያበሳጩታል ። . . . እኔም ብሆን ይህን የሚበሳጭበትን ለማስተው ጓደኛ ልፈጥርለት አልቻልኩም ። እየደጋገመ የነገረኝም ወንዶች ልጆች እፈልጋለሁ ። የበለጠ አንድ ዛለልም እፈልጋለሁ ።. . . አያስ ነው ። በምግብ አበላሉ በኩልስ እንዴት ነህ ብዬ ብጠይቀው ምግብ አሁን አይበላልኝም ምክንያቱም ውጭ ወጥቼ ስለማልዛለልና ስለማልጫወት አይርበኝም ። የምበላው በትንሹ ነው ብሎ መለሰልኝ ። እኔ እንደማስበው አለማየሁ ደስተኛና በሚደረግለት የረካ ልጅ አይደለም . . . .” ብላ አመለከተች ።

ቄስ ብላኬ ዘጠኝ ሴት ልጆች አሏቸው ። አለማየሁ የሚኖረው ከእነኝህ ዘጠኝ ሴት ልጆች ጋር ነው ። የቄስ ብላኬ ሚስት ሴቶች ልጆች የቤት ሥራ እንዲሠሩ ስታስገድድ አለማየሁ ያለጓደኛ ይቀራል ። ስዚያውም ቢሆን ወንድ ልጅ ብቻውን ከሴቶች ጋር መጫወቱ አይጣጣሙም ። ሴቶቹም ቢሆኑ ከወንድ ጋር መጫወቱ አያግባባቸውም ። ወንዱ እየሮጠ መዝለል ሲፈልግ የሴቶቹ ፍላጎት ቁጭ ብሎ የጨዋታ ወጥ መሥራትና አሻንጉሊት ማሳመር ሊሆን ይችላል ። እንዲህ ዓይነቱ ያለመግጣጠም ነው አለማየሁን አላስደስት ያለው ።

የእስፒዲ ሚስት የጻፈችው ሪፖርት ከንግሥት ቪክቶሪያ ዘንድ ደረሰ ።ንግሥቲቱም ስለዚህ ጉዳይ ሌዲ ኢሊይ አንድ ደብዳቤ ለቢዱልፍ እንዲጽፍ አዘው ልዲያቱ በጻፉት ደብዳቤ “. . . . ትንሹ ልዑል በጥሩ ሁኔታ ሊጫወት የሚችልበትና የሚያስደስተውን ዝላይ ሁሉ እንዲዛለል ጓደኞች እንዲዘጋጁለት ንግሥት አዘዋል ። . . .” ብለው ትእዛዙን አሳለፉ ። በዚህ ምክንያት አለማየሁ ለሶስት ሳምንት ከእስፒዲ ሚስት ዘንድ እንዲከርም ተፈቀደለት ። ጁን 15 ቀን ወደ እስፒዲ ሚስት ዘንድ ተወሰደ ። በዚያም የድሮ ጓደኞቹንና የሚወዳቸውንም ሰዎች ሁሉ አገኘ ። የእስፒዲ ሚስትም አገስት 1 ቀን ለቢዱልፍ በጻፈችው ሪፖርት አለማየሁ በጥሩ ጤንነት በደስተኛ መንፈስ እንደሚገኝና በንባብና በጽሕፈትም እንደተሻሻለ አሳወቀች ። አለማየሁንም የተለያዩ ፎቶግራፎች እንስታ ንግሥቲቱ ደስ እንዲላቸው ሁለቱን ፎቶግራፍ ለንግሥት ቪክቶሪያ ላከች ።

በእስፒዲ ቤት የተፈቀደለትን የእረፍት ጊዜውን ከጨረሰ በኋላ እንደገና ደግሞ በቢዱልፍ ቤት የሶስት ሳምንት ረፍት ለማድረግ

ተወሰደ። ቢዱልፍ በዚህ ጊዜ ቢያዙት ማስታወሻ "....ይህ ምስኪን ልጅ የእረፍት ጊዜውን እጋማሽ ከኔ ጋር እሳልፏል። ጨዋ ልጅ ነው። ቢሆንም የዘርኛ ኃይለኛነት አለበት።" ብለዋል በዚያው በቢዱልፍ ቤት በከረመበት ጊዜ የቢዱልፍ ሚስት አለማየሁን ወደ ንግሥት ቪክቶሪያ ዘንድ ወስደውት ነበር። ንግሥቲቱ ሴፕቴምበር 6 በሚለው ማስታወሻቸው ላይ "..... ሚሪ ቢዱልፍ ትንሹን አለማየሁን ይዛው መጥታ ነበር። የሚወደድ የተከበረ ልጅ ነው። ጥቂት ጌጣጌጦችና አንድ የእኔን ፎቶግራፍ ሰጠሁት" ብለው ጽፈዋል።

አለማየሁ በሁሉም ዘንድ ያለውን የእረፍት ጊዜውን ጨርሶ ወደ ቦታው ተመለሰ። በቢዱልፍ ቤት በነበረበት ጊዜ ከሌዲ ቢዱልፍ ጋር በጣም ተዋደው ነበር። ከትምሕርት ቤቱ ከተመለሰ በኋላ ለሌዲ ቢዱልፍ አንድ ደብዳቤ ጻፈ። ዛሬ ከአለማየሁ ደብዳቤዎች በሚገባ ተቀምጦ የሚገኘው ይህ ለሌዲ ቢዱልፍ የጻፈው ብቻ ነው። ደብዳቤው እንዲህ ይላል። ".. በጣም ደህና እንደሆንሽ ተስፋ አለኝ። ይህን በመናገሬ አዝናለሁ እንጂ አቶ ጀክሲ ብላኬ ግጥሚያውን ለማየት እንድመጣ አልፈቀደልኝም። ከካፒቴን እስፒዲ የተጻፈ ደብዳቤም ደርሶኛል። እሱም እንዳለኝ ከጥቂት ሰዎች ጋር ወደ ሕንድ መሔዱን ገልጾልኛል። ከቻይናዎች ጋር ከመዋጋታቸው በፊት ሰላም ይፈልጉ እንደሆን የከሩት ራጋ እንዲጠይቃቸው መደረጉን፤ እነሱ ግን ይህን ነገር ሊሰሙትም እንደማይፈልጉ መናገራቸውን ሁሉ ገልጾልኛል። ራጋውም ለካፒቴን እስፒዲ ሲያሚውተው ሔደው ምሽጋቸውን እንዲይዙ በነገራቸው መሠረት ካፒቴን እስፒዲ መቶ ሰዎች ይዞ ሔዶ በድስት ምሽጉቻቸውን ወሰደባቸው። ካፒቴን እስፒዲ እንደሚለው ቻይናዎቹ እንደ ጦር የሾለ ቀርከሃዎች ጫፋቸውን ደግሞ መርዝ እያደረጉ በመቅበላቸው የማለያ ሰዎች ወደ ምሽጉ መጠጋት ፈርተው ነበር። ሕንዶቹ ግን አልፈሩም። ምክንያቱም ቧት ጫማ ስላደረጉ ነው። ሰር እስታፎርድ ኖርዝኮት ስለኔ ጉዳይ ምን አደረገ። አሁን ከፍል ተዛውሬአለሁ። በክፍሉም ጥሩ ውጤቶች አገኛለሁ። በኃይል ስለምሠራም ሽልማት እንደማገኝ ተስፋ አለኝ። በቸልተኝነትም ከቆየሁ እድገቴን አገኛለሁ። ግን ለማወቅ የምፈልገው ሰር እስታፎርድ ኖርዝኮት ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላል!"

በ1867 ዓ.ም አለማየሁ ወደ ራግቢ ትምህርት ቤት ተዛወረ። የተዛወረው ወደ ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን ከቄስ ጀክሲ ብላኬ ቤት ወጥቶ ከሊ. ዋርነር ቤት እንዲኖር ተደረገ። በዚያም ስላልተ




ደሰተ በቀጠለው ዓመት በሚያዝያ ወር ሚስተር ድራፐር ቤት እንዲኖር ተደረገ። ወደዚህ የሆረው የአለማየሁ እኩዮች የሆኑ አስር ያህል ተማሪ ልጆች ስላሉ ነው። አለማየሁ ወደ ራግቢ ትምህርት ቤት የገባው ቄስ ጀክሲ ብላኬ ወደዚያ ትምህርት ቤት ስለተዛወሩ እሱም አብረዋቸው መዛወሩ ነበር። አለማየሁ በኑሮው ከቄስ ጀክሲ ጋር ባይገናኝም በትምህርት ቤት ግን ይገናኛሉ።

በ1868 ዓ.ም /1876 እ.ኤ.አ./ በግንቦት ወር ጀክሲ ብላኬ አንድ ሪፖርት ለቢዱልፍ አስተላልፈው ነበር። ሪፖርታቸውም "....እኔ እንደምመኘው ያህል በትምህርቱ አልገፋም። እሱ ግን ሙሉ ነው... እንደማስበው ከሌላው የኑሮ ሕይወት ይልቅ ለውትድርና ተግባር የሚስማማ ነው። በወታደርነት ጥሩ ትምህርት ሊሰጠው ይገባል። በጨዋታም በጣም ጥሩ ውጤት የሚያመጣ ልጅ ነው። በተለይ በእግር ኳስ ጨዋታ በጣም ጉበዝ ነው። ምንግዜም ቢሆን ከመልካም ጠባይ ውጭ ሆኖ አላየሁትም..." ብለዋል። በዚህ ሪፖርት መሠረት አንደ ኤርፓ አቆጣጠር በሴፕቴምበር ወር 1878 ዓ.ም ያለምንም ፈተና ሳንድኸርስት የወታደር ትምህርት ቤት እንዲገባ ተደረገ። በዚያ ዘመን በፓሪስ ከተማ የዓለም ኤግዚቢሽን ይታይ ስለነበረ አላማየሁ ባልደረባ ተሰጥቶት ፖሪስ ሔዶ ኤግዚቢሽኑን እንዲያዩ ተደረገ። ከዚያም ተመልሶ ትምህርት ቤት ገባ።

አንድ ጊዜ ለእረፍት ወደ ዲቮንሻየር መጥቶ ሶስት ሳምንት ያህል በኖርዝኮት ቤት ሰንብቶ ነበር። ከዚያ ከርሞ ቡተመለሰበት ጊዜ ኖርዝኮት እ.ኤ.አ. ጥቅምት 20 ቀን ለሌዲ ቢዱልፍ በጻፉት ደብዳቤ "....ልጁ በትውልድ አገሩ ላይ ማተኮርና ማሰብ ጀምሯል። በአገሩም ሁለት አክስቶችና አንድ ወንድም እንዳለው ይናገራል እኔም ወደ አበሻ አገር የመመለስህ ጉዳይ የማይታሰብ ነው ብየዋለሁ። በእንግሊዝ አገር እኮ እንደ አቶ ራንስም የሚያስደስቱኝና ሁሉን ነገር የሚያደርግልኝ ሰው አንድም የለም ይላል ወደ እሱም ዘንድ ለመሔድ ይፈልጋል።...." ብለው ነበር።

በዚያው ዘመን ወደ ሊድስ ሔደ በጠየቀው መሠረት በሚስተር ስሪል ራምሶን ቤት ተቀምጦ ሳለ በጥቅምት ወር ታመመ። ኖርዝኮትም ስለአለማየሁ ሕመም ለሌዲ ቢዱልፍ ደብዳቤ ጻፉ "... አደገኛ የሆነ ሕመም መታመሙን እንድታውቁ ይሁን። ምንም ጥረት ብናደርግ ሕመሙ እየጠናበት ሔደ።.... ሕመሙ



አለማየሁ ቴዎድሮስ

እደገኛ በመሆኑና በጣም ስለጠናበትም . . . አሁን ምግብ አይበ ላም መድኃኒትም አይወስድም ።....”

ሐኪሙ ዶክተር ክሊፎርድ ከሌሎች ሐኪሞች ጋር ሆነው ያክሙታል ። ሰር ዊልያም ጉር እና ሰር ጀምስ ፖሬት ከአጠገቡ እን ዳይለዩና አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርጉለት ታዘዋል ። ንግሥት ቪክ



ቶሪያም መታመሙን እንደሰሙ ሌዲ ቢዱልፍ ሔደው አይተውት ሁኔታውን እንዲነግሩዋቸው በስልክ ታዘዙ ። ንግሥቲቱ በጠና መታ መሙ ሲነገራቸው ለአለማየሁ አንድ የማጽናኛ ደብዳቤ ጽፈው ላኩ ለት ። አለማየሁ የንግሥቲቱ ደብዳቤ እንደደረሰው “. . . . ከየት የመጣ ነው ብሎ ጠየቀና ከንግሥቲቱ መሆኑ ሲነገረው በጣም ተደ ሰተ ። ቀስ ብሎም ከፈተውና ጥቂት መስመሮችን አነበበ ። ግን ሕመሙ ስላስቸገረው ጨርሶ ሊያነበው አልቻለም ። እኔንም ጠራ ኝና ደብዳቤውን ሊያየው ከሚችልበት ቦታ እንዳስቀምጥለት ጠየ ቀኝ። በዚያም ባስቀመጥኩለት ቦታ ሳይነሳ እስከመጨረሻ ድረስ ቆየ። . . . . ” በማለት የንግሥቲቱ መልዕክተኛ ሰር ጆን ኮዊል ጽፈዋል ።

በአለማየሁ አልጋ አጠገብ የቄስ ጂክስ ብላኬ ሚስትና ራንሶም ተቀምጠዋል ። አለማየሁ የሁለቱንም እጆች እንደያዘ ሕዳር 5 ቀን 1872 ዓ.ም /ኖቬምበር 14/1879 ከጧቱ በሶስት ሰዓት ተሩብ በተ ወለደ በ19 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ ። በንግሥት ቪክቶሪያ ትእዛዝ ዊንድሰር ባለው የነገሥታት መቀበሪያ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ ። በመቃብሩም ላይ

የአበሻው ልዑል አለማየሁ
አፕሪል 13.1861 ተወለደ
ኖቬምበር 14.1879 አረፈ ። የሚል አረፍተ ነገር ተጻፈበት ። ንግሥት ቪክቶሪያ ግን ከዚህ ጽሁፍ በታች “ እንግዳ ሆኜ መጣሁ ተቀበላችሁኝም ” የሚለው የወንጌል ቃል እንዲጻፍ በት አዘው ተጻፈበት ።

# ዋቢ መጽሐፍት


| | |
|---|---|
| ሔንሪ ብላንክ (ዶክተር) | የእሥራት ዘመን በአበሻ አገር ትርጉም ዳኘው ወልደ ሥላሴ |
| ተክለ ኢየሱስ (አለቃ) | የኢትዮጵያ ታሪክ ያልታተመ |
| ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ) | ሃይማኖተ አበው ቀደምት |
| ወልደ ማርያም (አለቃ) | የዳግማዊ ቴዎድሮስ ታሪክ |
| ዘነበ (ደብተራ) | የቴዎድሮስ ታሪክ |
| ገሪማ ታፈረ | አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ |
| ALAN MOOREHEAD | THE BLUE NILE |
| GIRMA SELASSIE ASFAW & DAVID L.APPLE YARD | THE AMHARIC LETTERS OF EMPERÒR THEODORE OF ETHIOPIA |
| HENRY DUFTON | NARRATIVE OF A JOURENY THROUGH ABYSSINIA |
| MARKHAM, C.R. | HISTORY OF ABYSSINIA EXPEDITION |
| PLOWDEN, W.C. | TRAVELS IN ABYSSINIA |
| POLLSÓN NEWMANN | ETHIOPIAN REALITIES |
| RAŠSAM NORMUZD | NARRATIVE OF THE BRITISH MISSION TO THEODORE KING OF ETHIOPIA VOL. I, II |
| STANLEY, H.M. | COOMASSIE AND MAGDALA |
| SYEN RUBENSON | 1) KING OF KINGS TEWODROS OF ETHIOPIA<br>2) THE SURVIVAL OF ETHIOPIAN INDEPENDENCE |
| WALDMEIER, T. | TEN YEARS LIFÈ IN ABYSSINIA |